አሪት ዘፍጥረት

መግቢያ

1. ዳራ

የአሪት ዘፍጥረት መጽሐፍ መቼ እንደ ተጻፈና ጸሓፊውም ማን እንደ ሆነ እንብዛም አይታወቅም። ባለ ዐምስት ቅጽ መጻሕፍት[1] (ፔንታቱክ) ከሚባሉት መጻሕፍት መካከል አንዱ ሲሆን፣ በአይሁድ ወግና በዐዲስ ኪዳን መሠረት ጸሓፊው ሙሴ ነው (ከዮሐ 1፥17፤5፥46፤7፥19:23 ጋር ያነጻ)። በጥቅሉ "የአሪት ዘፍጥረት ጸሓፊ ማን ነው?" የሚለው ጥያቄ የሚነሣው ከባለ ዐምስት ቅጽ መጻሕፍት ሥነ ጽሑፋዊ ታሪክ ጋር ተያይዞ ነው።

የአሪት ዘፍጥረት መጽሐፍን በተመለከተ ሁለት ዐይነት ታሪካዊ ዳራዎች እንዳሉ መገንዘብ ያስፈልጋል። እነርሱም፦ (1) መጽሐፉ የተጻፈበት ታሪካዊ ዳራ እና (2) በመጽሐፉ ውስጥ የተወሱት ሁነቶች የተፈጸሙበት ዐውድ ናቸው። የመጀመሪያው፣ መጽሐፉ የተጠናቀረበትን ጊዜና ቦታ (ስፍራ) ይመለከታል። ሁለተኛው ደግሞ ረጅም መቼቶችን ይሸፍናል (ለምሳሌ፦ የዔድን ገነት፣ የጥፋት ውሃ፣ የባቢሎን ከተማ፣ ከነዓን፣ ግብፅ)።

ዘፍጥረት ሁለት ዐይነት ሁነቶችን ዘግቧል፦ እነርሱም በዓለም ወይም በአጥናፈ ዓለም ደረጃ የተፈጸሙ ክሥተቶችና (ለምሳሌ ሥነ ፍጥረት፣ የጥፋት ውሃ) በተወሰነ አካባቢ ወይም በተወሰኑ ግለሰቦች ሕይወት የተከወኑ ድርጊቶች ናቸው (ለምሳሌ የኖኅ መስክር፣ የአብርሃም ሕልም) በዘፍጥረት ውስጥ የምናያቸው ሁነቶች በአብዛኛው በተወሰነ ጊዜና አካባቢ የተፈጸሙ በመሆናቸው "ቤተ ሰባዊ ጉዳዮች" ናቸው ማለት ይቻላል።

2. የመጽሐፉ ዐይነትነትና አንድ ወጥነት

መጽሐፈ አሪት ዘፍጥረት በቀላሉ የሚስተዋል ወጥነት እንዲሁም የዚያኑ ያህል ግልጽ በሆነ መልኩ አንድ ዐይነት ያለመሆን ጠባይ ይታይበታል። እንደ ዐዲስ ኪዳን ወንጌሎችና እንደ ብሉይ ኪዳን ደኃራይ[2] ታሪካዊ መጻሕፍት ጸሓፊዎች ሁሉ የአሪት ዘፍጥረትም ጸሓፊ ጽሑፉን ያጠናቀረው እግዚአብሔር በቀደመው ዘመን ያከናወነውን ታላቅ ሥራ ከዘገቡ ጥንታዊ ምንጮችና ሰነዶች ነው። ይህን የመሳሰሉ ዘገባዎች በእስራኤል ታሪክ ውስጥ የተለመደ እንደ ሆነ በቀዳማይ[3] ታሪካዊ መጻሕፍት ውስጥ ተጠቅሶ እናገኛለን (ዘፀ 17፥14፤ ዘኍ 21፥14፤ ኢያሱ 10፥13)። እናም ተመሳሳይ ዘገባዎች በግለሰቦችና በነገድ አባቶች ቤት ውስጥ ተቀምጠው ሊሆን ይችላል። በዘፍጥረት ውስጥ የምናገኛቸው ትረካዎች በአብዛኛው የተገነቡት ከዐጫጭርና ራሳቸውን ከቻሉ ታሪኮች ነው። እነዚህ ትረካዎች እንዲጎለብቱ ወይም ታላላቅ ክፍል እንዲወጣቸው የተደረገው፣ የተለያዩ የመልክአ ምድርና የትውልድ ሐረግ ገበታዎችን መሠረት በማድረግ ነው። እንግዲህ በደኃራይ ታሪካዊ መጻሕፍት ውስጥ የምናገኘውን ዐይነት ፍጹም ተመሳሳይነት በእያንዳንዱ ትረካ ላይ ፍጹም ተመሳሳይ ዘዬ፣ ቃል፣ ወዘተ ልናገኝ አንችልም። እንደ እውነቱ ከሆነ ጸሓፊው በእግዚአብሔር እየተመራ ዘገባዎቹን ያሰፈረልን ልክ እንደ ተቀበላቸው ነው፤ በዚህም፣ ለታሪካዊ ተአማኒነት ሲል ተመሳሳይነትን ሠውቷል ማለት ይቻላል።

3. ጸሓፊ

እዚህ ላይ የሚነሣው ጥያቄ የአሪት ዘፍጥረትን ዘገባ በዚህ መልክ የጻፈው ወይም ያጠናቀረው ማን ነው? የሚለው ይሆናል። ትረካዎቹን በሙሉ በዚህ መልክ ማን አጠናቀራቸው? የዘፍጥረት ጸሓፊና በጥቅሉ የባለ ዐምስቱ ቅጽ መጻሕፍት ጸሓፊ አንድ ሰው ሳይሆን አይቀርም። በመጽሐፉ ውስጥ ጸሓፊው የራሱን ስም ወይም ማንነት አንድም ስፍራ ላይ አልገለጸም። ይሁንና የጥንትና ተአማኒ ምንጮች ጸሓፊው ሙሴ እንደ ሆነ ይናገራሉ። ሙሴ ከባለ ዐምስቱ ቅጽ መጻሕፍት ጋር ጥብቅ ቍርኝት እንዳለው ምንም ጥርጥር የለውም (ዘፀ 17፥14፤ 20፥1፤ ከኢያሱ 8፥31-32 ጋር ያነጻ)። በኢየሱስና በዐዲስ ኪዳን ጸሓፊዎች እምነት የባለ ዐምስት ቅጽ መጻሕፍት ጸሓፊ ሙሴ ነው (ለምሳሌ፣ ዮሐ 5፥46)።

4. ዐላማ

የአሪት ዘፍጥረት ዐላማ ከባለ ዐምስቱ ቅጽ መጻሕፍት ዐላማ ጋር በእጅጉ የተቈራኘ በመሆኑ እዚህ ላይ በጥቅሉ የምንመለከተው የባለ ዐምስቱን ቅጽ መጻሕፍት ዐላማ ይሆናል። እንዲህ የመሰለውን ትልቅ መጽሐፍ ዐላማ ለመመርመር መጽሐፉ የተጠናቀረበትን ዘዴና ቴክኒክ ማወቅ ያስፈልጋል።

የባለ ዐምስቱ ቅጽ መጻሕፍት ቀኖና የመጨረሻ ቅርጹን ለማግኘት ቢያንስ አራት የተለያዩ የሥነ ጽሑፍ ዐይነቶችን አጣምሮአል፤ እነርሱም፦ ትረካ፣ ግጥም፣ ሕግና ነገረ መለኮት ናቸው። በእነዚህ መጻሕፍት በተለይም በአሪት ዘፍጥረት ውስጥ የትውልድ ሐረጎቹ ምንባባት ቍልፍ ሚና አላቸው። ይሁን እንጂ የዐምስቱን ቅጽ መጻሕፍት ቅርጽ ወይም ውቅር በተመለከተ ወደ ፍሬያማ መደምደሚያ አያደርሱም። በእነዚህ ዐምስት ቅጽ መጻሕፍት ውስጥ የምናገኛቸውን ሕገጋት ብናጤናቸው፣ ተመሳሳይ የሆነ አስተያየት መስጠት ይቻላል። የእነዚህ ሕገጋት አስፈላጊነት ምንም አያጠያይቅም፤ ይሁንና መላው ፔንታቱክ የመጨረሻ ቅርጹን ያገኘው በእነዚህ አማካይነት ነው ማለት አይቻልም።

ይሁን እንጂ በመጻሕፍቱ ውስጥ የምናገኛቸውን ትረካዊና ቅኔያዊ ምንባቦችን በጥልቀት ከመረመረን፣ የመጨረሻ ቅርጻቸውን እንዴት እንዳገኙ ፍንጭ ሊሰጡን ይችላሉ። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንድን ትረካ በቅኔያዊ/በግጥማዊ ንግግርና በመዝጊያ ንግግር መጨረስ የተለመደ የአጻጻፍ ዘዴ ነው፤ እንዲህ ዐይነት የአጻጻፍ ዘዴዎችን በዐምስቱ መጻሕፍት ውስጥ በግልጽ እናገኛለን። በዘፍ 1 እና 2 ላይ የምናገኘው የሥነ ፍጥረት ታሪክ የተደመደመው በአዳም ዐጭር ቅኔያዊ ንግግርና (2፥23) በመዝጊያ ንግግር ነው (ቍ. 24)። በምዕ. 3 ላይ የምናገኘው የውድቀት ታሪክ የተደመደመው በቅኔያዊ ንግግርና (ቍ. 14-19) በመዝጊያ ንግግር ነው (ቍ. 20-24)። በምዕ. 4 ላይ የምናገኘው የቃየን ታሪክ የተደመደመው በቅኔያዊ ንግግርና (ቍ. 23-24) በመዝጊያ ንግግር ነው (ቍ. 25-26)።

እንዲህ ዐይነቱን ባሕርይ በዘፍጥረት ውስጥ ማግኘታችን ጸሓፊው መልእክቱን ለማዋቀር የተጠቀመበት ሁነኛ ዘዴ መሆኑን እንገነዘባለን። ይህን ባሕርይ ይበልጥ የምናየው በዮሴፍ ታሪክ ላይ ነው (ምዕ. 37-48)፤ ታሪኩ የተደመደመው ያዕቆብ ኤፍሬምንና ምናሴን በባረከበት ቅኔያዊ ንግግር ነው (48፥15-16;20)። ከዚህም በላይ ግን ቅኔያዊ ንግግርና ዐጫጭር መዝጊያዎች በዐምስቱም የአሪት መጻሕፍት ውስጥ መገኘታቸው የአጻጻፍ ዘዴው የዐምስቱም መድበሎች (መጻሕፍት) አካል እንደሆነ ያስገነዝባል።

በዐምስቱ የአሪት መጻሕፍት ውስጥ የምናገኘው ሌላው ሥነ ጽሑፋዊ ቅርጽ "ትረካዊ መርገፍ"[4] ብሔረ አሪትን የሚያነብ አንድ ሰው የትረካዎቹን ተመሳሳይነት ባሕርይ ሳያስተውል ማለፍ አይችልም (ለምሳሌ፦ ዘፍ 12፥10-20፤20፥1-18 እና 26፥1-11)። የአብርሃም ወደ ግብፅ ከዚያም ወደ ጌራራ መሰደድ (በሁለቱም ጊዜ የተሰደደው በረኃብ ምክንያት ነው) እንዲሁም የይስሐቅ ወደ ጌራራ መሰደድ (እርሱም የተሰደደው በረኃብ ምክንያት ነው) ለእስራኤል ወደ ግብፅ መሰደድ ዘፍ 41 - ዘፀ 12 መርገፍ ነው፤ በዮሴፍ ታሪክ ላይ እንደ ተገለጸው እስራኤል ወደ ግብፅ የተሰደደችው በረኃብ ምክንያት ነው። ጸሓፊው ሊያሳየን የፈለገው ያለፉት ሁነቶች ወደ ፊት ለሚመጡት መርገፍ ወይም ጠቋሚ መሆናቸውን ነው።

---

[1] በዚህ ማብራሪያ ባለ ዐምስት ቅጽ መጻሕፍት፣ ፔንታቱክ ወይም ብሔረ አሪት የሚሉት ስያሜ ቃላት አንድን ነገር ለመግለጽ የተለዋዋጭ ጥቅም ላይ ውለዋል።

[2] በስተ ኋላ የተጻፉ

[3] ቀድመው የተጻፉ

[4] አንዱ ታሪክ ለመጨረው ታሪክ መገለጫ ከወዲሁ ጠቋሚ የሚሆንበት የትረካ መንገድ ነው ይባላል።

5. ሥነ ጽሑፋዊ ቅርጹ

በዘፍጥረት ውስጥ እዚያና እዚህ ተበታትነው ከምናገኛቸው ቅኔያዊ ክፍሎች በስተቀር አጠቃላይ ሥነ ጽሑፋዊ ቅርጹ ታሪካዊ ትረካ ነው። ይህም፣ ያለፉት ሁነቶች ወደ ፊት ለሚመጣው ትውልድ ትምህርት እንዲሆኑ ነው። ለትረካዎቹ ቅርጽ የሰጧቸው ሁለት የእይታ አንጻሮች አሉ። እነርሱም ታሪካዊ ሁነቶችና ሁነቶቹን የዘገበው ጸሓፊ እይታ ናቸው። እንግዲህ መመልከት ያለብን የሁነቶቹን ታሪካዊ መቼት ብቻ ሳይሆን ሁነቶቹን የዘገበው ጸሓፊ ዐላማና ግቡ ምን እንደ ሆነም ጭምር ነው።

ማንኛውም ታሪካዊ ዘገባ ቢሆን፣ በወቅቱ የተፈጸሙትን ድርጊቶች ሁሉ በሙሉ ያካተተ ሊሆን አይችልም። ጸሓፊው ከተፈጸሙት ድርጊቶች መካከል ተዛማጅ የሆኑትን ብቻ ሳይሆን የድርጊቶቹንም ትርጉምና ከትራኬው ጋር ያላቸውን ጠቀሜታ መምረጥ አለበት።

ዘፍ 1፥1-2፥4ሀ በጥልቀት ስንመረምር ጸሓፊው የሥነ ፍጥረትን ታሪክ ሲዘግብ ጥንቃቄ የተሞላበት ምርጫ አድርጓል። ስለ መላእክት፣ ከዋክብትና ሌሎችም ሰማያውያን አካላት ዝርዝር ዘገባ ከማቅረብ ይልቅ፣ ጸሓፊው በምድር አፈጣጠርና አዘገጃጀት ላይ ማትኩሩን መርጧል። እንደ እውነቱ ከሆነ ጸሓፊው በዚህ በሥነ ፍጥረት ዘገባው ያካተተው ሦስት አርእስት ብቻ ነው፦ እግዚአብሔር፣ ወንድና ሴት እንዲሁም መሬት። ምንም እንኳ በፀሓይና በጨረቃ አፈጣጠር ላይ መጠነኛ ትኩረት ቢያደርግም፣ እነዚህን ሰማያውያን አካላት የጠቀሰው የሰው ልጆች በዚህ ምድር ካላቸው ተልእኮ ጋር በመዛመዳቸው ብቻ ነው (1፥14-15)። እንግዲህ ዘፍ 1፥1-2፥4 ስለ መሬት የሚነግረን ምንድን ነው? ምንባቡ የሚነግረን ምድር የእግዚአብሔር መሆኗን ነው። እርሱ ምድርን ፈጠረ፤ አዘጋጀ፤ ደስ ላለውም ሰጠ (ኤር 27፥5)።

በዘፍ 1፥1-2፥4 ላይ የምናየው ሌላው ትረካ ስለ እግዚአብሔር የተሰጠው ገለጻ ነው። እርሱ የመላው ዓለም ፈጣሪ ነው። እስራኤል እግዚአብሔርን ይበልጥ ለማወቅ በመታደሏ፣ እግዚአብሔርን የእስራኤል አምላክ ወይም የአንድ አገር ብሔር አምላክ አድርጎ የማየት አዝማሚያ ተከሥቶ ነበር (ሚክ 3፥11)። የዘፍ 1 መልእክት ከዚህ ሐሳብ ጋር ፍጹም ይቃረናል፤ እግዚአብሔር የመላው ዓለም ፈጣሪና የሰው ልጆችን ሁሉ የባረከ አምላክ ነው። ከብሔረ ኦሪት ጸሓፊ እይታ አንጻር የመላው ዓለም ፈጣሪ ለሰዎች ሁሉ የሚሆን በረከት አለው። ነገረ መለኮታዊ መሠረቱ ይኸው ነው። ከዚህ በኋላ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለምናገኛቸው ተልእኳዊ ዐዋጆች በመሉ ነገረ መለኮታዊ መሠረቱ ይኸው ነው።

በመጨረሻም ዘፍ 1፥1-2፥4ሀ ለዐምስቱ የኦሪት መጻሕፍት ማእከላዊ ጭብጥ እንደ መንደርደሪያ ያገለግላል። በእነዚህም መጻሕፍት ውስጥ የምናገኘው ትልቁ ድርጊትና ትልቁ ጭብጥ በሲና ተራራ ላይ በእግዚአብሔርና በእስራኤል መካከል የተደረገው ቃል ኪዳን ነው። ይህ ኪዳን እግዚአብሔር ከመጀመሪያው አንሥቶ የአዳምን ዘር ለመባረክ ውጥን እንዳለው በተጨባጭ ያሳየናል። ስለ ኪዳኑ ጭብጥ ሦስት ነገሮችን መናገር ይቻላል፤ (1) የሲናው ኪዳን እግዚአብሔር በአብርሃም ዘሮች አማካይነት የሰው ልጆችን ለመባረክ ዕቅድ እንዳለው ያመለክታል (ዘፍ 12፥1-3፤ ዘፀ 2፥24)። (2) ይሁን እንጂ በሲና የተደረገው ኪዳን እግዚአብሔር የሰው ልጆችን ለመባረክ የነበረውን ዕቅድ ከግቡ አላደረሰም፤ ምክንያቱም እስራኤል እግዚአብሔርን ልትታመንና ፈቃዱንም ልትፈጽም አልቻለችም። (3) ነገር ግን ጸሓፊው የእግዚአብሔር ተስፋ አንድ ቀን እውን እንደሚሆን በሚገባ ለማሳየት ሞክሯል፤ ምክንያቱም ራሱ እግዚአብሔር ወደ ፊት አንድ ቀን እርሱን የሚያምንና የሚታዘዝ ልብ ለእስራኤል እንደሚሰጥ ቃል ገብቷል (ዘዳ 30፥1-10)። በሌላ አነጋገር የዐምስቱ መጻሕፍተ ኦሪት መላ አመለካከት መጪው ዘመን ላይ ያተኮረ ነው። ምክንያቱም የእግዚአብሔር ተስፋ (በረከት) አንድ ቀን ሙሉ በሙሉ የሚፈጸምበትን ጊዜ አሻግረው ይመለከታሉና።

እንግዲህ ዘፍ 1፥1-2፥4ሀን ስናጠቃልለው፣ የዐምስቱ መጻሕፍተ ኦሪት ጸሓፊ የሥነ ፍጥረት ትረካው ከተደራሲያኑ ሕይወት ጋር እንዲዛመድ ይፈልጋል፤ ይኸውም የመላው ዓለም ፈጣሪ እግዚአብሔር ለተለዩ ፍጡራኑ ማለትም ለሰው ልጆች ምድርን መኖሪያ ቤታቸው አድርጎ አዘጋጅቷል፤ ደግሞም ፍጥረታቱን ሁሉ ለመባረክ ወጥኗል።

ትንተና

፩. የእስራኤል አባቶችና የሲናው ተራራ ኪዳን መግቢያ (1፥1-11፥26)

ከ1-11 ያሉት ምዕራፎች የኦሪት ዘፍጥረትና የዐምስቱ መጻሕፍተ ኦሪት አጠቃላይ መግቢያ ናቸው። ስለ እስራኤል አባቶች ለተነገረውም ሆነ (ዘፍ. 12-50) የብሔረ ኦሪትን ማእከላዊ ርእስ በአግባቡ ለመረዳት እንደ መንደርደሪያ ያገለግላሉ፤ የዐምስቱ የኦሪት መጻሕፍት ማእከላዊ ርእስ የሲናው ተራራ ኪዳን ነው (ዘፀ 1- ዘዳ 34)።

ሀ. መሬትና በረከቱ (1፥1-2፥24)

1. የሥነ ፍጥረቱ አምላክ (1፥1)

1 ፈጣሪው፣ "እግዚአብሔር" (ዕብራይስጡ ኤሎሂም) እንደ ሆነ ተገልጿል፤ እርሱም የአባቶችና የሲናው ተራራ ኪዳን አምላክ ነው። 1፥1 በቅጡ ለመረዳት ትክክለኛው ዐውድ መላው ኦሪት ዘፍጥረትና የኦሪት መጻሕፍት ናቸው። እግዚአብሔር ፈጣሪ እንደ ሆነ በመግለጽ በአባቶች አምላክና በሌሎች ሕዝቦች አማልክት (ማለትም ጣዖታት) መካከል መሠረታዊ ልዩነት እንዳለ ተመልክቷል። ይህ ቁጥር በመላው ዓለም ውስጥ የሚገኙ ነገሮች በሙሉ መገኛቸው ማን እንደ ሆነ ይናገራል፤ በዚህም እግዚአብሔር ብቻ ዘላለማዊ እንደ ሆነ ይመሰክራል፤ ሌሎች ነገሮች በሙሉ የተገኙትም ሆነ የሚኖሩት በእርሱ ነው። "በመጀመሪያ" የሚለው ቃል የነገሩን መነሻ ጊዜ (ከዘዳ 11፥12 ጋር ያነጻ) ማለትም የእግዚአብሔርንና የሕዝቡን ታሪክ መጀመሪያ ያመለክታል።

2. የምድሪቱ መዘጋጀት (1፥2-2፥3)

ሀ. የመጀመሪያ ቀን (1፥2-5)

2ሀ ቁጥር ሁለት እግዚአብሔር ምድሪቱን ለሰው ልጆች ከማዘጋጀቱ በፊት የነበረችበትን ሁኔታ ይገልጻል። ከቅርቡ ዐውድ እንደምንረዳው ምድሪቱ "ባዶ ነበረች፤ አንዳችም አልነበረባትም"፤ ምክንያቱም ጨለማ በላይዋ ላይ ነበር፤ በውሃም ተሸፍና ነበር። በሌላ አነጋገር ለመኖር አትመችም ነበር (ኤር 45፥18)። በመሆኑም ከዚህ በኋላ የምናገኘው ታሪክ እግዚአብሔር ምድሪቱን ለሰው ልጆች እንዳዘጋጀ የሚገልጽ ነው። እስራኤል እግዚአብሔርን ባለመታዘዟ ምድሪቱ እንደ ገና "ሰው አልባ ሆነች"፤ ሕዝቡም ለምርኮ ተዳረገ፦ "ምድሪቱን አየሁ፤ እነሆ ባዶ ነበረች፤ አንዳችም አልነበረባትም፤ ሰማያትንም አየሁ፤ ብርሃንም አልነበረባቸውም። . . . እነሆ ፍሬያማ እርሻ ምድረ በዳ ሆነች" (ኤር. 4፥23-26)። በሌላ አነጋገር ምድሪቱ ከምርኮ በኋላ የነበረችበት ሁኔታ እግዚአብሔር በፍጥረት ጊዜ ምድሪቱን ከማዘጋጀቱ በፊት ከነበረችበት ሁኔታ ጋር በእጅጉ ይመሳሰላል። ምድሪቱ ባዶ፣ ጨለማና ጠፍ ነበረች፤ እግዚአብሔር ብርሃንና ሕይወት ይሁን እስኪል ድረስ መጠበቅ ነበረባት።

2ለ የቁ. 2 ሁለተኛ ክፍል የእግዚአብሔርን ወይም የእግዚአብሔርን መንፈስ ሥራ ይተርካል፤ የእግዚአብሔር መንፈስ፣ ልክ ንስር ለጫጩቶቿ ብላ በላያቸው ላይ "እንደምትሰፍፍ" ሁሉ (ዘዳ 32፥11) ገና ባልተዘጋጀው ዓለሙ ላይ እንዲሁ "ይሰፍፋል"። በሥነ ፍጥረት ታሪክና (ዘፍ. 1) በመገናኘ ው ድንኳን አሠራር ታሪክ መካከል አስደናቂ ንጽጽር አለ። በሁለቱም መጻሕፍት ላይ እንደምናነበው የእግዚአብሔር ሥራ (ዘፍ 2፥2፤ ዘፀ 31፥5) የተከናወነው "በእግዚአብሔር መንፈስ" ነው። እግዚአብሔር የፍጥረት ሥራውን "በእግዚአብሔር መንፈስ" አማካይነት እንደ አከናወነ ሁሉ፣ እስራኤላውያንም ሥራቸውን ማከናወን ያለባቸው "በእግዚአብሔር መንፈስ" አማካይነት ነው።

3-5 አብዛኛውን ጊዜ ቁ. 3 የማታየው እግዚአብሔር ብርሃንን የፈጠረው ፀሓይን ከመፍጠሩ በፊት ነው በሚለው ትርጉሙ ነው፤ ለዚህ እንደ ምክንያት የሚጠቀሰው እስከ ቁ 16 ድረስ ትረካው እግዚአብሔር ፀሓይን እንደ ፈጠረ አይገልጽም። ይሁን እንጂ ፀሓይ፣ ጨረቃና ከዋክብት "ሰማይንና ምድርን" በሚለው ሐረግ ውስጥ ተካተዋል፤ በመሆኑም በዚህ ትረካ መሠረት ሰማያውያን አካላት በሙሉ የተፈጠሩት በቁ. 1 ላይ ነው። ቁ. 3 የሚተርከው በጨለማው ውስጥ ስለ ተገለጠችው ፀሓይ ነው (44፥3፤ ዘፀ 10፥23፤ ነህ 8፥3)። "ቀን" እና "ሌሊት" የሚለው አገላለጽ በቁ. 3 ላይ ብርሃን የሚለው ቃል ትርጉሙ ምን እንደ ሆነ እንድናስብ ይጋብዛል። ብርሃን ሲል ፀሓይ ማለቱ ነው? ወይስ ሌላ?

“እግዚአብሔርም አየ” (ቁ. 4:10:12 እና ሌላም ቦታ) የሚለው ሐረግ እግዚአብሔር የሚያይ አምላክ መሆኑን ይገልጻል። ጸሓፊው ስለ እግዚአብሔር ሊናገር አጽንዖት ለመስጠት ከፈለገው ነገር አንዱ ይህ ነው። በመጽሐፉ ውስጥ ለእግዚአብሔር የተሰጠው የመጀመሪያ ስም አጋር የተጠቀመችበት ነው:- “ኤልሮኢ” (“የሚያይ አምላክ”፤ 16፥13፤ ከ22፥1-19 ጋር ያነጻ፤ “አየ” የሚለው ግስ “አዘጋጀ” ተብሎ በትክክል ተተርጉሞአል)። ጸሓፊው እግዚአብሔር የሚያይ አምላክ መሆኑን የገለጸባቸው ሌሎች ዐቢይት ምንባቦች 6፥5፤ 11፥5፤ 18፥21 ናቸው፤ ይሁን እንጂ በእነዚህኞቹ ምንባቦች ላይ ግን አሳዛኝ ትረካ እናያለን፤ በዘፍ 1 ላይ እንደ ተዘገበው ግን እግዚአብሔር ያየው መልካም ነው።

“መልካም” የተባለው ለሰው ልጆች ጠቃሚ የሆነው ነገር ነው። በሁለተኛው ቀን (ቁ. 6-8)። ትረካው “እግዚአብሔርም ያ መልካም እንደ ሆነ አየ” አይልም። ምክንያቱም በዚያን ቀን ለሰው ልጆች በቀጥታ “መልካም” ወይም ጠቃሚ የሆነ አንዳች ነገር አልተፈጠረም ወይም አልተሠራም። ሰማያት ተሠርተው ነበር፤ ውሆችም ተከፍለው ነበር። ይሁንና ሰዎች የሚኖሩባት ምድር “በጥልቁ” ሥር ነበረች። “መልካም” የሚለው ቃል እንደ ገና ተጠቅሶ የምናገኘው ባሕሩ ከተከፈለና የብሱም መታየት ከጀመረ ከሦስተኛው ቀን በኋላ ነው (ቁ. 10)። በመላው ምዕ. 1 ውስጥ እንደ ተገለጸው፣ ለሰው ልጆች “መልካም” የሆነውን ነገር የሚያውቅና ለእነርሱም “መልካም” የሆነውን ነገር የሚያዘጋጅ እግዚአብሔር ነው። በመሆኑም ጸሓፊው በምዕ. 3 ላይ ለተፈጠረው አሳዛኝ ክሥተት ተደራሲያኑን ያዘጋጃል፤ የሰው ልጆች “መልካምንና ክፉን” ለራሳቸው ለማወቅ ያደረጉት ሙከራ ኀጢአት ብቻ ሳይሆን ከንቱም ነበር።

ለ. ሁለተኛ ቀን (1፥6-8)

6-8 በሁለተኛው ቀን የተከናወነውን ነገር ለመረዳት በቅድሚያ ጠፈር የሚለውን ቃል መረዳት ያስፈልጋል። ቃሉ የሚያንጸባርቀው መላለማዊ[5] አመለካከትን ነው? ወይስ የዕለት ተሞክሮን (ለምሳሌ ዝናብ ያዘሉ “ደመናትን ”)? ምንባቡ የሚሰጠን ትርጉም ውሃን ከውሃ የሚለይ የሚለውን ሲሆን፣ ይህንንም ጠፈር ብሎ ይጠራዋል፤ ይህ ቃል (“ሰማይ”) ፀሓይ፣ ጨረቃና ከዋክብት ያሉበትን (ቁ. 14) ብቻ ሳይሆን ዖፎችም የሚበሩበትን (ቁ. 20) ስፍራ ያመለክታል። ጠፈር የሚለውን ስያሜ ሊወክል የሚችል ቃል ወይም ሐሳብ ይኖር ይሆን? ምናልባት ሰማይ የሚለው ቃል በትክክል ሳይገልጸው አይቀርም። ከሰማይ በላይ ያሉት ውሆች ምናልባትም ደመናት ናቸው (ከ7፥11-12፤ ከ2ነገ 7፥2፤ ከመዝ 104፥3፤ 147፥8፤ 148፥4 ጋር ያነጻ)

ሐ. ሦስተኛ ቀን (1፥9-13)

9-13 እግዚአብሔር በሦስተኛው ቀን የሠራቸው ሁለት ነገሮች አሉ:- ደረቁን ምድርና ባሕርን አዘጋጀ፤ደግሞም ደረቁን ምድር በተክሎች ሞላ። በሁለተኛው ቀን ከተሠሩት ነገሮች በተቃራኒ እነዚህ ሁለት ክንውኖች “መልካም” እንደ ሆኑ ተገልጿል፤ በርግጥም ለሰው ልጆች የሚጠቅሙ ነበሩ። ሁለቱም ክንውኖች ከምድሪቱ መዘጋጀት ጋር የተያያዙ ናቸው (በቁ. 3-5 ላይ የተሰጠውን ገለጻ ይመ)፤ ይህም የጸሓፊው ዋና ትኩረት ነው (ከ12፥7፤ 13፥15፤ 15፥18፤ 26፥4 ጋር ያነጻ)። በደረቁ ምድር ላይ እንዳይኖሩ ውሃው ትልቅ ጋሬጣ ነበር፤ ስለዚህ ሰዎች እግዚአብሔር በሰጣቸው ስጦታ ደስ እንዲሰኙ ውሃው መወገድ አለበት (ከጥፋት ውሃ፣ ምዕ. 6-9 እና “ከቀይ ባሕር” መከፈል ጋር ያነጻ፤ ዘፀ 14-15)።

እግዚአብሔር በሦስተኛው ቀን ባከናወነው በሁለተኛው ሥራ ምድርን በዛፎችና በፍሬ ሞላ። ጸሓፊው በምዕ. 1 ላይ እግዚአብሔር ምድሪቱን በፍሬ ለመሙላት ያከናወነውን ተግባር በምዕ. 2 ላይ ገነትን “ለመብል መልካም በሆነ ዛፍ” ለመሙላት ካከናወነው ተግባር ጋር ለማዛመድ ቢፈልግ ኖሮ፣ የሥነ ፍጥረቱ ታሪክ ትኩረት በዔድን ገነት ላይ ይሆን ነበር። እዚህ ላይ የተመረጡ የሥነ ፍጥረት ዘገባዎች ትኩረት እንደ ተሰጣቸው ልብ ማለት ያሻል፤ ጸሓፊው ያተኮረው ለሰው ልጆች ለመብልነት በሚያገለግሉ “ዘር በሚሰጡ ተክሎች” እና “ፍሬ በሚያፈሩ ዛፎች” ላይ ብቻ ነው። ሌላ ምንም ዐይነት ተክል አልተጠቀሰም።

መ. አራተኛ ቀን (1፥14-19)

14 በአራተኛው ቀን ስለ ተከናወኑት ድርጊቶች የቀረበው ዘገባ በርካታ ጥያቄዎችን ያስነሣል። ምንባቡ ፀሓይ፣ ጨረቃና ከዋክብት የተፈጠሩት በአራተኛው ቀን ነው የሚል ከሆነ ፀሓይን፣ ጨረቃንና ከዋክብትን የሚያካትቱት “ሰማይና ምድር” እንዴት “በመጀመሪያ” ሊፈጠሩ ይችላሉ (ቁ. 1)? ፀሓይ ገና ባትፈጠር እንኳ በመጀመሪያዎቹ ሦስት ቀኖች ቀንና ምሽት ሊኖሩ ይችላሉ? ፀሓይ ከመፈጠሯ በፊት ዛፎችና ተክሎች (በሦስተኛው ቀን የተፈጠሩት) ነበሩ? ምንም እንኳ ሰማይና ምድር በመጀመሪያ ቢፈጠሩም፣ እስከ አራተኛው ቀን ድረስ ተፈጥረው አላለቁም ወይም ምናልባት በውሆች ተሸፍነው ሊሆን ይችላል የሚል የተለመደ አስተያየት አለ።

ይህን ምንባብ ከ1፥1 እና 1፥14-18 ጋር በእጅጉ ሊያዋድድ የሚችል ሌላ አተያይ አለ። አንደኛው ሰማይና ምድር ማለት “መላለም” ወይም “ዓለማት” ማለት ከሆነ (ቀደም ሲል እንደ ተጠቀሰው) ፀሓይን፣ ጨረቃንና ከዋክብትን ጨምሮ መላው ዓለም የተፈጠረው በአራተኛው ቀን ሳይሆን “በመጀመሪያ” ነው።

ሁለተኛው አተያይ የቁ. 14 አገባብ ነው። በቁ 6 አገላለጽ መሠረት እግዚአብሔር ጠፈር ይሁን ሲል፣ ከዚህ በፊት ያልነበረ ጠፈር ፈጥሯል (ይህም “ካልነበረ ነገር መፍጠር” ይባላል)። እንግዲህ ጸሓፊው እግዚአብሔር ጠፈርን የፈጠረው በሁለተኛው ቀን እንደ ሆነ ሊነግረን ፈልጓል። ይሁንና በቁ. 14 ላይ እግዚአብሔር “እንዲለዩ . . . . ብርሃን ይሁን” አላለም፤ ይህን ትእዛዝ ከመስጠቱ በፊት ብርሃን አልነበረም፤ ብርሃናቱ የተፈጠሩት ከዚያ በኋላ ነው ማለት አይደለም። ይልቁንም የዕብራይስጡ ምንባብ እንዲህ ይላል:- “በሰማይ ጠፈር ያሉ ብርሃናት ይለዩ”። በሌላ አነጋገር ይህ የእግዚአብሔር ትእዛዝ ብርሃናቱ አስቀድመው እንደ ነበሩ ፍንጭ ይሰጣል፤ በትእዛዙም መሠረት ዐላማና ግብ ተሰጣቸው ማለትም “ቀኑን ከሌሊት እንዲለዩ” እና “ለዘመኖች፣ ለዕለታት፣ ለዓመታትም” መለያ እንዲሆኑ።

15-19 ሦስተኛው አተያይ የተመሠረተው በቁ 15-16 ላይ ነው። በቁ. 15 መጨረሻ ላይ ጸሓፊው “እንዳለውም ሆነ” ይላል። ይህ አገላለጽ የጸሓፊው “ዘገባ” መፈጸሙንና “አስተያየቱ” ደግሞ መጀመሩን ይጠቁማል። በመሆኑም ቁ 16 በአራተኛው ቀን ስለ ተፈጠሩት ስለ ፀሓይ፣ ጨረቃና ከዋክብት የሚተርክ አይደለም፤ ይልቁንም ከዚህ በፊት የተዘገቡት ነገሮች ዐላማቸው ምን እንደ ሆነ የሚገልጽ ነው:- “ስለዚህ እግዚአብሔር [ሌላ ማንም ሳይሆን] ብርሃናትን ፈጥሮ በሰማይ ጠፈር ላይ አኖራቸው”። ከዚህ ትረካ በስተ ጀርባ ጸሓፊው በአጽንዖት ለመናገር የሚፈልገው ነገር አለው። ይኸውም የሰማያትን ብርሃናት የፈጠረው እግዚአብሔር ብቻ ነው፤ በመሆኑም ለእርሱ ብቻ የሚገባውን ክብርና ምስጋና ለሌላ ለማንም መስጠት አይገባም (በርግጥ ሌላ አምላክ የለምና)።

ሠ. ዐምስተኛ ቀን (1፥20-23)

20-23 የሕያዋን ፍጡራን አፈጣጠር በሁለት ቀኖች ተከፍሏል። በዐምስተኛው ቀን እግዚአብሔር የባሕርና የሰማይ ፍጥረታትን ፈጠረ። በስድስተኛው ቀን ደግሞ (ቁ. 24-28) ወንድና ሴትን ጨምሮ የምድር ፍጥረታትን ፈጠረ። በሥነ ፍጥረት ዘገባው ላይ “ፈጠረ” የሚለው ቃል ስድስት ጊዜ ተጠቅሷል (1፥1:21:27፤ 2፥3)። በሌላ ስፍራ የእግዚአብሔርን ተግባር ለመግለጽ የገባው ቃል “አበጀ” የሚለው ነው። “በባሕር ውስጥ የሚኖሩ ታላላቅ ፍጡራን” (ቁ.21) እንዴት እንደ ተፈጠሩ ለመግለጽ “ፈጠረ” የሚለው ቃል የገባው ለምንድን ነው? ለዚህ የተሰጠው አንዱ መልስ እዚህ ላይ የምናየው በሥነ ፍጥረት ታሪክ ዐዲስ መጀመሪያ ማለትም “ሕይወት” (ከቁ. 1:2:26 ጋር ያነጻ) ነው። ታሪኩ ሥርዐት እንዳለው በግልጽ ማየት ይቻላል፤ ጸሓፊው የሕያዋኑን አፈጣጠር በሦስት የተለያዩ ፈርጆች አስቀምጦአል:- በዐምስተኛው ቀን የባሕር ውስጥ ፍጡራንንና የሰማይ ላይ ፍጡራንን፤ በስድስተኛው ቀን ደግሞ የምድር ፍጡራንን።

“በረከት” የሚለው ቃል ለመጀመሪያ ጊዜ ተጠቅሶ እናገኛለን። የባሕርና የሰማይ ፍጥረታት መባረክ ከሰው ዘር መባረክ ጋር ተመሳሳይ ነው። ልዩነቱ ምድርን “መግዛት” የተሰጠው ለሰው ልጆች ብቻ መሆኑ ነው። “ሕይወት ያላቸው ነገሮች” ወዲያው እንደ ተፈጠሩ መባረካቸው አግባብነት አለው። ምክንያቱም በረከቱ ከሕይወት መሰጠት ጋር የተዛመደ ነው።

[5] ስለ መላው ዓለም ያለ

ረ. ስድስተኛ ቀን (1፥24-31)

24-25 በስድስተኛው ቀን ስለ ምድር ፍጥረታት አፈጣጠር የቀረበው ዘገባ ሁለት ነገሮችን ለይቶ አስቀምጧል፦ እነርሱም በምድር ላይ የሚኖሩ “ሕያዋን ፍጡራንና” የሰው ልጆች ናቸው። የመጀመሪያዎቹ በሦስት ቡድን ተከፍለዋል፦ እነርሱም እንስሳት፣ በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱ ፍጥረታት እና የምድር አራዊት ናቸው (ቁ. 24)። የሰው ልጆች ደግሞ “ወንድ” እና “ሴት” ተብለው ተከፍለዋል (ቁ. 27)።

ጸሓፊው እንደ ገና በአምላካዊ ትእዛዝ ይጀምራል፤ እግዚአብሔርም “አለ” በማለት ከተናገረ በኋላ እግዚአብሔርም “አደረገ” ይላል። በቁጥር 25 ላይ ተጨማሪ ገለጻ ተሰጥቷል። ምንም እንኳ ተክሎች የሚበቅሉት ከመሬት ቢሆንም፣ እንስሳቱ የተፈጠሩት ግን በራሱ በጌታ እግዚአብሔር ነው (ከምዕ. 2 ጋር ያነጻ)።

26-27 የሰው ልጆች አፈጣጠር የተነገረው፣ “እግዚአብሔርም አለ” በሚለው የተለመደ አነጋገር ነው። ይሁን እንጂ የእግዚአብሔር ትእዛዝ የተነገረው “ይሁኑ” ተብሎ ሳይሆን (በሦስተኛ መደብ)፣ “እንፍጠር” ተብሎ ነው (በአንደኛ መደብ)። ሁለተኛው፣ ቀደም ሲል በቀረበው ታሪክ ላይ ስለ እያንዳንዱ ፍጥረት አፈጣጠር የተነገረው “እንደ ወገኑ” ተብሎ ሲሆን፣ ስለ ሰው ልጆች አፈጣጠር የተነገረው ግን “በመልካችን [በእግዚአብሔር] እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር” ተብሎ ነው። መልካቸው የሰው መልክ ብቻ አይደለም፤ የፈጣሪንም አምሳል ወስደዋል። ሦስተኛው፣ የሰው ልጆች የተፈጠሩት ወንድና ሴት ተደርገው እንደ ሆነ በግልጽ ተነግሯል። ቀደም ሲል ግን ሌሎች ፍጥረታት ሲፈጠሩ ጾታ እንደ አስፈላጊ ነገር ተቁጥሮ አልተጠቀሰም፤ የሰው ልጆች ሲፈጠሩ ግን ጾታቸው በግልጽ ተጠቅሷል። በመሆኑም እግዚአብሔር “ሰውን” ወንድና ሴት አድርጎ መፍጠሩ አጽንዖት ተሰጥቶታል። አራተኛው በእግዚአብሔር ፍጥረት ላይ የመግዛት ሥልጣን የተሰጠው ለሰው ልጆች ብቻ ነው። የሚገዙትም ፍጥረታትን በሙሉ እንደ ሆነ በግልጽ ተወስቷል፦ ፍጥረታቱም ሰማይ፣ ባሕርና ምድር ናቸው። እንግዲህ ምንባቡ የሚነግረን፣ የሰው ልጆች ከሌሎች ፍጥረታት ሁሉ ልዩ ፍጥረታት መሆናቸውን ነው። የተፈጠሩት በራሱ በእግዚአብሔር መልክና አምሳል ነውና።

በብዙ ቁጥር የተነገረውን “ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር” የሚለውን ሐረግ ለመፍታት ብዙ መከራ ተደርጓል፦። ከተሰነዘሩት አስተያየቶች መካከል፦ (1) ብዙው ቁጥር የሚያመለክተው ሥላሴን ነው፤ (2) ብዙው ቁጥር የሚያመለክተው እግዚአብሔርንና ሰማያውያን አካላቱን ማለትም መላእክቱን ነው፤ (3) በብዙ ቁጥር የተነገረው ሰዎች እግዚአብሔርን ይመስላሉ የሚለውን ሐሳብ ለማስወገድ ነው፤ (4) በብዙ ቁጥር የተነገረው እግዚአብሔር የሰው ልጆችን የፈጠረው አስቦበት እንደ ሆነ ለማሳየት ነው የሚሉ ይገኙበታል። በቁ. 27 ላይ የምናገኘው ነጠላ ቁጥር (“በራሱ መልክ ፈጠረው፤ በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው”) የሚለው ሁለተኛውን አስተያየት ያስወግደዋል፤ ምክንያቱም ወንድና ሴት የተፈጠሩት “በመልኩ” ነው፤ በመላእክት መልክ ስለ መፈጠራቸው አልተገለጸም። ሦስተኛውና አራተኛው አስተያየት ሁለቱም ሊያስሄዱ ይችላሉ፤ ይሁን እንጂ ሁለቱም አስተያየቶች ዐውደ ምንባባዊ መሠረት የላቸውም። በቁጥር 27 ላይ ሰው የተፈጠረው በእግዚአብሔር መልክ እንደ ሆነ ሁለት ጊዜ ተወስቷል፤ ወንድና ሴት ተደርገው መፈጠራቸው ደግሞ ሦስት ጊዜ ተጠቅሷል፤ ከዚህ ጋር ተመሳሳይ የሆነ አገላለጽ በዘፍ 5፥1-2 ላይ ይገኛል። አንዱ ሰው ወንድና ሴት ተደርጎ ተፈጠረ። ልክ እንደዚሁ አንዱ እግዚአብሔር (“እግዚአብሔርም አለ”) የብዙነቱ ነጸብራቅ አድርጎ የሰው ልጆችን ፈጠረ (“ሰውን በመልካችን . . . . እንፍጠር”)። ከዚህ ፍንጭ በመነሣት በቁ. 26 ላይ የተገለጸው የመለኮት ብዙነት እንዲታወቅ የተደረገው በሰው ብዙነት ማለትም ወንድና ሴት ተደርገው በመፈጠራቸው ነው። በወንድና በሴት መካከል ያለው ኅብረትና አንድነት የራሱ የእግዚአብሔር ኅብረትና አንድነት ነጸብራቅ ነውና።

28-31 “ባረካቸው” የሚለው ቃል ትኩረት ሳይሰጠው ሊታለፍ አይገባም። ምክንያቱም በመላው አሪት ዘፍጥረትና በቀሪዎቹ የአሪት መጻሕፍት ውስጥ ማእከላዊ ጭብጥ ነው። ቀደም ሲል ሕያዋን ፍጡራኑ በዐምስተኛው ቀን ተባርከዋል (ቁ. 22)፤ በመሆኑም የሰው ልጆችን ጨምሮ መላው የእግዚአብሔር ፍጥረታት መባረክ አለባቸው። በረከቱ ራሱ መጪ ትውልዶችን የሚያካትት ነው። በመሆኑም የበረከቱ ፍጻሜ ከሰው “ዘር” እና “ከሕይወት” ጋር ተሳስሮ እናገኘዋለን። እነዚህ ሁለት ጭብጦች በዘፍጥረት ትረካ ውስጥ ሰፊ ቦታ ተሰጥቷቸዋል።

ሰ. ሰባተኛ ቀን (2፥1-3)

1-3 ሰባተኛው ቀን በእግዚአብሔር ስለ ተቀደሰ ከመጀመሪያዎቹ ስድስት ቀናት ተለይቷል። በሌሎቹ ቀናት እንደምናየው፣ በዚህ ቀን እግዚአብሔር ሲናገርም ሆነ ሲሠራ አናይም። በዚህ ቀን ባርኳል፤ ደግሞም ቀድሷል፤ ይሁን እንጂ ምንም አልሠራም፤ እዚህ ላይ ተደራስያኑ አንድ ትልቅ ቁም ነገር እንዲያስተውሱ ተፈልጓል፤ ይኸውም እግዚአብሔር በሰባተኛው ቀን ምንም አልሠራም። ምንም እንኳ ዘገባው መጠነኛ ቢሆንም፣ ስለ እግዚአብሔር ዕረፍት ሦስት ጊዜ በአጽንዖት ተናግሯል። ሰዎች በፈጣሪያቸው አምሳል መፈጠራቸው የተነገረው ተደራስያኑ እግዚአብሔርን ይበልጥ እንዲመስሉ ለማሳሰብ ከሆነ (ለምሳሌ፣ ዘሌ 11፥45)፣ በሰባተኛው ቀን እርሱ ያደረገውን እንዲያደርጉ አበክሮ ያስገነዝባቸዋል፤ በሌላ ስፍራ በሰባተኛው ቀን ዕረፉ የሚል ትእዛዝ ተሰጥቷቸዋል (ከዘፀ 20፥8-11፤ ከመዝ 95፥11፤ ከዕብ 3፥11 ጋር ያነጻ)።

3. የምድሪቱ መሰጠት (2፥4-24)

ሀ. የሰው መፈጠር (2፥4-7)

4-6 ይህ ታሪክ የሚጀምረው የመጀመሪያው ሰው ከመፈጠሩ በፊት ምድር የነበረችበትን ሁኔታ በመግለጽ ነው (ከ1፥2 ጋር ያነጻ)። አትኩሮቱም በውድቀት ምክንያት በቀጥታ በተጐዳው የምድር ክፍል ላይ ነው (3፥8-24)። ከትረካው እንደምንገነዘበው ሰው ከመፈጠሩ በፊት (ቁ. 7) የዐመፁና የውድቀቱ መዘዝ ምድሪቱን “ገና” አልጐዳም ነበር። ከዚህ በኋላ ባለው ትረካ የምድሪቱ ሁኔታ በሰው ልጆች ውድቀት ምክንያት እንደ ተጐዳ እናነባለን (ቁ. 4-6)። “የሚዳ ተክል” እና “የሚዳውም ቡቃያ” የሚሉት ሐረጎች በምዕ. 1 ላይ የተጠቀሰውን ተክል አያመለክቱም፤ ነገር ግን በርግማኑ ምክንያት የተከሠቱትን “እሾህና አሜከላ” እንዲሁም የምድር ቡቃያ ነው (3፥18)። ልክ እንደዚሁ በትረካው ላይ “እግዚአብሔር አምላክ በመሬት ላይ ገና ዝናብ አላዘነበም ነበር” የሚል ስናነብ፣ ነገሩ የጥፋት ውሃን እንደሚያጣቅስ ልንገነዘብ እንችላለን (7፥4)።

“ምድርንም የሚያለማ ሰው አልነበረም” የሚለው ሐረግ ወንድና ሴት መሬትን ያርሱ ዘንድ (3፥23) ከዔድን ገነት የተባረሩበትን ጊዜ አሻግሮ ያጣቀሻል። በመሆኑም ለሰው ፍጥረት ታሪክ መግቢያ እንዲሆን ምድሪቱ ለእርሱ እንደ ተዘጋጀች ተነግሮናል። ይሁንና ስለ ምድሪቱ ሲነገረን ሰዎች በባዕድ ምድር እንግዶችና መጻተኞች የሚሆኑበትን በጭላንጭል ልናስተውል እንችላለን።

7 እዚህ ላይ ስለ መጀመሪያው ሰው የተሰጠው ገለጻ በምዕ. 1 ላይ ከምናገኘው ገለጻ ፍጹም የተለየ ሊመስለን ይችላል። ሁለት ገለጻዎች ፍጹም የተለያዩ ላይሆኑ ይችላሉ። ምንም እንኳ ሰው የተፈጠረው በእግዚአብሔር መልክ ቢሆንም፣ አጀማመሩ ግን እንደ “ሰማያዊ ፍጥረት” አይደለም፤ ሰው የተፈጠረው ከምድር ዐፈር ነው። ይህም እንደ ገና ወደ “ዐፈር” የሚመለስበትን የውድቀቱን መጨረሻ አስቀድሞ ያመላክታል (3፥19)። በፍጥረት ጊዜ ሰው የወጣው ከዐፈር ነበር፤ በውድቀት ጊዜ ደግሞ ወደ ዐፈር ተመለሰ።

ለ. የዔድን ገነት መዘጋጀት (2፥8-14)

8 ገነት ለሚለው ገለጻ ትልቅ ትኩረት ተሰጥቷል። እግዚአብሔር አምላክ ገነትን ከተከለ በኋላ ሰውን በዚያ እንዳኖረው ተነግሮናል። በኋላ ግን ይህ ፍጹም በተለየ መንገድ ሲነገር እናያለን። ከዚያም ገነት በምሥራቅ፣ በዔድን ተተከለች። ዔድን የሚለው ቃል አንድ በጣም የሚታወቅ ቦታን ሳያመለክት አይቀርም። ትርጕሙ መደሰት ማለት ነው፤ ይህም ፍጹም ደስታ፣ ሰላምና ዕረፍት የሰፈነበትን ሁኔታ ይገልጻል። በምሥራቅ የሚለው እጅግ አስገራሚ ነው፤ ምክንያቱም በሌላ ስፍራ በዚሁ በአሪት ዘፍጥረት ውስጥ በስተ ምሥራቅ የሚለው የተያያዘው ከፍርድና ከእግዚአብሔር ጋር ከመለየት ነው (ለምሳሌ፣ 3፥24፤ 11፥2፤ 13፥11)። ለምሳሌ፣ ወንድና ሴት ከገነት ሲባረሩ፣ እግዚአብሔር ኪሩቤልን ያስቀመጠው በዔድን ገነት ምሥራቅ (3፥24) ነው፤ ገነት ራሷ በምሥራቅ አይደለችም እንዴ? ብለን እንድንጠይቅ ያደርጋል። እንዲህ ዐይነቱ እርስ በርሱ የሚጋጭ የሚመስለው ነገር የሚፈታው በቁ. 8 ላይ ስለ ገነት የተነገረው “የዔድን ገነት” ተብሎ ሳይሆን “በዔድን ገነት” መባሉን ስናስተውል ብቻ ነው፤ በዚህ ስፍራ ብቻ የሚገኝ አገላለጽ ነው። በመሆኑም ገነት የተተከለችው በዔድን ሲሆን ይህም ከራሷ ከገነት የሚበልጥ ስፍራ

እንደ ሆነ ያመለክታል። በምሥራቅ የሚለው ከራሱ ከዔድን ጋር ተጣምሮ ከታየ ገነት ያለችው በስተ ምሥራቅ በኩል ነው።

9-10 በገነት ለማየትና ለመብላት ደስ የሚያሰኝ ዛፍ፣ የሕይወት ዛፍ፣ መልካምንና ክፉን የሚያስታውቅ ዛፍ እንዲሁም ወንዞች ነበሩ። ወንዞቹ የት እንደሚገኙና በየትኛው ምድር እንደሚፈሱ ሲነገረን ትልቅ ጥንቃቄ ተደርጓል። ምድሩ በወርቅና በከበረ ድንጋይ የተሞላ ሲሆን ስፍራውም ከጊዜ በኋላ ለአብርሃምና ለዘሩ ከተሰጠው ምድር ጋር ይዛመዳል። በኋላ ግን የዔድን ገነት ለእስራኤል አባቶች ተስፋ ከተሰጠው ምድር ጋር ተዛምዷል (ከኢሳ 51፥3፤ ከሕዝ 36፥35፤ ከኢዩ 2፥3 ጋር ያነጻ)።

11-14 የዔድን ገነት ያለችው የት ነው? የሚለው ጥያቄ ለብዙ ጊዜ ሲያከራክር ቈይቷል። የተጠቀሱት ሁለት ወንዞች የኤፍራጥስና የጤግሮስ ወንዞች እንደ ሆኑ በርግጠኝነት መናገር ይቻላል። ስለ ቀሩት ስለ ሁለቱ ወንዞች ለመናገር ግን አስቸጋሪ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ “የኩሽ ምድር” ከኢትዮጵያ ጋር ተያይዞ በመነገሩ “ግዮን” ኢትዮጵያን ምናልባትም ግብፅን አቋርጦ የሚፈሰው ወንዝ ሳይሆን አይቀርም። ስለ “ኤውላጥ” ምድር ምንም የሚታወቅ ነገር የለም።

በትረካው ውስጥ ትልቅ ትኩረት የተሰጠው “ለፊሶን” ነው፤ ይሁንና ስለዚህም ምድር ቢሆን የሚታወቀው እምብዛም ነው። በሌላ በኩል ደግሞ በትረካው ውስጥ የኤፍራጥስ ወንዝ አራተኛው ወንዝ እንደ ሆነ ያለ አንዳች መግለጫ ተወስቷል። የኤፍራጥስና የጤግሮስ ወንዞች መጠቀስ የዔድን ገነትና የተስፋዪቱ ምድር የት እንደሚገኙ ሊጠቁም ይችላል። እነዚህ ወንዞችና “የግብፅ ወንዝ” ለአብርሃም ተስፋ የተሰጠው ምድር ወሰኑ ከየት እስከ የት ድረስ እንደ ሆነ ለማሳየት በአንድነት እንደ ገና መጠቀሳቸው ያጋጣሚ ጉዳይ አይደለም (15፥18)።

ሐ. በገነት የሰው ስፍራ (2፥15-24)

15-24 እግዚአብሔር ሰውን በገነት “እንዳኖረ” ጸሓፊው አስቀድሞ ተናግሯል (ቍ. 8)። አሁን ደግሞ ይህ የሆነበትን ዐላማ ይገልጻል። እዚህ ላይ ከአማርኛችን ትርጉም የተነሣ ሁለት ነገሮች ሊሰወሩብን ይችላሉ። አንደኛው “አኖረው” የሚለውን ቃል ለመግለጽ የገባው የዕብራይስጡ ቃል በሌላ ስፍራ የገባው የእግዚአብሔርን “ዕረፍት” ወይም “ዋስትና” ለመግለጽ ሲሆን፣ ይህም በምድሪቱ ለሚኖሩ ሕዝቡ የሚሰጠው ዋስትና ነው (ለምሳሌ፣ ዘፍ 19፥16፤ ዘዳ 3፥20፤ 12፥10፤ 25፥19)፤ እንዲሁም በጌታ ፊት ለእርሱ “የሚሰጡትን ” ነገር ለመግለጽ ነው የገባው (ዘፀ. 16፥33-34፤ ዘሌ. 16፥23፤ ዘኍ 17፥4፤ ዘዳ 26፥4፡ 10)። እነዚህ ሁለት ትርጉሞች ከቃሉ በስተ ጀርባ አሉ። ሰው በገነት “እንዲኖር” የተደረገው እንዲያርፍና ዋስት እንዲያገኝ እንዲሁም በገነት በእግዚአብሔር ፊት “እንዲኖር” የተደረገው ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት እንዲያደርግ ነው (3፥8)።

ሁለተኛው ነጥብ እግዚአብሔር ሰውን በገነት ያኖረበት ምክንያት ነው። በርካታ ትርጉሞች “እንዲያለማትና እየተንከባከበ እንዲጠብቃት በዔድን የአትክልት ስፍራ አስቀመጠው” ይላሉ። በምዕ. 3፥23 ላይ እንደምናነበው መራትን ያርስ ዘንድ የሚለው ነገር የመጣው በውድቀት ምክንያት ነው። ትረካው እንደሚጠቀመው ጸሓፊው ይህን እንደ ቅጣት አንድንወስደው ፈልጓል፤ ነገሩን በዚህ መንገድ ከተረዳነው ሰው ከተፈጠረበት ከመጀመሪያው ዐላማ ፈጽሞ እንደ ወደቀ እንገነዘባለን። እንዲህ ከሆነ ገነትን ማበጀትና መጠበቅ ያርስ ዘንድ ለሚለው ንጽጽር ሊሆን አይችልም ማለት ነው።

ነገሩን ከእነዚህ ሁለት ምክንያቶች አንጻር ካጤንነው ቍ. 15 መተርጉም ያለበት ያመልክና ይታዘዝ ዘንድ በዔድን ገነት አኖረው ተብሎ ነው። ሰው በገነት እንዲኖር የተደረገው እግዚአብሔርን እንዲያመልክና እንዲታዘዝ ነው። በገነት ሲኖር ሕይወቱ በአምልኮና በመታዘዝ መገለጥ አለበት። ገነትን የሚያበጅና የሚጠብቅ ብቻ ሳይሆን ካህንም ጭምር ነው። ይህ ትርጓሜ ወደ ፊት ከምናገኘው ከትረካው ሐሳብ ጋር ይስማማል። ጸሓፊው በምዕ. 2 ሰው የተፈጠረው በእግዚአብሔር አምሳል ነው የሚለውን ጭብጥ ከመላው ብሔረ አሪት ዐቢይ ጭብጥ ማለትም ከአምልኮና ከሰንበት ዕረፍት ጋር በተጓዳኝ በሚገባ ተንትኗል።

በቍ. 16 ላይ እግዚአብሔር ለመጀመሪያ ጊዜ ለፈጠረው ሰው ትእዛዝ ሲሰጥ ማየታችን ሌላ ተጨማሪ ማረጋገጫ ነው። በእግዚአብሔር መልካም ምድር ደስ ለመሰኘት የእግዚአብሔርን ትእዛዝ መጠበቅ ያስፈልጋል (ከዘዳ 30፥16 ጋር ያነጻ)። ይህ የሚያስገነዝበው ለሰው መልካም የሆነውንና መልካም ያልሆነውን የሚያውቅ እግዚአብሔር ብቻ መሆኑን ነው። መልካም በሆነው ደስ ለመሰኘት የሰው ልጅ በእግዚአብሔር መታመንና እርሱንም መታዘዝ አለበት። የማይታዘዝ ከሆነ ግን ለእርሱ መልካም የሆነውንና መልካም ያልሆነውን መወሰን አለበት። በዚህ ዘመን ለሚኖሩ ሰዎች ይህ ግሩም ሐሳብ ሊመስላቸው ይችላል፤ ይሁን እንጂ በሰው ልጆች ላይ የደረሰ እጅግ አስከፊ ጣጣ ነው፤ ለእነርሱ መልካም የሆነውን የሚያውቅ እግዚአብሔር ብቻ ነውና።

ጸሓፊው በቍ. 16-17 ላይ ይህን በጥቅሉ ከተናገረ በኋላ በቀረው ክፍል ደግሞ እግዚአብሔር “መልካም” ብሎ የሚጠራው ማንን እንደ ሆነ አንድ ተጨባጭ ምሳሌ ይጠቅሳል፤ ይኸውም የሴት መፈጠር ነው። እግዚአብሔር ወንድን ብቻውን ሲያየው “ሰው ብቻውን መሆኑ መልካም አይደለም” አለ። ጸሓፊው በምዕ. 2 መዝጊያ ላይ ሰው በእግዚአብሔር መልክና አምሳል ተፈጥሯል ማለት ምን ማለት እንደ ሆነ የመጨረሻ ሐሳቡን ይናገራል። በመጀመሪያው ምዕራፍ ላይ የሰው ዘር “በእግዚአብሔር መልክ” መፈጠሩ ወንድና ሴት መሆንን እንደሚያካትት ተገልጿል (ቍ. 27)። ስለ ሴት መፈጠር በሚያወሳው በምዕ. 2 ትረካው ደግሞ ጸሓፊው የሰው “በእግዚአብሔር መልክ” መፈጠር “መደጋገፍን” እንደሚያካትት አሳይቷል (“የሚመቸውን ረዳት እንፍጠርለት”)። በዚህ ምዕራፍ ለማጎልበት የሞከረው ይህንን ጭብጥ ነው። በምዕ. 1 ላይ ወንድና ሴት ከእግዚአብሔር የተጋሩት “አምሳል” በምዕ. 2 ላይ በወንዱና በሚስቱ መካከል ባለው መመሳሰል ተገልጧል። በምዕ. 1 ላይ ስለ ወንድና ሴት መፈጠር ከተተረከ ጀምሮ ስለ መለኮት ውይይት ሲነገር ይህ የመጀመሪያው ነው። “እንፍጠር” የሚለው የብዙ ቍጥር አነጋገር “አበጅለታለሁ” በሚለው ነጠላ አነጋገር ተተካ፤ በዚህ ዐይነት የተነገረው ምናልባት እየተፈጠረች ያለችው ሴት ብቻ ስለ ሆነች ሊሆን ይችላል።

በምዕ. 1 ላይ የመለኮት ብዙነት አምሳሉን ያገኘው “በወንድና በሴት” መፈጠር ሲሆን የመለኮት አንድነት አምሳሉን ያገኘው በሰው ብቻውን መሆን ነው። ለሴት የእግዚአብሔር ፈቃድ “ረዳት” እንድትሆን ነው። እዚህ ላይ ለመግለጽ የተፈለገው ለሰው ረዳት ሊሆንለት የሚችል ሌላ ነገር አለመኖሩን ነው። በመሆኑም ልዩ የፍጥረት ተግባር የሆነችውን ሴት መፍጠር አስፈላጊ ሆነ። ሰው ገነትን ለመጠበቅና ለመንከባከብ ረዳት ያስፈልገዋል፡ ይሁንና ነገሩን በ1፥28 ላይ ከተነገረው በረከት አንጻር ካጤንነው “ረዳት” የሚለው ቃል ትኩረቱ ምናልባት ልጅ በመውለድ ላይ ሳይሆን አይቀርም። ከዚህም በተጨማሪ በሴቲቱ ላይ የተላለፈው ፍርድ ልጅ ከመውለድ ሚናዋ ጋር የተዛመደ ነው (3፥16)።

በሌሎች ወሳኝ ተግባሮች እንደ ሆነው ሁሉ ዐዲስ ግንኙነት በተመሠረተ ጊዜ እግዚአብሔር ሲሠራ፣ የእግዚአብሔር በረከት ተቀባዮች በከባድ እንቅልፍ ላይ ነበሩ (ምሳሌ፣ 15፥12፤ 28፥11)። በእንቅልፍ እንዲወሰዱ የተደረገው ሰዎቹን ለማደንዘዝ ሳይሆን፣ ፈጣሪው እርሱ መሆኑንና እነርሱ ግን የተበረከቱ ተቀባዮች ብቻ መሆናቸውን ለማስገንዘብ ነው (ከመዝ 127፥2 ጋር ያነጻ)። አንድ የሚድራሽ ትርጓሜ[6] መጽሐፍ እንዲህ ይላል፡- “ዐጥንቱ በጎኑ እንደ ሆነና ከእርሱም ጋር እንደ ተጣበቀ ሁሉ፣ ልክ እንዲሁ የባሏ ዐጥንት የሆነች መልካም ሚስትም ረዳቱ ለመሆን በጎኑ ቈማለች፤ ነፍሷም ከእርሱ ጋር ተጣብቋል”። በቍ. 23 ያለው የአዳም ልባዊ ምላሽ፣ “ይህች ዐጥንት ከዐጥንቴ፣ ሥጋም ከሥጋዬ ናት” የሚለው በቍ. 21-22 ላይ ከቀረበው ትረካዊ ዘገባ ለየት ይላል፤ በዚህ ክፍል የተጠቀሰው “ዐጥንት” ብቻ ነው። ከዐጥንቱ የሚለው ከዐጥንቱ የሆነች ዐጥንት የሚለውን ያስተጋባል። ከዚህም በተጨማሪ በንግግሩ መዝጊያ ላይ ሥጋ የሚለው ከሥጋዬ የሆነች ሥጋ የሚለውን ያስተጋባል። ዐጥንትና ሥጋ የሚለው ሴቲቱ የተሠራችው ወንዱ ከተሠራበት ተመሳሳይ ነገር እንደ ሆነ ያሳያል።

ለእንስሳቱ ስም የማውጣቱ ተግባር ስለ ሴት መፈጠር የሚያወሳው ታሪክ አካል እንደ ሆነ ግልጽ ነው። ምክንያቱም በቍ. 20 መዝጊያ ላይ ጸሓፊው “ለአዳም ተስማሚ ረዳት አልተገኘ ለትም” ይላል። አዳም ለእንስሳቱ ስም ሲያወጣ የሚመቸውን ረዳት ይፈልግ እንደ ነበር ጸሓፊው አመልክቷል። የሚመቸው ረዳት አለመገኘቱ፣ ሰው ከሌሎቹ ፍጥረታት ጋር ጨርሶ እንደማይመሳሰል ያሳያል። ባንጻሩም “ከዐጥንቱ የሆነች ዐጥንት፣ ከሥጋዬ የሆነች ሥጋ” የሚለው አዳም የራሱን አምሳል በሴት ላይ እንዳስተዋለ ያስገነዝባል።

[6] የአይሁድ ስብከት ማብራሪያ

ለ. ምድሪቱና ከምድሪቱ መወገድ (2፥25-3፥24)

1. አለመታዘዝ (2፥25-3፥7)

የእኩይ ጣጣንና የኀጢአት ፈተናን በተመለከተ እዚህ ከምናየው በበለጠ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሰፊ ትንተና ተሰጥቶ አናገኝም።

ሀ. ሽግግር (2፥25)

25 ቍጥር 25 የምድርንና የበረከትን ታሪክ (1፥1-2፥24) ከውድቀት ታሪክ ጋር ያያይዘዋል (2፥25-3፥24)። “ሁለቱም” የሚለው ቃል ቀደም ሲል የቀረበውን ዘገባ ሲጠቍም “ዕራቍታቸውን ነበሩ፤ ይሁን እንጂ አይተፋፈሩም ነበር” የሚለው ደግሞ ከዚህ በኋላ የምናገኘውን ዐቢይ ጣጣ ያስተጋባል።

የአዳምንና የሚስቱን “ዕራቁትነት” ለመግለጽ ሁለት የተለያዩ ነገር ግን የተዛመዱ ቃሎች ገብተዋል። በትረካው መጀመሪያ ላይ “አሮም” (“ዕራቁት”) የሚለው ቃል የተመረጠው “አሮም” እና “አሩም” (“ተንኰለኛ”) በሚሉት ቃላት መካከል ካለው የድምጽ መመሳሰል የተነሣ ሳይሆን አይቀርም። ይህም ትረካውን ከቀደመው ዘገባ ጋር ለማያያዝና ከዚህ በኋላ የምናገኘው ታሪክ ድርጊቱና ውጤቱ ምን እንደ ሆነ ለመጠቁም ነው። ከዚህም በተጨማሪ የእባቡን ተንኰለኛነት እና በዕራቍትነታቸው የተመሰለውን የአዳምንና የሔዋንን ንጹሕነት በተመለከተ ፍንጭ ይሰጠናል፤

ሁለተኛው፣ በ2፥25 ላይ “አሮም” በሚለውና በ3:7 ላይ “ኤሮም” (ዕራቁት) በሚሉት ቃሎች መካከል የትርጕም ልዩነት አለ። ኤሮም የሚለው ቃል በዘዳ 28፥48 ላይ የገባው የእግዚአብሔርን ቃል ባለመታመናቸውና ባለመታዘዛቸው ምክንያት ተቀጥተው ለምርኮ የተዳረጉትን የእስራኤላውያንን ሁኔታ ለመግለጽ ነው። (ከሕዝ 16፥39፤ 23፥29 ጋር ያነጻ)። ጸሓፊው ሰዎች የነበሩበትን የመጀመሪያውን ዕራቍትነት ከሁለተኛው ለመለየት ሲል፣ ለመለየት ከባድ የሆነ፣ ነገር ግን ሊደረስበት በሚችል ፍንጭ ለታሪኩ ትርጕም ሰጥቷል። ውድቀት ሲባል አዳምና ሔዋን “ዕራቍታቸውን እንደ ሆኑ ዕወቁ” ማለት ብቻ ሳይሆን በእግዚአብሔር ፍርድ ሥር በመሆናቸው ዕራቍታቸውን ነበሩ ማለት ነው።

ለ. ፈታኙ (3፥1)

1 ጸሓፊው ስለ እባቡ መሠረታዊ ፍንጭ ይሰጣል፦ ከተፈጠሩት ፍጥረታት ሁሉ እጅግ “ተንኰለኛ” ነበር። ይህ ቃል ቀዳማይ ትርጕሙ አሉታዊ ሳይሆን ጠቢብነትንና ብልኀነትን የሚገልጽ ስያሜ ነው። ይህ የሚያሳየው በውድቀትና የሰው ልጆች ጥበብን ለማግኘት በነበራቸው ጥማት መካከል ዝምድና መኖሩን ነው። የሰው አለመታዘዝ እንደ ታላቅ ዐመፀኛነት ወይም ሕግ ተላላፊነት ሳይሆን እንደ ታላቅ ሞኝነት ነው መታየት ያለበት። ለእርሱ የሚያስፈልጉ “መልካም” ነገሮች ሁሉ ነበሩት፤ ነገር ግን ተጨማሪ ፈለገ፤ እግዚአብሔርን ለመምሰል ፈለገ።

የተከለከለችው ዛፍ “መልካምንና ክፉን” የምታስታውቅ ዛፍ ናት። አዳምና ሔዋን ከዛፉ ወስደው ሲበሉ ሔዋን ዛፉ፣ “ጥበብንም ለማግኘት የሚያጓጓ እንደ ሆነ” አየች (ቍ 6)። በመሆኑም እባቡ የጥበብ ትክክለኛ ምሳሌ ማለትም የጠቢቡን ሰው እውነተኛ ምሳሌ ወክሎ ቀርቧል። ይሁን እንጂ እባቡና ጥበቡ ስርግማን ተዳረጉ (ቍ 14)። እባብ እግዚአብሔር ከፈጠራቸው “የዱር እንስሳት” መካከል አንዱ እንደ ሆነ መረሳት የለበትም (ከ 1፥25፤ 2፥19 ጋር ያነጻ)። ልዕለ ፍጡር[7] አልነበረም።

ሐ. ፈተናው (3፥2-7)

2-7 የፈተናው ታሪክ የተነገረው በሚያስገርም ግልጽነት ነው። እባቡ የተናገረው ሁለት ጊዜ ብቻ ነው፤ ይሁንና በአዳምና በሔዋን እንዲሁም በፈጣሪያቸው መካከል ሊኖር የሚገባውን መታመንና መታዘዝ ለመገለባበጥ ያ በቂ ነበር። የታሪኩ ማእከል “መልካምንና ክፉን” የሚያስታውቀው ጥያቄ ነው። እግዚአብሔር ይህን ዕውቀት ከአዳምና ከሔዋን እየሸሸገ እንደ ሆነ እባቡ ቢናገርም፣ በመጀመሪያዎቹ ሁለት ምዕራፎች ላይ የምናገኘው ትረካ ግን እግዚአብሔር ይህን ዕውቀት ለአዳምና ለሔዋን እየጠበቀ ነበር (ለምሳሌ፣ 1፥4፤10፡12)። በሌላ አነጋገር የእባቡ ሐሳብ የሰው ልጆች እግዚአብሔርን ቢታመኑና ቢታዘዙ እርሱ “መልካም” የሆነውን ነገር ያዘጋጅላችኋል የሚለውን ማእከላዊ ጭብጥ መገዳደር ነው።

ከውድቀት በፊት በመጨረሻው ሰዓት የሴቲቱ ሐሳብ “የዛፉ ፍሬ . . . . መልካም እንደ ሆነ አየች” የሚለው ነበር። እስከ አሁን ድረስ ይህ አገላለጽ የተነገረው ለእግዚአብሔር ብቻ ነበር። እንግዲህ ፈተናው የተዘገበው በእግዚአብሔር ሥልጣን ላይ እንደ ዐመፁ ሳይሆን ይልቁንም ያለ እግዚአብሔር ከእርሱ ያልተሰጠውን ጥበብና መልካምን እንደ ፈለጉ ተደርጎ ነው። ይህን ለማድረግ እንደ ወሰኑ ወዲያውኑ ዐመፁ። የታሪኩ ጭብጥ የተመሠረተው ጥበብን ለማግኘት ባደረጉት አሳዛኝ ምፀታዊ ገለጻ ላይ ነው። በርግጥም እባቡ የሰጣቸው ተስፋ ምፀታዊ በሆነ መንገድ ተፈጽሟል፤ አዳምና ሔዋን ከዛፉ በበሉ ጊዜ እንደ እግዚአብሔር ሆኑ። ምፀቱ ግን እነርሱ ራሳቸው ድሮውንም ቢሆን እንደ እግዚአብሔር ነበሩ፤ ምክንያቱም በመልኩ ተፈጥረዋልና (1፥26)።

ከፍሬው ከመብላታቸው በፊት “ክፉን” ብቻ እንጂ “መልካምን” ሊያውቁ አይችሉም የሚለው በትረካው ላይ አልተነሣም። ይሁን እንጂ ከፍሬው ሲበሉና ዐይናቸውም ሲከፈት ያዩትና የተደሰቱበት ነገር “መልካም” አልነበረም። ዐዲስ ያገኙት ዕውቀት ቢኖር የገዛ ዕራቍትነታቸው ነበር። “እንደ እግዚአብሔር” እንዲሆኑ ያደረጋቸው “የመልካምና የክፉ” ዕውቀታቸው እርስ በርስ እንዳይዋደዱ አደረጋቸው፤ በዕራቍትነታቸው ተፋፈሩ። ልዩነቶቻቸውን እንዲሸፍንላቸው በአንድነት ቅጠል ሰፉ። ጥበብን ተመኙ፤ ነገር ግን ከንቱነትንና ድካምን ዐጨዱ።

2. ፍርድ (3፥8-20)

ሀ. ትዕይንቱ (3፥8)

8 የፍርዱ ትዕይንት የተከፈተው በእግዚአብሔር መምጣት “ድምፅ” ነው፤ ይህም እግዚአብሔር ሕዝቡ እንዲታዘዘው ሲጣራ ለመግለጽ የተለመደ አነጋገር ነው (ከዘዳ 5፥25፤ 8፥20፤ 13፥18 ጋር ያነጻ)። የርግማኑ ትዕይንት የእግዚአብሔርን በረከት ለማግኘት መመዘኛው ምን እንደ ሆነ አንድ ወሳኝ ማሳሰቢያ በስውር ትቶልናል።

እዚህ ላይ የእግዚአብሔር በሲና ተራራ መገለጥ (መምጣት) አስቀድሞ ተመስሏል። በሲና ተራራ ላይ ሕዝቡ “የአምላችንን የእግዚአብሔርን ድምፅ” ሰምቷል። በሁለቱም ስፍራ ፍርሀት እንደ ነገሠ እናነባለን። በዚህ በአሁኑ ምንባብ አዳምና ሔዋን በገነት የእግዚአብሔርን ድምፅ ሲሰሙ ከፊቱ ሸሹ። የሸሹት ወደ ዛፎቹ ነበር። ዛፎች የሰው ልጆች ከእግዚአብሔር ጋር የነበራቸው ኅብረት እንደ ተለወጠ ለመግለጽ ዐቢይ ሚና ተጫውተዋል። በምዕ. 1-2 ፍሬ የሚያፈሩ ዛፎች የእግዚአብሔርን የተትረፈረፈ ስጦታ ይወክላሉ። በምዕ. 3 ደግሞ የሰው ልጆችን በዐመፅ ለማጥመድና ከእግዚአብሔርም ፊት ለማምለጥ ምክንያት ሆነዋል። በመጨረሻም አዳምና ሔዋን ከገነት ሲባረሩ መንገዳቸው “ወደ ሕይወት ዛፍ” በሚወሰደው ተዘግቷል (ቍ. 24፤ ከዘዳ 21፥22-23፤ ከገላ 3፥13 ጋር ያነጻ)።

ለ. ምርመራው (3፥9-13)

9-13 እግዚአብሔር ከመፍረዱ በፊት ለዐመፀኞቹ ሰዎች የተናገረው ነገር ቢኖር ጥያቄ ብቻ ነው (ከ4፥9-10፤ 18፥21 ጋር ያነጻ)። ጸሓፊው በሚያስደንቅ ክሂሎት “ዕራቍት” የሚለውን ቃል በመደጋገም አዳም በራሱ ቃል እንዲፈረድበት አድርጓል። ከዚያም በኀጢአት ምክንያት በአዳምና በሔዋን መካከል የተፈጠረውን ጠላትነት ለማሳየት ብርቱ ጥረት አድርጓል፤ አንዱ በአንዱ ፊት ሲቆም ከሚሰማው መተፋፈር ባሻገር፣ አዳም ሔዋንን፣ ይባስ ብሎም እግዚአብሔርን ሲከስ አሳይቷል። አዳም የተናገረው ቃል በ2፥18 ላይ እግዚአብሔር በመጀመሪያ ለተናገረው እንደ ምፀት ነው። ከውድቀቱ ታላቅነት የተነሣ የእግዚአብሔርን መልካም ስጦታ የችግሩ ምንጭ አድርጎ መመልከት ጀመረ።

ሐ. ብያኔው (3፥14-20)

ምንም እንኳ ስለ እባቡ፣ ስለ ሔዋንና እንዲሁም ስለ አዳም መረገም ብዙ መናገር ቢቻልም፣ የተጻፈው ግን በጥቂቱ ነው። በዚህም ይህ የሰው ልጆች ሁሉ ታሪክ እንጂ የእነርሱ ታሪክ ብቻ እንዳልሆነ እንገነዘባለን። ጸሓፊው በሚያስደንቅ ክህሎት እነዚህ ሦስት ወገኖች የየዘራቸው “ራስ” እንደ ሆኑ አመልክቷል። በአንድ በኩል እባብ፣ በሌላ በኩል ደግሞ አዳምና ሔዋን ሁለት ታላላቅ ሕዝብ ሆነው ታላቅ ትግል ሲገጥሙ እናያለን፤ ይህ ትግል ፍጻሜውን የሚያገኘው ወደ ፊት በሚመጣው “ዘር” ብቻ ይሆናል።

[7] ከፍጡርነት በላይ አልነበረም

14-15 በአንድ ወቅት እባብ “ተንኰለኛ” (አሩም፣ ቍ. 1) ነበር፤ አሁን ደግሞ “ተረገመ” (አሩር)። “መረገሙ” ከእንስሳት ከምድር አራዊትም ሁሉ እንዲለይ አድርጎታል፤ አሁን “በደረቱ ይሄዳል፤ ዐፈርም በሕይወቱ ዘመን ሁሉ ይበላል”። ይህ ርግማን እባብ ከዚህ ቀደም እንደ ሌሎቹ የምድር እንስሳት ቆሞ ይሄድ እንደ ነበር አያመለክትም። እዚህ ላይ ለመግለጽ የተፈለገው እባብ በደረቱ ሲሄድ በሕይወት ዘመኑ ሁሉ “ዐፈር እንደሚበላ” ነው፤ ይህም “ፍጹም ድል መደረጉን” ይገልጻል (ከኢሳ 65፥25፤ ከሚክ 7፥17 ጋር ያነጻ)።

እዚህ ላይ የእባብና የሴቲቱ ዕድል የዘሮቻቸው ሁሉ ዕድል ሲሆን እናያለን። በመጀመሪያ በቍ. 15 ላይ “ጠላትነቱ” በእባቡና በሴቲቱ እንዲሁም በእባቡ ዘርና በሴቲቱ ዘር መካከል ነበር። ነገር ግን በዚሁ በቍ. 15 ላይ የሴቲቱ “ዘር” “እርሱ” (ዘሯ ወንድ እንደ ሆነ ልብ ይሏል) የእባብን ራስ እንደሚቀጠቅጥ ተገልጿል። የሴቲቱ “ዘር” እዚህ ላይ የገባው እንደ ቡድን (ወይም ግለሰብ) ቢሆንም፣ የእባቡ “ዘር” ከራሱ ከእባቡ እንደሚለይ ሁሉ የእርሷም ዘር ከእርሷ ይለያል። ይሁንና በዚህ ቍጥር ላይ እንደ ተገለጸው የእባቡን ራስ የሚቀጠቅጠው የሴቲቱ “ዘር” ነው። ምንም እንኳ በሁለቱ ዘሮች መካከል ጠላትነት ቢኖርም፣ በቀኑ መጨረሻ የሚቀጠቀጠው የእባቡ “ዘር” ሳይሆን ራሱ እባቡ ነው፤ “ራስህን ይቀጠቅጣል”። በሌላ አነጋገር ጸሓፊው እባቡንና “ዘሩን” እንደ አንድ ሊቈጥራቸው ፈልጓል። “ዘሩ” ሲቀጠቀጥ፣ የእባቡ ራስ ተቀጥቅጧል። በዚህ ምንባብ ላይ በርካታ ጥያቄዎች ሊነሡ ይችላሉ። በፈተናው የእባቡ ሚና ምንድን ነው? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ሙከራ አልተደረገም። ፈታኙስ ማን ነው? ሰይጣን? ይሁንና ሌሎች የቅዱሳት መጻሕፍት ጸሓፊዎች ከእባቡ ዘር በስተ ጀርባ ሰይጣን እንዳለ ገልጸዋል (ከሮሜ 16፥20፤ ከራእ 12፥9 ጋር ያነጻ)።

ቍ. 15 ግራ የሚያጋባ፣ ነገር ግን ወሳኝና አሻሚ ሐሳብ ይዟል፦ የሴቲቱ “ዘር” ማን ነው? የዚህ ቍጥር ዐላማ ይህን ጥያቄ ለመመለስ ሳይሆን ጥያቄውን ማንሣት ነው። ጸሓፊው መልሱን የሚሰጠን በቀረው የመጽሐፉ ክፍል ነው።

16 በሴቲቱ ላይ የተላለፈው ፍርድ በመጀመሪያ ከልጆቿ፣ ከዚያም ከባሏ ጋር ተሳስሯል። ልጆች የምትወልደው በብርቱ ጭንቅ ነው። ፈቃዷም ወደ ባሏ ይሆናል፤ እርሱም ይገዛታል። ፍርዱን ከመጽሐፉ ስፊ ዐውድ አንጻር ካጤንነው፣ በምዕ. 1 እና 2 ላይ በተወሣው የሴቲቱ ሚና ላይ ይመረኮዛል። ሴቲቱና ባሏ በልጅ ባርኮታቸውና (1፥28) በጋብቻ ጥምረታቸው ደስ እየተሰኙ መኖር ነበረባቸው (2፥18፡21-25)። ፍርዱ ከእነዚህ ሁለት ነገሮች ጋር ይዛመዳል። ለበረከት የተፈጠረችው ሴት (የትዳር ጓደኛ እንድትሆንና ልጅ እንድትወልድ) በርግማኑ ምክንያት ከዚህ ጐደለች። ሴቲቱ በእነዚያ ታላቅ የሕይወት በረከት ጊዜዎች (ጋብቻና ልጅ) በእግዚአብሔር ላይ ማመፅ ያመጣባትን ክፉ መዘዝ በግልጽ ሳታስተውለው አልቀረችም።

በቍ. 15 ላይ በተሰጠው ተስፋና በቍ. 16 ላይ ለሴቲቱ በተነገረው ቃል መካከል ዝምድና መኖሩን ሳናጤን ልናልፍ አይገባም። በዚያ ተስፋ መሠረት የመጨረሻው ድል የሚገኘው በሴቲቱ “ዘር” ነው። በመጀመሪያ ወንድና ሴት ሲፈጠሩ፣ ልጅ መውለድ ከፈጣሪያቸው የተሰጣቸው በረከት ነበር (1፥28) አሁን ደግሞ ከውድቀት በኋላ ልጅ መውለድ እባቡ ድል የሚሆንበትና በረከትም እንደ ገና የሚመለስበት መንገድ ይሆናል። እያንዳንዱ ልጅ ሲወለድ ጭንቅና ሥቃይ ቢኖርም፣ የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ተስፋ ትልቅ ማጽናኛችን ነው። የምጥ ሥቃይ የሚያስታውሰን የውድቀት መዘዝን ብቻ አይደለም፤ በቅርብ ጊዜ ለሚሆነውም ደስታ ምልክት ነው (ሮሜ 8፥22-24፤ ከማቴ 24፥8 ጋር ያነጻ)።

17-20 በርግማኑ ምክንያት የሰው ልጅ ከፈጣሪ ከተሰጠው መልካም ምድር ከእንግዲህ በኋላ በነጻ ሊበላ አይችልም። በመላው ምዕ. 2-3 የሰው ልጆች ከፈጣሪያቸው ጋር ያላቸው ቀጣይ ግንኙነት “መብላት” ከሚለው ጭብጥ ጋር ተሳስሯል። በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰውን ሲባርከውና ሲመግበው በ2፥16 ላይ ተመልክቷል። ከዚያም ፈታኙ መጥቶ እግዚአብሔር ለአዳምና ለሚስቱ በርግጥ እግዚአብሔር መልካም አምላክ ነው ወይ የሚለውን ጥርጣሬ የዘራባቸው “መብልን” ጠቅሶ ነው (3፥1-3)። በመጨረሻም የአዳምና የሔዋን አለመታዘዝ “ሴቲቱ . . . . ከፍሬው ወስዳ በላች፤ . . . . እርሱም በላ” በሚለው ተገልጿል (3፥6)። እንግዲህ “መብላት” በሰዎች ላይ ከመጣው ፍርድ ጋር ተያይዟል (“ስለ መብላትና” ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር ስላላቸው ግንኙነት ዘሌ 11 ይመ፤ እንዲሁም ስለ ንጹሕና ንጹሕ ስላልሆኑ ምግቦች ዘዳ 14፣ ዘሌ 23 ደግሞ ሰዎች የእግዚአብሔርን ግብዣ ስለ መካፈላቸው ይመ)።

ስለ “ምድር” የተሰጠው መግለጫ በምዕ. 2 ላይ ከምናገኘው ጋር የተገላቢጦሽ ነው። ምድር አሁን ያለችበት ሁኔታ በመጀመሪያ ስትፈጠር የታለመላት አይደለም፤ ይልቁንም የሰዎች ዐመፅ ውጤት ነው (የ2፥4-6 ማብ ይመ.)። ይህም “ዐዲስ ሰማይና ዐዲስ ምድር” ስሚለው ጭብጥ መንገድ ከፈተ (ራእ 21፥1፤ ከኢሳ 65፥17፤ ሮሜ 8፥22-24 ጋር ያነጻ)። ልክ እንደዚሁ ቍ. 19 ሰው ሲፈጠር ከታለመለት ዐላማ ጋር የተገላቢጦሽ መሆኑን ያሳያል። ከውድቀት በፊት ሰው ከምድር ዐፈር ከተበጀ በኋላ “የሕይወት እስትንፋስ” ተሰጠው (2፥7)። አሁን ወደ መጣበት ዐፈር መመለስ አለበት። በመሆኑም የሞት ፍርድ ተበየነበት (2፥17)። ስለ ውድቀት መዘዝ ይበልጥ የሚያስረዳን፣ በወንዱ ስም ማለትም “አዳም” (አዳም፣ ቍ. 20) በሚለውና በተበጀባት “ምድር” አዳማህ መካከል ያለው ዝምድና ነው። አዳምም ለሚስቱ ስም አወጣላት፤ አሁን “ሔዋን” ብሎ ጠራት፤ ይህም የወደ ፊት ዕጣ ፈንታዋን ሲገልጽ (“የሕያዋን ሁሉ እናት”) የቀድሞ ስሟ ግን (ከ2፡23 ጋር ያነጻ) መገኛዋን ያመለክታል (“ከጕድኑ ዐጥንት”)።

3. ክለላ (3፥21)

21 እግዚአብሔር ያዘጋጀላቸው የልብስ ዐይነት የተጠቀሰው (ከቈዳ ልብስ) ምናልባት አዳምና ሔዋን ከውድቀት በፊት የነበሩበትን ሁኔታ ለማስታወስ ሳይሆን አይቀርም። ከውድቀት በፊት ዕራቍታቸውን ነበሩ፤ ደግሞም አይተፋፈሩም ነበር (2፥25)። ጸሓፊው ከቈዳ ልብስ እንደ ተዘጋጀላቸው ሲገልጽ ምናልባት ስለ እንስሳት መሥዋዕት አስፈላጊነት ከወዲሁ ለማስተጋባት ፈልጎአል (ከዘፀ 28፥42 ጋር ያነጻ)።

4. ከገነት መባረር (3፥22-24)

22-23 በአዳምና በሔዋን ላይ የተላለፈው የሞት ፍርድ ከገነት መባረርንና ከሕይወት ዛፍ መከልከልን ያካትታል (ዘፀ 31፥14)፤ ደግሞም በገነት ካለው የእርስ በርስ መጠባበቅ መወገዳቸውን ያካትታል (ከዘፍ 4፥14 ጋር ያነጻ)። በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠሩ ሰዎች (ከ1፥26 ጋር ያነጻ) “እንደ እግዚአብሔር ለመሆን” ሲመኙ (ቍ. 5-7) ከውድቀት በኋላ ራሳቸውን ከእግዚአብሔር ተነጥሎ አገኙት። ከእግዚአብሔር ጋር በመሆን የሚያገኙትን ደስታ እንደ እግዚአብሔር ለመሆን በተመኙ ጊዜ አላገኙትም (ከመዝ. 16፥11 ጋር ያነጻ)።

በ2፥15 (ማብ. ይመ.) ላይ አዳም በገነት እንዲሆን የተደረገው እግዚአብሔርን እንዲያመልክና እንዲታዘዝ ነበር፤ አሁን ግን ከውድቀት በኋላ ምድርን “እንዲያርስ” ከገነት ተባረረ (ቍ. 23)፤ ወደ ሕይወት ዛፍ እንዳይደርስም ተከለከለ (ቍ. 24)።

24 ከውድቀት በኋላ ገነትና የሕይወት ዛፍ በኪሩቤል መጠበቃቸው፣ እግዚአብሔር በሲና ተራራ ላይ በገባው ኪዳንና በሕጉ በረከትንና ሕይወትን ለሰዎች እንደ ገና ለመስጠት ውጥን እንዳለው ያመለክታል (ዘፀ. 25፥10-22፤ ከዘዳ 31፥24-26 ጋር ያነጻ)። ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸው ኅብረት ሊታደስ የሚችለው በኪዳኑ አማካይነት ብቻ ነው (ዘፀ. 25፥22)። በኪዳኑ አማካይነት ሰዎች በዘፍ. 2፥15 ላይ ሐሜት ሲያደርጉበት ወደ ነበረው ሁኔታ ይመለሳሉ፤ እግዚአብሔርን የሚያገለግሉ፣ ፈቃዱን የሚታዘዙና በረከቱንም የሚካፈሉ ሕዝቦች ይሆናሉ። በዚህ ትረካ ላይ “ምሥራቅ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው “ከኤድን ውጭ” ያለውን ስፍራ ነው (ሆኖም ከ11፥2፤13፥11 ጋር ያነጻ)።

ሐ. ሕይወት ከገነት መባረር በኋላ (4፥1-26)

1. አምልኮ (4፥1-8)

1-2 ሔዋን ከውድቀት በኋላ የተናገረችው ቃል በርካታ ጥያቄ ያስነሣል። በእግዚአብሔር ርዳታ ወንድ ልጅ መውለዷን ስትገልጽ፣ የእባቡን ራስ ይቀጠቅጣል የተባለው “ዘር” (3፥15) በዚህ ልጅ አማካይነት እንደሚፈጸም ርግጠኛ መሆኗን ሊያሳይ ይችላል። ይሁንና የተናገረችው ቃል ከትምክሕት ያለፈ አይደለም። እግዚአብሔር አዳምን እንደ ፈጠረ ሁሉ፣ እርሷም አዳምን የመሰለ ሰው ፈጠረች፤ በዚህም በ3፥15 ላይ የተሰጠውን ተስፋ ለመፈጸም ችሎታ እንዳላት አሳየች። ይህ ትርጓሜ በብዙ መንገድ ያስሄዳል። አንደኛው፣ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ብዙ ጊዜ ተደጋግሞ የተወሳው ጭብጥ ሰዎች ከእግዚአብሔር የሚገኘውን በረከት በራሳቸው ጥረት ለማግኘት መሞከራቸው ነው። (ከምዕ. 11፤ 16፥1-4 ጋር ያነጻ)። ሁለተኛው፣ ሔዋን ራሷ የተናገረችው ተቃራኒ ቃል ነው። በመጀመሪያ ሔዋን “ወንድ ልጅ አገኘሁ” ብላ ነበር፤ በትረካው መጨረሻ ግን “እግዚአብሔር ምትክ ሰጠኝ” አለች (ቍ. 25)።

ከዚህም በተጨማሪ ሔዋን ሄት የተሰጣት ለቃየን ምትክ እንዲሆነኝ ነው አላለችም፤ ነገር ግን ለአቤል ምትክ እንዲሆን ነው፤ ይህም ተስፋዋን የጣለችው በአቤል እንጂ በቃየን አለመሆኑን ያሳያል።

3-4 የቃየንና የአቤል ታሪክ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘው አምልኮ ምን ዐይነት እንደ ሆነ መልካም ትምህርት ያስተምራል፤ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘው አምልኮ ከንጹሕ ልብ የሚመነጭ ነው። ታሪኩ ስለ ንጹሕ ልብ የሚያስተምረው እንዴት ነው? ጸሓፊው ሁለቱ ወንድማማቾች ባቀረቡት መሥዋዕት መካከል ያለው ልዩነት ምን እንደ ሆነ በግልጽ አልተናገረም። ቃየን ያቀረበው መሥዋዕት የደም መሥዋዕት አይደለም የሚለው ዝነኛ አመለካከት እምብዛም አያስዔድም። ምክንያቱም ከትረካው እንደምንረዳው ሁለቱም መሥዋዕቶች በራሳቸው ተቀባይነት አላቸው፤ ሁለቱም መሥዋዕቶች "መሥዋዕት" እንደ ሆኑ ተገልጿል። ከዚህም በተጨማሪ ሁለቱም ያቀረቡት መሥዋዕት "የመጀመሪያ ፍሬ" ወይም በኩራት ናቸው፤ በመሆኑም አቤል ልክ እንደ አንድ እረኛ "መጀመሪያ ከተወለዱት በጎች መካከል" እንዳቀረበ ሁሉ፣ ቃየንም እንደ አንድ ገበሬ "ከምድር ፍሬ" አቀረበ።

5-7 እግዚአብሔር የቃየንን መሥዋዕት ያልተቀበለበት ምክንያት ምንም ይሁን ምን፣ ትረካው ግን በቃየን ሁለት ምላሾች ላይ ትኩረት እንድንሰጥ አድርጓል፦ (1) ቃየን በእግዚአብሔር ተናደደ (ቁ. 4) እንዲሁም (2) በአቤል ተናደደ (ቁ. 8)። ጸሓፊው ችግሩን በዚህ ዐይነት በመግለጽ ለማለት የፈለገውን ነገር "መልካም ብታደርግ ተቀባይነትን አታገኝምን?" በሚለው ስውር ትረካ ዙሪያ አዋቅሯል፤ "ስለዚህ በፍሬአቸው ታውቋቸዋላችሁ" (ማቴ 7፥20)። እግዚአብሔር ቃየን መልካም ቢያደርግ ለእርሱ የተሻለ እንደ ሆነ ለምናታል፤ አለበለዚያ ንጹሕ ደም ቢያፈስ መዘዙ ከባድ እንደ ሆነና ከምድሪቱም እንደሚባረር አስጠንቅቆታል (ከቁ. 2 ጋር፤ ከኤር 7፥5-7 ጋር ያነጻ)።

8 ይህ ትረካ ከመማጸኛ ከተሞች ሕግ አንጻር ሊጤን ይችላል። የከተሞቹ ዐላማ "በሚሰጥህ ምድር የንጹሕ ሰው ደም እንዳይፈስ" ለማድረግ ነው (ዘዳ 19፥10)። ይህም የቃየንና የአቤል ታሪክ ማእከላዊ ርእስ ነው (ቁ. 10)።

በሕጉ መሠረት (ዘዳ 19፥11) አንድ ሰው ነፍስ ገዳይ ነው የሚባለው ባልንጀራውን አድፍጦ ከገደለው ("ጥቃት ካደረሰበት") ነው። በዚህ ምንባብ ላይ እንደ ተገለጸው "በመስኩም ሳሉ ቃየን ወንድሙን አቤልን አጠቃው (በቁሙ "ተነሣበት")፤ ገደለውም"። በዘዳግሙ ሕግ መሠረት የቃየን ድርጊት ሞት የሚገባው ነበር። እግዚአብሔር ግን ቃየንን ማረው፤ በታሪኩ ላይ እንደምናነበው የእግዚአብሔር ምሕረት ቃየን ከሠራው ከተማ ጋር ተሳስሯል፤ ይህም በቃየን ታሪክና በመማጸኛ ከተሞቹ መካከል ያለው ትስስር የአጋጣሚ ጉዳይ አለመሆኑን ያስገነዝባል።

2. ንስሓ (4፥9-15ሀ)

9-12 አሁንም እግዚአብሔር ለፍርድ ሲመጣ በመጀመሪያ ጥያቄ ሲያቀርብና (ቁ. 9) ከዚያም ወደ ፍርድ ሲሄድ እንመለከታለን (ቁ. 11-12)። ስለ ቃየን ፍርድ የተሰጠው ገለጻ በዘዳ 28፥16-18 ላይ ለእስራኤል ከተሰጣት ብርቱ ማስጠንቀቂያ ጋር በእጅጉ ተመሳሳይ ነው (ከኢሳ 26፥21፤ ከሚዕ. 27 ጋር ያነጻ)።

13-14 "ልሸከመው" የሚለው ትርጉምና በቁ. 15 ላይ እግዚአብሔር ለቃየን የሰጠው መልስ፣ ቃየን በቅጣቱ እያጉረመረመ ሳይሆን በኀጢአቱ እየተጸጸተ መሆኑን ይገልጻሉ። በቁ. 14 ላይ ቃየን የእግዚአብሔር ፍርድ ከምድረ ገጽ እንደሚያጠፋው ተገንዝቧል፤ ምክንያቱም ለእርሱ ከለላ የሚያደርግለት ኀብረተ ሰብ የለም። ከመኖሪያቸው እንደ ተባረሩት እንደ ወላጆቹ እንደ አዳምና ሔዋን በቃየን ላይ የተበየነው የሞት ፍርድ የሚፈጸመው ከለላ ከሚያደርግለት ኀብረተ ሰብ እንዲወገድ በማድረግ ነው።

15ሀ ቃየን የተናገራቸው ቃሎች በራሳቸው ንስሓ መግባቱን አያመለክቱም፤ ሆኖም የእግዚአብሔር ምላሽ ቃየን በቁ. 13 ላይ የተናገረው ቃል የንስሓ ቃል እንደ ሆነ ያመለክታል።

3. ከለላ (4፥15ለ - 24)

15ለ-18 የመማጸኛ ከተሞቹ ዳራ (ዘኍ 35፥9-34) ለቃየን የተሰጠው ምልክት ምን እንደ ሆነ ፍንጭ ሊሰጠን ይችላል። ዐላማው ቃየን በቀል እንዳይደርስበት ለመከለል ነው። አንዳንድ የአማርኛ ትርጉሞች (ለምሳሌ ዐመት) "ምልክቱ" በቃየን "ላይ" እንደ ተደረገ ይገልጻሉ፤ ምንባቡ የሚናገረው ግን ለቃየን ምልክት እንደ ተደረገለት ነው (በቁሙ "ለቃየንም ምልክት ሾመለት"፤ 21፥14ን፤ 44፥21ን፤ ከ21፥ 13:18፤ 27፥27፤ 45፥7:9፤ 46፥3 ጋር ያነጻ)። ምንም እንኳ ምልክቱ ምን እንደ ሆነ በግልጽ ባይጠቀስም፣ ትረካው ግን ቃየን ከተማ በሠራባትና "ከዔድን በስተ ምሥራቅ" ወደምትገኘው ወደ ኖድ ምድር እንደ ተሰደደ መዘገቡን ይቀጥላል። ነገሩን ከመማጸኛ ከተሞች አንጻር ካጤንነው፣ ስለ "ከተሞቹ የተነገረው ትረካ" ስለ "ምልክቱ ከተነገረው ትረካ" ተከትሎ መገኘቱ ትልቅ ትርጉም ሳይኖረው አይቀርም። "ምልክቱ" የተሰጠው የአቤልን ሞት ለመበቀል ከሚያስብ ሰው ቃየንን ለመከለል በመሆኑ፣ የቃየን ከተማ መለኮታዊ ከለላ የምታደርግለት "ምልክቱ" ናት (ከዘኍ 35፥12 ጋር ያነጻ)። በላሜሕ ዘመን እንኳ የቃየን ከተማ "ለነፍስ ገዳዮች" መጠለያ ነበረች። በመሆኑም የቃየን ከተማ እግዚአብሔር ቃየንንና ዘሩን ከደም ተበቃዮች ለመከለል ሲል የሰጠው "መማጸኛ ከተማ" ተደርጋ ልትታይ ትችላለች (ዘዳ 19፥11-13 ይመ)። ቀሪው የምዕራፉ ክፍል የሚያተኩረው ቃየን በሠራት "ከተማ" ዐውድ በዳበረው "ባህል" ላይ ነው።

19-24 ከከተማ ሕይወት ጋር ተቈራኝተው ከምናገኛቸው ነገሮች መካከል ከብት እርባታ (ያቤል፣ ቁ.20)፣ ኪነ ጥበብ (ዩባል፣ ቁ.21)፣ የእጅ ጥበብ (ቱባልቃይን፣ ቁ.22)፣ ምናልባት ጥብቅና (ላሜሕ፣ ቁ. 23-24) ትልቁን ስፍራ ይይዛሉ። ላሜሕ ለሁለቱ ሚስቶቹ የተናገራቸው ቃሎች አብዛኛውን ጊዜ የሚወሰዱት እንደ ትምክሕተኛና እብሪተኛ ንግግር ተደርገው ነው። ይሁንና በሙሴ ሕግና ስለ መማጸኛ ከተሞች በተነገሩት ትምህርቶች ዐውድ መሠረት የላሜሕ ቃሎች የሕግና የፍትሕ አቤቱታዎች ናቸው። በሙሴ ሕግ መሠረት አንድ ነፍስ ገዳይ ፍትሓዊ ፍርድ እስኪቀበል ድረስ በመማጸኛ ከተሞች ሊቀመጥ ይችላል (ዘኍ 35፥12)። ላሜሕ ስለ ቃየን ተበቃዮች ሲናገር (ቁ. 24) እርሱም በራሱ ከተማ ተበቃዮች እንዳሉለት ገልጿል።

ላሜሕ የንጹሕ ሰው ደም አለማፍሰሱን ለማሳየት እርሱ የገደለው እርሱን "ያቈሰለውንና የጐዳውን" ሰው እንደ ሆነ ይናገራል። እንደ ቃየን "ባልንጀራውን አልጠላውም፤ አድፍጦ አልጠበቀውም፤ ተነሥቶም አልገደለውም" (ከዘዳ 19፥11 ጋር ያነጻ)። ነገር ግን ይህን ሁሉ ያደረግሁት ራሴን ለመከላከል ስል ነው በማለት አቤቱታውን ያቀርባል። የላሜሕ አቤቱታ "ዐይን በዐይን፣ ጥርስ በጥርስ" ከሚለው መርሕ ጋር በእጅጉ ይመሳሰላል (ዘፀ 21፥25)። በዚህ መርሕ መሠረት አንድ በደል ወይም ወንጀል መቀጣት ያለበት በፍትሓዊ ፍርድ ብቻ ነው። በመሆኑም ላሜሕ ሰው የገደለው ስላቈሰለው እንጂ "ስለ ጠላው" አይደለም (ዘዳ 19፥4-6)። በተንኰል ወንድሙን የገደለው ቃየን የሚበቀልለት ሰው ካለው፣ ራሱን ለመከላከል ሲል ሰው የገደለው ላሜሕ በርግጥ የሚበቀልለት ሰው ይኖረዋል። እዚህ ላይ መልእክቱ የላሜሕ የፍትሕ ግንዛቤ ትክክል ነው ወይም እንደ ምሳሌ ይሆነናል ለማለት ሳይሆን፣ የቃየን ከተማና ዘሮች ራሱን ያዋቅረ አንድ ኀብረተ ሰብ፣ የራሱ የሕግና ፍትሕ ሥርዐትም ያለውም እንደ ነበረ ለመግለጽ ነው።

4. በረከት (4፥25-26)

25-26 ምንም እንኳ ከውድቀት በኋላ የቃየን ልጆች ቢበለጽጉና የዐዲስ ዓለም መሥራቾች ቢሆኑም፣ ትረካው ትኩረታችንን ከቃየን ዘር በአቤል "ምትክ" ወደ ተወለደው ዐዲስ ልጅ ይመልሳል። ጸሓፊው እንደዚህ በመሳሰሉ ትረካዎች ስለ ሴቲቱ ዘር ለመናገር ያለውን ፍላጎት ባጭሩ ይቀጨዋል። እዚህ ላይ ለመጽሐፉ ጭብጥ ማእከል የሆነ አንድ አብነት ሲመሠረት እናያለን። ተስፋ የተነገረለት ዘር የሚመጣው ከአስመሳዩ ወራሽ ሳይሆን እግዚአብሔር ከመረጠው ወራሽ ነው። ቃየን የተስፋው "ዘር" ከሚመጣበት መሥመር ካልሆኑት ሰዎች አንዱ ሆነ (ያፌት፣ 10:2-5፤ ካም፣ 10:6-20፤ ናኮር፣ 11፥29፤ 22፥20-24፤ እስማኤል፣ 17፥20፤ ሎጥ፣ 19፥19-38፤ ዔሳው፣ ምዕ. 36)። የሔዋን ልጅ የሄት ትውልድ ሐረግ ወሳኝነት የተገለጸው ሰዎች በእርሱ ዘመን እግዚአብሔርን በእውነተኛ አምልኮ ያመልኩት እንደ ነበረ በሚያሳየው ጭብጥ ነው።

መ. የኖኅ ታሪክ (5፥1-10፥32)

በምዕራፍ 5 መግቢያ ላይ አንድ ዐቢይ ጭብጥ መጀመሩን የሚጠቁም ዐዲስ አርእስት እናገኛለን፦ "የአዳም የትውልድ ሐረግ እንደሚከተለው ነው"። በ9፥29 ላይ የሚፈጸመው ይህ ክፍል የተዋቀረው በአዳም ዐሥር ትውልዶች ዝርዝር ዙሪያ ነው፤ ዝርዝሩ የተፈጸመው በኖኅ ነው። የኖኅ ሞት ከተዘገበ በኋላ (9፥29) የእርሱ ልጆች ዐዲስ ዝርዝር ይጀምርና በአብርሃም መወለድ ይጨርሳል (11፥26)። በመጠናቸው የተለያዩ በርካታ

ትረካዎችን እያቀጣጠለና እየደራረበ የትውልድ ሐረጎችን መዘርዘር የዘፍጥረት መጽሐፍ ትልቁ ባሕርይ ነው።

1. *መግቢያ (5፥1-3)*

1-3 መግቢያው የተደራስያኑን አትኩሮት በምዕ. 1 ላይ ወደ ተወሡት ድርጊቶች በተለይም ወደ እግዚአብሔር “አምሳል” ጭብጥ ይመልሳል። ቁ. 1-3 ምዕራፍ 5ን ከ 4፥25-26 ጋር ያያይዛል፤ በዚህም ስለ ልደትና ስለ ስም የተወሡት ገለጻዎች ቀጥለዋል። በመጀመሪያዎቹ ወላጆችና ልጆቻቸው እንዲሁም በእግዚአብሔርና በአዳም ገለጻዎች መካከል መመሳሰል አለ። በዘፍጥረት ውስጥ እግዚአብሔር ለአዳም ስም ሲያወጣለት ይህ የመጀመሪያው ነው፤ ይህም፣ እግዚአብሔር ለልጁ ስም እንደሚያወጣ አባት የራሱን ሚና ያሳያል። እግዚአብሔር እንደ አባት የራሱን ሚና ሲፈጽም ይበልጥ የምናየው፣ እግዚአብሔር አዳምን “በእግዚአብሔር መልክ” ሲፈጥረውና አዳምም በምሳሌው እንደ መልኩ ልጅ ሲወልድ በመካከላቸው ባለው ጉድኝት ነው። ምንም እንኳ አዳም የሴት አባት፣ ሴትም የሄኖስ አባት፣ ወዘተ. ቢሆኑም፣ የሁሉም አባት ግን እግዚአብሔር ነው። እግዚአብሔር የሰው ልጆችን እንደ ባረካቸው በድጋሚ የተጠቀሰው (ቁ. 2)፣ አባት ለልጆቹ የሚያደርገውን ክብካቤ ለማስታወስ ነው፤ ዘፍጥረት መጽሐፍ ውስጥ ብዙ ጊዜ ተደጋግሞ የተወሣ ጭብጥ ነው። እዚህ ላይ የምናየው አንድ አፍቃሪ አባት በበረከቱ ለልጆቹ የወደ ፊት ሕይወት ዋስትና ሲሰጥ ነው። ምንም እንኳ ከሰዎች ሞኝነት የተነሣ ቢሰናከልም፣ የእግዚአብሔር የመጀመሪያው የበረከት ሐሳብ ግን በሴቲቱ ዘር (3፥15)፣ በአብርሃም ዘርና (12፥3) “ከይሁዳ ነገድ በሆነው አንበሳ” (49፥8-12፤ ከራእ 5:5-13 ጋር ያነጻ) እንደ ገና ይፈጸማል።

2. *የአዳም ልጆች (5፥4-32)*

4-32 በምዕራፍ 5 ላይ የምናገኛው የትውልድ ሐረግ በ11፥10-26 ላይ ከምናገኘው ከሴም የትውልድ ሐረግ ጋር በቅርጹ ተመሳሳይ ነው። ሁለቱን ስናነጻጽር የምናገኘው ልዩነት ቢኖር “ከኖረ በኋላ ሞተ” (ምዕ. 5) የሚለው ሐረግ መካተቱን ብቻ ነው። የዚህ ምክንያቱ የሄኖክ አለመሞት ነው፤ በምዕ. 5 ላይ የእያንዳንዱ ቀዳማይ አባት መሞት በግልጽ የተጠቀሰው የሄኖክን ልዩ ታሪክ አጉልቶ ለማሳየት ነው። እርሱም “አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር አደረገ”። ይህ ሐረግ ለኖኅ (6፥9)፣ ለአብርሃምና ለይስሐቅ ተነግሯል (17፥1፤ 24፥40፤ 48፥15)።

በሄኖክ ታሪክ የሞት ፍርድ የመጨረሻው ቃል አይደለም። በዚህም ወደ ሕይወት ዛፍ ለመድረስ የሚያስችል በር እንዳለ እንገነዘባለን። ሄኖክ “አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር ስላደረገ” በሩን አገኘው፤ ይህም ሕይወትን ለማግኘት ለሚፈልጉ ሁሉ ምሳሌ አደረገው። ይህ ጭብጥ በምዕ. 17 መግቢያ ላይ እግዚአብሔር ኪዳኑን ከአብርሃም ጋር ሲመሠርት እንደ ገና ተወሥቷል። “አካሄድን ከእግዚአብሔር ጋር ማድረግ” ማለት ሕግን መጠበቅ ብቻ ሳይሆን የሕይወት መንገድ ነው። ይህ ጭብጥ “ሕግ” ከሌላቸው ሰዎች/ሕዝቦች ጋር ተዛምዷል፤ ይህም ሕግን በመጠበቅ ሳይሆን ከዚህ የተሻለ ሌላ የሕይወት መንገድ እንዳለ ያሳያል።

በምዕራፍ 5 የምናገኘው የትውልድ ሐረግ በምዕራፉ መዝጊያ ላይ የጥፋት ውሃን ታሪክ እንዲያካትት ሲባል ሆነ ተብሎ በተለየ መንገድ ተዋቅሯል። የጥፋት ውሃ ታሪክ በትውልድ ሐረጉ ላይ የተካተተው፣ ሦስት ወንድ ልጆቹን በወለደበት በኖኅ ዘመን በነበሩ ሕዝቦችና (5፥32) ኖሮ በሞተበት ዘመን መካከል ነው (9፥29)። እዚህ ላይ ሁለት ነገሮች ጉልተው ይታያሉ። አንደኛው፣ ኖኅ በርግማን ምክንያት ከመጣው ልፋትና ድካም መጽናናትን እንደሚያመጣ ተነግሯል (ቁ. 29) ምናልባት ኖኅ የሚያመጣው መጽናናት የሰው ልጆች በመርከቢ እንዲድኑና ከጥፋት ውሃ በኋላ የመሥዋዕት ሥርዐት በመመሥረቱ ሊሆን ይችላል (ከ8፥21 ጋር ያነጻ)። ሁለተኛው፣ የጥፋት ውሃ ታሪክ በትውልድ ሐረጉ ላይ የተካተተው ስለ ኖኅ መሞት የመጨረሻው ቃል ከመነገሩ በፊት ነው፤ የኖኅ መሞት የሕዝቦች ትውልድ ሐረግ አካል ሆኗል (ምዕ. 10)። ሄኖክ ከሞት ለመትረፍ የበቃበት ምክንያት (“አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር ስላደረገ”) እንደ ሆነ ሁሉ ኖኅም ከጥፋት ውሃ ለመትረፉ ይህ መሠረቱ ሆነ።

ዐጭር የትውልድ ሐረግ መግለጫ በመስጠት የኖኅ ስካር ታሪክ ለጥፋት ውሃ ታሪክ መዝጊያ ሆነ (9፥18-27)። ይህ የኖኅ አስገራሚ ድርጊት፣ ስለ እርሱ የተነገረው ታሪክ በዚህ ዐይነት እንዲፈጸም ምክንያት ሆነ፡- ኖኅ . . . ኖሮ ሞተ (ቁ. 29) የኖኅ ድርጊት የሚያሳፍርና የሚያስነውር ነበር (የወይኑን ተክል ፍሬ ወሰደ፤ ዕራቍቱንም ሆነ)። ይህም ከአዳምና ከሔዋን ታሪክ ጋር የሚጐዳኝ ነው፤ (በገነት ያለውን ፍሬ በሉ፤ ራቍታቸውን መሆናቸውንም ዐወቁ)።



ይህ ሠሌዳ የባቢሎንን የጐርፍ መግለጫ ይዟል። አሁን በእንግሊዝ ቤተ መዘክር ውስጥ ይገኛል።

3. *መዝጊያ (6፥1-4)*

1-2 ጸሓፊው በአበው ትውልድ ሐረግ መደምደሚያና ከጥፋት ውሃ ታሪክ በፊት ስለ አዳም ልጆች ሁኔታ ዐጭር መግለጫ ይሰጣል (ከ10፥31-32፤ 11፥27-32፤ ዘፀ 1፥7 ጋር ያነጻ)። ቁ. 1-4 በተመለከተ እስከ አሁን ሦስት ዐበይት አስተያየቶች አሉ። “የእግዚአብሔር ልጆች” የተባሉት (1) መላእክት ናቸው፤ (2) ነገሥታት ናቸው፤ (3) “ከሄት ነገድ የሆኑ” መንፈሳውያን ሰዎች ናቸው። የመጀመሪያው አስተያየት ከማቴ 22፥30 ጋር ስለሚቃረን እምብዛም ተቀባይነት የለውም። በብዙዎች ዘንድ ተቀባይነት ያለው አስተያየት፣ “የእግዚአብሔር ልጆች” የሚለው የሚያመለክተው ከሄት ነገድ የሆኑትን ነው። ይህ አስተያየት የተመሠረተው በቁ. 1-4 ላይ ነው፤ ምንባቡ የጥፋት ውሃን ታሪክ ከማስተዋወቁም ባሻገር የጥፋት ውሃም የመጣው በእነዚህ ቁጥሮች ላይ በተነገረው ምክንያት ነው። ሆኖም ቁ. 1-4 የምዕ. 5 ማጠቃለያ ከሆነ፣ በምንባቡ ላይ የተነገሩን ነገሮች በሙሉ በሰው ልጆች ታሪክ ውስጥ እንግዳ ያልሆኑ ናቸው ማለት ነው። እንግዲህ ይህ ዐጭር ታሪክ የአዳም ልጆች በቍጥር እየበዙ መሄዳቸውን፣ መጋባታቸውንና ልጅም መውለድ መቀጠላቸውን ያስታውሰናል፤ ይህም እስከ ዛሬ ድረስ የሰው ልጆች የዕለት ተዕለት ሕይወት ነው (ከማቴ 24፥38-39 ጋር ያነጻ)።

3 ቍጥር 3 በራሱ ዐውድ ውስጥ ከላይና ከታች ከተባሉት ነገሮች ጋር ከተገናዘበ ትርጕሙ ግልጽ ነው። እግዚአብሔር ሰዎችን ወንድና ሴት አድርጎ ከፈጠራቸው በኋላ፣ “ሰው (አዳም) ብሎ ጠራቸው” (5፥2)። ይህም በምዕ. 4 ላይ ከምናገኛቸው ግለሰቦች በተጨማሪ ሌሎችንም እንደሚያካትት ግልጽ ነው። በተቀረው የምዕ. 5 ክፍል አትኩሮቱ እንደ ገና በግለሰቦች ላይ ይሆናል። በዚህ በቍ. 3 ላይ እግዚአብሔር ለሁለተኛ ጊዜ ስለ ሰው ልጆች ሲናገር “ሰው” ብሎ ይጠራቸዋል። እግዚአብሔር ስለ ሰው ልጆች በተናገራቸው በእነዚህ ሁለት ቃሎች መካከል የዐሥር ታላላቅ ግለሰቦች ስም ዝርዝር ተጠቅሷል፤ የእነዚህ ግለሰቦች ዕድሜ በቍ. 3 ላይ “ዕድሜው 120 ዓመት ይሆናል” ተብሎ ከተወሣው የሰው ልጆች ዕድሜ በእጅጉ ይልቃል። ይህ የሚያመለክተው ለእነዚህ ሰዎች ረጅም ዕድሜ የሰጣቸው በውስጣቸው የሚኖረው የእግዚአብሔር መንፈስ መሆኑን ነው። ከእነዚህ ግለሰቦች በቀር ረጅም ዕድሜን የኖሩ ሰዎች በሌላ ዘመን ቢኖሩም፣ ሁልጊዜ የሚከሠት አይደለም። ዐጭሩ ዕድሜ የሰው ልጆችን ውድቀትና ከፈጣሪ መለየት ያሳያል። በመሆኑም ጸሓፊው በመጽሐፉ ውስጥ የሰዎችን ዕድሜ በመጥቀስ ዕድሜያቸው በየጊዜው እየቀነሰ መምጣቱን በሚገባ አሳይቷል (ከ11፥10-26 ጋር ያነጻ)። በዐምስቱ የኦሪት መጻሕፍት መዝጊያ ላይ በመጨረሻ በ120 ዓመቱ የሞተ ግለሰብ ተጠቅሶ እናገኛለን (ዘዳ. 34፥7)።

ሉተርና ሌሎች ግለሰቦች 120 ዓመቱን የሚመለከቱት እግዚአብሔር የጥፋት ውሃን ከመላኩ በፊት ለሰዎች የሰጠው የንስሓ ጊዜ አድርገው ነው። ይህ ምናልባት በ120 ዓመቱና በ11፥10-26 ላይ በተነገረው ዘገባ መካከል ያለውን ልዩነት ለመፍታት የተደረገ ሙከራ ነው። የንስሓ ጊዜ የሚለው ትርጓሜ

ምናልባት የ1ጴጥ 3፥20 ተጽዕኖ ሳይኖርበት አይቀርም፤ ምንባቡ በዘፍ 6፥3 ላይ የተወሣውን 120 ዓመት ይጠቅሳልና።

4 በዐምስቱ የኦሪት መጻሕፍት በሌላ ስፍራ "ኒፊሊም" የሚለው የሚያመለክተው በዘፀአቱ ዘመን በከነዓን ምድር ይኖሩ የነበሩ ታላቅ ሕዝቦችን ነው (ዘኁ 13፥32-33)። እዚህ ላይ "ኒፊሊም" የሚለው የሚያመለክተው በጥንት ዘመን የነበሩ ታላላቅ ሰዎችን ነው። ጸሓፊው ቀደም ሲል እንደ እነዚህ የመሳሰሉ ዐሥር ታላላቅ ሰዎችን ስለ ጠቀሰ (ምዕ. 5)፣ እነዚህ ሰዎች ምናልባት "ከፍ ያለ ዝና ያተረፉ" የተባሉት ናቸው። በዘፀአቱ ዘመን የኒፊሊም ትሩፋን ይኖሩ እንደ ነበር በዘኁ 13፥33 ላይ ተወሥቷል፤ ቃሉ የወል መጠሪያ ነው (ማለትም "ታላላቅ ሕዝቦች") ካላልን በስተቀር፣ የሚያመለክተው በምዕ. 5 ላይ የተጠቀሱትን ታላላቅ ሰዎች ነው።

4. የጥፋት ውሃ (6፥5-9፥17)

ሀ. ውሳኔው (6፥5-12)

5-8 እነዚህ ቁጥሮች የጥፋት ውሃ የመጣበትን ምክንያት በሚገባ ይገልጻሉ። ርግጥ የጥፋት ውሃ የመጣበት ምክንያት ቀደም ሲል ከተወሣው ከሰው ልጆች ውድቀት ታሪክ ጋር በቀጥታ ይያያዛል (ምዕ. 3)። ምንም እንኳ የሰው ልጆች "መልካምና ክፉን መለየት የሚያስችል ዕውቀት" ቢያገኙም፣ ይህ ግን ምንም አልጠቀማቸውም። "መልካም" ለሆነው ሁሉ በእግዚአብሔር መታመን ይሻላቸው ነበር። ኀጢአት፣ ሐዘንና ሥቃይ ሰዎችን ብቻ የሚመለከቱ አይደሉም። ራሱ እግዚአብሔር በነገሩ እጅግ ዐዝኗል። የቁ. 8 ተግባር ኖኅ በእግዚአብሔር ዘንድ ሞገስ ያገኘበትን ምክንያት መግለጽ ነው።

9-12 የጥፋት ውሃ ታሪክ የሚጀምረው ኖኅ "ጻድቅ" ሰው መሆኑን በመግለጽ ነው። የታሪኩ ዐቢይ ዐላማ እግዚአብሔር የጥፋት ውሃን ለምን እንደ ላከ ለመግለጽ ሳይሆን እግዚአብሔር ኖኅን ለምን እንደ አዳነ ለመግለጽ ነው። የኖኅ ጽድቅ ከሰው ሁሉ "ዐመፅ" ጋር ተነጻጽሯል። መልእክቱ ፍጹም ግልጽ ነው። እግዚአብሔር ኖኅን ያዳነው "አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር ስላደረገና" የእግዚአብሔርን መንገድ "ስላላረከሰ" ነው (ከ5፥22-24 ጋር ያነጻ)። የኖኅ ታሪክ ከእግዚአብሔር ዘንድ ጸጋ የምታገኝ ሕይወት ምን ዐይነት እንደ ሆነች ትልቅ ምሳሌ ይሰጣል። የእግዚአብሔርን ቃል መታዘዝና በእምነት መግቡቱን መታመን ጸጋውን ያትረፈርፍልናል (ከዕብ 11፥7 ጋር ያነጻ)።

ለ. ኖኅ መርከብ እንዲሠራ ታዘዘ (6፥13-22)

13-15 መርከቢ እንዴትና ከምን እንደምትሠራ የተነገረው መርከቢ ምን እንደምትመስል ለመግለጽ ሳይሆን፣ ኖኅ የእግዚአብሔርን ቃል ፈጽሞ እንደ ታዘዘ ለመግለጽ ነው። የመርከቢ መጠንና ቅርጽ የተነገረው በጥቅሉ ነው።

መርከቢ የተሠራበት ቁሳቁስ ምን እንደ ሆነ በትክክል አይታወቅም። ዐመት "ከጎፈር ዕንጨት" እንደ ተሠራች ይገልጻል። ይሁንና የቃሉ ትርጉም እስከ አሁን ድረስ ለማንም ግልጽ አይደለም። ይህ ዕንጨት የተሰበጠው "በቅጥራን" ነው፤ ይህም ቃል ቢሆን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሰው በዚህ ስፍራ ብቻ ነው። መርከቢ ሣጥን የምትመስል ትልቅ መርከብ ናት። በአሁኑ ጊዜ ከዕቃ መጫኛ መለስተኛ መርከብ ጋር ልናመሳስላት እንችላለን።

16 መርከቢ ባለ ሦስት "ክፍሎች" ወይም "ጕርጆች" (ቁ. 14) መርከብ ናት፤ ማለትም ሦስት ዋና ዋና ክፍሎች አሏት፤ ለብርሃን ማስገቢያ የሚሆኑ መስኮቶችና ለመተላለፊያ የሚያገለግሉ በሮች አሏት። መርከቢቷ እዚህ ላይ ያልተነገሩ ሌሎች ነገሮችም ሊኖሯት እንደሚችል ግልጽ ነው። ከዚህ ዐጭር ገለጻ በመነሣት እንዲህ የመሰለችውን ታላቅ መርከብ የሠሩት ኖኅና ልጆቹ ብቻ ናቸው ብለን ለመደምደም አንችልም።

ሐ. ኖኅ ወደ መርከቢ እንዲገባ ታዘዘ (7፥1-5)

1-5 ኖኅ መርከብ እንዲሠራ የተሰጠውን ትእዛዝ በሚገባ ፈጸመ (6፥22)። ከዚህ ቀጥሎ የምናገኘው ትዕይንት የተጀመረው ዝናቡ ከመምጣቱ በፊት በተሰጠው ትእዛዝ ነው። ምንባቡ የሚያተኩረው ወደ መርከቢ እንዲገቡ በተዘጋጁት "ንጹሕ እንስሳት" ላይ ነው። ስለ "ንጹሕ እንስሳት" በግልጽ የተነገረው ኖኅና ቤተ ሰቡ በመርከቢ ውስጥ ሳሉ የበሉት ንጹሕ ሥጋ ብቻ መሆኑን ለመግለጽ ነው (ከዘሌ 7፥19-21 ጋር ያነጻ)። ወደ መገናኛው ድንኳን ለመግባት ነውር የሌለባቸው እንስሳት መሠዋት እንዳለባቸው ሁሉ፣ ኖኅም ወደ መርከቢ ለመግባት ከእርሱ ጋር ከእያንዳንዱ ንጹሕ እንስሳ "ሰባት ጥንድ" ይዞ መግባት ነበረበት። እነዚህ "ንጹሕ እንስሳት" ለመሥዋዕት አስፈላጊ እንደ ነበሩ በ8፥20-21 ላይ ተገልጿል።

መ. የጥፋት ውሃ (7፥6-24)

6-24 በጥፋት ውሃው ዘገባ መጀመሪያ ላይ በግልጽ ተወሥቶ የምናገኘው መርከቢን የሞሉት ፍጡራን ጉዳይ ነው። ወደ መርከቢ የሚገቡት ፍጡራን አንድ በአንድ ተነግሮ ስናይ የተደራስያኑን ዐይን ትዕግሥት ያስጨርሳሉ። ስለ ኖኅ ዕድሜ፣ ዝናቡ ስለ ጀመረበት ወርና ቀን፣ ስለ ውሃው ምንጭ፣ ወደ መርከቢ ስለ ገቡት እንስሳት ቍጥር የተነገረው ሐቅ በሙሉ ከሁሉ በፊት የሚያሳየው የኖኅን መዳን ነው። ጸሓፊው በመርከቢ ውስጥ ለመጠለል ወዳልፈለጉት ሰዎች ትኩረቱን የመለሰው፣ በምዕ. 7 መዝጊያ ላይ መርከቢ ውሃው ጐድሎ ከፍ ባለ ተራራ ላይ በደኅና ካረፈች በኋላ ነው (ቍ. 21-23)። ይህም ሆኖ ጸሓፊው ከጥፋት ውሃው ወዳልተረፉት ሰዎች ትኩረቱን የመለሰው፣ ለምን እንደ ጠፉ ለመግለጽ ስለ ፈለገ ብቻ ነው፡- "ኖኅና ከእርሱ ጋር በመርከቢ ውስጥ የነበሩት ብቻ ተረፉ" (ቍ. 23)። በመሆኑም ከጥፋት ውሃው የተረፉት "እግዚአብሔር ባዘዘው መሠረት" ያደረጉት ሰዎች እንደ ሆኑ አራት ጊዜ በተደጋጋሚ ሲነገር (7፥9፡16፣ ከቍ. 5፤ 6፥22 ጋር ያነጻ)፣ መልእክቱ እጅግ ግልጽ ነው። እግዚአብሔርን መታዘዝ የድነት መንገድ ነው።

ሠ. የጥፋት ውሃው ጕደለ (8፥1-14)

1 በመርከቢ ውስጥ ያሉት ደኅና ቢሆኑም፣ ገና አልዳኑም። ጸሓፊው ኖኅና ቤተ ሰቡ ወደ ደረቁ ምድር እስኪመለሱ ድረስ ታሪኩን አልቋጨም (ቍ 14)። በመርከቢ ውስጥ ያሉት ግን እግዚአብሔር ማዳኑን እስኪልክላቸው ድረስ መጠበቅ ነበረባቸው። በመሆኑም ታሪኩ በመርከቢ ውስጥ ማዳኑን ከሚጠብቁት ሰዎች ተሻግሮ "እግዚአብሔር ኖኅንና በመርከቢ ውስጥ ከእርሱ ጋር የነበሩትን . . . ሁሉ ዐሰበ" ወደሚለው ወሳኝ ጊዜ ይመጣል።

2-14 ጸሓፊው የእግዚአብሔርን ማዳን እንዴት እንዳዘገየው በቀላሉ ማየት ይቻላል። እግዚአብሔር በብርቱ ሥራ ተጠምዶ ማለትም ዝናቡን ሲያቆምና የጥልቁን ምንጭ ሲዘጋ ይታያል። ኖኅ ወደ ደረቁ ምድር ከመምጣቱ በፊት እነዚህ ሁሉ ነገሮች በጊዜ ውስጥ መከናወን አለባቸው፤ በመርከቢም ውስጥ ሆኖ መጠበቅ ነበረበት። ጸሓፊው እግዚአብሔር እየሠራ እንደ ሆነ ከገለጸልን በኋላ፣ ትኩረቱን በመርከቢ ውስጥ ወዳለው ወደ ኖኅ ይመልሳል፤ ኖኅ የእግዚአብሔርን ማዳን በትዕግሥት እየተጠባበቀ መሆኑን ይገልጽልናል። ከአርባ ቀን በኋላ ኖኅ በቅርቡ የሚፈጸመውን የማዳኑን ምልክት መመልከት ጀመረ። ቁራና ርግብ ላከ፤ ነገር ግን የደረቅ ምድር ምልክት አላገኘም። ኖኅ በትዕግሥት መጠበቁን ቀጠለ። የደረቅ ምድር ምልክት ሳያገኝና ርግቧም ሳትመለስ አንድ ድፍን ዓመት ጠበቀ (ከ7፥6:11 እና 8፥13-14 ጋር ያነጻ)። ይኼም ቢሆን ኖኅ ማድረግ የሚችለው የመርከቢን መስኮት ከፍቶ መመልከት ብቻ ነበር። ከመርከቢ ወጥቶ ለመሄድ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ መጠበቅ ነበረበት (ቍ 15-17)።

ከዚህ የኖኅ ታሪክ ዘገባ የምንረዳው ጻድቅና ታማኝ ትሩፋን ("ኖኅም ብቻውን ቀረ" 7፥23) የእግዚአብሔርን ማዳን በትዕግሥት ይጠባበቃሉ (ከኢሳ 8፥17-18፤ 40፥31፤ ከያዕ 5፥7-11 ጋር ያነጻ)። እንግዲህ የጥፋት ውሃ በመጨረሻው ዘመን ከሚመጣው ፍርድ ጋር ተመሳሳይ ነው (ኢሳ 8፥7-8)፤ የኖኅ መዳን ደግሞ ለታመኑት መዳን ምሳሌ ነው (ማቴ 24፥37-39)።

ረ. ኖኅ ከመርከቢ እንዲወጣ ታዘዘ (8፥15-19)

15-19 ኖኅ ከመርከቢ የወጣው በእግዚአብሔር ትእዛዝ ነው። ምንም እንኳ ዘገባው ዐጭር ቢሆንም፣ በዘፍ. 1 ላይ ከምናገኘው የሥነ ፍጥረት አብነት ጋር ተመሳሳይ ነው። ትረካው "በመጀመሪያ" ወዳየነው የሥነ ፍጥረቱ ሥራ ይመልሰናል። እዚህ ላይ ጸሓፊው ስለ ኪዳኑ ሰፊ ገለጻ ይሰጣል (8፥20-9፥17)። የእግዚአብሔር ሥነ ፍጥረት እንደ ገና ሊታደስ የቻለው በኪዳኑ መመሥረት ነው።

ኖኅ ከመርከቢ እንዲወጣ እግዚአብሔር ባደረገለት ጥሪና (8፥15-20) በአብርሃም ጥሪ መካከል አስገራሚ የጭብጥ ጕድኝት አለ (12፥1-7)። ኖኅና አብርሃም የዐዲስ ጅማሬ ምሳሌዎች ናቸው። ሁለቱንም እግዚአብሔር እንደሚባርካቸውና ኪዳኑንም ከእነርሱ ጋር እንደሚመሠርት ቃል ገብቶላቸዋል።

ሰ. መሠዊያውና ኪዳኑ (8፥20-9፥17)

8፥20-9፥17 ጸሓፊው ስለ ኖኅ መሠዊያና ኪዳን ሲናገር ነገሩ ከምዕ. 1 ጋር ያለውን ጥብቅ ዝምድና ማሳየቱን ቀጥሏል። ከዚህ መሠዊያና መሥዋዕት የተነሣ ከውድቀት በፊት የነበረው የሰው ልጆች ሁኔታ እንደ ገና አንሰራራ። የሰው ልጆች አሁንም እንደ ወደቁ ናቸው (9፥21)፤ ይሁን እንጂ በመሠዊያው ላይ በሚቀርበው መሥዋዕት አማካይነት የእግዚአብሔርን በረከት ሊያገኙ ይችላሉ። ልክ እንደ ዘፍ. 1 ሁሉ ከጥፋት ውሃ በኋላም የጸሓፊው አትኩሮት ሰው በእግዚአብሔር አምሳል በመፈጠሩ ላይ መሆኑ ልዩ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ነው (9፥6)።

ይህ ምንባብ ከሥነ ፍጥረቱ ታሪክ ጋር መዛመዱ ልዩ ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባ ሁሉ፣ በኖኅ መሠዊያና ከፀአተ እስራኤል በኋላ በሙሴ መሠዊያ መካከል ያለው ጥብቅ ዝምድናም ልዩ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል (ዘፀ. 24፥4-18)። እግዚአብሔር ከኖኅ ጋር ባደረገው ኪዳንና በሲናው ተራራ ኪዳን መካከል ያለው መመሳሰል፣ እግዚአብሔር በሲና ተራራ ላይ ያደረገው ኪዳን ዐዲስ ርምጃ ሳይሆን ወደ መጀመሪያው ተስፋ ለመመለስ ያደረገው ርምጃ ነው። ከኖኅ ጋር ያደረገው ኪዳን በረከቱን በመመለስ ረገድ ትልቅ ሚና አለው፤ ምክንያቱም ይህ ኪዳን የሚገኘው እግዚአብሔር የሰው ልጆችን ሁሉ ለመባረክ በገባው ተስፋና (1፥28) እግዚአብሔር በአብርሃም አማካይነት "በምድር የሚኖሩ ሕዝቦችን ሁሉ" ለመባረክ በገባው ተስፋ መካከል ነው (12፥1-3)።

5. የኖኅ መስከር (9፥18-29)

18-19 እነዚህ ቁጥሮች የጥፋት ውሃን ታሪክ በመደምደም ስለ ኖኅ መስከር ዐጭር መግለጫ ይሰጣሉ። በዚህ የመሸጋገሪያ ምንባብ ላይ ከነዓን ከካም ልጆች መካከል አንዱ መሆኑን ልናስተውል ይገባል። ይህም ከዚህ በኋላ ላለው ዘገባ ወሳኝ ነው (ከቁ. 22፥25 ጋር ያነጻ)።

20-21 እግዚአብሔር በፍጥረት ጊዜ ገነትን የተከለው የሰው ልጆች ደስ ይሰኙበት ዘንድ እንደ ሆነ ሁሉ፣ ኖኅም ወይን ተከለ። የሁለቱ ውጤት በእጅጉ ይመሳሰላል። ኖኅ ከወይኑ ተክል በላ፤ ዕራቁቱንም ሆነ። ይህ የሚያሳየን የሰው ልጆች ከጥፋት ውሃ ከዳኑም በኋላ በእግዚአብሔር መልካም ስጦታ ደስ መሰኘትን ሊማሩ አለመቻላቸውን ነው። እንደ አዳም ሁሉ ኖኅም ኀጢአት ሠራ፤ መዘዙም ለሚመጡት ትውልዶች ሁሉ ተረፈ። ልክ እንደ ምዕ. 3 ሁሉ የኖኅም ኀጢአት መዘዝ "በዕራቁትነቱ" ተገለጠ (ከ2፥25፤ 3፥7 ጋር ያነጻ)።

22-29 ካም የአባቱን ዕራቁትነት አየ። ሴምና ያፌት ግን የአባታቸውን ዕራቁትነት ሳያዩ ሸፈኑ። ስለ ካም ኀጢአት ብዙ የተባሉ ነገሮች ቢኖሩም፣ ጸሓፊው እዚህ ላይ የሚያነጻጽረው በአንድ በኩል ካም ያደረገውን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ሴምና ያፌት ያደረጉትን ተግባር ነው። ከዚህ በኋላ የምናገኘው መርገምና በረከት የተመሠረተው በዚህ ንጽጽር ላይ ነው። በእነዚህ ልጆች መካከል የተደረገው ንጽጽር የተጠነው ጸሓፊው በምዕ. 3 ላይ ስለ ውድቀት ካቀረበው ዘገባ አንጻር ነው። ሴምና ያፌት የአባታቸውን ራቁትነት በመሸፈናቸው፣ የአዳምንና ሔዋንን (3፥7) ራቁትነት እንደ ሸፈነው እንደ እግዚአብሔር ሆኑ (3፥21)፤ እርሱ የሰዎችን ራቁትነት ይመለከት ሸፈናቸው (ከ2፥25 ጋር ያነጻ)። ካም ይህን ምሳሌነት አልተከተለም። ተግባሩም እግዚአብሔር በሕጉ ላይ በእርሱና በሌሎች ፊት "ኀፍረተ ሥጋቸው እንዳይገለጥ" ካስጠነቀቃቸው ሰዎች ተግባር ጋር ይመሳሰላል (ከዘፀ 20፥26ን ጋር ያነጻ)። አንዳንድ ሊቃውንት ዘፀ 20፥24-26ን የሚተረጉሙት የከነዓናውያንን ሥርዐተ አምልኮ የሚከለክል ሕግ አድርገው በመሆኑ "ዕራቁተነት" የሚለው ቃል የገባው በካምና በከነዓናውያን መካከል ትስስር መኖሩን ለማሳየት ሳይሆን አይቀርም። የኖኅ ልጆች በሁለት ጎራ ተከፍለዋል፤ እንደ አዳምና ሔዋን ራቁትነታቸውን የሸፈኑና እንደ ካም ወይም ከነዓናውያን በእግዚአብሔር ፊት በራቁትነታቸው ምንም ያላፈሩ። አንደኛው ወገን ማለትም የሴም ነገድ ተባረከ (ቁ. 26)፤ ሌላው ግን ማለትም ከነዓናውያን (ካማውያን ሳይሆኑ) ተረገሙ። እነዚህ ሦስት ልጆች የሰው ልጆች ኀጢአትና አለመታዘዝ ሁለት ምላሽ ብቻ (ወይ በረከት አልያም መርገም) እንዳለው ይመሰክራሉ። አንድ ሰው የሚባረከውም ሆነ የሚረገመው ከተወለደበት ቤተ ሰብ አይደለም።

6. የኖኅ ነገድ (10፥1-32)

እዚህ ላይ ጸሓፊው የሰዎችን ስም የዘረዘረበትን ምክንያት በ10፥32 ላይ ልናገኘው እንችላለን። ስሞቹ ስለ ሕዝቦች ሰፊ እይታ እንዲኖረን ከማድረጋቸውም ባሻገር፣ ለቀረው መጽሐፉና ከዚያም በኋላ ለምናገኛቸው መጻሕፍት እንደ ዳራ ያገለግላሉ። በዚህ ዝርዝር ላይ ሰባ ነገዶች/ሕዝቦች ተጠቅሰዋል፤ ይህም ሁሉንም ነገዶች/ሕዝቦች ለማመልከት የገባ ነው። በሌላ አነጋገር "ሕዝቦች ሁሉ" የሚለው የተገኘው ከኖኅ ሦስት ልጆች ነው።

ምንም እንኳ ጸሓፊው አሁን ይበልጥ እያተኮረ የመጣው "በአብርሃም ዘርና በእስራኤል ልጆች" ላይ ቢሆንም፣ በቅድሚያ ግን እግዚአብሔር አብርሃምን ስለ መረጠበት ምክንያት ጽኑ መሠረት ይጥልልናል፦ "በዘሩ" አማካይነት "በምድር የሚኖሩ ሕዝቦችን ሁሉ" ለመባረክ ነው (12፥3)። ጸሓፊው በዘፍጥረት መዝጊያ ላይ የአብርሃም "ዘሮች" ቁጥር "ሰባ" መሆኑን ለተደራሲያኑ የገለጸው ያለ ምክንያት አይደለም (46፥27፤ ከዘፀ 1፥5 ጋር ያነጻ)። ከአብርሃም በፊት የሕዝቦች ቁጥር "ሰባ" ነበር። በመጽሐፉ መዝጊያ ላይ ከአብርሃም በኋላ የአብርሃም ዘሮች ቁጥር "ሰባ" ነበር። ይህ ከሕዝቦች የተወሰደው አብርሃም የሕዝቦችን ቁጥር ሞላ።

ሀ. የኖኅ ልጆች (10፥1)

1 ምዕራፍ 10 በሁለቱም ጫፍ ማለትም ሲጀምርና ሲጨርስ የተቀነበበው በስሞች ዝርዝርና ("በኖኅ ልጆች" ቁ. 1፥32) በምልክት ("ከጥፋት ውሃ በኋላ"፣ ቁ. 1፥32) ነው። ጸሓፊው በምዕ. 10 የዘረዘራቸው ስሞች ከዐውደ ምንባቡ ውጪ እንዳይተረጐሙ በእጅጉ ተጨንቋል። ጸሓፊው ለዐውደ ምንባቡ ያን ያህል የተጨነቀው ወደ ፊት ደረጃ በደረጃ የሚተርካቸው ነገሮች እንዳሉትና ይህንንም ተደራሲያኑ እንዳይስቱት ከወዲሁ ለማስገንዘብ ነው።

ለ. የያፌት ልጆች (10፥2-5)

2-5 የስም ዝርዝሩ የሚጀምረው "በደሴቶች፣ በየምድራቸው የሚኖሩ" (ከቁ. 5 ጋር ያነጻ) ተደርገው ከሚቁጠሩ ሕዝቦች ነው፤ ይህም የጸሓፊው መልክአ ምድራዊ ድንበር እስከ የት ድረስ እንደ ሆነ ጠቋሚ ነው። እነርሱም ከካምና (ከስነዓንና) ከሴም ሕዝቦች በተቃራኒ እንደ ሦስተኛ ዓለም ነው የተቈጠሩት። በኋላ አትኩሮቱ በእግዚአብሔር አጥናፈ ዐለማዊ መንግሥት ላይ ሲሆን፣ ዕቅዱ ሕዝቦችን ሁሉ እንደሚያካትት ለማሳየት እነዚህ ሕዝቦች እንደ ገና ብቅ ይላሉ (መዝ 72፥8፡10)።

ጸሓፊው የያፌት ልጆችን ስም ሲዘረዝር አንድ በግልጽ የሚታይ መርገፍ (ምሳሌ፣ አምሳል፣ ንድፍ) እናስተውላለን። በአጠቃላይ ዐሥራ አራት ስሞች ተዘርዝረዋል። ሰባቱ የያፌት ልጆች ስም ሲሆን ሰባቱ ደግሞ የልጅ ልጆች ስም ነው። ጸሓፊው የያፌት ሰባት ልጆች ከወለዷቸው መካከል የዐምስቱን የልጆቻቸውን ስም አልጠቀሰም (ማጎግ፣ ማዴ፣ ቶቤል፣ ምሳሕ፣ ቴራስ)። የጠቀሰው የጋሜርንና የያዋንን ልጆች ስም ብቻ ነው። ሐሳቡ የሁሉንም ስም መዘርዘር ሳይሆን "ሙሉ" ዝርዝር ማቅረብ ነው፤ ይኸውም "ሰባት" ቁጥር ሙሉ ቁጥር በመሆኑ ነው።


ሐ. የካም ልጆች (10፥6-20)

6-12 የካም ልጆች ስም ዝርዝር የሚጀምረው እንደ ያፌት ልጆች ስም ዝርዝር ነው፤ የሚጀምረውም የካምን አራት ልጆች ስም በመጥቀስ ነው። ከዚያም እንደ ያፌት ዝርዝር ሁሉ ቅድሚያ የተሰጠው ለልጅ ልጆች ነው። ይሁንና ወደ ተከታዩ ልጅ (ምድራይም) ከመሄዱ በፊት የልጅ ልጅ ልጆች (የራዕማ ልጆች) ስም ተዘርዝሯል። በመጨረሻ የምናገኘው "የሰባት ልጆችን" ስም ማለትም ሙሉ ዝርዝር ነው። ከዚህ በኋላ የምናገኘው የናምሩድንና የከተሞቹን ብዝበዛ ነው፤ ይህም የባቢሎንን ከተማ ከወዲሁ ያስተዋውቀናል የ11፥1-9 ርእስ ነው።

የአሦር ከባቢሎን ጋር ሆነ ተብሎ መጐዳኘት ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ነው። ምክንያቱም አሦር መጐዳኘት የነበረበት ከሴም ጋር ሆኖ ሳለ እዚህ ላይ የተጐዳኘው ግን ከባቢሎን ጋር ነው። በዚህም ማንኛውንም ከተማ ከባቢሎን ከተማ ጋር የማጐዳኘት ና የማመሳሰሉ መንገድ ተጠረገ (ኢሳ 13-14፤ ራእ 17፥5)። ነቢዩ ሚክያስ አሦርን የናምሩድ ምድር በማለት ጠርቶታል (ሚክ. 5፥6)።

13-20 የካም ትውልድ ሐረግ ከምድራይም ልጆች ዝርዝር ጋር ተጠቅሷል፤ እዚህም ላይ የምናገኘው ሰባት ስሞችን ነው። ይህም "የሰባት" መርገፉ ቁጥር የመጨረሻው ዝርዝር ነው። ከዚህ በኋላ የምናገኘው የስም ዝርዝር ንድፍ ቁጥር ላይ የተመሠረተ አይደለም። ከዚህ በኋላ የስሞቹን ዝርዝር ውጦ የምናገኘው "የቤተ ሰቡ ቁጥር ሰባ" ነበር የሚለው ንድፍ ነው። ስሞቹ በሰባት በሰባት እየተቀናጁ ያልተዘረዘሩት (ቁ 15-29) ሁሉን ዐቀፍ ገጽታ

ሕዝቦች የት ቦታ እንደ ሰፈሩ



እንዲኖራቸው ነው። ምክንያቱም በአሪት ዘፍጥረትና በሌሎቹ የአሪት መጻሕፍት ውስጥ ከነዓናውያንና የሴም ልጆች ላቅ ያለ ሚና ይጫወታሉ። ከሌሎቹ ተለይቶ የከነዓን ወሰን ብቻ ከየት እስከ የት ድረስ እንደ ሆነ በግልጽ የተጠቀሰው፣ ይህ አካባቢ የመጽሐፉ ዐላማ ማእከል በመሆኑ ነው። ምንም እንኳ "በዚያን ጊዜ ከነዓናውያን በዚሁ ምድር" ቢኖሩም ለአብርሃም ተስፋ የተሰጠው ይህ ምድር ነበር (12፥6)።

መ. የሴም ልጆች (10፥21-31)

21-31 የሴምና የያፌት ስም ሲጠቀስ የካም ስም አለመጠቀሱ በ9:26-27 ላይ ኖኅ ሴምንና ያፌትን ሲባርክ የነበረውን ሁኔታ ያስታውሳል፤ በዚያ ክፍል የከነዓንም ስም አልተጠቀሰም። "የዔቦር ልጆች" ስም መጠቀሱ ገና ወደ ፊት የምናገኘውን የትውልድ ሐረግ ያስተጋባል፤ የአብርሃም ልደት ከዚህ የተገኘ ነው (11፥10-26)።

የሴም ትውልዶች ዝርዝርም በተመረጡት ላይ ብቻ ያተኰረ ነው፤ የዔቦርን ሁለት ልጆች ስም ከጠቀሰ በኋላ ወደ ሁለተኛው ልጅ ወደ ዮቅጣን ትውልዶች መጥቶ ይህን መሥመር ተከትሎ ይሄዳል። ስለ ባቢሎን ግንብ መገንባት ከተነገረም በኋላ (11፥1-9)፣ ሌላ የሴም ትውልዶች ዝርዝር እንደ ገና ተነግሯል፤ በዚያ ክፍል የትውልዱ ዝርዝር የሚቀጥለው የዔቦር የመጀመሪያ ልጅ በሆነው በፋሌቅ እስከ አብርሃም ድረስ ነው (11፥10-26)። ስለዚህ በሴም ትውልዶች መካከል በባቢሎን ከተማ ግራና ቀኝ በሁለት ተከፍለው እናያለን። ይህም የሆነው የዔቦር ሁለት ልጆችን የፋሌቅንና የዮቅጣንን መሥመር ተከትሎ ነው። አንደኛው ትውልድ ወደ ባቢሎን ግንብ ሲመራን፣ ሌላው ደግሞ ወደ አብርሃም ቤተ ሰብ ይመራናል። በቁ 25 ላይ የዚህ መከፈል ፍንጭ ተወሥኗል። "ምድር" የሚለው ቃል የሚያሳየው "የምድሪቱን ነዋሪዎች" ነው። እንግዲህ ምድሪቱ የተከፈለችው በቋንቋቸው መደበላለቅ ብቻ አይደለም (11፥1)፤ ነገር ግን ከሴም ልጆች ጉያ ሁለት ታላላቅ ትውልዶች የየራሳቸውን መንገድ ተከትለው ሄዱ፦ የባቢሎንን ከተማ በመገንባት ለራሳቸው ስም (ሴም) መጠሪያ የሚያኖሩና (11፥4) አብርሃምን በመጥራት እግዚአብሔር ራሱ ስም (ሴም) የሚያኖርላቸው።

ሠ. መዝጊያ (10፥32)

32 የምዕራፍ 10 የመጨረሻ ቁጥር የሕዝቦችን መከፈል ጭብጥ ያወጣል፤ ይህም ከዚህ በኋላ ስለሚተረከው የባቢሎን ከተማ ታሪክ እንደ መንደርደሪያ ያገለግላል። በምዕ. 10 ላይ "በመልክአ ምድራዊና በሥነ ልሳናዊ" ረገድ የተወሣው ነገር በምዕ. 11 ላይ "በነገረ መለኮታዊ" ረገድ ሲወሣ እናያለን። ይኸውም እግዚአብሔር በባቢሎን ላይ በመፍረድ ሕዝቦችን መበተኑ ነው።

ሠ. የባቢሎን ከተማ (11፥1-9)

1-9 እስከ አሁን ድረስ አንድ የነበረው ሕዝብ በዔቦር ሁለት ልጆች ይከፈላል (10፥25)። አንደኛው ትውልድ መጨረሻው ባቢሎን ሆነ፤ ሌላው ደግሞ በተስፋዱቱ ምድር ሆነ። የመጀመሪያው ትዕይንት የተከፈተው ወደ "ምሥራቅ" ወደ "ሰናዖር ሜዳ" በተደረገው ጉዞ ነው። በመሆኑም የታሪኩ ሁነት የጀመረው ከባቢሎን በስተ ምዕራብ ነው። አዳምና ሔዋን እንዲሁም ቃየን ከእግዚአብሔር ፊት ከተባረሩ በኋላ የሄዱት "ወደ ምሥራቅ" አቅጣጫ ነው (3፥24፤ 4፥16)። ሎጥ ከአብርሃም ሲለይ የሄደው ወደ ምሥራቅ ነው (13፥10-12)። አዳም (የሰው ልጅ) ወደ ምሥራቅ ሲሄድ፣ ከበረከቱ ምድር (ከዔድንና ከተስፋዱቱ ምድር) ተለይቶ ተስፋው ሁሉ ወደሚጠፋበት ምድር (ባቢሎንና ሰዶም) እያመራ ነበር።

እዚህ ላይ "ስም" (ሴም) የሚለው ቃል ቍልፍ ሚና አለው። አንደኛው፣ ከተማዋን የሚገነቡት ሰዎች ለራሳቸው "ስም" (ሴም) ለማኖር ፈለጉ። ሁለተኛው፣ የታሪኩ መዝጊያ የከተማዋን "ስም" (ሴም) አውሥቶ ይጨርሳል፤ ይህም ምፀታዊ በሆነ መንገድ ስሟን (ባቢሎን) ከቋንቋቸው መደበላለቅ ጋር ያያይዘዋል። በተናቸው የሚለው ሌላው ቍልፍ ቃል ነው። ከተማዋ የተገነባችው ነዋሪዎቿ በምድር ላይ እንዳይበተኑ ነበር። በታሪኩ መዝጊያ ላይ ግን እግዚአብሔር ራሱ "በምድር ላይ በተናቸው"። ይህ እውነታ በታሪኩ መዝጊያ ላይ ሁለት ጊዜ ተወሥቷል። "በምድር ሁሉ" የሚለው ሐረግ ሦስተኛ ቍልፍ ቃል ነው። ሰዎቹ ከተማዋን በምሥራቅ ለመገንባት የመጡት ከመላው ምድር (አመት፣ ዓለም)

ነበር። ከተማዋን የገነቡት በምድር ሁሉ እንዳይበተኑ ነበር። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ሐሳባቸውን ገልብጦ “በመላው ዓለም” በታተናቸው።

ገና በዘፍጥረት የመጀመሪያ ምዕራፎች የጸሓፊው አትኩሮት እግዚአብሔር “መልካም” የሆነውን ሁሉ ለሰው ልጆች በመስጠት እነርሱን ለመባረክ በነበረው ዕቅድና የሰው ልጆች በእግዚአብሔር ታምነው እርሱ በሰጣቸው “መልካም” ነገር ደስ እየተሰኙ ለመኖር አለመቻላቸው ላይ ነው። ውድቀታቸውም “መልካም” የሆነውን ሁሉ በራሳቸው ለማግኘት መሞከራቸው ነው። ጸሓፊው ስለ እግዚአብሔር በረከት የሚሰጠውን ገለጻ ያማከለው በምድሪቱ ስጦታ ላይ ነው (1፥28)። መልካሚቱ ምድር የበረከት ስፍራ ናት። ይህችን ምድር ትቶ ሌላ ምድር መፈለግ የእግዚአብሔርን መልካም ስጦታ ያሳጣል። ስጦታው “በዔድን በስተ ምሥራቅ” መኖር ነውና።

ረ. የሴም ትውልድ (11፥10-26)

10-26 እንደ አዳም ሁሉ (ምዕ. 5) ይህ የሴም ዐሥር ትውልዶች ስም ዝርዝር “የታመኑትን” (ከኖኅ እስከ አብርሃም) ሲዘረዝር “ያልታመኑትን” (10፥26-30) ትቷቸዋል። በምዕ. 5 ከአዳም እስከ ኖኅ ድረስ ያሉት ዐሥር አባቶች ዝርዝር ለሴቲቱ ተስፋ በተሰጠው “ዘር” (3፥15) እና ከጥፋት ውሃ በተረፉት የኖኅ ዘሮች መካከል ትስስር እንዲኖር አድርጓል (7፥23)። ዝርዝሩ “የተስፋውን ትውልድ” ብቻ በግልጽ ሲያወጣ የቃየንን ትውልድ ግን ትቷል (4፥17-22)፤ የተተዉትም በጥፋት ውሃ የተደመሰሱት የከተማዪቱና (ቍ. 17) የሥልጣኔው (ቍ. 20-24) መሥራቾች ናቸው።

በቍጥር 10-26 እንደሚያሳየው፣ እግዚአብሔር የሴቲቱን ዘር በተመለከተ የሰጠው ተስፋ በቋንቋቸው መደበላለቅና ሕዝቦቹም በባቢሎን መበተናቸው ሊሰናከል አይችልም። ምንም እንኳ የኖኅ ዘር በባቢሎን ቢበተንም፣ እግዚአብሔር ግን ከኖኅ እስከ አብርሃም ድረስ የዐሥር ታላላቅ ሰዎችን ትውልድ ጠበቀ።



ይህ የጥንታዊ ባቢሎን የማሳያ ግንቦች አንዱ ዓይነት ነው። በዚህ ልዩ በሆነ ግንብ አናት ላይ የማርዱክ፣ በ600 ቅ.ክ የባቢሎን መሪ የሆነው አምላክ፣ ቤተ መቅደስ ተቀምጧል። እነዚህ ግንቦች ኋላ የባቢሎን ግንብ ተነሣሪ ነበሩ።

፪. አብርሃም (11፥27-25፥11)

ሀ. የአብርሃም ትውልድ (11፥27-32)

27-32 ከአብርሃም ታሪክ በፊት የምናገኘው የትውልድ ሐረግ በሕይወት ዘመኑ የተከሠቱ ነገሮችን ለመረዳት መልካም ዳራ ነው። እስከ አሁን ድረስ ጸሓፊው በየዐበይት ግለሰቦች ትረካው መካከል ዐሥር ስሞችን ሲዘረዝር ነበር፤ይህ ዐሥር ዝርዝሩ ግን ስምንት ስሞችን ብቻ ይዟል። ይህም፣ ዘጠነኛው ስም በተለይም ዐሥረኛው ስም ማን ነው የሚል ጥያቄ ያስነሣል። ትረካው እንደሚያሳየው፣ ዘጠነኛውና ዐሥረኛው ስሞች የአብርሃም ሁለቱ ልጆች “የእስማኤልና” (16፥15) “የይስሐቅ” (21፥3) ስም ነው። እንግዲህ የትውልድ ሐረጉ መግቢያ የይስሐቅን መወለድ ማለትም ዐሥረኛ ውን ስም ያስተጋባል።

በየስም ዝርዝሮቹ መካከል አብርሃምንና ሎጥን ጨምሮ ታራምና ቤተ ሰቡ የከለዳውያንን ዑር ምድር ትተው በከነዓን ምድር በኩል እስከ ካራን ድረስ ስለ መሄዳቸው ዐጭር መግለጫ ተሰጥቷል። እስከ 12፥1 ድረስ ስለ አብርሃም መጠራት ምንም አልተነገረም፤ ይህም ታራም ከሞተ በኋላ መሆኑ ነው (ቍ. 32ለ)። በመጀመሪያ ስናየው አብርሃም አገሩን ትቶ እንዲሄድ የታዘዘው በከላዳውያን ዑር ምድር እያለ ሳይሆን አባቱ ታራም ከሞተ በኋላ በካራን እያለ ይመስላል። ይህም በ12፥4-5 ትረካ ይበልጥ ተጠክናሯል፤ ምንባቡ አብርሃም ለእግዚአብሔር ጥሪ የሰጠውን ምላሽና “የወጣውም ከካራን” እንደ ሆነ በግልጽ ዘግቧል፤ የከለዳውያን ዑር ምድር አልተጠቀሰም። ይሁንና ጸሓፊው ትረካውን በተለየ መንገድ እንድናየው ፈልጓል።

በቍጥር 27-32 ላይ እንደ ተገለጸው አብርሃም የተወለደው በካራን ሳይሆን በከለዳውያን ዑር ምድር ነው። በመሆኑም አብርሃም የተወለደባትን ምድር (ዐመት፣ “አገርህን” 12፥1) ትቶ እንዲሄድ ትእዛዝ የተሰጠው በከለዳውያን ዑር ምድር ነው ማለት ይቻላል። አብርሃም የተጠራው በዑር ምድር እያለ ከሆነ፣ ትረካውን በትንቢታቱ መጻሕፍት ውስጥ ከምናገኛቸው ጭብጦች ጋር ከማጐዳኘቱም በላይ የአብርሃምን መጠራት (12፥1-3) ከባቢሎን ከተማ መበተን ጋር ያስተሳስረዋል (11፥1-9)። በዚህ ዐይነት አብርሃም ወደ ፊት ወደ ምርኮ ለሚጋዙትና ወደ ተስፋዪቱ ምድር ለመመለስ በእምነት ለሚጠባበቁት ምሳሌ ሆኗል (ከሚክ 7፥18-20 ጋር ያነጻ)።

በአብርሃምና በይስሐቅ ትረካዎች መግቢያ መካከል ጉልሕ ምስስሎች ይታያሉ (25፥19-26)። የአብርሃም ወንድም ሐራን የሞተው አባቱ ከመሞቱ በፊት ነው፤ የይስሐቅ ወንድም እስማኤል የሞተው ደግሞ ወንድሞቹ ከመሞታቸው በፊት ነው (25፥18ለ)። አብርሃም ሚስት አገባ፤ ነገር ግን መካን ነበረች። ይስሐቅ ሚስት አገባ፤ ነገር ግን መካን ነበረች (25፥20-21)። ሁለቱም ትረካዎች በወንድማማቾች መካከል ስለ ተደረገው ትግል የሚያወጣ ክፍል አላቸው። አብርሃም ከመወለዱ ጀምሮ ሎጥ ዐብሮ አደጉ ነበር፤ ያዕቆብ ከመወለዱ ጀምሮ ዔሳው ዐብሮ አደጉ ነበር (25፥22-24)። በመካከላቸው ከነበረው ትግል የተነሣ አብርሃም ከሎጥ ተለየ (13፥9፡ 11፡ 14)፤ ያዕቆብ ደግሞ ከዔሳው ተለየ (25፥23)።

ለ. የአብርሃም መጠራት (12፥1-9)

1-5 እንደ ኖኅ ሁሉ የአብርሃምም ታሪክ የዐዲስ ጅማሬ ታሪክ ነው፤ ከዚህም በተጨማሪ እግዚአብሔር “በምድር የሚኖሩ ሕዝቦችን ሁሉ” ለመባረክ የነበረውን የመጀመሪያ ሐሳቡን ያስተጋባል (ከ1፥28 ጋር ያነጻ)። በአብርሃምና በትውልዱ ትረካ ውስጥ የእግዚአብሔር “በረከት” ተደጋግሞ መወሣቱ ጉልቶ ወጥቷል (12፥1-3፤ 13፥15-16፤ 15፥5:18፤ ወዘተ)። እዚህ ላይ አብርሃም የሚወክለው ዐዲሱን አዳምን ነው፤ የአብርሃም ዘር የሚወክለው ደግሞ ሁለተኛውን አዳም ማለትም ዐዲሱን ሰው ነው። እርሱን “የሚባርኩትን”፣ እግዚአብሔር ይባርካቸዋል፤ እርሱን “የሚረግሙትን”፣ እግዚአብሔር ይረግማቸዋል። በአንድ ወቅት “መልካምና ክፉን በሚያሳውቀው ዛፍ” (2፥17)፣ በኋላም በመርከቢቱ (7፥23) የተመሰለው “የሕይወትና የበረከት” መንገድ አሁን የተመሰለው ከአብርሃምና ከዘሩ ጋር አንድ በመሆን ነው።

ከዚህ ቀጥሎ የምናገኘው ትረካ ከሚያነሣቸው ዐበይት ጭብጦች መካከል አንዱ የአብርሃም ዘር ማንነት ነው። በመጽሐፉ መዝጊያ ላይ (49፥8-12) ወደ ፊት የሚነሣው የአብርሃም ዘር በጭላንጭል ጠቀስ ተደርጎ ታልፏል። ይህ ወደ ፊት የሚመጣውና መንገሥ የሚገባው ዘር “ከይሁዳ ነገድ የሆነው አንበሳ” (49፥9) “ሕዝቦች ሁሉ ይታዘዙታል” (49፥10)።

6-9 አብርሃም ወደ ከነዓን ምድር ስለ መግባቱ የተነገረው ታሪክ የተመረጠ ነው። ሦስት ቦታዎች ብቻ ተጠቅሰዋል፤ እነርሱም በቤቴልና በጋይ መካከል የምትገኘው ሴኬምና ኔጌብ ናቸው። እነዚህ ሦስት ቦታዎች ያዕቆብ ከካራን ወደ ከነዓን ሲመለስ የጎበኛ ቸው (ምዕ. 34-35) እንዲሁም ኢያሱ ድል አድርጎ ስለ ያዘው ምድር በሚያወሣው ትረካ ውስጥ የሚገኙ ቦታዎች ናቸው።

ሐ. አብርሃም በግብፅ (12፥10-13፥4)

12፥10-13፥4 በቍጥር 10 ላይ አብርሃም ወደ ግብፅ ለመሰደድ የተገደደው በረኀብ ምክንያት እንደ ሆነ ተገልጿል። በ12፥1-3 ላይ እግዚአብሔር የሰጠውን ተስፋ የሚገዳደሩ ነገሮች ለመጀመሪያ ጊዜ በዚህ ታሪክ ላይ ተወሥተዋል። ከዚህ በኋላ በተከታታይ በምናገኛ ቸው ትረካዎች ውስጥ “ዘርህን አበዛዋለሁ”፣ “በምድር የሚኖሩ ሕዝቦች በአንተ አማካይነት ይባረካሉ” ወይም “ምድሪቱን እሰጥሃለሁ” የሚሉት የተስፋ ቃሎች የትረካው ገጸ ባሕርያት በሚወስዱት ርምጃ አደጋ ሲገጥማቸው እናያለን። የተስፋ ቃሉ

የማይፈጸም ይመስላል። ይሁን እንጂ በዚህ ሁሉ ውስጥ እግዚአብሔር በቃሉ ሲታመንና የተስፋ ቃሉንም ሲጠብቅ ይታያል። ምንም እንኳ ሰዎች ቢወድቁም እግዚአብሔር ግን የተስፋ ቃሉን መፈጸም ይችላል።

ስለ አብርሃም መጻተኛነት የተነገረው ታሪክ እግዚአብሔር እስራኤልን ከግብፅ ስለ መታደጉ ከተነገረው ታሪክ ጋር በብዙ ረገድ ይጐዳኛል (ዘፍ 41- ዘፀ 12)። ሁለቱም ምንባቦች ተመሳሳይ መልእክት አላቸው። ያለፈው ታሪክ ዐልፋል ተብሎ መዘጋት የለበትም። ካለፈው ታሪክ ስለ ወደፊቱ የምንማራቸው ብዙ ነገሮች አሉ። ይኸውም አብርሃም በግብፅ ያሳለፈው ሕይወት ከጊዜ በኋላ እስራኤል በግብፅ ላሳለፈችው ከወዲሁ ምልክት ነው (ሁለቱም ወደ ግብፅ የተሰደዱት በረኃቡ ምክንያት ነው)። ከዚህ ታሪክ በስተ ጀርባ የታመነው አፍቃሪ አምላክ አለ። በአብርሃም ሕይወት ፈቃዱን የፈጸመ አምላክ፣ ዛሬም ሆነ ነገ በሕዝቡ ሕይወት ፈቃዱን ይፈጽማል። ከዚህ ጉድኝት አንጻር አብርሃም በግብፅና (ምዕ. 12) በጌራራ (ምዕ. 20) ስላሳለፈው የመጻተኛነት ሕይወት የተነገረውን ታሪክ ይስሐቅ በጌራራ (ምዕ. 26) ካሳለፈው ጋር ተመሳሳይነት እንዳለው መረዳት አለብን። ምስስሉ የተስተዋለው ቀደም ብሎ ቢሆንም፤ ብዙ ጊዜ ጐልቶ አይታይም።

መ. የሎጥ ታሪክ (13፥5-19፥38)

1. አብርሃምና ሎጥ (13፥5-18)

5-18 እዚህ ላይ የምናገኘው ታሪክ የተገራው "በትግሉ" ጭብጥና ከዚህም የተነሣ በተከሠተው "መለያየት" (ቍ. 9:11:14) ነው። በስተ መጨረሻ እግዚአብሔር ለአብርሃም የሰጠውን ተስፋ እናገኛለን። ለአብርሃም የተሰጠው የመጀመሪያ ተስፋ በአብርሃም መለየት እንደ ተቀደመ ሁሉ (10፥32፤12፥1)፣ ሁለተኛውም ተስፋ የተሰጠው ከቅርብ ዘመዱ ከሎጥ ጋር በተለያየ ጊዜ ነው። ለአብርሃም የተሰጠውን የመጨረሻ ተስፋ የምናገኘው ከአንድ ልጁ ከወራሹ ይስሐቅ ለመለየት ከወሰነ በኋላ ነው(22፥15-18)።

አብርሃም ከሎጥ ጋር ለመለየት የወሰደው ርምጃ የተስፋ ቃሉን አደጋ ላይ የሚጥለውን ጭብጥ ያስታውሳል። አብርሃም የተስፋዱቱን ምድር የአሞናውያንና የሞዓባውን አባት ለሆነው ለሎጥ ለመስጠት ዳድቶት ነበር (19፥37-38)። እነዚህ ሕዝቦች በእስራኤል ታሪክ ሁሉ (ዘዳ 23፥3-6፤ ዕዝ 9፥1) የተስፋው ቃል እንዳይፈጸም ቀንደኛ ጠላቶች ነበሩ። የተስፋው ቃል በሞዓውያኑ አባት እጅ ለጥቂት ወድቆ ነበር። ሎጥ ግን ወደ "ምሥራቅ" ለመሄድ "መረጠ"፤ ስለዚህ አብርሃም በምድሪቱ ተቀመጠ። አብርሃም ዳተኛ ቢሆንም፣ የእግዚአብሔር የተስፋ ቃል ግን ጸና።

ሎጥ የመረጠው ምድር "እንደ እግዚአብሔር ገነት በግብፅ ምድር አምላል ነበረ"፤ ነገሩን በዘፍጥረት ዐውድ ውስጥ ካየነው አሥንታዊ ገለጻ ነው። ይሁን እንጂ "እስከ ዞዓር ድረስ" የሚለው መልክአ ምድራዊ መለያ የሎጥ ምርጫ አስከፊ መዘዝ እንዳለው ያመለክታል። ሎጥ ከሰዶምና ከገሞራ ጥፋት ለማምለጥ የሸሸው ወደዚህ ስፍራ ነበርና (19፥22)። ሎጥ "በስተ ምሥራቅ" የሚገኘውን ምድር መምረጡ መዓት እንደሚመጣበት ይጠቁማል።

የሎጥን ከአብርሃም መለየትና የአብርሃምን (10፥32) ከባቢሎን ሕዝቦች መለየት (11፥1-9) ከሶዶም ሕዝቦች ፍርድ ጋር የሚያስተሳስራቸው ሁነኛ ነገር አለ (19፥1-29)። በምዕራፍ 13 እና በሰዶም መደምሰስ መካከል ያለውን ትስስር (ምዕ. 19) በቍ. 10ለ እና በቍ. 12ለ-13 ላይ ማጤን ይቻላል።

ስለ ሕዝቦች መበተን የተነገረው ታሪክ የተደመደመው "አሕዛብም ከጥፋት ውሃ በኋላ በምድር ላይ ከእነዚህ ተከፋፈሉ [ማለትም ተለያዩ]" በሚለው ነው (10፥32ሀ)። ከዚያም ስለ ባቢሎን መበተን የተነገረው ታሪክ የሚጀምረው ሕዝቡ "ከምሥራቅ ተነሥተው" ሄዱ በሚለው ነው (11፥2)። ልክ እንዲሁ ሎጥ ከአብርሃም ሲለይ የሄደው "ወደ ምሥራቅ" ነው (13፥11)። በባቢሎን ሕዝቦች ከተለያዩ በኋላ ታሪኩ የሚጀምረው አብርሃም በከነዓን ምድር ሲጓዝ ነው፤ አብርሃም ምድሪቱን እንደሚወርስ ከእግዚአብሔር ተስፋ ተቀበለ፤ ከዚያም ለእግዚአብሔር ተስፋ ምላሽ መሠዊያ ሠራ (12፥1-9)። እንዲሁም ሎጥ ከሰዶም ከተለየ በኋላ አብርሃም በከነዓን ምድር ተጓዘ፤ እንደ ገና ለሁለተኛ ጊዜ ምድሪቱን እንደሚወርስ ተስፋ ተቀበለ፤ በምላሹም መሠዊያ ሠራ።

2. አብርሃምና ሕዝቦች (14፥1-24)

1-11 ላይ ላዩን ስናየው በምዕ. 13 እና 14 መካከል ያለው ትስስር እምብዛም ትኩረት የሚሻ አይመስልም። ታሪኩ ድንገት የሚጀምረው "አምራፌል የሰናዖር ንጉሥ . . . በነበሩበት ዘመን" በሚለው የዘመን መለያ ነው። ይህም ስፍራው ድንገት ከኬብሮን (13፥18) ወደ ዓለም ዐቀፉ ክልልና ወደ አራቱ ነገሥታት ጦርነት እንደ ተዛወረ ያሳያል። እዚህም ላይ እንደምናየው ሁለቱን ታሪኮች የሚያስተሳስረው ሎጥ ነው። የሎጥ መያዝ ከተነገረ በኋላ ታሪኩ ወደ ኬብሮን ይመለሳል (14፥13ለ)። በዚህ ጊዜ አብርሃም ወደ ታሪኩ ማእከል ይመጣል (ቍ. 14-17)። በቍ. 24 ላይ "መምሬ" መጠቀሱ በምዕ. 13 መዝጊያ ላይ ወዳለው ትዕይንት ይመልሰናል።

አብርሃም በኬብሮን ሲያመልከው የነበረው "አምላክ" (13፥18) "የሰማይና የምድር ፈጣሪ" ነው (14፥22)፤ አራቱን የምሥራቅ ነገሥታት ለአብርሃም የሰጠው እርሱ ነው። በምድሪቱ በሰላም ለመኖር የቻለ አንድ ሰው ቢኖር፣ ከዚህ ዓለም ነገሥታት አንዳች ያልጠየቀውና ያልተመኘው አብርሃም ብቻ ነው (ቍ. 22-23)። በ12፥3 ላይ እንደ ተተነበየው ከአብርሃም ጋር የወገኑ (ቍ. 13ሀ) ለእርሱ የተሰጠውን በረከት ይካፈላሉ (ቍ. 24ሀ)፤ ነገር ግን ሎጥ እንዳደረገው (13፥12) ከእርሱ የተለዩ የሰዶምንና የገሞራን ጽዋ ይጠጣሉ (14፥11-12)።

ሰናዖርና ባቢሎን አንድ እንደ ሆኑ አስቀድሞ ተገልጿል (10፥10፤11፥2:9)። ጸሓፊው በታሪኩ ላይ የሰናዖርን ንጉሥ ስም በመጀመሪያ የጠቀሰው ሆነ ብሎ ነው፤ በዚህ ዐይነት ታሪኩን በምዕ. 10 (ቍ. 10) እና 11 (ቍ. 2) ላይ ከተወሣው "የባቢሎን" ጭብጥ ጋር ያስተሳስረዋል። በሌላ ስፍራ ከአራቱ ነገሥታት መካከል ሁል ጊዜ ስሙ በመጀመሪያ የተጠቀሰው ኮሎዶጎምር ነው (ቍ. 4:5:9:17)።

ምንም እንኳ የሰዶምና የገሞራ ነገሥታት ተደምስሰው ከመወገዳቸው በስተቀር ስለ ጦርነቱ የተሰጠው መረጃ እጅግ ጥቂት ቢሆንም፣ ታሪኩ የታጨቀው በመልክአ ምድራዊና በፖለቲካዊ ዘገባዎች ነው። ከዚህ ታሪካዊ ዘገባ የምናገኘው መረጃ ቢኖር፣ የተዘገቡት ድርጊቶች በይዘታቸው ዓለም ዐቀፋዊ መሆናቸውን ነው፤ ታሪኩ የተፈጸመው በሰዶምና በገሞራ ነገሥታት ላይ በደረሰው አሳዛኝ ሽንፈት ነው።

12 የትረካው አተያይ ከአራቱ የምሥራቅ ነገሥታት ጋር ሲደረግ ከነበረው ጦርነት ወደ ሎጥ ዕጣ ፈንታ ሲዞር ይታያል። ሎጥን ለዚህ ዕድል የዳረገው "በሰዶም መኖሩ" ነው፤ ይህም በምድሪቱ ያለውን በረከትና (12፥1-3፤13፥14-17) ራሳቸውን ከአብርሃም የሚለዩ ሁሉ ዕጣ ፈንታቸው ምን እንደ ሆነ ያስታውሳቸዋል።

የሎጥ ዕጣ ፈንታ አንድ መሠረታዊ ትምህርት ትቶለት ዐልፏል፤ ይኸውም ሎጥ በሕይወት ለመኖር የአብርሃም ምልጃ ያስፈልገው ነበር (18፥23-32)። አብርሃም ሁለት ጊዜ ለሎጥ ማልዶለታል፤ በዚህ ክፍል ሎጥን ከባቢሎን ጦርነት ታደገው፤ በኋላ ደግሞ (ምዕ. 18-19) ከሰዶም ጥፋት ታደገው (18፥23-32፤ 19፥29)። እዚህ ላይ የምናገኘው የአብርሃም ምስል በ20፥7 ላይ "ነቢይ ነውና ይጸልይልሃል፤ አንተም ትድናለህ" ተብሎ ከተጠቀሰው ጋር ተመሳሳይ ነው።

13-16 ትዕይንቱ ወደ አብርሃምና በኬብሮን ወደ ነበሩት ወደ ሦስቱ ወዳጆቹ ይመለሳል፤ በዚህ ዐጭር ትዕይንት እንደ ተገለጸው አብርሃም ምርጥ ሰራዊት አሰባስቦ አራቱን ነገሥታት ድል ካደረገ በኋላ የቀሩትን ምርኮኞች ይዞ ወደ ሎጥ ተመለሰ።

17-20 አብርሃም ከጦርነቱ ከተመለሰ በኋላ ሁለት ንጉሦች የንጉሥ ሸለቆ እየተባለ በሚጠራ ስፍራ ተገናኙት። ድንገትም ስለ መልከ ጼዴቅ መነገር ተጀመረ፤ ብዙም ሳይቈይ ወዲያው ተፈጸመ፤ ከዚህ በኋላ ስለ እርሱ ሲነገርም ሆነ ማን እንደ ሆነ ሲተረክ አናገኝም። ስለ ሰዶም ንጉሥ በሚያወሣው ታሪክ መካከል የአብርሃምና የመልክ ጼዴቅ መገናኘት ጣልቃ መግባቱ ከሰዶም ንጉሥ ጋር ለነበራቸው ግንኙነት እንደ ዳራ ያገለግላል። በመሆኑም አብርሃም ለሳሌም ንጉሥና ለሰዶም ንጉሥ በሰጣቸው ምላሽ መካከል ልዩነት እንዳለ ተነጻጽሯል። አንዱ አዎንታዊ ሲሆን፣ ሌላው ግን አሉታዊ ነው። ከዚህም የተነሣ ሁለቱ ንጉሦች ያመጡለት ስጦታ የተለያየ ነበር። የሳሌም ንጉሥ "እንጀራና የወይን ጠጅ" አመጣለት፤ ተግባሩ ክህነታዊ ከመሆኑም በላይ ጠላቶቹን በእጁ የጣለለት "ሰማይንና ምድርን የፈጠረ ልዑል እግዚአብሔር" መሆኑን የሚመሰክር ነው። የሰዶም ንጉሥ አብርሃም በምርኮ ያገኘውን ሀብት ሁሉ እንዲወስድ ፈቀደለት (ቍ. 21)። አብርሃም ለመልክ ጼዴቅ የሰጠው ምላሽ ለስጦታውም ሆነ ለክህነቱ የተገባ ምላሽ ነው፦ አብርሃም ዐሥራት አወጣ (ዘኍ 18፥21 ይመ)።

21-24 የሰዶም ንጉሥ አብርሃም በጦርነቱ ያገኘውን "ንብረት" በሙሉ እንዲወስድ ፈቀደለት። አብርሃም ከሰው ከሚገኝ ስጦታ ምንም ጕዳይ የለውም። አብርሃም ብድራቱን የሚቀበለው ሰማይንና

ምድርን ከፈጠረ ከልዑል አምላክ ነው (15፥1፡14ለ ጋር ያነጻ)። ምንም እንኳ አብርሃም ከሰዶም ንጉሥ የቀረበለትን ሰጦታ አልወሰድም ቢልም፣ ብላቴኖቹ የበሉት ግን ድርሻቸውን መሆኑን ገልጿል (ከዘዳ. 20፥14ለ ጋር ያነጻ)። ከዚህም በተጨማሪ አብርሃም ሦስቱ ወዳጆቹ ከምርኮው ድርሻ እንዳላቸው ተናግሯል። አብርሃም ግን ከሰዶም ንጉሥ አንዳች ለመውሰድ አይሻም (ከዘዳ. 20፥17 ጋር ያነጻ)፤ ምክንያቱም አብርሃም የእምነት ሰው ነው።

3. አብርሃምና ኪዳኑ (15፥1-21)

1-4 እግዚአብሔር ለአብርሃም መልእክቱን ያደረሰበት መንገድ በትንቢታቱ መጻሕፍት ውስጥ ከምናገኘው ጋር ፍጹም ተመሳሳይ ነው (ሩ. 1፡4፤ ከኤር 34፥12 ጋር ያነጻ)። እንደ ነቢዩ በለዓም ሁሉ (ዘኍ. 24፥4፡16) አብርሃም የእግዚአብሔርን ቃል "በራእይ" አየ። አብርሃም ለመጀመሪያ ጊዜ ለእግዚአብሔር መልስ ሲሰጥ እናያለን። ከዚህ በፊት እግዚአብሔር ሲያናግረው ይታዘዛል እንጂ መልሶ ሲያናግረው አናይም። አብርሃም የተሰጠው ተስፋ እንዴት ሊፈጸም እንደሚችል ጠየቀ። እንደ እውነቱ ከሆነ አብርሃም ብዙ ጥያቄዎችን አቅርቧል፤ ይህም የእምነቱን ጽኑነት ያሳያል (ሩ. 6)።

የአብርሃም ጥያቄ በምዕራፉ ውስጥ ለምናገኘው ማእከላዊ ርእስ እንደ መንደርደሪያ ነው። የምዕራፉ ማእከላዊ ርእስ የእግዚአብሔር የተስፋ ቃል ሳይፈጸም የዘገየው ለምን እንደ ሆነ ፍንጭ ይሰጣል። እዚህ ላይ የምናገኘው አንገብጋቢ ሐሳብ ለኤርምያስም ዕንቆቅልሽ ነበር። የእግዚአብሔር ሕዝቦች በተስፋው በረከት ደስ በመሰኘት ፈንታ ራሳቸውን ያገኙት ወደ ባቢሎን ምርኮ ለመጓዝ ሲዘጋጅ ነው። የተስፋው ቃል ትርጉመ ቢስ የሆነ ይመስላል (ከኤር 25፥11 ጋር ያነጻ)። በኤርምያስ ትንቢት ላይ እንደምናየው ግን ተስፋው በረከት እንዳለው ፍጹም ርግጥ ነው። የምርኮው ዘመን ገደብ አለው (ቍ. 12)። የአብርሃም ጭንቀት በየዘመኑ ካሉ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ጭንቀት ጋር ይመሳሰላል። እርሱም የተስፋውን ፍጻሜ በእምነት መጠባበቅ ነበረበት፤ በእምነቱ ጻድቅ በመሆኑ (ቍ. 6)፤ የተስፋው ቃል በሌሎች ዘመን እንደሚፈጸም ተረድቷል (ቍ. 15-16፤ ከዕብ 11፥13 ጋር ያነጻ)።

ታዲያ አብርሃም የሚፈራው ምንድን ነው? በእግዚአብሔር ዘንድ ያለው "ብድራት" ምንድን ነው? በምዕ. 14 ላይ የነበረው ጦርነት አሁንም ለአብርሃም ሥጋት ነው? በምዕ. 15 እና በምዕ. 14 መካከል ዐቢይ ልዩነት በመኖሩ ("ከዚህም በኋላ"፤ ከ22፥1፤ 39፥7፤ 40፥1 ጋር ያነጻ) እግዚአብሔር ለአብርሃም የተናገረው ቃል ምናልባት ከምዕ. 14 ዐውድ ጋር ላይዛመድ ይችላል። ምናልባት አብርሃም "ዘርህን እንደ ምድር ትቢያ አበዛዋለሁ" የሚለው ተስፋ የመጨረሻ ውጤቱ ምን እንደ ሆነ መፍራት ሳይጀምር አይቀርም (13፥16፤ ከቍ. 2 ጋር ያነጻ)።

አብርሃም ያነሣው ጥያቄ አንድ የሚያሳየው ነገር አለ። ይኸውም እግዚአብሔር "አትፍራ" (ቍ. 1) በማለት ያጽናናው፣ አብርሃም ሊፈራ እንደሚችል ስለሚያውቅ ነው። የአብርሃም ጥያቄ የሚያሳየው በውስጡ ያለውን ፍርሀት ብቻ ሳይሆን፣ እግዚአብሔር በተደጋጋሚ የሰጠው ማረጋገጫ ወደዚሁ አቅጣጫ የሚያመላክት ነበር (ቍ. 4)። አብርሃም በዙሪያው ከሚያያቸው ነገሮች የተነሣ እግዚአብሔር በቃሉ የታመነ ለመሆኑ እምብዛም ተስፋ ሰጭ ነገር አላገኘም። አብርሃም ለእግዚአብሔር የተናገረው ቃል መጠራጠሩን ይገልጻል (17፥18)። በሌላ በኩል ደግሞ አብርሃም ዝም ካለ፣ ተግባሩ የእምነት ሰው መሆኑን ይመሰክራል።

5 "የሰማይ" ከዋክብትን ቍጥር እንዲመለከት የቀረበለት ግብዣ ራሱ አብርሃም በ14፥22 ላይ የተናገረውን ቃል ያስታውሳል። በዚያ ክፍል የብድራቱ ተስፋ የተመሠረተው በሰማይና በምድር ፈጣሪ ላይ ብቻ እንደ ሆነ ገልጿል። ማንም ሊቈጥራቸው የማይችለውን ከዋክብት የፈጠረው እግዚአብሔር ከሆነ፣ ለአብርሃምም ልክ እንደዚሁ ብዙ ዘሮች ሊሰጠው ይችላል (ከ22፥17፤ 26፥4፤ ከዘዳ 32፥13፤ ከዘዳ 1፥10፤ 28፥62 ጋር ያነጻ)። በቀደመው ዘመን እግዚአብሔር ያሳየው ታማኝነት በሚመጣውም ዘመን ለአብርሃም እምነት መሠረቱ ነው።

6 እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር ኪዳን ሊገባ ነው። ይህም በሚመጡት ዘመናት እግዚአብሔር ከአብርሃምና ከዘሮቹ (ቍ. 7-21) ጋር ለሚያደርገው ግንኙነት መሠረት ነው። ቍ. 6 ዘገባውን ቁልጭ አድርጎ አቅርቧል። አብርሃም በእግዚአብሔር ስላመነ ጻድቅ ሆነ። በውስጡ ጽድቅ የፈጠረለት "ኪዳኑ" አይደለም። ይልቁንም ጻድቅ ተደርጎ የተቈጠረው "በእምነቱ" አማካይነት ነው።

7-16 እነዚህ ቍጥሮች በእግዚአብሔርና በአብራም መካከል የተመሠረተውን ኪዳን ይተርካሉ። በመግቢያው ላይ የምናገኛቸ ቃሎች በሲና ተራራ ላይ ከተደረገው ኪዳን ጋር በእጅጉ ተመሳሳይ ናቸው (ዘፀ 20፥2)። "ከከለዳውያን ዑር" የሚለው ሐረግ ከ11፥28 እና 31 ጋር ይመሳከራል። ይህም የአሁኑ ኪዳን የተመሠረተው በቀደመው ዘመን እግዚአብሔር "ከባቢሎን" በመታደግ በፈጸመው ተግባር ላይ እንደ ሆነ ያሳያል (ከዘፀ 20፥2 ጋር ያነጻ)። እግዚአብሔር በሲና ተራራ ላይ በታላቅ አሳትና ጨለማ ውስጥ መገለጡ (ዘፀ 19፥18፤ 20፥18፤ ዘዳ 4፥11) የአብርሃምን ራእይ እንዲያስተጋባ የተፈለገ ይመስላል (ቍ. 12፡17)። እግዚአብሔር ለአብራም ከተናገረው ቃል እንደምንረዳው በአብራም ኪዳንና በሲናው ኪዳን መካከል ትስስር እንዳለ ግልጽ የሆነው የአብራም ዘሮች ለአራት መቶ ዓመት በባርነት ከተገዙ በኋላ ነጻ እንደሚወጡ በመነገሩ ነው።

17 የእንስሳት ሥጋ ከፋፍሎ በመካከሉ ተራምዶ መሄድ በጥንት ዘመን የተለመደ የውል ስምምነት መግለጫ ነው (ከኤር 34፥18 ጋር ያነጻ)። ትርጉሙ ግልጽ ባይሆንም፣ የዘፍጥረት ጸሓፊ ግን ሥርዐቱን አስረድቷል፡- "በዚያ ዕለት እግዚአብሔር ለአብራም እንዲህ ሲል ኪዳን ገባለት"።

አብራም ያባረራቸው አሞሮች (ቍ. 11) በእንድ በኩል የአብርሃም ዘሮች የሚጠብቃቸውን አይቀሬ ዕጣ ፈንታ ሲያመለክት፣ በሌላ በኩል ደግሞ የእግዚአብሔርን ጥበቃና ክብካቤ ያመለክታል (ከማቴ 24፥28 ጋር ያነጻ)። በድኑን ለመብላት ስለ ተሰበሰቡት አሞሮች ከተነገረው በኋላ ስለ ፀሓይ መግባትና (ዘፍ 15፥12፤ ከማቴ 24፥29 ጋር ያነጻ) ወደ ፊት ስለሚገለጠው ማዳን ተስፋ ተሰጥቶ እናገኛለን (ዘፍ 15፥14፤ ከማቴ 24፥30 ጋር ያነጻ)።

18-21 ጸሓፊው የተስፋዱቱን ምድር ጕዳይ እንደ ገና ወደ ትረካው በማምጣት የኪዳኑ ምድር ወሰን ከየት እስከ የት ድረስ እንደ ሆነ ይነግረናል። የተስፋዱቱ ምድር ወሰን ከዔድን ገነት ወሰን ጋር ተመሳሳይ ይመስላል (ከ2፥10-14 ጋር ያነጻ)።

4. ሐጋር (16፥1-16)

1-6 በዚህ ክፍል የአጋር ትውልድ ስፍራ ("ግብፃዊት") መጠቀሱ ይህን ታሪክ ከ15፥18-21 ጋር ያስተሳስረዋል። በታሪኩ ላይ ግብፃዊቷ አጋር ሦራን "ትንቃት" እንደ ነበር ሁለት ጊዜ ተወሥቷል (ከ12፥3 ጋር ያነጻ)። ከዚህም የተነሣ አጋር ወደ "ምድረ በዳ" (ቍ. 7) ተሰደደች፤ ለሦራ እስክትገዛለት ድረስ በዚያ መቀመጥ ነበረባት። እግዚአብሔር አጋርን የሚባርከው ለሦራ ስትገዛላት ብቻ ነው (ቍ. 10፤ ከ17፥2፡ 20 ጋር ያነጻ)።

ሦራ ለመካንነቷ መፍትሔ ለመስጠት የወሰደችው ርምጃ በዘመኑ ማኅበራዊ ልማድ መሠረት ተቀባይነት አለው። አገልጋይዋን ለአብርሃም በመስጠት ወራሽ እንድትወልድለት አደረገች። ይሁንና የሦራ ዕቅድ አሁንም የሚያሳየን የሰው ልጆች የእግዚአብሔርን በረከት በራሳቸው መንገድ ለማግኘት የሚያደርጉትን ከንቱ ጥረት ነው። ምንም እንኳ ሦራ ውጤት ብታገኝበትም፣ ዕቅዷ ግን ከእግዚአብሔር ሐሳብ ጋር አይጣጣምም (17፥15-19፤ ከ11፥1-9፤ 12፥10-20፤ 13፥1-12፤ 14፥21-24 ጋር ያነጻ)።

7-12 ስፍራው ወደ ምድረ በዳ ማለትም "ወደ ሱር በሚወስደው የውሃ ምንጭ አጠገብ" ሲዞር እናያለን። አጋር ወደ ግብፅ እየተመለሰች ነው (25፥18 ይመ.)። የእግዚአብሔር መልአክ ሰላምታ ያቀረበላት በጥያቄ ነበር (የ3፥9 ማብ ይመ)። ከዚያም በሐዘን ለተኰራመተችው አገልጋይ የበረከት ተስፋ ሰጣት። ከእርሷ የሚወለደው ልጅ ስሙ "እስማኤል" እንደሚባል ነገራት፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር "ችግርሽን ሰምቷል" (እስማኤል የሚለውና "ሰምቷል" የሚለው የወጡት ከአንድ የዕብራይስጥ ቃል ነው፤ ቃላቱ ተመሳሳይ ድምፀት እንዳላቸው ልብ ይሏል)። በምዕራፉ ውስጥ የምናገኘው ቍልፍ ቃል "ችግርሽን" የሚለው ነው፤ በቍ. 11 ላይ የገባው እንደ ስም ሲሆን በቍ. 6 ላይ እና በቍ. 9 ላይ የገባው ደግሞ እንደ ግሥ ነው ("ባሠቃየቻት ተገዥነት")። አጋር በሦራ ሥቃይ ደርሶባታል (ቍ. 6)፤ በዚያ ሥቃይ ሥር ተገዝታ እንድትኖር ተነግሯታል (ቍ. 9)፤ እግዚአብሔር ግን ሥቃይዋን ሰማ (ቍ. 11)።

ለአጋር የተሰጠው "በረከት" ሁለተኛው ግማሽ የልጇን ዕጣ ፈንታ ቁልጭ አድርጎ አያሳይም፡- "እርሱም እንደ ዱር አህያ" ይሆናል። "አህያ" እና "ፋራን" በሚሉት ቃሎች መካከል ተመሳሳይ ድምፀት አለ። ፋራን የእስማኤል ነገዶች መኖሪያ ስፍራ ነው። የዚህን በረከት ትርጉም ምናልባት የምናገኘው በ21፥21 ላይ ነው፤ በዚህ ክፍል እንደ ተነገረው እስማኤል "በፋራን ምድረ በዳ" ይኖር ነበር። እስማኤል ከሥልጣኔ አድማስ ውጭ ማለትም በምድረ በዳ ይኖር ነበር።

13-16 የታሪኩ የመጨረሻ ክፍል የሚያወሣው፣ አጋር ለእግዚአብሔር ስላወጣችለት ስምና ስለ እስማኤል መወለድ ነው። ሁለቱ ሁነቶች ዐብረው የሚሄዱ ናቸው፤ ይኸውም የልጁ መወለድ በዚህ ክፍል ለእግዚአብሔር የተሰጠው ስም ትክክለኛ መሆኑ ያረጋግጣል፦ “የሚያይ አምላክ”።

5. አብርሃም፣ ሣራና እስማኤል (17፥1-27)

1^{ሀ} እስማኤል ሲወለድ አብራም የሰማንያ ስድስት ዓመት ሰው ነበር (16፥16)። በምዕራፍ 17 መግቢያና መዝጊያ ላይ ዕድሜው ዘጠና ዘጠኝ እንደ ሆነ ተገልጿል። በመሆኑም ዕድሜው ታሪኩን እንደ ማቀፊያ ያገለግላል።

1^{ለ}-2 እግዚአብሔር ለአብራም የተናገረው የመጀመሪያው ቃል ለተቀረው የምዕራፉ ክፍል ትርጓሜ መሠረት ነው። ከዚህም በተጨማሪ በምዕራፉ ውስጥ የተከናወኑት ሁነቶች በእግዚአብሔርና በአብራም መካከል ለተደረገው ኪዳን ምልክት ናቸው። ኪዳኑ እጅግ ብዙ ዘሮች እስጥሃለሁ የሚል ተስፋ ነው።

እዚህ ላይ ለእግዚአብሔር የተሰጠው ስም “ያህዌ” የሚለው ነው፤ እርሱም የሲናው ኪዳን አምላክ ነው (ዘፀ 3፥15)። ይሁንና በትረካው ውስጥ እግዚአብሔር ራሱን ለአብራም የገለጠለት “ሁሉን የሚገዛ አምላክ ” ብሎ ነው። አብርሃም የሚያመልከው የኪዳኑን አምላክ “ያህዌን” ቢሆንም፣ እርሱን የሚያውቀው ግን እንደ “ሁሉን የሚገዛ አምላክ” ነው፤ (ዘፀ 6፥3 ይመ.)። እግዚአብሔር ማንነቱን ከገለጠለት በኋላ ስለ ኪዳኑ ምንነትና ስለ አብራም ኀላፊነት ዐጭር መግለጫ ይሰጣል፦ “በፊቴ ተመላለስ፤ ነቀፋም አይኑርብህ”። ተስፋው ደግሞ፦ “ዘርህንም እጅግ አበዛለሁ”። በ15፥18 ላይ እንደምናነበው እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር ኪዳን “መሥርቶ” አልነበረም? ከአብርሃም ጋር ለሁለተኛ ጊዜ ኪዳን የመሠረተው ለምንድን ነው? እንደ እውነቱ ከሆነ እነዚህ ሁለት ኪዳኖች እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር የመሠረተው ኪዳን ሁለት የተለያየ ገጽታ ያላቸው ናቸው። አንደኛው ትኩረቱ በተስፋዱቱ ምድር ላይ ሲሆን (15፥18-21)፣ ሁለተኛው ደግሞ ዘርህን አበዛዋለሁ በሚለው ላይ ነው (17፥2)።

3^{ሀ} ስለ አብራም ምላሽ የተሰጠው ገለጻም ዐጭር ነው። አብራም “በግንባሩ መሬት ላይ ተደፋ”፤ የአክብሮት ምልክት ነው። የአብራምን ምላሽ እግዚአብሔር ለሁለተኛ ጊዜ ከተናገረው ቃል ጋር ስናነጻጽረው (ቁ. 17)፣ አብራም በግንባሩ መሬት ላይ መደፋት ብቻ ላይሆን ሲሠቅም እናየዋለን። አብራም እግዚአብሔር ዘሩን እጅግ እንደሚያበዛው ሲሰማ ምላሹ አክብሮትና መገዛት ነበር። ይሁንና እግዚአብሔር ዕቅዱን የሚፈጽመው እንዴት እንደ ሆነ ሲሰማ የአክብሮቱ ስሜት ሣቅ የተቀላቀለበት ነበር።

3ለ-16 ሁለተኛው የእግዚአብሔር ንግግር፣ “እግዚአብሔርም እንዲህ አለው” በሚለው ሐረግ በሦስት ክፍል ተከፍሏል። እያንዳንዱ ክፍል ከኪዳኑ ተጋቢዎች መካከል በአንዱ ላይ ያተኮራል (በእግዚአብሔር፣ በአብራምና በሦራ)። የእያንዳንዱ ክፍል ዐቢይ ሐሳብ እንዲታወስ የተደረገው በየክፍሎቹ ውስጥ በሚገኘው ምልክት ነው። ምልክቱም የአብራም ስም መለወጥ፣ የወንዶች ልጆች ሁሉ መገረዝና የሦራ ስም መለወጥ ናቸው። በእግዚአብሔር በኩል ኪዳኑ ሁለት ተስፋዎችን ይዟል፦ ዘሩን ማብዛትና ለዘላለም የታመነ መሆን። ከዚህ ኪዳን ወገን የሆኑ የአብርሃም ዘሮች ህልውናቸው የተመሠረተው በእግዚአብሔር ላይ ብቻ ነው። ዘሩን እንደሚያበዛው የተነገረው ተስፋ እንዲታወስ የተደረገው የአብራም ስም “አብርሃም” ተብሎ በመለወጡ ነው፤ ትርጕሙም “የብዙ ሕዝቦች አባት” ማለት ነው።

በቁጥር 6 እና በቁ. 2 ላይ አበዛለሁ የሚለው ቃል በ1፥28 ላይ የሰው ልጆች ሁሉ መባረካቸውን ያስታውሰናል። በ9፥1 ላይ በድጋሚ መወሣቱ ደግሞ እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር የገባው ኪዳን ሰዎችን ሁሉ ለመባረክ የሚጠቀምበት መንገድ እንደ ሆነ ያሳየናል።

በቁጥር 6ለ ላይ ዐዲስ ሐሳብ ታክሏል፦ “ነገሥታትም ከአንተ ይወጣሉ”። ይህ የሚያስተጋባው በሳሙኤልና በነገሥት መጻሕፍት ላይ የተነገረላቸውን የአብርሃም ዘሮች ብቻ ሳይሆን፣ ይልቁንም በአብርሃም ዘር አማካይነት የሚፈጸመው በረከት፣ የዚህም በረከት ውጤት በሆነውና ከይሁዳ ቤት በሚወጣው ንጉሥ መካከል ትስስር እንዳለ ፍንጭ ይሰጠናል (ዘፍ 49፥8-12፤ ዘኁ 24፥7-9)። በረከቱ የሚፈጸመው በአንድ ንጉሥ ነው የሚለው ሐሳብ ዐዲስ አይደለም (ከ14፥18-19 ጋር ያነጻ)፤ ይሁንና ይህ ንጉሥ የሚወጣው ከአብርሃም ዘር ነው የሚለው ዐዲስ ነው።

የቁጥር 7-8 አትኩሮት የተመራውዘው “ለዘላለም” በሚለው ቃል ላይ ነው። ተስፋ የተሰጠው ኪዳን ዘላለማዊ ነው፤ ስለ ምድሪቱም የተነገረው ተስፋ “ዘላለማዊ” ነው። በእነዚህ ቁጥሮች ላይ የምናገኛቸው ተስፋዎች አስቀድሞ የተሰጡ ናቸው (ከ13፥14-15፤ 15፥18-21 ጋር ያነጻ)፤ ይሁንና እዚህ ላይ አጽንዖት የተሰጠው የተስፋዎቹ ዘላለማዊነት ነው፤ በእርግጥ ምድሪቱ ለዘላለም እንደ ተሰጠቻቸው ተጠቁሟል (13፥15)፤ ይሁን እንጂ በምዕ. 15 ላይ ኪዳኑ ሲሰጥ “ዘላለማዊ” ስለ መሆኑ አልተነገረም። እንግዲህ እግዚአብሔር በኪዳኑ ውስጥ ያለውን ሚና በድጋሚ የተናገረው ለዘላለም የታመነ አምላክ መሆኑን ለመግለጽ ነው።

አብርሃም በኪዳኑ ውስጥ ያለው ኀላፊነት ለኪዳኑ መታዘዝ ነው። ይህም “በመካከላችሁ ያለ ወንድ ሁሉ ይገረዝ” የሚለውን ያካትታል። ኪዳኑን መጠበቅ ማለት ግርዘትን በታማኝነት መፈጸም ማለት ነው፤ ኪዳኑን ማፍረስ ማለት ደግሞ ያልተገረዘ መሆን ማለት ነው። ነገር ግን የኪዳኑ ትእዛዝ የግርዘትን ሥርዐት መፈጸም ብቻ አይደለም፤ ይህ “የኪዳኑ ምልክት” ብቻ ነው።

ሦራ በኪዳኑ ውስጥ ያላት ኀላፊነት የሕዝቦች እናት መሆን ነው። “የሕዝቦችም ነገሥታት ከእርሷ ይወጣሉ”። እንደ አብርሃም ሁሉ ሣራ የሚለው ዐዲሱ ስሟ በኪዳኑ ውስጥ ላላት ኀላፊነት ምልክት ነው። በዕብራይስጥ ቋንቋ “ሣራ” ማለት “ልዕልት” ማለት ነው።

17-18 የአብርሃም በግንባሩ መሬት ላይ መደፋትና መሣቅ ያልተጠበቀ ምላሽ ነው። የራሱ የአብርሃም ቃል ከሣቁ በስተ ጀርባ ሐሳቡ ምን እንደ ሆነ ያሳየናል። በ18፥12 ላይ ሣራም ለእግዚአብሔር ተስፋ ምላሿ ሣቅ ቢሆንም፣ ሣቋ ግን በእግዚአብሔር ተገሥጿል። እዚህ ላይ አብርሃም አለመገሠጹ ሣቁ እምነት ያጣ ሰው መሆኑን ሳይሆን የእምነቱን ውስንነት ነው የሚያሳየው። አብርሃም በእግዚአብሔር ተስፋ ላይ ያለው ታማኝነት እንዲያድግ ከፈለገ፣ እምነቱ ማደግ አለበት። በአብርሃም ሣቅ ላይ የምናየው አንድ ግልጽ ነገር ቢኖር፣ ሣቅ የሚለውን ለመግለጽ የገባው የዕብራይስጡ ቃል ይስሐቅ የሚለውን ስም ያስተጋባል።

የአብርሃም ምላሽ ምፀቱ ግልጽ ነው። ሣቁ የተስፋው ቃል በመጨረሻ ላይ የሚፈጸመው በይስሐቅ እንደ ሆነ ቋሚ የቃል ምልክት ሆነበት። ከዚህ በኋላ በይስሐቅ መወለድ ዙሪያ የምናገኛቸው ትረካዎች በሙሉ ማለትም በእያንዳንዱ ዐቢይ ክፍል ውስጥ ቁልፉ ቃል “መሣቅ” ነው። ሣራ “ሣቀች” (18፥12)፤ የሎጥ አማቾች ሣቁ (19፥14)፤ ሣራ ይስሐቅን መውለዷን የሰሙ ሁሉ “ሣቁ” (21፥6)፤ የአጋር ልጅ በይስሐቅ ሣቀበት (21፥9፤ ዐመት “አሾፈበት”)። በመጨረሻም ራሱ ይስሐቅ በእግዚአብሔር እንዳልታመነ (26፥7) የተገለጸው የፍልስጥኤሙ ንጉሥ ሲሥቅ (26፥8ለ ዐመት “ሲዳራት”) ባየው ጊዜ ነው። እንግዲህ የእግዚአብሔር ኀይል፣ የሰዎች እምነት ውስንነትም በዚህ በሰዎቹ እጅግ አሻሚ ድርጊት ማለትም በሣቅ ተወክሎ እናያለን።

19-22 ሦስተኛው የእግዚአብሔር ንግግር ኪዳኑን አራዝሞ ይስሐቅን እንዲካተት አድርጓል። ይስሐቅ የሚወለደው ከሣራ ሲሆን የአጋርን ልጅ እስማኤልን ከኪዳኑ ውጭ ያደርገዋል። በመሆኑም ይስሐቅ የኪዳኑ ተስፋ ተካፋይ ለመሆን ወደሚችልበት ደረጃ ከፍ ሲልና ለአብርሃምም በተሰጠው ተስፋ መሠረት “ዘርህ” የተባለው ማን እንደ ሆነ ግልጽ ሲሆን እናያለን። የኪዳኑ ወራሽ የሆኑት የአብርሃም ዘሮች በሣራ በኩል የሚወለዱትና በ26፥3ለ ላይ የተጠቀሱት ናቸው፤ እነርሱም የይስሐቅ ዘሮች ናቸው።

ምንም እንኳ እስማኤል ለአብርሃም በተሰጠው ኪዳን ውስጥ ባይካተትም፣ እስማኤልና ዘሮቹ አሁንም መኖር ያለባቸው በእግዚአብሔር በረከት ሥር ነው። እንደ እውነቱ ከሆነ እግዚአብሔር እስማኤልን ሲባርከው በ1፥28 ላይ የሰውን ልጆች በሙሉ እንደ ባረከና በ12፥2 ላይ አብርሃምን እንደ ባረከ በድጋሚ መግለጹ ነው። የይስሐቅ “ዘሮች” የዐሥራ ሁለት ነገዶች ታላቅ ሕዝብ እንደሚሆኑ ሁሉ (49፥1-27)፣ የእስማኤልም “ዘሮች” ከእግዚአብሔር በረከት የተነሣ የዐሥራ ሁለት አለቆች ታላቅ ሕዝብ ይሆናሉ (25፥13-15)።

23 የአብርሃም የመጨረሻው ምላሽ ለኪዳኑ መታዘዙን ያሳያል፤ እግዚአብሔር ባዘዘው መሠረት በቤቱ ውስጥ የተወለዱትን ወንዶች ልጆች በሙሉ ገረዛቸው። የአብርሃም መታዘዝ በቁ. 1 ላይ የተሰጠውን ብርቱ ትእዛዝ ያንጸባርቃል፤ ትእዛዙ “በፊቴ ተመላለስ፤ ነቀፋም አይኑርብህ” የሚል ነበር። “ነቀፋ አይኑርብህ” የሚለው ቃል በዘፍጥረት ውስጥ የሚገኘው በዚህና በ6፥9 (ኖኅ) ላይ ብቻ ነው። “አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር አደረገ” የሚለው

ግን ብዙ ጊዜ ይገኛል (5፥22፡24፤ 6፥9፤ 17፥1፤ 24፥40፤ 48፥15)። እንግዲህ አብርሃምና ኖኅ ኪዳኑን የታዘዙ ሰዎች ነበሩ፤ በዚህም ምክንያት በእግዚአብሔር ፊት "ነቀፋ አልነበረባቸውም"።

24-27 የአብርሃምና የእስማኤል ዕድሜ በቃል ኪዳኑ ውስጥ መካተትን ያመለክታል (የቁ. 1 ማብ. ይመ) ባጭሩ የመጨረሻው ቃል አብርሃም ለቃል ኪዳኑ በታማኝነት የተሞላ ምላሽ መስጠቱን ይጠቅሳል።

6. ሦስቱ እንግዶች (18፥1-33)

ሀ. የአብርሃም እንግዳ ተቀባይነት (18፥1-8)

1[ሀ] ታሪኩ የሚጀምረው ምዕ. 17 በጀመረበት መንገድ ነው፤ "እግዚአብሔር ለአብርሃም ተገለጠለት"። የዚህ አባባል አስፈላጊነቱ በቀላሉ መታየት የለበትም፤ ምክንያቱም ሦስቱ ሰዎች እነማን እንደ ሆኑ፣ አብርሃምን የጐበኙት እነማን እንደ ሆኑና ተልእኳቸውም ምን እንደ ሆነ ያብራራልናል። ምንም እንኳ በግልጽ ባይነገርም ሦስቱ ሰዎች የሚወክሉት የእግዚአብሔርን መገለጥ ነው።

"በመምሬ ትልልቅ ዛፎች አቅራቢያ ተቀምጦ ሳለ" የሚለው ሐረግ በዚህ ወቅት አብርሃም የት እንደ ነበር ስፍራውን ይነግረናል (ከ13፥18 ጋር ያነጻ)። በምዕራፍ 18 ውስጥ የአብርሃም ማንነት እስከ ቁ. 6 ድረስ ባይታወቅም (በቁ. 1 ላይ አመት ስሙን ቢጠቅስም በዕብራይስጡ ግን "እርሱ" የሚል ቃል ነው የተጠቀሰው)፣ የምዕ. 18 መግቢያ ከምዕ. 17 መዝጊያና ከአብርሃምና ከቤተ ሰቡ መገረዝ ታሪክ ጋር በጥብቅ ተሳስሯል።

የመጨረሻው ቁጥር (ቁ. 33) ይኸውም እግዚአብሔር ንግግሩን ከጨረሰ በኋላ "ሄደ" የሚለው ዘገባ የሚያሳየን መላውን ምዕራፍ መረዳት ያለብን እግዚአብሔር ለአብርሃም ከተገለጠበት ዐውድ አንጻር ነው (17፥1 እና 22፤ 35፥9 እና 13)።

1[ለ]**-8** በአብርሃም ድንኳን አጠገብ ሦስት ሰዎች መታየታቸውን በተመለከተ የቀረበው ዘገባ ብዙ ውስብስብ ነገሮች አሉበት፤ አንደኛ ው፣ በሦስቱ ሰዎችና በእግዚአብሔር መገለጥ መካከል ያለው ዝምድና (ቁ. 1ሀ) ምን እንደ ሆነ በግልጽ አልተጠቀሰም። ሁለተኛ ው፣ በቁ. 3 (ነጠላ ተባዕታይ) እና በቁ. 4-9 (ብዙ ተባዕታይ) ላይ የምናየው ግሳዊ ቅርጽ ከነጠላ ወደ ብዙ የተለወጠው ሆነ ተብሎ ሳይሆን አይቀርም። በመጨረሻም በምዕ. 18 ላይ በምናገኘው ውስብስብ ዘገባና በምዕ. 19 ላይ በምናገኘው አቻ ውስብስብ ዘገባ መካከል ያለው ዝምድና ምንድን ነው የሚለውን ጥያቄ ነው። በምዕራፍ 19 ላይ "በሁለቱ መላእክት" (ወይም መልእክተኞች፤ 19፥1) እና በእግዚአብሔር ("ያህዌ") መካከል ያለው ዝምድና አልተገለጸም (ለምሳሌ፣ ሁለቱ ሰዎች [19፥12] ሰዶምንም እንደሚያጠፏት ለሎጥ ነግረውት ነበር [19፥13]፤ ነገር ግን ምንባቡ እግዚአብሔር በሰዶምና በገሞራ ላይ ከሰማይ የሚያቃጥል ዲንና እሳት አዘነበባቸው ይላል [19፥24])። ሎጥን ሊገናኙት ስለ መጡትም ሲነገር ግሶቹና ተውላጠ ስሞቹ በሙሉ በብዙ ተባዕታይ ቁጥር ነው የተነገሩት (19፥2)፤ የታሪኩ ዘገባ እስኪፈጸም ድረስ ነገሩ የተነገረው በዚሁ ዐይነት ሲሆን በምዕ. 18 ላይ የምናገኘውን ዐይነት ያልተመጣጠነ ግሳዊ ቅርጽ በዚህም ላይ እናገኛለን (ለምሳሌ፣ 19፥17፡- "ወደ ሜዳም ካወጡአቸው [ብዙ ተባዕታይ] በኋላ እንዲህ አለው [ነጠላ ተባዕታይ]፤ ወይም 19፥18፡- ሎጥም እንዲህ አላቸው [ብዙ ተባዕታይ] . . . እነሆ እኔ ባሪያህ" [ነጠላ ተባዕታይ])።

ጸሓፊው እንዲህ ዐይነቱን ያልተመጣጠነ ግሳዊ ቅርጽ በትረካው ውስጥ የተጠቀመው ሆነ ብሎ ነው። ይኸውም የእግዚአብሔር መገኘት ተስፋ ከምጠቅነቱ ማለትም ከልዑልነቱ ጋር ስላለው ነገረ መለኮታዊ ተያያዥነት አጽንዖት ለመስጠት ነው። በመሆኑም ያልተመጣጠነ ግሳዊ ቅርጽ መጠቀም ያስፈለገው፣ እጅግ ወሳኝ የሆኑትን ሁለቱን የእግዚአብሔር ባሕርያት ለማስታረቅ ነው። እግዚአብሔር ምጡቅ ቢሆንም ቅርብ ነው፤ ልዑል ጌታ ቢሆንም፣ ራሱን በእኛ ደረጃ ማስገኘት የሚችል ነው።

አብርሃምን ስለ ጐበኙት "ሦስቱ ሰዎች" በተነገረውና ሎጥን ስለ ጐበኙት "ሁለቱ መላእክት/ ሰዎች" በተነገረው ዘገባ መካከል ትልቅ መመሳሰል አለ (19፥1-2)። በምዕ. 18 ላይ አብርሃምን የምናገኘው "በድንኳኑ ደጃፍ ተቀምጦ" ሲሆን፣ በምዕ. 19 ላይ ደግሞ ሎጥን "በሳዶም ከተማ መግቢያ በር ተቀምጦ" (ቁ. 1) እናገኘዋለን። ሁለተኛው አብርሃም ሰዎቹን "ሲመለከት" ወዲያውኑ "ሊቀበላቸው" ወደ እነርሱ ሄደ፤ "ወደ መሬት ዝቅ ብሎም እጅ ነሣ"፤ እንዲህም አለ፡- "ጌታዬ በፊትህ ሞገስ አግኝቼ እንደ ሆነ"። በምዕ. 19 ላይ ሎጥም መላእክቱን /ሰዎቹን "ሲያይ" ሊቀበላቸው ተነሣ፤ "በግምባሩም ወደ ምድር ተደፍቶ እጅ ነሣቸው"፤ እንዲህም አለ፡- "ጌቶቼ እባካችሁ"። በሁለቱ ዘገባዎች መካከል የምናገኘው መሠረታዊ ልዩነት ለእንግዶቹ የተደረገላቸው አቀባበል ነው። አብርሃም ሦስቱንም ሰዎች በአንድነት "ጌታዬ" ብሎ ነው በነጠላ ቍጥር የጠራቸው። ሎጥ ግን ሁለቱን መላእክት/ሰዎች "ጌቶቼ" ብሎ ነው በብዙ ቍጥር የጠራቸው። ከእግዚአብሔር ጋር ኪዳን የገባው አብርሃም (ምዕ. 17) ጌታ በተገለጠለት ጊዜ ማን እንደ ሆነ ዐወቀው፤ በሰዶም የሚኖረው ሎጥ ግን ያ ጌታ ማን እንደ ሆነ አላወቀም። አብርሃም እግዚአብሔርን ያውቀው ነበር፤ ሎጥ ግን አያውቀውም።

በቍጥር 3 እና በቁ. 4-8 ላይ የምናገኛቸው የነጠላና የብዙ ቍጥር አገባቦች "በመለኮትና በሰው" መካከል ያለውን ግንኙነት ለመግለጽ እንደ ተፈለገ ያሳያሉ። እግዚአብሔር "በራእይ በመናገር" (15፥1) ወይም "በመላእክቱ" (16፥7) ለማካይነት ራሱን ለኪዳኑ ሕዝብ በተጨባጭ ይገልጣል። ለግለሰቦችም እንኳ ይገለጣል (12፥7፤ 17፥1፤ 18፥1)። የኪዳኑ ሕዝብ እግዚአብሔርን በቍሳዊና በተቀረጹ ምስሎች ከቶ እንዳይመስሉት ከተሰጣቸው ትእዛዝ አንጻር (ዘዳ 4፥15) እግዚአብሔር ራሱን በቃል፣ በራእይና በመላእክት እንደ ገለጸ የሚያወሡት ምንባቦች ምንም ጥያቄ አይፈጥሩብንም። ነገር ግን እግዚአብሔር ለእገሌ "ተገለጠለት" (12፥7፤ 17፥1፤ 18፥1) የሚሉት ምንባቦች ትልቅ ጥያቄ ይፈጥሩብናል። እግዚአብሔር ሲገለጥ መልኩና ቅርጹ የማይታየው ለምንድን ነው (ዘዳ 4፥15)? እግዚአብሔር ተገልጦ ሳለ "ፊቴ ግን አይታይም" (ዘፀ 33፥23) ለማለት የሚችለው እንዴት ነው? ጸሓፊው በነጠላና በብዙ ቍጥር ግሳዊ ቅርጾች አማካይነት በታሪኩ ውስጥ የምናገኛቸውን ገጸ ባሕርያት ማንነት በሚገባ በመለየት የእግዚአብሔር ለአብርሃም መገለጥና የሦስቱ ሰዎች ጕብኝት በአንድ ጊዜ የተፈጸሙ አንድ ድርጊት መሆናቸውን ለማሳየት ችሏል። እግዚአብሔር ለአብርሃም ተገልጦለታል፤ የተገለጠለት ግን በአካል "ፊት ለፊት" አይደለም። ነጠላና ብዙ ቍጥሮቹ በዚህ ዐይነት የተቀናጁት ሦስቱ ሰዎች ሁልጊዜ የሚወክሉት የእግዚአብሔርን መገኘት በመሆኑ ነው፤ ሦስቱ ሰዎች የእግዚአብሔርን መገኘት ቢወክሉም፣ ከእርሱ ግን የተለዩ ናቸው።

እንግዲህ ከዚህ የምንረዳው ሦስቱን ሰዎች መመልከት ያለብን እግዚአብሔር ለአብርሃም በአካል እንደ "ተገለጠለት" አድርገን ነው። ምንም እንኳ ራሱ እግዚአብሔር ለአብርሃም በአካል ባይገለጥለትም፣ ሦስቱ ሰዎች መታየት ያለባቸው የመገኘቱ ወካይ ተደርገው ነው (ዘፀ. 3፥2-3)። በዚህ ዐይነት እግዚአብሔር በኪዳኑ ሕዝብ መካከል የሚገኝ አምላክ መሆኑ ተረጋገጠ፤ እንዲህ ሲሆን ግን እግዚአብሔር ቍሳ አካላዊ ቅርጽ አለው የሚለውን ግምት ሳያሳድር ነው።

ለ. አብርሃም ልጅ እንደሚወልድ ተስፋ ተሰጠው (18፥9-15)

9-11 ሦስቱ ሰዎች ሣራ የት እንዳለች ቢጠይቁም፣ ያነጋገሩት ግን አብርሃምን ብቻ ነው። አብርሃምና ሣራ ከእርጅና የተነሣ ልጅ ለመውለድ አይችሉም ነበር። ሣራ በእርሷ ዕድሜ ክልል እንዳሉ ሴቶች ሁሉ ልጅ ለመውለድም ሆነ ለመፅነስ አትችልም ነበር። ምንም እንኳ የአብርሃም ዕድሜ እንደ ምክንያት ቢጠቀስም፣ የተስፋው ቃል እንዳይፈጸም ትልቅ መሰናክል የሆነው የሣራ ዕድሜ ነበር (25፥1-4)። የዕድሜዋ አሳሳቢነት በቁ. 12 ላይ ተወሥቷል፤ እርሷም በመጀመሪያ የራሷን፣ ቀጥሎም የአብርሃምን መውለድ አለመቻል ገለጸች። በመጨረሻም በቁ. 13 ላይ የሣራ ሐሳብ ተገለጠ፤ የአብርሃም እርጅና ግን አልተጠቀሰም። እንግዲህ ለእርሷ ልጅ መውለድ የማይታሰብ ብቻ ሳይሆን የማይቻል (ቁ. 14፣ "የሚሳነው ነገር") ነበር።

12-15 የዚህን ዐጭር ምንባብ ትርጉም ቁልፍ የምናገኘው ሣራ ለምን እንደ ሣቀች እግዚአብሔር አብርሃምን ሲጠይቀው ነው። የሣራ ሐሳብ በዚህ ዐይነት የተነገረው እግዚአብሔር ሐሳቧን እየደገመው ብቻ ሳይሆን እየተረጐመውም እንደ ሆነ ለማሳየት ነው። በመጀመሪያ እግዚአብሔር የሣራን አሻሚ ቃል ደገመው፤ "ካረጀሁ በኋላ . . . በዚህ ነገር መደሰት ይሆንልኛል? የሚለውን "ልጅ እንዴት አድርጌ እወልዳለሁ?" በማለት ደገመው። ከዚያም ሣራ ስለ ባሏ "ጌታዬም ከደከመ በኋላ" በማለት የተናገረችውን "ካረጀሁ በኋላ" በማለት ስለ ራሷ እንደ ተናገረች አድርጎ አቀረበው። በመጨረሻም ከቃሏ ባሻገር ወደ ሐሳቧ ዘልቆ ሄደ፡- "ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር አለን?" እንግዲህ ዋናው ቁም ነገር የተስፋው ቃል በሣራ በኩል ሊፈጸም ያልቻለው ከእርጅናዋ የተነሣ ነው።

ሣራ ከእርጅናዋ የተነሣ ልጅ መውለድ እንደማትችል በግልጽ ከተነገረ በኋላ እግዚአብሔር የተስፋ ቃሉን ለአብርሃም በድጋሚ ነገረው። በዚህ ጊዜ በእግዚአብሔርና በአብርሃም መካከል የተደረገውን ውይይት ስታደምጥ የነበረችው ሣራ ወደ ውይይቱ ዘላ በመግባት "እረ አልሣቅሁም" አለች። ጸሓፊው ፈጥኖ ድርጊቷ ውሸት እንደ ሆነ ከገለጸ በኋላ የዋሸችው ስለ ፈራች ነው ይለናል። ይህ ዐጭር ታሪክ የተደመደመው እግዚአብሔር በተደጋጋሚ የተናገረው ነገር እውነት መሆኑን ተደራስያኑ እንደሚያስተውሉት በመግለጽ ነው።- ሣራ በርግጥ ሥቃለች።

ሐ. ሰዶም ስትመዘን (18፥16-22)

16 ሦስቱ ሰዎች ወደ ሰዶም ለመሄድ ሲነሡ፣ አብርሃም ሊሸኛ ቸው ተነሣ። ሦስቱ ሰዎች በተከታዩ ምዕራፍ ላይ ዶጋ ዐመድ ወደምትሆነው ከተማ ወደ ሰዶም ቀጥቀጥል ተመለከቱ።

17-19 በእግዚአብሔር ንግግር ውስጥ ያሉ ቃሎች ምን ለማድረግ እንዳሰበ የውስጥ ሐሳቡን ይነግሩናል ("እኔ የማደርገውን ነገር")። ቁጥር 18 አብርሃም ታላቅ ሕዝብ (12፥2) እንደሚሆንና በምድር የሚኖሩ በእርሱ አማካይነት እንደሚባረኩ (12፥3) ወደ ኋላ ተመልሶ የመጀመሪያውን ሐሳብ ያስታውሰናል።

ቁጥር 19 በ17፥1 ላይ የተነገረውን ሐሳብ ይበልጥ ያስፋፋል። እግዚአብሔር የታሪኩ ማእከላዊ አካል የሆነውን ማለትም የአብርሃምን መመረጥ በግልጽ ይናገራል፦ "መርጬዋለሁ"። ሁለተኛው፣ እግዚብአሔር አብርሃምን የመረጠበትን ምክንያት ይናገራል። እዚህ ላይ እግዚአብሔር አብርሃምን የመረጠበት ምክንያት ተገልጿል ("የእግዚአብሔርን መንገድ ይጠብቁ ዘንድ")። ሐሳቡ አብርሃምና ዘሮቹ "ትክክለኛና ቀና የሆነውን" እንዲያደርጉ ነው። እግዚአብሔር ለአብርሃም የገባውን ተስፋ የሚፈጽመው ይህን ሲያደርጉ ብቻ ነው። እግዚአብሔርን መታዘዝ ዐዲስ ኪዳን (ኤር 31፥33) ከሚናገረው እሳቤ ጋር ተሳስሯል፤ ይህ እሳቤ በጽኑ የተመሠረተው በዘዳ 30፥6 ነገረ መለኮት ላይ ነው።

20-21 በቁጥር 17-19 ላይ እግዚአብሔር ለራሱ የሚናገር ይመስላል። ይሁንና እዚህ ላይ እየተናገረ ያለው ለአብርሃም ነው። የእግዚአብሔር ቃል በቁ 17 ላይ የተነሣውን ጥያቄ ይመልሳል። ስለዚህ እግዚአብሔር የሰዶምንና የገሞራን ዐመፀኛነት ለማየት ወደዚያ እንደሚሄድ ለአብርሃም ገለጠለት።

22 ታሪኩ በመጀመሪያ "እግዚአብሔር እንዲህ አለ፤ . . . . ኀጢአታቸውን . . . ለማየት ወደዚያው እወርዳለሁ" (ቁ. 21) ካለ በኋላ ሰዎቹም ፊታቸውን ወደ ሰዶም አቅንተው ሄዱ እንደሚል ልብ እንበል። እግዚአብሔርና ሰዎቹ እንደ ገና በቅርብ ሲዛመዱ እናያለን። ሰዎቹ የእግዚአብሔር መልእክተኞች ከሆኑና የሚወክሉትም የእርሱን በዕለት ተዕለት ሕይወት ውስጥ መገኘት ከሆነ፣ ወደ ሰዶምና ገሞራ ሲሄዱ እነዚህን ከተሞች በርግጥ ሊጐበኝ የሄደው እግዚአብሔር ነው ማለት እንችላለን።

በዚህ ታሪክ ውስጥ እንደምናየው እነዚህ "ሰዎች" የሚወክሉት የእግዚአብሔርን መገለጥ ነው፤ ይሁንና እነርሱ ራሳቸው እግዚአብሔር ስለ መሆናቸው በግልጽ አልተነገረም። በመሆኑም "ሁለቱ ሰዎች" ከሄዱ በኋላ እግዚአብሔር ወደ ኋላ ቢቀርም፣ ወዲያው ደግሞ "ከሁለቱ ሰዎች" ጋር (19፥12:16) በሰዶም ከሎጥ ጋር መገኘቱ ሊያስደንቀን አይገባም። ስለዚህ እግዚአብሔር "ወርጄ አያለሁ" ሲል እንደ ምዕ. 18 ሁሉ በምዕ. 19 ላይም ሰዎቹ የሚወክሉት የእግዚአብሔርን ከሎጥ ጋር መገኘት ነው።

ቢሆንም አንድ ጥያቄ ግን ይቀራል። ከአብርሃም ተለይተው የሄዱት ሦስት ሰዎች ከሆኑ፣ ወደ ሰዶም ሲገቡ ግን "ሁለት መልእክተኞች" (19፥1) ብቻ የሆኑት ለምንድን ነው? ሎጥን የገ0በ ኙት ሁለቱ መልእክተኞች አብርሃምን ከጐበኙት "ሦስት ሰዎች" መካከል ሁለቱ ለመሆናቸው ግልጽ ነው፤ በተለይ በምዕ. 19 "መልእክተኞቹ" ብዙ ጊዜ የተጠቀሱት "ሰዎቹ" ተብለው ነው። ይሁንና ሌላው ሰው የት ደረሰ? ለማለት የምንችለውና እጅግ በጣም የተለመደውም ማብራሪያ ሰውየው ሌላ ማንም ሳይሆን "አስተርእዮተ ክርስቶስ" ነው፤ ማለትም ከትስብእቱ በፊት (ክርስቶስ ሥጋ ከመሆኑ በፊት) ከሥላሴ አካላት መካከል ሰው ሆኖ የተገለጠው ሁለተኛው አካል ነው። እንግዲህ ምንባቡ "ሰዎቹ ፊታቸውን ወደ ሰዶም አቅንተው ሄዱ"፤ እንዲሁም እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር በዚያው ቀረ፤ ደግሞም ወደ ሰዶም የመጡት ሁለቱ ሰዎች ብቻ ናቸው ሲለን (19፥1)፣ ከሁለቱ ሰዎች አንዱ ከአብርሃም ጋር ቀርቷል ማለት ነው። እግዚአብሔር በዚያው እንደ ቀረ ስለምናውቅ፣ ያ ሰው እግዚአብሔር መሆን አለበት። እንግዲህ አብርሃም በክርስቶስ ቅድመ ትስብእት ተገብኝቶ ነበር፤ ከእርሱም ጋር ሁለት መላእክት ነበሩ።

ወደ ሰዶም የሄዱት ሁለቱ ሰዎች የሚወክሉት እግዚአብሔር ሊፈጽመው ያቀደውን ሐሳቡን ነው፤ እግዚአብሔር "አድራጎታቸው እኔ ዘንድ እንደ ደረሰው ጩኸት መሆኑን ለማየት ወደዚያው እወርዳለሁ" ብሎ ነበርና። ይሁንና እግዚአብሔር "የሰዶምን ጩኸት የሚያየው" እንዴት ነው? ታሪኩ የሚያውሣው ሰዎቹ ሰዶምን ለመገብኘት እንደ ሄዱና በምዕ. 19 መዝጊያ ላይ እግዚአብሔር የደመሰሰው ሰዶምን ብቻ ሳይሆን ገሞራንም በመሆኑ (ቁ. 24) ሦስተኛው ሰው ወደ ገሞራ በመሄድ በዚያች ከተማ ተመሳሳይ ተግባር ሳይፈጽም አልቀረም። ጸሓፊው ወደ ሰዶም የሄዱትን ሰዎች ቁጥር በግልጽ በመጥቀስ የእግዚአብሔርን ጽድቅና በገሞራ ላይ የሚያመጣውን ቅን ፍርድ በተመለከተ ሊነሡ ለሚችሉ ጥያቄዎች መልስ አዘጋጅቶልናል። በመሆኑም "የምድር ሁሉ ዳኛ" (ቁ. 25) በቅን ይፈርዳል (ከ19፥15 ጋር ያነጻ)።

መ. የአብርሃም ምልጃ (18፥23-33)

23-33 በአብርሃምና በእግዚአብሔር መካከል የተደረገው ንግግር ዐቢይ ሐሳብ አብርሃም በቁ 25 ላይ ባነሣው ጥያቄ ተገልጿል። የእግዚአብሔር መልስ አዎንታዊ ነበር። አብርሃም ጥያቄውን የጀመረው በከተማዪቱ ውስጥ ንሥሳ ጻድቃን ሰዎች ቢገኙስ በሚለው ሲሆን የጨረሰው ዐሥር ጻድቃን ሰዎች ቢገኙስ በሚለው ነው። ሄዶ ሄዶ ዐሥር ሰዎች ላይ ያቆመው ለምንድን ነው? ስለ ሎጥና ቁጥራቸው አራት ብቻ ስለ ሆነው ስለ ቤተ ሰቡ አይገደውም? አንዱ መልስ በዐሥር በዐሥር ቤት እየቁጠረ ከንሥሳ ጀምሮ ወደ ዐሥር ቢወርድ ሊቆም የሚችለው ዐሥር ላይ ነው። አብርሃም እስከ ዜሮ ድረስ ሊወርድ አይችልም፤ ምክንያቱም እርሱን ያሳሰበው በኀጢአተኞች መካከል የሚኖሩ የጻድቃን ጉዳይ እንጂ የኀጢአተኞች መጥፋት አይደለም። አብርሃም ለጥያቄው ጠቅለል ያለ መልስ ስላገኘ፣ የሚድኑት ሰዎች ትክክለኛ ቁጥር ምን ያህል እንደ ሆነ መጠየቅ አላስፈለገውም።

አብርሃም ስለ ሎጥ ግድ እንደ ተሰኘ የሚያወሣው ይህ ታሪክ እግዚአብሔር በኀጢአተኞች ላይ ሲፈርድ ጻድቅ ሰዎችን የሚያየው እንዴት እንደ ሆነ ተመልክቷል። የሰዶም ከተማ ስትደመሰስ፣ ሎጥ ተረፈ። ስለዚህ በከተማዪቱ ውስጥ ከዐሥር ያነሡ ጻድቃን ቢገኙ እግዚአብሔር ምን ሊያደርግ እንደሚችል መልስ አግኝተናል። ምንም እንኳ ሰዶም ስለ ሎጥ ተብሎ ባትተርፍም፣ ትንሿ ከተማ ዞዓር ግን በሎጥ ምክንያት እንደ ተረፈች መጠቀስ አለበት (የ19፥17-22 ማብ ይመ.)።

7. ሎጥና ሰዶም (19፥1-38)

ሀ. ሁለት መላእክት በሰዶም (19፥1-4)

1ሀ በቁ 10፡ 12፡ 15-16 መሠረት ሁለቱ "መላእክት" ሰዎች ናቸው (ቁ. 10)፤ እነርሱም አብርሃምን የጐበኙት ሰዎች ናቸው (18፥3)። እዚህ ላይ ልብ ልንለው የሚገባው ወደ ታሪኩ መዝጊያ ስንዳረስ ሰዎቹ የሚወክሉት የእግዚአሔርን ጉብኝት ነው (ቁ. 18)። የመጡትም በከተማዪቱ ዐመፅ ላይ የእግዚአብሔርን ፍርድ ለማስፈጸም ነው (ቁ. 13)፤ እንዲሁም አብርሃም ለጻድቃን በጸለየው መሠረት (18፥23-32) ሎጥን ለማዳን ነው (19፥29)።



ይህ ለም ከሆነ ከበረሓ ገነት ጋር የሚታየው የሙት ባሕር ደቡባዊ ጫፍ ማጠቃለያው ሲሆን፣ ሰዶምና ገሞራ የነበሩበት ስፍራ ሊሆን ይችላል።

1ለ-11 ሰዶምና ገሞራ ከመደምሰሳቸው በፊት በዋዜማው ምሽት በሎጥ ቤት የነበረው ሁነት በሁለቱ ከተሞች ላይ የተላለፈው

መለኮታዊ ፍርድ ተገቢ መሆኑን ያረጋግጣል። ከፍርድ የተረፈው ጻድቁ ሎጥ እንኳ ከሰዶም ጋር በመነካካቱ ረክሷል። እንደ አብርሃም ሎጥም ከመልእክተኞቹ ጋር እግዚአብሔር እንደ ነበር አላስተዋለም፤ ያናገራቸውም ጌቶቼ ሆይ ብሎ ነው (ቁ. 2)። ምንም እንኳ ሎጥ እንደ አብርሃም እንግዳ ተቀባይ ቢሆንም፣ ደግሞም ከሰዶም ሰዎች ተርታ ባይፈረጅም፣ የከተማዪቱ ሰዎች በገዛ ሴቶች ልጆቹ ላይ ያሻቸውን እንዲያደርጉ ሐሳብ ማቅረቡ መልካም ባሕርይ እንዳለው ሰው ሊያስቈጥረው አይችልም። ይህ ሐሳቡ ምፀታዊ በሆነ መንገድ በራሱ ላይ ተፈጽሟል፤ ሎጥ ራሱ የገዛ አጸያፊ ሐሳቡን ሳያውቀው ፈጸመ (ቁ. 30-38)።

12-14 መልእክተኞቹ የተላኩት ለሁለት ምክንያት እንደ ሆነ በግልጽ ተናገሩ፦ የተላኩት ከተማዪቱን ለማጥፋትና ሎጥንና ቤተ ሰቡን ለማዳን ነው። የሁለቱ አማቾች መልስ ከተቀሩት የከተማዪቱ ሰዎች ጋር አንድ መሆኑን ያሳያል። ይህም መለኮታዊ ፍርዱ ተገቢ መሆኑን ይበልጥ ያረጋግጣል።

ለ. የሎጥ መዳን (19፥15-28)

15-16 የሰዶም ሰዎች የሎጥን ቤት በእጃቸው ሲዳስሱ፣ ሎጥና ቤተ ሰቡ ግን እጃቸውን ተይዘው ከከተማዋ በጠዋት እንዲወጡ ተደረገ። ሎጥ ሊድን የቻለው ከአብርሃም ጸሎት የተነሣ ነው፤ መላእክቱ የተናገሩት ቃል አብርሃም የተናገረውን ቃል በግልጽ ያስታውሰናል (ከ18፥23፤ 19፥15፤ 17 ጋር ያነጻ፤ በተለይ 19፥29 ይመ.)።



ውሃ ከበስተጀርባው ሆኖ የሚታየው በሙት ባሕር የሚገኝ የጨው ዐምድ መታሰቢያ ሐውልት ነው።

ይህ ክፍል ሎጥን በነጢአተኞች መካከል የሚኖር ጻድቅ ሰው አድርጎ ያሳየናል፤ እርሱም እግዚአብሔር ከመረጠው ሰው ምልጃ የነተነሣ ሊደርስ ከነበረው ፍርድ ዳነ። ይሁንና እግዚአብሔር ሎጥን ያዳነው ከጽድቁ የተነሣ ሳይሆን "እግዚአብሔር ስለ ራራለት" ነው። የሎጥ "ጽድቅ" (ከ2ጴጥ 2፥7 ጋር ያነጻ) የተመሠረተው በምዕ. 18 አብርሃም "ለጻድቃን" በጸለየውና በምዕ. 19 በሎጥ መዳን ሁነት ላይ ነው። የታሪኩ አትኩሮት ራሱ በእግዚአብሔር ርኅራኄና ምሕረት ላይ ነው። በቁጥር 19 ላይ ሎጥ በእግዚአብሔር ፊት "ሞገስና ምሕረት" እንዳገኘ ተገልጿል።

17-22 በታሪኩ መዝጊያ ላይ ሎጥ በአቅራቢያው ወደ ምትገኝ ዞዓር ወደ ምትባል ከተማ መሸሽ እንዲችል ጥያቄ አቀረበ። ለጥያቄው መልስ በማግኘቱ እግዚአብሔር ያቺን ከተማ ከጥፋት አዳነ። እንግዲህ ሎጥ የዳነው በጸሎት ነው፤ በአብርሃምና በራሱ ጸሎት። እግዚአብሔር በከተማዪቱ ውስጥ ጻድቅ ሰው ካለ ያቺን ከተማ እንደማያጠፋ ቃል ገብቶ ነበር። ምንም እንኳ አሁን ሰዶም ብትጠፋም፣ ዞዓር ግን በመካከሏ ከሚገኘው ከጻድቁ ሎጥ የተነሣ ከመጥፋት ዳነች።

23-28 ጸሓፊው ስለ እግዚአብሔር ፍርድ ገለጻ ከመስጠቱ በፊት ሁለት ነገሮችን ልብ እንድንል ፈልጓል። አንደኛው፣ "ፀሓይ በምድሩ ላይ ወጥታ ነበር፤" ሁለተኛው፣ "ሎጥ ዞዓር ሲደርስ። እዚህ ላይ ስለ ፀሓይ መጠቀሱ ይህ ክፍል ሎጥ ሊነጋጋ ሲል ማለትም ጎሕ ሲቀድ ከሰዶም ጥፋት ከመዳኑ ጋር ትስስር እንዳለው ያሳያል (ቁ. 15)። ከዚህም በተጨማሪ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የፀሓይ መውጣት የሚያመለክተው እግዚአብሔርን ነው፤ ጻድቃንን የሚያድንበትንና ኀጥኣንን የሚኰንንበትን ፍርድ ነው (ኢሳ 9፥2፤ ሚል 4፥1-2)። ጸሓፊው ይህን መግቢያ ከሰጠን በኋላ ክፉ ሰዎችን የሚጠብቃቸው ዕጣ ፈንታ ምን እንደ ሆነ ዘወትር ታዋሽ በሆነ ቃል ይነግረናል፦ "እግዚአብሔር በሰዶምና በገሞራ ላይ ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ የሚቃጠል ዲንና እሳት አዘነበባቸው"።

የሎጥ ሚስትና አብርሃም ሁለቱም በከተሞቹ ላይ የደረሰውን ጥፋት "ተመልክተዋል"፤ ይሁንና የዚህ ውጤት የተለያየ ነበር። የሎጥ ሚስት "ወደ ኋላዋ ስለ ተመለከተች" የጨው ዐምድ ሆነች፤ ይህም ሊያድኗቸው የመጡትን ሰዎች ቃል አለማክበሯን ያሳያል (ቁ. 17)። ባንጻሩም አብርሃም የተመለከተው በቁ. 17 ላይ ሰዎች እንደ ተናገሩት ከሩቅ ነው። ሰዎቹ "በዚህም ዙሪያ ሁሉ አትቁም" ብለዋቸው ነበር፤ ስለዚህ አብርሃም ". . . ከዚህ ቀደም በእግዚአብሔር ፊት ቆሞ ወደ ነበረበት ቦታ ሄደ። ሰዶምንና ገሞራን እንዲሁም በረባዳው ስፍራ የሚገኘውን ምድር ሁሉ ቁልቁል ተመለከተ" (ቁ. 27-28)። አብርሃም ለሎጥና ለቤተ ሰቡ የተሰጠውን ማስጠንቀቂያ ባያውቅም፤ በመታዘዙ ግን ከጥፋት አመለጠ።

ሐ. ሎጥ ከገዛ ልጆቹ ወለደ (19፥29-38)

29-38 ቁጥር 29 አብርሃም ለሎጥ መዳን የተጫወተውን ሚና በግልጽ ያስታውሰናል። ይህም እግዚአብሔር ለአብርሃም ከሰጠው ተስፋ ጋር ዝምድና እንዳለው ያስገነዝበናል፤ ምክንያቱም በአብርሃምና በዘሩ አማካይነት "በምድር የሚኖሩ ሕዝቦች . . . ይባረካሉ" (12፥3)። ሎጥ ከስካሩ የተነሣ ለሰዶም ሰዎች አቅርቦላቸው የነበረውን ሐሳብ እርሱ ራሱ አደረገው (19፥8)፤ ከገዛ ሴት ልጆቹ ጋር ተኛ። ይህ ዘገባ ኖኅ ከጥፋት ውሃ ከተረፈ በኋላ ከተነገረው ታሪክ ጋር በእጅጉ ይመሳሰላል (9፥20-27)። በዚህ ስፍራ እንደምናነበው ሁሉ በዚያም ክፍል ኖኅ ከስካሩ የተነሣ በልጆቹ ፊት ዕርቃኑ ሥጋው ተጋለጠ፤ ይህም አሉታዊ መዘዝ ነበረው። እንግዲህ በእነዚህ ሁለት ታሳላቅ የእግዚአብሔር ፍርድ ታሪኮች መዝጊያ ከእግዚአብሔር ቁጣ የዳኑ ሰዎች፣ በፍርድ የሞቱ ሰዎች በተያዙበት ኀጢአት ሲወድቁ እናያለን።

በዘዳግም 2፥9፡ 19 ላይ ሎጥ የሞዓባውያንና የአሞናውያን አባት እንደ ሆነ ተገልጿል። በዚህ ምንባብ ላይ እነዚህ ሕዝቦች ከእስራኤል ማኅበር እንደ ተወገዱ በአጽንዖት ተጠቅሷል። ሞዓባውያንና አሞናውያን ከዚህ በኋላ በሚኖረው የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ውስጥ ጉልሕ ሚና ሲጫወቱ ይታያል።

መ. አብርሃምና አቤሜሌክ (20፥1-18)

የምዕራፍ 20 እና 21 ትኩረት በአብርሃምና በሕዝቦች መካከል ስላለው ዝምድና ነው። የአብርሃም ሚና በተስፋ ቃሉ ላይ "በምድር የሚኖሩ ሕዝቦች ሁሉ በአንተ አማካይነት ይባረካሉ" እንደ ተባለው ነቢያዊ አማላጅ መሆን ነው (12፥3)። ለፍልስጥኤም ሰዎች ጸለየ (20፥7)፤ እግዚአብሔርም ፈወሳቸው (ቁ. 17)። በታሪኩ ላይ አቤሜሌክን የምናየው፣ አብርሃም በሰላምና በበረከት ዐብሮት የሚኖረውን የአንድ ጻድቅ አሕዛብ ሚናን ሲጫወት ነው። ምንም እንኳ በግልጽ ባይነገርም፣ በምዕራፍ 19 (ሎጥ ቅይጥ ሕዝቦችን ይወክላል) እና 20 (አቤሜሌክ ጻድቅ መጻተኞችን ይወክላል) መካከል ንጽጽር አለ።

1 አብርሃም በጌራራ ለመቀመጥ "ከመምሬ ትልልቅ ዛፎች" ተነሥቶ (18፥1፣ 33) ወደ "ኔጌብ" ማለትም ወደ ደቡብ ሄደ፤ ጌራራ "በፍልስጥኤማውያን ምድር" የምትገኝ ስፍራ ናት (21፥34)።

2 ሣራ ወደ አቤሜሌክ ቤት ተወሰደች። እዚህ ላይ የምናገኘው ታሪክ በምዕ. 12 ላይ ከተወሣው ሁኔት ይልቅ በእጅጉ ዐጭር ነው። በግልጽ እንደሚታየው ትኩረቱ በሣራ ዕጣ ፈንታ ላይ ሳይሆን በፍልስጥኤማውያን ላይ ነው። አብርሃም ስለ ራሱ እንዲናገር ዕድል ከማግኘቱ በፊት (ቁ. 11-13) ዝርዝር ሐተታው ተዐቅቦ ተደርጎበታል። እዚህ ላይ የአብርሃም ተግባር የራሱን ሳይሆን የፍልስጥኤማውያንን ውስጣዊ ሐሳብ ወደ ብርሃን ሲያመጣው እናያለን። የአብርሃም ንግግር ፍልስጥኤማውያን ክፉ ሰዎች እንደ ሆኑ ቢያስመስላቸውም፣ ተግባራቸው ግን እንደዚያ ዐይነት ሰዎች እንዳልሆኑ መስክሮላቸዋል።

3-16 ታሪኩ አቤሜሌክ ንጹሕ ሰው መሆኑን ለማሳየት በእጅጉ ጥሯል፤ "አቤሜሌክ ግን አልደረሰባትም" ነበር። በመሆኑም

አቤሜሌክ “ንጹሕ” (ጻድቅ) ሰው መሆኑና እርሱም ንጹሕ ሰው ለመሆኑና ያቀረበው አቤቱታ ከአብርሃም አታላይነት ጋር ጉልሕ ንጽጽር ይታይበታል። በመሠረቱ በቍ. 6 ላይ እግዚአብሔር ራሱ የአቤሜልክ አቤቱታ ትክክል መሆኑን አጽንቷል። ይሁንና አቤሜሌክ ንጽሕናውን ጥሎ የአብርሃምን ቤተ ሰብ ከበደለ፣ ከእግዚአብሔር ብርቱ ማስጠንቀቂያ አያመልጥም። የአብርሃም ሚስት መመለስ አለባት፤ ነቢዩ አብርሃምም ስለ አቤሜሌክ ሕይወት መጸለይ አለበት። እግዚአብሔር አቤሜሌክን በመጐብኘቱ (ለአቤሜሌክ በሕልም በመገለጡ) አቤሜሌክ በጠዋት ተነሥቶ ያየውን ራእይ ለአገልጋዮቹና ለአብርሃም ነገራቸው። ፍልስጥኤማውያንም ከእግዚአብሔር ለደረሳቸው ማስጠንቀቂያ ፈጥነው ምላሽ ሰጡ (ከዮናስ 3፥6-9 ጋር ያነጻ)።

የአብርሃም መልስ ለውሸቱ ማስተባበያ ብቻ ሳይሆን በምዕ. 12 ላይ እንደምናነበው፣ በግብፅ ሳለ የወሰደውን ተመሳሳይ ርምጃ ለመረዳትም ያገለግላል። እንዲሁም ገና የአባቱን ቤት ትቶ ሲወጣ ለፍልስጥኤማውያን የነበረው አመለካከት የተዛባ ነበር። በመሆኑም አብርሃም ለፍልስጥኤማውያን የነበረው አመለካከት ለምን እንደ ተዛባ ምክንያቱ ተገልጿል። ምንም እንኳ በምዕ. 11 ላይ አብርሃም የአባቱን ቤት ትቶ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ሕይወቱን በቅርብ ብንከታተልም፣ አብርሃም ከሣራ ጋር ባለው ጉዳይ በራሱ መንገድ ሲሄድ ስናይ ይህ የመጀመሪያው ነው። የሆነው ሆኖ አሁን ሐሳቡን ሲገልጽ የምናየው ራሱ አቤሜሌክ ነው። አቤሜሌክ የአብርሃምን ማብራሪያ አንዳች ሳይጠራጠር በመቀበሉ ለስሕተት ተዳረገ። አቤሜሌክ ማብራሪያውን በቅንነት መቀበሉን የምናየው ከሣራ ጋር ሲነጋገር አብርሃምን ይጠራው የነበረው “ወንድምሽ” እያለ ነበር። አቤሜሌክ የአብርሃምን የፈጠራ ታሪክ መቀበሉ ሳያንሰው የሸከረውን ግንኙነት ለማደስ ውድ የሆኑ ስጦታዎች መስጠቱ የዋህነቱን ይበልጥ ያሳያል።

17-18 አብርሃም ስጦታውን ከፍልስጥኤማውን ከተቀበለ በኋላ እርሱም በፈንታው ስለ እነርሱ ጸለየ። እግዚአብሔር በቍ. 7 ላይ ለአቤሜሌክ የተናገረው ቃል ትርጕሙ ምን እንደ ሆነ የምናውቀው አሁን ነው። እግዚአብሔር “በአቤሜሌክ ቤት የሚገኙትን ሴቶች ማሕፀናቸውን ሁሉ ዘግቶ ነበርና”።

ረ. አብርሃምና ይስሐቅ (21፥1-25፥11)

1. የይስሐቅ መወለድ (21፥1-7)

1-7 ቍጥር 1 በ18፥10 ላይ የተወሣውን ማእከላዊ ጭብጥ ያነሣል። ስለ ይስሐቅ መወለድ የተነገረው ዜና ዘግይቶ ቢፈጸምም፣ እዚህ ላይ የተዘገበው ግን እንደ ተጠበቀው አስደሳች ሆኖ አይደለም። በምዕራፍ 18 ብዙ ትኵረት የተሰጠው የተስፋው ቃል ስለ መፈጸሙ ሳይሆን ስለሚወለደው ልጅ የምሥራች ነው። ይስሐቅ የተወለደው “እግዚአብሔር በተናገረው መሠረት” ነው፤ ይህም በመጀመሪያዎቹ ሁለት ቍጥሮች ላይ ሦስት ጊዜ አጽንዖት ተሰጥቶታል። በመሆኑም ታሪኩ እግዚአብሔር በቃሉ የታመነና ሐሳቡንም ለመፈጸም የሚተጋ አምላክ እንደ ሆነ ያስገነዝበናል።

ስለ ይስሐቅ መወለድ የተነገረው ዜና ትልቅ ስፍራ እንዳለው የምንረዳው “እግዚአብሔር ሣራን . . . . አሰባት” በሚለው አረፍተ ነገር ነው። ይህም የእግዚአብሔርን ክብካቤና ፍቅር ያሳያል። እንዲሁም ይስሐቅ የተወለደው “አብርሃም . . . . ዕድሜው መቶ ዓመት” ሳለ ነው የሚለው ማስታወሻም ትልቅ ስፍራ ይሰጠዋል። የተወለደውም እግዚአብሔር ባለው ጊዜ ነው፤ ይህም ከዚህ በፊት የተነገሩትን የተስፋውን ቃል ቍልፍ ጭብጦች ያስታውሰናል (ለምሳሌ፣ 18፥10-14)። ከዚህም በተጨማሪ ታሪኩ ስለ አብርሃም መታዘዝ በአጽንዖት ይናገራል (ከ17፥12 ጋር ያነጻ)። ይስሐቅ በተወለደ ጊዜ አብርሃም የመቶ ዓመት ሰው ነበር (ከ17፥1:24 ጋር ያነጻ)። በቍጥር 7 ላይ ሣራ የተናገረችው ቃል ዕድሜው ምን ያህል እንደ ሆነ ያመላክታል።

2. ሐጋርና እስማኤል (21፥8-21)

8-12 ይስሐቅ ዕድሜ በሚከበርበት ጊዜ የእስማኤል መባረር ሆነ። በዚህ ምዕራፍና በምዕ. 16 በተፈጸመው ሁነት መካከል ያለው መመሳሰል ልብ ሊባል ይገባዋል። ጸሓፊው በሁለቱ ምዕራፎች መካከል ስላለው ምስስል በሚገባ ለመግለጽ የሞከረው ብዙ ጊዜ በተጠቀመበት የጥላና የጥላ መፈጸሚያ መጪውን እውነተኛ ነገር የማሳያ ስልቱ ነው፤ ይህም በሁለቱ ታሪኮች መካከል ያለውን መሠረታዊ ትስስር ለመግለጽ አስችሎታል። በዚህ ዐይነት እግዚአብሔር ለሐጋር የሰጣት ተስፋ (16፥11-12) የተነገረውና የተፈጸመው በሚያስደንቅ መንገድ ነው (ቍ. 18-21)። ተስፋው ለፍጻሜው እንደ ጥላ ነው።

3. አብርሃምና አቤሜሌክ (21፥22-34)

22-34 ስለ አቤሜሌክ እንደ ገና መነገሩ አብርሃም አሁንም የሚኖረው ከፍልስጥኤማውያን ጋር መሆኑን ያሳያል (ቍ. 34)። ይህም አብርሃም ዘመኑን በሙሉ የኖረው በተስፋዱቱ ምድር ሳይሆን ብዙ ዘመኑን ያሳለፈው በስደት እንደ ሆነ ያስገነዝበናል። ሌላው ቀርቶ የተስፋው ልጅ ይስሐቅ እንኳ የተወለደው በተስፋዱቱ ምድር አይደለም። ይስሐቅ የተወለደው በስደት አገር በመሆኑ ከአባቱ ጋር መጻተኛ ነበር፤ አባቱ ከሕዝብ ወደ ሕዝብ ሲንከራተት፣ ከአንዱ መንግሥት ወደ ሌላው ሲቅበዘበዝም ኖረ (መዝ. 105፥13)። ምንም እንኳ አብርሃም የአባቱን አገር ትቶ ወደ ተስፋዱቱ ምድር ቢመጣም፣ በዕብ. 11፥8-13 ላይ እንደ ተገለጸው፣ በዚያ የኖረው ግን “በባዕድ አገር እንዳለ መጻተኛ” ነበር፤ “በዚህ ምድር ሲኖሩ መጻተኞችና እንግዶች መሆናቸውን ተገንዝበው ነበርና”። አብርሃም በስደት አገር ሲኖር እግዚአብሔር ወደ ተስፋዱቱ ምድር ለመግባት በተስፋ ለሚጠባበቁ ጻድቃን የሚያደርግላቸውን ክብካቤ ያሳያል። የአቤሜሌክ አገልጋዮች የአብርሃምን የውሃ ጕድጓድ ወስደውበት ነበር። ይሁንና እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር ስለ ነበር አብርሃም ከንጉሣቸው ጋር ውል አደረገ፤ ከዚያም የተወሰደበት ነገር በሙሉ ተመለሰ።

4. የይስሐቅ መታሰር (22፥1-14)

1-14 “እግዚአብሔር አብርሃምን ፈተነው” የሚለው ግልጽ ቃል የእግዚአብሔርን ሐሳብ በሚገባ ያሳየናል። ምንም እንኳ ከታሪኩ ገለጻ እንደምንረዳው በአብርሃም ኅሊና ውስጥ ሊመላለስ የሚችለው የይስሐቅ መሠዋት ቢሆንም፣ በታሪኩ ውስጥ ስለ ይስሐቅ መሠዋት የሚናገር አንድም ነገር የለም። እግዚአብሔር ድንገት ተነሥቶ ይህን ጥያቄ ለአብርሃም ማቅረቡ እርሱን እንዳስደነቀው ሁሉ እኛንም ሊያስደንቀን ይችላል። ያለ ምንም ተጨማሪ ገለጻ ጥያቄው በሦስት ትእዛዞች ተጠቃሏል፦ “ይዘህ”፣ “ሂድ”፣ “ሠዋው”።

ምንም እንኳ ይህ ፈተና እንደ ሆነ እኛ ብናውቅም (አብርሃም ግን እንዲህ መሆኑን አላወቀም)፣ እንደ አብርሃም ሁሉ እኛም የእግዚአብሔር ሐሳብና መንገድ ምን እንደ ሆነ አናውቅም በታሪኩ ላይ አብርሃም ለጉዞውና ስለ ራሱ ስለ ጉዞው ያደረገው ዝግጅት ሆነ ተብሎ በዝርዝር የተነገረው ለምን እንደ ሆነ ልብ ማለት አለብን። ምንም ዐይነት ግልጽ ማብራሪያ ባይሰጥም፣ አብርሃም የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ተቀብሎ ሲሄድ በኅሊናው ውስጥ የሚመላለሰው ሐሳብ ምን እንደ ሆነ መመርመሩ ለእኛ ተትቷል። በመጨረሻ ዝምታው ተሰብሮ ንግግር ሲጀመር ተናጋሪው እግዚአብሔር ሳይሆን ይስሐቅ ነበር። የይስሐቅ ጥያቄ ታሪኩን ይበልጥ ልብ አንጠልጥል አድርጎታል። አብርሃም ለይስሐቅ ጥያቄ የሰጠው መልስ የታሪኩን መጨረሻ ያስተጋባል፦ “እግዚአብሔር ራሱ ያዘጋጃል”።

የአብርሃም ንግግር ዝምታውን በተለየ መንገድ እንድንረዳው ያደርገናል። አብርሃም በፈተናው ቢጨነቅም፣ በሚያዘጋጀው በእግዚአብሔር ላይ የነበረው እምነት ግን ጽኑ ነበር። የአብርሃም መልስ ግራ የተገባውን ይስሐቅን ዝም ለማሰኘት የተሰጠ አይደለም። ነገር ግን በእግዚአብሔር ላይ ያለውን ጽኑ እምነት የሚገልጽ ነው። እግዚአብሔር ጣልቃ ገብቶ ለፈተናው መውጫ መንገድ ከማዘጋጀቱ በፊት በመጨረሻው ሰዓት ላይ የታሪኩን ውጥረት አመጣጥነው የሚያቀርቡ በጣም ጥቂት ታሪኮች ናቸው። እያንዳንዱ የአብርሃም ድርጊት ልብ አንጠልጥል በሆነ መንገድ ተገልጿል። በመጨረሻው ወሳኝ ሰዓት እግዚአብሔር ጣልቃ ገባ፤ አብርሃም አስቀድሞ እንደ ተናገረው ምትኩን አዘጋጀ። ስለዚህ አብርሃም የሠራውን መሠዊያ “እግዚአብሔር ያዘጋጃል” ብሎ ጠራው።

5. የእግዚአብሔር መልአክ (22፥15-19)

15-19 በታሪኩ መዝጊያ ላይ አብርሃም ከእግዚአብሔር መልአክ ጋር “ዳግመኛ” ሲገናኝ እናነባለን። በቍ. 19 ላይ አብርሃም የተመለሰው ዐብረውት ከሄዱት ሁለቱ አገልጋዮቹ ጋር በመሆኑ፣ ከመልአኩ ጋር ዳግመኛ የተገናኘው እንደ መጀመሪያው ሁሉ በዚያው ጉዞ ሳይሆን አይቀርም። ይሁን እንጂ በተለያየ ጊዜ ነው (አብርሃም የሚቃጠል መሥዋዕቱን ካቀረበ በኋላ መሆኑ ነው)። አብርሃም ከመልአኩ ጋር “ዳግመኛ” መገናኘቱ የተገለጸው እግዚአብሔር ለአብርሃም የገባለት ቃል ኪዳን መታደስ የተመሠረተው አብርሃም ከፈተናው ለመውጣት በወሰዳቸው ርምጃዎች ሳይሆን በፈተናው ጊዜ አብርሃም ባሳየው እምነትና መታዘዝ ላይ መሆኑን ለማሳየት ነው።

እዚህ ላይ ዳግመኛ የተነገረው ተስፋ ቀደም ባሉት ምዕራፎች ከተነገረው ጋር ተመሳሳይ ነው። “እባርክሃለሁ” የሚለው ቃል በ12፥2 ላይ የተነገረውን ያስታውሰናል። የአብርሃም ዘሮች እንደሚበዙ የተነገረው ደግሞ በ13፥16፤ 15፥5 እና 17፥2 ላይ ከተነገረው ጋር ተመሳሳይ ነው። “ሕዝቦች” የአብርሃም በረከት ተካፋይ እንደሚሆኑ የተነገረው ከ12፥3 እና 18፥18 ጋር ተመሳሳይ ነው። አብርሃም ለተስፋው ቃል ያሳየው መታዘዝ ከ18፥19 ጋር ተመሳሳይ ነው። ምናልባትም የአብርሃም ዘሮች “የጠላቶቻቸውን ደጆች እንደሚወርሱ” (ቁ. 17) የተነገረው ምድራቱ ለእርሱ እንደምትሰጥ ሊያመለክት ይችላል (12፥7፤ 13፥15፤ 15፥18፤ 17፥8)።

6. የአብርሃም ዘመዶች (22፥20-24)

20-24 የአብርሃም ዘር ጉልቁ መሳፍርት እንደሌለው ዳግመኛ ከተነገረ በኋላ፣ አብርሃምና ሣራ ቀድሞ በሚኖሩባት አገር ቤተ ሰባቸው እጅግ ስለ መብዛቱ ዐጭር መግለጫ ተሰጥቷል። በዘገባው ላይ ዐሥራ ሁለት ስሞች መዘርዘራቸው ምናልባት ጸሓፊው እነዚህን ስሞች ከያዕቆብ ዐሥራ ሁለት ልጆች ወይም ከእስማኤል ዐሥራ ሁለት ልጆች (25፥12-15) ጋር ለማነጻጸር ፈልጎ ይሆናል። ስሞቹ የተዘረዘሩበት ዐቢይ ዐላማ የይሐቅን የወደ ፊት ሙሽራ ማለትም ርብቃን ለማስተዋወቅና እርሷም ከሚልካ ወገን እንጂ ከቁባቷ ወገን እንዳልሆነች ለማሳየት ነው።

7. መክፈላና የሣራ መሞት (23፥1-20)

1-20 ሣራ በኬብሮን ሞተች፤ አብርሃምም ሊያለቅስላት ከቤርሳቤህ መጣ (22፥19)። የምዕራፍ 23 ዐላማ አብርሃም ሕጋዊ በሆነ መንገድ በከነዓን እንዲት አንዲት ትንሽ መሬት እንዳገኘ ለማሳየት ነው። ከብዙ ክርክር በኋላ አብርሃም ሚስቱን ለመቅበሪያ የሚሆን ዋሻ ብቻ ሳይሆን ብዙ ዛፎች ያሉበት ትልቅ መሬት ገዛ። ይህም ለእስራኤል አባቶችና ለሚስቶቻቸው መቀበሪያ የተሰየ ስፍራ ሆነ (ከ49፥30-32፤ 50፥13 ጋር ያነጻ)። አብርሃም ከእኔ የተነሣ በለጸግህ እንዳይለው ከሰዶም ንጉሥ ስጦታን እንዳልተቀበለ ሁሉ (14፥23)፣ እዚህም ላይ መሬት እንስጥህ ሲሉት አልቀበልም አለ። የኬጢያውያኑን ሐሳብ ትቶ ሙሉ ዋጋውን ከፈለ። የአብርሃም በረከት ምንጭ እግዚአብሔር እንጂ ሰው አይደለም። ከእግዚአብሔር ተስፋ ውጭ ለመበልጸግም ሆነ መሬት ለመያዝ አይፈልግም። አብርሃም መሬቱን ሲገዛ አንድ ቀን ምድሪቱ በሙሉ የእርሱና የዘሮቹ እንደምትሆን በእግዚአሔር ላይ ያለውን ተስፋ ያንጸባርቃል (ከኤር. 32፥6-15 ጋር ያነጻ)።

8. የይስሐቅ ሙሽራ (24፥1-67)

1-9 አብርሃም የእግዚአብሔር ተስፋ በይስሐቅ ዘሮች ይፈጸም ይሆን የሚለው ጭንቀቱ ከአገልጋዩ ጋር ባደረገው መሐላ ይታያል። ወደ ፊት የሚመጡትን የአብርሃም ዘሮች በተመለከተ ሁለት ነጥቦች ተነሥተዋል፤ አንደኛው፣ በከነዓን ከሚኖሩ ሰዎች ጋር መጋባት የለባቸውም፤ ይህም ስለ በረከትና መርገም የተነገረውን ቃል (9፥25-27) ይበልጥ ይገልጻል። የአብርሃም ዘር ከከነዓን ዘር መለየት አለበት። ሁለተኛው፣ የአብርሃም ዘሮች ወደ አባታቸው ምድር መመለስ የለባቸውም። መኖሪያቸው ከነዓን ናት፤ አብርሃም ይስሐቅን ወደ አባቶቹ ምድር እንዳይመለስ በግልጽ አስጠንቅቆታል።

ይህ ክፍል የአብርሃምን እምነት ለመጨረሻ ጊዜ ይተርካል። በአገልጋዩ የተነሣው ጥያቄ ለታሪኩ መሠረት ሆኗል። እንደ ከዚህ በፊቱ ሁሉ የአብርሃም መልስ ትንቢታዊና (የታሪኩን የመጨረሻ ውጤት ከወዲሁ በማሳየት ጭብጥን መሠረት ያደረገ (የታሪኩን ማእከላዊ መሠረት በማቅረብ) ነው። “. . . የሰማይ አምላክ እግዚአብሔር መልአኩን ከፊትህ ይልካል፤ ለልጄም ሚስት ከዚያ ታመጣለታለህ”። ቍልፉ ሐሳብ እግዚአብሔር የአገልጋዩን መንገድ ቀና ለማድረግ በፊቱ መሄዱ ነው።

10-27 አገልጋዩ ከእግዚአብሔር የሚፈልገው ምልክት ምን እንደ ሆነ በግልጽ ተናገረ። እግዚአብሔር የአገልጋዩን መንገድ አቃናለት፤ ጥያቄውን ተናግሮ ሳይጨርስ ልጃገረዲ መጣች። ስለ እርሷ ዝርዝር ዘገባ የቀረበው ልክ እንደ መጣች ነው። አገልጋዩ ስለ ልጃገረዲ ማንነት ምንም የሚያውቀው ነገር ባይኖርም፣ እኛ ግን ይህች ሴት የባቱኤል ልጅ፣ የሚልካ ልጅ ርብቃ መሆኗን እናውቃለን። በግልጽ እንደምናየው እግዚአብሔር የአገልጋዩን ጸሎት መልሷል። ከተሰጠው መረጃ ዐይነት አንጻር ይህች ልጃገረድ ልክ አገልጋዩ የጠየቃት ዐይነት መሆኗ አያጠራጥርም፤ እግዚአብሔር በርግጥም መልእክተኛውን በፊቱ ልኮ መንገዱን ቀና አድርጎለታል። በቍጥር 26-27 ላይ እንደምናነበው አገልጋዩ ደስታውንና ምስጋናውን በዚያ ዐይነት የገለጸው እግዚአብሔር ለአብርሃም ዘሮች ካሳየው ቸርነትና በረከት የተነሣ ነው።

28-49 አገልጋዩ ከላባና ከቤተ ሰቦቹ ጋር ከተገናኘ በኋላ ታሪኩን ሁሉ ነገራቸው። ይሁንና ታሪኩን እንዳለ ከመድገም ይልቅ የመጀመሪያውን ታሪክ ማእከላዊ ሐሳብ ብቻ ተናገረ። አብርሃም በመጀመሪያ በጥቅሉ የተናገረው እግዚአብሔር መልእክተኛ እንደሚልክና አገልጋዩም ለይስሐቅ የምትሆን ሚስት እንደሚያመጣለት ነበር (ቍ. 7)። ይሁንና እርሱ ታሪኩን እንደ ገና ሲናገር እግዚአብሔር መልአክ እንደሚልክና መልአኩም ጉዞውን ቀና በማድረግ ለይስሐቅ የምትሆን ሚስት ከራሱ ቤተ ሰብ እንደሚያመጣለት ጨምሮ ተናገረ። ተጨማሪ ገለጻው የእግዚአብሔርን ተአምራዊ ሥራ በመጀመሪያ ከተነገረው ይልቅ ይበልጥ ታላቅ አድርጎታል።

50-61 አገልጋዩ ታሪኩን ተናግሮ እንደ ጨረሰ ላባና ባቱኤል አገልጋዩ ርብቃን እንዲያገኛት መንገዱን ቀና ያደረገለት እግዚአብሔር መሆኑን ተረዱ። በመሆኑም በርካታ ምስክሮች ይህ ክንውን የእግዚአብሔር ሥራ መሆኑን መሰከሩ። ተራኪው (ቍ. 15-16)፣ አገልጋዩ (ቍ. 26-27) እንዲሁም ላባና ባቱኤል (ቍ. 50)። የመጨረሻዋ ምስክር ራሷ ርብቃ ናት፤ እርሷም የወንድሟንና የእናቷን ሐሳብ ወደ ጐን ትታ ከአገልጋዩ ጋር ወደ ይስሐቅ ተመለሰች። ለቀረበላት ጥያቄ የሰጠችው መልስ (ቍ. 58) በአብርሃም አምላክ ላይ ያላትን እምነት ይገልጻል (ከሩት 1፥16 ጋር ያነጻ)።

62-67 የርብቃ ቤተ ሰቦች ርብቃን ባርከው መስደዳቸው ይህ በረከት በ22፥17 ላይ እግዚአብሔር ለአብርሃም ከሰጠው በረከት ጋር ተመሳሳይ ነው። ይህም እግዚአብሔር ለይስሐቅ ሚስት ለመምረጥ ያደረገውን ብርቱ ጥንቃቄ ያሳያል። በእግዚአብሔር ዕቅድ ይኸው በረከት ለይስሐቅና ለሙሽራው ተሰጥቷል።

አገልጋዩ ልጃገረዷን ይዞ እንደ መጣ ይስሐቅ ለመጀመሪያ ጊዜ ከታሪኩ ተዋንያን አንዱ ሆነ። ሁለቱም ዐይናቸውን አንሥተው አሻግረው ተመለከቱ። ተራኪውና ተደራሲያኑ ይስሐቅና ርብቃ የተመለከቱት ማንን እንደ ሆነ ያውቃሉ፤ እነርሱ ራሳቸው ግን አያውቁም።

ቍጥር 66 ጸሓፊው ታሪኩን እስከ ምን ድረስ መናገርና የት ላይ ማቆም እንዳለበት በትክክል እንደሚያውቅ ያሳያል። “አገልጋዩ ያደረገውን ሁሉ ለይስሐቅ ነገረው” ይላል። የመጨረሻው ቃል እንደሚያሳየን በዕለት ተዕለት ሕይወት ውስጥ የእግዚአብሔር ምሪት በእርሱ ለሚታመኑ ሁሉ መልካም ነው። ይስሐቅ ርብቃን ሚስቱ አድርጎ ሲወስዳት ወዳዳት፤ ከእናቱ ሞት በኋላ በእርሷ ተጽናና። እንግዲህ ርብቃ በአብርሃም ዘሮች መሥመር ሣራን ተከተለች።

9. የአብርሃም መሞት (25፥1-11)

1-6 ታሪኩ ሣራ ከሞተች በኋላ አብርሃም ኬጡራ የተባለች ሚስት እንዳገባ ይገልጻል። የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ኬጡራን “ቁባቱ” ብሎ ስለሚጠራት (1ዜና 1፥32) አንዳንዶች በቍ. 6 ላይ ከተጠቀሱት “ቁባቶች” መካከል አንዷ ናት ብለው ይናገራሉ። ስለዚህ እነዚህ ልጆች ከአብርሃምና ከኬጡራ የተወለዱት ሣራ በሕይወት እያለች ነው። ምንም እንኳ በዜና መዋዕል ላይ ኬጡራ “ቁባት” ተብላ ብትጠራም፣ በዚህ ስፍራ ግን “ሚስት” ተብላ ተጠርታለች፤ ይህም ሣራ በሕይወት እያለች ኬጡራ ቁባት ብቻ ነበረች የሚለውን አባባል እንዳንቀበል ያግደናል።

ሣራ ከሞተች በኋላ የአብርሃም ሕይወት የተዘከረው እንደ ቀደመው ታሪክ ያረጀ ሰው ሳይሆን ይበልጥ የተነቃቃ ሰው ሆኖ ነው። የብዙ ልጆች አባት በመሆኑ ዘሩ መባረክ ቀጠለ። ይሁን እንጂ የተስፋው ወራሽ ይስሐቅ ብቻ ሆነ።

7-10 ስለ አብርሃም መሞት እምብዛም ትኩረት አለመሰጠቱ ያስደንቃል። ምን ያህል ዘመን እንደ ኖረ መገለጹ ከአባቶቹ ጋር ያስተሳስረዋል (ከ11፥32 ጋር ያነጻ)። አብርሃም “ዕድሜ ጠግቦ” መሞቱ በ15፥15 ላይ እግዚአብሔር የተናገረውን ቃል ያስታውሰናል። የአብርሃም ዕድሜ ጠግቦ መሞት (“በመልካም ሽምግልና መሞት”) ከያዕቆብ ዐጭርና ችግር ከበዛበት (“ጥቂትና ክፉ”) ዘመን ጋር ተነጻጽሯል (47፥9)። እንግዲህ ይህ ታሪክ በመጽሐፉ የመጀመሪያ ምዕራፎች ላይ የተወሣውን የመልካምና የክፉ ጭብጥ በማንሣት እስከ መጨረሻው ይዞት ይዘልቃል (ከ50፥20 ጋር ያነጻ)። የመጨረሻው የአብርሃም መኖሪያ ስፍራ በሕጋዊ መንገድ ከኬጢያዊው ከኤፍሮን በገዛው በተስፋዪቱ ምድር ሆነ።

11 በይስሐቅ ሕይወት ውስጥ “የበረከትን” ጭብጥ የሚያነሡ በጣም ጥቂት ታሪኮች አሉ። አብዛኞቹን ተጐናጽነው የምናገኛቸው በምዕ. 26 ላይ ነው። በዚህ ዐጭር መግለጫ ላይ ትልቅ ስፍራ የሚሰጠው እግዚአብሔር ይስሐቅን መባረኩ ነው፤ ይህ የይስሐቅ መባረክ በእግዚአብሔር መለኮታዊ ዕቅድ ውስጥ ጽኑ መሠረት አለው (17፥21)።

፫. የእስማኤል ታሪክ (25፥12-18)

12-18 የይስሐቅ ታሪክ የሚጀምረው ስለ እስማኤል ነገድ መግለጫ በመስጠት ነው (ቊ. 11)። መግለጫው የዐሥራ ሁለቱን የእስማኤል ነገድ መሪዎች ትውልድ ሐረግ፣ የእስማኤልን የሕይወት ዘመን ዘገባና የሞቱን ዘገባ ይዟል። ዐሥራ ሁለት ቍጥር እንደ ገና የተጠቀሰው ሆነ ተብሎ ሲሆን እነዚህ ግለሰቦች የዐዲሱና የተለየው ሕዝብ መሥራቾች መሆናቸውን ለመግለጽ ነው (የ22፥20 ማብ ይመ.፤ ከ17፥20 ጋር ያነጻ)። 17፥20 ላይ ስለ እስማኤል መባረክ አንድም ዘገባ አናነብም፤ ከዚህ በኋላም በዘፍጥረት ውስጥ ስለ እርሱ ምንም አንሰማም። ይሁን እንጂ የእስማኤል ዘሮች በዘፍጥረት ታሪክ ውስጥ የራሳቸውን ሚና መጫወት ቀጥለዋል (28፥9፤ 36፥3፤ 37፥27-28፤ 39፥1)።

፬. የይስሐቅ ታሪክ (25፥19-35፥29)

ሀ. የያዕቆብና የዔሳው መወለድ (25፥19-28)

19 “የአብርሃም ልጅ የይስሐቅ ትውልድ” የሚለው ተለውጦ ስለ ራሱ ስለ ይስሐቅ ሳይሆን ስለ ልጆቹ መነገር ጀመረ። ምንም እንኳ ከአብርሃም ጋር የሚያያይዝ ዋና ነገር ቢሆንም፣ እንደ አንድ ግለ ሰብ ገጸ ባሕርይ ለይስሐቅ የተሰጠው ስፍራ ጥቂት ነው (ነገር ግን ከምዕ. 26 ጋር ያነጻ)።

20-28 እንደ ዔሳው ሁሉ ይስሐቅም (26፥34) ርብቃን ሚስቱ አድርጎ ሲወስዳት ዕድሜው አርባ ነበር። እንደ ሣራ ሁሉ (11፥30) ርብቃም መካን ነበረች። እንደ አብርሃም ሁሉ (20፥17) ይስሐቅም ለሚስቱ ጸለየ፤ እግዚአብሔርም ጸሎቱን ሰማ፤ እርሷም ሁለት ወንድ ልጆች ወለደች። የሣራና የርብቃ መካንነት፣ እንዲሁም የራሔልና (29፥31) እና የልያ (29፥35) በእጅጉ የሚያሳየው በተመረጠው በአብርሃም ዘር አማካይነት የተስፋው በረከት የሚፈጸመው በሰዎች ጥረት አለመሆኑን ነው። የተስፋው ቃል ፍጻሜ በእያንዳንዱ ወሳኝ ርምጃ የእግዚአብሔርን ክንድ ይሻል።

የዘፍጥረት ማእከላዊ ጭብጥ የሆነው (በሁለት ወንድማማቾች መካከል የሚደረግ ትግል) እዚህም ላይ በርብቃ ማሕፀን ውስጥ ሲከናወን ይታያል። በወንድማማቾች መካከል ትግሉ የጀመረው በቃየንና በአቤል ሲሆን በመጽሐፉ ውስጥ እስከ መጨረሻው ዘልቋል (9፥20-27፤ 13፥7-12፤ 21፥9፤ 29-31፤ 37-50)። ምናልባት ይህ የተከሠተው ከመጀመሪያው ፍርድ የነተሣ ሊሆን ይችላል (3፥15)። እዚህ ላይ ለመግለጽ የተፈለገው፣ የእግዚአብሔር ፈቃድ እንዲፈጸም ትግሉ የግድ መኖር አለበት የሚለውን ሳይሆን፣ ትግሉ ቢኖርም የእግዚአብሔር ፈቃድ ግን ይፈጸማል የሚለውን ነው።

ሌላው ዐቢይ ጭብጥ ታላቁ “ለታናሹ አገልጋይ ይሆናል” የሚለው ነው። ከምዕራፍ 4 ጀምሮ ታሪኩ እግዚአብሔር ፈቃዱን የሚፈጽምባቸውንና በረከቱን እውን የሚያደርግባቸውን ታናናሾችና ደካማ ሰዎች ሲመርጥና ሲደግፍ እንደ ነበር ይገልጽልናል (ከ4፥1-5፡ 26-5፥8፤ 17፥18-19፤ 29፥18፤ 37፥3፤ 49፥8)። በረከቱ እንደ መብት ይገባኛል ተብሎ የሚወሰድ ሳይሆን በእግዚአብሔር ጸጋ ብቻ የሚገኝ ነው (ሚል 1፥1-5፤ ሮሜ 9፥10-13)።

ለ. ብኵርናን መሸጥ (25፥29-34)

29-34 ዔሳው ብኵርናውን ስለ መተዉ የሚያወሣው ታሪክ እግዚአብሔር በዔሳው ፈንታ ያዕቆብን ሲመርጥ የሁለቱንም ፈቃድ አለመጋፋቱን ከሚያሳዩት መካከል አንዱ ነው። ዔሳው ብኵርናውን አቃለላት፤ ያዕቆብ ግን ይህን ለማግኘት ተጋደለ። ምንም እንኳ ዔሳው የብኵርና መብት ቢኖረውም፣ አንዲት ሳህን ወጥ ስለ በለጠችበት እንደ ትልቅ ነገር አልቈጠረውም። በመሆኑም ዔሳው በእግዚአብሔር ፊት ብኵርናውን፣ ከዚህም የተነሣ በረከቱን ሲያጣ በእርሱ ላይ የተፈጸመ አንድም ኢፍትሓዊ ድርጊት የለም።

ሐ. ይስሐቅና አቤሜሌክ (26፥1-35)

በዚህ ምዕራፍና በአብርሃም ሕይወት ዙሪያ በተፈጸሙ ሁኔቶች መካከል በርካታ ምስስሎች አሉ (12፥10-20፤ 20፥1-18)። እያንዳንዱ የይስሐቅ ታሪክ ከአብርሃም ሕይወት ጋር ይጐዳኛል። የምዕራፉ ዐጭርነት ራሱ መላው የይስሐቅ ሕይወት የአብርሃምን ሕይወት እንደ ገና እየተረከልን እንደ ሆነ ያሳያል። እዚህ ላይ መልእክቱ የእግዚአብሔርን ዘላቂ ታማኝነት ለመግለጽ ነው።

1-5 ይህ የአሁኑ ረኃብ አብርሃምን ወደ ግብፅ እንዲሰደድ ያደረገው ረኃብ አይደለም (12፥10)። በመጀመሪያ ይስሐቅ አቤሜሌክ ወደሚኖርበት ወደ ጌራራ እንደ ሄደ ተነግሮን ነበር፤ ይሁንና በቊ. 2 ላይ ይስሐቅ ባየው ሕልም ወደ ግብፅ እየሄደ ነበር። ወደ ግብፅ እንዳይሄድ የተከለከለው ለምን እንደ ሆነ አልተገለጸም፤ በግልጽ የተነገረው እግዚአብሔር በሚያሳየው ምድር እንዲኖር ነው። ይህ የእግዚአብሔር ማስጠንቀቂያ በረከቱን እንደ ገና የሚያስታውስ ነው። በረኃቡ ዘመን እግዚአብሔር ከይስሐቅ ጋር እንደሚሆን፣ እንደሚባርከውና ለአባቱ ለአብርሃም ቃል የገባቸውን ነገሮች በሙሉ እንደሚፈጽምለት ተስፋ ሰጠው። በመሠረቱ ለአብርሃም የተሰጠው ተስፋ ለይስሐቅም ተሰጥቷል። ዘሩ ይበዛል (12፥2)፤ ምድሪቱ የእርሱ ትሆናለች (12፥7)፤ የምድር ሕዝቦች ሁሉ በእርሱ ይባረካሉ (12፥3)።

ከዚያም እግዚአብሔር አንድ አስደናቂ ቃል ተናገረ፡- አብርሃም፣ “ቃሌን ሰምቶ ድንጋጌዬን፣ ትእዛዜን፣ ሥርዐቴንና ሕጌን” ጠብቋል (ከዘዳ 11፥1 ጋር ያነጻ)። አብርሃም ሕጉን ያውቅ ነበር? የሚያውቅ ከሆነ እንዴት ሊያውቅ ቻለ? ሕጉን የማያውቅ ከሆነ እግዚአብሔር ለማለት የፈለገው ምንድን ነው? አብርሃም ብዙ ጊዜ የኖረው በሕጉ በተለይም በዘዳግም ላይ በተጠቀሰው መሠረት ነው። ይሁንና ስለ ሕጉ የሚያውቀው አንዳች ነገር የለም። ለምሳሌ በምዕ. 14 ላይ የአብርሃም ተግባር የዘዳ 20 ሕግን የተከተለ ነበር፤ ሕጉን ከልቡ ይታዘዝ ነበር (ከዘዳ 30፥6፤ ከኤር 31፥33 ጋር ያነጻ)። የእውነተኛ መታዘዝ ምሳሌ ነው። እንግዲህ በእምነት የኖረው አብርሃም ሕጉን እንደ ጠበቀ ሰው ሊነገርለት ይችላል።

6-11 በዚህ ክፍል በአብርሃምና በይስሐቅ መካከል በርካታ ምስስሎች አሉ። አብርሃም “በጌራራ እንደ ተቀመጠ” ሁሉ (20፥1)፣ ይስሐቅም እንዲሁ አደረገ። አብርሃም በአንድ ወቅት ሚስቱን ሣራን “እኅቴ” ናት እንዳለ ሁሉ (20፥2)፣ ይስሐቅም ርብቃን እንዲሁ ብሏት ነበር። አብርሃም በሕዝቡ ላይ ታላቅ ውርደት ሊያመጣ ሲል በፍልስጥኤሙ ንጉሥ በአቤሜሌክ እንደ ተገሠጸ ሁሉ (20፥9)፣ ይስሐቅም እንዲሁ ተገሥጿል። እነዚህ ምስስሎች በአጋጣሚ እንደ ተፈጸሙ ተደርጎ ሊወሰዱ አይገባም። ባንጻሩም ይህ ነገር በአብርሃም ሕይወት በተፈጸመ ጊዜ፣ አቢሜሌክ የአብርሃምን ሚስት እንዳይደፍራት ያስጠነቀቀው እግዚአብሔር አይደለም (20፥6)፤ አቢሜሌክ ራሱ ማንም ሰው የይስሐቅን ሚስት እንዳይደፍራት ከለከለ። የአብርሃምን ሚስት የደፈረ በሞት ይቀጣል በማለት ሚስቱን የጠበቀው እግዚአብሔር አይደለም (20፥7)፤ አቢሜሌክ ይስሐቅን ወይም ሚስቱን ያወከ በርግጥ “በሞት ይቀጣል” የሚል ትእዛዝ አወጣ።

ቀደም ሲል አቤሜሌክ “ቅን ልቦና” ያለው ሰው እንደ ሆነ ቢገለጽም (20፥6)፣ በምዕ. 26 ተግባሩ ልቡ ቅን ሰው እንደ ሆነ ያሳያል። አቤሜሌክ በሕልም ማስጠንቀቂያ ሊሰጠው አላስፈለገውም። ለእርሱ አሁን የሚያስፈልገው ርብቃ የይስሐቅ እኅት እንዳልሆነች ማወቁ ነው፤ ይህን ማወቁ ለእርሱ በቂ ነው፤ ምክንያቱም በሕዝቡ ላይ ታላቅ ውርደት (አመት፤ “በደል”) እንዳይመጣባቸው ያስጠነቅቀዋል። እዚህ ላይ ታሪኩ የተነገረለት የፍልስጥኤም ንጉሥ ጻድቅ ወይም ሃይማኖተኛ አሕዛብ ነበር፤ እርሱም ቅን የሆነውን ነገር ያደርግ ነበር። ባንጻሩም የይስሐቅ ጽድቅ ከዚህ ሰው ያነሰ ነበር። ይህ በሰፊው የሚያሳየን የኪዳኑን ሕዝብ ሕይወት ነው። በደለኛና ፍርድ የሚገባቸው ሆነው ሳሉ ጻድቅና ከእግዚአብሔር ጋር ኪዳን ለመግባት የተመረጡ ሆኑ (21፥27፤ 32፤ 26፥28)። ፍልስጥኤማውያን የውሃውን ጕድጓድ በመድፈን ይስሐቅን በየጊዜው ያስቸግሩት ነበር (ቊ. 14-22)።

12-13 አብርሃም በአሕዛብ መካከል እንደ መጻተኛ ሲኖር እንደ በለጸገ ሁሉ (12፥16፤ 20፥14)፣ ይስሐቅም ከአቤሜሌክ ጋር እንደ መጻተኛ ሲኖር በለጸገ። የይስሐቅ ብልጽግና ምንጭ እግዚአብሔር ነው፡- “እግዚአብሔርም ባረከለት”። ይስሐቅ ሲባረክ ስናይ፣ ይህ ለሁለተኛ ጊዜ መሆኑ ነው፤ ይህም በይስሐቅ ብልጽግናና በ12፥2 ላይ እግዚአብሔር ለአብርሃም በሰጠው ተስፋ መካከል ትስስር መኖሩን በአጽንዖት ለማሳየት ነው። እግዚአብሔር ለአብርሃም የሰጠው ተስፋ በይስሐቅ ተፈጸመ።

14-22 የአብርሃም ብልጽግና በእርሱና በሎጥ እረኞች መካከል ጥል እንደ ፈጠረ ሁሉ (13፥5-7)፣ የይስሐቅም ሀብት ፍልስጥኤማውያንን አስቈጣ። “የጌራራ እረኞች . . . ከይስሐቅ እረኞች ጋር ጠብ አነሡ” (ቊ. 20) የሚለው አረፍተ ነገር በአብራምና በሎጥ እረኞች መካከል ከተነሣው ጠብ ታሪክ ጋር

ይጐዳኛል (13፥7)። ለውሃው ጕድጓድ የተሰጠው ስም (“ርኆቦት”) እንደሚያሳየው፣ ይስሐቅ ከፍልስጥኤማውያን እየራቀና ዐዲስ የውሃ ጕድጓድ እየቈፈረ በሄደ ቍጥር ጠቡ እየበረደና መፍትሒም እያገኘ መጣ። በርኆቦት ጠቡ ከተወገደ በኋላ “እኛም በምድር ላይ እንበዛለን” አሉ (ከ 1፥28 ጋር ያነጻ)።

23-25 አብርሃም ከሎጥ ከተለየ በኋላ እግዚአብሔር ተገልጦ ምድሪቱንና ብዙ ሀብት እንደሚሰጠው ተስፋ እንደ ገባለት ሁሉ (13፥14-17)፣ አሁንም ይስሐቅ ወደ ቤርሳቤህ ከተመለሰ በኋላ እግዚአብሔር ተገልጦ ተስፋውን ዐደሰለት። ለሦስተኛ ጊዜ እግዚአብሔር ይስሐቅን እንደሚባርከው ተነገረ (ቍ. 2፣ 12)። እንደ አባቱ ሁሉ (12፥7፤ 13፥3-4)፣ ይስሐቅም መሠዊያ በመሥራትና ለእግዚአብሔር በመስገድ መልስ ሰጠ።

26-31 ቀደም ሲል አቤሜሌክ እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር እንዳለ በመረዳቱ (21፥22) ከእርሱ ጋር ኪዳን ለመግባት ፈልጎ ነበር። ልክ እንዲሁ አቤሜሌክ እግዚአብሔር ከይስሐቅ ጋር እንዳለ ስለ ተረዳ ከእርሱ ጋር ኪዳን ለመግባት ፈለገ። እንደ አብርሃም ሁሉ፣ ይስሐቅም ከእርሱ ጋር ለመኖር ለሚፈልጉ ሁሉ የበረከት ምንጭ ነበር። እንደ አብርሃም ሁሉ ይስሐቅም በእግዚአብሔር በመታመን ከጎረቤቶቹ ጋር “በሰላም” ኖረ።

32-33 እዚህ ላይ ስለ ይስሐቅ የተነገረው የመጨረሻው ታሪክ የሚያበቃው ይስሐቅ ዐዲስ የውሃ ጕድጓድ እንዳገኘና ከጎረቤቶቹ ጋር በሰላም ለመኖር መሐላ የፈጸመበትን ቀን (አመት፣ “በዚያኑ ዕለት”) በመግለጽ ነው። በዚህም ጸሓፊው “ቤርሳቤህ” (በቁሙ የሰባት/የመሐላ ጕድጓድ 21፥31) የሚለውን የከተማዪቱን ስም “ከመሐላው” (አመት፣ “በመካከላቸው መሐላ ፈጸሙ”) ጋር ያያይዘዋል።

34-35 በመጀመሪያ ሲታይ ዔሳው ከሁለት ኬጢያውያት ሴቶች ጋር የፈጸመው ጋብቻ እምብዛም ቦታ የሚሰጠው አይደለም። ይሁንና የምዕ. 27 መግቢያ በመሆኑ በዚያ ምዕራፍ ላይ የተሰየ አሉታዊ ጥላ ያጠላል። ያዕቆብ አታሎ በረከቱን እንደ ወሰደ ከመነገሩ በፊት፣ በረከቱ የተወሰደበት ዔሳው ኬጢያውያት ሴቶችን በማግባቱ ለይስሐቅና ለርብቃ ሐዘን ምክንያት መሆናቸው ተነግሮናል። እነዚህ ቍጥሮችና ቍ. 29-34 ለምዕ. 27 ሁነት ማለትም ለያዕቆብ መባረክ እንደ ዳራ ያገለግላሉ። ይህ መግቢያ የያዕቆብንና የርብቃን የብልጣ ብልጥነት ዘዴ መረዳት እንድንችል ሁኔታውን ከማመቻቸቱም በላይ፣ ዔሳው በረከቱን ለመውረስ የተገባ ሰው እንዳልሆነ ጠቁም ያደርጋል።

መ. የተሰረቀው በረከት (27፥1-40)

1-26 ስለ ይስሐቅ “በረከት” የሚናገረው ይህ ታሪክ፣ ታሪኩን ልብ አንጠልጥል ለሚያደርጉና የያዕቆብን አታላይነት በተጨባጭ ለሚያወሡ ዘገባዎች ልዩ ትኩረት ሰጥቷል። በመሆኑም ለያዕቆብ ይህ ስም (ትርጕሙ አታላይ ማለት ነው፤ ቍ. 36) መመረጡ ተገቢ ነው። ይስሐቅ እጅግ ከማርጀቱና ዐይነ ስውርም ከመሆኑ የተነሣ ሁለቱን ልጆቹን ለመለየት ከማይችልበት ደረጃ እንደ ደረሰ ተገልጿል። ይህ የተደረገው ምናልባት በያዕቆብ ላይ ሊደርስ የሚችለውን ብርቱ ወቀሣ ለማለዘብ ሳይሆን አይቀርም። ይስሐቅ በረከቱን ከመስጠቱ በፊት ምግብ እንዲቀርብለት መወትወቱ ዔሳው ብኵርናውን ለአንዲት ሳሕን ወጥ ብሎ መለወጡን ያስታውሰናል፤ ይህም ይስሐቅና ዔሳው ተመሳሳይ ሚና ሲጫወቱ ያሳየናል። የይስሐቅ ዐይነ ስውርነት ታሪኩን ይበልጥ ተአማኒና ልብ አንጠልጥል አድርጎታል። በመሆኑም የታሪኩ ሁነቶች እውነተኛና ልብ አንጠልጥልነታቸውም ትክክለኛ ነው። ልባንጠልጥልነቱ እስከ መጨረሻው ዘልቋል፤ ዔሳው ከዐደኑ ተመልሶ የመጣው ያዕቆብ “ገና ከአባቱ ዘንድ ሳይወጣ ወዲያውኑ” (ቍ. 30) ነው። እስከ መጨረሻው ድረስ ዕቅዱ አደጋ ተጋርጦበት ነበር።

27-29 የያዕቆብ ስልት ግብ በረከቱን ከይስሐቅ ነጥቆ ለመውሰድ ነበር። ምንም እንኳ ነገሩ ባያሳምነውም፣ በመጨረሻ ግን ይስሐቅ ያዕቆብን ባረከው። ይህ “የበረከት” ጭብጥ በዚህ ታሪክና ከዚህ በፊትና ከዚህ በኋላ ባሉት ታሪኮች መካከል ትስስር እንዳለ ያሳያል። ለአብርሃም የተሰጠው ተስፋ (12፥2-3) በበረከቱ የመጨረሻ ቃሎች ላይ ተወሥቷል፤ ደግሞም የያዕቆብ በረከት ከይሁዳ ቤት ንጉሥ እንደሚወጣ ያዕቆብ የተናገረውን ትንቢት ያስተጋባል (49፥8)። በመሆኑም የያዕቆብ ቃሎች የአብርሃም ዘር እንደሚባረክ የተነገረውን ተስፋ የሚያጐለብቱ ወሳኝ ድልድይ ናቸው። እንዲሁም የያዕቆብ የድፍረት ዕቅድ የአብርሃም ዘር እንደሚባረክ የተነገረውን ተስፋ ከይሁዳ ቤት ንጉሥ እንደሚወጣ ከተነገረው ጋር የሚያያይዝ ሰንሰለት ነው።

30-40 የያዕቆብ በረከት በግልባጩ የሚያሳየን የዔሳውን ሐዘንና ቍጣ ነው። የቀረበውም፣ አሳዛኝ ሰውና የደፋር ወንድሙ ሰለባ ሆኖ ነው። በረከቱን እንደሚያጣ ሲሰማ፣ ሐዘኑ በ25፥21-34 ላይ የተወሣውን ሁነትና ብኵርናውን እንዳጣ ያስታውሳናል። ዔሳው ሁሉንም ነገር ዐጣ፤ ያዕቆብ ግን ሁሉንም አገኘ። በዚህ ታሪክ ውስጥ ያዕቆብ ለሁለተኛ ጊዜ የበረከቱን ዋና ነጥቦች በድጋሚ ያነሣቸዋል፤ ይህም ዔሳውን ሳይሆን ያዕቆብን እንደ ባረከ በአጽንዖት ይገልጻል። በመጨረሻም፣ ይስሐቅ እያለቀሰ የዔሳውን አቤቱታ ለመመለስ ሲል ለያዕቆብ የሰጠውን በረከት ለሦስተኛ ጊዜ ዋና ዋና ነጥቦቹን በመድገም ተናገረ፦ “ለወንድምህም ትገዛለህ”። እነዚህ በድጋሚ የተናገራቸው ነገሮች ያጣውን በረከት መልሶ ሊያገኘው እንደማይችልና በረከቱ ራሱ ከመፈጸም እንደማይገታ አበክረው ይገልጻሉ።

ሠ. ያዕቆብ ከቤርሳቤህ ሸሸ (27፥41-28፥5)

27፥41-28፥5 የያዕቆብ ዕቅድ (የብልጣ ብልጥነት ዘዴ) ይስሐቅ ለዔሳው ያሰበውን በረከት ብቻ ሳይሆን ያስገኘለት፣ ሚስት ፍለጋ ወደ ላባ ቤት እንዲሄድ አጋጣሚ ፈጥሮለታል። በዚህ ታሪክ መደምደሚያ ላይ ዔሳው የተሳለልን፦ መራር፣ ተንኳሽ ወንድምና ልጅ ተደርጎ ነው። ያዕቆብን ለመግደልና ያጣውን ብኵርናና በረከት በጎይል ለማግኘት አሜረ። ርብቃ ግን ሤራውን አክሽፈችበት፤ ይስሐቅም ያዕቆብን ሚስት ፍለጋ ወደ አገሯ እንዲሰደው አደረገች። በብዙዎቹ የዘፍጥረት ታሪኮች ላይ እንደምናየው፣ ተስይቶ ለሚሄደው ያዕቆብ ይስሐቅ የተናገረው የበረከት ቃል የታሪኩን የመጨረሻ ውጤት ያስተጋባል፤ ያዕቆብ ላባን ለመተካት “ለጥቂት ቀን” ይሄዳል፤ የዔሳውም ቍጣ ይበርዳል (ምዕ. 33 ይመ)፤ ያዕቆብም ሚስት አግኝቶ ታላቅ ሕዝብ ሆኖ ይመለሳል። በዚህ በይስሐቅ የስንብት በረከት ውስጥ የቀደመው ታሪክ ማእከላዊ ጭብጥ ለመጨረሻ ጊዜ ተወሥቶ እናገኛለን፤ የአብርሃም በረከት በያዕቆብ ቤት ላይ ይሆናል። አሁን የአብርሃምና የይስሐቅ ተስፋዎች የያዕቆብ ተስፋዎች ሆኑ።

ረ. የዔሳው መራርነት (28፥6-9)

6-9 በዚህ ታሪክ ላይ የቀረበው የዔሳው የመጨረሻ ዘገባ ዔሳውን በወላጆቹ ላይ ያለውን ጥላቻ ሆነ ብሎ ባለመታዘዝ የገለጠ መራር ልጅ አድርጎታል። ዔሳው የእስማኤልን ሴት ልጅ ማግባቱ ለአብርሃም የተሰጠው ተስፋ የተወሰነው በሰዎች ፈቃድ ሳይሆን በእግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑን ያስታውሰናል። የሁለቱ “ታላቅ” ልጆች ቤተ ሰቦች (የእስማኤልና የዔሳው) በጋብቻ ቢተሳሰሩም፣ ለአብርሃም የተሰጠውን ተስፋ በረከት ግን ሁለቱም አላገኙም። “የታናሽ” ልጆቹ ቤተ ሰቦች (የይስሐቅና የያዕቆብ) ግን አገኙ።

ሰ. ያዕቆብ በቤቴል (28፥10-22)

10-22 እንደ አብርሃም ሁሉ፣ ያዕቆብም (ምዕ. 15) የተስፋውን በረከት ማረጋገጫ ተኝቶ ሳለ ተቀበለ። አብርሃም የእግዚአብሔርን ቃል የተቀበለው “በራእይ” ነው (15፥1)፤ ያዕቆብ ደግሞ እግዚአብሔርን በሕልም አየ። በሁለቱም ጊዜ የተስፋው ኪዳን እንደሚመሠረት መለኮታዊ ማረጋገጫ ተሰጥቷል። በተመሳሳይ ሁኔታ ሁለቱም ምዕራፎች የአብርሃም ዘሮች ወደ “ምርኮ” እንደሚጋዙና ከዚያም እንደሚመለሱ ይናገራሉ። የአብርሃም ራእይ የእግዚአብሔር ሕዝብ በግብፅ እንደ መጻተኛ ሲኖርና እግዚአብሔር ከዚያ እንደሚታደገው ያወሣል። የያዕቆብ ሕልም ደግሞ እርሱ ራሱ በካራን እንደ መጻተኛ ሲኖርና እግዚአብሔርም ለአብርሃም ተስፋ ወደ ሰጠው ምድር እንደሚመልሰው ያወሳል። ሁለቱም አበክረው የሚያስገነዝቡን እግዚአብሔር ከቶ እንደማይተዋቸውና ወደ ምድራቸውም እንደሚመልሳቸው ነው።

በቍጥር 15 ላይ እግዚአብሔር “እኔ ከአንተ ጋር ነኝ፤ በምትሄድበት ስፍራ ሁሉ እጠብቅሃለሁ፤ ወደዚችም ምድር እመልስሃለሁ” በማለት የተናገረው ቃል የታሪኩን ሁነቶች የሚገራ ዐቢይ መርሕ ሆኗል። ስለዚህ ያዕቆብ ከብዙ ዓመት በኋላ ከላባ ቤት ሲመለስ፣ እግዚአብሔር እንደ ገና እርሱን ወደ ባረከበትና ሊሰጠውም ቃል ወደ ገባለት ምድር ማለትም ወደ ቤቴል ተመለሰ። ይህም እግዚአብሔር አስቀድሞ ለአብርሃም ሊሰጠው ቃል የገባለት ምድር ነው (35፥12)። ከዚህም በተጨማሪ እግዚአብሔር የያዕቆብን ዘር እንደሚያበዛው ተስፋውን አረጋገጠለት (35፥11)። ያዕቆብ ጉዞውን ሊጀምር ሲል “ሐውልት” እንዳቆመና ያንንም ስፍራ ቤቴል ብሎ እንደ ጠራው ሁሉ፣ ሲመለስም ሌላ “ሐውልት” አቁሞ ስፍራውን ቤቴል ብሎ ጠራው (35፥14-15)። በያዕቆብ ታሪክ መጀመሪያም ሆነ መጨረሻ ያዕቆብ በሚያደርገው ነገር እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር እንደ ነበርና እግዚአብሔርም በተስፋ ቃሉ የታመነ እንደ ሆነ እንገነዘባለን።

ሸ. ያዕቆብና ራሔል (29፥1-14ሀ)

1-14ሀ ከዚህ ስለ ያዕቆብ መጻተኛነት ከሚያወሣው ዘገባ ሳንወጣ ታሪኩ፣ “ያዕቆብም ጕዞውን ቀጠለ፤ የምሥራቅም ሰዎች ወደሚኖሩበት ምድር ደረሰ” በሚሉት ቃሎች ይጀምራል። ያዕቆብ ሚስት ፍለጋ ያደረገው ጕዞ የአብርሃም አገልጋይ ለይስሐቅ ሚስት ፍለጋ ካደረገው ጕዞ ጋር ተመሳሳይ ነው። በምዕራፍ 24 ላይ ታሪኩን የሚመራው የአገልጋዩ ቃል ሲሆን፣ ለይስሐቅ የምትሆነውን ትክክለኛ ሴት እንዲያገኝ መንገዱን ቀና ያደረገለት እግዚአብሔር ነው። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ያዕቆብ ምንም ሲናገር አይታይም ማለት ይቻላል። የእግዚአብሔርን ምሪትም ሆነ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር እንደሚሆን የሰጠውን ተስፋ ሲያሰላስል አናየውም (28፥15)። የእግዚአብሔርን ርዳታና ምሪት ታሪክ የሚናገረው የያዕቆብ ተግባር እንጂ ቃሉ አይደለም። በምዕራፍ 24 ላይ እንደምናገኘው አገልጋይ ሁሉ፣ እግዚአብሔር ራሔል በጎጆን ውሃ ወደምታጠጣበት ጕድጓድ ያዕቆብን መራው።

የውሃውን ጕድጓድ ስለ ከደነው ድንጋይና በዚያ ስለ ነበሩት እረኞች ቀጥር የተሰጠው ገለጻ ያዕቆብ ብርቱ ነገር እንደሚያደርግ ፍንጭ ይሰጣል። እረኞቹ በሙሉ ሲመጡ ነው ሰዎቹ ከጕድጓዱ ላይ ድንጋዩን ማንሣትና በጎቹን ማጠጣት የሚችሉት፤ ምክንያቱም ድንጋዩ ትልቅ ነው። ያዕቆብ ራሔልን ሲያይና እረኞቹም የላባ ልጅ እንደ ሆነች ሲያውቁ፣ ድንጋዩን አንከባሎ በጎቿን ውሃ አጠጣለት። ከዚያም ያዕቆብ ስሜቱን መቈጣጠር ስላልቻለ ራሔልን ሳማት፤ ድምፁንም ከፍ አድርጎ አለቀሰ። በዚህ ሁኔታ ውስጥ ያዕቆብ የእግዚአብሔርን እጅ በግልጽ አይቷል (ከ24፥27 ጋር ያነጻ)። የያዕቆብ አካላዊ ጥንካሬ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር እንደ ነበርና ተስፋውንም እንዳላጠፈ ይበልጥ ያረጋግጣል (28፥15፤ ከ24፥27 ጋር ያነጻ)።

ቀ. የያዕቆብ ጋብቻ (29፥14ለ-30)

14ለ-30 ያዕቆብ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲታለል እናያለን። ላባ የገባለትን ቃል ሁሉ አጠፈ። በረከቱን በሚወስድበት ጊዜ (ምዕ. 27)፣ ያዕቆብ የታላቁን ለታናሹ ለመለወጥ ችሎ ነበር፤ ላባ ደግሞ የታናሿን ለታላቋ በመለወጥ ማታለሉን ቀለበሰው። ያዕቆብ ያገኘው የእጁን ነው። ያዕቆብ ሌላ ሰባት ዓመት ላባን ለማገልገል የተፈረደበት በዔሳው ላይ ለፈጸመው በደል እንደ ካሣ ሳይሆን አልቀረም።

ያዕቆብ እጅግ ተቈጣ። ነገር ግን ላባ በቀ. 26 ላይ የሰጠው መልስ የሚናገረውን አሳጣው። ከዚህ በኋላ ታሪኩ ያዕቆብ የተባለውን ነገር ሁሉ ለማድረግ እንደ ተስማማ ይገልጻል። ለእርሱ ግልጽ ባይሆንም፣ የላባ ንግግር ያዕቆብን ለዚህ ሁሉ ያበቃው ምን እንደ ሆነ ቅልብጭ አድርጎ ይገልጻል። ያዕቆብ የቀድሞው ታሪኩ ሊለቀው አልቻለም፤ መዘዙን ከመቀበልና ላባን ሌላ ሰባት ዓመት ከማገልገል ውጭ ምንም ማድረግ አይችልም። በመጀመሪያ ስናየው የያዕቆብ ጕዞ በርግጥ ርብቃ የተከተለችውን መንገድ ያስተጋባል (27፥44)። በመሆኑም ያዕቆብ ላባን ሰባት ዓመት እንዳገለገለው ብናነብ ምንም አያስደንቅም፤ ምክንያቱም ዘመኖቹ እንደ “ጥቂት ቀን” ሊመስሉን ይችላሉ። ይሁን እንጂ ላባ ስላታለለው በርብቃ “ጥቂት ቀን” ላይ ሌላ ሰባት ዓመት ተጨመረበት፤ በዚህም የያዕቆብና የርብቃ ዕቅድ መተርተር ጀመረ።

በ. የያዕቆብ ልጆች መወለድ (29፥31-30፥24)

29፥31-30፥24 በአንድ በኩል ይህ የአብርሃምን ታሪክ መጀመሪያ ያስታውሰናል (11፡30)፤ ትልቁም ችግር ምን እንደ ሆነ ተነገረ። እግዚአብሔር የልያን ማሕፀን ከፈተ፤ ራሔል ግን መካን ነበረች። ቀደም ባለው ምዕራፍ ላይ እግዚአብሔር የያዕቆብን ዘር ከምድር አሸዋ ይልቅ እንደሚያበዛው ተስፋ ሰጥቶ ነበር። በዚህ ጊዜ ግን የያዕቆብ ሚስት ለመሆን የተመረጠችው ራሔል መካን ነበረች፤ ይህም የራሱ የእግዚአብሔር ሥራ ይመስላል። እናም የያዕቆብ ዕቅድ ችግር ገጠመው፤ ራሔልን ሚስቱ አድርጎ ለመውሰድ ዐቅዶ ነበር፤ ይሁንና እግዚአብሔር ልያን እንዲወስድ ነው የፈለገው። ያዕቆብ ቤተ ሰቡን ለመመሥረት የተነሣው በራሔል አማካይነት ነበር፤ እርሷ ግን መካን ነበረች፤ እግዚአብሔርም የልያን ማሕፀን ከፈተ።

እስከ አሁን ድረስ የዘለቀው የያዕቆብ ዘዴ መንኰታኰት ጀመረ። የእግዚአብሔርን ዕቅድ እውን ለማድረግ ዘዴ ብቻውን በቂ አይደለም። የእግዚአብሔር በረከት እንዲፈጸም ያዕቆብ በእግዚአብሔር መታመን አለበት። በያዕቆብና በወለዷቸው ልጆች ምክንያት በሁለቱ ሚስቶች መካከል የተቀሰቀሰው ጥል ከዚህ በኋላ ለምናገኘው ታሪክ እንደ መሠረት ነው። ከልያ ልጆች መካከል አንዱ ይሁዳ ሲሆን ራሔል ደግሞ የዮሴፍ እናት ነበረች።

ምንም እንኳ ዐሥራ ሁለቱም ልጆች አስፈላጊ ቢሆኑም፣ ከዚህ በኋላ በምናገኘው ታሪክ ውስጥ ግን ዮሴፍና ይሁዳ ጕልተው ይታያሉ። እግዚአብሔር ሁለቱንም በተለየ መንገድ ተጠቅሞባቸዋል፤ ይሁንና የእግዚአብሔርን በረከት በመፈጸም ረገድ ሁለቱም የተለያየ ሚና ተጫውተዋል። እዚህ ላይ ገና ከመጀመሪያው የልያ ልጅ ይሁዳ የላቀ ስፍራ ተሰጥቶታል። ከያዕቆብ ዕቅድ በተግራሪ፣ እግዚአብሔር የራሔልን ሳይሆን የልያን ማሕፀን ከፈተ።

በመጨረሻ ግን እግዚአብሔር ለራሔልም ስለ ራራላት ልጇ ዮሴፍ ተወለደ (30፥22)። ይሁን እንጂ ያዕቆብ ለራሔል የተናገረው ቃል እንደሚያስገነዝበን፣ እግዚአብሔር ለራሔል ልጆች ያልሰጣት የአብርሃም ዘሮች በልያ በኩል እንዲመጡ ነው (30፥2)። ልያ ልጅ መውለድ ባቆመች ጊዜ እንኳ ሁለት ወንዶች ልጆችንና አንዲት ሴት ልጅ ከአገልጋይዋ ለማግኘት ችላለች። ያዕቆብ በአንዲት ሳሕን ወጥ ብኩርናን እንደ ገዛ ሁሉ (25፥29-34)፣ ልያም ከያዕቆብ ብዙ ልጆች የመውለድ መብት በልጇ በሮቤል እንኮይ ገዛች። ከዚህ በኋላ በምናገኘው ታሪክ በዮሴፍና በውንድሞቹ በተለይም በዮሴፍና በይሁዳ መካከል የተፈጠረው ጥልና ውጥረት እዚህ ላይ ተሰተጋብቷል።

ተ. ያዕቆብና የላባ በጎች (30፥25-43)

25-43 ከልጆቹ መወለድ በኋላ ያዕቆብ ከካራን ተነሥቶ ሲሄድ ለመጀመሪያ ጊዜ እናነባለን። ከያዕቆብ የተነሣ የእግዚአብሔርን በረከት ለማግኘት የተመኘው ላባ፣ ያዕቆብ ለዓመታት ለሰጠው አገልግሎት ሒሳቡን ለማወራረድ ተነሣ። ስለዚህ ላባ የአገልግሎቱን ዋጋ እንዲነግረው ያዕቆብ ጠየቀው። የላባ ስጦታ ያዕቆብ ከእርሱ ጋር እንዲቈይና ከብቶቹንም እንዲጠብቅለት የሚያግባባ ነበር። ያዕቆብ ከላባ ጋር በመደራደሩ ብዙ በረከትና ሀብት አገኘ።

በረከቱን ያገኘው ከላባ አይደለም፤ ይልቁንም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው (ከ14፥21 ጋር ያነጻ)። ነገር ግን ያዕቆብ ለመቈየትና የላባን መንጎች ለመጠበቅ፣ እርሱም ተንኰባክቦ ላሳደጋቸው መንጎች እረኛ ለመሆን ወሰነ። ድርድሩ እልባት ካገኘ በኋላ ያዕቆብ ዝጕርጕር የሆኑትን ወይም ነቁጥ ያለባቸውን ፍየሎችና ጥቁር የሆኑትን በጎች በሙሉ መጠበቅ ነበረበት። የራሱን መንጎች የሚያረባው ከእነዚህ ነውና።


ይህ ምንባብ መወሰድ ያለበት ያዕቆብ በምሥራቅ መጻተኛ ሆኖ ሲኖር፣ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር እንደሚሆን በምዕ. 28 ላይ ለሰጠው ተስፋ እንደ አንድ ምሳሌ ተደርጎ ነው። ያዕቆብ የለውዝ ዕንጨቶችን በመላጥ የሠራው ብልኅ ተግባር የሚያሳየው፣ የእርሱን ችሎታ ሳይሆን እግዚአብሔር ለተስፋው ቃል የታመነ ነው የሚለውን ጭብጥ ነው። የምንባቡን ትርጕም ፍንጭ የምናገኘው በቍ. 43 ላይ ነው። በዚህ ቍጥር ላይ የታሪኩ እጥርጥር ማጠቃለያ ተሰጥቷል። እጥርጥሩ እግዚአብሔር ለአብርሃምና (12፥16) ለይስሐቅ (26፥14) የሰጠውን በረከት በግልጽ ያስታውሰናል፤ ይህም የዚህን ምዕራፍ ሁኔቶች በመላው የዘፍጥረት መጽሐፍ ውስጥ ከጐለበተው ጭብጥ ማለትም ከእግዚአብሔር በረከት፣ ተስፋና እርሱም ለተስፋው የታመነ ነው ከሚለው አንጻር እንድናጤናቸው ያደርገናል። እንግዲህ ያዕቆብ ከላባ ጋር የገባው ጥበብ የሞላበት ውል እግዚአብሔር መጻተኛ ሆኖ በኖረባቸው ዘመኖች እርሱን ለማበልጸግ የተጠቀመባቸው መንገዶች ናቸው። የዚህ ታሪክ ሐሳብ ይህ ለመሆኑ ይበልጥ ማረጋገጫ የምናገኘው በቀጣዩ ምዕራፍ ላይ ያዕቆብ ራሱ በተናገረው ቃል ነው። ወደ ኋላ እያስታወሰ የላባን መንጎች ወስዶ ለእርሱ የሰጠው እግዚአብሔር መሆኑን ለሚስቶች ነገራቸው (31፥9)።

ቸ. ያዕቆብ ከላባ ኰበለለ (31፥1-21)

1-3 የይስሐቅ ሀብት ፍልስጥኤማውያንን እንዳስቀናቸው ሁሉ (26፥14)፣ ላባ በያዕቆብ ሀብት መቈጣትና መቅናት እንደ ጀመረ ያዕቆብ ተረዳ። በዚህ ጊዜ ያዕቆብ ወደ አባቶቹ አገር እንዲመለስ እግዚአብሔር አሳሰበው። እግዚአብሔር በጕዞው ከያዕቆብ ጋር ዐብሮት እንደሚሆን በድጋሚ ተነግሮናል (28፥15)፤ በመሆኑም የያዕቆብ ሕይወት አቅጣጫ ወደ ቤቴል ማለትም ወደ መጀመሪያዎቹ ስፍራ ሲሆን እናያለን።

ይህ ምናልባት የታሪኩና የያዕቆብ ሕይወት መካከለኛ ሳይሆን አይቀርም። ያዕቆብ አሁን ወደ ቤቴል እየተመለሰ ነው። በኋላ ያዕቆብ ከዚህ ስፍራ ሆኖ ወደ ኋላ መለስ በማለት (32፥10) የእግዚአብሔርን የማጽናኛና የተስፋ ቃል በድጋሚ ተናገረ። ይሁንና “ከአንተ ጋር እሆናለሁ” በሚለው ተስፋ ፈንታ ያዕቆብ

የያዕቆብ ጉዞ



የተናገረው “አበለጽግሃለሁ” የሚለውን የእግዚአብሔር ቃል ነው (32፥10)። በመሆኑም የያዕቆብ ቃል ራሱ እግዚአብሔር ከእንተ ጋር እሆናለሁ ሲለው ምን ማለቱ እንደ ሆነ አስፋፍቶ ያብራራልናል።

4-13 የያዕቆብ ገለጻ በቀደመው ምዕራፍ ላይ የተወሣውን ዐቢይ ሁነት በድጋሚ ያስታውሰናል። ምንም እንኳ የምዕ. 30 ሁነቶች ያዕቆብ ከላባ የሚገባውን እንዳገኘ የሚናገሩ ቢመስሉም፣ ነገሩን ከሌላ አንጻር ስናጤነው የያዕቆብ ተግባር ላባ ለፈጸመበት ግፍ ከእግዚአብሔር ያገኘው አስችሎት ነው። ሁነቶቹ በሙሉ የእግዚአብሔር ዕቅድ አካሎች ናቸው፤ ዕቅዱ መፈጸም የጀመረው ያዕቆብ በቤቴል መሐላ በፈጸመና እግዚአብሔርም ከእርሱ ጋር እንደሚሆን ተስፋ በሰጠው ጊዜ ነው። የላባ በያዕቆብ ላይ መክፋትና የልጆቹም ቅናት የእግዚአብሔር ዕቅድ አካል ተደርገው ነው የተወሰዱት።

14-21 የያዕቆብ ሚስቶች ከቤተ ሰቦቻቸው ተለይተው ከያዕቆብ ጋር ወደ ከነዓን ምድር ለመሄድ ፈቃደኞች ነበሩ (ከ24፥58፤ ከሩት 1፥16 ጋር ያነጻ)። ከሁሉ በላይ ግን በእግዚአብሔር ለመታመንና የእርሱንም በረከት ለመሻት ዝግጁዎች ነበሩ። ሴቶቹ ለያዕቆብ አምንታዊ ምላሽ ቢሰጡም፣ ራሔል የላባን “ቤት ጣዖታት” በመስረቋ ከፊት ለፊታቸው አደጋ መደቀኑን የሚገልጽ ማስታወሻ ተሰጥቷል። የራሔል ተግባር በዚህ ስፍራ የሚገልጸው ምን እንደ ሆነ ግልጽ አይደለም። ራሔል ከባሏ ጋር ከቤቷ ኮብልላ ስትሄድ፣ የአባቷን ቤት ጣዖታት ሰርቃ በመሄዷና ያዕቆብ ሚስት ፍለጋ ኮብልሎ ሲሄድ፣ (ምዕ. 27) የአባቱን በረከት ሰርቆ በመሄዱ መካከል ተመሳሳይና ተነጻጻሪ ነገሮች አሉ። በሁለቱም ጊዜ ለታላቁ የሚገባውን የሰረቀው ታናሹ ነው። በኋላ እንደምናየው (ቊ. 32) ያዕቆብ ራሔል ጣዖታቱን እንደ ወሰደች አላወቀም። የላባ ውድ ንብረቶች ተሰርቀው የተወሰዱት ራሔል ለሀብት ካላት ጉጉት የተነሣ ብቻ ነው። ከዚህም በተጨማሪ የራሔል ድብቅ ተግባር ከያዕቆብ ማታለል ጋር ተዛማጅ ነው፤ ያዕቆብ ከላባ የኮበለለው በምስጢር ነው።

ጎ. *ያዕቆብ በላባ ተሳደደ (31፥22-55)*

22-42 በተሰረቁት ጣዓታት ምክንያት የተፈጠረው ክርክር ጸሓፊው ማእከላዊ ጭብጡን በሚገባ እንዲገልጽ ዕድል ሰጥቶታል፤ ይህም በቊ. 42 ላይ ያዕቆብ ለላባ በተናገረው ቃል ተገልጿል። የያዕቆብ ሀብት የተገኘው ከላባ ጋር ባለው ትስስር ሳይሆን፣ ያዕቆብ በገጠመው አስቸጋሪ የመጻተኛነት ሕይወት ሁሉ እግዚአብሔር በቸርነቱ ስለ ተንከባከበው ነው።

43-55 *ታሪኩ የተደመደመው በያዕቆብና በላባ መካከል በተደረገው ኪዳን ነው። ይስሐቅ ከአቤሜሌክ ጋር ሲለያይ ኪዳን እንደ ተጋባ ሁሉ (26፥28-31)፣ ያዕቆብና ላባም ሲለያዩ ኪዳን ተጋቡ።*

ነ. ያዕቆብ ከመላእክት ጋር ተገናኘ (32፥1-2)

1-2 *የዚህ ምዕራፍ ሁነቶች ያዕቆብ ከመላእክት ጋር እንደ ተገናኘ በሚያወሡ ሁለት ታሪኮች የታቀፉ ናቸው (ቁ. 1:25)። ያዕቆብ ወደ ምድሪቱ ሲመለስ ከመላእክት ጋር መገናኘቱ፣ በመጀመሪያዎቹ የዘፍጥረት መጽሐፍ ላይ ስለ ተስፋዩቱ ምድር የተነገረውን ያስታውሰናል። የምድሪቱ ምሥራቃዊ ወሰኖች በመላእክት ይጠበቁ ነበር (3፥24)። ያዕቆብ ከምሥራቅ ሲመለስ በተስፋዩቱ ምድር ወሰን አጠገብ ከመላእክት ጋር መገናኘቱ የአጋጣሚ ነገር አይደለም። ይህ ዐጭር ማስታወሻ ያዕቆብ በጰኒኤል ከአንድ "ሰው" ጋር የመታገሉ ትርጉም ምን እንደ ሆነ ፍንጭ ይሰጠናል (ቁ. 25-30)። ይህም ሰው ምናልባት መልአክ ሳይሆን አይቀርም።*

ኘ. መልአክተሮች ወደ ዔሳው ተላኩ (32፥3-22)

3-12 *የዚህና የተከታዩ ምዕራፍ አትኩሮት በያዕቆብ ሀብትና በያዕቆብና በዔሳው መካከል በተፈጠረው ዕርቅ ላይ ነው። ያዕቆብ ከወንድሙ ከዔሳው ጋር የሚያደርገው ዕርቅ በብዙ ልብ አንጠልጥል ነገሮች የተሞላ ነው። እንደ ያዕቆብ ሁሉ፣ እኛም ዔሳው አራት መቶ ሰዎችን አስከትሎ ያዕቆብን ሊገናኘው ለምን እንደ ፈለገ ርግጠኞች አይደለንም። ከዔሳው የሰማነው የመጨረሻው ንግግር ያዕቆብ በረከቱን ስለ ሰረቀበት ሊገድለው እንደ አሰበ ነው (27፥41)። ያዕቆብ ዔሳው ይበቀለኛል ብሎ እጅግ ፈራ። ከዚህ አንጻር ካየነው፣ በመካከላቸው የተፈጠረውን ሁኔታ ለመቀልበስ የያዕቆብ ጸሎት ቁልፍ ሚና ተጫውቷል። ያዕቆብ እግዚአብሔር እንዲጠብቀውና ቀደም ሲል የገባለትንም ኪዳን እንዲፈጽምለት ጸለየ።*

13-22 *ዔሳው ይበቀለኛል በማለት የሠጋው ያዕቆብ ራሱንና ቤተ ሰቡን ለማዳን ትልቅ ዕቅድ ነደፈ። ለዔሳው የሚያደርሱትን ስጦታ ከሰጠ በኋላ ዔሳውን ሲገናኙ እንዴት መቅረብ እንዳለባቸው ብርቱ መመሪያ ሰጣቸው። በዚህ ሁሉ ሐሳቡ የዔሳውን "ቁጣ አብርዶ" ቤተ ሰቡን ከእጁ ለመታደግ ነበር። እዚህም ላይ የያዕቆብን ዕቅድና ዘዴ እናያለን። የዔሳውን ብኵርናና በረከት ለመስረቅ እንዳደረገው ሁሉ፣ አሁንም የዔሳውን ልብ ለማራራት ዐቀደ። ይሁንና የጸናው የያዕቆብ ዕቅድ ሳይሆን ጸሎቱ ነው። ዔሳውን ሲገናኘው የዔሳው ልብ ተለውጦ ነበር። ያዕቆብን ሊገናኘው ወደ እርሱ እየሮጠ ሄደ፤ ዔሳው አንገቱን ዐቅፎ ሳመው፤ አለቀሰም (33፥4)። እግዚአብሔር አስቀድሞ መንገዱን አዘጋጅቶ ስለ ነበር የያዕቆብ ዕቅድና ዘዴ ከሸፈ።*

አ. የያዕቆብ ትግል (32፥23-32)

23-32 *ያዕቆብ ከመልአኩ ጋር ያደረገው ትግል የያዕቆብን መላ ሕይወት ይገልጻል። ያዕቆብ ከወንድሙ ጋር (ምዕ. 25፡27)፣ ከአባቱ ጋር (ምዕ. 27)፣ ከዐማቱ ጋር (ምዕ. 29-31) ታግሎ ነበር፤ አሁን ደግሞ ከእግዚአብሔር ጋር ታገለ (ምዕ. 32)። ያዕቆብ የተናገረው ቃል ይህ ታሪክ ስለ እርሱ ማንነት የሚያወሣውን ይነግረናል፦ "ካልባረከኸኝ አልለቅህም"። እዚህ ላይ ያዕቆብ ለበረከት ያደረገውን ትግል በጉልሕ እናያለን፤ ከእግዚአብሔርም ከሰውም ጋር ታገለ (ቁ. 28)።*

እጅግ የሚገርመው ያዕቆብ በትግሉ አሸነፈ። ድል ያደረገው መልአኩ "በባረከው" ጊዜ ነው። "ጰኒኤል" የሚለው ስም ያዕቆብ የታገለው ከማን ጋር እንደ ሆነ ፍንጭ ይሰጠናል። ያዕቆብ እግዚአብሔርን ፊት ለፊት አየሁት ሲል እርሱ የታገለው ሰው በርግጥ እግዚአብሔር ነው ማለቱ አይደለም። ይልቁንም አንድ ሰው የእግዚአብሔርን መልአክ ሲያይ የእግዚአብሔርን ፊት እንዳየ ይቈጠራል (ለምሳሌ፣ መሳ 13፥22፤ ከሆሴ 12፥2-4 ጋር ያነጻ)።

ከ. ያዕቆብ ከዔሳው ጋር ተገናኘ (33፥1-17)

1-17 *ያዕቆብ ዔሳው አራት መቶ ሰዎች አስከትሎ መምጣቱን ሲያይ፣ ያለውን ነገር ሁሉ በሁለት ከፈለው (32፥7-8)። ራሔልንና ዮሴፍን በመጨረሻ ማድረጉ ለእነርሱ ያለውን የተለየ ፍቅር ይገልጻል። የዔሳው አቀባበል ፍጹም ያልተጠበቀ ነበር። ያዕቆብ ከዔሳው የጠበቀው በቀልን ነበር፤ ወይም በቀል ባይሆን እንኳ ከባድ ካሣ ነበር። ከያዕቆብ ጸሎት የተነሣ ግን (ከ32፥11 ጋር ያነጻ) የዔሳው ልብ ተለወጠ ነበር።*

የዔሳው መለወጥና ወንድሙን ለማየት የነበረው ናፍቆት ከያዕቆብ ፍርሀት ጋር በጉልሕ ተነጻጽሯል። የዔሳው ልብ በመለወጡ የያዕቆብ ዕቅድና ዝግጅት ሁሉ ኩምሽሽ አለ። ዔሳው አስከትሏቸው የመጣው አራት መቶ ሰዎች ከያዕቆብ ቤተ ሰብ ጋር ጦርነት ለመግጠምና ሀብቱን ለመውሰድ ሳይሆን፣ ያዕቆብን በጉዞው ሁሉ ለመጠበቅ የመጡ ነበሩ። እዚህም ላይ ስለ ያዕቆብ የቀረበልን ሕይወቱን ለመጠበቅ ረጅም ጕዳና መጓዙን ነው፤ ነገር ግን ጥረቱ ሁሉ ዋጋ ቢስ ነበር። ያዕቆብ ዘዴና ዕቅድ ማውጣቱን ቢቀጥልም፣ የእግዚአብሔር ዕቅድ ግን የያዕቆብን ብልኀት ከንቱ ያደርገው ነበር።

ይህ የወንድማማቾቹ ዕርቅና ዔሳው ያዕቆብ የተቀበለውን በረከት መካፈሉ (ቁ. 11) እግዚአብሔር ለአብርሃም የሰጠው ተስፋ መፈጸሙን ያሳያሉ፦ "በምድር የሚኖሩ ሕዝቦች በአንተ አማካይነት ይባረካሉ" (12፥3)።

ኸ. ያዕቆብ በሴኬም (33፥18-34፥31)

33፥18-20 *እነዚህ ቊጥሮች ያዕቆብ በምሥራቅ መጻተኛ ሆኖ በኖረባቸውና በቀጣዮቹ ዓመታት በከነዓን ምድር በሕይወቱ በተፈጸሙ ሁነቶች መካከል እንደ መሸጋገሪያ ያገለግላሉ። ያዕቆብ በምዕ. 28 ላይ ከከነዓን ሲነሣ፣ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር በመሆን ወደ ምድሪቱ በሰላም (አመት፣ "በደኅና") እንዲደርስ የሚጠብቀው ከሆነ፣ ካለው ነገር ሁሉ ለእግዚአብሔር አንድ ዐሥረኛውን እንደሚሰጥ ምሎ ነበር (28፥20-22)። ታሪኩ በያዕቆብ ሕይወት የተፈጸሙ ሁነቶችን በጥንቃቄ በመዘገብ የእግዚአብሔርን ታማኝነት አሳይቷል። በመሆኑም ያዕቆብ ወደ ከነዓን ምድር "በደኅና" ተመልሷል። እግዚአብሔርም ታማኝ ነበር።*

በምዕራፍ 35 ላይ ያዕቆብ ወደ ቤቴል በመመለስ በዚያ መሠዊያ ሠራ (ቁ. 7)። ያዕቆብ ለእግዚአብሔር ዐሥራት ስለ መስጠቱ የሚያወሣ ምንም ነገር የለም። ይሁንና እዚህና በምዕ. 35 ላይ እንደምናየው፣ መሠዊያ መሥራቱና መሥዋዕት ማቅረቡ ምናልባት "ዐሥራት" መስጠቱን ሊያመለክት ይችላል። በያዕቆብ የተገዛው መሬት በኋላኞቹ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ታሪኮች ውስጥ ቍልፍ ሚና አለው። እስራኤላውያን የዮሴፍን ዐጥንቶች የቀበሩት በዚህ ስፍራ ነው (ኢያ 24፥32)፤ ይህም እግዚአብሔር ምድሪቱን በመስጠት የገባውን ተስፋ እንደሚፈጽም ያላቸውን እምነት ያሳያል።

34፥1 *በ30፥21 ላይ የዲና መወለድ ሲዘገብ፣ ምንም ማብራሪያ አልተሰጠም። ይሁንና ያዕቆብና ዘሮቹ ከፓዳን አራም ተነሥተው በሴኬም ሲሰፍሩ (ቁ. 18-20)፣ ዲና በያዕቆብና በከነዓን ነዋሪዎች መካከል ለተፈጠረው ግጭት ማእከል ሆነች። ታሪኩ ሊያሳስበን የሚፈልገው በእነዚህ ሁሉ ታሪኮች ውስጥ የያዕቆብ ማንነት ምን እንደሚመስል ነው። ያዕቆብን ሁልጊዜ የምናየው የራሱን ዕቅድና ዘዴ ሲተልም ቢሆንም፣ በርግጥ በመጨረሻ እየፈጸመ የምናገኘው የእግዚአብሔርን ሐሳብ ነው። በዚህ ታሪክ ላይ የእግዚአብሔር ሐሳብ የአብርሃምን ዘሮች ከፊት ለፊታቸው የተደቀነው የዲናና የሴኬም ጋብቻ ከሚያመጣው ጦስ መጠበቅ ነው። የጋብቻው ዐላማ የያዕቆብን ቤተ ሰቦች ከከነዓን ነዋሪዎች ጋር አንድ ሕዝብ (ቁ. 16፥22) ለማድረግ እንደ ሆነ ሁለት ጊዜ ተነግሮናል። ይህም ከአብርሃም ምክር (24፥3)፣ ከርብቃ ፍርሀትና (27፥46) ከያዕቆብ ትእዛዝ ጋር የሚጣረስ ነው (28፥1)።*

ታሪኩ ስለ ቤተ ሰብ ክብርና እኅታቸው ስለ ተደፈረችባቸው ወንድሞች ቍጭት ቢያወሣም፣ ከዚሁ ጋር በተጓዳኝ እግዚአብሔር ውሱንና ራስ ጠቀም በሆነው በሰዎች ዕቅድ አማካይነት ሐሳቡን እንደሚፈጽም ይተርካል።

2-4 *ምንም እንኳ የኤዊያዊው ልጅ ዲናን ከልብ ቢወዳትም፣ ያለ ፈቃዷ ከእርሷ ጋር ተኝቷል፣ በዚህም አስነውሯታል። ስምዖንና ሌዊ በመጨረሻ የተናገሩት ቃል ሁኔታውን እንዴት እንደ ተመለከቱት በሚገባ ያሳያል፦ "እኅታችንን እንደ ዝሙት ዐዳሪ ይድፈራት?" (ቁ. 31)።*

5-24 *ያዕቆብ ሁኔታውን የተከታተለው በመደነቅ ነበር። በዲና ላይ የደረሰውን ሲሰማ፣ ልጆቹ እስኪመለሱ ድረስ ታገሠ። ያዕቆብ ዝም ያለው ለምን እንደ ሆነ በታሪኩ መጀመሪያ ላይ ግልጽ አይደለም። ያታለለው ያዕቆብ ሳይሆን የያዕቆብ ልጆች መሆናቸው ትኵረት ሊሰጠው ይገባል፤ በታሪኩ መደምደሚያ ላይ ያዕቆብ ልጆቹን በድርጊታቸው ወቅሦአቸዋል። ዕቅዱና ዘዴው የያዕቆብ አልነበረም፤ የልጆቹ ዕቅድና ዘዴ እንጂ። የዚህን ምዕራፍ ሁነት በተመለከተ ያዕቆብ ለስምዖንና ለሌዊ የተናገረው የመጨረሻው ቃል እጅግ ብርቱ ነበር፦ "ወደ ሸን኎አቸው አልግባ፤ ጉባኤያቸው ውስጥ አልገኝ፤ በቍጣ ተነሣሥተው ሰዎችን ገድለዋል፤ . . . እጅግ አስፈሪ የሆነ ቍጣቸው፣ ጭከና የተሞላ ንዴታቸው የተረገመ ይሁን፤" (49፥6-7)።*

ስምዖንና ሌዊ የተፈጸመውን በደል ለመበቀል ዕቅድ እንደ ነበራቸው የምናውቀው ስለ ዲና ሁኔታ ሲሰሙ ባሳዩት ቁጣ ነው። የቁጣቸው ልክ ማጣት እንዲህ የመሰለው ድርጊት ተገቢውን ቅጣት ሳያገኝ እንደማያልፉት ያሳያል። በምዕራፍ 17 ላይ የግርዘት ሥርዐት ለኪዳኑ ሕዝብ አንድነትና ከተቀረው ሕዝብ የተለዩ ለመሆናቸው ምልክት ነው (ቁ. 11)። ግርዘት ለአብርሃም ዘሮች ብቻ የተሰጠ ሳይሆን፣ እግዚአብሔር ለአብርሃም የሰጠውን ተስፋ ተቀብለው የኪዳኑን ሕዝብ ለሚቀላቀሉ ሁሉ የተሰጠ ነው። በመሠረቱ ግርዘት አብርሃም "የብዙዎች አባት" እንደሚሆን ለተነገረው ተስፋ ምልክት ነው (17፥5)። የያዕቆብ ልጆች ግን እነዚህ ከነዓናውያን እንዲገረዙ ሲጠይቋቸው፣ የእግዚአብሔርን ሐሳብ እየቀለበሱ ነበር። ሁለቱ ቤተ ሰቦች "አንድ ሕዝብ" እንዲሆኑ ግርዘትን እንደ መሣሪያ ሊጠቀሙ ፈለጉ። የአብርሃምን ዘር የሚቀላቀሉት ከነዓናውያን አይደሉም፤ ይልቁንም የአብርሃም ዘሮች ከነዓናውያንን ይቀላቀላሉ። ይህን ሐሳብ ኤሞርና ሴኬም ለወገኖቻቸው የተናገሩት ቃል በአጽንዖት ይገልጸዋል፦ "ከብታቸው፣ ንብረታቸው፣ እንስሶቻቸው ሁሉ የእኛ ይሆኑ የለምን?"

25-31 የያዕቆብ ልጆች እስከ መጨረሻው ድረስ በአታላይነታቸው ሲዘልቁ፣ ድርጊታቸው ሳይገሠጽ አልታለፈም። በቁጥር 30 ላይ ያዕቆብ የተናገረው ቃል ድርጊታቸውን ክፉኛ እንደ ኰነነው ያሳያል። በታሪኩ መጨረሻ ልጆቹ የተናገሩት ቃል ሐሳባቸው ለመዝረፍ ሳይሆን የእኅታቸው ክብር ለማስከበር እንደ ሆነ ያመለክታል።

ወ. ያዕቆብ ወደ ቤቴል ተመለሰ (35፥1-15)

1-5 ምዕራፉ የሚጀምረው እግዚአብሔር ከዚህ በፊት ለያዕቆብ በቤቴል የተገለጠለትን ሁኔታ በመጥቀስ ነው (28፥10-15)። ያዕቆብ ከወንድሙ ከዔሳው ቁጣ ለማምለጥ ወደ ቤቴል እንደ ሸሸ ሁሉ፣ አሁን ደግሞ ወደ ቤቴል እንዲመለስና ሁለቱ ልጆቹ ስምዖንና ሌዊ በጫሩት ጠብ መካከል እንዲኖር እግዚአብሔር አዘዘው። ያዕቆብ እግዚአብሔርን ታዝዞ ወደ ቤቴል ሲሄድ፣ እግዚአብሔር በአቅራቢያው ከሚኖሩት ከነዓናውያን ቁጣ አዳነው። ያዕቆብ እግዚአብሔርን "በመከራዬ ጊዜ ለሰማኝ፣ በሄድሁበትም ሰፍራ ሁሉ ላልተለየኝ አምላክ" በማለት መጥራቱ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል። ይህም በያዕቆብ ታሪክ ውስጥ ትልቅ ሚና የተጫወተውን አምላክ ሥራ ለመግለጽ ተገቢ የሆነ ቃል ነው። ያዕቆብ በብዙ መከራ ውስጥ ዐልፏል፤ ባለፈበት መንገድ ሁሉ እግዚአብሔር ለተስፋ ቃሉ ታማኝ በመሆን ይታደገው ነበር።

ቀደም ሲል የተጠቀሱትና የያዕቆብ ቤተ ሰቦች የነበሯቸው "አማልክት" ራሔል ከአባቷ ቤት የሰረቀቻቸው ጣዖታት ናቸው (31፥19)። "ባዕዳን አማልክት" ተብለው የተጠሩት እነዚህ ሳይሆኑ አይቀሩም፤ ይሁንና ጸሓፊው ከባዕዳን አማልክቱ በተጨማሪ የጆሮ ጉትቻቻቸውን አውልቀው እንደ ቀበሩ ሲነግረን፣ የያዕቆብ ቤተ ሰቦች በሴኬም ሲኖሩ ሌሎች ሃይማኖታዊ ምስሎችን ሳይወስዱ አልቀረም። እዚህ ላይ ለመግለጽ የተፈለገው ያዕቆብና ቤተ ሰቡ እነዚህን ነገሮች ወደ ኋላቸው ትተው ወደ ቤቴል ለሚያደርጉት ጉዞ ራሳቸውን በማንጻት እያዘጋጁ መሆኑን ነው።

6-15 ያዕቆብ ቤቴል መድረሱ ጉዞው እንደ ተጠናቀቀና እግዚአብሔር ታማኝ እንደ ሆነ ያሳያል። በጉዞው ሁሉ ከያዕቆብ ጋር ነበረ፤ አሁን ያዕቆብ ወደ ቤቴል በደኅና ተመለሰ። አብርሃምና ይስሐቅ ብዙ ጊዜ እንዳደረጉት ሁሉ፣ ያዕቆብም መሠዊያ ሠርቶ ስም አወጣለት፤ ይህንንም ያደረገው ከካራን ተነሥቶ ሲሄድ፣ እግዚአብሔር በዚያ ለእርሱ የተገለጠበትን ጊዜ ለማስታወስ ነው (28፥10-22)። እግዚአብሔርም ለያዕቆብ እንደ ገና ተገለጠ "ባረከው"፤ ለሁለተኛ ጊዜም የያዕቆብ ስም "እስራኤል" ተብሎ ተለወጠ (ከ32፥28 ጋር ያነጻ)። ስሙ መለወጡ ለሁለተኛ ጊዜ የተነገረው "እስራኤል" ለሚለው ስም የወል ወይም አዎንታዊ ትርጉም ለመስጠት ነው። ይህም የተደረገው ከቃሉ ጋር የተሳሰረውን "የትግል" ሐሳብ በማስወገድ አዎንታዊ ሐሳብ እንዲይዝ በማድረግና "ያዕቆብ" ከሚለው ስም ጋር በማነጻጸር ነው (32፥28)፤ ይህ ስም በዚህ ታሪክ ውስጥ የተሳሰረው ከያዕቆብ አታላይነት ጋር ነው። የያዕቆብ ስሞች በእግዚአብሔር ፊት ያለውን አቋም ይገልጻሉ።

በቁጥር 11-12 ላይ እግዚአብሔር ለያዕቆብ የተናገራቸው ቃሎች አጽንዖት ሊሰጣቸው ይገባል። አንደኛው፣ እነዚህ የእግዚአብሔር ቃሎች የጥንቱን የሥነ ፍጥረት በረከት ያስታውሱናል (1፥28)፤ ይህም እግዚአብሔር በያዕቆብ አማካይነት በረከቱን ለሰዎች ሁሉ ለማድረስ "በሥራ" ላይ እንደ ሆነ ያሳያል። ሁለተኛው፣ ከ17፥16 በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ከያዕቆብ ዘር ንጉሥ እንደሚወጣ ተነገረ። ሦስተኛው፣ በመጀመሪያ ለአብርሃም፣ ቀጥሎም ለይስሐቅ የተሰጠችው የተስፋዪቱ ምድር፣ ለያዕቆብም እንደ ገና ተሰጠች። እንግዲህ በእነዚህ ዐጭር ቃሎች ውስጥ በርካታ ዐቢይ ጭብጦች ተሳስረው እናገኛለን። የጥንቱ የሰው ልጆች በረከት የታደሰው በንጉሣዊው ዘርና በተስፋዪቱ ምድር አማካይነት ነው።

በታሪኩ ሂደት መሠረት ይህ ክፍል ዐቢይ ለውጥ ይታይበታል፤ በጭብጡም ረገድ እንዲሁ ነው። እስከ አሁን ድረስ ሁለት መሥመሮች ጐን ለጐን ሲሄዱ ነበር፤ አሁን ግን ሊገናኙና አንድ ጭብጥ ብቻ ይዘው ሊዘልቁ ነው። ያዕቆብ ሁለት ሚስቶች አሉት፤ ሁለቱም የቀረቡት የተስፋው ቃል የሚፈጸመው በእነርሱ በኩል እንደ ሆኑ ነው። አብርሃም ሁለት ወንዶች ልጆች ቢኖሩትም፣ የተስፋው ልጅ ግን አንዱ ብቻ እንደ ሆነ ሁሉ፣ እንዲሁም ይስሐቅ ሁለት ወንዶች ልጆች ቢኖሩትም፣ የበረከቱ ልጅ ግን አንዱ ብቻ እንደ ሆነ ሁሉ፣ ያዕቆብም ምንም እንኳ ልጆቹ ዐሥራ ሁለት ቢሆኑም፣ ሁለት ሚስቶች ነበሩት (ልያና ራሔል)፤ ከልያና ከራሔል የተወለዱት ሁለት ልጆቹ (ይሁዳና ዮሴፍ) የበረከቱ ወራሽ ለመሆን ይቀናቀኑ ነበር። በያዕቆብ ታሪክ ላይ አስቀድሞ እንደ ተስተጋባው፣ በመጨረሻ በረከቱን የሚያገኘው የራሔል ልጅ ዮሴፍ ሳይሆን የልያ ልጅ ይሁዳ ነው (49፥8-12)።

ዐ. የብንያም መወለድና የራሔል መሞት (35፥16-20)

16-20 የዮሴፍ እናትና የተወደደች የያዕቆብ ሚስት ራሔል ሁለተኛ ልጇን ብንያምን ስትወልድ ሞተች። የዚህ ልጅ መወለድ ታሪክ በ29፥32-30፥24 ላይ ከምናገኛቸው ከዐሩት ልጆች ተለይቷል፤ ይሁንና ከዚህ ምንባብ ጋር ያለው ትስስር የጠበቀ ነው። የመጨረሻው ልጅ ከራሔል የተወለደው ዮሴፍ ነው። ዮሴፍ ሲወለድ ራሔል እንዲህ ብላ ነበር ፦ "እግዚአብሔር ሌላ ወንድ ልጅ ጨምሮ ይስጠኝ" (30፥24)። ይህን ጥያቄዋን የተመለከተችው የራሔል አገልጋይ እንዲህ አለቻት፦ "አይዞሽ አትፍሪ ሌላ ወንድ ልጅ ልትገላገይ ነው"። ራሔል ልትሞት ስትል ልጇን "ቤንኦኒ" አለችው፤ ትርጉሙም "የመከራዬ ልጅ" ማለት ነው። ያዕቆብ ግን ልጁን "ብንያም" (በቁሙ "የቀኜ ልጅ" ማለት ነው) ብሎ ጠራው። ያዕቆብ ለልጁ ያወጣለት ስም በ "ኦኒ" ላይ የተመሠረተ ሲሆን ኦኒ ማለት "መከራ" ወይም "ብልጽግና" ማለት ነው። ያዕቆብ ራሔል ለልጇ "የብልጽግናዬ ወይም የመልካም ዕድሌ ልጅ" ብላ ያወጣችለትን ስም እንደ ገና በመተርጐም ነው ስም ያወጣለት።

ራሔል የተቀበረችበት ስፍራ ኤፍራታ ሲሆን ከቤተ ልሔም ከተማ ጋር አንድ ነው፤ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ቤተ ልሔም ቍልፍ ከተማ ናት (ከ1ሳሙ 17፥12፤ ከሚክ 5፥2 ጋር ያነጻ)። ይህ ስፍራ ያዕቆብ ለራሔል መቃብር ባቆመው ሐውልት እንዲታወስ ተደርጓል (ከ1ሳሙ 10፥2 ጋር ያነጻ)። ይህ ምንባብ በኋለኞቹ ቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ጕልሕ ሚና ሲጫወት ይታያል (48፥7፤ ኤር 31፥15፤ ከሚክ 5፥2፤ ከማቴ 2፥18 ጋር ያነጻ)።

ዘ. የያዕቆብ ልጆች (35፥21-26)

21-26 ከአጸያፊ ድርጊታቸው የተነሣ የመጀመሪያዎቹ ሦስቱ የያዕቆብ ልጆች ሞገስ ሳያገኙ ቀሩ። ጸሓፊው የስምዖንንና የሌዊን ተግባር አስቀድሞ ገልጾልናል (ምዕ. 34)፤ አሁን ደግሞ የሮቤልን ተግባር ባጭሩ ይገልጽልናል። ከዚህ የሚከተለው የስም ዝርዝር እንደሚያሳየው፣ የሚቀጥለው ወንድም የልያ ልጅ ይሁዳ ነው። ታላላቆቹ ልጆች ከተወገዱ በኋላ ሰፊ ቦታ የተሰጠው ለይሁዳና ለዮሴፍ ነው፤ በተቀረው ብሉይ ኪዳንም የላቀ ስፍራ የተሰጠው ለእነዚሁ ልጆች ነው። ከዚህ በኋላ የምናገኘው የዘፍጥረት ታሪክ በአብዛኛው የሚያተኩረው በዮሴፍ ላይ ቢሆንም፣ ይህ ግን የመጨረሻ ውጤቱን አያመላክትም። እስከ ምዕ. 48 እና 49 ድረስ የእነዚህን ሁለት የአብርሃም ዘሮች የወደፊት ዕድል በተመለከተ ምንም ነገር አናነብም።

ዠ. የይስሐቅ መሞት (35፥27-29)

27-29 የያዕቆብ ታሪክ ፍጻሜ የተነገረን በአባቱ በይስሐቅ ሞት ነው። ይህ መግለጫ የተሰጠው የይስሐቅን ሞት ለመዘገብ ብቻ ሳይሆን፣ እግዚአብሔር ለያዕቆብ የገባውን ተስፋ በሚገባ መፈጸሙንም ለመግለጽ ጭምር ነው (28፥21)። ያዕቆብ በፈጸመው መሐላ መሠረት መጻተኛ ሆኖ በሚኖርበት ዘመን ሁሉ እግዚአብሔር እንዲጠብቀውና ወደ አባቱም ቤት በደኅና እንዲመልሰው ጠይቆ ነበር። በመሆኑም ይስሐቅ ከመሞቱ በፊት ያዕቆብ ወደ አባቱ ቤት ሲመለስ እነዚህ ቃሎች ተፈጸሙ፤ በዚህም ታሪኩ ተደመደመ።

፮. የዔሳው ታሪክ (36፥1-43)

1-8 የያዕቆብና የዔሳው መለያየት ከአብርሃምና ከሎጥ መለያየት ጋር ይመሳሰላል (ምዕ. 13)። የሁለቱ ወንድማማቾች ንብረት እጅግ ታላቅ በመሆኑ፣ ምድሪቱ ለሁለቱም ልትበቃ አልቻለችም (ከ13፥6 ጋር ያነጻ)። ስለዚህ ሎጥ ከአብርሃም ተለይቶ ወደ ምሥራቅ እንደ ሄደ ሁሉ፣ ዔሳውም ከያዕቆብ ተለይቶ ወደ ሴይር ሄደ። የተስፋው ወራሽ በምድሪቱ ሲቀመጥ፣ ሌሎቹ ልጆች ግን ወደ ምሥራቅ ሄዱ። የያዕቆብና የዔሳው መለያየት ለሁለቱም ጠቃሚ ነበር።

ጸሓፊው በቀሪው የምዕራፉ ክፍል የዔሳውን ዘር ዕድገትና ጤና ይነግረናል። በተለይ ዔሳው በርግጥ "ኤዶም" መሆኑን በሚገባ ገልጿል። "ኤዶም የተባለው ዔሳው" የሚለው ሐረግ በኋለኛው የእስራኤል ታሪክ ውስጥ ኤዶም ያለውን ስፍራ እንድናስተውል ከወዲሁ ያዘጋጀናል። ይህ ሐረግ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ብዙ ጊዜ ተጠቅሷል።

9-19 የዔሳው "ትውልድ ሐረግ" ከብዙ ዝርዝሮች ተሰባስቦ የተዘጋጀ ነው። ስለ ዔሳው ልጆች የሚያወሣው የመጀመሪያው ዝርዝር በአብዛኛው የተወሰደው የዔሳውን ሚስቶች በተመለከተ ከተነገረው ዐጭር ታሪክ ላይ ነው (26፥34፤ 28፥9፤ 36፥3)። ቊጥር 10 የዔሳውን ልጆች ከሁለት ይከፍላቸዋል፤ እነርሱም የዓዳ ልጆችና የቤሴሞት ልጆች ናቸው። የዓዳ ልጆች (እንዲሁም የልጅ ልጆች) በቊ. 11-12 ላይ ተዘርዝረዋል፤ ከዚያም የቤሴሞት ልጆች በቊ. 13 ላይ ተዘርዝረዋል። በቊጥር 15-19 ላይ ከዔሳው የተወለዱ "የነገድ አለቆች" ተዘርዝረዋል፤ የተዘረዘሩትም ከታላቁ ከኤልፋዝ ጀምሮ በየእናቶቻቸው መሠረት ነው። ከዘካርያስ 12፥5-6 በቀር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ "አለቃ" የሚለው ቃል የገባው የኤዶምን መሪዎች ለመግለጽ ነው፤ በዘካርያስ 12፥5-6 ላይ ቃሉ የሚወክለው የባዕዳን ሕዝቦችን መሪዎች ነው። እንግዲህ ቃሉ በአብዛኛው የሚያገለግለው በፖለቲካዊና በወታደራዊ አገባቡ ነው።

20-23 ከላይ ከምናገኛቸው ከሁለቱ ዝርዝሮች በተጨማሪ "በዚያች ምድር ይኖሩ የነበሩ የሖሪው የሴይር ልጆች እነዚህ ነበሩ" የሚል እናገኛለን። ከዚያም የነገድ "አለቆቻቸው" ስም ተዘርዝሯል። ሴይር ኤዶማውያን የሚኖሩባት ምድር መጠሪያ ቢሆንም፣ እዚህ ላይ ግን የግለ ሰብ ስም መጠሪያ ሆኖ ገብቷል። እርሱና የእርሱ ዘሮች እዚህ ላይ የተጠቀሱት የኤዶምን ግዛት ስለ ያዙ ነው። በ2ዜና 25፥11፡14 ላይ "የሴይር ልጆች" ኤዶማውያን ተብለዋል። የስም ዝርዝሩ ሴይርን የሚያዛምደው "ከሖሪው " ጋር ሲሆን፣ ቀደምት ሊቃውንት ቃሉን የተረጐሙት "የዋሻ ነዋሪዎች" ብለው ነው። ቃሉን በዚህ ዐይነት የተረጐሙት፣ "ሖሪው " የሚለው ቃል በዕብራይስጥ ቋንቋ "ዋሻ" ከሚለው ቃል ጋር ተመሳሳይ በመሆኑ ነው።

31-43 የኤዶማውያን ነገሥታት ዝርዝር የተመለከተው "ልጆች ላይ ንጉሥ በእስራኤል ከመንገሡ በፊት በኤዶም አገር የነገሡ ነገሥታት እዚህ ነበሩ" በሚለው አርእስት ነው። ይህም በእስራኤል ላይ ንጉሥ እንደሚነግሥ ከወዲሁ ያስተጋባል። በመሆኑም ይህ ክፍል የእግዚአብሔርን ተስፋ መጠባበቅን (ዘፍ 49፥10፤ ዘኁ 24፥7፡17-18) እና (ከ1ሳሙ 2፥10 ጋር ያነጻ) የሚያመለክቱ ምንባቦች (ለምሳሌ፣ 17፥6፡16፤ 35፥11) አካል ነው።

፯. የያዕቆብ ታሪክ (37፥1-49፥33)

ሀ. ያዕቆብ በምድሪቱ (37፥1)

1 ያዕቆብ አሁን ያለው በተስፋዪቱ ምድር ነው፤ ይሁንና እንደ አባቱና አያቱ ሁሉ (ዕብ 11፥13)፣ በዚያ የሚኖረው መጻተኛ ሆኖ ነው። እንደ አባቶቹ ሁሉ፣ የእግዚአብሔር ተስፋ እስኪፈጸም ይጠባበቅ ነበር። ይህ ቊጥር የያዕቆብ ልጆች ከተስፋዪቱ ምድር ተነሥተው ወደ ግብፅ ምድር መግባታቸውን ለሚተርከው ዘገባ መልካም መሸጋገሪያ ነው። በ25፥11 መሠረት የያዕቆብ አባት ይስሐቅ በብኤርለሃይሮኢ ይኖር ነበር፤ ያዕቆብም በዚህ ወቅት ይኖር የነበረው በዚሁ ስፍራ ነው።

ለ. የዮሴፍ ሕልም (37፥2-11)

2-3ሀ "የያዕቆብ ትውልድ ታሪክ ይህ ነው" የሚለው መደበኛ ርእስ የቀረው ዘገባ ስለ ያዕቆብ ሳይሆን፣ ስለ ዮሴፍና በኋላም ስለ ይሁዳ መሆኑን ይሰውርብናል። ዮሴፍ ገና የዐሥራ ሰባት ዓመት ልጅ ሳለ (ከወንድሞቹ ጋር) የአባቱ በጎች እረኛ ነበር። ከሌሎቹ ወንድሞቹ ጋር ሲነጻጸር በርግጥም ዕድሜው ትንሽ ነው። ዮሴፍ ስለ ወንድሞቹ ለአባቱ መጥፎ ወሬ ይዞ እንደ መጣና አባቱም ያዕቆብ በእርጅናው ዘመን የወለደው ልጅ በመሆኑ ከሌሎቹ ወንድሞቹ ይልቅ እጅግ ይወደው እንደ ነበር ተነግሮናል። ያዕቆብ ለራሔል የነበረው የተለየ ፍቅር (29፥30) ወደ ልጇ ወደ ዮሴፍም ተላለፈ። የዮሴፍ ታሪክ በቃላት ጨዋታ ወይም ተመሳሳይ ድምፅት ባላቸው ቃሎችና ቅልብሶች የተሞላ በመሆኑ "መጥፎ ወሬ" የሚለው ሐረግ በ50፥20 ላይ እንደ ተገለጸው የወንድሞቹን "ክፉ" ሐሳብ (አመት፣ "እኔን ለመጉዳት ዐስባችሁ") ያስተጋባል።

3ለ-11 ያዕቆብ ለዮሴፍ የሠራለት "በጎብረ ቀለማት ያጌጠ እጀ ጠባብ" ምን ያህል አብልጦ ይወደው እንደ ነበር ይመሰክራል። በታሪኩ ውስጥ የዮሴፍ እጀ ጠባብ ተደጋግሞ መነገሩ፣ ወንድሞቹን ያስቈጣቸውና በእርሱም ላይ እንዲነሡ ያደረጋቸው ትልቁ ምክንያት የዮሴፍ ይበልጥ መወደድ እንደ ሆነ ያስገነዝበናል። የኋላ ኋላ ግን ቊጣቸው አይሎ እስከ ወዲያኛው እንዲያስወግዱት አደረጋቸው። ይሁንና ጥላቻቸውን ያባባሰው ዮሴፍ ያለማቸው ሁለት ሕልሞች ናቸው፤ ሁለቱም ሕልሞች ወንድሞቹ "ለእርሱ እንደሚሰግዱለት" ያወሣሉ። ይህም ዮሴፍ የግብፅ ምድር አገረ ገዥ ስለ ነበር ወንድሞቹ "ለጥ ብለው እጅ ነሡት" (42፥6) የሚለውን የታሪኩን መደምደሚያ ያስተጋባል፤ ዮሴፍም "ስለ ወንድሞቹ ያየው ሕልም ትዝ አለው" (42፥9)።

የሁለቱን ሕልሞች ዐላማ መረዳት የምንችለው ዮሴፍ ራሱ በምዕ. 41 ላይ በተናገረው ቃል ነው፤ በዚህ ክፍል ዮሴፍ ሁኔታውን ለፈርዖን ሲያብራራ ሕልሙን ሁለት ጊዜ ሊያይ የቻለው፣ "ነገሩ ከእግዚአብሔር ዘንድ የተቈረጠ ስለ ሆነ ነው" (41፥32)። ልክ እንዲሁ እግዚአብሔር የዮሴፍን ሕልም ወደ ፍጻሜ ያመጣዋል። የሕልሙን ማእከላዊ ሐሳብ የዮሴፍ ወንድሞች በተናገሩት ቃል ማየት ይቻላል፡- "በላያችን ለመንገሥ ታስባለህ"፤ ይህም "ተጐንብሶ መስገድ" ማለት ንግሥናን መቀበል ማለት እንደ ሆነ ያመለክታል። የታሪኩን ምፀት የምናገኘው በመጨረሻ ይህ ንጉሣዊ ክብር ለዮሴፍ ቤት ሳይሆን ለይሁዳ ቤት ሲሰጥ ነው (49፥10)።

ሐ. ዮሴፍ ወደ ግብፅ ተጓዘ (37፥12-36)

12-18 ዮሴፍ መንገዱን ስቶ ሲባዝን አንድ ሰው አግኝቶት ከመለሰው በኋላ ወንድሞቹን በዶታይን አገኛቸው። የዚህን ታሪክ ዐላማ ለመረዳት ወንድሞቹን በግብፅ እንደ ተገናኛቸው ከሚያወሣው ከሁለተኛው ክፍል ታሪክ ጋር ማነጻጸር ይኖርብናል (ምዕ. 42-44)። ታሪኩ አበክሮ እንደሚያሳየው እያንዳንዱ ሁኔታ በእግዚአብሔር የተወሰነ ነው። በዚህ በዮሴፍ ታሪክ መጀመሪያ ላይ የዮሴፍ ወንድሞች ወደ እነርሱ ሲመጣ፣ "ሲያዩት . . . . ሊገድሉት ተማከሩ"። ልክ እንዲሁ በታሪኩ አጋማሽ ላይ ዮሴፍ በግብፅ "ወንድሞቹን ገና ሲያያቸው" (42፥7) ራሱን በመለወጥ ተሰወረባቸው፤ ምናባልባት እንዲህ ያደረገው እንዳያውቁትና እርሱም በተራው ሊያሤርባቸው ስላሰበ ነው፤ ላይ ላዩን ስናየው ሊገድላቸው ያስበ ይመስላል።

19-36 የወንድሞቹ ዕቅድና ሐሳብ በዝርዝር ተነግሯል። ከዕቅዳቸው በስተ ጀርባ የዮሴፍ ሁለት ሕልሞች አሉ። የዕቅዳቸው ሤራ ለእነዚህ ሕልሞች መፈጸም ምክንያት እንደሚሆን ጨርሶ አልጠረጠሩም። የመጀመሪያው ዕቅዳቸው እርሱን መግደል ነበር፤ ጉድጓድ ውስጥ ከጣሉት በኋላ "ክፉ አውሬ በላው" ብለን ለአባታችን እንነግረዋለን አሉ። የወንድማማቾቹ ዕቅድ ምፀታዊ በሆነ መንገድ መፈጸሙን ከገዛ አንደበታቸው የወጣው ቃል ይመሰክራል፡- "እስቲ ሕልሞቹ ሲፈጸሙ እናያለን" (42፥9)። ይህ የመጀመሪያ ዕቅዳቸው ዮሴፍን ከእጃቸው ባዳነው በሮቤል ተሰናከለ።

ወረድ ብሎ የሮቤል ሐሳብ በይሁዳ ሐሳብ ይበልጥ ሲጠናከር እናያለን። ዮሴፍን ከወንድሞቹ ዕቅድ ያዳነው ሮቤል ብቻ ሳይሆን፣ ይሁዳም ጉልሕ ሚና ተጫውቷል። እዚህም ላይ ያዕቆብ ይሁዳን በተመለከተ በ49፥8-12 ላይ የተናገረው የመጨረሻው ቃል ቊልፍ ስፍራ እንዳለው ማየት ይቻላል። የኋላ ኋላም የታሪኩ ማእከል ሲሆን የምናየው ይሁዳ ነው፤ የእግዚአብሔር በረከት የሚፈጸመው በእርሱ ነውና። ወደ ፊት የሚነሡት የተስፋው ዘሮች የይሁዳ ልጆች ናቸው። የሮቤል ዕቅድ ወንድሞቹን እንደ ምንም አግባብቶ ዮሴፍ ጉድጓድ ውስጥ እንዲጣልና በዚያው እንዲሞት ለማድረግ የፈለገ ሊመስለን ይችላል። ይሁንና የሮቤል ሐሳብ ጉድጓድ ውስጥ ከተጣለ በኋላ ተመልሶ መጥቶ ሊያድነው ነበር። የሮቤል ሐሳብ በከፊል ውጤታማ ነበር። ወንድሞቹ ዮሴፍን ከነ ሕይወቱ ጉድጓድ ውስጥ ጣሉት። የዮሴፍ እጀ ጠባብ የተወሣው የታሪኩን ማእከላዊ ሐሳብ ለማጉላት ሲሆን፣ የአሁኑ ዕቅድ በዮሴፍ ሕልም ላይ የተስተጋባው መለኮታዊ ዕቅድ አካል ነው።

“የእስማኤላውያን ” መምጣት የነገሩን አቅጣጫ ቀየረው። እነርሱም ይሁዳ ወደ ታሪኩ ሜዳ እንዲገባ ምክንያት ሆኑ፤ እርሱም ለወንድሞቹ “[ዮሴፍን] ለእስማኤላውያን ነጋዴዎች እንሽጠው” የሚል ሐሳብ አቀረበ። ከዚህ በኋላ የዮሴፍ ዕጣ ፈንታ ምን እንደ ሆነ የተገለጸው በጣም በጥቂቱ ነው። በዚህ ታሪክ ውስጥ እስማኤላውያን ከሚለው በተጨማሪ “ምድያማውያን” የተባሉ ሰዎች ሲመጡ ዮሴፍ ለእነርሱ በሃያ ጥሬ ብር ተሸጠ። እነርሱም ዮሴፍን ወደ ግብፅ ይዘውት ሄዱ።

እንደ እውነቱ ከሆነ የታሪኩ አትኩሮት ወደ ሮቤልና እርሱም ወዳቀረበው ዕቅድ የተመለሰው፣ ዮሴፍን በማዳን ረገድ ይሁዳ የተጫወተውን ሚና ለመግለጽ ነው። ቁጥር 29 እንደሚያመለክተው ሮቤል ዮሴፍን ለእስማኤላውያን ለመሸጥ ምንም ዐይነት ዕቅድ አልነበረውም። ዮሴፍን ለማግኘትና ለማዳን ወደ ጉድጓዱ ሲመለስ፣ ዮሴፍ ግን በዚያ አልነበረም። ዮሴፍ በዚያ ባለ መኖሩ በመደነቅ እጅግ ተቁጣ። እንግዲህ የዮሴፍን ሕይወት ያዳነው ሮቤል ሳይሆን ይሁዳ እንደ ሆነ በርግጠኝነት መናገር እንችላለን። በመጨረሻም ወንድማማቾቹ ወደ መጀመሪያው ዕቅዳቸው በመመለስ ዮሴፍን የገደለው “ክፉ አውሬ” ነው በማለት ለአባታቸው መናገር ሊኖርባቸው ነው።

እዚህም ላይ የዮሴፍ እጀ ጠባብ የታሪኩ አገናኝ ሆኖ ሲያገለግል እናያለን። ወንድማማቾቹ ለዮሴፍ የነበራቸው ጥላቻ ያዕቆብ የልጁን መጥፋት እንዲገነዘብ ምልክት ሆኖለታል። በመጨረሻ ከዮሴፍ የቀረው በደም የተነከረው እጀ ጠባቡ ብቻ ነበር፤ ያዕቆብ ይህን ሲያይ የራሱን እጀ ጠባብ ቀደደ፤ በምትኩም ማቅ ለበሰ። እንግዲህ በዚህ ታሪክ መክፈቻ ላይ የራሱ የያዕቆብ የልጆቹ ዕጣ ፈንታ በዐጭሩ ተገልጸልናል። በዮሴፍ ላይ የደረሰው ነገር በሙሉ በያዕቆብ ልጆች ላይ የሚደርሰውን ነገር ያስተጋባል። እነርሱም ወደ ግብፅ ይወሰዳሉ፤ በዚያም ባሮች ይሆናሉ። በዚህ ዐይነት ያዕቆብ የተናገረው የመጨረሻው ቃል ከዚህ በኋላ ለምናገኘው ታሪክ መንገድ ጠረገ፡- “በሐዘን እንደ ተኩራመትሁ ልጄ ወዳለበት መቃብር [ሲኦል] እወርዳለሁ።” ከሁሉ የሚገርመው የዮሴፍ ታሪክ የተደመደመው ያዕቆብ ልጁን አይቶ ለመሞት (50፥24-26) ወደ ግብፅ ሲወርድ ነው (46፥3-4)።

መ. ይሁዳና ትዕማር (38፥1-30)

1-11 የምዕራፍ 38 ታሪክ ከዮሴፍ ታሪክ ጋር ያለው ትስስር እምብዛም ነው። የመጀመሪያው ቁጥር እንደሚያሳየው እነዚህ ሁነቶች የተፈጸሙት “በዚያም ወራት” ነው። ይህ መግለጫ ባይኖር ኖሮ፣ ይህን ታሪክ ከዮሴፍ ታሪክ ጋር ለማያያዝ በቂ ምክንያት አይኖረንም ነበር። ይሁንና ከመላው የመጽሐፉ ስልት አንጻር ይህ ምዕራፍ ወሳኝ ሚና ይጫወታል።

ታሪኩ የሚጀምረው የሦስት ልጆችን ስም በመጥቀስ ነው (ከሦስቱ የአዳም፣ የኖኅና የታራ ልጆች ጋር ያነጻ)። ሁለቱ ልጆች በሠሩት ክፉ ነገር ሞቱ። ይህ የመግቢያ ቃል የሚያሳየን፣ የይሁዳ ቤት ህልውና ያለው በይሁዳ እጅ መሆኑን ነው። ከዚህ በታች የምናገኘው ታሪክ እንደሚያሳየው፣ የራሱን ቤተ ሰብ ለማቄየት ያደረገው አንዳች ነገር የለም። የይሁዳን ዘር ለማቄየት የትዕማር “ጽድቅ” ያስፈልግ ነበር (ቁ. 26)። ይህ ታሪክ የተስፋው ዘር ህልውና አደጋ ላይ ሲወድቅ ዘሩን ለማቄየት እምብዛም ካልጣረው ከሌላው የእስራኤል አባት ታሪክ ጋር ይመሳሰላል። በምዕራፍ 20 ላይ የአብርሃም ዘር የተጠበቀው “በጻድቁ” (አመት፣ “በንጹሑ”) አቤሜሌክ እንደ ሆነ ሁሉ፣ እዚህም ላይ የእስራኤል አባት ይሁዳ ሳይሆን ትዕማር ለይሁዳ ቤት ዘሮች መጠበቅ ምክንያት ሆነች።

ያዕቆብ ትዕማርን ለልጁ ሚስት አድርጎ የወሰደው ከማን ቤት እንደ ሆነ በምንባቡ ላይ አልተገለጸም። የራሱ የይሁዳ ሚስት ከነዓናዊት እንደ ሆነች ቢነገረንም፣ ትዕማርም ከነዓናዊት ብትሆን ኖሮ ተመሳሳይ ገለጻ ይሰጥ ነበር። ከነዓናዊት ባለ መሆኗ ይህ መግቢያ ለአብርሃም የተሰጠው ተስፋ አደጋ እንደ ገጠመው የሚያሳይ ሌላው ክፍል ነው። ይሁዳ የከነዓናዊ ልጅ በማግባቱ አብርሃምንና (24፥3) ይስሐቅን (28፥1) የሚያስጨንቃቸውን ብርቱ ፍርሀት ተገነዘበ፤ ስለዚህ የአብርሃምንና የይስሐቅን ዘሮች በተመለከተ የተነገረው ተስፋ ያለ መፈጸም አደጋ ገጠመው። ይሁንና በትዕማር ብልኀታዊ ዘዴ አማካይነት የአብርሃም ዘር ተጠበቀ፤ በከነዓናውያን ልጆች ማለትም በሴዋ ሴት ልጅ አማካይነት ግን እንዳይቀጥል ተደረገ። ዘሩ በይሁዳና በትዕማር በኩል ቀጠለ። በታሪኩ መዝጊያ ላይ የምናገኘው የትውልድ ሐረግ ለዚህ ነጥብ አጽንዖት ይሰጣል።

12-26 የትዕማር ዘዴ ከያዕቆብና ከርብቃ ዘዴ ጋር ይመሳሰላል (ምዕ. 27)። ራሷን በመቀየሯ የብኩርናው በረከት ተካፋይ ሆነች። እንዲህ በማድረጓ እንደ ያዕቆብና ርብቃ ሁሉ፣ የእስራኤል አባቶች ሊያገኙት የሚገባቸውን ነገር እርሷም አገኘች። የይሁዳ ልጅ ሴሎም ለዐቅመ አዳም የደረሰ በመሆኑ ትዕማር ሚስቱ ሆና ልትሰጠው ይገባ ነበር። ስለዚህ በመጨረሻ የይሁዳ ዘር ሊቀጥል የቻለው በይሁዳ የጽድቅ ተግባር ሳይሆን “በጻድቋ” በትዕማር ነው።

27-30 የያዕቆብ መላ ታሪክ በሚያስደንቅ ሁኔታ የተጠናቀቀው ስለ ፋሬስና ስለ ዛራ በተነገረው ዐጭር ታሪክ ነው። የያዕቆብ ታሪክ በመንትዮች ትግል እንደ ጀመረ ሁሉ (25፥22)፣ አሁንም ታሪኩ ሲደመደም የምናየው በተመሳሳይ ትግል ነው። በሁለቱም ትግሎች እንደምናየው የበኩሮች መብትና የበረከት መብት ተቀልብሷል። በውጤቱም ታናሹ በታላቁ ላይ የበላይ ሆነ። ያዕቆብ ከዔሳው ጋር ታግሎ እንዳሸነፈ ሁሉ፣ ፋሬስም ታላቁን ዛራን አሸንፎ የብኩርናን መብት አገኘ (ከዘጉ 26፥20 ጋር ያነጻ፤ በዚህ ስፍራ ፋሬስ የተቈጠረው እንደ በኩር ልጅ ነው)። የታሪኩ እጥር ምጥን ማለት የምንባቡን ትርጉም ለተደራሲያኑ የተተወ አስመስሎታል። በመሠረቱ ታሪኩን የምናገኘው ታናሹ በታላቁ ላይ ሲሠለጥን በምናየው ረጅም ታሪክ ውስጥ በመሆኑ ትርጉሙ እምብዛም ስውር አይደለም።

ሠ. ዮሴፍ በጲጥፋራ ቤት (39፥1-23)

1 መሀል የገባው የይሁዳ ታሪክ ሳይዘነጋ፣ ምንባቡ የዮሴፍን ታሪክ የሚጀምረው ምዕ. 37 ካቆመበት ነው። በ37፥27 ላይ እንደምናነበው ዮሴፍን ወደ ግብፅ ያመጡት ሰዎች “እስማኤላውያን” ተብለው እንደ ተጠሩ ሁሉ በ37፥28፣36 ላይ “ምድያማውያን” ተብለው ተጠርተዋል።

2-6 ቁጥር 2 የታሪኩን መላ ጭብጥ ይናገራል፡- “እግዚአብሔር ከዮሴፍ ጋር ነበረ፤ ሥራውም የተከናወነለት ሰው ሆነ”። ቁጥር 3-6 ጭብጡን ከዚህ በኋላ ከምናገኛቸው ሁነቶች ጋር ያስተሳስረዋል። ይኸውም ዮሴፍ በእግዚአብሔር መባረኩን ግብፃዊው ጌታ ተገንዝቦ ዮሴፍን በቤቱ ሁሉ ላይ ሾመው። እንደ አባቱ እንደ ያዕቆብ ሁሉ (30፥27) ዮሴፍም በግብፅ የመጻተኛነት ሕይወት ሊያሳልፍ የቻለው፣ “የምድር ሕዝቦች ሁሉ በአንተ አማካይነት ይባረካሉ” (12፥3) ተብሎ ለአብርሃም በተሰጠው ተስፋ ምክንያት ነው። በመሆኑም “እግዚአብሔር የግብፃዊውን ቤት ስለ ዮሴፍ ባረከው” የሚል እናነባለን። ይህ ጭብጣዊ መግቢያ በመላው ታሪኩ ውስጥ ሊነገር የተፈለገው ዐቢይ ሐሳብ ምን እንደ ሆነ ለማወቅ ተደራሲያኑ ዝግጁ እንዲሆኑ ያደርጋል። ይህ ታሪክ ስለ ዮሴፍ ስኬት የሚናገር ታሪክ አይደለም፤ ይልቁንም እግዚአብሔር ለተስፋ ቃሉ የታመነ አምላክ መሆኑን የሚመሰክር ታሪክ ነው። በዚህ መግቢያ ላይ ስለ ዮሴፍ የተሰጠው መግለጫ ከዚህ በኋላ ለሚነገረው ነገር እንደ መንደርደሪያ ያገለግላል።

7-20 ይህ ስለ ዮሴፍ የተነገረው ታሪክ በእሥራኤል አባቶች ታሪክ ውስጥ የምናገኘውን ዕውቅ ሚራ ቀልብሶታል። ከዚህ በፊት በባዕዳን ገዦች የተፈለጉት የአባቶች መልከ መልካም ሚስቶች ነበሩ (12፥11፤ 26፥7)፤ አሁን ግን በባዕዳን ገዦች ሚስት የተፈለገው መልከ መልካሙ ዮሴፍ ነው። ቀደም ባለው ታሪክ ሚስቶቻቸውን የታደገው ከአባቶች ይልቅ ራሱ እግዚአብሔር (12፥17፤20፥3) አልያም የባዕዳን ገዦቹ ምግባራዊ ንጽሕና ነበር (26፥10)፤ አሁን ግን ውድቀቱን የታደገው የራሱ የዮሴፍ ምግባራዊ ንጽሕና ነው። ቀደም ባለው ታሪክ አትኩሮት የተሰጠው የኪዳኑን ተስፋ በሚፈጽመው የታመነ አምላክ ላይ ነበር፤ የዮሴፍ ታሪክ አትኩሮት ግን በሰዎች ምላሽ ላይ ነው።

ምንም እንኳ አብርሃም፣ ይስሐቅና ያዕቆብ በእግዚአብሔር ቢያምኑም፣ በተደጋጋሚ ግን እግዚአብሔር ከሚጠብቃቸው ደረጃ ወድቀዋል። ይሁንና ዮሴፍ ለእግዚአብሔር በመታመንና ለፈቃዱም በመታዘዝ ያሳየው ፍጹም ምላሽ እጅግ የሚያስደንቅ ምሳሌ ያደርገዋል። የዮሴፍ ታሪክ በ18፥19 ላይ የተነገረው ተስፋ ትርጉሙ ምን እንደ ሆነ በሚገባ ያስረዳናል፡- “ትክክለኛና ቀና የሆነውን በማድረግ የእግዚአብሔርን መንገድ ይጠብቁ ዘንድ ልጆቹንና ከእርሱ በኋላ ቤተ ሰቦቹን እንዲያዝ መርጬዋለሁ”። የእግዚአብሔር ዕቅድ ይፈጸም ዘንድ ሰዎች የሚጫወቱት ሚና አለ። የእግዚአብሔር ሕዝቦች እንደ ዮሴፍ ምላሽ ሲሰጡ፣ መንገዳቸው ይቃናላቸዋል፤ የእግዚአብሔርም በረከት ይፈጸምላቸዋል። እጅግ የሚያስገርመው በመላው ኦሪት ዘፍጥረት ውስጥ በእግዚአብሔር መንፈስ እንደ ተሞላ የተነገረው ዮሴፍ ብቻ ነው (41፥38)። ግብፃዊቷ ሴት ልታጠምደውና ልትጥለው በሸረበችው ሤራ ሁሉ ንጹሕ ሰው እንደ ሆነ በታሪኩ ላይ አጽንዖት ተሰጥቶታል። ሐሰተኛ ምስክሮች በሰጡት ቃል እስር ቤት ተጣለ።

21-23 የመዝጊያው አጽንዖት ግልጽ ነው። እግዚአብሔር በዮሴፍ ላይ የተደረገውን ክፉ ነገር ሁሉ ለበጎ አደረገው።

እግዚአብሔር ከዮሴፍ ጋር በመሆን ሥራውን አከናወነለት። ከዮሴፍ ታሪክ የምንማረው ትልቁ ነገር በእነዚህ ቃሎች ታጠቃሏል፦ “እናንተ ክፉ ነገርን ዐሰባችሁብኝ፤ እግዚአብሔር ግን ለመልካም ዐሰበው” (50፥20)። በምርኮ ዘመን እንደ ዳንኤል ሁሉ፣ ዮሴፍም ቅን የሆነውን ነገር በማድረግ መከራ ተቀበለ፤ እግዚአብሔር ግን ክፉውን ለበረከት አደረገው።

ረ. ዮሴፍ በእስር ቤት (40፥1-23)

1-23 ምዕራፍ 40 የዮሴፍን ታሪክ በማጕልበት ረገድ የሚጫወተው ሚና መሠረታዊ ነው። ዮሴፍ ቢጣልም፣ ከዚያ ተነሥቶ የላቀ ደረጃ ላይ ደረሰ። ዮሴፍ በእስር ቤት ሳለ፣ እስር የተፈረደባቸው፤ ሁለት የንጉሥ ሹማምት እንዲጠብቅ ተደረገ። ሁለቱ ሹማምት ሕልም ዐልመው ዮሴፍ በትክክል ተረጕመላቸው፤ ይሁንና ከእስር የተፈታው ሹም ነገሩን ሁሉ ረሳው። ከጊዜ በኋላ ፈርዖን ራሱ ሕልም ዐለመ፤ የጠጅ አሳላፊዎቹ አለቃ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የሆነውን ነገር አስታውሶ ለንጉሡ ስለ ዮሴፍ ነገረው። እንደ ዳንኤል ሁሉ በዚህ ታሪክ ላይ ዮሴፍ የቀረበልን እንደ ሕልምና ምስጢር ተርጓሚ ሆኖ ነው። ለሌሎች ፍጹም የተሰወረውን የወደፊቱን ታሪክ እርሱ ገለጠው።

የጠጅ አሳላፊዎቹ አለቃ ሕልም ትርጕም ግልጽ ነው፤ ይሁንና የእንጀራ አበዛዎቹ አለቃ ሕልም እንደሚያሳየው፣ ይህ ግልጽ የሚመስለው ትርጕም ምን እንደ ሆነ በትክክል አይታወቅም። የሁለቱን ሕልሞች ትርጕም መናገር የሚችል ማን ነው? አንደኛው የተወደሰ፣ ሌላው ያልተወደሰ ነው። በግልጽ ከምናየው ባሻገር ሕልሞቹ የሚያስተላልፉት የላቀ መልእክት አለ። በዚህ ታሪክ ውስጥ የምናየው የዮሴፍ ምስል ፈርዖን ራሱ እንደ ተናገረው ነበር፦ ዮሴፍ “የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት ሰው ነው” (41፥38)። ዮሴፍ የሕልሞቹን ትርጕም ያውቃል፤ እርሱ ራሱ እንደ ተናገረው “ሕልምን የሚተረጕም እግዚአብሔር ” ነው (40፥8)። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ከእርሱ በፊት ከነበሩት ሁሉ የተለየ ነው። “ብልኅና ዐዋቂ” ሰው ከመሆኑም በላይ (41፥39)፣ ነገሮች ሁሉ እርሱ እንደ ተረጕማቸው ይሆኑ ነበር (41፥13)። አብርሃም “ነቢይ” (20፥7) ነበር፤ ዮሴፍ ግን “ብልኅና ዐዋቂ” (41፥39) ሰው ነበር። አብርሃም መጪውን ታሪክ የተመለከተው በራእይ (15፥1) ነበር፤ ዮሴፍ ግን መጪውን ታሪክ ይገልጥ የነበረው (41፥39) በሌሎች ሰዎች ምስጢራዊ ሕልም ነበር።

ሰ. ዮሴፍ የፈርዖንን ሕልም ተረጐመ (41፥1-36)

የምዕራፍ 41 ዐቢይ ጭብጥ የተነገረው በቁ. 32 ላይ በራሱ በዮሴፍ ነው፦ “ሕልሙም ለፈርዖን በሁለት መልክ በድጋሚ መታየቱ ነገሩ ከእግዚአብሔር ዘንድ የተቈረጠ ስለ ሆነ ነው”። አንድ ዐይነት ትርጕም ያላቸው ሁለቱ ሕልሞች የሚያሳዩን፣ እግዚአብሔር በሕልሞቹ የታየውን ነገር በርግጥ ከፍጻሜ እንደሚያመጣው ነው። ቀደም ባለው ምዕራፍ “ሁለቱ” የንጉሡ ሹማምት ሕልም አይተው ነበር። አንደኛው ሕልም መልካም ሲሆን ሌላው ግን መጥፎ ነበር። ሕልሞቹና ትርጕማቸው ሁለት ጊዜ ተወሥተዋል፤ አንድ ጊዜ በምዕ. 40 ላይ የተወሣ ሲሆን፣ በድጋሚ ደግሞ በጠጅ አሳላፊዎቹ አለቃ በፈርዖን በቁ. 9-13 ላይ ተወሥቷል። “ከሁለቱ ዓመት” በኋላ ንጉሡ ራሱ “ሁለት” ሕልሞችን አየ። የሁለቱም ሕልሞች ገሚሱ ክፍል መልካም ሲሆን (ቁ. 29)፣ ገሚሱ ክፍል ደግሞ መጥፎ ነበር (ቁ. 27፡30)። በታሪኩ ውስጥ እያንዳንዱ ሕልም ሁለት ጊዜ ተወሥቷል፤ አንድ ጊዜ በራሱ በጸሓፊው፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ በፈርዖን። በሰዎች ታሪክ ውስጥ እንዲህ ያለው ማጠቃለያ የመለኮት ሥራ ምስክር ነው።

1-8 ሁለቱ ሹማምት ካዩአቸው ሕልሞች ይልቅ ፈርዖን ያየው ሕልም ግልጽ ነው። የሁለቱን ሕልሞች ትርጕም ከሕልሞቹ ይዘት መረዳት ይቻላል። ሰባቱ መልካም ላሞችና ሰባቱ እሸቶች ሰባቱ መልካም ዓመቶች ናቸው። ሰባቱ አስቀያሚ ላሞችና ሰባቱ አስቀያሚ እሸቶች ሰባቱ መጥፎ ዓመቶች ናቸው። ጸሓፊው የሕልሞቹ ቀላልነት ትርጕሙን ከመሰወር ይልቅ እንደሚገልጥ ለማሳየት ሲል፣ የንጉሡ ጠንቋዮችና ጠቢባን ሁሉ ሕልሞቹን መፍታት እንዳልቻሉ ይነግረናል (ከዳን. 2፥4-12 ጋር ያነጻ)። ዮሴፍ ከሕልሞቹ በመነሣት ወደ ፊት ለሚመጣው ነገር ዝግጅት እንዲያደርግ መከረ። እንደ ሕልሞቹ ትርጕም ሁሉ ዮሴፍ በሕልሞቹ ለተመለከተው መጪ ሁኔታ የሰጠው ብልኅ ምክር እጅግ ወሳኝ ነው። የዮሴፍን ብልኅነት ይበልጥ የምናየው ምስጢራዊ በሆኑ ነገሮች ባለው ዕውቀቱ ሳይሆን በማቀድና በማስተዳደር ነው።

9-13 ምንም እንኳ የጠጅ አሳላፊው ዮሴፍን ቢረሳውም፣ የዮሴፍ ትርጓሜ በጊዜ ውስጥ የጸና መሆኑን አስታወሰ። ሌላው ቀርቶ የጠጅ አሳላፊው መርሳት ለዮሴፍ መልካም ነገርን አስገኝቶለታል፤ ምክንያቱም ዮሴፍን አስታውሶ ስለ ዮሴፍ አስተዋይነት ለንጉሡ የተናገረው በተገቢው ጊዜ ነበር። ጸሓፊው የተደራጅነታችን አትኵሮት ቀደም ባሉት ምዕራፎች ወደ ተከናወኑት ሁኔቶች በመመለስ የዮሴፍ አስተዋይነትና የእግዚአብሔር ሉዓላዊ አሠራር ጕልተው እንዲታዩ አድርጓል። የዮሴፍ አስተዋይነት አጽንዖት እንደ ተሰጠው የምናውቀው ከግብፃውያኑ ጠቢባን ይልቅ “የአንድ ዕብራዊ ወጣት” ትርጓሜ እውነት ሆኖ በመገኘቱ ነው። እዚህ ላይ የእግዚአብሔር ሉዓላዊ ሥልጣን አጽንዖት ተሰጥቶታል። ምንም እንኳ የጠጅ አሳላፊው በወቅቱ ዮሴፍን ቢረሳውም፣ በትክክለኛው ጊዜ ግን አስታውሶታል፤ ይህም፣ ዮሴፍ ሥልጣን ለመጨበጥ የሚያስችለውን አጋጣሚ ፈጠረለት።

14-36 ፈርዖን ሕልሙን በድጋሚ ሲናገር ሁለት ዐቢይ ነገሮችን አክሏል፤ ይኸውም እንደ ቀድሞው ሁሉ አስቀያሚዎቹ ላሞች መልካሞቹን ላሞች ከዋጧቸው በኋላ መልካቸው አስቀያሚ (በቁሙ የከፋ) መሆኑን ነው። ሕልሙ በድጋሚ የተነገረው ከመጀመሪያዎቹ መልካሞቹ ላሞች በተቃራኒ መልካቸው ክፉ ስለ ሆኑት ላሞች በአጽንዖት ለመግለጽ ነው።

ስለ “መልካም” እና “ክፉ” በአጽንዖት ሲነገር፣ ዮሴፍ “መልካምን” እና “ክፉ” ለመለየት ችሎታ እንዳለው ያሳያል። በመሠረቱ እንዲህ ዐይነቱ ዕውቀት ሊገኝ የሚችለው ከእግዚአብሔር ብቻ (ቁ. 39) በመሆኑም ቀደም ባሉት የዘፍጥረት ምዕራፎች ላይ የተወሣው መሠረታዊ ትምህርት በእነዚህ የመጨረሻዎቹ ምዕራፎችም ላይ ልዩ በሆነ ክህሎት በድጋሚ ተወሥቷል። ነገሩን ከዚህ አንጻር ካጤንነው፣ የዮሴፍ ዕቅድ ለፈርዖንና ለአገልጋዮቹ በሙሉ “መልካም” ሆኖ መታየቱ የአጋጣሚ ጕዳይ ነው ለማለት አያስደፍርም።

ሸ. ዮሴፍ በግብፅ ላይ ከፍ ከፍ አለ (41፥37-57)

37-57 ንጉሡ ዮሴፍን በመላው መንግሥቱ ላይ እንደ ሾመው የሚያወሣው ታሪክ ዮሴፍን የሚያሳየን በዘፍ 1 ላይ እንደምናገኘው አዳም ነው። አዳም “መልካምንና ክፉን” ለመለየት በእግዚአብሔር መደገፍ እንዳለበት ሁሉ፣ ዮሴፍም በዚህ ክፍል የተሣለው በተመሳሳይ መንገድ ነው። አዳም የእግዚአብሔር “እንደ ራሴ ” ሆኖ መላውን ምድር ለመግዛት እንደ ተሾመ ሁሉ፣ ዮሴፍም የፈርዖን “እንደ ራሴ ” ሆኖ መላውን ምድር እንዲገዛ ተሾመ። አዳም መላውን ምድር ለመግዛት በእግዚአብሔር አምሳል ተፈጠረ፤ ንጉሡም “በስሙ የተቀረጸውን ቀለበት” ለዮሴፍ ከሰጠው በኋላ የንጉሥ ልብስ አለበሰው። እግዚአብሔር ለአዳም ሚስትና መላዱቱን ምድር ደስ እንዲሰኝባት እንደ ሰጠው ሁሉ፣ ንጉሡም ለዮሴፍ ሚስት ሰጠው፤ በመላው ምድርም ላይ ሾመው።

በዚህ ታሪክ ውስጥ ዮሴፍ የቀረበው አንድ አስተዋይና የታመነ ሰው ማለት ምን ዐይነት እንደ ሆነ የሚያሳየን “የተለየ” ሰው ሆኖ ነው። ዮሴፍ የእውነተኛ ሰውና የእውነተኛ ንጉሥ ምሳሌ ነው። አዳም ያላደረገውን ነገር በሙሉ እርሱ አደረገ። የዮሴፍ ታሪክ አዳም ለእግዚአብሔር የታዘዘና በእርሱም የታመነ ሰው ቢሆን ኖሮ፣ ነገሩ ምን ሊመስል እንደሚችል የሚያሳየን መስተዋት ነው። ደግሞም የዮሴፍ ታሪክ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ልክ እንደ ዮሴፍ እግዚአብሔርን በፍጹም በመታዘዝና እርሱንም በመታመን ቢኖሩ፣ ነገሩ ምን ሊሆን እንደሚችል የሚያስተጋባም ነው። እንግዲህ የዮሴፍ ታሪክ ወደ ኋላ ወደ አዳም ቢመለከትም፣ ከዚህ ይበልጥ ግን ገና ወደ ፊት ወደ ሚመጣው ማለትም ከይሁዳ ቤት ወደ ሚወጣውና መንግሥት ሁሉ የእርሱ ወደ ሆነው አሻግሮ ይመለከታል (49፥10)። በመሆኑም በዮሴፍና በይሁዳ ቤቶች መካከል የተፈጠረው ውጥረት የረገበው የዮሴፍ ሕይወት ከይሁዳ ቤት ለሚመጣው ነጋሤ ምሳሌ እንዲሆን በማድረግ ነው።



እነዚህ ትልቅ የጥንዝዛ ምስል የተቀረጸባቸው ቀለበቶች፣ ዮሴፍ ከፈርዖን ተቀብሏቸዋል ከሚባሉ ቀለበቶች ጋር ተመሳሳይ ናቸው።

ቀ. የዮሴፍ ወንድሞች በግብፅ (42፥1-28)

በቀደመው ምዕራፍ ላይ ዮሴፍ ወደ ሥልጣን እንደ ወጣ ተዘግቧል። ይህ ምዕራፍ ደግሞ ዮሴፍ ወደ ሥልጣን ሲወጣ ከበስተ ጀርባው የነበረውን መለኮታዊ ዐላማ ያወሣል።

1-2 *ታሪኩ ከምዕ. 37፥34 በኋላ ስሙ ወዳልተነሣው ያዕቆብ ይመለሳል። ብዙ ጊዜ በቅዱሳት መጻሕፍት ታሪካዊ ዘገባዎች ላይ እንደሚታየው ሁሉ፣ በታሪኩ መጀመሪያ ላይ የምናገኛቸው ቃሎች የታሪኩን ውጤት ያስተጋባሉ። ያዕቆብ ልጆቹን ወደ ግብፅ ሲልክ እንዲህ አላቸው፡- “ወደዚያ ወረዱ . . . እንድንድንና እንዳንሞት” (ከ45፥5 ጋር ያነጻ)።*

3-13 *በመላው ታሪኩ ውስጥ የያዕቆብ “ዐሥራ ሁለት” ልጆች በሁለት ቡድን ተከፍለዋል። እነርሱም “የዮሴፍ ዐሥሩ ወንድሞች” እና ያዕቆብ ከራሔል የወለዳቸው ሁለቱ ልጆች ማለትም ዮሴፍና ብንያም ናቸው። ሁለቱ ልጆች ከልያ ሁለት ልጆች ማለትም ከሮቤልና ከይሁዳ ጋር ተነጻጽረዋል። በታሪኩ ውስጥ ሮቤልና ይሁዳ ጉልሕና ተመሳሳይ ሚና ይጫወታሉ። በሌሎቹ ወንድሞች ስም ሆነው ሲናገሩና በዮሴፍ የታቀደው የሤራ ውሳኔ ላይ ለውጥ አምጪዎች ሆነው እናያለን። ይሁንና ራሱን በወጣቱ ልጅ በብንያም ምትክ በማስያዝ የዚያን ዕለት ያተረፋቸው ይሁዳ ነው። ደግሞም “እኛና አንተ ልጆቻችንም እንድንድን እንዳንሞትም” በማለት የያዕቆብን ጭብጣዊ ቃሎች በድጋሚ የተናገረው ይሁዳ ነው (43፥8፤ ከ42፥2 ጋር ያነጻ)። በመጨረሻም፣ በአባቱ በያዕቆብ ላይ ምንም ዐይነት ክፉ ነገር እንዳይደርስ በማሰብ በዮሴፍ ፊት ራሱን በብንያም ምትክ ለመስጠት ፈቃደኛ መሆኑን የገለጸው ይሁዳ ነው (44፥33-34)።*

በታሪኩ ውስጥ ሤራው የተጐነጐነው ዮሴፍና ይሁዳ በሚጫወቱት ቁልፍ ሚና ነው፤ በመጨረሻ ግን ግጭቱን የሚፈታው ይሁዳ ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ በታሪኩ ውስጥ የግጭቱና የውጥረቱ ፈጣሪ ዮሴፍ ነው። ወንድሞቹ እህል ለመሸመት ወደ እርሱ ሲመጡ ራሱን “ለወጠባቸው”፤ ሰላይ ናችሁ በማለትም ከሰሳቸው። ቁጥር 9 ዮሴፍ በወንድሞቹ ላይ ሊያሤርና ሊያደባ የተነሣው ወንድሞቹ በእርሱ ላይ በፈጸሙት በደል ተገፋፋቶ ሳይሆን ቀደም ሲል ባየው ሕልም እንደ ሆነ ይገልጻል።

ሰላይ ናችሁ በማለት ዮሴፍ ላቀረበባቸው ክስ ወንድማማቾቹ መልስ ሲሰጡ፣ “ባሪያዎችህ ዐሥራ ሁለት ወንድማማቾች” ነን በማለት ራሳቸውን ተከላከሉ፤ ሐቀኛነታቸውንም ለማሳየት ሲሉ “አንዱ ግን የለም” አሉ። የዮሴፍ ዘዴ የሚያሳየን፣ ከዚህ በፊት በእርሱ ላይ የፈጸሙት በደል አሁን ክፉ መዘዙን ይዞባቸው መምጣቱን ነው። ወንድማማቾቹ ይህን ድርጊት ለአባታቸው ሲናገሩ (ቍ. 32) ሁኔታውን የገለጹት እነርሱ ራሳቸው በቍ. 13 ላይ ከተናገሩት በተለየ መንገድ ነው። እዚህ ላይ በመጀመሪያ የጠቀሱት “አንዱ ግን የለም” የሚለውን ቢሆንም፣ ዮሴፍ ስላቀረበባቸው ክስና እነርሱም ስለ ሰጡት መልስ ለአባታቸው ሲናገሩ “አንዱ ግን የለም” የሚለውን የጠቀሱት በመጨረሻ ነው፤ ከዚያም ብንያም ከአባታቸው ጋር በቤት እንደሚገኝ ተናገሩ። አነጋገራቸው ብልጣ ብልጥነት ቢታይበትም፣ ነገሩን መቀልበሳቸው ግን በዮሴፍ ላይ የፈጸሙት በደል ሁልጊዜ ጎሊናቸውን ይወቅሣቸው እንደ ነበር ያሳያል።

ዮሴፍ ወንድሞቹን ግራ ለማጋባት እንዳሰበ የሚያሳየን ሌላው ነጥብ፣ እህል ለመግዛት የከፈሉትን ገንዘብ በስልቻዎቻቸው ውስጥ ተመልሶ ሲያገኙት የተናገሩት ቃል ነው። ገንዘቡ ተመልሶ ሲያዩ “እግዚአብሔር ምን ሊያመጣብን ይሆን? ” አሉ (ቍ. 28)። ለማለት የፈለጉት ምንም ይሁን ምን ከአፋቸው የወጣው ቃል ስለ እነርሱ የሚናገረው እውነት አለ። ምንም እንኳ ገንዘቡን በስልቻዎቻቸው ውስጥ እንዲመለስ ያደረገው ዮሴፍ እንደ ሆነ ብናውቅም፣ የተናገሩት ቃል ወደ እግዚአብሔር ሥራ ይጠቀሙናል፤ ይህም የታሪኩን አቅጣጫ የሚወስነው ማን እንደ ሆነ ያረጋግጥልናል።

14-24 *ዮሴፍ ወንድሞቹን ለመፈተን ሁለት ዕቅዶች ነደፈ፤ አንደኛው ዕቅድ ከመካከላቸው “አንዱ” ተመልሶ ታናሹን እንዲያመጣ፣ የቀሩት ደግሞ እንዲታሰሩ የሚገልጽ ነበር። ከሦስት ቀን በኋላ ሁለተኛው ዕቅድ ተገለጸ፤ ከመካከላቸው “አንዱ” እንዲታሰርና የተቀሩት ተመልሰው ታናሹን እንዲያመጡ ያሳስባል። አትኩሮቱ “አንደኛው” ወንድም ሌሎቹን እንዲታደግ ነው። በታሪኩ ውስጥ ይህ “አንደኛው” ወንድም “አንዱ ግን የለም” የሚለውን ያስተጋባል። እንግዲህ ወንድማማቾቹ ራሳቸው የተናገሩት ቃል ይህ ሁሉ የደረሰባቸው በዮሴፍ ላይ በፈጸሙት በደል እንደ ሆነ ቢመሰክርባቸው ምንም አያስደንቅም። አሁን ስለ ደረሰባቸው ሐዘን ሲናገሩ ስናይ፣ የዮሴፍ ዘዴ ወዴት ሊያመራ እንደሚችል ለመገመት አያዳግትም። ሮቤል የተናገረው ቃል ዋናውን ሐሳብ ይገልጻል፡- “ደሙ ከእኛችን ይፈለጋል”። የዮሴፍ ዕቅድ ወንድሞቹ በእርሱ ላይ የፈጸሙትን በደል ለመበቀል አይደለም፤ ይልቁንም በእግዚአብሔር ዓለም ወንድማማቾች የፈጸሙት “በደል” በራሳቸው ላይ ተመልሶ እንደ መጣባቸውና ፍትሕም እንደሚያስፈልገው ለማሳየት ነው። በታሪኩ ውስጥ የምናገኘው አስደናቂ መልእክት ዮሴፍ ወንደሞቹን ገና ድሮ ይቅር ብሏቸው ነበር፤ በዕቅዱ ምክንያት እጅግ ስላዘነ፣ ሐዘኑን ለመደበቅ ከፊታቸው ዘወር ማለት ነበረበት። ወንድሞቹን የጠበቃቸው፣ በዮሴፍ ላይ ያሰቡት “ክፉ” ነገር ሳይሆን በዮሴፍ አማካይነት እግዚአብሔር ለእነርሱ ያሰበላቸው “መልካም” ነው (50፥20)።*

25-28 *የዮሴፍ ቀጣዩ ዕቅድ ወንድሞቹ እህል ለመያዣ ያመጡትን ስልቻ በገንዘብ መመላት ነበር (የቍ. 3-13 ማብ. ይመ)። ከዚህ ሁሉ በስተ ጀርባ እግዚአብሔር አለ፤ በዚህም ሁሉ ፈቃዱን ይፈጽም ነበር።*

በ. የዮሴፍ ወንድሞች ብንያምን ለማምጣት ተመለሱ (42፥29-38)

29-38 *የዚህን ምዕራፍ ድርጊቶች በወንድማማቾቹ አማካይነት እንደ ገና ሲነገሩ እናያቸዋለን። አትኩሮታቸው ታናሹ እንዲመጣ ባደረገው በዮሴፍ ዕቅድ ላይ ነበር። ያዕቆብ በልጆቹና በዮሴፍ መካከል የሆነውን ነገር ሁሉ ያወቀ ይመስል፤ በቍ. 36 ላይ የተናገረው ቃል ከጠረጠረው በላይ እውነት ነበር። ወንድሞቹ ዮሴፍን ወስደውበታል፤ ስምዖንም ዐብሮአቸው ሊመጣ ያልቻለው በእነርሱ ምክንያት ነው፤ አሁን ደግሞ ብንያምን ሊወስዱ ነው። እንግዲህ ከአባታቸው አነጋገር እንደምንረዳው በዮሴፍ ላይ የፈጸሙት በደል እስከ አሁን ድረስ እየተከተላቸው ነው።*

የሮቤል መልስ አስገራሚ ነው። ብንያምን በርግጥ መልሶ እንደሚያመጣው ሲናገር ከልቡ ነበር፤ ይሁንና በታሪኩ ዐውድ ውስጥ ንግግሩ በያዕቆብ ቍስል ዕንጨት እንደ መስደድ ነው። ያዕቆብ ለሮቤል የሰጠው መልስ የሮቤልን ቃል የሚያጣጥል ብቻ ሳይሆን የዮሴፍን መጥፋት በድጋሚ የሚያስታውስ ነው።

ተ. የዮሴፍ ማንነት (43፥1-45፥28)

1 የዮሴፍ ወንድሞች ዳግመኛ ወደ ግብፅ ሄዱ (43፥1-34)

1-14 *በዮሴፍ መላ ታሪክ ውስጥ ከምናገኛቸው “ጥንድ” ድርጊቶች ሳንወጣ፣ ታሪኩ የሚጀምረው የያዕቆብ ልጆች ወደ ግብፅ “ዳግመኛ” ሲሄዱ ነው። ረኃቡ አሁንም በምድሪቱ እንደ ጸና ነው፤ ቀደም ሲል የተገዛውም እህል ዐልቋል። ስለዚህ አባት ልጆቹን እንደ ገና እህል እንዲያመጡ ላካቸው። በዚህ ጊዜ ይሁዳ በዮሴፍ ጥያቄ መሠረት ብንያምን ይዘን መሄድ አለብን ሲል አጥብቆ ተናገረ።*

ይሁዳ አባቱን ደስ ለማሰኘት ሲል፣ ብንያም ወደ ግብፅ ዐብሯቸው እንዲሄድ የሚፈቀድለት ከሆነ ሙሉ ኀላፊነቱን እርሱ እንደሚወስድ አረጋገጠ። ሮቤልና ይሁዳ ብንያም ወደ ግብፅ በደኅና ስለሚወሰድበት መንገድ የሰጡት ሐሳብ በምዕ. 38 ላይ የተገለጸውን ድርጊትና በዮሴፍ ላይ የተፈጸመውን በደል ያስታውሰናል። በዚያ ምዕራፍ ላይ እንደ ተገለጸው፣ ሮቤልና ይሁዳ የዮሴፍን ሕይወት ለማዳን ሙከራ አድርገዋል (37፥21፡26)። በዚህ ክፍል ደግሞ ዮሴፍ በወንድሞቹ ላይ ካቀደው ውጥን ብንያምን ለማዳን ሞከሩ። ትዕግሥቱን የጨረሰው ይሁዳ እስከ አሁን “ሁለት ጊዜ” ግብፅ ደርሰን መመለስ እንችል ነበር በማለት ቍጭቱን ገለጸ (ከ41፥32 ጋር ያነጻ)።

ያዕቆብ በነገሩ ተስማማ። የዮሴፍን ሕይወት ያዳነው የይሁዳ ዕቅድ እንደ ነበረ ሁሉ (37፥26)፣ አሁንም የስምዖንን፣ በመጨረሻም የብንያምን ሕይወት ያዳነው የእርሱ ዕቅድ ነው። ያዕቆብ በቍ. 14 ላይ (በተለይ “በምሕረቱ” የሚለውን ቃል ልብ ይሏል) የተናገረው የመሰናበቻ ቃል ከዚህ በኋላ ለምናገኘው ታሪክ ቍልፍ ነው። በታሪኩ መደምደሚያ ማለትም ልጆቹ ዮሴፍ ዘንድ ሲደርሱና እርሱም ብንያምን ሲያየው፣ ለወንድሞቹ ከመራራቱ የተነሣ “ስሜቱ በጥልቅ ተነካ” የሚል እናነባለን (ቍ. 30)። ዮሴፍ ለወንድሞቹ ያን ያህል ሊራራላቸው የቻለው፣ “ሁሉን ከሚችል አምላክ” የተነሣ እንደ ሆነ ልብ ልንል ይገባል።

15-25 *ወንድማማቾቹ “ሰላይ” ናችሁ ተብለው የተከሰሱበት ነጥብ ዳግመኛ አልተነሣም (42፥9)። ወደ ዮሴፍ ቤተ መንግሥት ሲገቡ በልባቸው የነበረው ፍርሀትና ጭንቀት በዚህ ጉዞአቸው አንዳች መልካም ነገር እንደማይገኝ የነበራቸውን ሐሳብ ይገልጻል። ይሁንና ወንድማማቾቹ ታላቅ ግብዣ ሊደረግላቸው እንደ ተወሰዱ*

በመጀመሪያ ተነግሮናል። በቍጥር 18 ላይ የነበራቸው ፍርሀት የተሳሳተ እንደ ሆነ እናውቃለን። የዮሴፍ ባሮች ቢሆኑም እንኳ አንዳች መፍራት አይገባቸውም።

ወንድማማቾቹ በስልቻዎቻቸው ውስጥ ገንዘቡን እንዴት እንዳገኙት ለቤቱ አዛዥ ሲናገሩ፣ ነገሩ ለምን እንዳሳሰባቸውና በርግጥም ፍርሀታቸው የተሳሳተ እንደ ሆነ እናስተውላለን። ታሪኩን በድጋሚ የተናገሩት የቤቱን አዛዥ ትኩረት ለማግኘት ነው። የዮሴፍ ቤት አዛዥ ገለጻቸውን ከቁብ አልቈጠረውም። የቤቱ አዛዥ ንግግር ከቁም ነገር ሊወሰድ እንደማይችል ተደራስያኑ በርግጥ ያውቃሉ። ምክንያቱም ለቤቱ አዛዥ ገንዘብ መሰጠቱን የሚገልጽ ምንም ነገር የለም። ምናልባት ግን የቤቱ አዛዥ ዮሴፍ ምስጢራዊ ዕቅዱን ሲነድፍ ዐብሮት ሳይኖር አይቀርም። ነገር ግን የቤቱ አዛዥ ሳያውቀው የመጽሐፉን ማእከላዊ ጭብጥ ተናገረ፦ “ያገኛችሁትን ገንዘብ የሰጣችሁ የእናንተም የአባቶቻችሁም አምላክ ነው”።

26-34 ዮሴፍ ስለ ወንድማማቾቹ አባትና ከእነርሱም ጋር ዐብሯቸው ስለ መጣው ስለ ብንያም ደኅንነት ያነጋገራቸው ጥንቃቄ በተሞላበት መንገድ ነው። ዮሴፍ ዕንባው እንዳይታይበት ፈጥኖ ወደ ሌላ ክፍል ሲገባ ስናይ፣ ማንነቱ አሁንም ድረስ በግልጽ እንዳልታወቀ ርግጠኞች ነን። ወንድማማቾቹ ራሳቸው ስለ ዮሴፍ ጥያቄና በቤቱም ስለ ተደረገላቸው መልካም አቀባበል ምን ያስቡ እንደ ነበር ለመገመት አይቻልም። የመጡት ባሮች ለመሆን ነው፤ ነገር ግን የተገለገሉት እነርሱ ነበሩ። ምንባቡ “በመገረም እርስ በርሳቸው ተያዩ ” ይላል። ምንም ዐይነት ጥያቄ አላቀረቡም፤ የዮሴፍን ቤት አዛዥ ቃል (ቍ. 23) እንዲሁም ዮሴፍ ስለ ብንያም የተናገረውን ቃል (ቍ. 29) ተቀብለው በነገሩ የተስማሙ ይመስላል።

2. የብሩ ዋንጫ (44፥1-34)

1-13 ዮሴፍ የብር ዋንጫውንና የብንያምን ገንዘብ በብንያም ስልቻ ውስጥ እንዲጨመር በማድረግ ወንድሞቹን እንደ ገና አሞኛ ቸው። ዮሴፍ ለሰዎቹ ከሰጠው መመሪያ እንደምንረዳው ዐላማው ግልጽ ነው። አገልጋዮቹ የዮሴፍን መልእክት ሲያደርሱላቸው ወንድማማቾቹ ከሆኑት ነገር ተነሥተን የምንፈርድ ከሆነ፣ አገልጋዮቹ የተናገሩት ቃል በታሪኩ ላይ ከቀረበው ዘገባ ይበልጥ ዝርዝር ነው። ወንድማማቾቹ ወዲያውኑ በስልቻዎቻቸው ውስጥ አለ ስለ ተባለው ብርና ወርቅ መናገር ጀመሩ። ምናልባት የዮሴፍ መልእክት የተነገረው በጥቅሉ ሳይሆን አይቀርም፤ ምክንያቱም ቃላቸው የዮሴፍን ታሪክ ዐቢይ ጭብጥ ያስተጋባል፤ ይህም ወንድሞቹ በእርሱ ላይ ባሰቡት “ክፉ” ነገርና፤ እግዚአብሔር ግን “ለመልካም” ባሰበው መካከል ያለው ተቃራኒ ሐሳብ ነው (ከ50፥20 ጋር ያነጻ)።

የዮሴፍ ጥያቄ ወንድሞቹ በምዕ. 37 ላይ የፈጸሙበትን በደል ያካትታል፤ ይህም በዮሴፍ ላይ የፈጸሙትን በደል እንደ ገና ያስታውሰናል። የበደለኛነት ስሜቱ አሁንም ከጎሊናቸው አልጠፋም። በሄዱበት ስፍራ ሁሉ በዮሴፍ ላይ የፈጸሙት በደል ከፊታቸው ይደቀንባቸዋል።

የዮሴፍ ዕቅድ ልክ እያንዳንዱ ነገር አስቀድሞ በጥንቃቄ እንደ ተነደፈው መጠን ሠራለት። ወንድማማቾቹ ጽዋውና ገንዘቡ በብንያም ስልቻ ውስጥ እንዳለ ሳያውቁ ፈጥነው መሐላቸውን ደረደሩ፤ በዚህም የብንያምን ሕይወትና የራሳቸውን ነጻነት አደጋ ላይ ጣሉ። ጽዋው ሲገኝ መልሳቸው ፍጹም ተስፋ ቢስነት ይታይበት ነበር፦ “ልብሳቸውን በሐዘን ቀደዱ”፤ ወደ ከተማዪቱም ተመለሱ። ሊያደርጉት የሚችሉት አንዳች ነገር አልነበረም። ምላሻቸው ከዚህ በፊት አባታቸው የዮሴፍን መጥፋት ሲሰማ ከሆነው ነገር ጋር ይመሳሰላል (37፥34)። በአባታቸው ላይ ያመጡት ሐዘን በእነርሱም ደረሰ።

14-17 ላይ ላዩን ስናየው ዮሴፍ ወንድሞቹን እየተበቀለ ቢመስልም፣ ዐላማው ግን በቀል ሳይሆን ንስሓ ነው። በዕቅዱ አማካይነት ወንድሞቹ በእርሱ ላይ የፈጸሙትን በደል እንዲያስተውሉና ጥፋታቸውንም እንዲቀበሉ አደረጋቸው። ፍጹም ተስፋ መቍረጣቸውን ከጥያቄያቸው መረዳት ይቻላል። ለጥያቄያቸው የሰጡት መልስ፣ ለማለት የሚችሉትም ሆነ ሐቀኛ መሆናቸውን ለማስረዳት የሚችሉበት ምንም ነገር አለመኖሩን ነው። ስለዚህ ለማለት የሚችሉት ነገር ቢኖር “እግዚአብሔር የእኛ ን የአገልጋዮችህን በደል ገልጧል” ነበር።

ምንም እንኳ በወንድማማቾቹ ኅሊና ውስጥ የሚብላላው “የጽዋው” መጥፋት ጉዳይ ብቻ ቢሆንም፣ ነገሩን ከመላው የዮሴፍ ታሪክ አንጻር ካየነው፣ የተናገሩት ቃል ለቀደመው በደላቸው ኑዛዜ ነው። ጽዋውን ወንድማማቾቹ እንዳልወሰዱት እናውቃለን፤ በብንያም ስልቻ ውስጥ እንዲከተት ያደረገው ዮሴፍ ነው። ጽዋውን ወንድማማቾቹ እንዳልወሰዱት እነርሱም እንደሚያውቁ እናውቃለን። ስለዚህ እግዚአብሔር “በደላቸውን እንደ ገለጠው” ሲናገሩ፣ ከመላው ታሪክ አንጻር የበደለኝነት ስሜታቸውን ልናጠቃልለው እንገደዳለን። የዮሴፍ ንግግር የታሪኩ አቅጣጫ ወንድሞቹ በእርሱ ላይ ከፈጸሙት በደል ጋር እንዲመሳሰል አድርጓል። ታናሹ ልጅ በግብፅ ባሪያ ሆኖ መሸጥ ነበረበት፤ ወንድማማቾቹም ወደ አባታቸው መመለስ ነበረባቸው።

18-34 ይሁዳ በመጨረሻው ንግግሩ የዮሴፍን መላ ታሪክ እንደ ገና ተናገረ። ታሪኩን እንደ ገና መናገሩ ወንድማማቾቹ ስለ ድርጊቱ ያላቸውን ግንዛቤና ሁኔታቸውም ያለቀና ያበቃለት መሆኑን ያሳያል። የይሁዳን ንግግር በጥቅሉ ስናየው፣ የተበደሉት ወንድማማቾቹ ናቸው። እንዲያውም ለዚህ ሁሉ ተጠያቂው ዮሴፍ ነው። እንደ ይሁዳ አባባል ከሆነ ለዚህ ሁሉ ሥቃይ የዳረጋቸው የዮሴፍ ምክር ነው። እነርሱ ያደረጉት ነገር ቢኖር፣ የእርሱን መመሪያና የአባታቸውን መመሪያ መከተል ብቻ ነበር። ይሁን እንጂ የይሁዳ ንግግር እርሱ ለማለት ከፈለገው በላይ ለተደራስያኑ የሚገልጠው ነገር አለ፤ ጥፋቱ የዮሴፍ ሳይሆን ወንድማማቾቹ በዮሴፍ ላይ ያላቸው “ክፉ” ሐሳብ እንደ ሆነ ያሳያል። ንግግሩ ወንድማማቾቹ በዮሴፍ ላይ የፈጸሙትን በደል እንደ ገና ያስታውሰናል።

ይሁዳ በዚህ ስፍራ ዮሴፍ “ሞቶአል” ቢልም፣ በሌላ ስፍራ ግን ስለ ዮሴፍ የተነገረው “[እርሱ] ግን የለም” ተብሎ ነው (42፥13)። “እርሱ ግን የለም” ማለት ሞቷል ማለት አይደለም (ከ5፥24፤ 42፥36 ጋር ያነጻ)። በመሆኑም ይሁዳ ታሪኩን እንደ ገና ሲናገር ከዚህ በፊት ያልነበረ ዐዲስ ነገር ጨምሯል። አሁን ታሪኩ ወንድማማቾች በመጀመሪያ ከነበራቸው ውጥን ጋር ይመሳሰላል (37፥18)፤ ደግሞም ወንድማማቾቹ ለያዕቆብ ከተናገሩት ታሪክ ጋር ይጐዳኛል። በገሃዱ ዓለም “የምላስ ድጠት” የሚመስለው ነገር የወንድማማቾቹን ልቡናና በደል የሚያሳይ ፍንጭ ሊሆን ይችላል።

ሆኖም የይሁዳ ንግግር በዮሴፍ ላይ የተፈጸመውን በደልና ያዕቆብ ብንያምን ወደ ግብፅ እንዲወስዱት በተጠየቀ ጊዜ የሰጠውን መልስ ይበልጥ ያጐላዋል። በወቅቱ ያዕቆብ እንዲህ አለ፤ “ሚስቴ ሁለት ወንዶች ልጆች እንደ ወለደችልኝ ታውቃላችሁ፤ አንዱ በወጣበት በመቅረቱ በርግጥ የአውሬ እራት ሆኗል አልሁ።” ይሁዳ ታሪኩን በዚህ ዐይነት እንዴት እንደ ገና ሊናገር ቻለ? ያዕቆብ የተናገራቸው ቃሎች የተሳሳቱ መሆናቸውን በርግጥ ተረድቷል። ዮሴፍን የገደለው አውሬ አይደለም፤ ለባርነት የሸጡት ራሳቸው ወንድማማቾቹ ናቸው። ይሁንና ታሪኩን ልክ በተፈጸመበት መንገድ መናገር ማለት ጥፋተኞነትን መቀበል ማለት ነው፤ ይህም በዚህ ስፍራ ከቀረበባቸው ክስ ይልቃል። ይሁዳ የራሱን ንጽሕና ለማሳየት ሲል እንደ ገና የተናገረው ታሪክ የራሱንና የወንድሞቹን በደለኛነት ይመሰክራል። ምንም እንኳ ተደራስያኑ የወንድማማቾቹን በደል እንደ ገና የሰሙት በይሁዳ ንግግር አማካይነት ቢሆንም፣ በብንያም እግር የተተካውም ሆነ ውድቀታቸውን የታደገው ይሁዳ ነው።

ከዚህ ንግግር በኋላ ዮሴፍ ራሱን መቈጣጠር አልቻለም። ማንነቱን ለወንድሞቹ ሊነግራቸው ግድ ሆነበት።

3. ዮሴፍ ራሱን ገለጠ (45፥1-28)

1-8 ዮሴፍ ወንድሞቹን በማታለል የሚያገኘው አንዳች ደስታ የለም። መቈጣጠር ሲያቅተው እውነተኛ ማንነቱን ገለጠ። ዮሴፍ የሆነውን ነገር ሁሉ ሲያስረዳቸውና ወንድሞቹንም ሲያጽናናቸው፣ ወደ ታሪኩ ዐቢይ ጭብጥ እንደ ገና ተመለሰ። ለዮሴፍ መሸጥ ተጠያቂዎቹ እነርሱ ቢሆኑም፣ ይህን ሁሉ “ለክፉ” ቢያደርጉትም፣ ከዚህ ሁሉ በስተ ጀርባ ግን እግዚአብሔር ነበረ፤ “ለመልካምም” ይጠቀምበት ነበር። ለወንደሞቹም ሲናገር እንዲህ አላቸው፦ “እግዚአብሔር ሕይወት ለማዳን ሲል ከእናንተ አስቀድሞ እኔን ወደዚህ ልኮኛል። . . . ሕይወታችሁን በታላቅ ማዳን ለመታደግና ዘራችሁ ከምድር ላይ እንዳይጠፋ በማሰብ ከእናንተ አስቀድሞ ወደዚህ ላከኝ”። እስከ አሁን ድረስ በታሪኩ ውስጥ ይህ ጭብጥ የተነገረው በያዕቆብና (42፥2) በይሁዳ (43፥8) ቢሆንም በራሱ በዮሴፍ ደግሞ በእጅ አዙር ተነግሯል (42፥18)። እዚህ ላይ እና በ50፥20 ላይ ግን ጭብጡ በራሱ በዮሴፍ ቃል ይበልጥ ተስፋፍቶ ተተርኳል።

ከዚህም በተጨማሪ ዮሴፍን ወደ ግብፅ የላኩት ወንድሞቹ ሳይሆኑ እግዚአብሔር ነው። እግዚአብሔር ደግሞ ለዚህ ሁሉ ምክንያት አለው። ቀደም ባሉት ታሪኮች ላይ ለሚራመዱና ለንኡስ ሚራመዶቹ መጠንሰስ ምክንያት የሆነው ዮሴፍ ከዚህ ሁሉ በስተ ጀርባ ያለውን የእግዚአብሔርን ዕቅድና ሐሳብ ገለጠ። በዚህ ሁሉ ውስጥ እግዚአብሔር ታላቅ ማዳኑን እየፈጸመ መሆኑን ተረዳ። ዮሴፍ እግዚአብሔር እንዴት እንደ ተንከባከበው ሲገልጽላቸው

ወጣት በነበረበት ጊዜ ወንድሞቹ ሕልሙን በተመለከተ የነበራቸውን ጥያቄ ጠቀሰ (37፥8)። “በግብፅ ምድር ላይ ገሸር” እንደ ተደረገ አስታወሳቸው።

9-20 ዮሴፍ በንግግሩ ሁለተኛ ክፍል አባቱን ወደ ግብፅ እንዲያመጡት ሐሳብ አቀረበ፡ ወንድማማቾቹ ወደ ያዕቆብ ሄደው በፍጥነት ወደ ግብፅ እንዲያመጡት ሁለት ጊዜ አሳሰባቸው። በረኃቡ ዘመን የእስራኤል ልጆች በጌሤም ምድር በክብካቤ መኖር አለባቸው። ፈርዖን የዮሴፍን ግብዣ እንደ ገና ሲጠቅስና ለወንድማማቾቹም መልካም (ኩ. 18:20፤ ዐመት “ለም”) ከሆነው ከግብፅ ምድር እንደሚሰጣቸው ሁለት ጊዜ ሲናገር፣ ለአዳም የተሰጠውን መልካም ምድር (1፥31) ለማየት አያዳግትም። ዮሴፍ የያዕቆብ መልካም ዕድል ብቻ ሳይሆን የተሐድሶም ምሳሌ ነው። ለያዕቆብ ዘሮች የተሰጠው ተስፋም በረከት ነው።

21-28 በመጀመሪያ ያዕቆብ የዮሴፍን በሕይወት መኖር ሲሰማ “በድንጋጤ ክው አለ”፤ ሊያምናቸውም አልቻለም። ዮሴፍ የተናገረውን ሁሉ ሲሰማና ወደ ግብፅ እንዲያመጡትም የላከውን ሁሉ ሲያይ፣ “የያዕቆብ መንፈስ ታደሰ”፤ ሄዶም ሊያየው ቁረጠ። በያዕቆብ እምነት ላይ የምናየው አንድ ዐዲስ ንጽጽር አለ፤ በመጀመሪያ “ልቡ ደነገጠ”፤ ከዚያም “መንፈሱ ታደሰ”። ያዕቆብ እምነተ ቢስ ሰው እንደ ሆነ የተነገረው “ልቡ ደነገጠ” በሚለው ቃል ቢሆም፣ መንፈሱ ሲታደስ ግን “አመነ”።

ቸ. *ያዕቆብ ወደ ግብፅ ሄደ (46፥1-7)*

1-4 ያዕቆብ ወደ ግብፅ ከመሄዱ በፊት ወደ ቤርሳቤህ ሄዶ በዚያ መሠዊያ ሠራ፤ ለአባቱም ለይስሐቅ አምላክ መሥዋዕት ሠዋ። የእስራኤል አባቶች ያመለኩት አንዱን አምላክ ነው። እግዚአብሔር ይስሐቅን “ወደ ግብፅ አትውረድ” ብሎት ነበር (26፥2)፤ አሁን ደግሞ ያዕቆብን “ወደ ግብፅ ለመውረድ አትፍራ” አለው። የእስራኤል አባቶች ወደ ግብፅ መውረዳቸውን በተመለከተ የምናየው የአቋም ለውጥ እግዚአብሔር ለሕዝቡ የተለየ ዕቅድ እንዳለው ያመለክታል።

በሌሊቱ ራእይ ለያዕቆብ የመጣለት ቃል ለአብርሃም የተሰጠውን ተስፋ በድጋሚ ያወሣል (12፥2)፤ ሆኖም እግዚአብሔር ይህን ተስፋ የሚፈጽመው በግብፅ መሆኑን በተጨማሪ ይገልጻል። ሕዝቡን ወደ ግብፅ ይወስዳል፤ በዚያም ዐብሯቸው ይሆናል፤ ታላቅ ሕዝብ ከሆኑ በኋላ ወደ ተስፋዱቱ ምድር መልሶ ያመጣቸዋል፤ ይህም እግዚአብሔር መጪው ዕቅዱን ለአብርሃም ዘሮች የገለጠበት ሁለተኛው ራእይ ነው (ከ15፥1፡13-14 ጋር ያነጻ)።

5-7 ያዕቆብና ቤተ ሰቡ ወደ ግብፅ መውረዳቸውን በተመለከተ የተለየ አትኩሮት ተሰጥቷል። አብርሃም ከዑር ተነሥቶ ወደ ከነዓን እንደ ሄደ ሁሉ (12፥4-5)፣ ያዕቆብም ከከነዓን ተነሥቶ ወደ ግብፅ ሄደ። ሁለቱም ሰዎች እግዚአብሔርን በመታዘዝ የተወለዱበትን አገር ትተው ሄዱ፤ የሁለቱም ሰዎች መታዘዝ እግዚአብሔር የአብርሃምን ዘር ሲመርጥ ቁልፍ ሚና ተጫውቷል። በመሆኑም በቁ. 6-7 ላይ “ዘሮቹ በሙሉ” ከያዕቆብ ጋር ወደ ግብፅ እንደ ወረዱ የተገለጸው ለታሪኩ አጽንዖት ለመስጠት ነው። ጸሓፊው የዚህን ነጥብ አስፈላጊነት ለመግለጽ ሲል “የዘሮቹን በሙሉ” ስም በመዘርዘር ቁጥራቸው “ሰባ” እንደ ሆነ ይናገራል (ቀጥሎ ያለውን ማብ ይመ)።

ኀ. *የያዕቆብ ልጆች በግብፅ (46፥8-27)*

8-27 በእነዚህ ቁጥሮች ላይ የተዘረዘሩት ስሞች ምናልባት ቁጥሩ ሰባ (ቁ. 27) ሆኖ የተመረጡ ናቸው። በዘፍጥረት 10 ላይ የሕዝቦቹ ቁጥር “ሰባ” መሆኑ የአጋጣሚ ጉዳይ ተደርጎ ሊወሰድ አይችልም። “ሰባዎቹ ሕዝቦች” የአዳምን ዘሮች በሙሉ እንደሚወክሉ ሁሉ፣ እነዚህም “ሰባ ልጆች” የሚወክሉት የአብርሃም፣ የይስሐቅና የያዕቆብ ማለትም የእስራኤል ልጆችን በሙሉ ነው። በዘዳግም 32፥8 ላይ የተነገረው ጭብጥ ተገልጾ እናያለን፤ ይኸውም እግዚአብሔር የሕዝቦችን ርስት ድንበር የለየው (ዘፍ 10) በእስራኤል ልጆች ቍጥር ልክ ነው። እንግዲህ ዐዲሱ የእስራኤል ሕዝብ የተገለጸው እንደ ዐዲሱ ሰው ሲሆን፣ አብርሃም ደግሞ እንደ ሁለተኛው አዳም ነው። በአብርሃምና በዘሩ አማካይነት የሚመጣው በረከት ለአዳም የተሰጠው በረከት መታደሱን ያረጋግጣል፤ ለአዳም የተሰጠው በረከት በአዳም መውደቅ ጠፍቶ ነበር።

ነ. *በጌሤም ምድር መሰፈር (46፥28-47፥12)*

28-34 ከሁሉ የሚገርመው የእስራኤልን ልጆች እየመራ ወደ ጌሤም የወሰዳቸው ዮሴፍ ሳይሆን ይሁዳ ነው። እዚህም ላይ ከዮሴፍ ይልቅ ለይሁዳ የላቀ አትኩሮት ተሰጥቶ እናገኛለን። ምንም እንኳ በዮሴፍ ታሪክ ውስጥ የእስራኤል ልጆች በግብፅ እንዲጠበቁ የላቀውን ሚና የተጫወተው ዮሴፍ ቢሆንም፣ እዚህ ላይ ወደ ጌሤም ምድር እንዲሄድ መመሪያ የሰጠው ይሁዳ ነው። ለይሁዳ እንዲህ ያለ የተለየ አትኩሮት ተሰጥቶ ስናይ በእግዚአብሔር ዕቅድ ውስጥ ለእስራኤል መዳን የሚጫወተውን ወሳኝ ሚና አበክሮ ያሰገነዝበናል። የይሁዳን የላቀ ደረጃ በግልጽ የምናየው ያዕቆብ ለዐሥራ ሁለቱ ልጆች በተናገረው በረከት ነው (49፥8-12)።

ምዕራፉ የሚጨርሰው ዮሴፍ የጌሤም ምድር ለእስራኤል ልጆች መኖሪያ እንድትሆን ሲያቅድ ነው። ዕቅዱ እረኞች መሆናቸውን ለፈርዖን መናገር ነበር። ግብፃውያን እረኞችን ይጠሉ ስለ ነበር፣ እስራኤላውያን በጌሤም ምድር እንዲኖሩ ሊፈቅዱላቸው ይችላሉ። የዮሴፍ ዕቅድ ሠመረ፤ የጌሤምም ምድር ለቤተ ሰቦቹ ተሰጠ። በእነዚህ ሁለት ዐጫጭር ታሪኮች ላይ እንደምናየው ይሁዳና ዮሴፍ በጉልሕ ተነጻጽረዋል። ይሁዳ ወንድሞቹን ወደ ጌሤም ምድር እየመራ ወሰደ፤ በዚያ እንዲኖሩ ያስቻላቸው ግን የዮሴፍ ብልኅ ዕቅድ ነበር።

47፥1-12 የዮሴፍ ጥበብ የእስራኤል ልጆች በጌሤም ምድር በደኅና እንዲኖሩ አስቻላቸው፤ በከነዓን ምድር ግን ጽኑ ረኃብ ነበረ። ከፈርዖን ያገኙት መልስ ቀደም ባለው ታሪክ ላይ ከተነገረው ይልቅ ብዙ ቸርነት ይታይበታል። ፈቃዳቸውን መፈጸምና የዮሴፍ ወንድሞች በጌሤም ምድር እንዲኖሩ መፍቀድ ብቻ ሳይሆን፣ ውንድማማቾች የከብቶቹ ኀላፊዎች እንዲሆኑም ሾማቸው፤ ይህም ዮሴፍ በፈርዖን ቤት ላይ ኀላፊ ሆኖ መሾሙን ያስታውሰናል (ከ41፥41 ጋር ያነጻ)። እንግዲህ የዮሴፍ ዕድል በወንድሞቹ ዕድል ተባዛ። የጌሤም ምድር ምርጥ ምድር ነው፤ ይህም እግዚአብሔር “ለመልካም ዐሰበው” ከሚለው ጋር ሳይጉዳኝ አይቀርም (50፥20)።

የዚህ ታሪክ ዐቢይ ትኩረት ያዕቆብ በፈርዖን ፊት በቀረበ ጊዜ ፈርዖንን እንደ “ባረከው” (ቁ. 7፡10) ለማሳየት ነው። ከዚህ አጽንዖት በስተ ጀርባ እግዚአብሔር ለአብርሃም የሰጠው ተስፋ አለ፤ እግዚአብሔር የአብርሃምን ዘር የሚባርኩትን ይባርካቸዋል። ምንባቡ ለአብርሃም የተሰጠው ተስፋ በዮሴፍና በያዕቆብ፣ በዙሪያቸውም በሚገኙ ሕዝቦች መካከል እየተፈጸመ መሆኑን ያሳያል።

በቍጥር 9 ላይ ያዕቆብ ለፈርዓን የሰጠው መልስ ፈርዖንን ሁለት ጊዜ እንደ ባረከው ከሚያወሣው ዘገባ ጋር ስናነጻጽረው እንግዳ ይሆንብናል። ምናልባት ግን በዘዳግም ውስጥ አባቱንና እናቱን የሚያከብር ሰው በምድር ላይ ዕድሜው እንደሚረዝምና መልካምም እንደሚሆንለት ከተነገረው ተስፋ ጋር ለማነጻጸር ተፈልጎ ሳይሆን አይቀርም (ዘዳ 5፥16)። አባቱን አታሎ በረከቱን ያገኘው ያዕቆብ መሞት ያለበት ከተስፋዱቱ ምድር ውጭ ብቻ ሳይሆን፣ እኛም ዘመኖቹ ዐጭርና ችግር የበዛባቸው እንደ ሆኑ እናስተውላለን፤ ይህ ምናልባት ከዚህ በፊት ለፈጸመው ድርጊት ቅጣት ሊሆን ይችላል። አብርሃም እግዚአብሔርን በመታዘዙ በምድሪቱ ረጅም ዘመን ኖረ (ዘፍ 26፥5)፤ የያዕቆብ ዘመኖች ግን ዐጭርና ችግር የበዛባቸው ነበሩ። በተስፋዱቱ ምድር ባይሆንም፣ ያዕቆብ የቀረውን ዘመኑን የኖረው “ምርጥ በሆነው ምድር” ነው። ልጁ ዮሴፍም ለእርሱና ለቤተ ሰቦቹ መኖሪያ አዘጋጀላቸው።

ኘ. *በግብፅ የዮሴፍ ኣመራር (47፥13-27)*

13-27 ይህ ታሪክ የሚመለሰው በ41፥57 ላይ ወደ ተነገረው ታሪክ ሲሆን ዮሴፍ በግብፅ ስለ ነበረው አመራርና በፈርዖንም ስም ስላከናወነው ሥራ ይዘግባል። ወንድማማቾቹ አትኩሮት ሲሰጣቸው አናይም፤ አሁን አትኩሮቱ በዮሴፍና በልጆቹ ላይ ነው።

የዮሴፍና የወንድሞቹ ታሪክ (ምዕ. 42-46) ዮሴፍ በግብፅ ሥልጣን ስለ መጨበጡ በሚያወሣው ታሪክ መካከል የገባው (ምዕ. 39-41፤47) ይህ የመጨረሻው ታሪክ ከዮሴፍና ከወንድሞቹ ታሪክ ጋር ስለሚመሳሰል ነው። በእነዚያ ታሪኮች ውስጥ የዮሴፍን ጥበብና የአመራር ክህሎት የሚያወሣው ጭብጥ ተደጋግሞ ተጠቅሷል። በመሆኑም በታሪኩ መጀመሪያ ላይ ያዕቆብ ልጆቹ ወደ ግብፅ እንዲወርዱና እህል እንዲሸምቱ ሲያደርግ እናያለን፤ ይህንንም ያደረገው “እንዲድኑና እንዳይሞቱ” ነው (42፥2)። ከዚያም ይሁዳ በሁለተኛው ዓመት (45፥6) እንዲድኑና እንዳይሞቱ (43፥8)፣ ወደ ግብፅ እንዲመለሱ ለአባቱ ተናገረ። በመጨረሻም፣

ዮሴፍ ራሱን ለወንድሞቹ ሲገልጥላቸው እግዚአብሔር ሕይወት ለማዳን ሲል ወደ ግብፅ እንደ ላከው ተናገረ (45፥5)።

ይህ የአሁኑ ታሪክ የሚጀምረው ግብፁውያን እህል ለመሸመት ወደ ዮሴፍ ሲመጡ በተናገሩት ቃል ነው፦ “ዐይንህ እያየ እንዴት በራብ እንለቅ? ” ከዚያም “በሁለተኛው ዓመት ” (አመት፣ “ያም ዓመት ካለፈ በኋላ”) ወደ ዮሴፍ መጥተው “ታዲያ እያየኸን እንዴት እንለቅ?” ደግሞም “እንድንድን እንዳንሞትም” በማለት ታሪኩ ሲቀጥል እናያለን። እንዲህ ዐይነቱ ድግግሞሽ ጭብጣዊ ስልት መኖሩን ያመልክታል። የዮሴፍ ጥበብ በምድሪቱ ለሚኖሩ ሁሉ የሕይወት ምንጭ ሲሆን ይታያል፤ በመጀመሪያ ወንድሞቹን አዳነ፤ ቀጥሎም ግብፁውያንን አዳነ። ከዚህም በተጨማሪ ለአብርሃም ዘሮች በተሰጠው ጥበብ አማካይነት ሕዝቦች በረከትን ይቀበላሉ (ከ12፥2-3 ጋር ያነጻ)።

በምዕራፍ 47 ላይ ከምናገኘው ታሪክ በስተ ጀርባ የተለየ ስልት መኖሩን የምናውቀው በቀደሙት ምዕራፎች ላይ የተወሣው ታሪክ በዚህ ምዕራፍ ውጤት ምፀታዊ በሆነ መንገድ በመጠምዘዙ ነው። የዮሴፍና የወንድሞቹ ታሪክ የሚጀምረው ዮሴፍ ለባርነት (39፥17) በሃያ ጥሬ ብር (37፥28) ሲሸጥ ነው (37፥28)። አሁን ደግሞ በታሪክ መዝጊያ ላይ ዮሴፍ መላውን የግብፅ ምድር ለባርነት ሲሸጥና ገንዘባቸውንም ሲወስድ ይታያል (ቁ. 18)። በመጨረሻ ከዮሴፍ ጥበብ የተነሣ የአብርሃም ዘሮች “ሀብት ንብረት” አፈሩ “ቍጥራቸው እጅግ በዛ፤”፤ በጌሤምም ምድር በሰላም ኖሩ። ይህ የሚያሳየን ቀደም ባሉት የዘፍጥረት ምዕራፎች ላይ የተነገረው በረከት አንድ በአንድ መፈጸሙን ነው። (1፥28)።

ሐ. ያዕቆብ በሞት ዐልጋ (47፥28-49፥33)

1. የያዕቆብ ሥርዐተ ቀብር መመሪያ (47፥28-31)

28 ከዚህ ቍጥር በመነሣት የያዕቆብ ታሪክ ሊፈጸም የተቃረበ ሊመስለን ይችላል፤ ይሁንና ነገሩ እንዲህ አይደለም። ገና ሁለት ወሳኝ ምዕራፎች ይቀራሉ። በቍጥር 28 ላይ የተቋረጠው የያዕቆብ ታሪክ ሲቀጥል እናያለን፤ ታሪኩ ዮሴፍ በግብፅ በቀጣይነት ሥልጣን ስለ መጨበጡ በሚያወሣው ዘገባ ተቋርጦ ነበር (ቁ. 13-27)፤ ከዚህም በተጨማሪ ለታሪኩ ዐዲስ የጊዜ ስፋት በመስጠት ዐሥራ ሰባት ዓመት ወደ ፊት እንዲራመድ አድርጓል። ምናልባት እዚህ ላይ አጽንዖት ለመስጠት የተፈለገው አሁን ረኃቡ ጋብ ማለቱንና ዮሴፍም በግብፅ የጨበጠው ሥልጣን መደላደሉን ነው።

29-31 ያዕቆብ የሚሞትበት ጊዜ ሲደርስ፣ ብቸኛ ጥያቄው በግብፅ ምድር እንዳይቀበር ነበረ። አጠያየቁ ከአብርሃም ጋር ይመሳሰላል (24፥2)። አብርሃም የሚሞትበት ጊዜ ሲደርስ፣ ልጁ እርሱ በዚያን ወቅት ይኖርበት ከነበረ ምድር ሕዝቦች መካከል ሚስት እንዳይወስድ ፈልጎ ነበር (24፥3-4)። ልክ እንዲሁ ያዕቆብም የሚሞትበት ጊዜ ሲደርስ (ቁ. 29)፣ ከአባቶቹ ጋር በራሱ ምድር እንጂ በግብፁውያን መካከል ለመቀበር አልፈለገም። ዮሴፍ ልጆቹ ዐጥንቱን ወደ ተስፋዱቱ ምድር እንዲወስዱ ቃል ሲያስገባቸው፣ ይኸው ጭብጥ በምዕ. 50 ላይ እንደ ገና ተወሥቷል፤ ጥያቄው በኢያ 24፥32 ላይ ተጠቅሷል።

ከአብርሃም ጋር የተደረገው ኪዳን ማእከል ያደረገው የተስፋዱቱን ምድር ነው። የእስራኤል አባቶች ከአባቶቻቸው ጋር በምድሪቱ እንዲቀበሩ ሲጠይቁ፣ በቃሉ በታመነው አምላክ ላይ ያላቸውን እምነት በአጽንዖት ይገልጻል። ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር በሰጠው ተስፋ ላይ የእስራኤል እምነት አንዱ ቍልፍ ምልክት በተስፋዱቱ ምድር የተቀበረው የታመኑቱ ዘሮች ዐጥንት ነው። ሌላው የመጽሐፍ ቅዱስ ምዕራፍ ማለትም ሕዝ 37 ስለ “ደረቁ ዐጥንቶች” ትንቢት ሲናገር ለዚህ ምልክት የተለየ አትኩሮት ሰጥቷል።

በይሁዳ እናት በልያና በዮሴፍ እናት በራሔል መካከል ከነበረው የከረመ ባላንጣነት ጀምሮ (ምዕ.30) ከወንድሞቹ መካከል አንዱ በሌሎቹ ላይ ይሽቀዳደማል የሚለው ጥያቄ ቍልፍ ሚና አለው። በምዕራፍ 48 (የዮሴፍ መባረክ) እና 49 (የይሁዳ መባረክ) ውዝግቡ መፍትሒ አግኝቷል፤ ይኸውም ከይሁዳ ነገድ የሚወጣው በሌሎቹ ወንድሞች ላይ ይነግሣል (49፥8-10)። ልክ እንዲሁ በሕዝ 37 ላይ ነቢዩ ወደ ዮሴፍ ታሪክና በወንድማማቾቹ መካከል ወደ ተፈጠረው ባላንጣነት ይመለሳል። እዚህ ላይ እንደ ተገለጸው ሁሉ በዚያም ክፍል ወንድማማቾቹ ከይሁዳ ነገድ በሚወጣው ንጉሥ ማለትም በዳዊት አንድ እንደሚሆኑ ተገልጿል (ሕዝ 37፥15-17፡22-24)።

2. ኤፍሬምና ምናሴ ተባረኩ (48፥1-22)

“ከጥቂት ጊዜ በኋላም” የሚለው ሐረግ ቀደም ሲል ከተወሡት ድርጊቶች የተለየ ነገር መኖሩን ያሳያል። ምዕራፍ 48 የዮሴፍን ታሪክ በግራም ሁኔታ ደምድሟል። በቀደሙት የእስራኤል አባቶች ታሪክ እንደ ሆነው ሁሉ የአባት በረከት ወደ ቀጣዩ ትውልድ ተላልፏል። ሁለት ነገሮች ጐልተው ይታያሉ፤ አንደኛ ው፣ እንደ ቀደመው ሁሉ በኩር ልጅ ተደርጎ የተባረከው ታላቁ ልጅ ምናሴ ሳይሆን ታናሹ ኤፍሬም ነው (ቁ. 19)፤ ይህም በረከቱ የሚሰጠው ለባለ መብቱ እንዳልሆነ የሚገልጸውን ጭብጥ የተከተለ ነው። በረከቱ የሚሰጠው እንደ ባለ መብት ለማይጠይቁ ሰዎች ነው። ሁለተኛው፣ እዚህ ላይ የተዘገበው በረከት በምዕ. 49 ላይ በተነገረው በረከት ተተክቷል።

የኋላ ኋላ ከወንድሞቹ መካከል ልቆ የምናገኘው ዮሴፍን ሳይሆን ይሁዳን ነው። ሚናውም ከይሁዳ ያነሰ ነው። ከዚህም በተጨማሪ በቀጣዩ የተስፋና የበረከት ታሪክ ውስጥ ጐልሕ ሚና ሲጫወት የምናየው የዮሴፍ ልጆች በረከት ሳይሆን የይሁዳ በረከት ነው። የዳዊት ቤት የወጣው ከይሁዳ ነው፤ ከዳዊት ቤት ደግሞ መሲሑ መጣ። ኤፍሬምና ምናሴ ስለ ተከፋፈለው የሰሜኑን መንግሥት በሚያወሡት ምንባቦች ውስጥ ቍልፍ ሚና ቢኖራቸውም፣ ወደ ምርኮ በመሄድ ተበታትኖ የጠፋው ይህ መንግሥት ስሙ እየገነነ በመጣው ዳዊት ፊት ከሰመ።

1-4 የያዕቆብ ማርጀት የሕይወቱ ፍጻሜ እንደ ደረሰ ያሳያል። ይሁንና ያዕቆብ ዮሴፍንና ሁለቱን ልጆቹን ሲያያቸው ተበረታታ፤ የእግዚአብሔርንም በረከት ለዮሴፍ ቤት ለመስጠት ተነሣ። ያዕቆብ እግዚአብሔር በቤቴል የሰጠውን ተስፋ ማስታወሱ ትልቅ ስፍራ የሚሰጠው ነው (35፥9-13)። እግዚአብሔር የሰጠውን ተስፋ ቃል በቃል ደገመው። ሆኖም የተሰጠውን ተስፋ በመጠኑ ሲለውጠው፣ ያዕቆብ ስለ ተስፋው ያለውን መረዳት ብቻ ሳይሆን የጸሐፊውንም እይታ ማየት ይቻላል። በ35፥9 ላይ እንደ ተናገረው ሁሉ፣ አሁንም እግዚአብሔር እንደ ባረከው ገለጸ። ያዕቆብ እግዚአብሔር የሰጠውን ተስፋ ሲያስታውሰን፣ የእግዚአብሔርን ተስፋ በረከት በተመለከተ ያለንን ግንዛቤ እንድናጠራ ረድቶናል።

በ35፥11 ላይ እግዚአብሔር “ብዛ ተባዛ፣ ሕዝብና የሕዝቦች ማኅበር ከአንተ ይወጣሉ፤ ነገሥታትም ከአብራክህ ይከፈላሉ” ብሎት ነበር። እግዚአብሔር እንዲህ ሲለው በዘፍ 1፥28 ላይ እንደምናነበው “ብዙ ተባዙ” ማለቱ ነበር። ሆኖም ያዕቆብ ታሪኩን ለዮሴፍ እንደ ገና ሲነግረው፣ የተሰጠውን ተስፋ ሁሉ ወደ ፍጻሜ የሚያመጣው እግዚአብሔር እንደ ሆነ በአጽንዖት ገልጿል፦ “ፍሬያማ አደርግሃለሁ፤ ይህችንም ምድር ከአንተ በኋላ ለሚነሡ ዘሮችህ የዘላለም ርስት አድርጌ እሰጣቸዋለሁ።” ያዕቆብ በረከቱን ወደ ኋላ ተመልሶ ሲቈጥርና ይህንንም ለልጆቹ ሲያስታውቃቸው፣ በዮሴፍ ታሪክ ውስጥ ዐቢይ የሆነውን ጭብጥ ፈልቅቆ ያሳየናል፤ ይኸውም የሰጠውን ተስፋ ሁሉ ከፍጻሜ የሚያደርሰው ራሱ እግዚአብሔር መሆኑን የሚያመለክት ነው።

ያዕቆብ በተናገረው ታሪክ ውስጥ የምናየው ሌላ ነገር አለ፤ እግዚአብሔር ምድሪቱን በተመለከተ የሰጠውን ተስፋ ቃል በቃል ደገመው፦ “ይህችን ምድር ከአንተ በኋላ ለሚነሡ ዘሮችህ . . . እሰጣቸዋለሁ” (ከ35፥11 ጋር ያነጻ)። ሆኖም ያዕቆብ ታሪኩን ሲናገር የጨመረው ነገር አለ። “የዘላለም ርስት አድርጌ” የሚል ሐረግ ጨምሯል። ከዚህ በቀር የተስፋዱቱ ምድር የዘላለም ርስት እንደ ሆነች የተነገረው አንድ ጊዜ ብቻ ነው (17፥8፤ ከ13፥15 ጋር ያነጻ)።

5-7 ኤፍሬምና ምናሴ ከያዕቆብ ቤተ ሰብ ጋር ተቀላቅለው እንደ ልጆቹ ይቈጠራሉ። እንደ ሌሎቹ የያዕቆብ ልጆች ሁሉ እነርሱም ለአብርሃም የተሰጠውን ተስፋ ይወርሳሉ። ከዚህ በኋላ የኤፍሬምና የምናሴ ቤተ ሰቦች ከያዕቆብ ልጆች ጋር ዐብረው ሲቈጠሩ እናያለን፤ በኋላም ከእስራኤል ነገዶች መካከል ጐልተው የሚታዩት እነርሱ ናቸው። ከጊዜ በኋላ እነዚህ ሁለት ስሞች የሰሜኑ የእስራኤል መንግሥት የሚጠራባቸው ሲሆን ለደቡቡ የይሁዳ መንግሥት ተቀናቃኝ ሆነዋል።

ራሔልና የተቀበረችበት ስፍራ ሊጠቀስ የቻለው፣ ያዕቆብ ወደ ተስፋዱቱ ምድር ሊገባ ሲል (48፥7) ራሔል “ሁለት ወንዶች ልጆች እንደ ወለደችለት ሁሉ (44፥27፤ ዮሴፍንና ብንያምን)፣ ዮሴፍም ወደ ግብፅ ሊገባ ሲል ለያዕቆብ “ሁለት ወንዶች ልጆች” እንደ ሰጠው ለመግለጽ ነው። እንዲህ ዐይነት አኩላዊ አገላለጽ የሚያስገነዝበን ኤፍሬምና ምናሴ የዮሴፍና የብንያም ምትክ መሆናቸውን ነው፤ ይህም ከያዕቆብ ሕይወት በስተ ጀርባ የእግዚአብሔር መግቦት እንዳለ ያረጋግጥልናል።

ከዚህም በላይ ያዕቆብ የተናገረው ታሪክ በ35፥16-19 ላይ ስለ ራሔል መሞት ከተወሣው ጋር ቃል በቃል ተመሳሳይ ነው። ሁለቱም ምንባቦች “ኤፍራታ” የት እንደምትገኝና ቤተ ልሔም ተብላም እንደምትጠራ ገልጸዋል። የእስራኤል አባቶች በተስፋዱቱ ምድር እንዲቀበሩ አሳስበው እንደ ነበር ሁሉ፣ ያዕቆብም የራሔልን መቀበር የጠቀሰው፣ ምድሪቱ ለአብርሃም ዘሮች “የዘላለም ርስት” ተደርጋ ከመሰጠቷ ጋር ትስስር ስላለው ነው። ይህም እግዚአብሔር ለኪዳኑ ተስፋ የታመነ አምላክ መሆኑን ያስታውሰናል።

8-14 የኤፍሬምና የምናሴ በረከት ሰፊ ስፍራ ተሰጥቶት ተተርኳል፤ ያዕቆብ ልጆቹን በባረከበት ዘገባ ላይ (ምዕ. 49) እነዚህ ሁለት ልጆች አልተጠቀሱም። በሌላ አነጋገር ይህ ታሪክ የምዕ. 49ን ታሪክ ያጐላዋል። እነዚህ ሁለት ልጆች ሲባረኩ ታናሹ ኤፍሬም የበኩሩ ልጅ በረከት (ቁ. 20ለ) እንደ ተሰጠው በአጽንዖት ለመግለጽ ትልቅ ጥንቃቄ ተደርጓል።

በመጀመሪያ የተባረከው (ቁ. 15-16) ሁለቱ ልጆች ሳይሆኑ ዮሴፍ ነው (ከዚህ በኋላ ዮሴፍን ባረከ፤ ቁ. 15)። ይሁንና በረከቱ ሲነገር ስለ “ታናሾቹ ልጆች” (ቁ. 16) ተወሥኗል፤ የዮሴፍ በረከት ለእነርሱም ይሆናል። ያዕቆብ ስለ ሁለቱ ልጆች ከመናገሩ በፊት ዮሴፍ አቋረጠው፤ ይህንንም ያደረገው አባቱ ቀኝ እጁን በኤፍሬም ራስ ላይ ሳይሆን በምናሴ ራስ ላይ በማድረግ የብኩርናው መብት ለታላቁ ለምናሴ እንዲሰጥ ፈልጎ ነው። ያዕቆብ የዮሴፍን ሙከራ ወደ ጎን በመተው (ቁ. 19) ሁለቱንም አንድ በአንድ መባረኩን ቀጠለ (“ባረካቸው”፤ ቁ. 20)፤ በዚህም ከምናሴ ይልቅ ኤፍሬምን ከፍ ከፍ አደረገ።

15-16 የያዕቆብ ባርኮት ሙልፍ ጭብጣዊ ቃሎች የተከማቹበት ነው። ስለ እግዚአብሔር የተነገረው “አባቶቼ አብርሃምና ይስሐቅ በፊቱ የተመላለሱለት እግዚአብሔር” ተብሎ ነው። የአብርሃምና የይስሐቅ መጠቀስ ያዕቆብ በእግዚአብሔር ላይ ያለውን እምነት ከቅርብ አባቶች ጋር የሚያስተሳስር ብቻ ሳይሆን፣ በዘፍጥረት፣ ውስጥ የምናገኛቸውን ቀደምት አባቶች እምነት ከአብርሃም፣ ከይስሐቅና ከያዕቆብ ጋር እንድናገናኝም ይረዳናል። ቀደም ሲል በመጽሐፉ ውስጥ የጥንት አባቶች እምነት “አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር አደረገ” ተብሎ ሁለት ጊዜ ተገልጿል (5፥22፡ 24፤ 6፥9)። የጥንት አባቶች እምነት ከእስራኤል አባቶች እምነት ጋር አንድ ነው፤ አካሄዳቸውን ከእግዚአብሔር ጋር አድርገዋል።

ከዚህም በተጨማሪ እግዚአብሔር “በዘመኔ ሁሉ እረኛ የሆነኝ አምላክ” እንዲሁም “ከጉዳትም ሁሉ የታደገኝ መልአክ” ተብሎ ተገልጿል። እዚህ ላይ እግዚአብሔር እንደ መልአክ መገለጹ እጅግ አስገራሚ ነው። ምክንያቱም ቀደም ሲል በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተነገረው እግዚአብሔር መልአኩን (24፥7) እንደሚልክ ወይም ከእስራኤል አባቶች አንዱ “በእግዚአብሔር መልአክ” (22፥11) እንደ ተጠቦኘ ነው።

የሁለቱ ልጆች በረከት ለአብርሃም የተሰጠውን ተስፋ ጭብጥ ያስታውሰናል። እግዚአብሔር “ስምህን ገናና አደርገዋለሁ” (12፥2) በማለት ለአብርሃም ተስፋ በገባለት መሠረት እነዚህም ልጆች በያዕቆብ “ስም” እንዲሁም በአብርሃምና በይስሐቅ “ስም” ይጠራሉ። እግዚአብሔር “ታላቅ ሕዝብ አደርግሃለሁ” (12፥2) በማለት ለአብርሃም ተስፋ በሰጠው መሠረት “በምድር ላይ እጅግ ይበዛሉ”።

17-20 እዚህ ላይ በአጽንዖት ለመግለጽ የተፈለገው፣ ከምናሴ ይልቅ ታናሹ ልጅ ኤፍሬም ከፍ ከፍ መደረጉን ነው። ምንም እንኳ የያዕቆብ ዐይኖች ቢደክሙም (ቁ. 10)፣ ይስሐቅ የፈጸመውን ስሕተት እርሱም ሊፈጽም ነበር፤ በምዕ 27 ላይ እንደምናነበው ይስሐቅ የተሳሳተው ያዕቆብ ስላታለለው ነው። ዮሴፍ ሊያርመው ቢሞክርም፣ ሐሳቡን በግልጽ አስታወቀ፡- “ታናሽ ወንድሙ ከእርሱ ይበልጣል”። ከፍ ከፍ የሚደረገው ዮሴፍ ወይም ሁለቱ ልጆቹ ሳይሆን ይሁዳ ሆኖ ሳለ ኤፍሬም ወይም ምናሴ ቅድሚያ እንዲሰጣቸው በእጅጉ የተፈለገው ለምንድን ነው? ከፍ ከፍ ስለሚደረገው ሰው ትልቅ ትኩረት የተሰጠው የእግዚአብሔርን በረከት ለመቀበል በዚህ ዓለም ያለን ስፍራ መሠረት አለመሆኑን ለማሳየት ነው። ይልቁንም በረከቱ በእግዚአብሔር ጸጋ ላይ ብቻ የተመሠረተ ነው። በረከቱ ሊሰጠው የማይገባው ሰው የተስፋው ወራሽ ሆነ።

21-22 በዚህ ታሪክ ውስጥ ያዕቆብን የምናየው “የሰይፍና የቀስት” ሰው ሆኖ ሳይሆን “ጭምትና ከድንኳኑ የማይወጣ” ሰው ሆኖ ነው (25፥27)። በሌላ ስፍራ ያዕቆብ ስለ ከነዓን ምድር ሰዎች እንዲህ ብሎ ነበር፡- “. . . ተባብረው ቢነሡብኝና ቢያጠቁኝ እኔና ቤተ ሰቤ መጥፋታችን አይደለምን?” (34፥30)። ያዕቆብ በሞት ዐልጋ ላይ ሆኖ በጎይል የወሰደውን ምድር ለዮሴፍ በሚያስተላልፍበት ጊዜ፣ ራሱን የሚያሳየን በተለየ መንገድ ነው። አሁን የሚናገረው ለዮሴፍ ቢሆንም፣ ከብዙ ቊጥር ተውላጠ ስም አጠቃቀሙ “ከእናንተ” እንደምንረዳው የሚናገረው ለብዙ ሕዝብ ነው። ይህ ብዙ ሕዝብ በኤፍሬምና በምናሴ ነገዶች የተወከለው የዮሴፍ ቤት ሳይሆን አይቀርም።

3. *ያዕቆብ ልጆቹን ባረከ (49፥1-28)*

1-2 ያዕቆብ ለልጆቹ የተናገራቸው የመጨረሻ ቃላት የመጽሐፉ ዐቢይ ጭብጥ የመጨረሻ አረፍተ ነገር ሆነዋል። ይኸውም የእግዚአብሔር ዕቅድ ዘሮቹ ዐጥተውት የነበረውን የአብርሃምን በረከት ተመልሶ እንዲያንሰራራ ማድረግ ነው። ያዕቆብ የተናገረውን የመጨረሻ ቃል ጸሓፊው ምን ያህል እንደ ተረዳው የምናውቀው ታሪኩን በከበቡት ጭብጮች ነው። ያዕቆብ የሚናገረው “በኋለኛው ዘመን” ዘኍ. 24፥14-24፤ ዘዳ 31፥29 ይመ) ስለሚሆኑት ነገሮች እንደ ሆነ በግልጽ ተነግሮናል። በሦስቱም ምንባቦች ላይ ርእሰ ጉዳዩ የተነገረው “በኋለኛው ዘመን” በሚለው ሐረግ ሲሆን፣ ይህም እግዚአብሔር የመረጠውን ሕዝቡን እንደሚያድን ያሳያል። በዚህ የማዳኑ ታሪክ ዋና ተዋናይ የሆነ አንድ ንጉሥ አለ (ዘፍ 49፥10፤ ዘኍ 24፥7፤ ዘዳ 33፥5)። በዘፍጥረት 49 ላይ ይህ ንጉሥ ከይሁዳ ቤት ጋር ተሳስሯል።

በያዕቆብ ንግግር መዝጊያ ላይ (ቁ. 28) ጸሓፊው በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ያዕቆብ የተናገራቸውን ቃሎች ከ1፥28 ጀምሮ የመጽሐፉ ዐቢይ ሐሳብ ከሆነው “ከበረከት” ጭብጥ ጋር አስተሳስሯቸዋል። ይህንንም ያደረገው በቁ. 28 ላይ ብቻ “በረከት” የሚለውን ቃል ሦስት ጊዜ በመጥቀስ ነው፤ ቊጥር 28 እንዲህ ይነበባል፡- “. . . ባረካቸው፤ እያንዳንዳቸውን እንደ በረከታቸው ባረካቸው።” የያዕቆብ የመጨረሻ ቃሎች ወደ ፊት ማለትም በኋለኛው ዘመን ስለሚሆኑት ነገሮች ይናገራሉ፤ ለዚህም መሠረት ያደረገው ከዚህ በፊት እግዚአብሔር ለሰው ልጆች የሰጠውን በረከት ነው። የልጆቹ ቅደም ተከተል ከሞላ ጐደል የተዘገበው እንደ አወላለዳቸው ነው (ምዕ 29-30)። በመጀመሪያ የተጠቀሱት የልያ ልጆች ሲሆኑ፣ ቀጥሎም የአገልጋዮቹ ማለትም የባላን፣ የዘለፋ፣ እንደ ገናም የባላን ልጆች በመጨረሻም የራሔል ልጆች ተጠቀሱ።

3-4 ስለ ሮቤል የተነገረው ቊልፍ ቃል “አለቅነት ለአንተ አይሁን” (አመት፣ “እልቅና አይኖርህም”) የሚለው አረፍተ ነገር ነው። “አለቅነት” የሚለው ቃል ከዚህ ቀደም ብሎ ከተነገሩት ሁለት ሐረጎች ጋር ተመሳሳይ ነው፡- “የክብር አለቃ” እና “የጎይል አለቃ”። ሮቤል ቢልቅም አለቃ ግን አይሆንም። አለቃ የማይሆንበት ምክንያት በግልጽ ተጠቅሷል፡- ወደ አባትህ መኝታ ወጥተሃልና . . . አረከሰኸውም (ከ35፥22 ጋር ያነጻ)። ሮቤል የአባቱን ክብር ስላረከሰ የብኩርናውን መብት አያገኝም (ከ1ዜና 5፥1-2 ጋር ያነጻ፤ የበኩሩ መብት ለዮሴፍ ተላለፈ)።

5-7 ስምዖንና ሌዊ በአንድነት የተጠቀሱት በሴኬም ከተማ ብዙ ሰዎች ላለቁበት ተግባር መንሥኢ በመሆናቸው ነው (34፥35)፤ በወቅቱ ያዕቆብ እነዚህ ሁለት ልጆች ረዳት የለሾችን በመጨፍጨፋቸው ክፉኛ ወቅሦአቸዋል (34፥30)። በዚህ ክፍል ያዕቆብ ለፈጸሙት ተግባር የመጨረሻ ፍርዱን ሰጠ፤ የሌዊና የስምዖን ሁለቱ ነገዶች በተስፋዱቱ ምድር ርስት አይኖራቸውም። የያዕቆብ ቃሎች በትክክል መፈጸማቸውን እናያለን፤ ከኢያሱ ዘመን በኋላ የስምዖን ነገድ በቅዱሳት መጻሕፍት ታሪክ ውስጥ ስሙ ተጠቅሶ አናገኝም (ምክንያቱም “የሰምዖን ልጆች በርስታቸው [በይሁዳ ልጆች] መካከል ወረሱ”፤ ኢያ 19፥9)፤ ደግሞም የሌዊ ነገድ የክህነት አገልግሎት ስለ ተሰጠው በተስፋዱቱ ምድር ርስት አልተሰጠውም።

8-12 ያዕቆብ ታላላቆቹ ወንድሞች የበረከቱ ወራሽ እንደማይሆኑ ከገለጸ በኋላ፣ የይሁዳ ነገድ የላቀውን ስፍራ እንደሚይዝ ትንቢት ተናገረ። በዘፍጥረት 48፥5 መሠረት የብኩርናው መብት የሚገባው ለዮሴፍ እንደ ሆነ ተመልክተናል (ከላይ የተሰጠውን ትንተናና 1ዜና 5፥1-2 ይመ)። ምንም እንኳ ይሁዳ የብኩርና መብት ባይኖረውም፣ ከሌሎቹ ይልቅ ንጉሣዊ ነገድ ሆኖ ተመረጠ። በ1ዜና 5፥2 መሠረት በሌሎች ወንድሞች ላይ በረታ (አመት፣ ብርቱ ነበር)፤ በዚህም የዙፋኑ ወራሽ ሆነ (ከመዝ 78፥67-68 ጋር ያነጻ)።

ያዕቆብ ስለ ሌሎቹ ልጆች ከተናገረው ይልቅ ይሁዳን በተመለከተ የተናገራቸው ቃሎች ግልጽ ናቸው። ስለ ይሁዳ የተናገረው ልክ እንደ ድል አድራጊ ዐርበኛ ከጦር ሜዳ ወደ አገሩ ሲመለስ ወንድሞቹ በሆታ ሲቀበሉት ነው። የቊጥር 8 ጒድኝት “ወንድሞችህ በፊትህ የሰገዱልሃል” በሚለው አረፍተ ነገር

ተራዝሟል። እዚህ ላይ ጸሓፊው የዮሴፍን ሕልም ሆነ ብሎ እንደ ጠቀሰ ለማየት አስቸጋሪ አይደለም (37፥10)። በዮሴፍ ቤት ላይ የደረሰው ነገር በዚህ ዐይነት ከመወሣቱም በላይ ወደ ፊት ለሚነሣው የይሁዳ ቤትም ተላልፏል።

የድል አድራጊው ዐርበኛ ምስል "ይሁዳ የአንበሳ ደቦል ነው" በሚለው ተራዝሟል። ስለ አንበሳው ደቦል የተነገረው ያደነውን ከበላ በኋላ በዋሻው እንደ ተኛ ተደርጎ ነው። በቁጥር 9 መጨረሻ ላይ የተነሣው ጥያቄ መልሱ ግልጽ ነው። በቁጥር 10 ላይ ድል አድራጊው ዐርበኛ ንጉሥ እንደ ሆነ ተገልጿል። በትረ መንግሥትና የገዥም ዘንግ በእጁ ነው። እንግዲህ ከያዕቆብ ቃሎች እንደምንረዳው ገዥ የሆነው እስኪመጣ ድረስ (ከሕዝ 21፥27 ጋር ያነጻ)፣ ይሁዳ በእስራኤል ነገዶች መካከል ትልቅ ሥልጣን ይኖረዋል።


የይሁዳን ነገድ በተመለከተ ከተነገሩት ሁሉ እጅግ የሚያስገርመው ቀጥሎ የምናገኘው ገለጻ ነው፦ "ሕዝቦች ሁሉ ይታዘዙልሃል"። "ሕዝብ" በሚለው ነጠላ ቁጥር ፈንታ "ሕዝቦች" የሚለው ብዙ ቁጥር የገባው የያዕቆብ ሥልጣን የእስራኤልን ልጆች ዐልፎ ሌሎች ሕዝቦችንም የሚጨምር መሆኑን ለማመልከት ነው። ይህም በ28፥3 እና በ48፥4 ላይ እግዚአብሔር ለያዕቆብ የተናገረውን ያስተጋባል፦ "ለብዙም ሕዝብ ጉባኤ አደርግሃለሁ"።

ጠጅ እጅግ የሚትረፈረፍ መሆኑን ነው፤ ምርጥ የሆነው የወይን ግንድ እንኳ ለስብቶች ማሰሪያ ይሆናል፤ ወይን ጠጅ ደግሞ እንደ ልብስ ማጠቢያ ውሃ የትም ይገኛል። ቁጥር 12 ወደ ይሁዳ ንጉሥ ገለጻ ይመለሳል። ዐይኖቹ ከወይን ጠጅ ይልቅ የቀሉ ናቸው፤ ጥርሶቹም ከወተት ይልቅ የነጡ ናቸው። እርሱ የብርታትና የኀይል ምልክት ነው። የኋላኞቹ ጸሓፊዎች ወደ ፊት ስለሚገለጠው የመሲሑ አገዛዝ እጅግ ብዙ የተናገሩት ከዚህ ዐጭር ምንባብ ተነሥተው ነው (ከኢሳ 63፥1-6፤ ከራእ 19፥11፣13፣15 ጋር ያነጻ)።

ከዮሴፍ በቀር ያዕቆብ ስለ ቀሩት ልጆች የተናገራቸው ቃሎች ታዋሽ ናቸው፤ ታዋሽ የሆኑት ዐጭር ስለ ሆኑ ብቻ ሳይሆን የቀደመውንና ወደ ፊት ሚመጣውን ታሪካቸውን ስለሚያወሡም ነው። የቀሩት ልጆች ዕጣ ፈንታ ከስሞቻቸው ጋር የተያያዘ ነው። ሁሉንም ምስሎች የሚያቄራኘው ጭብጥ ብልጽግና ነው። ከይሁዳ ነገድ የሆነው ድል አድራጊ ንጉሥ በሕዝቦች ሁሉ ላይ እንደሚነግሥ ሁሉ፣ የቀሩት ወንድሞችም ተመሳሳይ ሀብትና በረከት ያገኛሉ።

13 የርስቱ ድርሻ ድንበር እስከ ባሕሩ የማይዘልቀው ዛብሎን (ኢያ 19፥10-16) ወሰኑ እስከ ባሕሩ ማለትም እስከ ሲዶና ይደርሳል። ዛብሎን የሚለው የዕብራይስጡ ስም ትርጉም "መኖሪያ" ማለት

የእስራኤል ነገዶች



*በጵንኤል ያዕቆብ ከመለኮታዊ መልእክተኛ ጋር ሲታገል ስሙ ትእምርታዊ በሆነ መልኩ ወደ እስራኤል ተቀየረ። የ12ቱ ነገዶች አባት እንደ መሆኑ መጠን፣ ይህ ሕዝብ በእርሱ ስም መጠራት ጀመረ፤ በግጥምም ያዕቆብ እየተባለ ይጠራል።

**ከነዓንን ከወረሱ በኋላ ለሌዊ ወገን ርስት አልተሰጠውም ነበር (ዘፍ 49፥7)። በምትኩ ሌዋውያን ለሕዝቡ የክህነት አገልግሎትን በመስጠት ለእግዚአብሔር የተለዩ እንዲሆኑ ሙሴ አደረገ (ዘኍ 3፥1-4፡49)፤ ኢያሱም በመላው እስራኤል የተለያዩ 48 ከተሞችን ለሌዋውያን ሰጠ (ኢሱ 21፥1፥45)።

***ያዕቆብ የዮሴፍን ልጆች ኤፍሬምንና ምናሴን ልጆቹ አድርጎ ስለ ወሰዳቸው ዮሴፍ በእስራኤል የሁለት ነገዶች አባት ሆኖአል።

የሆነ ሆኖ የኋላኞቹ ቅዱሳት መጻሕፍት ጸሓፊዎች ወደ ፊት የሚነሣው ዳዊታዊው ንጉሥ (ለምሳሌ፣ መዝ 2፥8፤ ዳን 7፥13-14፤ ራእ 5፥5፡9) በመላው ዓለም ላይ እንደሚነግሥ የተናገሩት በእነዚህ ምንባቦች እየተመሩ ነው።

ቁጥር 11-12 ከይሁዳ ነገድ ስለሚወጣው አገዛዝ ሰፊ ገለጻ ይሰጣል። በእርሱ አገዛዝ ዘመን ለሁሉ የሚበቃ ነገር ይኖራል። ይህ ለሁሉ የሚበቃው ነገር የተገለጸው በምርጥ የወይን ግንድ ላይ በታሰረ አህያና በወይን ጠጅ በታጠበ ልብስ ነው። እዚህ ላይ ለመግለጽ የተፈለገው የሀብትና የበረከት ምልክት የሆነው የወይን ሲሆን የተስፋዱ ምድር ዳርቻ እስከ ሲዶና እንደሚደርስ ያመላክታል። "ይኖራል" እና "መኖሪያው" በሚሉት ቃሎች መካከል የድምፅ ተመሳሳይነት እንዲኖር ሳይፈለግ አይቀርም።

14-15 ይሳኮር የሚለው ስም "ዋጋዬን" (30፥18) ከሚለው ቃል ጋር ተመሳሳይ ድምፀት ያለው ሲሆን፣ ጥንካሬው እንደ ብርቱ አህያ እንደ ሆነ ተነግሮለታል፤ እርሱም የዕረፍት ምድሩ መልካም እንደ ሆነች ባየ ጊዜ፣ ችግሯን ለመሸከም ትከሻውን አዘጋጀ። "ማረፊያ ምድሩ መልካም እንደ ሆነች ባየ ጊዜ" የሚለው ሐረግ በምዕ. 1 ላይ "እግዚአብሔርም ያ መልካም እንደ ሆነ አየ" የሚለውን ተመሳሳይ አገላለጽ ሳያስተጋባ አይቀርም። ይህም

በፍጥረት የእግዚአብሔር ሐሳብ መልካም የሆነውን ለሰው ልጆች ለመስጠት እንደ ሆነ ሁልጊዜ ያስታወሰናል። ያዕቆብ ማረፊያ ምድሩ ወይም የዕረፍት ምድሩ ለማለት የተናገራቸው ቃሎች እግዚአብሔር በተስፋዩቱ ምድር ለሕዝቡ ከሚሰጠው፣ ዕረፍት ጋር ይተሳሰራሉ (ከመዝ 95፥11 ጋር ያነጻ)።

16-18 ዳን የስሙ ትርጉም ይፈርዳል ማለት ሲሆን በሕዝቡ ላይ የሚፈርድ እርሱ ነው። እርሱም እንደ መንገድ ዳር እባብ ፈረሰኛ ውን አድብቶ ለመጣል የፈረሱን ቁርጭምጭሚት በሚነድፍ እባብ ተመስሏል። ምንም እንኳ የምስሉ ትርጉም ግልጽ ባይሆንም፣ ያዕቆብ ዳንን በተመለከተ የተናገራቸው የመጨረሻ ቃሎች ምስሉን በአዎንታዊ ትርጉሙ እንድንረዳው ተፈልጓል፡- እግዚአብሔር ሆይ ማዳንህን እጠብቃለሁ (ቊ 18)። የእግዚአብሔርን ማዳን ተስፋ እንደሚያደርግ መገለጹ የያዕቆብ ቃሎች ትርጉም ምን እንደ ሆነ ፍንጭ ይሰጠናል። ስለ እያንዳንዱ ልጆች የወደ ፊት ዕጣ ፈንታ የተነገሩት ቃሎች የእስራኤልን ተስፋ አካተዋል። ተስፋው ሕዝቡ ይበለጽጋል፤ በጠላቶቹም ላይ ድል ይቀዳጃል የሚል ሲሆን ከይሁዳ ነገድ የሚወጣው ንጉሥም የዚህ ተስፋ ማእከል ነው።

19 ስለ ጋድ የተነገሩት ቃሎች በሙሉ ተመሳሳይ ድምፀት አላቸው ማለት ይቻላል። “ጋድ (ጋድ) ዘማቾች (ገዱድ) ይዘምቱበታል (የጉዱኑ) እርሱ ግን ተከታትሎ ይዘምትባቸዋል (ያጉድ)” ምንም እንኳ ስለ ጋድ የተነገረው በጥቂቱ ቢሆንም፣ የተባሉት ነገሮች ግን ለሌሎቹ ልጆች ከተነገረው ጋር ይመሳሰላሉ፤ ስለ ይሁዳ የተነገረውን ትንቢት በመከተል ጠላቶቹን ድል እንደሚያደርግ ተነግሮለታል።

20 ስለ አሴር የተነገሩት ቃሎች ተመሳሳይ ድምፀት ባይኖራቸውም፣ ትርጉማቸው ግን ግልጽ ነው። በሚመጡት ዘመናት የአሴር ልጆች እጅግ ይበለጽጋሉ።

21 ስለ ንፍታሌም የተነገሩት ቃሎች ጥቂት ናቸው። የሚያስተላልፉት መልእክት እንደ ሌሎቹ ልጆች ሁሉ እርሱም ሀብቱ የተትረፈረፈ ይሆናል የሚል ነው።

22-26 ያዕቆብ ስለ ዮሴፍ ነገድ የወደ ፊት ዕድል የተናገረው ብዙ ነው። የተናገራቸው ቃሎች በይዘታቸው ከይሁዳ ቀጥሎ ስለ ሌሎቹ ወንድሞች ከተናገራቸው ጋር ይመሳሰላሉ። ይሁንና ልዩነቱ “በረከት” የሚለው ቃል መደገሙ ነው። ያዕቆብ ስለ ሌሎቹ ወንድሞች የተናገራቸው ቃሎች ነገዶቹ በሚመጡት ዘመናት እንደሚበለጽጉና እንደሚባረኩ ቢገልጹም፣ ስለ ዮሴፍ የተናገራቸው ቃሎች ግን በሚመጡት ዘመናት የሚያገኘውን ይህን ብልጽግና የሚጠቅሱት እንደ “በረከት” ነው። እንግዲህ ስለ ዮሴፍ የተነገሩት እነዚህ ቃሎች የሚመደቡት ከዚህ በፊት ስለ በረከቱ ተስፋ በግልጽ ከሚናገሩት ምንባቦች ረድፍ ነው፤ እንዲሁም በቊ 28 ላይ ያዕቆብ ለተናገራቸው የመጨረሻ ቃሎች መንገዱን ይጠርጉልናል፡- “. . . ባረካቸው፤ እያንዳንዳቸውንም እንደ በረከታቸው ባረካቸው።” በቊጥር 24 ላይ “እረኛ” የሚለው ቃል ያዕቆብ ከዚህ በፊት ኤፍሬምንና ምናሴን በባረካቸው ጊዜ የተናገረውን ያስታውሰናል (48፥15)።

27 ስለ ብንያም የተነገረው ከይሁዳ ጋር ይመሳሰላል። ለሁለቱም የተነገሩት ቃሎች የእስራኤል አባቶች በሚመጡት ዘመናት በጠላቶቻቸው ላይ ድል እንደሚቀዳጁ ይገልጻሉ። ለሁለቱም በተነገረው መሠረት ድል አድራጊው ዘነጣጥሎ እንደሚበላ አንበሳና ተኩላ ነው። ይሁንና ለብንያም የተነገሩት እነዚህ ቃሎች ከይሁዳ ይልቅ የብንያምን ድል አድምቀው ገልጸውታል።

28 ጸሓፊው ያዕቆብ ስለ ልጆቹ የተናገራቸውን ቃሎች ያጠቃልላል። እነርሱም፡- በአብርሃም፣ በይስሐቅና በያዕቆብ ዘሮች አማካይነት መተላለፍ ያለበትን በረከት የሚያንጸባርቁ ናቸው። ያዕቆብ ለእያንዳንዱ ልጅ በተናገራቸው ቃሎች ውስጥ (ከይሁዳ በኋላ) የበረከቱ ጭብጥ በሁለት ዐበይት ምስሎች ተገልጧል። አንደኛው፣ የበረከቱ ሌላው ጉን አጽንዖት የተሰጠው በድል አድራጊው ጦረኛ ምስል ነው። ጠላት ተሸነፈ ማለት የመሲሑ ሰላም መጣ ማለት ነው። ሁለተኛው፣ የበረከቱ አዎንታዊ ጉን አጽንዖት የተሰጠው በሰላምና በብልጽግና ምስል ነው። ከዚህ ምስል በስተ ጀርባ የዓድን ገነት አለች፡- የሰው ልጆች ያጧት ገነት። የያዕቆብ ቃሎች ያተኮሩት፣ በትረ መንግሥት የሚገባው ሲመጣ (ቊ 10)፣ እግዚአብሔር በዓድን ገነት አስቀድሞ ያሰበው (ያዘጋጀው) ሰላምና ብልጽግና እንደ ገና ይሰፍናል በሚለው ተስፋ ላይ ነው።

4. የያዕቆብ ሥርዐተ ቀብር መመሪያ በድጋሚ ተነገረ (49፥29-33)

29-33 ያዕቆብ የመሞቻው ቀን ሲደርስ ከአባቶቹ ጋር በተስፋዩቱ ምድር እንዲቀበር ልጆቹን በድጋሚ አዘዛቸው። እንዲቀበር የፈለገውም “በመክፈላ” ነው፤ መክፈላ አብርሃም ለመቃብር ቦታ እንዲሆን የገዛው ነው (ምዕ.23)። ምንም እንኳ ያዕቆብ ቀደም ሲል ተመሳሳይ ጥያቄ ቢያቀርብም (47፥29-33)፣ ይህ የመጨረሻው ግን የሚፈልገውን ሁሉ የተናገረበት ነው። ከአብርሃም፣ ከሣራ፣ ከይስሐቅ፣ ከርብቃና ከልያ ጋር ለመቀበር ፈለገ። ጥያቄው ስለ ተስፋዩቱ ምድር ያለንን ግንዛቤ ያድሳል፤ የያዕቆብ ዘሮች ለአብርሃምና ለይስሐቅ ተስፋ በተሰጣቸው ምድር በሰላም ይኖራሉ። ያዕቆብ በእግዚአብሔር ተስፋ ላይ የነበረው እምነት እስከ መጨረሻው የጸና ነበር። ያዕቆብ ይህን ከተናገረ በኋላ “እግሮቹን በዐልጋው ላይ ሰብስቦ የመጨረሻ ትንፋሹን ተነፈሰ፤ ወደ ወገኖቹም ተሰበሰበ።”

ሰ. የያዕቆብ መሞትና መቀበር (50፥1-14)

1-14 ከግማሽ በላይ የሚሆነው የመጨረሻው ምዕራፍ የተሰጠው ለያዕቆብ ሥርዐተ ቀብር ነው። ራሱ ዮሴፍ፣ ከዚያም ግብፃውያን አልቅሰውለታል። ዮሴፍና ግብፃውያን ታላቅ ዝማጅት አድርገውለታል። ያዕቆብ በገዛ ምድሩ እንዲቀበር ከፈርዖን ልዩ ትእዛዝ ተሰጥቶ ነበር። በመሆኑም የያዕቆብን አስክሬን ወደ ከነዓን ለመውሰድ እጅግ ብዙ ሕዝብ ወጣ። “የፈርዖን ባለሥልጣኖች ሁሉ . . . የግብፅ ምድር መኳንንት ሁሉ” እንዲሁም። የፈርዖን ሠረገሎችና ፈረሰኞች ዮሴፍን ተከትለው ወደ ከነዓን ሄዱ። ከነዓናውያንም፣ “ይህ ታላቅ ልቅሶ” እንደ ሆነ ተረድተው ነበር።

ሌሎቹ የእስራኤል አባቶች ወደ ወገኖቻቸው ሲሰበሰቡ፣ ሞቱና ተቀበሩ ተብሎ ባጭሩ ሲነገር፣ ስለ ያዕቆብ ሥርዐተ ቀብር በዝርዝር የተነገረው ለምንድን ነው? ሌላው ቀርቶ ስለ ዮሴፍ ሞት እንኳ የተነገረው በጣም ባጭሩ ነው፤ ስለ መሞቱና በሣጥንም ውስጥ እንዳኖሩት ከመነገሩ በቀር ሌላ ምንም አልተባለም (ቊ 26)። በታሪኩ ውስጥ ለዚህ ነገር አጽንዖት የተሰጠው ለምን እንደ ሆነ መመርመሩ ተገቢ ነው።

ጸሓፊው እስከ አሁን ድረስ ያተኰረው እግዚአብሔር ምድሪቱን ለመስጠት ባሳየው ታማኝነትና የእግዚአብሔርም ሕዝብ አንድ ቀን ወደ ምድሪቱ ለመመለስ ባላቸው ተስፋ ላይ ነበር። በነቢያቱ መጻሕፍት ላይ የምናገኘው ምስል እንደሚያስገነዝበን እስራኤል ወደ ተስፋዩቱ ምድር በምትመለስበትና የተሰጣትም ተስፋ በሚፈጸምበት ጊዜ፣ ብዙ ሕዝብ አጅቢት ተመልሳለች። የእስራኤል ነቢያት ስለ መመለሷ የተናገሩት እንዲህ በማለት ነበር፡- “ሕዝቦች ሁሉ ወደ ኢየሩሳሌም ይጐርፋሉ፤ ብዙ ሕዝቦችም ‘ኑ ወደ እግዚአብሔር ተራራ እንውጣ፤ ወደ ያዕቆብ አምላክ ቤት መቅደስም እንሂድ ይላሉ’ (ኢሳ 2፥2-3፤ ዘካ 8፥23)።

በዚህ ታሪክ ውስጥ ተመሳሳይ ምስል መኖሩን ለማየት እምብዛም አይከብድም። ያዕቆብ ወደ ተስፋዩቱ ምድር ለመጨረሻ ጊዜ የተመለሰው፣ ከግብፅ ምድር እጅግ ብዙ ሕዝብና መኳንንት አጅበውት ነበር። ከእርሱም ጋር የግብፃውያን ኃያላን ወታደሮች ነበሩ። እንግዲህ የያዕቆብ በተስፋዩቱ ምድር መቀበር የሚያስተጋባው፣ እግዚአብሔር የያዕቆብን ምርኮ እመልሳለሁ፤ ለእስራኤልም ቤት ሁሉ እራራለሁ በማለት የተናገረውን መጪውን ጊዜ ነው (ሕዝ 39፥25)።

፯. የዮሴፍ የመጨረሻው ታሪክ (50፥15-26)

ሀ. የዮሴፍ ይቅርታ (50፥15-21)

15-21 ታሪኩ እንደ ገና ወደ ዮሴፍ፣ ወደ ወንድሞቹና ወደ ዮሴፍ ታሪክ ማእከላዊ ጭብጥ ይመለሳል፡- እናንተ ክፉ ነገርን ዐሰባችሁብኝ፤ እግዚአብሔር ግን ዛሬ እንደ ሆነው ብዙ ሕዝብ እንዲድን ለማድረግ ለመልካም ዐሰበው”። በዮሴፍ ሕይወት ከተፈጸሙትና ሰዎች ካሰቡበት ሁሉ በስተ ጀርባ የማይለወጠው የእግዚአብሔር ዕቅድ ነበር። ይህም በመጽሐፉ መጀመሪያ ላይ የምናገኘው ዕቅድ ነው፤ እግዚአብሔር ለሰዎች የፈጠረውን ነገር ሲመለከት “እነሆ መልካም ነበረ” (1፥4-31)። እግዚአብሔር በእስራኤል አባቶችና በዮሴፍ ሕይወት መልካም ሐሳቡን ይፈጽም ነበር። ለዕቅዶቹም የታመነ ነበር።

ዮሴፍ ከወንድሞቹ ጋር የነበረውን ግንኙነት በተመለከተ የተነገረው የመጨረሻው ገለጻ እንዲህ የሚል ነበር፡- “አጽናናቸውም፤ ደስ አሰኛቸውም”። ይህ ምስል የእስራኤል ልጆች ከምርኮ ወደ ተስፋዩቱ ምድር ለመመለስ የሚጠባበቁበትን ጊዜ

እንደሚያሳይ ለመረዳት ከባድ አይደለም (ከኢሳ 40፥1-2 ጋር ያነጻ)።

ለ. የዮሴፍ ሕይወትና ሞት ዕጣፈ (50፥22-26)

22-26 ምንም እንኳ ቃሎቹ ጥቂት ቢሆኑም፣ ዮሴፍ ለልጆቹ የተናገራቸው ቃሎች በእነዚህ ታሪኮች ውስጥ የምናገኘው ተስፋ ምን ዐይነት እንደ ሆነ በግልጽ ያሳዩናል። እንደ ያዕቆብ ሁሉ፣ ልጆቹ ወደ ምድሪቱ ሲመለሱ ዐጥንቱን (ዐፅሙን) ይዘው እንዲመለሱ አስማላቸው። ምንም እንኳ እንደሚሞትና ልጆቹም ወደ ምድሪቱ የሚመለሱበትን ቀን እንደማያይ ቢያውቅም፣ በእግዚአብሔር ተስፋ ላይ ያለውን እምነትና ተስፋ በግልጽ አሳይቷል። “እግዚአብሔርም መጐብኘትን ይጐበኛችኋል፤ ከዚችም ምድር ያወጣችኋል፤ ለአብርሃምና ለይስሐቅ፣ ለያዕቆብም ወደ ማለላቸው ምድር ያደርሳችኋል።” በዮሴፍ ታሪክ ሥነ ጽሑፋዊ ስልት እንደ ተለመደው ሁሉ፣ ዮሴፍ በእግዚአብሔር ላይ ያለውን እምነት ለሁለተኛ ጊዜ ገለጸ (ከ41፥32 ጋር ያነጻ) ፡- “እግዚአብሔር ሲያስባችሁ ዐጥንቴን ከዚህ አንሥታችሁ ከእናንተ ጋር ውሰዱ”።

ኦሪት ዘፍጥረት የሚጨርሰው እስራኤላውያን በግብፅ ምድር እንደ ነበሩ በመግለጽ ነው። ታሪኩ ግን በዚህ አይደመደምም። ከዚህ በፊት በመጽሐፉ ክፍሎች እንደ ሆነው ሁሉ፣ የእስራኤል አባቶች እንደ ሞቱ በሚቀጥለው መጽሐፍ ላይ ወዲያው የምናገኘው የስም ዝርዝር ነው፤ ይህም፣ ታሪኩ በተተኪው ትውልድ ሕይወት እንደ ቀጠለ ያሳያል (ከዘፍ 50፥26 - ዘፀ 1፥5 ከዘፍ 35፥29-36፥43 ጋር ያነጻ)።

ብሉይ ኪዳን በዐዲስ ኪዳን

የብሉይ ኪዳን ምንባብ	የዐዲስ ኪዳን ምንባብ	ርእሰ ጉዳዩ
ዘፍ 1፥3	2ቆሮ 4፥6	የብርሃን መፈጠር
ዘፍ 1፥27	ማቴ 19፥4፤ ማር 10፥6	የሰው ልጆች መፈጠር
ዘፍ 2፥2	ዕብ 4፥4	እግዚአብሔር በሰባተኛው ቀን ዐረፈ
ዘፍ 2፥7	1ቆሮ 15፥45	የአዳም መፈጠር
ዘፍ 2፥24	ማቴ 19፥5፤ ማር 10፥7፤ 1ቆሮ 6፥16፤ ኤፌ 5፥31	የጋብቻ መመሥረት
ዘፍ 5፥2	ማቴ 19፥4፤ ማር 10፥6	የሰው ልጆች መፈጠር
ዘፍ 12፥1	ሐሥ 7፥3	የአብርሃም መጠራት
ዘፍ 12፥3	ገላ 3፥8	ወንጌል ለአብርሃም
ዘፍ 13፥15	ገላ 3፥16	የአብርሃም ዘሮች
ዘፍ 14፥18-20	ዕብ 7፥17:21	መልከ ጼዴቅ
ዘፍ 15፥5	ሮሜ 4፥18	የአብርሃም ዘሮች
ዘፍ 15፥6	ሮሜ 4፥3:9:22፤ ገላ 3፥6፤ ያዕ 2፥23	የአብርሃም እምነት
ዘፍ 15፥13-14	ሐሥ 7፥6-7	ትንቢት ስለ አብርሃም
ዘፍ 17፥5	ሮሜ 4፥17	አብርሃም የብዙዎች አባት
ዘፍ 18፥10:14	ሮሜ 9፥9	ለሣራ የተሰጠ ተስፋ
ዘፍ 18፥18	ገላ 3፥8	ወንጌል ለአብርሃም
ዘፍ 21፥10	ገላ 4፥30	የእስማኤል መባረር
ዘፍ 21፥12	ሮሜ 9፥7፤ ዕብ 11፥18	እግዚአብሔር ይስሐቅን መምረጡ
ዘፍ 22፥17	ዕብ 6፥14	እግዚአብሔር ለአብርሃም የገባው መሐላ
ዘፍ 22፥18	ሐሥ 3፥25	ሕዝቦች በአብርሃም አማካይነት መባረካቸው
ዘፍ 24፥7	ገላ 3፥16	የአብርሃም ዘሮች
ዘፍ 25፥23	ሮሜ 9፥12	እግዚአብሔር ያዕቆብን መምረጡ
ዘፍ 26፥4	ሐሥ 3፥ 25	ሕዝቦች በአብርሃም አማካይነት መባረካቸው

ኦሪት ዘፀአት

መግቢያ

1. ርእስ

“ፀአት” በግእዝ መውጣት፣ ቦታ መልቀቅ ማለት ነው። በዕብራይስጥ ይህ መጽሐፍ “እና” በሚል መስተዋድድ ይጀምራል፤ይህም የዘፍጥረት መጽሐፍ ተከታይ ለመሆኑ አጽንዖት ይሰጣል። በዚህ ዐይነት ይህ መጽሐፍ በዕብራውያኑ ቀኖና መጻሕፍት ውስጥ የመጀመሪያዎቹ ዐምስቱ በተካተቱበት ቶራ (ትርጉሙ፡- ሕግ ወይም ትምህርት) በተባለው ክፍል ውስጥ ይገኛል ማለት ነው። ከሁለተኛው ምታመት ድ.ል.ክ ጀምሮ እነዚህ ዐምስት መጻሕፍት “ፔንታቱክ” (በግሪክ ዐምስት መጻሕፍት ማለት ነው) ተብለው ይጠራሉ።

2. ጸሓፊ

ይህን መጽሐፍ ሙሴ እንደ ጻፈው በቀጥታ የሚናገሩ ውስጣዊ ማስረጃዎች ያሉ ሲሆን (17፥14፤ 34፥4፡27-29፤ 24፥4፤ 20፥22-23፥33) እነዚሁ ማስረጃዎች የሙሴን ደራሲነት በሚያጸኑ የሌሎች የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ምንባቦች ድጋፍ አላቸው (ከኢያ 1፥7፤ 8፥31-32፤ 1ነገ 2፥3፤ 2 ነገ 14፥6 እና ከሌሎችም ጋር ያነጻ)። የዐዲስ ኪዳን ጸሓፊዎችም ይህንኑ የሙሴ ጸሓፊነት ይደግፋሉ (ከማር 12፥26 እና ከዘፀ 3፥6፤ ሉቃ 2፥22-23 እና ዘፀ 13፥2፤ ማር 7፥10 እና ዘፀ 20፥12፤ 21፥17 ጋር ያነጻ)።

3. የተጻፈበት ዘመን

ሙሴ ሕዝበ እስራኤልን መምራት የጀመረው በ80 ዓመቱ ስለ ሆነ (7፥7) ኦሪት ዘፀአት የተጻፈው በዚህ ዘመንና በምድረ በዳው ጕዞ ማብቂያ መዳረሻ ማለት ሙሴ 120 ዓመት ዕድሜ ሲሞላው በነበረበት ጊዜ መካከል መሆን አለበት (ዘዳ 34፥7) ስለዚህ የዘፀአት መጽሐፍ የተጻፈበት ግምታዊ ጊዜ እስራኤል ከግብፅ የወጡበትን ቀን ያገናዘበ ይሆናል።

4. እስራኤል ከግብፅ የወጡበት ጊዜ

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉትን ሁነቶች ከግብፃውያን የጊዜ ሰሌዳ ጋር ያለማመንታት ለማዛመድ የሚያስችል በቂ ዝርዝር በዘፀአት መጽሐፍ የትኛውም ቦታ አልተሰጠንም። የምናውቀው ነገር ቢኖር “ዮሴፍን ያላወቀ ዐዲስ ንጉሥ” (1፥8) ወይም ስሙ በውል ያልታወቀ “ፈርዖን” (1፥11፡19፡22፤ 2፥15) ወይም “የግብፅ ንጉሥ” (1፥15፤2፥23) እንደ ነበረ ብቻ ነው። ፈርዖን› የሚለው ቃል ፍቺው “ታላቅ ቤት” የሚል ሆኖ የንጉሡን መኖሪያና ቤተ ሰቡን የሚገልጽ ቃል ነበረ። ይህ ቃል ለንጉሡ ለራሱ መጠሪያ መሆን የጀመረው በግብፅ 18ኛው ሥርወ መንግሥት መሆኑን ልብ ማለት ይገባል። በዚሁ አካሄድ እንግዲህ ዘፀ 2፥23 አስጨናቂው “ፈርዖን” (ከ4፥19 ጋር ያነጻ) እንደ ሞተ ስለ ነገረን በእስራኤል መውጣት ጊዜ የነበረው “ፈርዖን” ሌላ እንደ ሆነ እናውቃለን። ይሁን እንጂ የሁለቱንም ማንነት በስም ለይተን በግል ልናውቃቸው የሚያስችል ውስጣዊ መረጃ አናገኝም።

ስለነዚህ ሁለት ፈርዖኖች ማንነት የተሰጡት መግለጫዎች በሁለት አመለካከቶች ላይ ማእከል ያደርጋሉ፡- (1) ፀአተ እስራኤልን በ18ኛው የግብፅ ሥርወ መንግሥት ዘመን መፈጀ (1580-1321 ዓቅክ ገደማ) (2) በ19ኛው የግብፅ ሥርወ መንግሥት ዘመን ማስቀመጥ (1321-1205 ዓቅክ ገደማ) ባጠቃላይ አነጋገር ወግ አጥባቂ ምሁራን ቀደም ያለውን ጊዜ ይቀበላሉ። ይህ ማብራሪያም ያንኑ ያካትታል።

5. ነገረ መለኮት

ኦሪት ዘፀአት በብሉይ ኪዳን ካሉት በጣም የበለጸጉ የነገረ መለኮት ምንጮች አንዱ ነው። ከሁሉ በላይ ስለ እግዚአብሔር ማንነት፣ ስለ ማዳን ሥራው (መቤዠቱ)፣ ስለ ሕጉና ለእርሱ ስለሚቀርበው አምልኮ መሠረት ይጥላል። እንዲሁም ስለ ታላቁ የክህነት ተቋምና የነቢይ ሚና መነሻ ይሰጣል። ደግሞም በእግዚአብሔርና በሕዝቡ መካከል ያለውን ኪዳናዊ ግንኙነት ቅርጽ ይሰጠዋል።

ዘፀአት የእግዚአብሔርን ባሕርይ በዝርዝር ከማቅረቡም በላይ ያህዌ በሚለው ስሙ አማካይነት የተገለጸውን የሀልዎቱንና የክብሩን ታላቅነት ያሳያል። ፍትሓዊነቱ፣ እውነተኛነቱ፣ ምሕረቱ፣ ታማኝነቱና ቅዱስነቱ ጕልሕ ስፍራ ተሰጥቷቸዋል። “በምስጋና የተፈራ፣ ድንቅን የሚያደርግ፣ በቅድስና የከበረ” (15፥11)።

እርሱን የመሰለ ስለሌለ እግዚአብሔር የታሪክም ጌታ ነው። እንግዲያው የእስራኤል መከራም ሆነ የግብፅ መቅሠፍት ከቁጥጥሩ ውጪ አልነበሩም። በዚህ መጽሐፍ እግዚአብሔር ከብዙ ምታመታት በፊት ለአባቶች የተናገራቸውን ተስፋዎች መፈጸም ሲጀምር ይታያል።

የትድግናና የድነት (ደኅንነት) ትምህርቶች መጽሐፉ አጽንዖት የሰጠባቸው አርእስት ናቸው። ዐዲስ ኪዳን የተቀበለው የትምህርተ መቤዠት ዋና ማእከል (ዮሐ 1፥29፤ 1ቆሮ 5፥7 ይመ)፣ በዘፀአት ውስጥ በተገለጡት የፋሲካው ትረካ (ምዕ 12) እና የቃል ኪዳኑ መታተም (ምዕ 24) ታይቷል።

ኦሪት ዘፀአት እንዴት ባለ ሁኔታ መኖር እንዳለብንም ያስተምረናል። መጽሐፍ ቅዱሳዊው ሥነ ምግባርና የሞራል ሕይወት መሠረት የተጣለው ከሁሉ በፊት በእግዚአብሔር ዕጹባት ባሕርያት ላይ ሲሆን ደግሞም በዐሠርቱ ትእዛዛትና በቃል ኪዳኑ መጽሐፍ ትእዛዛት ላይ ነው።

መጽሐፉ በነገረ አምልኮ ላይ በቀረቡ ዝርዝር ትምህርቶች ወደ መደምደሚያ ይመጣል። የመገናኛው ድንኳን በጊዜ፣ በሥራ ድካምና በገንዘብ ወጪ ሲተመን በጣም ውድ ቢሆንም፣ ዐላማውና ቁም ነገሩን ስናጤን ወደ ሰው ልጅ የኑሮ ግብ ጠቋሚ ሆኖ እናገኘዋለን። ያም የሰው ልጅ ዋና የሕይወት ግብ እግዚአብሔርን ማክበርና ለዘላለም በእርሱ መደሰት ነው።

ትንተና

፩. መለኮታዊ መቤዠት (ማዳን) (1፥1-18፥27)

ሀ. የተሰፋ ፍጻሜ ፍሬያማነትና የማጥፋት ዘመቻ (1፥1-22)

1. ተስፋ የተነገረለት መባዛት (1፥1-7)

ሦስቱ የዘፀአት ዋና ዋና ርእሰ ጕዳዮች የሚከተሉት ናቸው፡- (1) የእግዚአብሔር የትድግና ዕቅድ (2) የእግዚአብሔር የምግባር መመሪያ (3) የእግዚአብሔር የአምልኮ ሥርዐት። መጽሐፉ ሲጀምር አንድ ሌላ ዋና ርእስ ወዲያው

ፊታችን ይደቀናል። ይህም ከቍ 1-7 ያለው ለአብርሃም ለይስሐቅና ለያዕቆብ ስለ ዘራቸው የተሰጠው ጥንታዊ ተስፋ ትንታኔ ነው (ዘፍ 15፥5፤ 22፥17)።

1-4 በዕብራይስጡ መጽሐፍ ኦሪት ዘፀአት የሚጀምረው "ስሞቻቸውም እነዚህ ናቸው" በሚል ሐረግ ነው፣ (እንዲያውም በዕብራይስጥ የመጽሐፉ ስም ራሱ ይኸው ሐረግ ነው ዘፍ 46፥8 ይመ)። ለአብዛኞቹ የብሉይ ኪዳን የታሪክ መጻሕፍት የወል የሆነው ይህ በአዲጋሚው "ም" ወይም "እና" የሚል ቃል መጽሐፍ የመጀመር ልምድ ለመጀመሪያ ጊዜ የሚጠቀሰው እዚህ ቦታ ነው (ኢያሱን፣ መሳፍንትን፣ ሩትን፣ 1ኛና 2ኛ ሳሙኤልን እና ሌሎችንም ያነጻ)። ይህ የሚጠቍመው ያልተቋረጠ አስተርእዮ (መገለጥ) እና ተከታታይ ትረካ መኖሩን ነው። የያዕቆብ ሚስቶች የነበሩት የልያና የራሔል ልጆች ከአገልጋዮቹ ልጆች በፊት በዕድሜያቸው ቅደም ተከተል ተዘርዝረዋል፤ ዮሴፍ በግብፅ ስለ ነበረ እዚህ ላይ አልተጠቀሰም።

5 በዘፍጥረት 46 ያለው የቤተ ሰብ ዝርዝር ከዚህ በታች ያለውንr ቁጠራ ይሰጠናል፦ የልያ ስድስት ወንዶች ልጆች ሃያ ዐምስት ወንዶች ልጆችና ሁለት የልጅ ልጆች አሏቸው፤ በድምሩ ሠላሳ ሦስት ናቸው። የራሔል ሁለት ወንዶች ልጆች ዐሥራ ሁለት ወንዶች ልጆች ስለ ነበሯቸው በድምሩ ዐሥራ አራት ናቸው። የባላ ሁለት ወንዶች ልጆች ዐምስት ወንዶች ልጆች ስለ ነበሯቸው በድምሩ ሰባት ናቸው። የዘለፋ ሁለት ወንዶች ልጆች ዐሥራ አንድ ወንዶችና አንዲት ሴት ልጅ (ምናልባት ሳትቁጠር አይቀርም) እና ሁለት የልጅ ልጆች ስለ ነበሩ በድምሩ ዐሥራ ስድስት ናቸው። ስለዚህ ሠላሳ ሦስት ሲደመር ዐሥራ አራት ሲደመር ሰባት ሲደመር ዐሥራ ስድስት በጠቅላላው "ሰባ" ይሆናሉ። ዘፍ 46፥26-27 የሚጀምርበት ቍጥር ስድሳ ስድስት ሲሆን (ምናልባት ኤርና ኦናን በከነዓን ስለ ሞቱ ሳይዘላቸው አልቀረም፤ ዮሴፍንና ሁለቱን ልጆቹንም እንዲሁ በግብፅ ስለ ነበሩ ዐልፏቸዋል፤ ዲና ግን መተው የሰባትም በሚል ተጨምራለች።) በዚህ ጠቅላላ ቍጥር ስድሳ ስድስት ላይ ዮሴፍን ሁለት ልጆቹንና ያቆብን ራሱን ጨምሮ ጠቅላላው ድምር ሰባ ሆኗል።

6-7 የእግዚአብሔር የመብዛትና የመባዛት ቡራኬ ተስፋ ለአዳም (ዘፍ 1፥28)፣ ለኖኅ (ዘፍ 8፥17፤ 9፥1፡7)፣ ለአብርሃም (ዘፍ 17፥2-6፤ 22፥17)፣ ለይስሐቅና (ዘፍ 26፥4) ለያዕቆብ (ዘፍ 28፥3፡14፤ 35፥11፤ 48፥4) እንደ ተሰጣቸውና እግዚአብሔር ይህን ዕቅዱን እስራኤል በግብፅ በኖረችባቸው 430 ዓመታት ውስጥ እንደ ፈጸመው ሙሴ መዝግቦልናል።

2. የመጀመሪያው የጥፋት ዘመቻ (1፥8-14)

8 ዮሴፍ ለግብፅ ያደረገውን ያላወቀው "ዐዲስ ንጉሥ" ማን እንደ ነበረ የተለያየ ግምት ተሰጥቷል። በጣም ተአማኒ የሚመስለው የሂክሶስ ንጉሥ እንደ ነበረ የሚናገረው ነው። ሂክሶሶች ግብፁያንን ወደ ደቡብ ያባረሩ የግብፅን ጥንታዊ ጽሑፍ (ሄሮግሊፊክ) ያልተጠቀሙ የውጭ ወራሪዎች እንደ ነበሩ ይታወቃል፤ እነርሱም ቢሆን ሴማውያን ነበሩ።

9-10 እስራኤል ለመጀመሪያ ጊዜ እዚህ ቦታ "ሕዝብ" ተብላ ተጠርታለች። ሁኔታው ከፍተኛ ሚዛናዊ ጥንቃቄ የሚያስፈልግበት ጊዜ ነበር፤ ፈርዖን የእስራኤላውያን በግዛቱ መኖር የሚያስገኘውን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ሳያጣ፣ የግብፅን ብሔራዊ ደኅንነትም አደጋ ላይ ሳይጥል ለማቈየት መጣር ነበረበት።

11 "ጌቶች" የሚለው ቃል ለዕብራውያኑም ለግብፃውያኑም የተለመደ ቃል ነበረ። ይኸው የግብፅ የማዕረግ ስም ሣልሳዊ ቱትሞስ በሚገዛበት ዘመን የጡብ ሠሪዎች አለቃ በነበረው በሬክማየር የቴብስ መቃብር ገነኛ የግድግዳ ሥዕሎች ላይ ይገኛል። ሥዕሉ እነዚህ አለቆች ከባድ ጅራፎች ይዘው ያሳያል። የአለቆቹ ደረጃ የሚታወቀው በእጃቸው በያዙት ረዥም ዘንግ እና በግብፅ ሄይሮግሊፊክ አጻጻፍ የቀጭኔ ራስና ዐንገት በሚወክሉት የማዕረግ ደረጃ ነው። የእስራኤል ልጆች የነነሏቸው ሁለቱ የጎተራ ከተሞች የእህልና ምናልባትም የጦር መሣሪያ ማከማቻ ሳይሆኑ አልቀሩም። "ፊቶም" የተባለው ቦታ ምናልባት ቴሉር ሬታቤህ ይህም አንዳንዶች እንደሚያስቡት ሄሊዮፖሊስ የሚባለው ስፍራ ሳይሆን አይቀርም። ራምሴ ደግሞ አሁን በቅርቡ እንደ ተገመተው ቃንቲር ("ድልድይ") የሚባለው ስፍራ ወይም አካባቢው ሳይሆን አይቀርም።

12-14 "ቍጥራቸው እንዳይጨምር" (ቍ 10) የሚለው የፈርዖን ሥጋት ቍ 12 ላይ ያለውን ስናስተውል የሞኝ አሳብ ሆኖ እናገኘዋለን። ውጤቱ በግብፁያኑ ላይ ታላቅ ፍርሀት መንገሡ ነው። ምፀታዊ በሆነ አካሄድ እግዚአብሔር ለሁለቱም ሕዝቦች ደኅንነት ያቀደው መንገድ በሰው ልብ ጥንካሬ ምክንያት ወገብ የሚፈታ ፍርሀት ምክንያት ሆነ (ዘፍ 12፥3 ይመልከቱ)። ግብፁያኑ የእስራኤልን ልጆች ሕይወት አስመረሩ፤ ይህም በፋሲካው በዓል በሚበላው "መራራ ቅጠል" (12፥8) ይታወሳል። ከቍ 8-14 ያለው ክፍል አጽንዖት በእስራኤል ላይ በተደረገው ከባድ ቀንበርና የሥራ ጫና ላይ ነው።

3. ሁለተኛው የጥፋት ዘመቻ (1፥15-22)

15-16 ሁለቱ አዋላጆች ምናልባት የአዋላጆቹ ሁሉ ወኪሎች ወይም የሙያው ተቈጣጣሪዎች ሊሆኑ ይችላሉ። ማማጫ (ማዋለጃ) ድንጋዮቹ ሁለት መንታ ድንጋዮች ናቸው።

17-21 አዋላጆቹ የግብፅን ንጉሥ ከሚፈሩት ይልቅ እግዚአብሔርን ይፈሩ ነበር። እነዚህ አዋላጆች ግብፁያኑ ከነበሩ ፈሪሀ እግዚአብሔር ማሳየታቸው ለሁሉ የተሰጠውን የእግዚአብሔርን ጸጋ ያመለክታል። አባቶቻቸው ተረድተውት የነበረው ቀደም ብሎ የተሰጠው የእግዚአብሔር መገለጥ ጭላንጭል እያደር እየደበዘዘ የሄደ ይመስላል (ከዘፍ 20፥11፤ ከዘዳ 25፥18፤ ከሚል 3፥5 ጋር ያነጻ)። አዋላጆቹ እግዚአብሔር እንደሚጠብቅባቸው ሁሉ ለሕይወት አክብሮት ነበራቸው። ምንም እንኳ ፈርዖንን ቢዋሹትም የለጋ ሕፃናትን ሕይወት ላለመቅጠፍ ያሳዩት ግልጽ እምቢታ አስመስግኗቸዋል። ሕይወትን ማክበራቸው እግዚአብሔርን የማክበራቸው ነጸብራቅ ነው። ስለዚህ እግዚአብሔር "ቤተ ሰብ" ሰጣቸው። ምናልባትም የፈርዖንን ጥያቄ ቀጥታ ከመመለስ ይልቅ እነዚህ አዋላጆች ዝርዝሩን ሁሉ መግለጡን ትተው የሆነውን እውነት ባጭሩ አስረድተው ይሆናል።

22 የመደምደሚያው መሸጋገሪያ ጥቅስ ምዕራፍ አንድን ባጭሩ ይሰበስብልናል። ፈርዖን በንግግር ብቻ ጉዳዩን ማስፈጸም ስላልሆነለት በግልጽ በዐዋጅ መደንገግ አስፈለገው። የእርሱ ሕዝብ የሆኑቱ ሁሉ የዕብራውያንን ልጆች ለማብዛት የሚደረገውን መለኮታዊ ሥራ በመቃወም የወንጀሉ አስፈጻሚዎች እንዲሆኑ ተደረገ። (በክርስቶስ ልደት ጊዜ ሄሮድስ ካደረገው ጋር ያነጻ) በዚህ ዐይነት ሦስተኛው የጥፋት ዘመቻ ተጀመረ።

ለ. የጉድግና ዝግጅት (2፥1-4፥26)

1. መሪ ሲዘጋጅ (2፥1-10)

1-4 የሙሴ ወላጆች ከሌዊ ወገን የሆኑ ስማቸው ያልተገለጸ ባልና ሚስት ነበሩ። ወንድሙ አሮን በሦስት ዓመት ስለሚበልጠው፤ እኅቱ ማርያም ደግሞ ወጣት ልጃገረድ ስለ ነበረች ሙሴ በኵር ልጅ እንዳልነበር ግልጽ ነው። "መልከ መልካም" ወይም "ያማረ" የሚለው ቃል የልጁን ቁመና (ከዘፍ

39፥6 ጋር ያነጻ) ወይም የልቡን ጥሩነት የሚያሳይ ቃል ሊሆን ይችላል። የሙሴ እናት ከዚያ በላይ ልትሸሽገው ባልቻለች ጊዜ ውሃ የማይገባው ቅርጫት መሰል ከሸምበቆ የተሠራ ታንኳ አበጀችለት። የሙሴ እናት ያደረገችው የሆነው ይሁን ተብሎ ለአደጋ እንዲጋለጥ የወለዱትን መጣል አልነበረም። ድርጊቷ ውስጥ ፍቅርና ተስፋ ነበሩበት።

5 የዕብራይስጡ ንባብ ንግሥታዊው አጅብ ወደ ወንዙ ውስጥ ገባ አይልም (ንዕማን እንዳደረገው 2ነገ 5፥14)። ይልቁን በወንዙ ዳርቻ ነበሩ እንጂ (በአማርኛው "በወንዙ ዳር ወዲያና ወዲህ ይሉ ነበር" ይላል) ለንጉሣዊው ቤተ ሰብ ወንዝ ውስጥ መታጠብ ያን ጊዜ የተለመደ ነገር ነው። ጥንታውያን ታሪክ ጸሓፊዎች እንደሚነግሩን የአባይ ውኃ እንደ ቅዱስ ተደርጎ ይቁጠር ስለ ነበር፣ ሰዎች ሊታጠቡ ሳይሆን ለጤንነትና ዘር ለማግኘት እንደ ጠበል ይጠመቁበት ነበር።

6-9 ልዕልቷ የደንገሉን ቅርጫት አይታ ስትከፍተው አንድ የሚያምር ዕብራዊ ሕፃን ሲያለቅስ አገኘች። ልቧ ወዲያውኑ በርኅራኄ ተሞላ። ሚሪያም ከተደበቀችበት ብቅ ስትል ዐላፊ አግዳሚ ለመምሰል ሳትሞክር አልቀረችም። ምናልባት እናቱ በጥንቃቄ መክራት ካልሆነ ልቧን ወደ ትክክለኛ ተግባርና ንግግር የቀሰቀሰው እግዚአብሔር ራሱ ነው። ልክ በጊዜው እና የሚያስፈልገውን ያህል ብቻ የተደረገው ቃለ ምልልስ አስገራሚ ነው! ልጁ ወደ ወላጅ እናቱ መመለሱ ብቻ ሳይሆን ሁለተኛ ላንገናኝ እንችላለን የተባለለትን ሕፃን ደሞዝ እየተከፈላት እንድታሳድግ መደረጉን ልብ እንበል። በዚህ ዐይነት የሙሴ አባትና እናት ልጁን የአባቶቹን አምላክ እንዲያውቅ ለማስተማር ዕድል አገኙ።

10 ዕብራዊው ብላቴና "እያደገ ሲመጣ" በማደጎነት ወደ ተቀበለችውና ሙሴ ብላ ስም ወዳወጣችለት ወደ ፈርዖን ልጅ ተወሰደ። ስሙ የግብጾች እንደ ሆነ ይታሰብ እንጂ ዕብሮት ያለው "ከውሃ ውስጥ አግኝቼዋለሁ" የሚለው ሐረግ ዕብራዊ አመጣጡን ያሳያል። የሆነው ሆኖ ስሙን ያወጣችው ግብፃዊት ልዕልት መሆኗና ጣምስ፣ ቱትሞስ፣ አሞስና ራምስ የመሳሰሉ ግብፃውያን ስሞች ስላሉ አሁን በሁሉም ዘንድ የሙሴ ስም ግብፃዊ እንደ ሆነ ይቁጠራል። "ከውሃ ማውጣት" የሚለው የዕብራይስጡ ሥርወ ቃል መጠቀሱ ምናልባት ከግብፃዊው ስም ጋር የድምፅ መመሳሰል ስላለው ይሆናል።



እነዚህ በጥንት ጊዜ በግብፅ የሸንበቆ ወረቀት የሚሠራባቸው ዛፎች ሲሆኑ ሕፃኑን ሙሴን በውሃ ላይ ለመጣል ቅርጫት መሰል ጀልባ የተሠራው በነዚህ ዛፎች ነው።

2. የዝግጅቱን ጊዜ ማራዘም (2፥11-22)

11-12 ቄይቶ ሙሴ ዕብራዊ እንደ ሆነ መረዳቱ አልቀረም። አርባ ዓመት ሲሞላው (ሐሥ 7፥23፤ ከዕብ 11፥24-25 ጋር ያነጻ) ዕብራዊ ወገኑን አንድ ግብፃዊ ሲመታ አይቶ ሙሴ ግብፃዊውን ይገድላል። ብንወቅሠው በትዕግሥት ማጣቱ እንጂ ስለ ፍትሕና ስለ ጭቁኖች በመቆርቆሩ ሊሆን አይችልም። ይህ ድርጊቱ እስራኤልን ለመታደግ ለተሰጠው ኀላፊነት የሚያበቃ እንዲሆን የሌላ የአርባ ዓመት ትምህርት ቤት ውስጥ አስገባው። ሙሴ ድርጊቱ ሕጋዊ እንዳልሆነ ልቦናው ነግሮታል፤ ቀኝና ግራ መገላመጡ፣ የገደለውን ሰው አሸዋ ውስጥ መቅበሩ የሚያመለክተን ይህንኑ ነው። ከሕጋዊ ሂደት ውጪ ክፉ ሥራን ለመቅጣት ሙሴ የተነሣሣበት ግፊት በኋላ የእግዚአብሔርን ሥራ ለመሥራት ጥቅም ላይ ውሏል።

13-14 ይህ የጭቁኖችና የተጠቁ ሰዎች ታዳጊ በማግስቱም ከራሱ ወገን በሆኑ ሁለት ሰዎች መካከል የተፈጠረ ግጭትን ለማብረድ ሞከረ። ነገር ግን ሙሴ ተቀባይነት አላገኘም፣ እንዲያውም መነሻ ዐላማውን እንኳ ሰዎቹ መጠራጠራቸውን ግልጽ አደረጉ። እንደ መልካም ጎረቤቶች እንዲተዛዘኑ የጠበቃቸው ሰዎች ይብሱን በእሱ ላይ አፈጠጡ። እንዲያውም አንደኛው ትናንት ያደረገውን እንዳወቀበት ሲናገር ባንድ ወገን ነፍስ ገዳይ፣ በሌላ በኩል ደግሞ በሰው ጉዳይ ጣልቃ ገቢ ሆኖ ታየ! ሙሴ ይህን ሲሰማ ጉዳዩ ሁሉ ይፋ እንደ ሆነ ገባውና ጊዜ ሳያባክን ግብፅን ለቆ መጥፋት እንዳለበት ወሰነ።

15-19 የፈርዖን ቊጣ የነደደው የአንድን ግብፃዊ ነፍስ መገደል ለመበቀል ሳይሆን ሙሴ የቀንደኛ ጠላቶቹ የጭቊን እስራኤላውያን ጓደኛና ነጻ አውጪ ሆኖ መንቀሳቀሱን በመረዳቱ ነው። ስለዚህ ሙሴ በአቃባ ባሕረ ሰላጤ አጠገብ በሚገኘው የዐረብ ልሳነ ምድር ውስጥ ወዳለው ወደ ምድያም ኰበለለ። እዚያም ሲደርስ ሌላ ኢፍትሓዊነት አጋጠመው። ራጉኤል የሚባል የአንድ ምድያማዊ ካህን ሰባት ሴቶች ልጆች መንጋቸውን ውኃ እንዳያጠጡ ጋጠወጥ የሆኑ እረኞች ሲያስጨንቋቸውና ሲያባርሯቸው ተመለከተ። ሙሴ እነዚህን ልጆች ከባለጌዎቹ ተከላከለላቸው። ሙሴ እስከዚያን ጊዜ የለበሰው የግብፅ ልብሱን በመሆኑ ግብፃዊ መሰላቸው።

20-22 በሴቶቹ ልጆች አባት ቤት እንግድነት መቀመጡ የኋላ ኋላ ሙሴ የራጉኤልን ልጅ ሲፓራን (የስሙ ትርጉም "ወፍ" ማለት ነው "ርግበ" እንደ ማለት) እንዲያገባ ምክንያት ሆኗል። ሚስቱ ሲፓራ ወንድ ልጅ ስትወልድለት የብቸኝነት ስሜቱን የሚያጋልጥ ስም አወጣለት። ጌርሳም የሚለው ስም "በባዕድ ምድር መጻተኛ ነኝ" የሚል ትርጉም አለው።

3. ሕዝቡን ለትድግና ማዘጋጀት (2፥23-25)

23 "ሞተ" የተባለው የግብፅ ንጉሥ ምናልባት ሙሴ ግብፃዊውን በመግደሉ ምክንያት ሕይወቱን ሊያጠፋ ፈልጎት የነበረው ሳይሆን አይቀርም (2፥15፤ 4፥19)። በ18ኛውና በ19ኛው ሥርወ መንግሥታት ውስጥ ከሠላሳ ዓመት ለሚበልጥ ጊዜ የገዙት ፈርዖኖች ሣልሳዊ ቱትሞስ (1483-1450 ዓቅክ) ሣልሳዊ አሜኖቴፕ (1410-1372 ዓቅክ) ሃሬምሃብ (1349-1315) እና ዳግማዊ ራምሴ (1301-1234 ዓቅክ) ናቸው። ሣልሳዊ ቱትሞስ በጭቁናው ዘመን የነበረው ፈርዖን ሳይሆን አይቀርም። ይህ ሰው ሥልጣኑን የጨበጠው አክስት የእንጀራ እናቱና ዐማቱ ከሆነችው ሴት ሞት በኋላ ነው።

ሥቃይ በመጨረሻው ድምፅ አገኘ። እስራኤላውያን በአካላቸው የተሠቃዩት *ሥጋዊ* ሕመም ስሜት የመንፈሳዊ ሁኔታቸውን ድክነት ከመረዳታቸው ይቀድማል። በዚህ ዐይነት እግዚአብሔር ታዳጊውን ሰው እያዘጋጀ ወዲያውም ደግሞ የሚታደጋቸውን ሕዝብ ያሰናዳ ነበር። ግብፅ ከዚህ በኋላ የጣፋጭ ምግብ፣ የብልጽግናና የሥብ ምሳሌ መሆኗ ቀረ። ይልቁን አሁን ግብፅ ማለት የባሪያ አሳዳሪዎች፣ የግዳጅ ሥራና የባርነት ምልክት ሆነች። ስለዚህ እስራኤል ወደ እግዚአብሔር ጮኸች።

24-25 እስራኤል እየተንተባተበች ለምታሰማው ለዚህ የመጀመሪያ የእምነት ጭላንጭል ምላሽ ለመስጠት እግዚአብሔር ወሷል። ይህ ብቻ ሳይሆን ለአባታቸው ለአብርሃም፣ ለይስሐቅና ለያዕቆብ የገባላቸውን የራሱ የተስፋ ቃልም ሊረዳቸው አነሣሣው (ዘፍ 17፥7፡ 19፤ 35፥11-12 ወዘተ)። በአእምሮው ማስታወስ (ማሰብ) ብቻ ሳይሆን ቃሉን በሥራ የሚተረጉም ውሳኔ ነው (ከዘፍ 8፥1 ከ1ሳሙ 1፥19 ጋር ያነጻ)። መለኮታዊው ተግባር በአራት ተከታታይ ግሶች ተገልጾአል። እግዚአብሔር ሰማ፤ እግዚአብሔር አሰበ፤ እግዚአብሔር ተመለከተ እና እግዚአብሔር ዐወቀ (ይህም ገደደው ማለት ነው)።

4. ታዳጊው ሲጠራ (3፥1-10)

ሙሴ በተግባሩ ላይ ተግቶ ሳለ እግዚአብሔር ለሌላ ተግባር ጠራው። ያሁኑ ጥሪው ከዚህ ቀድሞ ከአርባ ዓመት በፊት ሙሴ በራሱ ብቃት አለኝ ብሎ አስቦት የነበረው ነው፤ ያኔ በግብፅ ያስተዋለውን ግፍ ለመቃወም ርምጃ ወስዶ ነበር።

የኤር-ራሃ ሽለቆ በተለምዶ "የእግዜር ተራራ" ተብሎ በሚታወቁት ሦስት የኰረብታ አናቶች መካከል የሚገኝ ስፍራ ነው (የእግዚአብሔር ተራራ የሚለው ስያሜ እግዚአብሔር በዚህ ከተገለጠ በኋላ የወጣለት ስም ነው)። እዚህ ስፍራ ላይ እግዚአብሔር "በእሳት ነበልባል ቅርጽ" ተገለጠ። ነገሩ ለሙሴ እንግዳ ነው፤ አስገራሚም ነው። እሳቱ ቢነድም ቁጥቋጦው አልተቃጠለም፤ ተአምሩም ይኸው ነበረ።

እግዚአብሔር ራሱን ለመግለጽ የተጠቀመው የተናቀውን የሚነድ ቁጥቋጦ ሲሆን ሙሴን ለትልቅ ኀላፊነት ከማሰማራቱ በፊት ለሕይወት ጥቃቅን ጉዳዮች ያለውን ንቁ ስሜት ለማየት ታገሠ። እሳቱ የሚወክለው ኃያሉን የእግዚአብሔርን አውዳሚ ደግሞም ጠባቂ ሀልዎት ነው (ከ19፥18፤ 24፥17፤ ወዘተ ጋር ያነጻ)። ሙሴ ይህን እንግዳ ትዕይንት ለማጤን ሲጠጋ እግዚአብሔር የመልእክቱን አጣዳፊነት በሚያሳይ አጽንዖት የሙሴን ስም በመደጋገም ጥሪውን አቀረበለት (ከ1ሳሙ 3፥10 ጋር ያነጻ)።

5-6 የእግዚአብሔር ሀልዎት ወደፊቱ ለመቅረብ የሚፈልገውን ሁሉ በሁለንተናው ዝግጁ እንዲሆን የሚጠይቅ ሀልዎት (መገኘት) ነው። ስለዚህ ለሙሴ ይህን ትምህርት ለማስተማር እግዚአብሔር ሆነ ብሎ ድንበር ማበጀቱ እውነት ነው። "ወደዚህ አትቅረብ" ይለዋል። በተጨማሪም ጫማውን እንዲያወልቅ ያዝዘዋል። ይህን ያደረገው ያለ ጥንቃቄ ወደ እግዚአብሔር ሀልዎት ዘው ብሎ እንዳይገባ ለመከልከል ሲሆን እግዚአብሔር አምላክ ከሰዎች የተለየ መሆኑን ለማስተማርም ነው (ከ19፥10-13፤ ከ2ጴጥ 1፥18 ጋር ያነጻ) ። እግዚአብሔር ስለ ተገኘበት፣ ተራ የነበረው "ቅዱስ ስፍራ" ሆነ ስለዚህም ለተለየ ተግባር ተቀደሰ/ተወሰነ። ከጥቂት ጊዜ በፊት የበጎችና የፍየሎች መዋያ የነበረው ቦታ በእግዚአብሔር መገኘት (ሀልዎት) ቅዱስ መሬት ሆነ። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ "ቅዱስ" የሚለው ቃል ጥቅም ላይ የዋለው እዚህ ቦታ ነው (ከዘፍ 2፥3 ላይ ከሚገኘው ከግሱ ዘር ጋር ያነጻ)።

እግዚአብሔርን ለመገናኘት ብቁ የሚያደርገው ሥርዐት ከተሟላ በኋላ "እኔ የአባትህ አምላክ ነኝ" ብሎ እግዚአብሔር ራሱን ገለጸ። "አባት" የሚለው ነጠላ ጥቅል ስም ትርጉም ያለው ነው። ምክንያቱም ብዙዎች የእግዚአብሔርን በረከት ያገኙት የተስፋው ባለቤት በሆነ በዚያ አንድ ሰው በኩል ነው። ለዚህ ነው የአባቱ አምላክ እግዚአብሔር ለሙሴ ሲናገር የተደጋገመ የተስፋ ቃሉንም (ዘፍ 15፥1-21፤ 26፥2-5፤ 35፥1-12) ሆነ ሕዝቡን ያልጣላቸው መሆኑን ማረጋገጥ የፈለገው።

7-10 "አየ"፣ "ሰማ"፣ "ዐወቀ" (ግድ ተሰኘ) እና "ወረደ" የሚሉት ስለ እግዚአብሔር የተነገሩት ቃላት በሰው ዓለም ውስጥ ካለው እውነታ ጋር በከፊልም ቢሆን የሚመሳሰለውን የእግዚአብሔርን ሥራ በምሳሌ ለመግለጽ የቀረቡ ናቸው። የመለኮትን ተግባር በሰው ሁኔታ የሚናገር ዘይቤያዊ አገላለጽ ነው። ነገር ግን እነዚህ ቃላት እግዚአብሔር ወሰን ያለው ወይም የተገደበ ነው አያሰኙም። ይልቁን እርሱ ሕያው የሆነ ማንነት ያለው፣ የሰውንም ሁኔታ ሊያስተውል የሚችልና የሚያውቅ እንዲሁም በሰው ልጅ ጉዳይ ውስጥ ሊገባ የሚችልና የሚገባም መሆኑን ያመለክታሉ።

ቁ 8 ሦስት ጊዜ "ምድር" የሚለውን ቃል ይጠቅሳል። ለአባቶች በተደጋጋሚ ሲነገራቸው የቈየው ተስፋ ከ500 ዓመታት በኋላ ሊፈጸም ተቃርቧል። ስለ ምድሩ ሁለት ሐቆች ተነግረዋል፤ ምድሩ ለም ነው፤ ደግሞም ሰፊ ነው (ከዘዳ 8፥7-9 ጋር ያነጻ)። ለምነቱ "ማርና ወተት የሚያፈስ" ምድር ስለ ሆነ ሲሆን፣ ስፋቱ ደግሞ ስድስት ሕዝብ (ነገዶች) ይኖሩበት የነበረ ቦታ ስለ ሆነ ነው። እስራኤልም ሁሉን ልትወርስ ነው።

የሙሴ መጠራት በሁለት መግለጫዎች ወደ መደምደሚያው የደረሰው በቁ 9-10 ላይ በተገለጹት "አሁንም . . . በል እንግዲህ" በሚለው ሐረግ ነው። ቁ 9 በመሠረቱ ቁ 7ን ይደግማል። ቀደም ብሎ የተነገረውን በማጠቃለል እስራኤል አሁን ያለችበትን አሳሳቢ ሁኔታና የእግዚአብሔርን መፍትሔ ለጥሪው ዋና መነሻ አድርጎ ይደመድማል። ነገር ግን የቁጥቋጦው እሳት ተአምር ዋናው ምክንያት (ጉዳይ) ቁ 10 ላይ ይገኛል። ይኸውም ሙሴ የእግዚአብሔር መልእክተኛ ሆኖ እስራኤልን ከግብፅ እንዲያወጣ የቀረበለት ጥሪ፣ ሹመት ወይም ትእዛዝ ነው።

5. አጥጋቢ ላልሆኑ ምክንያቶች ምላሽ መስጠት (3፥11-4፥17)

ሀ. ወደ ፈርዖን የምሄድ እኔ ማነኝ? (3፥11-12)

እግዚአብሔር እየሰጠው ያለውን ኀላፊነት ላለመቀበል ካቀረባቸው ዐምስት ምክንያቶች/ መቃወሚያዎች መካከል ይህ የመጀመሪያው ተቃውሞው ሙሴ ባሳለፋቸው አርባ ዓመታት ውስጥ ከነበረው ጭምት አስተውሎትና እድገት የተነሣ በባሕርዩ ላይ የመጣውን ታላቅ ለውጥ ያሳያል። ራሱ በራሱ የሕዝብ ታዳጊ ሆኖ ለመቅረብ ትንሽ ይበቃው የነበረው ሰው አሁን ስለ ራሱ ርግጠኝነት የሌለው፣ "አለሁ አለሁ" የማይል መለኮታዊውን ኀላፊነት ለመቀበል ብቃት የማይሰማው ፈሪ ሰው ሆነ።

11 በቁ 10 ላይ የሚገኘውን ወደ ፈርዖን የመሄድና እስራኤልን ከግብፅ የማውጣት መንታ ኀላፊነት በንግግሩ ውስጥ ይደግመዋል። ይህን ንግግሩን በቅርብ ምሥራቅ ውስጥ በተለመደ ፈሊጣዊ አነጋገር "እኔ ማነኝ?" ብሎ ሲጀምር የተልእኮውንና የመልእክተኛውን ዐቅም አለመመጣጠን ማጕላቱ ነው (ከ6፥12፤ ከ1ሳሙ 18፥18፤ ወዘተ ጋር ያነጻ)።

12 እግዚአብሔር ለሙሴ የሰጠው ምላሽ ድርብ ነበር፡- ከእርሱ ጋር ዐብሮ እንደሚሆንና ምልክትን እንደሚሰጠው የሚገልጽ። እግዚአብሔር ርኅሳን አበው ለሆኑት ለአብርሃም፣ ለይስሐቅና ለያዕቆብ 14 ጊዜ "ከአንተ ጋር እሆናለሁ" ብሎ ቃል እንደ ገባ ሁሉ አሁን ደግሞ ለሙሴ የበረከት ተስፋውን ሊፈጽም በተግባር ዐብሮት እንደሚሆን ያረጋግጥለታል።

የተሰጠው "ምልክት" ለሙሴ ነገሩን ለማጽናት እምነትን ለማዳበር የቀረበ እንጂ ወዲያው እጅ በእጅ የሚታይ የተኣምር ማስረጃ እንዳለ ለማሳየት አልነበረም። ለጌዴዎን እንደ ተሰጠው ዐይነት (መሳ 6፥17) አልነበረም። ምክንያቱም ጌዴዎን ምልክት የተሰጠው ራሱ ጠይቆ ሲሆን ሙሴ ግን አልጠየቀም። ለሙሴ የተሰጠው ተኣምር ወደፊት የሚሆኑ ከሚባሉ ተኣምራት ተርታ ሊመደብ ይችላል (1ሳሙ 2፥34፤ 10፥2፡3፡5፤ 2ነገ19፥29፤ ወዘተ)። እግዚአብሔር ምልክቶችን እንደ

ማረጋገጫ ለሕዝቡ ቢሰጥም (ዘፀ 4፥1-9)፣ ለሙሴ ለራሱ ግን እንደዚህ ዐይነት ምልክት አለመስጠቱ ይገርማል። ይልቁን ሙሴ እግዚአብሔር በተናገረው ቃልና ዐብሮት እንደሚሆን በሰጠው ተስፋ (ከማቴ 28፥20 ጋር ያነጻ) እንዲታመን ጠየቀው። በዚህ ምልክት ውስጥ ሙሴ እስራኤልን ከግብፅ ባርነት የማውጣት ተልእኮ ብቻ ሳይሆን፣ እስራኤል እግዚአብሔርን "ለማምለክ" ነጻ ልትሆን እንደሚያስፈልጋት የሚጠቁም ፍንጭ አለበት።

ለ. ሰምህን ቢጠይቁኝስ? (3፥13-22)

13 ሙሴ "ይህ አምላክ መጠሪያ ስሙ ማነው?" ይሉኛል ብሎ ያሰበ አይመስልም። ይልቁን የአባቶቻቸው አምላክ ወደ እነርሱ እንደ ላከው ቢናገር፣ ሕዝቡ በጠንካራ አንደበት "ለመሆኑ እሱ ማነው?" ይሉኛል የሚል ፍርሀት ነው በልቡ የነበረው። የዕብራይስጡ አሳብ የስሙን ዋጋ፣ ባሕርይ ደረጃና ትርጓሜ ሁሉ የሚጠይቅ አነጋገር ነው። ስለዚህ ለማወቅ ያስፈለጋቸው "አሁን ባለንበት ሁኔታ ስሙ ምን ፋይዳና ፍቺ አለው?" የሚል ነበር።

14-15 ሙሴ ላቀረበው ችግር እግዚአብሔር ሁለት መልሶች ሰጠ። ሁለተኛው መልሱ የጌታን ስም ትርጉም በማብራራት ላይ ተመሥርቶ ስሙን ከቀደሙትና ወደፊት ከሚመጡት ትውልዶች ሁሉ ጋር ያያይዘዋል።

"እኔ ነኝ" ወይም "ያለና የሚኖር" የሚለው ሐረግ ተገቢ ትርጉም ምናልባት ከ"መሆን ግስ" ጋር የተያያዘ ነው የሚለው አስተያየት ከሁሉ የተሻለ መግለጫ ነው ማለት ይቻላል። ከዚሁ ጋር ይህ ስም በቁ. 12 ላይ የተሰጠውን "ከአንተ ጋር እሆናለሁ" የሚለውን ተስፋ ባሕርይና ምንነት የሚገልጽ ስም ነው። እንግዲያው ስሙ ምንድን ነው? መልሱ "ስሜ (ውስጣዊ ፍቺው ወይም ዋጋው) እኔ እኔ ነኝ፣ ያለሁ የምገኝ ነኝ።" የሚል ነው። በሌላ ባህል ለምንገኝ አንባቢዎች ይህ አባባል እግዚአብሔር ሆነ ብሎ ስሙን ለመደበቅ የሚፈልግ መስሎ እንዲታይ የሚያደርግ ቢመስለንም፣ ዐውደ ምንባቡ ግን የሚያመለክተን ተቃራኒውን ነው። እንዲህ ዐይነቱ የቋንቋ አወቃቀር ብዙውን ጊዜ ጥቅም ላይ የሚውለው ሁለንተናን፣ ብርቱ የሆነ አገላለጽን ወይም አጽንዖትን ለማሳየት ነው። ስለዚህ አነጋገሩ "እኔ በእውነት የምኖረውና በምልክህ ሁኔታ ውስጥ እዚያውና ያኔ በሕያውነት የምገኘው ነኝ" የሚል ፍቺ ይሰጣል።

ይህ አምላክ ለእስራኤል ዐዲስ አምላክ አልነበረም፤ ሙሴን እየላከው ያለው ያው የአብርሃም፣ የይስሐቅና የያዕቆብ አምላክ ነበር። ስሙ ያህዌ ነው። እግዚአብሔር ለመጀመሪያ ጊዜ እዚህ ቦታ ባለ አራት ተነባቢ ድምፆች "የሐወሐ" የሚታወቀውን ስም በሦስተኛ መደብ የመሆን ግስ ሲጠቀምበት እናያለን። ይህ ለዘላለሙ ስሙ ነው። ስሙ ማንነቱ፣ ባሕርዩ፣ ሥልጣኑ፣ ኀይሉና ዝናው ነው። የእግዚአብሔር ማንነትና ስሙ እርስ በእርስ ከመያያዛቸው የተነሣ አንዱ አንዱን እየተካ ሲነገር ይታያል (ለምሳሌ፣ ዘዳ 28፥58፤ መዝ 18፥49) ። ይህ ስሙ "መታሰቢያ" እንዲሆንም ተፈልጓል። በትውልዶች ሁሉ ዘንድ የእግዚአብሔርን ብርቱ ሥራዎች መናገሪያ፣ መዘከሪያም ነው።

16-18ሀ "የእስራኤል ሽማግሌዎች" የየቤተ ሰቡ አለቆች (6፥14 - 15፡25፤ 12፥21፤ ዘኁ 2) ወይም የጎሣ አለቆች ነበሩ። ሙሴ የእግዚአብሔርን መልእክት ለእነዚህ ሰዎች እየነገረ ወደ ፈርዖን ሲገባም እንዲከተሉት ያደርግ ነበር። መልእክቱ የሚመጣው የአባቶቻቸው አምላክ ከሆነው ከዚያው ከእግዚአብሔር ነበረ። ሲጀምርም ዮሴፍ በሞት ዐልጋው ላይ ሆኖ መጨረሻ የተናገረውን ቃል በመድገም ነበረ ይህም "እኔ በርግጥ ጐብኝቻችኋለሁ" በሌላ ትርጉም "እኔ ተመለከትኋችሁ" "በግብፅም ካለባችሁ መከራ ላወጣችሁ ቃል ገባሁ" የሚለው ነው። ሙሴ አሁን ያወጀውን የዐርነት ዐዋጅ ዮሴፍ ቀደም ሲል ተንብዮት ነበረ (ዘፍ 50፥24 ይመ)። ስለዚህ የቃሉ መደገም በዮሴፍ በኩል የተነገረው ተስፋ መፈጸሙን፣ እግዚአብሔር የጀመረውን ሥራ ማጠናቀቁንም የሚያመለክት ነው። በእውነቱ እንዲያውም በቁ. 17 ላይ የተጠቀሰው "መከራ" የሚለው ቃል ለአብርሃም በተሰጠው ቀዳሚ ተስፋ (ዘፍ 15፥13) ላይ ግብፃውያን ለአራት መቶ ዓመታት እንደሚያሠቃይዋቸው የተነገረበት ቃል ራሱ ነው። የሰዎች ልብ በእግዚአብሔር እጅ ውስጥ ስለ ሆነ ሙሴ ለሚናገረው መልእክት ቀና የሆነ ጆሮ እንደሚያገኝ ተረጋገጠለት።

18ለ-20 ሙሴና ሽማግሌዎቹ በመጀመሪያ የታዘዙት ለጌታ ለአምላካቸው መሥዋዕት እንዲያቀርቡ ጊዜያዊ ፈቃድ እንዲሰጣቸው ለፈርዖን ቀለል ያለ ጥያቄ እንዲያቀርቡ ነው። ይህ ግማሽ እውነት በመናገር ፈርዖንን ለማጭበርበር የታለመ አካሄድ አልነበረም። እግዚአብሔር ሆነ ብሎ ጥያቄዎቹን በተራ ሊያደርጋቸው ፈለገ። መጀመሪያ ከቀላሉ (የሦስት ቀን መንገድ ሄዶ መመለስ) ወደ ከባዱ (በባርነት የተያዙትን ሕዝብ ሁሉ በነጻ መልቀቅ) ጥያቄ ሲሄድ በርግጥ አስቸጋሪ የሆነ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ውሳኔ ለማድረግ የሚያስችል ዕገዛ እየሰጠው ነበረ። እግዚአብሔር ይህ የግብፅ ንጉሥ ምን ምላሽ እንደሚሰጥ አሳምሮ ያውቅ ነበር። ስለዚህ ሙሴ ምንም ዐይነት አሉታዊ ምላሽ ከፈርዖን ቢገጥመው "እግዚአብሔር ባይልከኝ ነው" ወይም "እርሱ ከእኔ ጋር ባይሆን ነው" ወደሚል አመለካከት እንዳይመራው ማስጠንቀቂያ አግኝቶ ነበር። ይሁን እንጂ ሙሴ እንደዚህ ማሰቡ አልቀረም። ምክንያቱም በኋላ ይህንኑ ጥያቄና ማጉረምረም ሲያቀርብ እናያለን (5፥22-23)።

21-22 እስራኤል በግብፅ አራት መቶ ዓመት ካገለገሉ በኋላ ከብዙ ንብረት ጋር እንደሚወጡ እግዚአብሔር ለአብርሃም ተስፋ ገብቶለት ነበር(ዘፍ 15፥14) ። በዚሁ መሠረት የዘፀአት ቀዳሚ ምዕራፎች ለአባቶች የተሰጠው ተስፋ ደረጃ በደረጃ ሲፈጸም በቅደም ተከተል እያሳዩ ነገሩን ግልጽ ያደርጉታል። ግብፃውያንን መበገዘዝ (ከእነርሱ ንብረት መውሰድ) ከእስራኤላውያን በቀረበ ቀላል ጥያቄና እግዚአብሔርም በላያቸው ካደረገው ሞገስ የተነሣ ሲከናወን ነገሩ ይፈታል (ፍጻሜ ያገኛል)። እስራኤላውያን ራሳቸው በዚሁ ዐይነት መርሕ እንዲኖሩ፣ በየሰባት ዓመቱ ነጻ ለሚለቀቅ ባሪያ ስጦታ በመስጠት እንዲሰዱት በኋላ ተደነገገ ((ዘዳ 15፥13)። የማጭበርበር፣ የማታለልና፣ የወሮበላነት ክስ ሁሉ ከእስራኤላውያን ላይ ተወገደ። የባርነታቸው ውርደት ተቀይሮ ሰብኣዊ ክብራቸው ተመለሰ፤ ልጆቻቸው እንኳ በጌጥና በልብስ ተሸሞነሞኑ።

ሐ. ባያምኑኝስ? (4፥1-9)

1 ሙሴ በ3፥17 ላይ የሚገኘውን እግዚአብሔር የሰጠውን የማረጋገጫ ቃል ፊት ለፊት አልተቃወመም። ዕብራይስጡም፣ በግሪክ ቋንቋ የተተረጎመውም የሰባ ሊቃናት ትርጉም ጥያቄውን መላምታዊ አድርገው ያቀርቡታል። ይሁን እንጂ ሙሴ በእግዚአብሔር ላይ ስለ መታመን አንጸባራቂ ምሳሌ ወይም ሞዴል ሆኖ አይታይም። በዚያው አፍ ደግሞ በግብፅ ስላሉት እስራኤላውያን ወገኖቹ ምላሽ ሙሴ ርግጠኛ ሊሆን አይችልም ነበር። የተነገረው ነገር የሚያስከትለውን ሁኔታ ቀኝና ግራ እያሰላሰለና እየጠየቀ ጊዜ መግዛት ፈልጓል።

2-5 ***የመጀመሪያው ምልክት፤*** የተናገሩት መልእክትም ይሁን ራሳቸው መልእክተኞቹ ከእግዚአብሔር ለመሆናቸው ማስረጃ እንዲሆን የእግዚአብሔር ነቢያት ድንቅና ታምራት ይከተሏቸዋል ነበር (ዘዳ 13፥1-3 ይመ)። በዚሁ መሠረት ሙሴም ምልክት ተሰጠው (በ3፥12 ላይ የተሰጠውን ማብ ይመ) "እግዚአብሔር እንደ ተገለጠልህ ያምኑ ዘንድ" ለማስረጃነት ተሰጠው።

በሙሴ እጅ የነበረችው በትር ምንም ምን የሌላት ማንኛውም ዐይነት በትር ነበረች። እግዚአብሔር ባዘዘው መሠረት ግን ሙሴ ወደ ምድር ሲጥላት እባብ ሆነች። ይህን እባብ ፈርዖን በራሱ ላይ በሚያደርገው ቆብ ላይ ከተቀረጸው እባብ (ኩብራ) ጋር አያይዞ ሙሴ የግብፅን ንጉሥ ጅራቱን ይዞ እንጠለጠለው ማለት እጅግ ሩቅ መሄድና የማይሆን ትርጉም

መፈለግ ይመስላል። ጉዳዩ ልዕለ ተፈጥሮታዊ መሆኑንና ምንጩም መለኮት መሆኑን ለማሳየት ሙሴ የእባቡን ጅራት በእጁ እንዲይዝ ይታዘዛል፣ምክንያቱም እባብ ከተያዘ የሚያዘው ዐንገቱ ስለ ሆነ።

6-7 ***ሁለተኛው ምልክት፣*** በዕብራይስጥ ለምጽ የሚለው ቃል ለበርካታ የተለያዩ የቁዳ በሽታዎች የተሰጠ ስም ነው። በርግጥ ለምጽ ከጥንት ጀምሮ የሚታወቅ በሽታ ነው። ለምጽ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሥጋ ደዌ በሽታን፣ የአንጀት ጥገኛ የሆኑ የተለያዩ የወስፋት ዘሮችን፣ ቂጢኝ፣ "ፈንገስ"፣ እና ልብሶችን፣ ቤቶችንና አንዳንዴም ሰዎችን የሚበክለውን ከእነዚሁ የሚወጣውን ፈሳሽ (መግል) የሚመለከት ነው። በዚህ ቦታ የተጠቀሰው ለምጽ ከላይ ከተጠቀሱት የትኛውን እንደሚመለከት ግልጽ አይደለም። ነገር ግን የቁዳው ሁኔታ የበረዶ መልክ እንደ ነበረው ተገልጸአል። የትኛውም አነስተኛ ወይም መደበኛ የቁዳ መቁጣት እንደ "ምልክት" ሊወሰድ አይችልም። የሙሴ ከመቅጽበት መፈወስ የእግዚአብሔርን ታላቅነት ግርማና ኀይል ለመግለጽ እንደ ሆነ ተደርጎ ይወሰድ ዘንድ የሙሴን ሕይወት አደጋ ላይ ሊጥል የሚችል የጤና ችግር የሚያስከትል መሆን ነበረበት። የዚህ የሰውነትን ጤና የመውሰድና ወዲያው ደግሞ የታመመው አካል ቀድሞ ወደ ነበረበት ሁኔታ የመመለስ፣ "እንደ ሌላው የሰውነቱ ክፍል" የመሆን ፋይዳው ይህ ሙሴን የላከው አምላክ በመረጠው ሰው ቃል ወይም ምልክት ብቻ የፈለገውን በበሽታ ላይ ሊጥል፣ የፈለገውን ሊፈውስ የሚችል ኀይል ያለው መሆኑን በማሳወቅ ፈርዖንን ለማስጠንቀቅ ነው።

8-9 ***ሦስተኛው ምልክት፣*** በመቀጠል እግዚአብሔር በቁ.1 ላይ በሙሴ የተገለጹትን ተመሳሳይ ቃላት በመጠቀም ሌላ ማስጠንቀቂያ ሰጠ። በእያንዳንዱ ክሥተት ሰሚ ያላገኘው በሁለቱ ምልክቶች የተላለፈው መልእክት በቁሙ "ድምፅ/ቃል" ነው። ነገር ግን "ድምፃቸው" እስራኤላውያንን ልክ እንደ ሙሴ ቃላት "ድምፅ" ሁሉ ተጠያቂ ያደርጋቸዋል (ቍ. 1)። እስራኤል ከእግዚአብሔር ጋር በቃሉ "ድምፅና" እና በተአምራቱ "ድምፅ" ፊት ለፊት ትገጥማለች። ይህም ከእያንዳንዱ "ምልክት" ጋር ዐብሮ የሚሄድ ወሳኝ የሆነ ነገር እንደ ተዳበለ ያመለክታል።

በዚህ በሦስተኛው ምልክት ሙሴ እፍኝ ውሃ ከወንዙ ይወስድና፤ (ኋላ ላይ የመጀመሪያው መቅሠፍት በአባይ ወንዝ ላይ ነው የሚከናወነው) ወደ ደም ይቀይረዋል። በንጹሓን ዕብራውያን ደም ተበርዞ የሚፈሰው የአባይ ወንዝ በዚህ ተአምር ያለ ፈቃዱ በርካታ ቍጥር ያላቸውን ሰዎች ነፍስ ለመቅጠፉ ራሱ ምስክር ይሆናል። የዚህ "ምልክት" መልእክት ወይም ትርጉም ሳይገባው የሚቀር ዕብራዊ ወይም ግብፃዊ ይኖር ይሆን? ከምድር ወደ እግዚአብሔር ይጮኽ እንደ ነበረው የአቤል ደም በፈርዖን እንዲገደሉ የተፈረደባቸው ሕፃናት ደምም (1፥22) እንዲሁ ወደ እግዚአብሔር ይጮኻል። የግብፅ ኃያል አምላክ አባይ የአብርሃም፣ የይስሐቅና የያዕቆብ አምላክ በሆነው ጌታ ተጽዕኖ ሥር ወድቋል።

መ. ኮልታፋና ንግግር የማልችል ሰው መሆኔስ? (4፥10-12)

10 ሙሴ አሁንም ሌላ የተቃውሞ ሰበብ ይዞ ቀረበ፡- "አንደበተ ርቱዕ አይደለሁም" (በቁሙ "ነገር ዐዋቂ አይደለሁም")። በመቀጠል የምሥራቅ ሰዎችን ዐይነተኛ የቋንቋ ዘዬ በመጠቀም፡- በቁሙ ሲወሰድ "ከትላንት ጀምሮም ሆነ ከሦስተኛው ቀን ወዲህም" ብሎ አከለበት። ይህም ባጭሩ "ፈጽሞ ከዚህ ቀደም" ማለት ነው። የቍጥቋጦው እሳት ተሞክሮም እንኳ ለዚህ ችግር መፍትሔ አልሰጠም። ሙሴም ችግሩን በጥቅሉ ሲያስቀምጥ፡- "እኔ ኮልታፋና ንግግር የማልችል ሰው ነኝ" አለ። ይህ ማለት ሙሴ ተፈጥሮታዊ የሆነ የመናገር ችግር አለበት ማለት ላይሆን ይችላል (ከሐሥ 7፥22 ጋር ያነጻ)። እናም የሙሴ ተቃውሞ ተፈጥሮታዊ የኮልታፋነት ወይም የሌላ መሰል ችግር አይደለም፤ ነገር ግን ከወንድሞቹም ሆነ ከፈርዖን ለሚቀርብበት ተቃውሞ የዕብራይስጥንና የግብፅን ቋንቋ አቀላጥፎ በተሰካካ የቋንቋና የሐሳብ ፍሰት ተገቢውን ምላሽ ለመስጠት ያለመቻል ሥጋት ነው፡- ምንም እንኳ ለእግዚአብሔር በሚገባ መልስ መስጠት ቢችልም!

11-12 እግዚአብሔር ለሙሴ በምሳሌነት ለመጠቀስ በበቃ ጥያቄ መልስ ሰጠው (መዝ 94፥9)። የመናገር፣ የማየትና የመስማት ስጦታዎች ባለቤት፣ ይኸው ላለመላክ እያንገራገረ ያለውን መሪ እየላከው ያለው አምላክ ነው። ምንም እንኳ እግዚአብሔር ስንኩል ለሆነ ተፈጥሮ በቀጥታ ተወቃሽ ባይሆንም፣ በሉዓላዊ ሥልጣኑ እነዚህ ብልቶች በሚገባ እንዳይሠሩ ሊያደርግም ሆነ፣ በቸርነቱ መደበኛ ሥራቸውን እንዲሠሩ ለማድረግ የሚችል መሆኑ፣ ሙሴ እንደ ችግር ለሚያነሣቸው የትኞቹም ነገሮች ሁሉ መልስ መስጠት የሚቻለው መሆኑን ያመለክታሉ። እናም እግዚአብሔር ለሙሴ "መናገር እንድትችል አደርግሃለሁ" (በቁሙ "ከአፍህ ጋር እሆናለሁ") "የምትሰውንም አስተምርሃለሁ" አለው።

ሠ. ለምን ሌላ ሰው አትፈልግም? (4፥13-17)

13-14*ሀ* የሙሴ መሠረተ ቢስ ተቃውሞ እግዚአብሔርን አስቈጣው። ሙሴ አንድም የመቃወሚያ ምክንያት ማቅረብ አልቻለም፤ እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ በቂ ምላሽ ስለ ሰጠ። እናም አሻፈረኝ ባዩ የእግዚአብሔር አገልጋይ ትክክለኛው የልቡ ማንነት ይፋ ሆነ፡- በቁሙ "በምትልከው ሰው እጅ እንድትልክ እለምንሃለሁ" ይህም በዕብራይስጥ ዘዬ "ሌላ ሰው ምረጥ፣ እኔን ለቀቅ አርገኝ" እንደ ማለት ነው። (በዐመት "እባክህ ሌላ ሰው ላክ")።

14ለ-17 ይሁን እንጂ እግዚአብሔር በምሕረቱ ይህንኑ አመንቺ አገልጋይ በመጠቀሙ ጸና፤ ሙሴ እንደ ችግር ላቀረበው ነገርም ወንድሙ አሮን ክፍተቱን እንዲሞላ ላከው። ሆኖም ሙሴን ግትርነቱ ዋጋ አስከፍሎታል። አሮን የክህነቱን አገልግሎት የመምራት ክብር ይሰጠዋል። "ሌዋዊ" የሚለው ቅጽል ለአሮን የተሰጠበት ምክንያት ይህ እንደ ሆነ ይታሰባል (ከ1ዜና 23፥13 ጋር ያነጻ)። የእግዚአብሔር ሁሉን ዐዋቂነት አሮን በዚያ ቅጽበት በእግዚአብሔር አነሣሽነት (ቍ. 27) ከሙሴ ጋር ለመገናኘት በጉዞ ላይ በመሆኑ ("አሁንም ወዳንተ እየመጣ ነው") ተገልጸአል። አሮን የመጣው የሙሴን ሕይወት ለመውሰድ የሚፈልገው ንጉሥ የመሞቱን ዜና ሊነግረው እንደ ሆነ (2፥15) ወይም በሌላ ምክንያት የሚታወቅ ነገር የለም።

እግዚአብሔር ያቀደው ግን ሙሴ በቁሙ የአሮን "አምላክ"፣ አሮንም የሙሴ አፍ (ወይም በ7፥1 መሠረት የሙሴ "ነቢይ") እንዲሆን ነው። በእግዚአብሔርና በነቢዩ ሙሴ መካከል ያለውን የጠበቀ ኅብረት ከ4፥16 እና ከ7፥1 በተሻለ ሁኔታ የሚገልጽ አንዳች ነገር የለም። ከእንግዲህ ሙሴ ምንም ዐይነት ሰበብ ወይም ምክንያት ማቅረብ የለበትም። በዚህ ጉዳይ ውይይትም አይኖርም፡- "አንተ ለእርሱ ትናገራለህ፤ ቃላትንም በአንደበቱ ታኖራለህ።" በተጨማሪም እግዚአብሔር ሁለቱንም ምን ማድረግ እንዳለባቸው ይነግራቸዋል። ተግባርንና ድርጊትን በሚመለከት እግዚአብሔር ተአምራትን ለመሥራት የሚጠቀመው በሙሴ እጅ ያለችውን ያቺኑ ተራ በትር ነው። ሙሴ ተአምራቱን አስመልክቶ ቀደም ብሎ መናገር ጀምሯል (3፥20) ለሙሴ ማሳየትንም እንዲሁ (4፥2-8)።

6. የመሪውን ቤተ ሰብ ማዘጋጀት (4፥18-26)

18 ሙሴ የሲናን አካባቢ ትቶ ዐማቱን ዮቶርን ወደ ግብፅ ተመልሶ እንዲሄድ እንዲፈቅድለት ሊጠይቀው ወደ ምድያም ተጓዘ። የእግዚአብሔር ጥሪ እንኳ ቢሆን ሰብኣዊውን የመቀባበልና የመከባበር አስፈላጊነት ሊሸር አይችልም። የሚያስገርመው ሙሴ ወደ ግብፅ ለመመለስ የፈለገበትን እውነተኛ ምክንያት ለዮቶር አልገለጸለትም። ለዮቶር የሰጠው ምክንያት፡- "ወገኖቼ እስካሁን በሕይወት መኖራቸውን አይ ዘንድ" የሚል ነው። በዚህ መሠረት ዮቶር ሙሴ ወደ ግብፅ

ተመልሶ እንዲሄድ ፈቀደለት፡- በሰላም ሂድ ብሎም መርቆ ሸኘው፡፡

19-20 ይህ ዐጭር ክፍል ሙሴ የተለወጠው በምድያም እንጂ እግዚአብሔር በተገለጠለት በሲና እንዳልነበር፣ ደግሞም ሙሴ ወደ ግብፅ ለመመለስ የወሰነው ሊገድለው የሚፈልገው ፈርዖን መሞቱን ከመስማቱ በፊት መሆኑን ያመለክታል፡፡ የጠላቶቹ መሞት ዜና ሚስቱን ሲፓራንና ሁለቱ ወንዶች ልጆቹን ይዟቸው ለመሄድ እንዲወስን ገፋፍቶት ሊሆን ይችላል፡፡ እስካሁን ድረስ በስም የተጠቀሰው የሙሴ አንደኛው ልጁ፣ ጌርሳም ብቻ ነው (2፥22)፡፡ ኤልኤዜር፣ ምንም እንኳ በዚህ ምንባብ ባይጠቅስም፣ በዚህ ጊዜ ሳይወለድ አይቀርም (18፥4)፤ እናም በብዙ ቍጥር መገለጡ ትክክል ነው፡፡ ከዚህ በኋላ ዮቶር ሙሴን እስኪጐበኝና እስራኤላውያን በሲና እስኪሰፍሩ ድረስ የሙሴ ቤተ ሰብ አይጠቀስም (ምዕ 18)፡፡ ሙሴ “የእግዚአብሔርን በትር” ይዞ ወጣ፡፡ በአንድ ወቅት ተራ የነበረው የሙሴ በትር ለእግዚአብሔር አገልግሎት ከመዋሉ የተነሣ ልዩ ኀይል ያለው በትር ሆነ፡፡ በዚህ ዐይነት ትጥቁን አሟልቶ ሙሴ ወደ ግብፅ ለመመለስ ተዘጋጀ፡፡

21-23 እግዚአብሔር በማጠቃለል ዐይነት ቀደም ብሎ ለሙሴ የሰጣቸውን ትእዛዛት ዋና ሐሳቦች በድጋሚ ገለጠለት፡- (1) በፈርዖን ፊት ተኣምራትን ታደርጋለህ፤ (2) ፈርዖን ልቡን ያደነድናል፤ ሕዝቡንም አይለቅም፤ (3) እስራኤል “በኵር ልጄ” ስለ ሆነ እስራኤላውያን ያመልኩኝ ዘንድ ነጻ ልታወጣቸው ይገባሃል ብለህ ትነግረዋለህ እና (4) የፈርዖን እምቢታ የበኵር ልጁን ሞት ያስከትልበታል፡፡

“እኔ ግን ሕዝቡን እንዳይለቅ ልቡን (የፈርዖንን) አደነድናለሁ” የሚለው ሐረግ ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠቀሰው በዚህ ቦታ ነው፡፡ በአጠቃላይ ልብ “መደንደን” ምክንያቱ እግዚአብሔር እንደ ሆነ የሚጠቅሱ ዐሥር ቦታዎች አሉ (4፥21፤ 7፥3፤ 9፥12፤ 10፥1፡ 20፡27፤ 11፥10፤ 14፥4፡8፡17)፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ፈርዖን የራሱን ልብ እንዳደነደነ አስረግጠው የሚናገሩ ዐሥር ምንባቦች አሉ (7፥13፡ 14፡ 22፤ 8፥15፡ 19፡ 32፤ 9፥7፡ 34፡ 35፤ 13፥15)፡፡ በመሆኑም የፈርዖን ልብ መደንደን የፈርዖን የራሱ ድርጊት የመሆኑን ያህል የእግዚአብሔርም ሥራ ነው፡፡ እንዲያውም በመጀመሪያው ምልክትና በመጀመሪያዎቹ ዐምስት ተከታታይ መቅሠፍቶች ብቸኛው የፈርዖን ልብ መደንደን ተዋናይ ፈርዖን ራሱ ነው፡፡ ቀደም ብሎ ሙሴ በምድያም እያለ “የፈርዖንን ልብ አደነድናለሁ” ብሎ እንዳስጠነቀቀው እግዚአብሔር እስከ ስድስተኛው ምእራፍ ድረስ የፈርዖንን ልብ አላደነደነም (9፥12)፡፡

እስራኤል የእግዚአብሔር “ወንድ ልጅ” እንዲያውም “በኵር ልጅ” ነው የሚለው ገለጻ ራሱን “የአማልክት ወንድ ልጅ” አድርጎ የሚቈጥረውን ፈርዖንን ክፉኛ ሳያስደነግጠው አልቀረም፡፡ ነገር ግን ለመላው ሕዝብ የመለኮት “ወንድ ልጅ” ተብሎ መጠራቱ ጥቂት ያስደንቃል፡፡ በዚህ የአባትና ልጅ ግንኙነት ላይ የተጨመረው እስራኤል የእግዚአብሔር “በኵር ልጅ” የሚለው ነው፡፡ ይህ ማለት ግን አስቀድሞ በመወለድ የተገኘ ብኵርና ማለት አይደለም፤ ምክንያቱም ያዕቆብ (ኋላ ላይ እስራኤል ተብሎ ዳግመኛ የተሰየመው) የተወለደው መንትያው ከሆነው ወንድሙ ከኤሳው በኋላ ነውና፡፡ በዚህ ቦታ እግዚአብሔር “በደረጃ (ማዕረግ) በኵር” ወይም የመጀመሪያ ማለቱ ነው፡፡ “ብኵርናው” በኵር መሆን የሚያስገኛቸውን መብቶች፣ ጥቅሞችና ኀላፊነቶች ጨምሮ ከሁሉ ልቆ የመገኘት ብኵርና ነው፡፡ በዚህ ዐይነት ከዚህ ቀደም አስቀድሞ የተወለደው ልጅ የወላጆቹን ንብረት በሙሉ የሚወርስበት ሥርዐት አሁን በጸጋ የሚገኝ ሆነ፡፡ እግዚአብሔር ለአብርሃም ዘር የሰጠው መብትና ጥቅም ሁሉ ከዚህ ጋር የሚሄድ ነው፤ ማለትም በዚህ “በኵር” አማካይነት እግዚአብሔር የምድርን አሕዛብ ሁሉ የሚባርክበት ነው፡፡ ፈርዖን የእስራኤልን የእግዚአብሔር (ወንድ) ልጅነት እና ብኵርና ለመቀበል አሻፈረኝ በማለቱ የሚደርስበት ቅጣት በገዛ በኵር ልጁ ላይ የታለመ ይሆናል፡፡ ልክ በ3፥12 የሙሴን ወደ ሲና የመመለስ ሁኔታ የሚጠቁም ሐሳብ እንደ ያዘ ሁሉ ቍ 21-23 የእግዚአብሔርን የወደፊት ሥራ፣ በመቅሠፍቶቹ “ድንቆች” ጀምሮ በፈርዖን በኵር ላይ አደጋ በማድረስ ወደ ፍጻሜው የሚደርሰውን የእግዚአብሔርን ሥራ ለማሳየት የታለመ ነው፡፡

24-26 ይህ ምንባብ የመጽሐፍ ቅዱስ ተርጓሚዎችን ግራ ማጋባቱን እንደ ቀጠለ ነው፡፡ እነዚህን የአተረጓጎም ችግሮች ለመፍታት መነሻ ቦታው ምንባቡ ራሱ ነው፡፡ ቍ 26ለ ሁሉም ክንውን፡- ሲፓራ ያደረገችው፣ የተናገረችውና ድርጊቱን የፈጸመችበት ማንነት፣ ሁሉም ከግዘረት ሥነ ሥርዐት ጋር ግንኙነት ያላቸው ናቸው፡፡ ይህ ምንባብ ከዐውዱ ጋር ያለው ግንኙነት ከፈርዖን “ወንድ ልጅ”፣ ወይም ከ“በኵር ልጁ” (ቍ 23) እና ከሙሴ “ልጅ” ምናልባትም “በኵር ልጅ” ጋርና እንዲሁም መላው እስራኤል የእግዚአብሔር ልጅ፣ በኵር ልጅ በመሆኑ ዙሪያ የሚሽከረከር ነው፡፡ ሙሴ የእግዚአብሔርን ተልእኮ በግብፅ ለመፈጸም በጕዞ ላይ እያለ “እግዚአብሔር ሊገድለው” ፈለገ፡፡ የዚህ የሙሴን ሕይወት ሊቀሥፍ የደረሰ ተሞክሮ ባሕርይ አይታወቅም፡፡ የመለኮት ቍጣ ሙሴ ላይ የተነጣጠረ ለመሆኑ ስሙ ያልተጠቀሰው ልጅ የሙሴ ሳይሆን የሌላ ሰው ልጅ እንደ ሆነ በመጠቀሱ ግልጽ ይሆናል፡፡ የሲፓራ ድርጊት በድንገት መጠቀሱ ሲፓራ በባሏ ላይ የታቀደውን አደጋ ልጃቸውን ካለመግረዛቸው ጋር በደመነፍስ እንዳገናኘችው እንድናምን ያደርገናል፡፡ (ይህ በሙሴ ላይ የተቃጣው አደጋ በጣም ከባድ መሆኑን የሚያመለክተን እጅጅን በማንቀሳቀስ ርምጃ መውሰድ የቻለችው ሲፓራ ብቻ እንጂ ሙሴ ይህን ለማድረግ እንኳ እስከማይችል እጅ እግሩ ተይዞ የነበረ መሆኑ ነው፡፡) ሲፓራ ልጇን ለመግረዝ ፈጣን ርምጃ ወሰደች፡፡ ራሷን በመውቀሥ መልክ ካደረገችው ንግግር የምንረዳው ነገር ልጁን በጊዜ ያለመግረዛቸው ችግር ሥሩ የሚገኘው እርሷ በግዘረት ሥነ ሥርዐት ላይ ካላት ጥላቻ ላይ መሆኑን ነው፡፡

ይህ ትረካ በዚህ ቦታ መጠቀሱ የሚያመለክተን የእግዚአብሔርን መልእክተኛ ለተልእኮው በብቃት ለማዘጋጀት አንድ ነገር የሚቀር መሆኑን ነው፡- ይህም የቤተ ሰቡ ዝግጅት ነው፡፡ በዘፍ 17፥10-14 እግዚአብሔር አብርሃምን ለገባለት ቃል ኪዳን ምልክት ይሆን ዘንድ በቤቱ የሚገኙትን ወንዶች በሙሉ በስምንተኛው ቀን እንዲገርዛቸው አዝዞታል፤ ማንኛውም ያልተገረዘ ወንድ ሁሉ ከወገኖቹ ተለይቶ መጥፋት ይኖርበታል፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ ቦታ የምንመለከተው አባት ልጁን ለመግረዝ ፈቃደኛ ባለመሆኑ ሲሠቃይ ነው፡፡ እናም በአንዲት ትንሽ ቸልተኝነት፤ በግልጽ ለሚስቱ ፍላጎት ካለው አክብሮት የተነሣ፤ ወይም ደግሞ ምናልባት የቤቱን ሰላም ለመጠበቅ ሲል ሙሴ እግዚአብሔርን ለማገልገል የተሰጠውን ዕድል ሊያጣና የሰማንያ ዓመት ዝግጅትና ሥልጠናውን ከንቱ ሊያደርገው ለጥቂት ነው ያመለጠው! ይህን በሙሴ አጣብቂኝ ውስጥ መግባትና የልጁ ግዘረት መካከል ያለውን ግንኙነት ግልጽ ለማድረግ ሲፓራ የተቈረጠውን ሸለፈት አንስታ የሙሴን እግሮች ነካችበት፡፡ እግዚአብሔር ሙሴን ማረው፣ የሞት ከበባም ተበተነ፡፡

ሐ. በመሪነት የመጀመሪያዎቹ ርምጃዎች (4፥27-7፥5)

1. በወንድም ዐብሮነት የተጠናከረ (4፥27-31)

27-28 በወቅቱ ዕድሜው ሰማንያ ሦስት ዓመት የሞላው አሮን በእግዚአብሔር ትእዛዝ ወደ ግብፅ በመጓዝ ላይ ከነበረው ከሙሴ ጋር “በእግዚአብሔር ተራራ” (ማለትም “ኮሬብ” 3፥1 ይመልከቱ) ለመገናኘት ተነሣ፡፡ በቍ 14 እንደ ተተነበየው አሮን ሙሴን “ሳመው”፡፡ ሰዎቹ ተለያይተው በነበሩባቸው አርባ ዓመታት ስለ ተፈጸሙት ነገሮች ብዙ የሚጨዋወቱት ታሪክ አላቸው፤ ይሁን እንጂ ሙሴ ከእግዚአብሔር የተቀበላቸው ነጻ የማውጣት ትእዛዞችና ተኣምራታውያን ምልክቶች ላይ የተደረገው ውይይት ከሁሉም የላቀውን ቦታ የያዙ ናቸው፡፡

29-31 ወዲያውኑ ትረካው ወደ ፊት ገሥግሦ ሙሴ ግብፅ እንደ ደረሰ እንዲፈጽም ወደ ታዘዘው የእስራኤልን ሽማግሌዎች የማነጋገሩ ትረካ ላይ ይገባል። እግዚአብሔር በሥልጣን ላይ ያሉ አካላት ተገቢው ክብር እንዲሰጣቸው በርግጥ ይፈልጋል። በመሆኑም ሙሴ ለፈርዖን አንዳች ጥያቄ ከማቅረቡ በፊት በወቅቱ ለነበረው የእስራኤል አመራር ጉዳዩን አሳውቆ ፈቃድ መጠየቅ ይገባው ነበር። እግዚአብሔር ለሙሴ የነገረውን ሁሉ ተቀብሎ ለማስተላለፍ አሮን እንደ ዋና አፈ ቀላጤ ሆኖ ሠርቷል። በተጨማሪም ምንም እንኳ ከቁ 1-9 እግዚአብሔር የሰጣቸውን ምልክቶች እንዲያደርግ የታዘዘው ሙሴ ብቻ ቢሆንም (ቁ 17)፣ ሙሴም አሮንም ተኣምራቱን ፈጽመዋል።

ሽማግሌዎቹ ሕዝቡን የሚወክሉ በመሆናቸውና በመጨረሻም ከሙሴና ከአሮን የሰሙትንና ያዩትን ለሕዝቡ ዘገባ ስለሚያቀርቡ ጽሑፉ እነዚህን ደረጃዎች በዐጭሩ በመቀሩጥ በቁ 30 ላይ ይህ ሁሉ በሕዝቡ ፊት (በቁሙ "ሕዝቡ እያየ") እንደ ተፈጸመ ይናገራል። የሕዝቡ ምላሽ በ3፥18 እንደ ተተነበየው ነው፦ "አመኑ" የነበሩበት ሥጋዊ ጭቈና እነዚህ ሰዎች ቃሉን እንዲቀበሉ አድርጓቸዋል፤ በኋላ ላይ ግን ይሄ ልማዳቸው በጣም ይቀንሳል። ሙሴ በቁ 1 ላይ ሥጋቱን እንደ ገለጸው ምልክቶቹ ያስፈልጉ ነበርን? ለሚለው ጥያቄ ምንባቡ ምንም አስተያየት አይሰጠንም። በጣም ልብ የሚያሞቀው እግዚአብሔር ስለ እነርሱና ስለሚያልፉበት መከራ ግድ የሚለው መሆኑ ነው። ለዚህ የሰጡት ምላሽ ወዲያውኑ ለእግዚአብሔር ሰገዱ፤ ምክንያቱም "የጐበኛቸው" (ዐመት "ግድ የተሰኘው") እና መከራቸውን ያየው እርሱ በመሆኑ ነው።

2. የጠላት እምቢታ ገጠመው (5፥1-14)

1-2 ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሙሴና አሮን፤ ምናልባትም የእስራኤል ሽማግሌዎችም ዐብረዋቸው ሆነው (3፥18 ያነጻ)፣ ወደ ፈርዖን ፊት ቀርበው ሕዝቡን ይለቃቸው ዘንድ በድፍረት ጠየቁ። ይህን ጥያቄ በስሙ ላቀረቡለት "የእስራኤል አምላክ፤ እግዚአብሔር" በምድረ በዳ በዓል ሊያደርጉለት እንደሚፈልጉ ገለጹ። (3፥14-15 የሚገኘውን ማብራሪያ ይመ)። እነዚህን ባሮች ለማዘዝ የነበረውን ብቸኛ ባለመብትነት ለተጋፋው ለዚህ ጥያቄ ፈርዖን የሰጠው ምላሽ ቆፍጣናና ጭካኔ የተሞላበት ነበር። በርግጥ እግዚአብሔር ከእነዚህ ዕድለ ቢስና ተስፋ-ቢስ ባሮች ጋር ለመወገን ከፈለገና፣ ነጻ ሊያወጣቸው ዐቅም የሌለው ከሆነ፣ ፈርዖን ለምን ይፈራዋል፤ ለምንስ ለድምፁ ይታዘዛል? በመሆኑም የፈርዖን ምላሽ ግልጽ "እምቢታ!" ነበር።

3 በፈርዖን የድፍረትና የትዕቢት ምላሽ ዕጢያቸው ዱብ ያለው ሙሴና አሮን ጥያቄያቸውን ለስለስ አድርገው አቀረቡ። እንደ ሕዝቡ ወኪልነታቸውና በሚነድደው ቍጥቋጦ ውስጥ በተሰጠው ቋንቋ፣ ጥያቄውን አለሳልሰው በትሕትና አቀረቡ። ፈርዖን ሕዝቡን ለጊዜው ለመልቀቅ ፈቃደኛ ካልሆነ የማይነገር ኪሣራ ሊደርስበት እንደሚችል፣ ይህ አምላክ ሁሉንም ዐይነት መቅሠፍቶች ሊያወርድባቸው ወይም እስራኤላውያን ለአደጋ ተጋልጠው በሰፈሩበት በምሥራቃዊው የአገሪቱ ድንበር ወራሪ ሊያመጣባቸው እንደሚችል የእግዚአብሔር ባሮች አስጠነቀቁት።

4-14 ፈርዖን በቀረቡለት ጥያቄዎችም ሆነ ዛቻዎች በአንዳችውም ፍንክች አላለም። በፈርዖን ግምት ሕዝቡ በጣም ሰነፎች ሥራፈቶች፣ ሙሴና አሮን ፀረ ሰላም፣ በጥባጮች ሲከፋም የዙፋኑ ተቀናቃኞች ተደርገው ተቈጠሩ። እናም ያቀረበላቸው ጥያቄ ጭብጥ "ይህን ዐይነቱን ነገር ለምን ታበረታታላችሁ?" የሚል ነው። እንዲያውም ቍጥራቸው እጅግ በዝቷል (ይህም እግዚአብሔር ለተስፋ ቃሉ ታማኝ የመሆኑ ሌላው ማስረጃ ነው) ታዲያ ፈርዖን ከሥራቸው እንዲያርፉ በማድረግ የመባዛት ተጨማሪ ዕድል ይስጣቸው እንዴ?

ግብፃውያኑ ጨቋኝ አለቆች ለእስራኤላውያኑ "አሠሪዎች" ከእንግዲህ ባሮቹ ለሚሠሩት ሸክላ ጭድ እንደማይቀርብላቸው አሳወቋቸው። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ እስራኤላውያን ገለባና ጭድ ለመቃረም ገጠሩን ለማሰስ ተገደዱ፤ እንዲያም ሆኖ ቀድሞ በየዕለቱ ያቀርቡ የነበረውን የሸክላውን ቍጥር ሳይቀንሱ ማቅረብ ነበረባቸው። ሸክላውን ጠንካራና ተጣጣፊ ለማድረግ እንዲያስችል ጭቃው በጭድ መለወስ ነበረበት። በመሆኑም ሕዝቡ በመላው ግብፅ ተበትኖ ገለባ ሲያስስ ግብፃውያኑ ጨቋኝ አለቆች እስራኤላውያኑን ‹‹አሠሪዎች›› የተመደበባቸውን ዕለታዊ የሸክላ ቍጥር ካላቀረባችሁ ብለው ይደበድቧቸው ነበር።

3. በባሮቹ ተቃውሞ ገጠመው (5፥15-21)

15-16 እስራኤላውያኑ "አሠሪዎች" ሙሴና አሮን ለፈርዖን ካቀረቡት ጥያቄ የተነሣ ሥልጣናቸው መሸርሸሩን ሳያውቁ "ገለባ አይሰጣችሁም" የሚለውን ዐዲስ መመሪያ አስመልክቶ በግል ለፈርዖን አቤቱታ አቀረቡ። በጨዋነት፣ ሆኖም በጽኑ ምሬት "እኛን ባሮችህን እንደዚህ የምታደርገን ለምንድን ነው? ጭድ አይሰጠንም፤ ነገር ግን ሸክላ አቅርቡ ብለው ፋታ ሳይሰጡ ያስጨንቁናል፦ እንደበደባለን፦ ጥፋቱ ግን ፈርዖን ሆይ የራስህ ሕዝብ ነው።" "ጥፋቱ ግን የራስህ ሕዝብ ነው" የሚለው የመጨረሻው የክስ ሐረግ በተዘዋዋሪ ፈርዖንን ራሱን ጥፋተኛ የሚያደርግ ነው።

17-18 ፈርዖን ሁኔታውን የተረዳበት መንገድ በአንድ ቃል ሲጠቃለል፦ "ልግመኞች!" የሚል ነው። ለአጽንዖት ቃሉን በመድገም "ልግመኞች!" ይላቸዋል፤ (ከቁ 8 ጋር ያነጻ)። የእነርሱ ጥያቄ "አሁን . . . እንድንሄድ ፍቀድልን" የእርሱ ማጠቃለያ ምላሽ "አሁን ወደ ሥራችሁ ተመለሱ" የሚል ነበር። ምንም ጭድ አይቀርብላቸውም፤ ዕለታዊ አቅርቦታቸውም ከተመደበው እንዲያንስ አይፈቀድላቸውም።

19-21 እስራኤላውያኑ "አሠሪዎች" የገቡበት አጣብቂኝ እውነተኛ ገጽታ ፍንትው ብሎ የታያቸው ገና አሁን ነው። ሙሴና አሮን ሆነ ብለው እስራኤላውያኑ "አሠሪዎች" ከፈርዖን ፊት ሲወጡ ሊገናኟቸው ከደጅ ይጠብቋቸው ነበር፤ ምክንያቱም ከግብፁ ንጉሥ የሚጠብቃቸው ምላሽ ምን ሊሆን እንደሚችል በሚገባ ገምተው ነበርና። ሙሴና አሮን ምናልባት እስራኤላውያኑ "አሠሪዎች" "ሲያገኟቸው" ይህን ያህል በብርቱ ቍጣ ይገነፍሉብናል ብለው አልጠበቁም ነበር።

ካሉበት አሠቃቂ መከራ ሊያሳርፏቸው ስላደረጉት ሙከራ ሙሴና አሮን ከእነዚህ ዕብራውያን "አሠሪዎች" በከበሬታ ፋንታ የጠበቃቸው ያለጥርጥር የቍጣቸው እስትንፋስ ወላፈን ነበር። የእስራኤል ልጆች ስምና ዝና በግብፃውያን ሹማምት ዘንድ እንዲበላሽ በማድረጋቸው፣ በእነዚህ ሁለት ችግር ፈጣሪዎች ላይ እግዚአብሔር እንዲፈርድባቸው ልመና አቀረቡ። ቍጥር 20 እና 21 በቍጥር 3 ላይ የተገለጸውን ሐሳብ ያንጸባርቃሉ። "መቅሠፍት" ወይም "ሰይፍ" ሳይሆን እስራኤልን የመታው፤ ሙሴና አሮን ናቸው፤ በፈርዖን እጆች ላይ ሰይፍን ያስቀመጠው ጠላት አይደለም። እናም እስራኤላውያኑ "አሠሪዎች" ሙሴና አሮንን "ገጯቸው" ወይም ደግሞ ከሙሴና ከአሮን ጋር "ተላተሙ"።

4. የድሮው የጥሪ ተቃውሞ እንደ ገና አገረሸበት (5፥22-23)

22-23 ምንም እንኳ እግዚአብሔር ሙሴን ገና ከመጀመሪያው ፈርዖን ቀና ምላሽ እንደማይሰጠው ቢያስጠነቅቀውም፣ ይህ የፈርዖን እምቢታ የገዛ ወገኖቹ በሆኑት በእስራኤላውያን ዘንድ ይህን የመሰለ ስሜት ይፈጥራል ብሎ አልገመተም። ሙሴ በተራው ወደ እግዚአብሔር መለስ ብሎ "ቀድሞውኑ አስጠንቅቀህ አልነበረም?" በሚል መንፈስ "ለምን ጌታ ሆይ?"

የሚል ጥያቄ አቀረበ (ፈርዖን ቁ. 4 ላይ፣ እስራኤላውያኑ “አሠሪዎች” በቁ. 15 ከተናገሩት ጋር ያነጻ)። የሙሴ አባባል በቁሙ ሲተረጎም “(ቀድሞውኑ) ለምን ላክኸኝ?” የሚል ነው። ደግነቱ ሙሴ ቁጣውን በእስራኤላውያኑ “አሠሪዎች” ላይ አልገለጠም፤ ይሁን እንጂ በርግጥ ቅሬታውን በቅንነት ለእግዚአብሔር አቅርቧል። ሙሴ እግዚአብሔርን በቀጥታ ይህን ክፋት ለምን አመጣህብን? ብሎ አልከሰሰውም፤ የዘይቤው አንድምታ ፈርዖን ይህን ያህል ችግር እንዲፈጥር ለምን ፈቀድህለት የሚል ነው።

የሙሴ የመጨረሻው ንግግሩ ቁ. 23 ላይ የሚገኘው ነው። የጸሎቱ ይዘት “ጌታ ሆይ ለምንድን ነው ይሄ እየሆነ ያለው? አንተስ ከቶ ለምን ላክኸኝ?” ነው። ቀጥሎም ማጠቃለያ ይሰጣል፦ “ደግሞም አደርጋለሁ ያልኸውን እስካሁን አላደረግህም፦ ነጻ አላወጣሃቸውም! እኔም ከመጣሁ ጀምሮ በዚህ ቦታ ችግር አመጣሁ እንጂ ምንም የፈየድሁት የለም!” አሁንም ሙሴ ቀድሞ ካቀረበው የ“አልሄድም!” ተቃውሞዎች ጋር በውስጡ እየታገለ ነው (ከ3፥11-4፥17 ጋር ያነጻ)። በእርሱ ግምት ነገሮች ከልክ በላይ እየተንቀረፈፉ ነው፤ የሕዝቡ መከራም ጋብ ከማለት ይልቅ እየባሰ መጥቷል።

5. በእግዚአብሔር ስም ኀይሉን አጠነከረ (6፥1-8)

1 ሙሴ ላቀረባቸው ጥያቄዎች ቀጥተኛ መልስ አላገኘም፤ የእነዚህን ጥያቄዎች መልሶች የሚያገኘው እንደ መሪ በሚያልፍበት የሕይወት ተሞክሮ ውስጥ ነውና። ሙሴ እግዚአብሔር በቶሎ ላለመምጣቱ ያቀረበው ቅሬታ ግን አሁን ምላሽ ሊያገኝ ነው፦ እግዚአብሔር የራሱን “አሁን” አስታውቋልና፦ ከእንግዲህ ወዲህ አይዘገይም። ተስፋ የተገባለት የእግዚአብሔር ኀይል መገለጥ “ኃያል ክንዱን›› በማሳየት በቅርቡ ሥራውን ይጀምራል (ከ3፥19 ጋር ያነጻ)።

2-5 እግዚአብሔር ለሙሴና ለሕዝቡ የሰጠው ምላሽ አንኳሩ ነጥብ ባሕርዩንና ማንነቱን እንደ ዐዲስ መግለጥ ነው። በተለይ “እኔ እግዚአብሔር ነኝ” የሚለው ሐረግ ጐልቶ ይታያል፤ ከቁ. 2 እስከ ቁ. 8 አራት ጊዜ ተጠቅሷል። አሁንም እግዚአብሔር አንድ ጊዜ በድጋሚ ለሙሴ የከነዓንን ምድር ለአባቶች ለመስጠት ኪዳን መግባቱንና የመረጣቸውን ሕዝቡን መከራ እንደ ተመለከተም አስታወሰው። ደግሞም የቀደሙት አባቶች ያወቁት በኤልሻዳይነት ባሕርዩና ችሎታው (“ሁሉን የሚችል አምላክ” ከዘፍ 17፥1፤ 28፥3፤ እና ከሌሎችም ጋር ያነጻ)፦ ይህ ስሙ ሕይወት ለመስጠት፣ ለሕይወት የሚያስፈልጉ ነገሮችን ለማብዛት፣ ዐመፃን ሁሉ ለመቅጣት ኀይል ያለው መሆኑ የተገለጠበት ስሙ። ከአሁን ወዲያ “ጌታ እግዚአብሔር” “ያህዌ” በመባል ይታወቃል።

ሙሴና እስራኤል (ወደ በኋላም ግብፃውያንም እንኳ) በዐጭር ጊዜ ውስጥ “እኔ እግዚአብሔር ነኝ” ማለት ምን ማለት እንደ ሆነ ያውቃሉ። ይህ ስም ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠቀሰው በዚህ ስፍራ አይደለም፤ ከዚህ በፊት በዘፍጥረት ውስጥ 162 ጊዜ ተጠቅሷል። በቅጡ “ሰዎች የእግዚአብሔርን ስም መጥራት” የጀመሩት ገና ከዘፍ 4፥26 ጀምሮ ነው። ይህ እግዚአብሔር እርሱ ራሱ በጥልቀትና በታማኝነት ከእነርሱ ጋር በመሆን ለአብርሃም፣ ለይስሐቅና ለያዕቆብ የገባላቸውን ኪዳን የሚፈጽመው አምላክ ነው። አባቶች የያዙት የተስፋውን ቃል ብቻ እንጂ ተስፋ የተገቡትን አልነበረም። አደርጋለሁ ብሎ የገባውን ተስፋ ሊፈጽምና እንደ ተናገረው ካደረገ በኋላ እግዚአብሔር በያህዌነቱ ባሕርይና ችሎታ የሚታወቅበት ዘመን ደረሰ። እነዚህ እግዚአብሔር አደርጋለሁ ያላቸው ነገሮች ከቁጥር 6-8 በቀረቡት ሰባት የተስፋ ቃሎች ውስጥ በዝርዝር ተገልጸዋል።

6-8 “እኔ እግዚአብሔር ነኝ” የሚለውን ሐረግ ትርጉም ለማስረዳት እግዚአብሔር ከጥንት ጀምሮ የገባቸው የተስፋ ቃሎች በአንድነት ተሰድረው ቀርበዋል።

የእግዚአብሔርን የመቤዠት የተስፋ ቃል የያዙ በአንደኛ መደብ የተነገሩ ሦስት ግሶች አሉ (ቁ. 6)፦ (1) “አወጣችኋለሁ”፤ (2) “ነጻ አወጣችኋለሁ”፤ (3) “እቤዣችኋለሁ”። እግዚአብሔር በ3፥20 እና በ4፥23 እንደ ጠቁመውና ገና ከጥንት ለአብርሃም በዘፍ 15፥14 ቃል በገባለት መሠረት ድንቅ የሆኑ ታምራትን በማድረግ እስራኤልን “እንደሚቤዣቸው” ተስፋ ይገባላቸዋል። መቅሠፍቶቹ በወንጀሎች ላይ ለመፍረድ እንዲሁም እምነትን የሚቀሰቅሱ ድንቃ ድንቆች እንዲሆኑ የታለሙ ነበሩ።

2. በአንደኛ መደብ የተነገሩ ሁለት ተጨማሪ ግሶች እግዚአብሔር እስራኤልን የራሱ ሕዝብ እንዲሆኑ እንደ መረጣቸው በዝርዝር ያስረዳሉ (ቁ. 7)፦ (1) “የራሴ ሕዝብ አደርጋችኋለሁ”፤ (2) “እኔም አምላክ እሆናችኋለሁ”። እነዚህ ሁለት የተስፋ ቃሎች በብሉይም በዐዲስም ከዐምሳ ጊዜ በላይ የተጠቀሱት ጣምራ (የሦስትዮሽ) ኪዳኖች አካል በመሆን ያገለግላሉ፤ “እኔም አምላክ እሆናችኋለሁ፤ እናንተም ሕዝቤ ትሆናላችሁ፣ እኔም በመካከላችሁ ዐድራለሁ” (ከዘፍ 17፥7-8፤ 28፥21፤ ከዘፀ 29፥45-46፤ እና ከሌሎችም ጋር ያነጻ)።

3. የመጨረሻዎቹ ሁለቱ የተስፋ ቃሎች እግዚአብሔር በገባላቸው የተስፋዪቱ ምድር ቃል ኪዳን ላይ የሚያተኩሩ ናቸው (ቁ. 8)፦ (1) “. . . ወደ ማልሁላችሁ ምድር አመጣችኋለሁ”፤ (2) “ርስት አድርጌ እሰጣችኋለሁ።” ይህን ቃል የገባው እጆቹን በመሐላ ወደ ላይ በማንሣት ነበር (ከዘፍ 22፥16፤ 26፥3 ጋር ያነጻ)። ይህም በሁለት በማይለወጡ ነገሮች፦ በተስፋ ቃሉና በመሐላው፦ እስራኤል (እና ቀጣይ አማኞች ሁሉ፤ ከዕብ 6፥17-18 ጋር ያነጻ) ወደ ፊት ጠንካራ፣ ብርቱ ድፍረትና ጽኑ መታመን እንዲኖራቸው ያደርጋል። ቀጥሎም እስራኤልን ዳግመኛ ለማስታወስ የፈለገ ይመስል፦ “እኔ እግዚአብሔር ነኝ” በሚለው ፊርማው ያጠቃልላል።

6. የሙሴን ከተዋረደ ሰፍራ መነሣት የሚያስታውሱ (6፥9-7፥5)

9-12 “እኔ እግዚአብሔር ነኝ” የሚለው ሐረግ ለእስራኤል ያለውን ታላቅ ትርጓሜ እንኳ ሕዝቡ “ከትንፋሽ እጥረት የተነሣ” (“ተስፋ ከመቁረጣቸው የተነሣ” (ዐመት) አላደመጡትም። በሚገባ እንዳይተነፍሱ ያደረጋቸው ጥልቅ የሆነ ተስፋ መቁረጥ ያስከተለው ውስጣዊ ጫና ነው፦ ልክ ሕፃናት ስቅስቅ ብለው ሲያለቅሱ፣ ሳማ እየተናነቃቸው አየር ለመሳብ እንደሚሞክሩት ዐይነት።

ይህ ሁኔታ ያሳደረበት ጫና የሙሴን ራሱን ያለመቀበልና ተስፋ የመቁረጥ “አባዜ” ቀሰቀሰበት። ከነበሩበት መከራ የተነሣ የሚለው ነገር ከፍተኛ ጉጉት ሊፈጥርባቸው ሲገባ የገባ ወገኖቹን እንኳ ቅንጣት ያህል ሊያሳምን ያልቻለው ሙሴ እንዴት ፈርዖንን ሊያሳምነው ይችላል? ለማንኛውም ከንፈሮቹ የተሰጣቸውን ሥራ በሚወጡበት ጊዜ “ይኸ ላተፋ” (ከዐመት ማስታ. “ያልተገረዘ” ጋር ያነጻ) ነበር። እናም ሙሴ ለአራተኛ ጊዜ ለጥሪው የእምቢታ ምላሽ ሰጠ (4፥10)።

13-30 በ1፥1-6፥12 ላይ ለዋናው ሥራ መጀመር መድረኩ ተመቻችቷል። ይሁንና ይህ ከመጀመሩ በፊት “እግዚአብሔር የተናገራቸው ሙሴና አሮን” እነማን እንደ ሆኑ መመልከቱ አስፈላጊ ነው። በርግጥ የትውልድ ሐረግ የሚዘረዝረው ከቁጥር 14-25 ያለው ክፍል የተከበበውና የተቀነበበው ቁጥር 10-13ን በቁጥር 26-30 እና ቁጥር 14ሀን በቁጥር 25ለ ቃል በቃል በመድገም ነው ማለት ይቻላል። ስለዚህ የትውልድ ሐረግ መዘርዘሩ የሚያተኩረው በሁለት ሰዎች ላይና እነርሱም

በሰዎችና በመንግሥታት ወሳኝ የታሪክ ክሥተት ውስጥ እንዴት እንደ ተገኙ በመግለጽ ነው።

በዚህ ዝርዝር ውስጥ የሚገኙት ነገሮች ሁሉ እግዚአብሔር ሙሴን ይመርጠው ዘንድ የሚያደርግ አንዳችም የተፈጥሮም ሆነ የችሎታ ጉዳይ እንደሌለ ይጠቁማሉ። ዝርዝሩ ሦስቱን የያዕቆብ ልጆች ሮቤልን፣ ስምዖንንና ሌዊን ጠቅሶ ያቆማል፦ ግቡን መታልና። ሙሴና አሮን የተገኙት "በኩር" ከሆነው ከሮቤል ሳይሆን የያዕቆብ ሦስተኛ ልጅ ከሆነው ከሌዊ ለዚያውም ከሌዊ በኩር ልጅ ሳይሆን ከሁለተኛው ልጁ ከቀሬ ነው። ሙሴም ቢሆን የአባቱ የመጀመሪያ ልጅ አልነበረም፤ አሮን ነው ታላቁ። የሙሴ ጥሪና ምርጫ የጸጋው ትሩፋት እንጂ ከልደት ጋር የተያያዙ መብቶችና ዕድሎች አልነበሩም።

ሦስቱ የያዕቆብ ልጆች ከክፋታቸው የተነሣ እያንዳንዳቸው የአባታቸውን ርግማን ወርሰዋል፦ ሮቤል የ"በኩርነት" መብቱን ዐጥቷል (ዘፍ 49፥3-4)፤ ስምዖንና ሌዊ ከወገኖቻቸው ጋር ርስት እንዳይካፈሉ ተከልክለው ይብሱን ተበታትነዋል (ቁ. 5-8)። የሮቤልና የስምዖን ልጆች የወላጆቻቸውን ክፉ ምግባር ፈለግ ቢከተሉም፣ የሌዊ ልጆችን ግን ለእግዚአብሔር በመሰጠት ርግማኑን ወደ በረከት ቀየሩት፤ በእስራኤል ነገዶች መካከል መበተናቸውንም በክህነታቸው አማካይነት በእግዚአብሔር መቅደስ ውስጥ በሰጡት አገልግሎት ለመላው እስራኤል የበረከት ምክንያት ሆነዋል። ይሁንና ይህ ክብር ከሌዊ ነገድ የሆነውን ቆሬን በራሱ ዐመፅ ራሱን ከማጥፋት አላዳነውም (ዘኍልቊ 16)፤ ይሁንና የእርሱ ልጆች ግን እስከ ወዲያኛው ለጥፋት ራሳቸውን አልሰጡም፤ ወደ በኋላ ላይ በመቅደሱ ዝማሬን እስከ መድረስ የደረሰ ከፍታ ላይ ወጥተዋል፤ መዝ 42-49፤ 84-85 እና 87 በቆሬ ልጆች የተደረሱ ናቸው። እናም ሙሴና አሮን የተቀረጹበት (የተሠሩበት) መንገድም ሆነ ከተሠሩ በኋላ ጥቅም ላይ የዋሉበት ሁኔታ ሙሉ በሙሉ የእግዚአብሔር ሥራ ነው። ሆኖም የሙሴ ተሞክሮዎችና በሰማንያ ዓመት የዕድሜ ዘመኑ የተቸራቸው ተሰጥኦዎች ስምም መሆናቸውን ገለጻው ቀጭጭ አድርጎ አስቀምጧል። እናም ምርጫው የሠራው በተፈጥሮታዊም በመንፈሳዊም አቅጣጫ ነው።

ምንባቡ ከቁ. 10-13 ያሉትን ቃላት በቁ. 26-30 መለስ ብሎ በመድገም፦ "ከእግዚአብሔር ጋር አፍ ለአፍ የሚነጋገረውን ሰው ማንነት ተመልከቱማ! በእግዚአብሔር ቸርነት ከተሰጠው ጸጋ ውጭ በራሱ ጥቂት ጠንካራ ነገሮች ብቻ ያሉት ሰው እኮ ነው!" የሚል ይመስላል። ይሄ ምንም ለውጥ አያመጣም፤ ቁ. 28 አሁን ፍጹም ዐዲስ ጨዋታ መጀመሩን የሚያስረግጥ ይመስላል። ሰዓቱ ደርሷል፤ አሁን የጌታ ስም ብቻ ነው ለሙሴ የሚያስፈልገው ብቸኛ መሣሪያ።



በእሥራኤል ሕዝብ ነጻ መውጣት ወቅት እንደ ነበረ የሚታሰበው፣ የግብፅ ፈርዖን ራምሴስ 2ኛ፣ በጠላት ላይ ድልን በመቀዳጀት ዕረፍት እንዳስገኘ የሚያመለክት በዚህ የግድግዳ ሥዕል ላይ ተመልክቷል

7፥1-5 እግዚአብሔር ሙሴን ለአሮን "አምላክ" ሲያደርገው አሮንን ደግሞ ለሕዝቡ የሙሴ "ነቢይ" አድርጎታል፤ ሙሴ በተጨማሪ ለፈርዖን "አምላክ" ሆኖ በመሾሙ ከሰማይ በሆነ ሥልጣንና ኀይል ይናገራል፤ ያደርጋልም፤ አሮንም የሙሴ "ነቢይ" በመሆን ለፈርዖን መልእክት ያደርሳል (ከ4፥15-16 ጋር ያነጻ)። ይሁን እንጂ አሁን ይሄ ቡድን የፈርዖን ልብ "ደንዳና" እንደሚሆን ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶታል (በ4፥21 የተሰጠውን ማብራሪያ ይመ)፤ ምንም እንኳ እግዚአብሔር በቸርነቱ በምልክቶችና በድንቆች ደጋፊ ማስረጃ ቢሰጠውም የፈርዖን ልብ ይደነድናል። ሆኖም እግዚአብሔር ግብፅን "በኀይል ፍርድ" ከቀጣት በኋላ እስራኤል "በየክፍሉ" ይወጣል።

"እኔ እግዚአብሔር" የሚለውን ስሜን እስራኤላውያን ብቻ ሳይሆኑ ግብፃውያንም ጭምር ያውቃሉ። እነዚህ ታምራት ግብፃውያን የዚህን ስም (በዕብራይስጥ ያህዌ የሚባለውን) ታላቅነት እንዲያውቁ የቀረበላቸው ግብዣም ነው። በመሆኑም ግብዣው ጠንከር ብሎ በተደጋጋሚ ነው የቀረበላቸው (7፥5፤ 8፥10፡ 22፤ 9፥14፡ 16፡29፤ 14፥4፡ 18፡- አንዳንዶቹ በግልጥ አምነዋል፤ ምክንያቱም ግብፅን ለቅቆ የወጣው "ድብልቅ ሕዝብ" ነውና።

መ. ፍርድና ማዳን በመቅሠፍቱ አማካይነት (7፥6-11፥10)

1. የመለኮትን ሥልጣን የሚያስረግጡ ምልክቶችን ማቅረብ (7፥6-13)

6-9 ከሰማንያ ዓመታት ዝግጅት በኋላ ሙሴ የሕይወቱን ተልእኮ ሥራ ጀመረ። እርሱና አሮን ዳግም ወደ ፈርዖን ፊት እንዲቀርቡ በሚል ሰበብ ታምራት እንዲያደርጉ ይጠይቃቸዋል።

የሚያስገርመው ፈርዖን በእግዚአብሔር ስም ለቀረበለት ጥያቄ የማረጋገጫ ምልክት መጠየቁን እንደ ተገቢ ጥያቄ መቍጠሩ ነው። እግዚአብሔር ለሙሴ የእግዚአብሔር መልእክትኛ መሆኑን ለማረጋገጥ በእስራኤል ፊት ያደረጋቸውን የመጀመሪያዎቹን ሦስት ታምራት እንዲያደርግ ነገረው (4፥2-9፡ 30-31 ይመ)። ይሁንና በዚህ ጊዜ የአሮን በትር (ከሙሴ በትር ጋር ወይም ከእግዚአብሔር በትር ጋር ተመሳሳይ ነው፤ 4፥17፤ 7፥15፡ 17፡ 19-20)፣ በጣላት ጊዜ ወደ ዘንዶነት ተለወጠች (በግሪክ "ታኒን"፤ "ትልቅ እባብ" "ዘንዶ" ወይም "አዞ"፤ በ4፥3-4 "እባብ" (በግሪክ "ናሻ") ሆነች ይላል። "ታኒን" የሚለው ስም የግብጽ ምልክት ከመሆኑ ጋር ያለው ዝምድና በመዝ 74፥13 እና ሕዝ 29፥3 ላይ በግልጽ ተቀምጧል።

10-13 ሙሴና አሮን በትክክል እግዚአብሔር እንዳዘዛቸው አደረጉ፤ ይሁን እንጂ የፈርዖን ጠቢባንና አስማተኞች በድብቅ መተታቸው ተመሳሳይ ነገር ሲያደርጉም አዩ። በግብፅ አስማት ይደረግ እንደ ነበር በዊስትካር የብራና ጽሑፍ በሚገባ ተዘግቧል፤ ጽሑፉም አስማተኞቹ ከሰም የተሠሩ አዞዎችን ወደ እውነተኛ አዞዎች ይለውጧቸውና ጅራታቸውን ሲይዟቸው ተመልሰው የሰም አዞ እንደሚሆኑ ይተርካል።

አሮን በሠራቸው ታምራትና ጳውሎስ በ2ኛ ጢሞ 3፥8 ላይ የጠቀሳቸው ኢያኔስና ኢያንበራስ በሠሯቸው ታምራት መካከል ያለውን ግንኙነት መግለጽ አስቸጋሪ ነው። ምናልባት ምትሃታዊ በሆነ ማስመሰል የአባቦችን ዐንገት ተጭነው እንዳይንቀሳቀሱ በማድረግ እንደ በትር ይዘዋቸው ገብተው አጭበርብረው ይሆናል። ወይም ደግሞ በኢጋንንታዊ ኀይል ነው ይህን ያደረጉት። ይሁን እንጂ የእግዚአብሔርን ኀይል ታላቅነት ለማሳየት የፈርዖን አስማተኞች "በትሮች" በአሮን በትር "በመዋጣቸው" "ያለበትር" ቀሩ። ይሁን እንጂ ፈርዖን ፍንክች አላለም። ልቡ "ደነደነ።"

2. የመጀመሪያው መቅሠፍት የውኃው ወደ ደም መለወጥ (7፥14-24)

14-18 በማለዳ ተነሥቶ ከወንድሙ ከአሮን ጋር በመሆን ፈርዖንና ባለሟሎቹ ወደ አባይ ወንዝ ሲሄዱ ሊገናኙት እንዲወጣ እግዚአብሔር ሙሴን አዘዘው (ቍ 20 ያነጻ)። ፈርዖን ለምን ጉዳይ ወደ አባይ እንደሚሄድ አይታወቅም፤ ምናልባት "ሀፒ" በመባል የሚታወቀውን የአባይን ወንዝ አምላክ ለማምለክ ይሆናል። ይሁንና ሙሴና አሮን "የዕብራውያን አምላክ እግዚአብሔር" እንደ ላካቸው ሊያስታውሱት ነበር በዚያ የተገኙት (5፥1)፤ ሆኖም የግብፅ ንጉሥ በእግዚአብሔር ትእዛዝ ላይ በማመፁ ጸና። ስለዚህ የእግዚአብሔርን ማንነት ማወቅ ይችል ዘንድ እግዚአብሔር ፈርዖንን ሊረዳው ፈቀደ (ከ5፥2 ጋር ያነጻ)። ሙሴ በበትሩ ሲመታው እግዚአብሔር የአባይን ወንዝ ወደ ደም ይለውጠዋል።

19-21 አሮን ግብፃውያን እንደ ቅዱስ ወንዝ በሚቈጥሩት አባይ ላይ በትሩን አንሥቶ በመታው ጊዜ ወንዙና በመላው ግብፅ የሚገኘው ውሃ ወደ ደም ተለወጠ። "ደመ" ምንድን ነው? አንዳንድ ምሁራን እንደሚጠቀሙት ሁሉም መቅሠፍቶች ተፈጥሯዊውን ዑደት የተከተሉ በመሆናቸውና ሁሉም በአንድ ዓመት ውስጥ የተፈጸሙ በመሆናቸው የመጀመሪያው መቅሠፍት በሐምሌና በነሐሴ ከልክ በላይ ሞልቶ የሚፈስሰው የአባይ ጕርፍ ነው። የአባይ ጕርፍ መነሻ የአባይን ወንዝ ጕርፎ እንዲያጥለቀልቅ የሚያደርገው የምድር ወገብ አካባቢ ዝናብ ነው። ይህ ዝናብ ከማእከላዊ ምሥራቅ አፍሪካ (ያሁኗ ኡጋንዳ) በመነሣት በምሥራቃዊ ሱዳን ረግረጋማ ቦታዎች በማለፍ፣ ከተራሮች እየቀለጠ የሚወርደው በረዶ ያቀለመውን ቀይ ዐፈር ተሞልተው በኀይል ከሚጕርፉት ጥቁር አባይና የአትባራ ወንዞች ጋር ይቀላቀላል። ጕርፉ ኀይለኛ በሆነ መጠን የወንዙ ቀለም ይቀላል። ከዚህ የመቅለም ሁኔታ በተጨማሪ ፍላጅሌትስ በመባል የሚታወቅ "አልጌ"፣ ከሱዳን ረግረጋማ ቦታዎችና በነጭ አባይ ካለው ከጣና ሐይቅ በመነሣት መጥፎ ሽታ ከማስከተሉም በላይ የውኃውን የኦክስጅን መጠን በጣም በመቀነስ ለዐሦቹ መሞት ምክንያት ይሆናል። የመጀመሪያው መቅሠፍት ምክንያት ይህ በእግዚአብሔር ትእዛዝ የሚፈጸም ሂደት እንጂ የውኃውን ኬሚካላዊ ንጥረ ነገር በመቀየር ወደ ነጭና ቀይ የደም ሴሎች ስለ ለወጣቸው የሆነ አይመስልም። (ከኢዮኤል 2፥31 ጋር ያነጻ "ጨረቃ ወደ ደም" ይለወጣል፤ ወይም 2ነገ 3፥22፣ ውሃው "እንደ ደም ቀልቶ" እንደ ታያቸው ይናገራል)። ከተፈጥሮ ሂደት ጋር በተስማማ ሁኔታ ይህ መቅሠፍት እንደ ሌሎች መቅሠፍቶች በድንገት ባንዳፍታ አልቆመም። ይህ ለውጥ "ምንጮችን" (ሰባቱን የአባይ ቅርንጫፎች (ሔሮዱተስ)፣ የመስኖ መውረጃ ቦዮችን፣ ሐይቆችን (የአባይ ሙላት የፈጠራቸውን) እና ሰው ሠራሽ የውኃ ማቈሪያዎችን ሁሉ ከጥቅም ውጭ አድርጓል።

22-24 አሁን የፈርዖን አስማተኞች "ድብቅ ጥበባቸውን" በመጠቀም ታምራቱን በሚገባ በመኰረጅ የፈርዖንን ልብ እስከ ማደንደን ደርሰዋል። አራቱም የግብፅ የውሃ መገኛ ምንጮች በሙሉ የተበከሉ ከሆነ (ቍ. 19፣21)፣ ንጹሕ ውኃ ግብፃውያን ከየት አገኙ የሚለው ጥያቄ በቍጥር 24 ላይ ምላሽ አግኝቷል፡- የአባይን ዳር ይዘው ከቈፈሯቸው ዐዳዲስ ጕድጓዶች። ፈርዖን ግን ከአቋሙ ፍንክች ሳይል ደም ከመሰለው ወንዝ ዳርቻ ወደ ቤተ መንግሥቱ ተመለሰ፡- ይህ ማስረጃ ቢሰጠውም በግትርነቱ ገፋበት፤ ልቡም ደነደነ።

3. ሁለተኛው መቅሠፍት፡- ንጉንቸሮች (7፥25-8፥15)

25-8፥5 የመጀመሪያው መቅሠፍት በጀመረ በሰባተኛው ቀን እግዚአብሔር ሙሴንና አሮንን ጥያቄያቸውን ይዘው ወደ ንጉሡ ቤተ መንግሥት እንዲቀርቡ አዘዛቸው። ወደ ምድረ በዳ ሄደው እግዚአብሔርን ያመልኩት ዘንድ እንዲፈቅድላቸው ላቀረቡት ተደጋጋሚ ጥያቄ መልሱ እምቢታ ከሆነ፣ "አገርህን ሁሉ በንጉንቸር መቅሠፍት እመታዋለሁ" የሚለውን ኀይለ ቃል ያስታውቁታል። ይህኛው "ምልክት" ሳይሆን "መቅሠፍት" ብቻ ነው። ቀጥሎ ሊመጣ ካለው ጋር ሲነጻጸር ይህኛው ትንሽ ችግር ብቻ ነው።

6-7 በአሮን ምልክት ሰጪነት ንጉንቸሮች ከውኃ አካላት ሁሉ ውስጥ እየወጡ ምድሪቱን "ሸፈኗት"። እነዚህ አስቸጋሪ ፍጥረታት በግብፃውያን እንደ ቅዱስ ነገር ቢቈጠሩም፣ ግብፃውያንን ወደ ሕያው አምላክ ፊት ለማቅረብ እግዚአብሔር እንደ አለንጋ ተጠቅሞባቸዋል። የፈርዖን ጠንቋዮች በአስማታቸው በችግሩ ላይ ችግር ቢጨምሩም ንቆ ትታቸዋል። እውነቱ ቍጥር ስፍር የሌላቸው የሚያንቋርሩ በደረታቸው የሚሳቡ መልክ-ጥፉ ወራሪዎች አገር ምድሩን መመላታቸው ነው።

8-15 ንጉንቸሮችም በነሐሴ ወር ጢም ብሎ የሞላውን ተፈጥሯዊ መኖሪያቸውን አባይን ባንዳፍታ ለቅቀው መኖሪያ ቤቶችን፣ መኝታ ቤቶችን፣ ምድጃዎችን፣ ቡሃቃዎችንና ቤተ መንግሥቱን ጭምር የወረሩት ለምንድን ነው? ደግሞስ

ለምንድን ነው በድንገት የሚሞቱት? ምናልባት ንጉንቸሮቹ የተበከሉትንና ካፍ እስከገደፋቸው ሞልተው የሚፈሱትን ወንዞች ትተው (ከ7፥19 ጋር ያነጻ) በመኖሪያ ቤቶች ከፀሓይ ለመጠለልና እንዲሁም ምናልባት ያልተበከለ ውኃ ለማግኘት በነበራቸው ፍላጎት ተስበው መጥተው ይሆናል። ይሁን እንጂ ቀደም ብሎ የውሃ መፋሰሶችን ተከትሎ የመጣው ሞት ያስከተለው በድን በፈጠረው ገዳይ የበሽታ ህዋስ ቀድሞውኑ የተለከፉ በመሆናቸው ንጉንቸሮች በድንገት በሞት ሊረፈረፉ ችለዋል።

በመጨረሻም ፈርዖን በጦር ሠራዊት ሳይሆን በትናንሽ አስጠሊታ የንጉንቸር ኮማንዶዎች ተገድዶ የእግዚአብሔርን ኃያልነት ለመቀበል ተገድዷል። አሁን ይሄ "እግዚአብሔር" ማን እንደ ሆነ (ከ5፥2 ጋር ያነጻ) ፈርዖን ዐውቋል፤ እናም የሙሴንና የአሮንን ጥያቄ ለመመለስ ተስማማ፡- ያው ትንሽ ቁይቶ ቢያገረሽበትም።

ለፈርዖን የጭንቅ (አንዳንዶች እንደሚሉት ራስ ወዳድ) ተማጽኖ የሙሴ ምላሽ መቼ መቅሠፍቱ እንዲቆምለት እንደሚፈልግ በመጠየቅ የሙሴን ነቢይነትና በይበልጥ ደግሞ የእግዚአብሔርን ኀይል ፈትኖ እንዲያውቅ የሚያደርግ ነበር። "ነገ" የሚለው የፈርዖን ፈጣን ምላሽ ሙሴ ጥልቅ በሆነ ምልጃ ወደ እግዚአብሔር እንዲጮኽ አደረገው። ሙሴ በራሱ መንገድ ከፈርዖን ጋር ለመደራደርና ከዚያ በኋላ እግዚአብሔር ይህንኑ እንዲደግፍለት ለማድረግ የነበረው ነጻነት አስገራሚ ነው። ንጉንቸሮቹ በሁሉም ስፍራ መረፍረፍ ጀመሩ፡- በመኖሪያ ቤቶች፣ በዕርሻ ቦታዎች እና በመስኮች ሁሉ። ንጉንቸሮች በየቦታው እንደ ኮረብታ ተከመሩ፡- ደግሞም የፈርዖንን የመርሳት ችግር እንዲያግዙ የሞቱ ንጉንቸሮች ክርፋት በአስታዋሽነት ተሰጥቶታል። ይሁን እንጂ ሽታው እየጠፋ ሲሄድ የፈርዖን እሽታም ዐብሮ ጠፋ። ይህ "የፋታ" ጊዜ ለትዕቢተኛው ንጉሥ ከመቅሠፍቱ ጊዜ ይልቅ የከፋ ነው። ምሕረቱንና ሞገሱን ሲያበዛላቸው ብዙ ጊዜ ሰዎች የእግዚአብሔርን ጻድቅነት ሳይማሩ ይቀራሉ (መዝ 78፥34-42፤ ኢሳ 26፥10)።

4. ሦስተኛው መቅሠፍት፡- ተባይ (8፥16-19)

16-17 ሦስተኛው መቅሠፍት የጀመረው ለፈርዖንም ሆነ ለአስማተኞቹ ማስጠንቀቂያ ሳይሰጣቸው ነው። አሁንም እግዚአብሔር ይህን መቅሠፍት ለመጀመር የተጠቀመው በአሮን እጅ የነበረችውን በትር በመሰንዘር ነበር። አሮን የምድሩን ትቢያ በበትሩ መታ፤ ልክ በመጀመሪያው መቅሠፍት የአባይን ውኃ እንደ መታው ዐይነት (7፥20) ከዚያም "በግብፅ ምድር ያለው ትቢያ ሁሉ ተናካሽ ትንኝ ሆነ"። "ትንኝ" የሚለው ቃል በዚህ ምንባብ ውስጥ ዐምስት ጊዜ ተጠቅሷል፤ ከዚህ ሌላ በመዝሙር 105፥31 ላይ ከሚገኘው ተጓዳኝ ምንባብ በስተቀር ቃሉ የትም አይገኝም። ይህ ቃል አንዳንድ ትርጉሞች እንደሚያስቀምጡት "ቅማል" መሆኑ፣ ወይም "ትንኝ" ወይም "የወባ ትንኝ" መሆኑ አከራካሪ ነው (ብዙ ተርጓሚዎች በዚህ ይስማማሉ)። እኛም ይኸኛውን አቋም እንደግፋለን።

18-19 የሙሴንና የአሮንን ታምራት ለአራተኛ ጊዜ ለመከሪጅ ባደረጉት ሙከራ የግብፅ አስማተኞች ሽንፈትን መቀበል ግድ ሆኖባቸዋል። የግብፅ ጠቢባን ከዚህ በፊት ያደረጓቸውን ሦስት ታምራት የመከናወንንም ሆነ ያለመከናወንንም ስሜት ቢፈጥርባቸውም (ታምራት ማድረግ የቻሉት ምናልባት ከነሙሴ አንደበት የመቅሠፍቱ ዐይነት ሲነገር ሰምተው ቀደም ብለው በመዘጋጀት በተጭበረበረ ሁኔታ ወይም ደግሞ የእግዚአብሔርን ኀይል ለመከሪጅ በሚሞክር ሙሉ በሙሉ አጋንንታዊ በሆነ ኀይል ሊሆን ይችላል)፣ አሁን ግን የተባዩ መቅሠፍት "የእግዚአብሔር ጣት" ማለትም የራሱ ኀይል ውጤት እንደ ሆነ ተገነዘቡ። ይሁን እንጂ ፈርዖን ግን በልቡም በአእምሮውም እንዲህ ዐይነት እምነት አላደረበትም፡- አሁንም በግትርነቱ ጸና፤ የእስራኤላውያንን ጥያቄም ተቃወመ።

5. አራተኛው መቅሠፍት፡- ዝንቦች (8፥20-32)

20፥21 እንደ መጀመሪያው መቅሠፍት ሁሉ፣ ፈርዖን ማልዶ ወደ አባይ ወንዝ ሲሄድ ሙሴ ወደዚያ ሄዶ እንዲያገኘው በእግዚአብሔር ተላከ። በዚህ ጊዜ ፈርዖን መላው ሕዝቡና ቤቶቻቸው በ"ዝንብ" መቅሠፍት አደጋ ደረሰባቸው። ይህን ዝንብ በሳይንሳዊ ስሙ ስቶሞክሲስ ካልሲትራንስ በመባል የሚታወቀው የዝንብ ዐይነት በሚገባ ይገልጸዋል። ይህ የዝንብ ዐይነት በሞቃታማና በወይና ደጋ የአየር ጠባይ ባላቸው አካባቢዎች በጸደይ ወቅት ቍጥራቸው ከስድስት መቶ እስከ ስምንት መቶ የሚደርስ ዕንቁላሎችን በእበትና በበሰበሱ ዕፀዋት ላይ በመጣል በከፍተኛ ሁኔታ ይራባል። የዕድገት ሂደቱን ሲጨርስ ይህ ዝንብ ቤቶችን፣ ግርግሞችን መበከል ይመርጣል። እንዲሁም ባብዛኛው የሰዎችንና የእንስሳትን የታችኛውን የሰውነት ክፍል ይነክሳል። በዚህ ዐይነት የቆላ ቍስል የሚያስከትለው ባክቴሪያ ዋነኛ አስተላላፊ ነው። ይህን በሽታ የሚያስከትለው ባክቴሪያ የሚጋባበት በዚሁ በሽታ ጦስ በሞቱ እንስሳት አካል ላይ በሚሳብበት ወቅት ነው።

22-24 እግዚአብሔር በሙሴ ሕዝቦችና በፈርዖን ሕዝቦች መካከል "ልዩነትን" ያደረገው ያለፉት ሦስት መቅሠፍቶች በአጋጣሚ ብቻ እንጂ ሌላ ምንም ምክንያት የላቸውም በሚል ልባቸውን ያደነደኑትን ግብፃውያን እውነቱን እንዲያውቁ ለማገዝ ነው። ይህ "ልዩነት" የመጣው በአራተኛው፣ በዐምስተኛው፣ በሰባተኛው፣ በዘጠነኛው እና በዐሥረኛው መቅሠፍቶች ላይ ነው። የዚህ የእስራኤልን ወገን ለይቶ በመተው ግብፅንና ሰዎቿን በመቅሠፍት የመምታቱ ዐላማ ፈርዖንንና ግብፃውያንን የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር በዚህች ምድር ውስጥ እነዚህን ሥራዎች እየሠራ መሆኑን ለማስተማርና ከአገር በቀል አማልክቶቻቸው አንዱ አለመሆኑን እንዲያውቁ ማድረግ ነው። በጥንታውያን የቅርብ ምሥራቅ ሰዎች ዘንድ አማልክት ከራሳቸው የመኖሪያ ክልል ውጭ ምንም ኀይል እንደሌላቸው ይታመናል። አሁን እዚህ ግብፅ ውስጥ እየሆነ ያለው ግን እንዲህ አይደለም። ንጹሓኑ እያመለጡ ወንጀለኞቹ ግን እየተቀጡ ነው፤ ምክንያቱም ይህ አምላክ በመካከላቸው ነውና። አሁንም ይህ አምላክ በግብፃውያን ዘንድ በእርሱ እንዲያምኑ የሚያደርግ፣ እስራኤላውያንን ደግሞ ነጻ ማውጣት የሚችል "ተአምራዊ ምልክት" ማድረግ ይችላል።

በሌላ አስደናቂ የአሠራር ጥበብ ሙሴ ቀደም ብሎ መቅሠፍቱ መቼ እንደሚመጣ በማስታወቅ ለግብፃውያን ለንስሓ ጊዜ ሰጣቸው። ይህ የቅድሚያ ማስታወቂያ የሚገኘው በአራተኛው፣ በዐምስተኛው፣ በስድስተኛው፣ በስምንተኛውና በዐሥረኛው መቅሠፍቶች ላይ ነው። በተጨማሪም ፈርዖንና ሹማምቱ ገታራ አቋማቸው ካስከተለባቸው ትልቅ ተጠያቂነት የተነሣ የመጀመሪያዎቹ የመቅሠፍቱ ገፈት ቀማሾች እንዲሆኑ ተለይተዋል።

25-32 ሙሴ እስራኤላውያን በግብፅ እንስሳትን የሠዉ እንደ ሆነ፣ በግብፃውያን ዘንድ አስጸያፊ ነው ማለቱን አንዳንድ የሥነ መለኮት ምሁራን "ጮሌነት" ብቻ ነው ይላሉ። በእንዲህ ዐይነት ሙሴ ፈርዖን እስራኤላውያን በግብፅ ምድር መሥዋዕት ያቅርቡ ብሎ ያቀረበውን ተለዋጭ አሳብ አጣጣለው። በመጨረሻው ፈርዖን ለረኸርም ጊዜ በእምቢታ ለመለሰው ጥያቄ የእሺታ መልስ ሰጠ። የራሱን ክብር በሚያንጸባርቅ ድምፀት " . . . እፈቅድላችኋለሁ . . . ነገር ግን ርቃችሁ እንዳትሄዱ" አላቸው። ከዚያም እውነተኛ ሥጋቱ ሌላ መሆኑን ለማሳወቅ የፈለገ ይመስል ፈጠን ብሎ "አሁንም ለእኔ ጸልዩልኝ" የሚል ሐረግ ጨመረበት።

ሙሴም በቀላሉ እጅ የሚሰጥ አልሆነም፤ የእርሱም ተልእኮ ክብር ያለው ነውና። እናም "እኔ" በሚል ተውላጠ ስም ጀመረ፦ "እኔ እነሆ ከእንተ እለያለሁ . . . እኔም ላንተ እጸልያለሁ" (በቁመ ሲተረጎም)። የሙሴ ግልጥ የሆነ ግሣዜ መልእክቱ "ነገር ግን" እያልህ ከእኔ ጋር ልትደራደር አትሞክር፤ የመደራደር ዐቅምህ እንዲህ ተመናምኖ ባለበት ጊዜ የሚል ነው። ወዲያው ግን በአክብሮታዊ ሦስተኛ መደብ ዕጥፍ ይልና "ብቻ ፈርዖን ሊያታልለን እንዳይሞክር" አለው።

መቅሠፍቱ በሙሴ ጸሎት ተወገደ (ከ1ነገ 18፥42፤ ከአሞጽ 7፥2፤5 ጋር ያነጻ)። በጸሎት ኀይልና እግዚአብሔር በመካከላቸው በግልጽ በመገኘቱ "አንድ ዝንብ እንኳ አልቀረም።" ነገር ግን አሁንም ደግሞ ፈርዖን (ከሁለተኛው መቅሠፍት፤ ከ8፥15 ጋር ያነጻ) የፈለገውን ፋታ ካገኘ በኋላ ወደ ተለመደው ገታራ አቋሙ ተመለሰ።

6. ዐምስተኛው መቅሠፍት፦ የእንስሳት እልቂት (9፥1-7)

1-4 ዐምስተኛው መቅሠፍት የቀረበበት መንገድ እንደ ሁለተኛው መቅሠፍት ነው፦ ሙሴ ወደ ፈርዖን ቤተ መንግሥት ሄዶ የሚቀጥለውን መቅሠፍት ምንነት ተናገረ። "አስከፊ መቅሠፍት" ይከተላል፤ የግብፅ ጠንቋዮች በ8፥19 እንዳሉት በእግዚአብሔር "ጣት" አይደለም፤ በእግዚአብሔር "እጅ" እንጂ። በመስክ ላይ ባሉት እንስሳት ሁሉ ላይ ይወርዳል። "እንስሳት ሁሉ" የሚለውን ሐረግ በመለጠጥ አንድም እንስሳ ሳይቀር ማለት ነው ብሎ መውሰድ ለሰባተኛው መቅሠፍት (ቁ 19፦25) የግብፅ እንስሳ እንደሌለ የተሳሳተ ግንዛቤ ይፈጥራል። ነገር ግን በቁ 3 ላይ በግልጥ እንደ ተመለከተው መቅሠፍቱ የወረደው "በመስክ" ባሉ እንስሳት ብቻ ነው። በመሠረቱ የግብፅ እንስሳት የሚውሉት ከግንቦት እስከ ታኅሣሥ ነው። ምክንያቱም በዚህ ጊዜ ማሰማሪያዎቹ ውኃ ስለሚያቀሩና በጣም ረግረጋማ ስለሚሆኑ ጠፈፍ እስኪሉ ይጠበቃል። በመሆኑም እንስሳቱ በከፊል ወደ ደቡብ ይሰማራሉ፤ ስለዚህ ይህ መቅሠፍት የተፈጸመው በጥር ወር ውስጥ ነው ማለት ይቻላል። እነዚህ እንስሳት ወደ መስክ ወጥተው በሁለተኛው መቅሠፍት ከሞቱት ጓጕንቸሮች ከቀረው የሬሳ ክምር ጋር ሲገናኙ ኮቴንና አፍን በሚያበሰብስ በሽታ ተመትተው ሞተዋል።

የእስራኤላውያን እንስሳት ከመቅሠፍቱ ነጻ ተደርገዋል፤ ምክንያቱ ምናልባት እስራኤላውያን የሠፈሩበት አካባቢ ዝቅተኛ በመሆኑ የአባይ ጕርፍ ሙላትና ተጽዕኖው ቀስ በቀስ ስለሚቀንስ ይሆናል። በተጨማሪም እስራኤላውያን ለሬሳ ያላቸው አመለካከት ለየት ያለ ነው፦ ከተከመረው ሬሳ ከብቶቻቸውንም ስላራቁ የገዛ እንስሶቻቸውን አትርፈው ይሆናል። ይህ እግዚአብሔር በግብፃውያንና በእስራኤል መካከል ልዩነት ያደረገበት ሁለተኛው መቅሠፍት ነው።


5-7 ዐምስተኛው መቅሠፍት እንደሚመጣ በተነገረበት ጊዜና ዐምስተኛው መቅሠፍት በሚፈጸምበት "በነገው ዕለት" በተባለው ጊዜ መካከል የጊዜ ክፍተት የተተወው ፈርዖንና ግብፃውያን የእምነት ርምጃ ለመውሰድ ቢፈልጉ ዕድል እንዲያገኙ ነው። አንዳንዶች ይህንኑ በማመናቸው ሊሆን ይችላል እንስሶቻቸውን ከመስክ ወደ ቤት በማስገባት ሊያድኗቸው ሞክረዋል። ሌሎቹ ደግሞ ሆነ ብለው እንስሶቻቸውን በመስክ አዘገዩዋቸው።

ፈርዖን የእስራኤላውያን ከብቶች በተኣምር ከመቅሠፍቱ እንዳመለጡ በሰማ ጊዜ ወራውን ለማጣራት መልእክተኞችን ወደ ጌሤም ላከ። ወራው እውነት ነበረ። ፈርዖን ለዚህ ሁሉ የራሱ የሆነ ሰበብ ሳይኖረው አይቀርም መሰል አቋሙና ልቡ ተመልሶ ደነደነ። በዚህ መሃል በርካታ የግብፅ አማልክት በመቅሠፍቱ ክፉኛ ተመቱ፦ እነዚህም "አፒስ" ወይም "ታ" በመባል የሚታወቀው ቅዱስ በሬ፤ "ራ" ጥጃው አምላክ፤ የ"ሃቶር" ላሞች፤ "አኑቢስ" ራስ-ቀበሮው አምላክ፤ እና የሜንቱ አምላክ በሬው "ቡኪስ" ናቸው።

7. ሰድስተኛው መቅሠፍት፦ ዕባጭ (9፥8-12)

8-9 እንደ ሦስተኛው መቅሠፍት ሁሉ ይህኛው መቅሠፍትም ያለማስጠንቀቂያ ነው የተላከው። ለመጀመሪያ ጊዜ በሰው ሕይወት ላይ ጥቃት ደረሰ፤ አደጋም ተደቀነ። ይህም ሊመጣ ያለውን ዐሥረኛውንና ከሁሉ ይልቅ አሰቃቂ የሆነውን መቅሠፍት የሚያመላክት ነው። ሙሴና አሮን እያንዳንዳቸው እፍኝ ዐመድ የእስራኤል ባርነት ምልክት ከሆነው ምድጃ (1፥14፤ 5፥7-19 ይመ) ወሰዱ። ዐመዱ በሆነ ዕቃ ውስጥ ተደርጎ (መሆን አለበት) ወደ ፈርዖን ፊት ከቀረበ በኋላ ሙሴ ወደ ላይ በተነው። ድርጊቱ የኋለኞች ነቢያት ያደርጉ እንደ ነበረው ትእምርታዊ ድርጊት ነበር (ኤር 19 ወይም ሕዝ 4-5)። እንዲሁም በባርነት በሚማቅቁ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ላብ (ድካም) የተፈጠረው ዐመድና በባርነት በገዟቸው ሰዎች አካል ላይ የወረደው ፍርድ አመክንዮታዊ ግንኙነት አላቸው።

10-12 ዐመዱ ወደ ሰማይ በተበተነ ጊዜ በግብፃውያን ሰዎችና እንስሳት ሁሉ ላይ የሚመግል ቊስል ወጣባቸው። ይህንን ደዌ ለይቶ ለማወቅ በተደረጉ ሙከራዎች ብዙ ግምቶች ተሰጥተዋል፦ (1) ፈንጣጣ (2) የአባይ ቊስል ከኩፍኝ ጋር የሚመሳሰል፤ (3) የቆላ ቊስል (4) ከንዳድ ጋር ተያይዞ በመላው አካል ላይ የሚዛመት የማይድን ክፉ ቊስል ነው። ይህ አራተኛው ዐይነት የማይድን ቊስል ነው የሚለው ግምት ሚዛን የሚደፋ ይመስላል፤ በዘዳግም 28፥35 ይህ ደዌ በዋናነት ታችኛውን የሰውነት ክፍል እንደሚያጠቃ ይናገራልና። በተጨማሪም ጥቊሩ ዐመድ በተለይ ጠቄር ካለ፤ ከሚለበልብ በእንስሳት ላይ ከሚወጣ መግል ጋር ይመሳሰላል።



ኮርማው፤ የግብፃውያን ዋነኛ እንስሳ ሲሆን፤ በግብፅ ከደረሱት ልዩ ልዩ መዓቶች መካከል አንዱ ገጥሞታል። ይህ የሚያመለክተው ግብፃዊ ሰው ኮርማውን እየመራ ሲሄድ ነው።

አራተኛው መቅሠፍት ያስከተላቸው ዝንቦች በጥቅሉ ለዚህ ቊስል መዛመት እንደ ምክንያት ይጠቀሳሉ፤ ይሁን እንጂ ዝንቦቹ ያ መቅሠፍት እንዳበቃ ፈጽሞ ተወግደዋል። መገመት የሚቻለው ይህ የዝንብ መንጋ ከዚያ በኋላ የተፈለፈለ መሆኑን ነው (እንደ አየሩ ጠባይ ምቹነት ሌላ የዝንብ መንጋ ከ27 እስከ 37 ቀናት ሊደርስ ይችላል)። ሰዎች ወይም እንስሳት በእነዚህ ዝንቦች እግራቸውን ሲነክሱ ትንሽ ጥቊር ቡናማ መግል የያዘ ዕብጠት ከሁለት ወይም ከሦስተ ቀናት በኋላ ይፈጠራል። የቊስሉ መሃል ይደርቃል፤ ይሁን እንጂ ወዲያው ዐዳዲስ ቊስሎች ይፈጠራሉ፤ የሰውነት ቈዳም በእሳት ተለብልቦ እንደ ተላጠ ያህል ያፈከፍካል።

በሚያስቅ ሁኔታ ቁ.11 ጠንቋዮቹ (ለመቅሠፍት ሁለት እጅ ከሰጡ በኋላ ትኩረት ያላገኙት፤ ምንም እንኳ በመቅሠፍት አራትና ዐምስት የተገኙ ሊሆን ቢችልም) በሙሴ ፊት (በሙያቸውም ሆነ) በአካል “ሊቆሙ አልቻሉም”። ይሄ በሁሉም ግብፃውያን ላይ የደረሰ ነው ማለት ይቻላል። በዚህ ቦታ ለመጀመሪያ ጊዜ እግዚአብሔር የፈርዖንን ልብ እንዳደነደነ ይገልጻል፦ በቀደሙት መቅሠፍቶች በእያንዳንዳቸው ፈርዖን ያደረገውን የሚደግፍ በሚመስል ሁኔታ።

8. ሰባተኛው መቅሠፍት፦ የበረዶ ናዳ (9፥13-35)

13-19 በመጀመሪያውና (7፥15) በአራተኛው (8፥20) መቅሠፍት እንዳደረገው ሁሉ ሙሴ ይህን ተልእኮ ለመፈጸም ማለዳ ተነሥቶ የእግዚአብሔርን መልእክት ለፈርዖን ማድረስ ነበረበት። ከየካቲት መባቻ አንሥቶ እስከ ዐሥረኛው አሠቃቂና የመጨረሻ መቅሠፍት ድረስ ፈርዖን በግምት ስምንት ያህል የሕይወቱን የመጨረሻ አስከፊ ሳምንታት አሳልፏል።

የእነዚህን ሳምንታትና ክሥተቶች ሥነ መለኮታዊ ትርጉም ይበልጥ ለማጕላት እግዚአብሔር ለሙሴ ቀሪዎቹን መቅሠፍቶች አስመልክቶ መለኮታዊ ማስጠንቀቂያ ከመስጠቱ በፊት ረዘም ያለ ትምህርተ መለኮታዊ መልእክት አቅርቦለታል። ይህ ቀዳሚ የሌለው ትምህርት ፈርዖንንና ከፈርዖን አገዛዝ ሥር የነበሩትን ሁሉ ዐመፃቸውን ትተው የዕብራውያንን አምላክ ወደ ማመን እንዲመጡ የታቀደ ነበር። ከበድ ካሉት መልእክቶች መካከል (1) በምድር ሁሉ እርሱን የሚመስል አምላክ እንደሌለ ማንም እንዳይጠራጠር “የመቅሠፍቱን ዐይነት” (“ቀሪዎቹን መቅሠፍቶች ሁሉ”) በግብፅ ላይ እንደሚያወርድ የሚያስጠነቅቅ መግለጫ፤ (2) ከፈርዖን ዐመፃ የተነሣ በመላው ዓለም የእግዚአብሔር ኀይልና ዝና ይታወቅ ዘንድ እግዚአብሔር ሆነ ብሎ በማለፉ ምክንያት እንጂ ቀደም ብለው በግብፅ የወረዱት መቅሠፍቶች የግብፅን ንጉሥና ሕዝቦቹንም ጭምር ከምድር ገጽ ጠራርጎ ሊያስወግዳቸው ይችል እንደ ነበር የሚገልጽ ማስታወሻ፤ (3) እስራኤልን አልለቅም ማለቱ ፈርዖን ሁሉን በሚችል አምላክ ላይ ማመፁ መሆኑን ማሳወቅ፤ (4) ግብጽ በታሪክ አይታ የማታውቀው እጅግ አስከፊ የበረዶ መቅሠፍት እንደሚወርድባት ማስጠንቀቅ፤ (5) አስገራሚ በሆነ ሁኔታ የሙሴን ቃል ያመኑት ግብፃውያን ከበረዶው መቅሠፍት የሚያመልጡበትን መንገድ ማዘጋጀት ናቸው።

ሰባተኛው መቅሠፍት የእምነትንና የመታመንን በረከት ሊያስከትል ይችላል ተብሎ የተጠበቀ ፍርድ ነበር። አብርሃም “ለምድር ሁሉ አሕዛብ” በረከት የመሆን ተልእኮ ተሰጥቶት አልነበረምን (ዘፍ 12፥3)? በእነዚህ መቅሠፍቶች ሁሉ ውስጥ “ግብፃውያን እኔ አምላክ እንደ ሆንሁ ያውቁ ዘንድ” የሚለው ሐረግ (ከመለስተኛ ለውጦች ጋር) በተደጋጋሚ ተጠቅሶ የለምን (7፥5፤ 8፥10፤ 9፥14፡ 16፡ 29-30፤ በኋላ ላይ 14፥14፡18)? ሙሴ እንደ አምላኩ ሁሉ በእስራኤል አለመታዘዝ ምርር ብሎት (ዘኍ 14፥11)፦ “ይህ ሕዝብ እስከ መቼ ይንቀኛል? እነዚህን ሁሉ ተኣምራዊ ምልክቶች በመካከላቸው አድርጌም እስከ መቼ ሊያምኑብኝ እምቢ ይላሉ?” ብሎአል ይህን መሰል አባባል ስለ ግብፃውያንም ማለት ይቻላል።

የትዕግሥቱ ወራት ሊያበቁ ተቃርበዋል። አሁን ቀጥለው የሚመጡት መቅሠፍቶች በሙሉ ኀይላቸው በቀጥታ በፈርዖን ላይ የተነጣጠሩ ናቸው (ቁ 14፤ አመት “በአንተ. . . ላይ እመጣብሃለሁ”)። “በአንተ ላይ” የሚለው ሐረግ በአካሉ ላይ ማለት ሳይሆን ይልቁን በውስጣዊ ማንነቱ፣ በባሕርዩና በደንዳና ልቦናው ላይ ማለት ነው። የዐዳዲሶቹ መቅሠፍቶች መዓት ሲወርድበት በግራ መጋባትና በመጠን የለሽ የነፍስ ሰቆቃ እስራኤላውያን ከፊቱ እንዲወጡ ተማጸናቸው። ሆኖም የእግዚአብሔር ሐሳብ ፈርዖንን እንደ ገበጣ ጠጠር እንደ ፈለገ በጕልበት ሊያሸክረክረው አልነበረም፤ የመቅሠፍቱ ጫና ፈርዖንም በግሉ እግዚአብሔርን ወደ ማወቅ እንዲመጣና አቻ የለሽ ማንነቱንና ታላቅነቱን እንዲያምን ማድረግ ነበር። የእግዚአብሔር አቻ የለሽ ሥራዎቹ “ወርዶ የማያውቅ” በረዶ (ቁ. 18፥24፤ የአንበጣ መንጋ 10፥6)፦ ንጉሡንና ሕዝቡን የእግዚአብሔርን አቻ-የለሽ ማንነት (“እንዳንተ ማን አለ?” 15፥11 እና “አንደ እኔ ያለ ማንም እንደሌለ” 9፥14) እንዲያውቁና እንዲመሰክሩ ሊያደርጋቸው ይገባ ነበር።

20-26 በላይኛው ግብጽ ዝናብ ዐልፎ ዐልፎ የሚዘንብ በመሆኑ ነጐድጓድና በረዶ የቀላቀለ የጥፋት ዝናብ ይዘንባል የሚለውን ማስጠንቀቂያ በብዙ ጥርጣሬ እንደ ተቀበሉት መገመት ይቻላል። የአባይ ደለላማ (ረባዳማ) አካባቢ ብቻ ነው በዓመት እስከ 10 ኢንች የሚደርስ ዝናብ የሚያገኘው፤ የግብፅ የላይኛው አካባቢ የሚያገኘው የዝናብ መጠን በዓመት አንድ ጫማ ቢሆን ነው፤ ባብዛኛው ምንም ዝናብ የማያገኝ ነው። ነገር ግን አንዳንዶቹ “የእግዚአብሔርን ቃል ፈርተው” ተገቢውን ርምጃ ወስደዋል። ከግብፃውያን አንዳንዶቹ የሙሴን ቃል በርግጥም ከእግዚአብሔር ከራሱ የመጣ ቃል እንደ ሆነ አድርገው ለቅቆ የወጣው “ድብልቅ ሕዝብ” ክፍል ሆነዋልና (12፥38 ይመ)።

በግልጽ እንደሚታየው ሙሴ አሁን ዐይናፋርነቱንና በራስ ያለመተማመን መንፈሱን የተወ ይመስላል፤ አሁን በትሩንና እጁን የሚያነሣው እሱ ነውና (በመጀመሪያዎቹ ሦስት መቅሠፍቶች አመራሩን የያዘው አሮን ነበር፦ ከ7፥19-20፤ 8፥6፡17 ጋር ያነጻ)። ካልተጠበቀ መብረቅና በመሬት ላይ ከሚሽከረከር የእሳት አሎሎ ጋር የተቀናጀ የበረዶ መዓት በግብፅ ምድር ሆኖ የማያውቅ እጅግ አስደንጋጭና አስደናቂ ትእይንት ነበር። ውድመቱ ወደር የለሽ ነው። ከቁጥር 24-25 ብቻ “ኮል” (“ሁሉ”) የሚለው ቃል ዐምስት ጊዜ ተጠቅሷል። ይሁን እንጂ “ሁሉ” የሚለው ቃል በ“ግነት” ዘይቤ የተጠቀሰ እንጂ በቁመ- የሚወሰድ አይደለም። ምክንያቱም የመጀመሪያዎቹ ሁለት “ሁሉ”ዎች (“በምድሪቱ ሁሉ” ቁ. 24-25ሀ፤ “በመላው ግብፅ”) ወዲያውኑ እስራኤላውያን የሚኖሩበትን የጌሤምን ምድር የማይጨምር መሆኑን ይገልጻሉና። የበረዶው ናዳ እያንዳንዱን ዛፍ፣ ቡቃያና፣ በሜዳ የሚገኘውን ፍጥረት ሁሉ ባያጠፋም እንኳ በጣም ጨካኝ የሆነን ሰው ልብ እንኳ ሊያንበረክክ እስኪችል አሳዛኝ ነበር።

27-30 ፈርዖን ደንዳናው ልቡ መንበርከኩን በሚያመለክት ሁኔታ፦ “በድያለሁ” ብሎ ተናዟል፤ “አሁንስ” በሚል ቃል ኀፍረቱን ለመሸፈን ቢያስቀድምም። ይህንን መቅሠፍት ከሌሎቹ መቅሠፍቶች የሚለየው ምንድን ነው? ከአሠቃቂነቱ በቀር። እግዚአብሔር ፈርዖንን ሲጐዳው ብቻ ነው (ለጊዜው ፋታ ለማግኘት) ሊፈልገው የሚነሣው (ከመዝ 78፥34 ጋር ያነጻ) ። እንደ ኤርምያስ (ኤር 12፥1)፤ ፈርዖን “እግዚአብሔር” (ማለት ያህዌ) ትክክል ነው፤ እኔና ሕዝቤ ግን ስተናል! ብሎ ተናገረ።

የሙሴ ምላሽ ቀላል፣ መተማመን የሞላበትና ጨዋ ነበር። የራሱ ሕዝብ ጋ እንደ ደረሰ እጆቹን ለጸሎት ወደ ላይ ይዘረጋል (ወደ እግዚአብሔር የመለመንና የአቤቱታ ምልክት ነው)፤ በረዶውና መቅሠፍቱም ያበቃል፦ ምድርና ሞላዋ የእግዚአብሔር እንደ ሆነች ይታወቅ ዘንድ (ይሄ ተደጋጋሚ “የወንጌሉ” መልእክት ኀይለ ቃል (አዝማች) ነው። “ነገር ግን” ሙሴ ቀጠለ፤ “ነገር ግን አንተም ሆንህ ሹማምትህ አሁንም ቢሆን እግዚአብሔርን እንደማትፈሩ ዐውቃለሁ።”

31-35 በግብፅ ተልባ የሚዘራው በጥር ወር መጀመሪያ፣ የሚያብበው ደግሞ ከሦስት ሳምንት በኋላ፣ ገብስም በነሐሴ ተዘርቶ በየካቲት ስለሚታጨድ መቅሠፍቱ በየካቲት ወር መጀመሪያ ወይም አጋማሽ ከወረደ እነዚህ ሁለት ምርቶች ከፍተኛ ውድመት ሊደርስባቸው ይችላል (የአባይ ወንዝ የሞላበት ጊዜ በመሆኑ ከተለመደው የመከር ወቅት ትንሽ ዘግየት ይላል)። ስንዴና አጃም በነሐሴ ወር የሚዘሩ ቢሆንም፣

ለዐጨዳ የሚደርሱት ግን በመጋቢት ወር መጨረሻ አካባቢ ነው። የጌሤም ምድር በዚህ መቅሠፍት ያልተጐዳበት ምክንያት ከግብርናዊ ምልከታ ጋር ስምም ነው። የሜዲተራንያን ወይና ደጋማ አካባቢ ይህን መሰሉን ጎይለኛ ዝናብ የሚያገኘው በጸደይ ማብቂያና በበልግ መባቻ እንጂ ከጎዳር እስከ መጋቢት ባለው ጊዜ አይደለም። ተልባ ብዙ ዐይነቶች ያሉት ሲሆን የተልባ እግር ልብሶችን ለመሥራት ያገለግላል። ታኒስና አካባቢው ለተልባ ምርት የሰጠ ነው። ገብስ ለጠላ ጠመቃ የሚውል ምርት ነው። (ጠላ በግብፅ የተለመደ የመጠጥ ዐይነት ነው)፤ እንዲሁም ለፈረስ መኖነትና በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ በሚገኙት የጎብረተ ሰብ ክፍሎች ለምግብነት ያገለግላል።

የሙሴ ጸሎት መልስ ካገኘ በኋላ ፈርዖን ኑዛዜውንና ጥፋተኛነቱን ማመኑን ረስቶ አሁንም ቃሉን አጠፈ።

9. ሰምንተኛው መቅሠፍት፡- የአንበጣ መንጋ (10፥1-20)

1-2 ለመጀመሪያ ጊዜ የፈርዖን ሹማምትም እንደ ፈርዖን ልበ ደንዳና እንደ ሆኑ ቃሉ ይናገራል። በመሆኑም እግዚአብሔር የሁሉንም ልብ አደነደነ። ነገር ግን ከዚህ መለኮታዊ የልብ ማደንደን ሥራ ውስጥ ሙሴ የሚማረው ነገር ነበር። ቀጥሎ የሚመጣው፣ እንግዲህ ሌላው ነገረ መለኮታዊ መቅድም ነው፤ ልክ በስምንተኛው መቅሠፍት ለፈርዖን እንደ ተደረገለት ዐይነት እንዲሁም በ9፥14-16 ከሰባተኛው መቅሠፍት በፊት እንደ ተሰጠው ዐይነት ትምህርት ለፈርዖን ይሰጠዋል።

እስራኤል ከዚህ የምትማረው ትምህርት ሁለት ዕጥፍ ነው፡- (1) እግዚአብሔር ግብፁያንን እንዴት "ጽኑ ቅጣት" እንደ ቀጣቸውና ታምራቱን በግብፅ ምድር እንዳደረገ ለሚመጣው ትውልድ እንዲያስተምሩ፣ እና (2) በዚህም እስራኤል በእግዚአብሔር እንድታምን ማድረግ ነው።

3-6 ሙሴ ወደ ቤተ መንግሥት አምርቶ የሚቀጥለውን መቅሠፍት አሳወቀው። መልእክቱ በጥያቄ ነው የሚጀምረው፡- "ራስህን በፊቴ ለማዋረድ እስከ መቼ እምቢ ትላለህ?" በቁ 9፥27 ፈርዖን ያደረገው ራስን መኰነንና ራሱን እጅግ ማዋረዱ ተውኔት ብቻ እንጂ ለካስ የምር አይደለም። ነገር ግን አሁን እግዚአብሔር ዐንገተ ደንዳና ጎጢአተኞችን ሁሉ የሚጠይቀውን የጥያቄዎች ሁሉ ጥያቄ፣ የመጨረሻ ጥያቄ ያቀርባል፡- "እስከ መቼ?"

የእስራኤል መለቀቅ ጥያቄ አሁንም ከበቂ የማሰላሰያና የንስሓ ጊዜ ጋር ሙሴ ለፈርዖን ቀረበለት፡- "ነገ በአገርህ ላይ አንበጣዎችን አመጣለሁ" አለው። ኢዩኤል 2፥25 አንበጦችን "ታላቁ ሠራዊቴ" ብሎ ይጠራቸዋል። ማንኛውንም የለምለም ተክል ትሩፍ ጥርግርግ አድርገው በመቀርጠፍ ምድሪቱን ውድማ ያደርጋሉ። ግብፅ ከዚህ ቀደም አይታ የማታውቀው ከፍተኛ ቊጥር ያለው የአንበጣ ወረራ ነው። ከዚያም ሙሴና አሮን ጀርባቸውን ለፈርዖን ሰጥተው (ከመደበኛው ፕሮቶኮል ወጣ ባለ አቀራረብ) ወጥተው ሄዱ።

7-11 የፈርዖን ሹማምት የሙሴን "እስከ መቼ" ኰርጆው ለራሳቸው "እስከ መቼ" ተጠቀሙበት። ለንጉሣቸውና ለሀገራቸው ካላቸው ታማኝነት ሙሴን ያወገዙት ቢሆንም፣ በሌላ በኩል ለፈርዖን ግትርነት ትዕግሥታቸው እየተሟጠጠ መምጣቱ ግልጽ ነው። ይሄ ሙሴ የሚባል ሰው በእነርሱ ላይ እያጠመደ ያለውን "ወጥመድ" ፈርዖን አላየ ይሆን? ግብፅ ፈጽማ ልትወድም እንደ ደረሰች አላስተዋለ ይሆን? አንዱ ወገን መሸነፍ አለበት። ፈርዖን በጀ ይል ዘንድ ግድ አሉት፡- "ሰዎቹን ልቀቃቸውና ይሂዱ" ብለው ተማጸኑት።

አሁንም ለመጀመሪያ ጊዜ ፈርዖን አሁን ሊመጣ ያለውን መቅሠፍት አስመልክቶ ለመደራደር ሙሴና አሮንን ወደ ቤተ መንግሥት አስጠራቸው። በፍርሀት ውስጥ የሚገኙትን ሹማምቱን ለማረጋጋት በሚመስል ሁኔታ ፈርዖን በተከፈለ ልብ ሙሴ እስራኤልን ይዞ ወደ ምድረ በዳ ወጥቶ መሥዋዕት ያቀርብ ዘንድ ፈቀደ። ይሁን እንጂ (የሙሴን የመጀመሪያ ጥያቄና የራሱ ባለሟሎች ያቀረቡለትን ጥያቄ ወይም ምክር የዘነጋ ይመስል) "ለነገሩ እነማን ናቸው (ወደዚህ ሃይማኖታዊ ጉዞ) የሚሄዱት?" የሚል ጥያቄ አቀረበ። ሙሴ እየተጠናከረ የመጣውን የአቋሙን ጥንካሬ በሚገልጽ ሁኔታ "እኛ ሁላችንም ይህን በዓል ለአምላካችን እናደርግ ዘንድ እንሄዳለን" (ቊ.9 ጋር ያነጻ) ብሎ መለሰ። "አይይ! ሁላችሁማ አትሄዱም!" ብሎ ፈርዖን ጣልቃ ገባ። "ወንዶቹ ብቻ ሂዱ፤ ለሃይማኖታዊ ሥርዐቱ ይሄ በቂ ነው።" በርግጥም ይሄ እውነትነት አለው፤ በኋላ ላይ እስራኤል በዓመት የምታከብራቸውን ሦስት ሃይማኖታውያን በዓላት ወንዶች ብቻ ናቸው እንዲሳተፉበት የተጠየቀው (23፥17፤ 34፥23፤ ዘዳ. 16፥16)። ይህ የፈርዖን ማዕቀብ ቅንነት የጐደለው መሆኑን የሚያጋልጠው በግብፃውያን ሃይማኖታውያን በዓላት ላይ ሴቶች የሚገኙ መሆኑ ነው።

ፈርዖን ለሙሴ ጥያቄና ለእግዚአብሔርም ጭምር ያለውን ንቀት በቊጥር 10 ላይ ከተጠቀሰው የሰላ ምፀቱና ስውር ዛቻው መገንዘብ ይቻላል፡- "እናንተን ከሚስቶቻችሁና ከልጆቻችሁ ጋር ስለቅ (የለቀቅሁ እንደ ሆነ) እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ይሁን (እግዚአብሔር ይሁናችሁ)!" ለፈርዖን ሙሴና ሕዝቡ የሆነ ተንኰል እንዳሰቡ ገብቶታል። ፈርዖን ለዚህ ለዘብ ያለ የመጀመሪያ ደረጃ ጥያቄ እሺ አላለም፤ የመጨረሻውን ጥያቄ (ወቅቱ ገና ምን እንደሚሆን ባያውቅም) በመፍራት። ሙሴና አሮን ከፈርዖን ፊት እየተገፈታተሩ እንዲወጡ ተደረጉ፡- ይህም ዐዲስ ዐይነት የተንኰል ድርጊት ነው።

12-15 እናም መቅሠፍቱ ይቀጥል ዘንድ ሙሴ እንደ ገና እጁንና በትሩን በግብፅ ላይ ዘረጋ። በጣም ቀዝቃዛ የሆነው የኢትዮጵያ ክረምት ከፈጠረው የተትረፈረፈ ሰብል ላይ የተነሣው የአንበጣ መንጋ በሱሳ ወደብና ጂዳ (በቀይ ባሕር ምዕራባዊ ክፍል፣ በአረብ ባሕረ ሰላጤ) ከሚገኘው ተፈጥሯዊ የመራቢያ ቦታ ሙሉ ቀንና ሙሉ ሌሊት የነፈሰው ነፋስ ጠርጎ አስወገዳቸው (ከ14፥21 ጋር ያነጻ)። እናም ይህ የአንበጣ መንጋ (በመስከረም ከተጣሉት ዕንቁላሎች በክረምቱ የተፈለፈሉት አንበጦች አሁን በየካቲትና በመጋቢት ወደ ሌላ ቦታ ለመሰደድ ዝግጁ ናቸው) ከዐረብ ባሕረ ሰላጤ በሚነሣው "ሲሮኮ" በተሰኘ ሞቃታማ ነፋስ እየተገፋ ወደ ግብፅ ዘመቱ። ነፋሱ ከደቡብ ምዕራብ ቢሆን ኖሮ፣ የአንበጣው መንጋ ወደ ከነዓን ነበር የሚዘምተው። እጅግ በከፋና በጠነከረ ሁኔታ ነው የመጡት። ከበረዶው የተረፈውን ማናቸውንም ነገር እምሽክ አደረጉት።

16-20 ፈርዖን በፍጥነት ሙሴንና አሮንን አስጠራ፤ በ9፥27-28 እንዳደረገው ምንም ዐይነት ማስተባበያ ሳያስቀምጥ በእግዚአብሔርና በእነዚህ ሰዎች ላይ የሠራውን ኀጢአት ተናዘዘ። ነገር ግን አሁንም የበላይነቱ የእርሱ እንደ ሆነ አስመሰለ፡- "እንግዲህ አሁን" አለ የሙሴን ማጠቃለያ ንግግር የሚያቀናጅለት በሚመስል አገላለጽ "አንድ ጊዜ ደግሞ (ለመጨረሻ ጊዜ) ኀጢአቴን ይቅር በሉኝ።" ከእንግዲህ ወዲህ አሳቡን አይቀይርም! ከእንግዲህ ወዲህ አያታልላቸውም! እግዚአብሔርን ብቻ ለምኑልኝ አላቸው በልምምጥ ዐይነት "ይህንን ቀሣፊ መቅሠፍት እንዲያስወግድልኝ።"

አሁንም አንድ ተጨማሪ ዕድል በመስጠት እግዚአብሔር ለሙሴ ጸሎት በቸርነቱ መልስ ሰጠ። እግዚአብሔር ጠንካራ "የባሕር" ነፋስ ላከ፤ ይህ ነፋስ ለከነዓን ሰዎች ቢሆን "የምዕራብ ነፋስ" ይሆን ነበር፤ በግብፅ ላሉት ግን የሰሜን ወይም የሰሜን ምዕራብ ነፋስ ነው። እናም እግዚአብሔር ይህን ነፋስ ልኮ የአንበጣውን መንጋ ቀይ ባሕር ውስጥ ዶለው። ይሁንና የቤተ መንግሥቱ ምላሽ እንደ ከዚህ ቀደሙ ነበር።

10. ዘጠነኛው መቅሠፍት፡- ጨለማ (10፥21-29)

21-23 እንደ ሦስተኛውና እንደ ስድስተኛው መቅሠፍቶች ሁሉ፣ ዘጠነኛው መቅሠፍት ያለምንም የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ሙሴ እንደ ገና እጁን ሲዘረጋ በወርኀ መጋቢት ወረደ። በርግጥ እግዚአብሔር ለዚህ መቅሠፍት በየዓመቱ የሚከሠት "ካሚዝን" ትርጉሙ "ዐምሳ" ቀን ነፋስ በመባል የሚታወቅ ክሥተት ተጠቅሟል። ካሚዝን ከሠሃራ በረሓ፣ ከደቡብና ከደቡብ ምዕራብ በመነሣት ኢኩዋኖክስ በመባል በሚታወቀው ቀኑና ሌሊቱ እኩል በሚሆንበት የጸደይ ወቅት የሚነፍስ ነፋስ ነው። በመጀመሪያዎቹ ሁለት ወይም ሦስት ቀናት ነፋሱ በታላቅ ኀይል በመንፈስ የአሸዋና የአቧራ ብናኝ ይዞ ይነሣል። ካፍ እስከ ገደፉ ሞልቶ ይፈስ የነበረው የአባይ ወንዝ ተሸክሞት የመጣው ቀይ ዐፈር በየዕርሻ ቦታው የከመረው ደለል፣ በረዶውና የአንበጣው መንጋ ዐፈሩን ቁንጥጠው ሊይዙ የሚችሉትን ዕፀዋት ድምጥማጣቸውን በማጥፋታቸው ዐፈሩ እርቃኑ ተጋልጧል፡- ይሄ ካሚዝን ተራ ካሚዝን አይደለም። ይህ የተበከለ አየር በጣም "ከመወፈሩ" የተነሣ "አንዱ ሌላውን ማየት አይችልም ነበር"፣ ፀሓይም "ለሦስት ቀናት" ጠፍታ ነበር። እስራኤል ግን ከዋዲ ቱሚላት በስተ ደቡብ በሚገኙ ኩረብታዎች ከአጨላሚው ነፋስ ተጋርዳ ነበረ። በተጨማሪም በጌሤም የነበሩት ዕርሻዎች ከአባይ ጕርፍ ተጽዕኖ የሚያገግሙት ዘግይተው በመሆኑ ቀዩ ዐፈር ክው ብሎ ባለመድረቁ አቧራ ሊያስነሣ አይችልም።

24-29 ፈርዖን አሁን በድርድሩ መቀጠል ፈለገ፡- እስራኤል ከቤተ ሰቦቻቸው ጋር ለዚህ በዓል አከባበር መሄድ ይችላሉ፣ ነገር ግን እንስሶቻቸውን ትተው መሄድ አለባቸው። ሙሴ ፍንክች አላለም። "አንድ ሰኮና እንኳ አይቀርም" አለ አስረግጦ፣ እግዚአብሔርን ለማምለክ ያስፈልጓቸዋልና። ይህ በዓል ፍጹም ዐዲስ በዓል ነው፣ ምን መልክ እንደሚኖረው ገና አልተገለጠም በማለት ሙሴ ማብራሪያ ሰጠ። ፈርዖን አሁን ትዕግሥቱ ተሟጠጠ። በቀጣ ከፊቱ እንዲጠፉ አዘዘ፣ ዳግመኛ ፊቱ ቀርበው ደስታውን ቢያጨልሙ በሞት እንደሚቀጡ ዛተባቸው። ነገር ግን ፈርዖን ይህን ማድረጉ ተጨማሪ መቅሠፍት እንዳይመጣ ይከላከላል ብሎ አምኖ ይሆን? ሦስተኛው፣ ስድስተኛውና ዘጠነኛው መቅሠፍት ያለምንም ማስጠንቀቂያ መጥተው አልነበረምን? የሞት ሽታ በእልፍኙና በመላው ግብፅ እየናኘ ባለበት በዚህ ጊዜ ፈርዖን ሙሴን ትሞታለህ ብሎ ማስፈራራቱ እንግዳ አይደለምን?

11. ዐሥረኛው መቅሠፍት፡- የበኵሮች መቀሠፍ (11፥1-10)

1-3 እነዚህ ጥቅሶች እንደ ተጨማሪ ማብራሪያ የገቡ ናቸው። ምክንያቱም ሙሴ በ10፥29 ከተጠቀሰው ከዘጠነኛው መቅሠፍት በኋላ ከፈርዖን ፊት ከመውጣቱ በፊት አንድ የመጨረሻ መልእክት ማቅረብ ነበረበት፣ በዚህ ዐይነት ፈርዖን ከእንግዲህ በፊቱ አትቆምም (ከ10፥28 ጋር ያነጻ) የሚለውን ማስጠንቀቂያ የምሩን እንደ ተናገረ ገብቶታል ማለት ነው። ዘጠነኛውን መቅሠፍት አስመልክቶ ሙሴ ፈርዖንን ለማነጋገር ሲገባ እግዚአብሔር ይሄ ግጥሚያ በድንገት ሊያበቃ እንደ ተቃረበ አሳውቆታል። ከአንድ ተጨማሪ መቅሠፍት በኋላ ፈርዖን እስራኤልን ይሸኛል "ለራስ ልጅ ለመዳር የታጨችን ባሪያ ልጃገረድ ነጻ አውጥቶ በመስደድ ዐይነት" (ይህ ትርጉም የNIV (የዐመት) ትርጉም "ሲለቃችሁም. . ." ከሚለው በተሻለ ሁኔታ ለዕብራይስጡ ፍቺ የቀረበ ነው።) ይህም ማለት ከባርነት ነጻ ስትወጣ ከብዙ ስጦታ ጋር ነው ማለት ነው። ይህ ትርጉም እስራኤላውያን ከግብፁያን የወርቅና የብር ጌጣጌጥ የጠየቁበትን አግባብ ግልጽ ያደርገዋል። ግብፁውያን አስገራሚ ቸርነት ያደረጉላቸው በሚከተሉት ምክንያቶች ነው፡- 1ኛ) እግዚአብሔር በግብፁውያን ፊት "ሞገስ" ስለ ሰጣቸው (ከመዝ 106፥46 ጋር ያነጻ)፣ እና 2ኛ) "ሙሴም እጅግ የከበረ ሰው" ስለ ነበረ ነው። የሙሴ ታላቅነት በራሱ ማንነት (ልሂቅነት) ላይ የተመሠረተ አልነበረም፣ ይልቁን ከአስማተኞቹ (8፥18-19)፣ ከፈርዖን ቤተ መንግሥት ሹማምት (9፥20፤ 10፥16) እና ከፈርዖን ከራሱ (9፥27፤10፥16) በተደጋጋሚ በሠራቸው ድንቆች ካስማቸው ዝና የተገኘ ነው።

4-8 የሙሴ ንግግር በ10፥29 ላይ ከተናገረው የሚቀጥል ነው። ከሌሎቹ መቅሠፍቶች ለየት ባለ መልኩ በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር ራሱ በግብፅ ምድር ያልፋል። የግብፁውያን ቤተ ሰቦች፡- ባሮችና እንስሳት፡- በሙሉ በኵሮቻቸው በእኩለ ሌሊት ይሞታሉ (ትክክለኛው ቀን አልተጠቀሰም)። ከዚህ በፊት ሆኖ የማያውቅ ታላቅ ልቅሶ በግብፅ ይሆናል፣ በእስራኤላውያን ዘንድ ግን ያ ሌሊት ውሻ እንኳ የማይጮኽበት ጸጥታ የሰፈነበት ይሆናል! የሙሴ የመጨረሻ ቃሉ ግብፁውያን በጕልበታቸው ተንበርክከው እስራኤላውያንን ፈጥነው እንዲወጡላቸው ይማጸኗቸዋል የሚል ነው። ሙሴም "ከዚያም በኋላ እወጣለሁ" አለ። ይሁን እንጂ ከሰው ግትርነትና ኀጢአተኛነት የተነሣ ይህ ሁሉ ኪሣራና የሰው ሕይወት መቀጠፍ ሙሴን በእጅጉ አበሳጨው።

9-10 ስለዚህ ከምዕራፍ 7፥8 ጀምሮ ሙሴ ያደረገውን ድርድር ጠቅለል አድርገን ስንመለከት፣ ሁሉም እግዚአብሔር በተናገረው መሠረት እንደ ተፈጸመ እንገነዘባለን። ምንም ዐይነት ማስረጃ የፈርዖንን ደንዳና ልብ ሊያንበረክከው አልቻለም፣ እስራኤልም እስካሁን በባርነት ነው ያለው።

ሠ. የፋሲካ በዓል (12፥1-28)

1. ለፋሲካ በዓል መዘጋጀት (12፥1-13)

1-2 የፋሲካ በዓልና የቂጣ በዓል እስራኤል ገና በግብፅ እያሉ የተሰጡ ሁለቱ ብቸኛ ትእዛዛት ናቸው። "በግብፅ እንዲህ አላቸው" የሚለው ሐረግ የዚህ ምዕራፍ ይዘት የተጻፈው ከግብፅ ከወጡ በኋላ መሆኑን ያመለክታል። ይህ ክሥተት እጅግ ትልቅ ስፍራ የተሰጠው ከመሆኑ የተነሣ ሃይማኖታዊው የእስራኤል የቀን ቁጠራ ከእንግዲህ ወዲህ በአቢብ ወር ይጀምራል (13፥4)። ይህ ወር "ገብስ የሚያብበት" ነው። (የከነዓናውያን አቢብ የሚለው ስም ከዚህ ጋር የተገናኘ ነው)። ወደ በኋላ ላይ በምትኩ ኒሳን በሚለው በባቢሎናውያን ወር ስም ተተክቷል (አስቴር 3፥7)። ይህም በአሁኑ የዘመን አቈጣጠር ከመጋቢት መገባደጃ እስከ ሚያዝያ መባቻ (ነህምያ 2፥1) ያለው ጊዜ ነው።

3-11 ቀጥሎ የተሰጡት መመሪያዎች በሸማግሌዎች አማካይነት ነው (ቍ. 21 ይመ) "ለመላው የእስራኤል ማኅበረ ሰብ" የደረሱት፡- (1) ዝግጅቱ በአቢብ ወር በአስረኛው ቀን መጀመር ይኖርበታል፣ (2) የእያንዳንዱ ቤተ ሰብ አባወራ በቤተ ሰቡ አባላት ቍጥር መሠረት "ጠቦት" ያዘጋጃል፣ (3) እንስሳው ነውር የሌለው የአንድ ዓመት ተባዕት ጠቦት መሆን አለበት፣ (4) እያንዳንዱ እንስሳ በ14ኛው ቀን አመሻሽ ላይ ይታረዳል፣ (5) በእንስሳቱ ደም የእያንዳንዱ ቤት ደጃፍ መቃንና ጕበን ይቀባል (6) በዚያን ምሽት እያንዳንዱ ቤተ ሰብ የተጠበሰውን ጠቦት ከመራራ ቅጠልና ካልቦካ ቂጣ ጋር ይበላዋል (7) እንስሳው ጭንቅላቱና እግሮቹ ሳይለያዩ፣ የታጠበ ሆድ ዕቃው በውስጡ ሆኖ ይጠበሳል፣ ጥሬ ወይም ቅቅል ሥጋ መብላት የለባቸውም፣ (8) ምንም ነገር ተርፎ በስብሶ እንዳይሸት ወይም ለከንቱ ምልኪ እንዳይውል (በ23፥18፤ 34፥25፤ ዘዳ 16፥24 መሠረት ከንጋት በፊት)፣ ትራፊው ሙሉ በሙሉ መቃጠል ይኖርበታል፣ (9) ይህን ራት በጥድፊያና በመጠባበቅ መንፈስ ሊበሉት ይገባል። በመሆኑም ልብሳቸውን ለብሰውና ባጭር ታጥቀው፣ ጫማቸውን ተጫምተው፣ በትራቸውን ይዘው ለእንቅስቃሴ ዝግጁ መሆን አለባቸው።

በዚህ ዐይነት መላው የእስራኤል ሕዝብ የካህናት መንግሥት ይሆናል (19፥5-6 ይመ፤ ከ1ጴጥ 2፥5፤ ከራእይ 1፥6 ጋር ያነጻ)። በ2ኛ ዜና 30፥17-18 እና 35፥5-6 የተገለጸው የሌዋውያን ጣልቃ ገብነት ከእግዚአብሔር የመጀመሪያ የፋሲካ በዓል ዕቅድ ጋር የሚዛረር ነው። በዚህ በመጀመሪያው ፋሲካ ካህናት አልነበሩም፤ መሠዊያ አልነበረም፤ የመገናኛው ድንኳን አልነበረም፤ ቤተ ሰቦች በእግዚአብሔር ፊትና በእነርሱ በእያንዳንዳቸው ምትክ ሊሠዋ ባለው ጠቦት ዙሪያ ጎብረት ያደርጋሉ። ጠቦቱ የአንድ ዓመትና ተባዕት መሆን ነበረበት፤ ምክንያቱም ወጣትና በአፍላ የሕይወት ዘመናቸው ላይ የሚገኙት የእስራኤል በኵር ወንዶች ምትክ ስለሚሆን ነው። መራራው ቅጠል መራራ የሆኑትን የባርነት ዓመታት እንዲያስታውስ የታሰመ ነው (1፥14)፤ አፍለኛው ቂጣ በዚያች የመጀመሪያ ምሽት የነበረውን ጥድፊያ ያስታውሳል። ይህ የእግዚአብሔር ፋሲካ ነው፤ እስራኤላውያንም የፋሲካን እራት ሊበሉ የሚገባቸው በእንዲህ ዐይነት ሁኔታ ነው።

12-13 በዚያው ሌሊት በአቢብ ወር በ15ኛው ቀን፣ እግዚአብሔር በግብፅ ምድር ሁሉ ያልፋል፤ በደሙ ካልተቀጠሩት ቤተ ሰብ ከሰው እስከ እንስሳ የተወለደውን በኵር ሁሉ ይገድላል። እንደ ቀደሙት ፈርዖን እንዳያቸው "ምልክቶች" እና "ተኣምራት" ሁሉ ደሙ የእግዚአብሔር ምሕረት ዋስትና ነው። እግዚአብሔር የደም ምልክት ያለባቸውን ቤቶች ሁሉ "ያልፋቸዋል"፤ ምንም ዐይነት "መቅሠፍት" አያገኛቸውም። በርግጥም በዚህ በመጨረሻው የእግዚአብሔር መቅሠፍት "የግብፅ አማልክት ሁሉ" ይፈረድባቸዋል። በግልጽ እንደሚታወቀው ወኪሎቻቸው በእንስሳት የተመሰሉት የግብፅ አማልክት የእግዚአብሔርን ቅጣት በቀጥታ ተቀብለዋል፦ በሬዎች፣ ላሞች፣ ፍየሎች፣ ቀበሮዎች፣ ወዘተ። ይህ በግብፅ አማልክት በራሳቸው ላይ በቀጥታ የወረደ መቅሠፍት ነው ብሎ ለመተርጎም እምብዛም የሚያጠራጥር አይደለም።

2. የቂጣ በዓልን ለማክበር መዘጋጀት (12፥14-20)

14-16 በፋሲካ በዓልና በቂጣ በዓል መካከል የጠበቀ ግንኙነት ቢኖርም ልዩነት ግን አላቸው። ብሉይ ኪዳን ሁለቱንም ስያሜዎች አንድን በዓል ለመግለጽ ይጠቀምበታል "የፋሲካ በዓል" በዘፀ 34፥25፤ በሕዝ 45፥21 እና "በቂጣ በዓል" በዘዳ 16፥16፤ በ2ዜና 30፥13፡ 21፤ በዕዝ 6፥22። ይሁንና ሁለቱ የተለያየ የአከባበር ሥነ ሥርዐት አላቸው፦ የቅደም ተከተል ቢሆንም እንኳ፦ በዘሌ 23፥5-6፤ ዘኍ 28፥16-17፤ 2ዜና 35፥1፡17፤ ዕዝ 6፤ ሕዝ 45፥21።

"ይህን ቀን" የሚለው ሐረግ ከቁ 1-13 የተገለጸውን በዓል የሚመለከት ነው። የአቢብን ወር ዐሥራ አራተኛውንና ዐሥራ ዐምስተኛውን ቀን የሚለየው የፋሲካ በግ የሚታረድበት ሌሊት ከግብፅ የወጡባትን ያቺን ሌሊት በማሰብ የሚደረግ ነው (ያም የፋሲካ ሌሊት ነው፤ አቢብ 15)። እስራኤላውያን ያንን ቀን "እንዲያከብሩት" (የመታሰቢያ በዓል እንዲያደርጉ፤) "ቋሚ" እና "ዘላቂ" ሥርዐት አድርገው እንዲያከብሩት ታዘዋል።

ለሰባት ቀናት "እርሾ የሌለበት ቂጣ" ይበላሉ (ዕብ ማትዘ፤)፣ ይህም እስራኤል ከግብፅ በጥድፊያ የወጣበትን ሁኔታ ለማስታወስና (ቁ 39) እንዲሁም (አንዳንዴ በእርሾ የሚመሰለው) የሕይወት ንጽሕና መጓደል ሰዎችን ለመንፈሳዊ አገልግሎት ብቁ እንዳይሆኑ እንደሚያደርጋቸው በአጽንዖት ለመግለጽ ነው። መላው ቤተ ሰብ ንጹሕና ቅን ልብ እንዲኖረው ያስፈልግ ነበር፤ ስለዚህ ማንኛውም ዐይነት እርሾ ሁሉ ከቤት ውስጥ ሊወገድ የግድ ነው (ቁ 19)። የፋሲካን በዓል ማክበር የሚጀመርባቸው የዚያ ሳምንት የመጀመሪያው ቀንና ሰባተኛው ቀን የተቀደሱ ቀናት ይሆናሉ።

17-20 "ሰራዊታችሁን ከግብፅ ምድር ያወጣሁት" የሚለው ሐረግ ከፀአት ማለት ከመውጣት በኋላ የተነገረ መሆኑን ያመለክታል። ቍጥር 19 ቁ 14 ባዶ ክለሣ ብቻ አይደለም። ይልቁን ቀደም ብሎ በአብርሃማዊው ኪዳን (ዘፍ 12፥3) እንደ ተተነበየው አሕዛብ ከእስራኤል ጋር ዐብረው በዓሉን የሚያከብሩ መሆኑን የሚያስታውስ ነው። "መጻተኞች" ቁ 38 "ድብልቅ ሕዝብ" የተባሉትን ከግብፅ ዐብረዋቸው የወጡትንና በኋላም በምድረ በዳ የተቀላቀሏቸውን ቁናውያንን (ዘኍ 10፥29-31፤ መሳ 1፥16)፤ ደግሞም በኋላ ላይ የተለወጡትን ረዓብንና ቤተ ሰቧን (ኢያሱ 2፥10-14) እንደሚጨምር ይታመናል። "የአገር ተወላጅ" የተባሉት ያለ ጥርጥር የአብርሃም ዘሮች ሲሆኑ፣ በዚህ ቦታ የከነዓን ምድር እውነተኛ ዜጎች ተብለዋል ምክንያቱም እስራኤል ከግብፅ ከመውጣታቸው ከስድስት መቶ ዓመት ቀደም ብሎ እግዚአብሔር ለእነርሱ ሰጥቷቸዋልና።

3. የፋሲካን በዓል ማክበር (12፥21-28)

21-23 ለፋሲካ እንዴት መዘጋጀት እንደሚያስፈልግ መመሪያ ተሰጥቶ ካበቃ በኋላ ለእስራኤል ቤት አለቆች እያንዳንዱ ቤተ ሰብ ምን ሊያደርግ እንደሚገባ ዐጭር መግለጫ ተሰጣቸው። በዚህ ቦታ ሁለት ዐዳዲስ ነገሮች ተጠቅሰዋል (1) "በጭብጥ የሂሶጵ ቅጠል" በሳሕን ውስጥ ካለው ደም ተነክሮ በእያንዳንዱ ቤት ጕበንና በር ላይ ይቀባ እና (2) ማንም ሰው "እስኪነጋ ድረስ" ከቤቱ አይውጣ የሚሉ ናቸው።

በእያንዳንዱ ቤተ ሰብ የሚታረደው በግ ወይም ጠቦት ራሱ "ፋሲካ" የሚል ስያሜ ተሰጥቶታል (አመት "የፋሲካ በግ" ይለዋል።) ከዚህ እንስሳ የተወሰደው ደም በሳሕን ውስጥ ይቀመጥና በ"ጭብጥ የሂሶጵ ቅጠል" እየተነከረ በበሩና በጕበኑ ላይ "ይቀባል"። በዚህ ዐይነት እስራኤል ነጻ የመውጣታቸውንና የመቤገታቸውን መሠረትና መንገድ ያውቃሉ።

"ቀሣፊው" የእግዚአብሔር ተቀናቃኝ የሆነ ጋኔናዊ ኀይል አይደለም፤ ምናልባት የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያስፈጽም የእግዚአብሔር መልአክ ሳይሆን አይቀርም። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር በግብፃውያን ላይ ቍጣውን ለመግለጽ አራት የተለያዩ ቃላትን በሚጠቀምበት በመዝ 78፥49 ላይ የዚህ ቍጣው ጥቅል መጠሪያው "አጥፊ የመላእክት ሰራዊት" የሚል ነው። እናም መልአኩ የመካከለኛነት ሚና ይኑረው ወይም እግዚአብሔር በግብፅ ላይ ያወረደውን የመጨረሻውን ፍርድ በሰውኛ ዘይቤ ለመግለጽ ያገልግል፤ ዞሮ ዞሮ ነገሩ የእግዚአብሔር ቀጥተኛ ሥራ ነው (ከ1ቆሮ 10፥9-10፤ ዕብ 11፥28 ጋር ያነጻ)።

24-28 በድጋሚ የዚህን ዓመታዊ ሥርዐት አፈጻጸምና ሥርዐቱ ወደፊት በየዓመቱ በሚደረግበት ወቅትም ትርጉሙንና ፋይዳውን አስመልክቶ ወላጆች ለልጆቻቸው የማስረዳት ግዴታ እንዳለባቸው ይናገራል። ይህ ክፍል የሚደመድመው በእስራኤል ታሪክ ውስጥ ብርቅዬ ከሆኑት አባባሎች አንዱን በመጥቀስ ነው፦ እስራኤላውያንም እግዚአብሔር እንዳዘዛቸው ልክ እንደዚያው አደረጉ። በርግጥ ይህን ቢያደርጉ እምብዛም ላያስደንቅ ይችላል፤ በዐመፀኞቹ የግብፅ ንጉሥ እና ሕዝቦቹ ላይ የደረሰባቸውን አይተዋልና!

ረ. ስለ ግብፅ መውጣት (12፥29-51)

1. ምት በእኩለ ሌሊት (12፥29-32)

29-30 የመጨረሻው ምት የተሠነዘረው በአቢብ ወር በ15ኛው ቀን እኩለ ሌሊት ላይ ነው። ከዚህ ቀደም የተፈጸሙት መቅሠፍቶች አንዳንድ ተፈጥሯዊና ሁለተኛ ደረጃ ተፈጥሯዊ ነገሮችን በመጠቀም የተከናወኑ ሲሆኑ ቁ 23 እና 29 ይህን ዐሥረኛውን መቅሠፍት በቀጥታ በእግዚአብሔር ብቻ እንደ ተከናወነ ይገልጻሉ። እግዚአብሔር በግብፅ ምድር ዐለፈ፤

ሞትም እያንዳንዱን "ቤተ ሰብ" (በቁሙ "ቤት") ጐበኘ፡- ከፈርዖን አንሥቶ በእስር ቤት እስካለው እስረኛ ድረስ (ከ11፥5 *ጋር ያነጻ*)።

31-32 ፈርዖን ሙሴንና አሮንን እንዴት "እንዳስጠራቸው" አይታወቅም። ለእስራኤል የተሰጠው ፈቃድ እግዚአብሔርን ለማምለክ የሦስት ቀን ጕዞ ከማድረግ የበለጠ ነበር። ከዚህ ቀደም ፈርዖን እንዲወጡ ሲፈቅድላቸው (ወዲያው ሐሳቡን ቢቀይርም፤ ወይም ደግሞ ተቀባይነት የሌለው ማዕቀብ ቢጥልም) "ሂዱ፤ አምላካችሁን እግዚአብሔርን አምልኩ" (10፥8፣24)፣ ወይም "ሂዱ፤ ለአምላካችሁ ሠዉ" (8፥25)፤ ብሏቸው ነበር። አሁን ግን ትእዛዙ "ተነሡ! ከሕዝቤ መካከል ውጡ!" በርግጥ እግዚአብሔር ቀደም ብሎ ከዘሥረኛው መቅሠፍት ጽናት የተነሣ ፈርዖን ". . . አንዳችሁን ሳያስቀር ይለቃችኋል" (11፥1) ብሎ ነበር። ሙሴ ንጉሡንና ምድሪቱን ተሰናብቶ ሲወጣ ፈርዖን አንድ የመጨረሻ ጥያቄ አቀረበ። "ባርከኝ" ብሎ ለመነ። ፈርዖን፣ የግብፅ አምላክ የሆነው ፈርዖን፤ የሙሴ አምላክ ይባርከው ዘንድ ተማጸነ!

2. ከግብፅ ለመውጣት መዘጋጀት (12፥33-36)

33-34 ግብፃውያን የእስራኤል ልጆች አገራቸውን በፍጥነት ለቀው እንዲወጡ ቍጣ በተቀላቀለበት ትእዛዝ አጣደፏቸው። ምክንያቱም ነገሮች እስካሁን እየሆኑ ባሉበት ሁኔታ ከቀጠሉ፣ አንድም ግብፃዊ አይተርፍም ብለዋልና። ስለዚህ እስራኤላውያን ያልቦካውን ሊጥ በየቡሀ ዕቃው አድርገው ከሌሎች ከቀሯቸው ቍሣቍሶች *ጋር* በትከሻቸው ተሸከሙ።

35-36 ግብፃውያንን እንዴት እንደ በዘበዟቸው 3፥21-22 እና 11፥2-3 *ይመ.*

3. ከግብፅ መውጣትና ድብልቁ ሕዝብ (12፥37-51)

37 የምድረ በዳው ጕዞ በትክክል የሚጀምረው ከዚህ ቍጥር ነው። *ራምሴ* በትክክል ካንቲር በመባል የሚታወቀው ቦታ እንጂ ሩቅ ነገር ግን ታዋቂ የሆነው (በሰሜናዊ ምሥራቅ 17 ማይልስ ርቀት የሚገኘው) ራምሴ አይደለም። ምክንያቱም የግብፃውያን የታሪክ ሰነዶች እንደሚገልጡት ካንቲር በውኃ አጠገብ "የራ ውኃዎች (ወንዞች)" አጠገብ ነው የሚገኘው፤ ይህም በምሥራቃዊ የናይል ወንዝ መፋሰሻ የሚገኝ ቡባስታይት ፔሉሳይክ በመባል የሚታወቅ ነው። የሱኮት አድራሻ እንደ ሆነ አሁን የሚታመነው ቦታ በዘመናይቱ እስማኤልያ አጠገብ የሚገኘው ቴል ኤል ማስኩታ ነው። ስድስት መቶ ሺሕ ተዋጊ ሰራዊት የነበራት እስራኤል የመላው ሕዝቧ ቍጥር እስከ 2 ሚሊዮን ይደርሳል።

38 "ሌሎችም ብዙ ሕዝቦች" ("ድብልቅ ሕዝብ" አመት) የተባሉት ግብፃውያን ናቸው (ከ9፥20 *ጋር ያነጻ*)፤ ምናልባት አንዳንዶቹ የሂክስ ዘመን ትሩፋን የሆኑ ጥንታውያን ሴማውያን እና የሌሎች አገሮች ዜግነት ያላቸው ባሮች ናቸው። ከእነዚህ አንዳንዶቹ በዘኍ 11፥4 የተፈጠረው ውካታ ተካፋዮች እንደ ነበሩ በርግጠኝነት መናገር ይቻላል። በዚህ ዐይነት በዘፍ 12፥3 ለአብርሃም የተገባለት ተስፋ ከእስራኤል *ጋር* ከግብፅ በወጣው የእንግዳ ሕዝብ ሰራዊት ለየት ያለ ፍጻሜ አግኝቷል። እግዚአብሔር ጎይሉን የገለጠበት ሌላው ምክንያት ግብፃውያን እግዚአብሔርን ያውቁ ዘንድ (ወንጌል ይደርሳቸው ዘንድ) ነው (7፥5፤ 8፥10፣19፤ 9፥14 ፡16 ፡29-30፤ 14፥4፡18)።

39 እግዚአብሔር በዘፀ 11፥1 አስቀድሞ እንደ ተናገረው፣ እስራኤላውያን ከግብፅ "ተባርረው ተሰደዱ"። በርግጥም እጅግ በጥድፊያ ከመውጣታቸው የተነሣ ምንም ነገር ማዘጋጀት አልቻሉም እንኳንስ ሊጣቸው ውስጥ እርሾ መጨመር ይቅርና። በመሆኑም ያልቦካ ሊጥ ይዘው መውጣት ነበረባቸው፤ ከዚሁ ሊጥ የጋገሩትን አፍለኛ እንጀራ ነው በመጀመሪያዎቹ ቀናት የተመገቡት (ቍ. 34 *ይመ*)።

40-42 በርግጥም አሁን ከግብፅ መውጣቱ ስለ ተጀመረ ተራኪው ለአፍታ ቆም ብሎ በእስራኤላውያን አጠቃላይ የግብፅ ተሞክሮ ላይ አስተያየት ይሰጣል። ሁለት ጊዜ "ልክ አራት መቶ ሠላሳው ዓመት በተፈጸመ በዚያች ዕለት" በማለት ይጠቅሳል። ያን "ምሽት" የሚመጣው ትውልድ ሁሉ "የሌሊት ዘብ በመቆም" ዐይነት ሊያከብረው ይገባል። ምክንያቱም በዚያ ምሽት እግዚአብሔር ቀሣፊው እስራኤልን እንዳይነካቸው "ጠበቀው" ወይም "አገደው"።

43-49 እነዚህን ከግብፅ አገር ከእስራኤል *ጋር* የወጡትን ለዘለቂታው ዐብረዋቸው ሊጓዙ ያሉትን "ድብልቅ ሕዝብ" አስመልክቶ ጥያቄ መነሣቱ አይቀርም። እነርሱም የፋሲካን በዓል ሊያከብሩ ይገባቸዋል? ስለዚህም ቀደም ብሎ የተነገረው መመሪያ ሊደገምና ሊብራራ አስፈላጊ ነበር።

ማንኛውም ወንድ እስካልተረገዘና የዚያ አማኝ ማኅበረ ሰብ አባል እስካልሆነ ደረስ ከፋሲካው ምግብ ሊቋደስ አይችልም። ይህ ዕቀባ ለጊዜው የተቀመጠ እንግዳና ቅጥር ሠራተኛን እንዲሁም ማንኛውንም ባዕድ የሆነ ሰው ሁሉ ያጠቃልላል። በተጨማሪም እያንዳንዱ ጠቦት (ከቍ. 3-10) በተጠቈመው መሠረት በአንድ ቤት ውስጥ መቈየት ይኖርበታል። ብልቶቹ ተከፋፍለው በተለያዩ ቤቶች ሊበላ አይገባም፤ ዐላማው የተሣታፊዎቹን አንድነትና ደስታ የሚልጽ የኅብረት መሥዋዕት እንዲሆን ነውና። እንዲሁም የፋሲካው በግ አጥንቱ አንድም ቦታ ሊሰበር አይገባም (ከመዝ 34፥20 እና ከዮሐ 19፥33-36 *ጋር ያነጻ*)። ይህ የእግዚአብሔር ፋሲካ ነው እንጂ እስራኤል ያሰናዳቸው ማዕድ አይደለም፤ ስለሆነም ለዜጎቹም ሆነ ለባዕዶቹ የተሰጠው ቅድመ ሁኔታ አንድ ዐይነት ነው።

50-51 የማጠቃለያው አስተያየት እስራኤላውያን "እግዚአብሔር ያዘዘውን ሁሉ ልክ እንዳለው አደረጉ" (ከቍ. 28 *ጋር ያነጻ*) ይላል፤ እንዲሁም "በዚያችው ዕለት" (ከቍ. 17፥41 *ጋር ያነጻ*) ከልክ በላይ ሲጓተት የነበረው ከግብፅ መውጣት እግዚአብሔር እስራኤልን "በየሰራዊታቸው" ሲያወጣቸው ፍጻሜ አገኘ። የሚያስደንቀው የምድረ በዳው ጕዞ በዕለተ ሰንበት መጀመሩ ነው!

ሰ. በሱራን ሁሉ ለእግዚአብሔር መቀደስ

(13፥1-16)

1-2 ከእስራኤል ከግብፅ መውጣትና ከፋሲካ *ጋር* በቅርብ የተያያዘው የእስራኤልን በኵራት ለእግዚአብሔር የመቀደሱ ጕዳይ ነው። በኵራትን ለእግዚአብሔር መቀደስን የሚመለከተው ትእዛዝ የተሰጠው ምናልባት እስራኤል ከግብፅ ከወጣ በኋላ የመጀመሪያ ቄይታውን (12፥37) ባደረገበት በሱኮት ሳይሆን አይቀርም። ይህም ጊዜ የቂጣ በዓልን ለማክበር ከተለዩት ሰባት ቀናት *ጋር* ተገጣጥሟል (12፥15)።

አጠቃላዩ መርሕ ማንኛውም የሰውም ሆነ የእንስሳ ወንድ (ከ12-13 *ጋር ያነጻ*) "በኵር" የእግዚአብሔር ነው፤ በመሆኑም ተራ ከሆነ ግልጋሎት ለተቀደሰ ዐላማ ለእግዚአብሔር "ይቀደሳል"። በዚህ ዐይነት እግዚአብሔር ሰባተኛውን ቀን፣ የማደሪያውን ድንኳን፣ የሌዊን ነገድ፡- በዚህ ቦታ በኵሮችን ሁሉ ለራሱ ለየ። እግዚአብሔር በኵራት ለእርሱ እንዲለዩለት የጠየቀበት መሠረቱ በግብፅ ያሉትን በኵራት በቀሠፈበት በዚያኑ ጊዜ የእስራኤልን በኵራት ለራሱ መለየቱ ነው። እግዚአብሔር እስራኤልን "በኵሬ" ብሎ ጕዲፈቻ ማድረጉ ነጻ እንዲያወጣቸው ምክንያት ሆኖታል። ከዚያን ጊዜ ወዲህ፣ ያ ያመለጠ ሕዝብ በዚያች ምሽት እግዚአብሔር ያደረገላቸውን

የፍቅር ሥራና ተኣምራት ለመዘከር የልጆቹንና የእንስሳቱን በኵር ይለያል።

3-10 ይህን በኵርን ለእግዚአብሔር መቀደስንና የቂጣ በዓል አከባበርን በሚመለከት ተጨማሪ ማብራሪያዎች ይሰጣሉ። እስራኤል ተስፋ የተገባላትን ምድር ስትወርስ ይህ በዓል በየዓመቱ ይከበራል። እስራኤላውያን ቂጣ የበሉበትንና በኵራትን ለእግዚአብሔር የለዩበትን ምክንያት ለቀጣዩ የእስራኤል ትውልድ (አማኝም) እስራኤልን ከግብፅ ባወጣ ጊዜ - "ለእኔ ብሉ" - ያደረገው ነው በማለት ለልጆቻቸው ያስረዳሉ። በተመሳሳይ ሁኔታ በቁ. 16 የሚቀጥለው ትውልድ "እኛን" ከግብፅ አወጣን ተብሎ ትምህርት ይሰጠዋል። ይህ በዓልና በኵራትን መቀደስ በሕዝቡ እጅ ላይ "ምልክት" በዐይኖቻቸውም መካከል እንደ "ማስታወሻ" ወይም "መታሰቢያ" ይሆናቸዋል። ይህ አባባል ዘይቤኣዊ ወይም ምሳሌያዊ የቋንቋ አጠቃቀም (ከምሳ 3፥3 ጋር ያነጻ) መሆኑ የሚያጠራጥር አይደለም፤ የእግዚአብሔር ሕግ "በክንፈራቸው" እንዲሆንም ታዟልና።

11-16 ቀሣፊው "በኵሮቻቸውን" እንዳለፈ እና እስራኤልም ቀይ ባሕርን "እንዳለፈች" አሁንም እነሱ ወደ ተስፋይቱ ምድር ሲገቡ በኵሮቻቸውን ለእግዚአብሔር "አሳልፈው ሊሰጡ" ይጠበቅባቸዋል። በዚህ መርሕ ላይ ሁለት አነስተኛ ማሻሻያዎች ብቻ ናቸው የተጨመሩበት፡- (1) በኵራት ወንድ ሰዎች ሁሉ (በኵራት ሴቶችን አይመለከትም) ሊዋጁ ወይም "በዋጋ ተገዝተው ሊመለሱ" ይገባል (ዋጋው ዐምስት ሰቅል ነው ዘኁ 18፥16፤ ከዘኁ 3፥46-47 ጋር ያነጻ) እና (2) አህዮች በበግ ወይም በጠቦት "ይዋጃሉ" ወይም "ይቤዣሉ"፤ ምክንያቱም አህዮች ንጹሕ እንስሳ ባለመሆናቸው መሥዋዕት ስለማይደረጉ ነው። እስራኤላውያን ይህን የመዋጀት ትእዛዝ እንዳይጥሱ ለመካለከል ያልዋጁትን እንስሳ ዐንገቱን በመስበር ይገድሉታል።

በኵሮች በቤተ መቅደሱ አካባቢ በሚሠሩ አንዳንድ ክህነታዊ ያልሆኑ ሥራዎች ይሰማሩ የሚለው ትእዛዝ በኋላ ላይ እግዚአብሔር እያንዳንዱን በኵር ወንድ ልጅ ወይም ወንድ ሰው እንዲወክሉ ሥልጣን ወደ ሰጣቸው ወደ ሌዋውያን ተሸጋግሯል (ዘኁ 3)። የሌዋውያን ቍጥር በቂ ሳይሆን ሲቀር ተጨማሪ ወንዶች እያንዳንዳቸው በአንዳንድ ሰቅል ዋጋ ተዋጅተው ሊያገለግሉ ይችላሉ። ቁ. 15-16 እንደ ገና ወደ ገለጻው ይመለሳል፡- በኵሮች የእግዚአብሔር ናቸው፤ ምክንያቱም አስደናቂ በሆነ ሁኔታ ከዐሥረኛው መቅሠፍት ታድጓቸዋል፤ ደግሞም ቀደም ብሎ "በኵሬ" ናቸው (4፥22) ብሏቸዋል።

ሸ. ጕዞ ወደ ቀይ ባሕር (13፥17-15፥21)

1. ወደ ምድረ በዳው መዝለቅ (13፥17-22)

17-18 ሦስት አማራጭ የማምለጫ መንገዶች አሉ፡- (1) ወደ ቃንጣራ የሚያቀናው ሰሜን ምሥራቃዊው መንገድ ሲሆን፣ በፍልስጥኤማውያን መሬት በኩል አድርጎ ወደ ጋዛና ወደ ከነዓን የሚወስደው፣ (2) ኔጌቭን አቋርጦ ወደ ቤርሳቤህ የሚወስደው ማእከላዊው መንገድ በቃዴስ በርኔ አጠገብ የሚገኘው ጀቤል ሃላል እና (3) ደቡብ ምሥራቃዊው መንገድ ሲሆን፣ ይህም ከዘመናይቱ እስማኤልያ በስተ ምሥራቅ አድርጎ ወደ ደቡባዊው የሲናይ ወሽመጥ የሚያመራው ነው። አቋራጭ ቢሆንም እንኳ በፍልስጥኤም ምድር በሚያልፈው መንገድ እንዳይሄዱ እግዚአብሔር እስራኤላውያንን አስጠንቅቋቸዋል፤ ምክንያቱም ከጦረኞቹ ፍልስጥኤማውያን ጋር ውጊያ ቢገጥሙ ልባቸው ዝሎ ሐሳባቸውን ቀይረው ዳግም ወደ ግብፅ ባርነታቸው እንዳይመለሱ ነው። የዚህ አባባል ትክክለኛነት የተረጋገጠው በዘኁ 14፥4 እስራኤል የጦርነት አደጋ ባንዣበባት ጊዜ ነው።

ከዚህ የተነሣ እግዚአብሔር እስራኤልን ዙሪያ ጥምጥም በሆነው "በምድረ በዳው መንገድ" ወይም "በበረሓው መንገድ" አድርጎ ወደ "ቀይ ባሕር" ወይም በተሻለ አገላለጽ "ወደ ሸምበቆ ባሕር" (ያም ሱፍ፣ የአመት ማብ. ይመ) መራቸው። እስራኤል በሲና የባሕር ወሽመጥ ምዕራባዊ ዳርቻ ወደ ኮሬብ/ሲና በሚወስደው መንገድ ሰፈሩ (ዘኁ 33፥10-11)፤ በኋላ ላይ ያም ሱፍ የሚለው ስያሜ በአቃባ ባሕረ ሰላጤ የሚገኘውን ጨዋማ ውኃ ለመግለጽም አገልግሏል (ዘዳ 1፥1፤ 1ነገ 9፥26፤ ሌሎችም)። በመሆኑም ሱፍ (የሸንበቆ ባሕር) የሚለውን ትርጉም ከቀይ ባሕር ጋር ከማገናኘት የሚከለክለን ነገር የለም።

19 በዚህ ጥቅስ በዘፍ 50፥25 ላይ ዮሴፍ የተናገረው ቃል በቃል ተደግሟል፤ "ከእናንተ ጋር" ከሚለው ጭማሪ ቃላት በቀር። በእነዚህ ምንባቦች ውስጥ እግዚአብሔር ተስፋ የገባላቸው ምድር ከእይታ ፈጽሞ የራቀች አይደለችም።

20 የኤታም ትክክለኛ አድራሻ የት እንደ ሆነ አይታወቅም። በዘኁ 33፥6 እንደ አንድ ግዛት ተጠቅሷል፤ ከሱር በረሓ ጋር አንድነት ያለው ይመስላል (ዘፀ 15፥22)።

21-22 እግዚአብሔር እስራኤላውያንን እንዴት እንደ መራቸው (ቁ. 17) አሁን ተብራርቷል። ይሄ ነጠላ "ዐምድ" (14፥24) ቀን ደመና፣ ማታ ደግሞ እሳት የሚሆነውና ምድር ላይ ሲያጠላ ከጽኑው የበረሓ ትኩሳት (መዝ 105፥39) መላውን እስራኤልን ሊሸፍን የሚችል ስፋት የነበረው፣ የእግዚአብሔር በመሓላቸው የመገኘቱ ተገላጭ ተምሳሌት ነበር። የደመናውና የእሳቱ ዐምድ "ለእግዚአብሔር መልአክ" የተሰጠ ሌላው ስም ነው፤ ዘፀ 14፥19 እና 22፥20-22 ሁለቱን እንደ አንድ ይቁጥሯቸዋልና። በርግጥ ወደ ከነዓን ሊያደርሳቸው ከፊታቸው ቀድሞ ይሄድ በነበረው መልአክ "ውስጥ" የእግዚአብሔር ስም ነበር (23፥20-23)። እርሱ "የሀልዎቱ መልአክ" ነበር (ኢሳ 63፥8-9)። ሚልክያስ 3፥1 "የቃል ኪዳኑ መልእክተኛ" ይለዋል፤ የመቅደሱ ባለቤት ከሆነው ጌታ ጋርም ያስተካክለዋል። እንግዲያውስ በግልጽ እንደሚታወቀው የዐዲስ ኪዳኑ ክርስቶስ የእግዚአብሔር የተገለጠ ክብር ወይም የብሉይ ኪዳኑ ጌታ ነው (ዮሐ 1፥14 ማብ ይመ)። በዚህ የደመና ዐምድ ውስጥ እግዚአብሔር ለሙሴ (33፥9-11) እና ለሕዝቡ (መዝ 99፥6-7) ተናገረ። ይሄ ከደመናና ከእሳት ዐምድ ወደ መልአክ፣ ደግሞ እንደ ገና ወደ ራሱ ወደ እግዚአብሔር በቀላሉ የመሸጋገሩ ሁኔታ በተመሳሳይ መንገድ ከሚቃጠል ቍጥቋጦ ወደ መልአክ እና በምዕራፍ 3 ደግሞ ወደ እግዚአብሔር በተደረገው መለዋወጥ ቀደም ብሎ የታየ ክሥተት ነው።

2. በቀይ ባሕር (14፥1-4)


1-4 "ተመልሰው" የሚለው ትእዛዝ የአቅጣጫ ለውጥንና ደግሞም ምናልባት ጊዜያዊ የጉዟቸውን መገታት ሊያመለክትም ይችላል፤ ግን በየትኛው መንገድ ሄዱ? በዘኁ 33፥7 መሠረት ፊሀሒሮት ከባል ዜፎን ተቃራኒ አቅጣጫና ከሚገዶልና ከባሕሩ መካከል ነው የሚገኘው። የፊሀሒሮት ትክክለኛ ቦታ እስካሁን አልታወቀም። የሚግዶል ("ማማ) አድራሻ ነው ተብሎ የሚታመነው አንድም በሱኮት አጠገብ የሚገኘው ሚግዶል፤ በሴቲ አይ ዘመን በተጻፈው ብራና የተገለጸው አልያም ከደቡባዊው የቢተር ሌክ ትይዩ የሚገኘው ጀቦል አቡ ሐሰን በሚባለው ከፍ ያለ ቦታ የሚገኘው የአራት ማእዘን ቅርጽ ያለው ማማ ፍርስራሽ ነው።

ፈርዖን እስራኤላውያን የመለኮት ርዳታ ተቋርጦባቸው በምድረ በዳ፣ በባሕርና፣ በረግረጋማ መሬት ተውጠው መውጫ ማምለጫ ያጡ መስሎ ታየው። ነገር ግን እግዚአብሔር ሙሴን ይህን አስቸጋሪ መንገድ እንዲይዝ በማዘዝ ለግብፃውያን አንድ ጊዜ ደግሞ አምላክነቱን (7፥17፤ 9፥14 ይመ)፣ ለእስራኤል

ደግሞ ታላቁን ኀይሉን (ቍ. 30-31) ሊያሳይ ወደደ። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ከፈርዖንና ከሰራዊቱ ክብርን ያገኛል። ፊርዖን ከእግዚአብሔር ጋር ቢስማማ ወይም ደግሞ "እስራኤላውያን ይህን ስፍራ ለቀው መሄድ የሚችሉት በበድኔ ላይ ተራምደው ብቻ ነው!" ብሎ ቢያምፅም እግዚአብሔር ክብር ማግኘቱ አይቀርም ነበር።

. . አስጠንቅቀን ነበር" ባዮቹ የሐሰት ነቢያት ቀጠሉ። በዚያች ቅጽበት የግብፁ የባርነት መከራቸው ሁሉ ተረሳ።

13-14 ለወትሮው በግልፍተኛነቱ የሚታወቀው ሙሴ በችኮላ ለቀረበውና ሚዛናዊነት ለጐደለው ለሕዝቡ ክስ በሦስት አቅጣጫ በትዕግሥት ምላሽ ሰጠ፦ (1) "አትሸበሩ"፤ (2)



5-12 እስራኤል ግብፅን ለቀው እንደ ወጡ ወዲያውኑ ፈርዖንና ሹማምቱ በኩሮቻቸውን በሞት ያጡበትን ሌሊት አስደንጋጭ ሁኔታ ወዲያ ብለው ከግብፅ ምድር "በልበ ሙሉነት" ወጥተው የተመሙትን እስራኤላውያንን ለማሳደድ ወሰኑ። የግብፅን ሰራዊት ባዩ ጊዜ እስራኤላውያን በጭንቀት ወደ እግዚአብሔር መጮኽ ጀመሩ፤ ግን ለረኻቦም ጊዜ አይደለም። ከእግዚአብሔር ይልቅ በቅርባቸው በሚገኘው ሙሴ ላይ አጕረመረሙ። "በግብፅ መቃብር ጠፍቶ ነውን?" እያሉ በከፍተኛ የምፀት ድምፅ ተሣለቁ፤ (ግብፅ በመቃብሮቿ የምትታወቅ አገር ከመሆኗም በላይ ወደ ¾ኛ የሚጠጋው መሬቷ ለመቃብር የተከለለ ነበርና)። ከዚያም "እኛ ቀድሞውኑ . "ጸንታችሁ ቁሙ" እና ማዳኑን እዩ፤ ማለትም "የእግዚአብሔርን መታደግ እዩ" "እግዚአብሔር ስለ እናንተ ይዋጋልና" እና (3) "ተረጋጉ" ማለትም እንቅስቃሴያችሁን በሙሉ አቁማችሁ "ዕረፉ" "እግዚአብሔር ስለ እናንተ ይዋጋልና"።

3. ቀይ ባሕርን ማቋረጥ (14፥15-31)

15-18 እግዚአብሔር እስራኤልን ከግብፅ አውጥቶ የከነዓንን ምድር እንደሚሰጣቸው ቃል ኪዳን ገብቶላቸው ከሆነ ሙሴና እስራኤል ልቅሷቸውን አቁመው ወደ ፊት መሄዱ ነው የሚሻላቸው። በቍ. 16 እና 17 መካከል ያለው ተቃርኖ ግልጽ ነው፦ "አንተ" ሙሴ (በአጽንዖት) በእጅህ ያለውን በትር

ተጠቀምና ባሕሩን “ክፈለው” ወይም “ገደል ፍጠር” እስራኤል በባሕሩ መካከል “በደረቅ መሬት” (የብስ) ይሻገሩ ዘንድ፤ “እኔ” (አሁንም በአጽንዖት) እግዚአብሔር (የሚያሳድዷቸውን) የግብፁያንን ልብ አጸናለሁ (ከ9፥12 ጋር ያነጻ)።

19-20 የእግዚአብሔር መልአክ ማንነት በቁ. 19 ሁለተኛ ክፍል ላይ ግልጽ ሆኗል፦ የደመናና የእሳት ዐምድ ነው (13፥22 ይመ)። ተስፋ የተገባላቸው የእግዚአብሔር ሀልዎት እውነታ በመገኘቱ ተምሳሌት (በደመናና በእሳት ዐምድ)፣ በመልአክተኛው አማካይነት (የእግዚአብሔር መልአክ) ወይም “በፊታቸው ይሄድ” በነበረው በእግዚአብሔር በራሱ (13፥21፤ ከ14፥24 ጋር ያነጻ) ተገልጸአል። ነገር ግን የእግዚአብሔር ሀልዎት “ሲመለስ” ወደ ኋላቸው ሄደ፣ ከኋላ ሆኖ እስራኤልን እንደ ደጀን ይከላከልላቸው ዘንድ። ለእስራኤላውያን ብርሃን የሆነው ለግብፁያን ጨለማ ሆነ። በማዳኑና በፍርዱ የሚገለጠው የእግዚአብሔር ክብር መንታ ባሕርይ ግሩም በሆነ ሁኔታ በዚህ ቦታ በሥዕላዊ መንገድ ተተርኳል።

21-22 ሙሴ አንድ ጊዜ ብቻ እጁን ከፍ አድርጎ በባሕሩ ላይ ሲዘረጋ እግዚአብሔር ባሕሩን “ወደ ኋላ አሸሸው” “ሌሊቱን በሙሉ ብርቱ የምሥራቅ ነፋስን” በማስነሣት (በቁ. የተተረጎመ፤ ከ15፥8 ጋር ያነጻ)። የዚህ “የቀይ ባሕር” ትክክለኛ አድራሻ አይታወቅም። ነገር ግን ከቢተር ሌክስ ደቡባዊ ጫፍ እና በስዊስ የባሕረ ሰላጤ ሰሜናዊ ጫፍ ላይ ነው የሚለው የተሻለ ግምት ነው። ይህ በእንዲህ እንዳለ ውኃው በግራና በቀኝ “ግድግዳ” ፈጠረ። ውሃው እንደ “ኮረብታ” ተቁለለ። ክሥተቱ ተፈጥሯዊ ነገሮችን ቢጠቀምም ለየት ባለ ሁኔታም (ከዘዳ 4፥32፡34 ጋር ያነጻ) የታጀበ መሆኑ የእግዚአብሔርን ሀልዎት አበክሮ ይገልጻል።

23-28 ሊነጋጋ አካባቢም እግዚአብሔር የግብፅን ሰራዊት በቅርቡ በባሕሩ መካከል በተፈጠረው ሸለቆ በኩል እስራኤልን ሲያሳድድ “ቁልቁል ተመለከተ” እና “ሽብር ላከባቸው” ይህ የእግዚአብሔር “ምልከታ” በተጨባጭ ተገለጠ። ምክንያቱም የእሳቱ ዐምድ በድንገት ስማዩን በብርሃን ስላጥለቀለቀው ሠረገሎቹ ደንብረው እርስ በርሳቸው እንዲላተሙ አድርጓቸዋልና።

በዚህ ጊዜ በሚያስፈራ ሁኔታ የሚያስገመግመው የመብረቅ ነጎድጓድና ብልጭታ፣ ዝናብና የምድር መናወጥ እጅግ ደፋሮችና እልኸኞች በሆኑት የግብፅ ሠረገሎች ላይ ከፍተኛ ድንጋጤ ፈጠረ (ከመዝ 77፥16-20 ጋር ያነጻ)። በዚሁ ውስጥ እያሉ ክፉኛ ግራ የተጋቡት ግብፁውያን ሌላ ችግር ገጠማቸው፦ እግዚአብሔር የሠረገሎቹን ጎማዎች “አወላለቀ” (ዐመት) ወይም አንዱን ከሌላው ጋር “ቁላለፈ” (ከNIV ዐመት ማብ ያነጻ)። ይህ ለግብፁውያን ከበቂ በላይ ነበር፣ እናም እስራኤልን ፈጽሞ ለመርሳት ፈቃደኞች ነበሩ፦ ነገር ግን ረፍደባቸዋል። እግዚአብሔር በቁ. 14 ቃል እንደ ገባው፣ በቁ. 27፡31 እንደ ተገለጠው፣ እና በ15፥3 በዝማሬ እንደ ተወደሰው ግብፅን መዋጋት ጀምሮ ነበር። እስራኤል ማድረግ የነበረባቸው ዝም ብለው ቆመው ድሉ ሲመጣላቸው መመልከት ነበር፤ ምክንያቱም የሙሴ እጅ ወደ ላይ ሲዘረጋ እንደ ግድግዳ የቆመው ውኃ እርስ በርሱ ተላትሞ ንጋት ላይ ቀድሞ ወደ ነበረበት በመመለስ መፍሰስ ጀምሯልና።

ፈርዖን ለዚህ ውጊያ ያሰለፈው ሰራዊትና ሠረገሎች አንድም ሳይቀር አለቁ። መዝ 136፥15 እግዚአብሔር “ፈርዖንንና ሰራዊቱን በኤርትራ ባሕር ያሰጠመ” ይላል። “መላው የግብፅ ሠራዊት” ተደመሰሰ የሚለው “እስራኤላውያንን ተከትለው ወደ ባሕሩ የገቡትን” በሚለው ሐረግ ተሰሳልሷል። ነገር ግን ያሳደዷቸው በሙሉ በርግጥ አልቀዋል፦ “አንድም እንኳ አልተረፈም።”

29-31 በዚያች ዕለት እግዚአብሔር እስራኤልን “አዳናቸው” እስራኤላውያን የግብፁውያንን ሬሳ በባሕሩ ላይ ሲንሳፈፍ ተመልክተዋልና። ከሁሉም በላይ እስራኤል እግዚአብሔር እንዴት ባለ ታላቅ ኀይል እንዳዳናቸው አዩ፤ እናም ፈሩ፤ በእግዚአብሔርና በባሪያው በሙሴም አመኑ። ምላሻቸው ቀደም ብሎ በ4፥31 የነበረው ዐይነት ነው፤ ግቡም በ9፥29-30 ተጠቅሷል “እናንተም” (በዚህ ጊዜ ግብፁውያን) “ምድር የእግዚአብሔር እንደ ሆነች ታውቁ ዘንድ . . . (እና) ትፈሩ(ት) ዘንድ ነው።”

4. መዝሙር በባሕሩ ዳር (15፥1-21)

ከቁ. 16-18 ያለው ዝማሬ በሙሴ ከተደረሱት ሦስት መዝሙሮች አንዱ ነው (ዘዳ 31፥22፤ መዝ 90 ይመ)። መዝሙሩ በግብፁውያን ላይ የተገኘው ድል መወድስ ሲሆን በተለይ እግዚአብሔር በፈርዖን ሠረገሎች ላይ ያሳየውን አስደናቂ ኀይልና የበላይነት ከፍ ባለ አድናቆት ያሞካሻል። የመዝሙሩ ትኩረት “እግዚአብሔር” ራሱ ነው (ይህ መለኮታዊ ስም ዐሥር ጊዜ ተጠቅሷል)። የመዝሙሩ አጠቃላይ ይዘት በሁለት ጭብጦች የተከፈለ ነው፦ ከቁ. 1ሀ-12፤ ወደ ኋላ በመመለስ የግብፅን ተዋጊዎች መደምሰስ ይተርካል፤ ከቁ. 13-18፣ የእስራኤልን ወደ ተስፋይቱ ምድር መግባት ወደ ፊት እያየ ይተነብያል።

እንደምንመለከተው መዝሙሩ አራት አንጓዎች (ስትሮፍስ) አሉት። እያንዳንዱ አንጓ እንደ ገና በሦስት ክፍሎች ይከፈላል።

ዘፀአት 15፦ ድል በባሕሩ አጠገብ

አንጓ ፩ ከቁ. 1ለ-5

ክፍል ሀ፦ መግቢያ፦ ቁ. 1ለ፦

“ለእግዚአብሔር እዘምራለሁ”

ክፍል ለ፦ ዕወጃ፦ ከቁ. 2-3

ክፍል ሐ፦ ትረካ፦ ከቁ. 4-5

ማጠቃለያ አነጻጻሪ ዘይቤ፦ “እንደ ድንጋይ” ቁ. 5ለ

አንጓ ፪ ከቁ. 6-10

ክፍል ሀ፦ መግቢያ፦ ከቁ. 6፦ “አቤቱ እግዚአብሔር ሆይ፦ ቀኝ እጅህ”

ክፍል ለ፦ ዕወጃ፦ ከቁ. 7-8

ክፍል ሐ፦ ትረካ፦ ከቁ. 9-10

ማጠቃለያ አነጻጻሪ ዘይቤ፦ “እንደ ብረት” ቁ. 10ለ

አንጓ ፫ ከቁ. 11-16ሀ

ክፍል ሀ፦ መግቢያ፦ ቁ. 11፦ “አቤቱ እግዚአብሔር ሆይ . . . እንዳንተ ማን አለ?”

ክፍል ለ፦ ዕወጃ፦ ከቁ. 12-13

ክፈል ሐ፦ ትንበያ፦ ከቁ. 14-16ሀ

ማጠቃለያ አነጻጻሪ ዘይቤ፦ “እንደ ድንጋይ” ቁ. 16ሀ

አንጓ ፬ ከቁ. 16ለ-18

ክፍል ሀ፦ መግቢያ፦ ቁ. 16ለ፦ “አቤቱ እግዚአብሔር ሆይ ሕዝብህ እስከሚያልፉ ድረስ”

ክፍል ለ፦ ዕወጃ፦ ቁ. 17

ክፍል ሐ፦ ትንበያ፦ ቁ. 18

1 *ክፍል ሀ፦ አምላሽ መግቢያ።* “እዘምራለሁ” የሚለው በአንደኛ መደብ ነጠላ ቍጥር የቀረበው በእንዲህ ዐይነቱ መላው ማኅበረ ሰብ የእግዚአብሔርን ስም እየጠራ እንደ አንድ ሰው ሆኖ በሚያወድስበት ዐውድ የተለመደ አባባል ነው፤ ይሁንና እያንዳንዱ ሰውም በነፍስ ወከፍ ይህን መሰል የየራሱን ውዳሴ ለዕወጃ ያቀርባል። ይህን ለማድረግ የሚያነሣሣው ምክንያት ወዲያውኑ ተሰጥቷል፦ “(በቁሙ) በክብር ከብሯልና” ምክንያቱም “ፈረሱንና ፈረሰኛውን በባሕር ውስጥ ጥሏልና”

2-3 *ክፍል ለ፦ ዕወጃ።* የመግቢያው ሁለት ጭብጦች ሁለት ስንኞች አሁን በቅደም ተከተል ተጠቅሰዋል፦ (1) እግዚአብሔር (ከቍ. 2-3) እና (2) የተጣለው ጠላት (ከቍ. 4-5 በሚገኘው ትረካ ውስጥ)። በዚህ ዕወጃ ዐምስት የእግዚአብሔር ባሕርያት ተገልጸዋል፦ ሁሉም በአንደኛ መደብ ነው የቀረቡት፦ “ብርታቴ፤” “ዝማሬዬ፤” “ድነቴ፤” “አምላኬ፤” እና “የአባቴ አምላክ።” ከዚያም ቍ. 3 በሦስተኛ መደብ ይቀጥላል፦ “እግዚአብሔር ተዋጊ ነው፤/ ስሙም እግዚአብሔር ነው።”

በቍ. 3 ለእግዚአብሔር የተሰጠውን የማዕረግ ስም አስመልክተው ብዙ ክርስቲያኖች “እንዴት ይዜ ‹የጦር ሰው (ከኢሳ 42፥13 ጋር ያነጻ) ከጌታ ከኢየሱስ አባትና አምላክ ጋር ሊዛመድ ይችላል?” የሚል ጥያቄ ያነሣሉ። እግዚአብሔር በጦርነት ውስጥ የመሳተፉ እውነታ የሚነግረን ነገር ቢኖር የእግዚአብሔርን በሰው ሕይወትና ጕዳይ ውስጥ መግባቱንና መገኘቱን ብቻ ነው። ነገር ግን ስለ እግዚአብሔር ሞራላዊ ማንነት (ባሕርይ) አንዳች የሚነግረን ነገር የለም፦ ልክ “እግዚአብሔር ዓለታችን ነው” ወይም “ዓለት ነው” ወይም “ግንብ ነው” የሚሉት አባባሎች የእግዚአብሔርን ሞራላዊ ማንነት እንደማይነግሩን ሁሉ ማለት ነው።

4-5 *ክፍል ሐ፦ ትረካ (ስለ እግዚአብሔር ሥራ)* አሁን ትኵረቱ ወደ ጠላት ይሸጋገራል፤ አራቱ ቍልፍ ቃላትም በውሃ ላይ ያተኵራሉ፦ “ባሕር፤” “ቀይ ባሕር፤” “ቀላያት፤” “ጥልቅ ውሃ።” ልክ በክፍል ለ የሚገኙት የዕወጃ ግሶች ጕድኝታዊ ሐሳቦች እንዳሏቸው፦ “አመሰግነዋለሁ” “ከፍ ከፍ አደርገዋለሁ” (ከመግቢያው ጋር ያነጻ “እዘምራለሁ”)፦ እዚህ ያሉት ግሶች ተመሳሳይ ናቸው፦ “ባሕር ውስጥ ጣላቸው . . . ሰጠመ . . . ቀላያትንም ለበሱ . . . ወደ ጥልቁ ወረዱ›” ከዚያም አንንው በአነጻጸሪ ዘይቤ ይደመደማል፦ “እንደ ድንጋይ ወደ ጥልቁ ወረዱ”

6 *አንን ፪፦ ክፍል ሀ፦ መግቢያ።* “አቤቱ እግዚአብሔር ሆይ ቀኝ እጅህ” የሚለውን ሐረግ ደጋግሞ በመጠቀም ዝማሬው የሁለተኛውን አንን መጀመር ያበሥራል፤ ይህንንም የሚያደርገው የእግዚአብሔርን ሁሉን ቻይነት ገላጭ ተለዋጭ ዘይቤ በመጠቀም ነው (በዘዳ 33፥2 ከሚገኘው የሙሴ መዝሙርና በመዝሙር መጽሐፍ ከሚገኙ በርካታ መዝሙሮች ጋር ያነጻ)። በዚህ አንን ተጨማሪ ዝርዝሮችና ጠላት የተደመሰሰበት ሁኔታ ተገልጸዋል።

7-8 *ክፍል ለ፦ ዕወጃ።* የአራቱ ስንኞች የመጀመሪያ መሥመር በመግቢያው ላይ የተጠቀሰውን “ከፍ ከፍ ብሎ ከብሯልና” የሚለውን ሐረግ ያስታውሳል (ቍ. 1)። “በግርማህ ታላቅነት” አንተ “ጣልካቸው” (አመት “አፈረስካቸው” ሕንጻ እንደሚፈርስ ዐይነት)፤ እነዚያን “የተነሡብህን” (አመት “የተቃወሙህን”)፤ በዚህ አገባብ የእግዚአብሔርን መቅደስ ለማፍረስ የፈለጉትን ማለት ነው)። እግዚአብሔር፤ በሚንተገተገው የቍጣው እሳት ግለት እና ከእሳት ዐምድ ውስጥ ሆኖ በሚንበለበሉ ዐይኖቹ “እንደ ገለባም በላቸው።” በ14፥21 የተጠቀሰው “ብርቱ የምሥራቅ ነፋስ” በዚህ ቦታ በሥነ መለኮታዊ አገላለጽ “በአፍንጫህ እስትንፋስ” ተብሏል። ይህም ከነፋሱ ጀርባ የመለኮት ተልእኮ እንዳለበት ማረጋገጫ ነው። በውጤቱም “ውሆች ተቈለሉ”፤ “የሚንዶለዶሉት፣ የሚገሠግሡት፣ የሚፈሱት” ወንዞች “እንደ ክምር ቆሙ” (ከመዝ 78፥13 ጋር ያነጻ)። (በኋላ ላይ የዮርዳኖስ ወንዝም እንዲሁ እንደ “ክምር” ተቈልሏል (ኢያሱ 3፥13፡16።) በዚህ ጊዜ ማዕበሉ “ረጋ፣” ወደ በረዶነት የተለወጠ ይመስል። ይህ እንግዲህ እስራኤል የመሰከረችው የእግዚአብሔር ኀይል ነው።

9-10 *ክፍል ሐ፦ ትረካ (የእግዚአብሔር ሥራ)።* ዐምስቱ ስንኞች አስደናቂ በሆነ ሁኔታ የተሰደሩ ዐጫጭር ሐረጎች ግብፃውያን ያለ የሌለ ጕልበታቸውን አሟጠው፣ ትንፋሻቸው ቍርጥ ቍርጥ እያለ፦ “አሳድዳቸዋለሁ” ወይም “እደርስባቸዋለሁ” “ምርኮን እካፈላለሁ” “ነፍሴ ከእነርሱ ትጠግባለች” “ሰይፌን እመዛለሁ” “እጄ ትደመስሳቸዋለች” (በቁሙና ምፀታዊ በሆነ መልኩ “ትበዘብዛቸዋለች”) አለ። ነገር ግን ቍ.10 ይህን ሁሉ ይቀይረዋል፤ በእግዚአብሔር “እስትንፋስ” ወይም “ነፋስ” (ከቍ. 8ሀ ጋር ያነጻ) ብቻ “ባሕርም ከደናቸው” እናም “ሰጠመ።” እንደ መጀመሪያው አንን (ቍ. 5) ሁሉ ሁለተኛው አንንም በአነጻጸሪ ዘይቤ ይጨርሳል፦ “በኃያላን ውሆች እንደ ብረት ሰጠመ።”

11 *አንን ፫፦ ክፍል ሀ፦ መግቢያ።* መዝሙሩ አሁን ወደ ሥነ መለኮታዊ ትርጓሜና የተፈጸሙትን ነገሮች ፋይዳ ወደ መግለጽ ይመለሳል። አቻ የለሽነቱን ለመግለጽ የሚያገለግለውን ቀመር በመጠቀም “እንደ አንተ ማን አለ?” በማለት እስራኤል የእግዚአብሔርን ወደር የለሽነት ትገልጻለች፤ እንዲሁም 'በቅድስና የከበረ' እና 'በክብሩ የሚያስፈራ' ወይም 'ድንቆችን የሚያደርግ' በሚሉት ሐረጎች “ኃያልነቱ ተረጋግጧል” ትላለች። “የአሕዛብ አማልክት” (በዚህ ቦታ ህልውናቸውን የሚያረጋግጥ ወይም የሚክድ ነገር ባይገለጽም፤ ከ12፥12 ጋር ያነጻ) ማናቸውም እግዚአብሔር ያደረገውን ሊያደርጉ አይችሉም።

12-13 *ክፍል ለ፦ ዕወጃ።* ሁለተኛ መደብ የተጠቀሙት እነዚህ ቍጥሮች ከቍ. 7-8 እና ከቍ. 17 ጋር ተመሳሳይነት አላቸው። በመሆኑም እነዚህ ቍጥሮች አንድነት ያላቸው ሲሆን፣ የእግዚአብሔርን ታላላቅ ሥራዎች በሦስት ስንኞች ይገልጻሉ፦ በባሕሩ ላይ የተገኘው ድል፣ በምድረ በዳ የእግዚአብሔር ምሪት፣ በከነዓን ምድር የሚገኘው የእግዚአብሔር “ቅዱስ ማደሪያ” ናቸው። እናም የባሕሩ አስደናቂ ሥራዎች እግዚአብሔር ተስፋ የገባላቸውን ምድር እንደሚያወርሳቸው ዋስትና ናቸው። በዚህ ቦታ “ምድር” የተባለው ሲያልን፣ መቃብርን (ከ1ሳሙ. 28፥13፤ ከኢሳ 29፥4 ጋር ያነጻ) ሳያመለክት አይቀርም። ምክንያቱም በርግጥ “የዋጠቻቸው ባሕር” ናትና። ነገር ግን “የተቤዠትን” የመራቸው “የእግዚአብሔር ጸጋ” ወይም “የማይለወጠው ፍቅሩ” ነው። የዕብራይስጡ ግሶች ደጊመ ቃላዊ ቅደም ተከተል፦ (“ዘረጋህ፣” “ትመራለህ፣” እና “ትመራቸዋለህ” ለቅርጹ ግርማዊነትና ለሐሳቡ አንድነት ተጨማሪ ፋይዳ ሰጥተውታል።

“ቅዱስ ማደሪያህ” (በቁሙ “ቅዱስ ማሰማሪያህ ወይም መስፈሪያህ”) ሲናን የሚመለከት አይደለም፤ ምክንያቱም ከቍ. 14-15 የተጠቀሱት አሕዛብ ያ ተራራ ምንም ለውጥ አያመጣባቸውምና። ከነዓንን ብቻ የሚመለከትም አይደለም፤ ነገር ግን ቍ. 17 በግልጽ እንደሚያመለክተው በሙሴ ልብ ውስጥ ያለው እግዚአብሔር “ስሜን በዚያ አኖራለሁ” (ዘዳ 12፥5፡11፡21፤ እና ሌሎችም) ብሎ ተስፋ የተናገረለት በከነዓን የሚገኘው እርሱ ራሱ የመረጠው ቦታ (ዘዳ 12፥14፡18፡26 እና ሌሎችም) ማለትም የጽዮን ተራራ መቅደስ ነው።

14-16*ሀ* *ክፍል ሐ፦ ትንበያ (የእግዚአብሔር ሥራ)።* አሁንም እንደ ገና መዝሙሩ ከሁለተኛ መደብ ወደ ሦስተኛ መደብ ይሸጋገራል (ከቍ. 4 እና 9 ጋር ያነጻ)። በቍ.14*ሀ* ላይ የተሰጠው የማጠቃለያ ኀይለ ቃል ከቍ. 14ለ-15 ያለውን ይቀድማል። ከቍ. 14ለ-15 የእስራኤል የወደፊት ጠላቶች ተዘርዝረዋል እነርሱም፦ ፍልስጥኤም፣ ኤዶም፣ ሞዓብ፣ እና

ከነዓን ናቸው። እናም በቁ.14 ላይ “አሕዛብ” የተባሉት ደቡባዊ ፍልስጥኤምን ወርረው ለያዙት “እስያውያን” ግብፃውያን የሰጡት ስያሜ ነው። የእስራኤል በአስደናቂ ሁኔታ ከግብፅ ሰራዊት ነጻ የመውጣቷ ዜና በአካባቢው ወደ ነበሩ አገሮች ለመናኘቱ ግልጽ ያለው ማስረጃ ረዓብ የሰጠችው ምስክርነት ነው (ኢያ 2፥10-11)። በዚህ ስፍራ ከነዓን በደቡባዊ ምዕራብ ወሰኗ በሰፈሩት ሰዎች ስም ተጠርታለች። የኤዶም “አለቆች” ወይም “መሳፍንት” የሚሉት ቃላት ሌላው የሙሴ አገላለጽ ነው። ምክንያቱም ቃላቱ በኤዶም ሥርወ መንግሥት ዘመን ላይ የዋሉ ናቸውና (ከዘፍ 36፥15-16 *ጋር ያነጻ*) ፤ ልክ ለሞዓብ “*መሪዎች*” ወይም “ወጠጤዎች” ተብሎ በአካባቢው ይሰየም እንደ ነበረው ነው። ነገር ግን እነዚህ ሁሉ ሕዝቦችና *መሪዎች* በአንድነት የሚጋሩት ነገር አለ፦ ፍርሀት። በዚህ አንጓ ፍርሀት በሰባት የተለያዩ መንገዶች ተገልጸአል፤ ማጠቃለያውም ፍጹም ጸጥታን የሚገልጽ አነጻጻሪ ዘይቤ ነው፦ “እንደ ድንጋይ የማይንቀሳቀሱ ይሆናሉ።”

16ለ *አንን ፬፦ ክፍል ሀ፦ መግቢያ።* አሁንም እንደ ገና በድግግሞሻዊ ጉድኝት ያለፈውን ያስተዋውቃል። በዚህ ጊዜ የአንጓው ጉልላት በባሕሩ ላይ ያደረገው የእግዚአብሔር ታላቅ *ሥራ* ነው፦ “ሕዝብህ እስኪያልፉ ድረስ” ወይም “እስኪሻገሩ ድረስ” ወደ ከነዓን (ወይም ምናልባት ዮርዳኖስን)፤ ሕዝቡም “የተቤዠሃቸው” የተባለላቸው ናቸው።

17 ክፍል ለ፦ ዕወጃ። እግዚአብሔር በፈርዖንና የሕዝቡን ወደ ከነዓን መግባት በሚቃወሙት በሌሎች *መንግሥታት* ባደረገው ላይ በመመሥረት እስራኤል አሁን እግዚአብሔር ለአባቶች የገባውን ተስፋ ለመቀበል ተስፋ ያደርጋሉ፦ በዚያ የወደፊት ጊዜ እግዚአብሔር ለዘላለም የሚገዛበት፦ እነርሱም የከነዓንን ምድር የሚወርሱበት ነው (“ትተክላቸዋለህ” ስለሚለው ዘይቤ *መዝ* 44፥2፤ 80፥8-16 *ይመ*)። ምንባቡ ‹‹በርስትህ ተራራ›› ከሚለው ይጀምርና “ማደሪያህ እንዲሆን በሠራኸው ስፍራ” ብሎም “እጆችህ በሠሩት *መቅደስ*” (ቁ.13 *ይመ*) እስከሚለው ይሄዳል።

18 *ክፍል ሐ፦ ትንበያ (የእግዚአብሔር ሥራ)* ሙሴና እስራኤል አንዴ ለመጨረሻ ገደብ በሌለው ደስታ በእግዚአብሔር የፍጥረተ ዓለም ገዢነትና በግዛቱ ዘላለማዊነት ሐሤት ያደርጋሉ። እንደ ፊርያን ያሉ ትዕቢተኛ ገዢዎችና የከነዓንና የአካባቢዋ አገሮች አገዛዝ በንጽጽር ሲታይ እንዴት ጊዜያዊ ነው!

19-21 የሙሴንና የማርያምን *መዝሙር* በቁጥር 21 ላይ የተጠቀሰው ትረካዊ *መሸጋገሪያ* ይለያቸዋል። ማርያም “ነቢይቱ” (ከዘኍ 12፥2 *ጋር ያነጻ*) እና የአሮን “እኅት” ተብላ ተጠርታለች፤ ምንም እንኳ የሙሴም እኅት ብትሆን እንኳ። ነገር ግን በግልጽ እንደሚታየው ደረጃዋ ከአሮን *ጋር* እንጂ ከሙሴ *ጋር* አይደለም። በእስራኤል ሌሎችም እንስት ነቢያት ይኖራሉ (*መሳ* 4፥4፤ 2ነገ 22፥14፤ ነህ 6፥14፤ እና ሌሎችም)። እንደ እስራኤል ነቢያትና እንደ *መሪ* (ሚክ 6፥4) ማርያም ሴቶቹን ምናልባት የመዝሙሮቹን መጨረሻ አንጓዎች በቅብብሎሽ በድጋሚ በማስዘመር በከበሮና በሽብሸባ በመታጀብ መርታለች።

I. *ገዛ ወደ ሲና (15፥22-18፥27)*

1.የማራ ውኃ (15፥22-27)

22-23 “የሱር ምድረ በዳ” የሚባለው ከግብፅ ሰሜናዊ ምሥራቅ ወሰን አንሥቶ ወደ ምሥራቅ ሲል የሲናን በረሓ ሰሜናዊ ምዕራብ ይዞ ወደ ደቡብ አቅጣጫ እስከሚገኙት የሲና ተራራዎች ድረስ የሚዘልቅ ነው። ሱር ማለት “ግድግዳ” ማለት ሲሆን፣ በዘፍጥረት ውስጥ ለበርካታ ጊዜያት ተጠቅሷል (16፥7፤ 20፥1፤ 25፥18)። በዘኍ 33፥8 ይህ አካባቢ “የኤታም ምድረ በዳ” ተብሏል። ምናልባት ኤታም ምሽግ የሚል ትርጉም ያለው ጥንታዊ የግብፅ ቃል ነው። እስራኤል ለመጀመሪያ ያረፉበት ስፍራ ዐይን ሙሳ፣ “የሙሴ ምንጮች” የሚባል ቦታ እንደ ሆነ ትውፊት ያስረዳል፤ ይህ ቦታ በመጽሐፍ ቅዱስ የትም ተጠቅሶ አይገኝም። ቦታው ከማራ (መራራ) ዐሥራ ስድስት ሰዓት ያህል ጉዞ በኋላ የሚገኝ የጣፋጭ ውሃ ምንጭ ሲሆን እስራኤል ለመጀመሪያ ጊዜ የቆሙበት (ያረፉበት) ቦታ ነው። ይህ እስራኤላውያን ቀይ ባሕርን ያቋረጡበት ስፍራ እንደ ሆነ በልማድ የሚነገርለት ስፍራ ከቀይ ባሕር ሰሜናዊ ጫፍ ዐሥር ማይሎች ርቀት ላይ የሚገኝ ሲሆን፣ ከባሕሩ ዳርቻ ደግሞ ግማሽ ማይል ያህል ይርቃል። ከዓይን ሙሳ እስከ ማራ የአርባ ማይሎች ጉዞ ነው።

በመጀመሪያ ላይ እስራኤላውያን የተጋፈጡት በስተ ቀኛቸው በስዊዝ የባሕረ ሰላጤ ጥቁር ሰማያዊ ውሃ የተከበበውን ዓለታማ በረሓ ሲሆን፣ በስተ ግራቸው ደግሞ የኤል ሩሃትን የተራራ ሰንሰለቶች ነበር። ከዘጠኝ ወይም ከዚያም በላይ ማይሎች በኋላ ኤል አቲ ወደሚባል ለጥ ያለ በረሓ ደረሱ፤ ይህ ለዐይን የሚያታክት የነጭ አሸዋ ክምር ሲሆን ቦታውን ወደ አሸዋማ ተራራ ለውጦታል። ነገር ግን ውሃ ከየትም ሊገኝ አይችልም። ማራ በአብዛኛው አይን ሃዋራ በመባል የሚታወቅ ከሰላጤው በርካታ ማይሎች ርቀት ላይ የሚገኝ ቦታ እንደ ሆነ ይታመናል። የአይን ሃዋራ ውኃ በጣም ጨዋማ ነው።

24 የሕዝቡ ማጉረምረም ለምድረ በዳው ዙረት ትረካዎች ታሪካዊ እውነትነት ጠንካራ ማስረጃ ነው። በጥቅሉ ከወርቁ ጥጃ ክሥተት በፊት የተደረጉ ማጉረምረሞች እውነተኛ የሆነ ፍላጎት (ችግር) ያስከተላቸው ሲሆኑ፣ ከዚያ በኋላ ያሉት ግን ተቀባይነት የሌላቸው የማጉረምረም ዐይነቶች ናቸው። “አይዋጡ” የሆነው የማራ ውሃ በግብፅ የተደረጉትን ተአምራትና የቀይ ባሕርን መከፈል እንኳ እስከ ማስረሳት ደርሷል፦ ወይም የደረሰ ይመስላል።

25ሀ እግዚአብሔር ለሙሴ ዛፍ “አሳየው”። “አሳየው” የሚለው ግስ *ሥርወ* ቃሉ “ማስተማር” ወይም “ትእዛዝ” የሚል ፍቺ ሲኖረው “ቶራ” (“ትእዛዝ” “ሕግ”፤) ከሚለው ቃል *ጋር* ተመሳሳይ *ሥርወ* ቃል ያለው ነው። እስራኤል ከግብፅ ነጻ ከወጡ በኋላ የሚያስፈልጋቸው ትእዛዝ ከሰማይ እንደ ሆነ ሊማሩ ያስፈልጋቸው ነበር። ይህም እንደ ገና የሙሴን ሕገጋት ለመቀበል ያዘጋጃቸዋል። ይህ ክፍል በግልጽ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ተስፋ *መቀረጥ* መልስ የሚሆኑ ልዩ *መመሪያዎች* እንደ ሰጠው ይናገራል። ይህ ዛፍ (በ2ነገ 2፥19-22) የኤልሳ ጨው የኢያሪኮን ውኃ ምንጮች እንደ ፈወሰው ጊዜያዊ ፈውስ ከማምጣት ያለፈ ፋይዳ የለውም። በሁለቱም ቦታ የተገኘው የእግዚአብሔር ኀይልና መታዘዝን የመፈተን ሁኔታ ብቻ ነው።

25ለ -27 ይህ ተአምራት ከቃል ኪዳን *ጋር* የተያያዘ ነው፦ ከአሁን ወዲህ ለትእዛዛትና ለሕገጋት *መታዘዝ* አካላዊም ሞራላዊም ጤናን ያመጣል። እግዚአብሔር እስራኤል ለሦስት ቀናት ያለውኃ እንዲጓዙ ያደረገው “ሊፈትናቸው” ነው። ቀጥሎ እግዚአብሔር እስራኤልን በመሪባ (17፥1-7)፣ በተቤራ (ዘኍ 11፥3፤ 13፥26-33) በሌሎችም ቦታዎች ፈትኗቸዋል፤ ነገር ግን “ትሑት ሊያደርጋቸው በልባቸው ያለውን ለማወቅ ነው የፈተናቸው” (ዘዳ 8፥2)። በሌላ በኩል፣ እግዚአብሔር በግብፃውያን ላይ “ያመጣባቸው” “በሽታዎች” እስራኤል ካልታዘዙትና ካመፁበት በእነርሱ ላይ ይመጡባቸዋል (ዘዳ 28፥27)።

እስራኤል ወደ “ኤሊም” ተጓዙ፤ ኤሊም ከዓይን ሃዋራ ሰባት ማይሎች ገደማ ርቀት ላይ በትልቁና ውበት በተላበሰው የጋራንደል ሸለቆ ውስጥ ይገኛል። ይህ ወሽመጥ ከሱር ምድረ

በዳና ከሲና ምድረ በዳ መካከል የሚገኝ ሲሆን እንዲሁም ከዋዲ ጋንዲል በተጨማሪ ሁለት "ዋዲዎች" (በረሓማ ቦታዎች) አሉት። በክረምት ወቅት የማያቋርጥ ወንዝ ወደ ቀይ ባሕር ይጮርፋል። በዚያ የሚገኘው ሳር ረገጥ ረገጥምና ወፈፍራም ሰንበሌጥ ሲሆን ብዙ ዛፎችም ይገኙበታል።

2. መናና ድርጭት (16፥1-36)

1-3 "በሁለተኛው ወር በዐሥራ ዐምስተኛው ቀን" በትክክል እስራኤል ከግብፅ ከወጡ ከአንድ ወር በኋላ ማለት ነው (12፥6፡31)። ዘኍልቁ 33፥5-11 እስራኤል የሰፈሩባቸውን ሰባት ቦታዎች ብቻ ስለሚጠቅስና ሦስት ቀናት የፈጀ አንድ ጉዞ ብቻ ስላደረጉ (ዘፀ 15፥122)፤ አንድም እስራኤል በእነዚህ ቦታዎች በብዙ ስፍራዎች ለበርካታ ቀናት ቈይተዋል አልያም ስማቸው ባልተጠቀሰ ሌሎች በርካታ ቦታዎች ሰፍረዋል። የዕብራይስጡ ቃል አገባብ አንድምታ ኤሊምን የለቀቁት በተለያየ አቅጣጫ በቡድን ተከፋፍለው እንደ ሆነና በመጨረሻም ወደ ሲና ምድረ በዳ ሲደርሱ በአንድነት እንደ ተሰባሰቡ ነው። የሲና ምድረ በዳን ትክክለኛ አድራሻ መጠቁም አስቸጋሪ ነው።

በዚህ ጊዜ ሕዝቡ "ያጕረመረሙት" ስለሚመገቡት ምግብ መጠን አነስተኛ መሆንና የሥጋ አለመኖር ነው። በድንገት ግብፅ የባርነትና የአስገባሪዎች ምድር መሆኗ ቀርቶ የምታስጎመዥ (የሥጋ መቀቀያ ምንቸትና የፈለጉትን ያህል ምግብ የሚበሉባት) ምድር ሆና ታየቻቸው። መንፈሳዊነት በሚመስል የተጣመመ ቋንቋና የእግዚአብሔርን ስምና ችሎታ የማቃለል አንድምታ ባለው አነጋገር በግብፅ አገር በእግዚአብሔር እጅ መሞት አሁን ካዩዋቸው በርካታ ታምራት ይልቅ እንደሚሻላቸው ገለጹ፤ በተለይ ካሁኑ መከራ አይብስብንም አሉ። ከግብፅ ይዘውት የወጡት ሥንቅ ላለፉት ሠላሳ ቀናት ድረስ ቈይቶ ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን አሁን ይዘውት የመጡትን ሁሉ አሟጠው ጨርሰዋል።

4-5 እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን ማጕረምረም "ከሰማይ እንጀራን በማዝነብ" በቸርነቱ ምላሽ ይሰጣቸዋል (ከነሀ 9፥15፤ ከመዝ 78፥24፤ ከዮሐ 6፥31-51 *ጋር ያነጻ*)። ነገር ግን እስራኤል እግዚአብሔርን በእምነት ይታዘዙት እንደ ሆነ ለማወቅ "ፈተና" ሊሰጣቸው ይገባ ነበር። ዐሠርቱ ትእዛዛት ከመሰጠታቸውም በፊት ሰባተኛው ቀን ለእግዚአብሔር እንዲለይለት (እንዲቀደስለት) በዘፍጥረት 2፥2-3 *መሠረት* አዝዟል። በስድስተኛው ቀን ሕዝቡ ከሌሎቹ ቀናት ከሚሰበስቡት ዕጥፍ መሰብሰብ አለባቸው። በሰበሰቡት መልክ ሊተው፣ ወይም ሊበላ አይችልም፤ ይልቁን በመፍጨትና በመጋገር መዘጋጀት ነበረበት (ከዘኍ 11፥8 *ጋር ያነጻ*)።

6-8 የቍ 8 የመጀመሪያ ክፍል የእስራኤል የማስታወስ ችግር የዚያኑ ምሽት እግዚአብሔር ገና ባልተገለጠ መንገድ ምግብ ሲሰጣቸው ይስተካከላል፤ ከዚያም እግዚአብሔር አምላክ እንደ ሆነ ያውቃሉ? (ያ በመቅሠፍቱ ጊዜ በተደጋጋሚ ይገለጥ የነበረው ወንጌላዊ ቃል ተመልሶ መጣ)። የቍ 8 ሁለተኛ ክፍል የቍ.7ለን ውስጣዊ ትርጉም ያብራራል፡- ማጕረምረማችሁ በእኛ በመሪዎቻችሁ ላይ ሳይሆን ዞሮ ዞሮ በእግዚአብሔር ላይ ነው። ስለዚህ እኛም ከእስራኤልና (ከራሳችንም!) ታሪክ፣ ነገረ መለኮትና ዘላቂ መርሖዎች እንማራለን ምክንያቱም እግዚአብሔር በዚህ ስፍራ የሚያደርገው ነገር ከድርጊቶች ቀጥተኛ ትረካ ፊት ለፊት ነውና።

9-12 ሙሴ አሮንን የእስራኤልን ማኅበር "ወደ እግዚአብሔር ፊት እንዲቀርቡ" እንዲያደርግ አዘዘው። ቍ 10 ላይ እግዚአብሔር በደመና ወደ ተገለጠበት ወደ ምድረ በዳው አቅጣጫ መመልከት እንደ ነበረባቸው ይናገራል። ከደመናና ከእሳት *ጋር* የተገናኘው የዚህ የእግዚአብሔር ትክክለኛ መገኘት ምሳሌ በ24፥15-17 ላይ ይብራራል። አሁንም በድጋሚ በቍ 6 እና 8 እንደ ተጠቀሰው እስራኤል "እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ መሆኔን ታውቃላችሁ።"

13-18 የድርጭቶችን ስጦታ የተመለከቱት ክሥተቶች በዘኍ 11፥4-22፡ 31-33 ካለው *ጋር* በቅርጽ ተመሳሳይ፣ በጊዜ ግን የተለያዩ ናቸው። (የዘኍልቁው የተፈጸመው በምድረ በዳው ሁለተኛ ዓመት ዙረት ላይ ነው፣ ዘኍ 10፥11)። ድርጭቶች (አንበጣ ወይም በራሪ ዐሣ አይደለም ነገር ግን "የሚበሩትን ወፎች" ነው፤ መዝ 78፥27-31 ግልጽ ያደርጋል) የታወቁ ወቅት እየጠበቁ ከስፍራ ስፍራ የሚሰደዱ ወፎች ናቸው። አብዛኛውን ጊዜ በበልግ በብዛት ወደ ሰሜን ክልል ይበራሉ፤ በመኸር ይመለሳሉ። ለረዥም ጊዜ በቀይ ባሕር ላይ በመብረራቸው ከብርቱ ድካም የተነሣ በሲና ባሕረ ሰላጤ ወረዱ።

ድርጭቶች ብቻ አልነበሩም ከአድማስ "የወረዱት" ጤዛውም እንዲሁ "ወረደ።" ጤዛው ከተነነ በኋላ በሜዳው ላይ ስስ አመዳይ የመሰለ ነገር በምድረ በዳው ላይ ታየ። ሕዝቡ ጠየቀ፡- "ምንድን ነው?" (በዕብ ማን ሁ) የሚለው እስራኤላውያን ይህን ከሰማይ የወረደ እንጀራ ለምን "መና" የሚል ስያሜ እንደ ሰጡት ግልጽ ያደርጋል (ቍ 31 ይመ)። የመናን መገኛ ምንጭ አስመልክቶ የተለያዩ ተፈጥሯዊ ማብራሪያዎች ተሰጥተዋል፤ ይሁን እንጂ ሁሉም ተኣምራዊ አመጣጡን በሙላት ለመግለጽ ሲሞክሩ ችግር ይገጥማቸዋል። በጥቅሉ ለተለየ ዐላማ ተኣምራዊ በሆነ መንገድ የተዘጋጀ ልዩ ነገር ነው። እያንዳንዱ የቤተ ሰብ አባል አንዳንድ ኀመር መና ይሰበስባል፤ ይህም ወደ ሁለት ሊትር ገደማ ወይም የኢፍ መስፈሪያ አንድ ዐሥረኛ ያህል ነው።

19-21 ምንም እንኳ እግዚአብሔር ሕዝቡን እስከ ንጋት ምንም መና እንዳያቈዩ "እንደሚፈትናቸው" (ቍ 4) ቢያስጠነቅቃቸውም፣ "አንዳንዶቹ ሙሴ የተናገረውን ቸል" አሉ። ይህ ፈተና ለእስራኤላውያን "ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣው በእያንዳንዱ ቃል እንጂ በእንጀራ ብቻ" (ዘዳ 8፥3) እንደማይኖር ሊያስታውሳቸው የተሰጠ ነው። በተጨማሪም እስራኤል የየዕለቱ እንጀራቸው እንኳ የእግዚአብሔር ስጦታ እንደ ሆነ ትምህርት ሰጥቷቸዋል፤ ስለዚህ በየዕለቱ በጌታ በመደገፍ ሊኖሩ ይገባቸዋል።

22-30 የዕረፍት ቀን፣ ለጌታ የተቀደሰ ሰንበት፣ በሲና በተሰጡት ሕገጋት የተጀመረ አይደለም፤ በዘፀ.20፥8-11 እንኳ የዚህ ትእዛዝ መሠረቱ በዘፍጥረት የተሰጡት ትእዛዞች ናቸው (ከዘፍ 2፥2-3፤ እስከ 29፥27 *ጋር ያነጻ*)። ይሄ ስድስት ቀን የመሰብሰብ በሰባተኛው ቀን የማረፍ ዕቅድ በጌታ የተሰጠ ነው (ቍ. 5)። ሰባተኛው ቀን "የማቆም ቀን" ወይም "የዕረፍት ቀን" ነው፤ ለማግስቱ የምግብ ዝግጅት መደረግ ያለበት በስድስተኛው ቀን ነው። ነገር ግን አንዳንዶቹ ይህን ትእዛዝ ሲጥሱ እግዚአብሔር ዐዘነ፡- "ትእዛዞቼንና መመሪያዎቼን ለመፈጸም እስከ መቼ ችላ ትላላችሁ?" አላቸው። ከዚያን ጊዜ በኋላ ብቻ ነው ሕዝቡ በሰንበት ቀን "ያረፉት" (በቁመ፣ "የሚቆሙት" "የሚያቋርጡት።")።

31 የመና ስያሜና ገለጻ በዘኍ 11፥6-9 ላይም ተሰጥቷል። የድንብላል ዘር፣ ትንሽ፣ ነጣ ያለ ወይም ብጫማ ግራጫ ሲሆን ለምግብ ማጣፈጫነት ያገለግላል። ዘኍ 11፥7 "የመጫ መልክ ነበረው" የሚል ገለጻ ይጨምርበታል፤ ደግሞም አንዳንድ የቄዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች የ"ዕንቍ" ቀለም ነበረው ይላሉ። ጣዕሙም የማር እንጀራ ወይም ደግሞ "በወይራ ዘይት የተጋገረ ያህል ይጣፍጥ ነበር" (ዘኍ 11፥8)፤ እንዲሁም በወፍጮ ሊፈጭ፣ በሙቀጫ ሊወቀጥ፣ በምንቸት ሊቀቀል፣ ወይም እንደ ኬክ (ቂጣ) ሊጋገር ይችላል (ዘኍ 11፥8)።

32-36 ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሙሴ የተወሰነ መና በቃል ኪዳኑ ታቦት በማኖር ለመታሰቢያ እንዲቀመጥ ትእዛዝ ሰጠ። በዚህ ጊዜ የቃል ኪዳኑ ታቦት እንኳ ሊሠራ ይቅርና ገና አልተገለጠም ነበር። ይህን አቋም የሚደግፍ ሐሳብ ታሪካዊ ማስታወሻ በቁ 35 የተጠቀሰው ሲሆን፤ እርሱም ለሚቀጥሉት ዐርባ ዓመታት መና በምግብነት ማገልገሉን ይናገራል፤ ስለዚህም እነዚህ ጥቅሶች የተጻፉት የምድረ በዳው ዙረት ካበቃ በኋላ በሙሴ ነው።

3. የመሪባ ውሃ (17፥1-7)

1-2 እስራኤል ወደ ራፊዲም ከመምጣታቸው በፊት፣ ሕዝቡ በራፍቃና በኤሉስ ሰፈሩ (ዘኍ 33፥12-14)። ራፊዲምን በሚገባ የሚገልጸው በደቡብ ምዕራብ የሚገኝ ዋዲ ሬፋይድ እንጂ ወዲ ፌይራን አይደለም። ውሃ እናገኝን የሚል ተስፋ ነበራቸው ረባዳማው ስፍራ ግን ደረቅ ነበር። ይህ ክሥተት እግዚአብሔር የእስራኤልን ፍላጎት በምድረ በዳ ያሟላበትን ሁኔታ ከሚተርኩ ምንባቦች ሦስተኛውን ይሰጠናል።

ከዚህ ተስፋ መቁረጥ የተነሣ ሕዝቡ ሙሴን "ተጣሉት"፤ ጥያቄያቸውም፡- "የምንጠጣው ውሃ ስጠን" የሚል ነው። "መጣላት" የሚለው ግስ (ራብ ከሚለው ሥርወ ቃል የተገኘ ነው) ከዚህ ቦታ ስያሜዎች አንዱ ነው፤ "መሪባ" በመባል የሚታወቅ ሲሆን ትርጉሙም "ጠብ"፤ "ጭቅጭቅ" ወይም "ሙግት" ማለት ነው። በሙሴ አማካይነት በጌታ ቸርነት የተሰጣቸውን ስጦታ ለችግራቸው በምትሃታዊ መንገድ መፍትሔ እንዲሆንላቸው ጠየቁ፡- "ውኃ ስጠን።"

የሚያስገርመው፣ እስራኤል ወደ ራፊዲም የተጓዙት "በእግዚአብሔር ትእዛዝ" (በቁሙ "በእግዚአብሔር አፍ") ነው። እናም እግዚአብሔር በገዛ ጥበቡ ከሲና ምድረ በዳ (የተራቡበትና ኋላም የጠገቡበት ስፍራ) ወደ ራፊዲም (ወደ ተጠሙበት ቦታ) እንዲጓዙ አዘዛቸው።

እግዚአብሔር እየሰጣቸው ለነበሩት "ፈተናዎች" በመገዛት ፋንታ (15፥25፤ 16፥4) እስራኤል እግዚአብሔርን መፈተን ጀመሩ (መዝ 78፥56፤ 106፥7፡ 14፡ 25፡ 29)! የእግዚአብሔር ሕዝብ አምላካቸውን የሚፈትኑት በእግዚአብሔር ቸርነትና መግቦት ጥርጣሬ ሲያድርባቸውና በእርሱ(ና) ወይም በመሪዎቹ ሲያጉረመርሙ ነው። ሙሴ ወደ ኋላ ላይ ሕዝቡን በማሳ ላይ እንዳደረጉት እንዳይፈታተኑት ያስጠነቅቃቸዋል (ዘዳ 6፥16)።

3 መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትረካ ዘወትር ታሪኩን በአጠቃላይ ጎይለ ቃል ወደ ሌላ አቅጣጫ ይመራውና (እዚህ ቁ.2) ቀጥሎ አያያዥ መስተዓምሮችን በመጠቀም ቀደም ብሎ የተጠቀሰውን ጭብጥ ይበልጥ ሰፋ አድርጎ ያብራራዋል። በመሆኑም ቁ. 3ን "ሕዝቡ ውሃ ከመጠማታቸው የተነሣ" ብሎ መተርጎም የተሻለ ሳይሆን አይቀርም።

4-7 ሙሴ ችግሮቹን ወደ እግዚአብሔር አቀረበ (15፥25፤ 32፥30 እና ሌሎችም)። እጅግ በስጨት ብሎ "በዚህ ሕዝብ ምን ላድርግ?" ሕዝቡ ሙሴን ሊወግሩት ተቃርበው ነበር፡- ይሄ የተበሳጨ የሕዝብ መንጋ ለአስቸጋሪ ሁኔታ የሚሰጠው ምላሽ ነው።

የእግዚአብሔር ምላሽ ለሕዝቡ ጥያቄ ቀጥተኛ መልስ መስጠት ነበር። ሙሴ፣ ከጥቂት ሽማግሌዎች ጋር ሆኖ፣ ወደ ሕዝቡ ፊት መሄድ ነበረበት፡- ምናልባትም ወደ ታች ወደ ረባዳማው በረሓ። በዚያ፣ የደመና ዐምድ የእግዚአብሔርን መገኘት ለማመልከት በታየበት ቦታ፣ ሙሴ "ድንጋዩን እንዲመታ" ይጠበቃል ልክ የአባይን ወንዝ "እንደ መታ" ሁሉ። ይሁን እንጂ በመጀመሪያው መቅሠፍት ውሃውን መምታት (7፥17፣20) የዚያችን ምድር የውሃ አቅርቦት አቋረጠ፤ በሌላ በኩል ይሄኛው መምታት የውሃውን መፍሰስ መቀጠል አመላካች ነው።

ይሄ ክሥተት በእስራኤላውያን የአርባ ዓመት ጕዞ ማብቂያ ላይ ከተከሠተው በዙኍ 20፥1-13 ካለው ጋር ሊላከር አይገባም። በዚህ በኋለኛው ትረካ የእግዚአብሔር ክብር አልነበረም፤ ሙሴም ድንጋዩን መምታት አልነበረበትም፤ ይልቁን ሊናገረው ነበር የሚገባው።

በመሆኑም በዚህ ቦታ ሕዝቡ እግዚአብሔርን መፈተናቸውን (ማሳ፤ "መፈተን" ማለት ነው) እና ጠብ መፍጠራቸውን (መሪባህ፤ "ጠብ" "ክርክር" ማለት ነው) ግልጽ የሚያደርጉ መንታ ስያሜዎችን እናገኛለን። ከስድስት ወር ባነሰ ጊዜ ውስጥ እስራኤላውያን ዐሥር መቅሠፍቶችን፣ የደመናና የእሳት ዐምድ፣ የቀይ ባሕርን መከፈትና መዘጋት፣ የውኃውን በተኣምር መጣፈጥ፣ እና ከሰማይ የእንጀራና የሥጋ መላክ ተኣምራት ምስክሮች ናቸው። ሆኖም የጥያቄያቸው ፍሬ ነገር "እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው ወይስ አይደለም?" የሚል ነው።

4. ከአማሌቅ ጋር የተደረገ ውጊያ (17፥8-16)

8 አማሌቃውያን የሚኖሩት በበረሓ፣ በደቡባዊ ከነዓን በቃዴስ አካባቢ ነው (ዘፍ 14፥7)፣ በሌላ ስሙ የኔጌቭ ሰሜናዊ ክፍል በመባል ይታወቃል (ዘኍ 13፥29፤ 14፥25፡ 43)። አማሌቅ ኤሊፋዝ (የኤሳው በኵር ልጅ) ቲምና ከምትባል ቁባቱ (ዘፍ 36፥12) የተወለደ ሲሆን በኤሳው ትውልድ ውስጥ ጕሣ ወይም መሪ ነበር (ዘፍ 36፥15)። እናም አማሌቃውያን ከእስራኤላውያን ጋር የሩቅ ዝምድና አላቸው።

የአማሌቃውያን እስራኤልን ማጥቃት የእግዚአብሔርን ቊጣ አስነሣባቸው። ምክንያቱም አማሌቃውያን እግዚአብሔር በእስራኤል ሕይወትና ዕድል ፋንታ ያለውን ዐላማ ባለማወቃቸውና በውጊያው የመጀመሪያዎቹ የጥቃት ዒላማዎቻቸው የታመመ፣ በዕድሜ የገፉና ከድካም የተነሣ ከእስራኤል የጕዞ መሥመር በኋለኛው ረድፍ ያሉት መሆናቸው ነው (ዘዳ 25፥17-19)። በዚህ ዐይነት አማሌቅ እስራኤልን ለማጥቃት ከተነሡት ሕዝቦች የመጀመሪያው ሆነ (ዘኍ 24፥20)።

በሚቀጥለው ምዕራፍ እንደሚገለጸው የእስራኤልን አምላክ ካመነ ከሌላ አሕዛብ ጋር (ከዮቶር ምድያማውያን ጋር) ተነጻጽረዋል። እነዚህ ሁለት ምዕራፎች ከአሕዛብ መካከል ሁለት ነገሥታት ለእግዚአብሔር ጸጋ የሰጡትን ሁለት ምላሾች ይገልጻሉ።

9 ከአማሌቃውያን ጋር የሚደረገውን ጦርነት ይመራ ዘንድ ሙሴ አንድ ወጣት ሰው፣ (ወደ ዐርባ ዐምስት ዓመት የሚሆነው) ከኤፍሬም ነገድ የሆነ (የዮሴፍን ልጅ) አውሴ የሚባለውን (ዘኍ 13፥8) የነዌን ልጅ (1ዜና 7፥27)፣ በኋላ ላይ ኢያሱ ተብሎ የተሰየመውን ሾመው። ኢያሱ አማሌቃውያንን የሚገጥመውን ሰራዊት ይመለምላል፤ ሙሴ ደግሞ የእግዚአብሔርን በትር በእጁ ይዞ በቅርብ ከሚገኙ ኮረብታዎች በአንደኛው ላይ በውጊያው ሜዳ ትይዩ ይቆማል። ሁለቱም መሣሪያዎች ጥቅም ላይ ይውላሉ፡- በኢያሱ እጅ ያለው ሰይፍና በሙሴ እጅ ያለው (የመለኮትን ጣልቃ ገብነት የሚወክለው) በትር ናቸው።

10-13 አሮንና ሖር ከሙሴ ጋር ወደ ኮረብታው ወጡ። ሖር እንደ ገና በ24፥14 ላይ ከአሮን ጋር ይጠቀሳል። በዚህ ቦታ የሚጠቀሰው ሖር ከይሁዳ ነገድ የሆነ በካሌብ የትውልድ ሐረግ ውስጥ ያለ (1ዜና 2፥18-20) እና የልጅ ልጁ ባስልኤል የመገናኛውን ድንኳን የሠራው ይሁን ወይስ ሌላ በውል ለመረዳት አስቸጋሪ ነው። በትውፊት ሖር የሙሴ እኅት የማርያም ባል እንደ ሆነ ይነገራል።

“ሙሴ እጆቹን ወደ ላይ ባነሣበት ጊዜ ሁሉ” ኢያሱና ሰዎቹ ድል ያደርጉ ነበር። ነገር ግን “እጆቹ ዝለው ወደ ታች በወረዱ ጊዜ ሁሉ” አማሌቃውያን በድል ወደ ፊት ይገሠግሡ ነበር። ይህ ድርጊት ዐላማው ሥነ ልቦናዊ ብቻ አይደለም፤ ማለትም ተዋጊዎቹ ወደ ኰረብታው አቅንተው ባዩ ቍጥር እንዲበረታቱ አይደለም። ወይም ደግሞ ክፍሉ ሙሴ እጆቹን ባነሣ ቍጥር ይጸልይ እንደ ነበረም በግልጽ አይናገርም። ይልቁን የሙሴ የተዘረጉ እጆች ሙሴ ወደ እግዚአብሔር የሚያቀርበውን አቤቱታ ይወክላሉ። በመጨረሻም ረኻሮሙ ጦርነት በኢያሱ ድል አድራጊነት፣ በአሮንና በሖር የሙሴን እጆች በመደገፍ ባደረጉት ርዳታ ተጠናቀቀ።

14 ይህ የእግዚአብሔር ታላቅ ሀልዎት ትልቅ ድርሻ የተጫወተበት የውጊያ ታሪክ ለመታሰቢያነት በጥቅልል መጽሐፍ ተጽፎ፣ ለኢያሱ ጥቅም ሲል በየጊዜው እንዲነበብ እግዚአብሔር አዘዘ። አማሌቅ ላደረገው አስከፊ ድርጊት ውድ ዋጋ ይከፍላል። መዝሙረኛው (መዝ 83፥4፡7) የአማሌቅን የተንኰል ሐሳብ ከሌሎች ሕዝቦች ጋር ያገናኘዋል፦ “ኑ ሕዝብ እንዳይሆኑ እንደምስሳቸው፤ የእስራኤል ስም ከእንግዲህ እንዳይታወስ።” ነገር ግን በእስራኤል ላይ ለማድረግ የዛቱት በእነርሱ በራሳቸው ላይ ይፈጸማል። ይህ ፈጽሞ የመደምሰስ ነገር እስከ ሳኦል ዘመን ድረስ እንኳ ገና አልተፈጸመም ነበር (1ሳሙ 15)፤ ምክንያቱም ሳኦል እግዚአብሔር አድርግ ያለውን ሳያደርግ ቀርቷልና። ዳዊት ይህንኑ ሥራ ቀጠለ (2ሳሙ 1፥1-8፥12)፤ ምናልባትም እስከ አስቴር ዘመን ድረስ ሳይቀጥል አልቀረም፤ በርግጥም ሐማ አማሌቃዊ ከሆነ።

15-16 “እግዚአብሔር አርማዬ ነው” የመሠዊያው ስም ይሁን (በዘፍ 33፥20 ከያዕቆብ ጋር ያነጻ) ወይም ደግሞ ለእግዚአብሔር ለራሱ የተሰጠው የማዕረግ ስም ይሁን በርግጠኝነት መናገር አይቻልም። ውጤቱ ግን በዚህም ሆነ በዚያ ያው ነው። “ዓላማ” ወይም “አርማ” የሚለው ቃል የዕብራይስጡ ሥርወ ቃል “ከፍ ማለት” “ከፍ ያለ” ወይም “ጐልቶ የሚታይ” እንደ ማለት ነው። ይሄ የሚያመለክተው በትሩን የእግዚአብሔርን ኀይል እንደሚገልጥ ምልክትና ምስክር ከፍ ማድረግን ነው። እንግዲያውስ ድሉ የእግዚአብሔር ነው፤ ሰልፉም የእርሱ እንደ ሆነ ሁሉ።

የቍ 16 ትርጉም አስቸጋሪ ነው፤ ምክንያቱም “ዙፋን” (ቁስ) የሚለው ቃል ሆህያት ያልተለመዱ በመሆናቸው ነው። ለዚህ ከሁሉ የተሻለው መፍትሒ (ከበድ ያለውን አነባብ በመውሰድ) “ኬሲ” የሚለውን ቃል “ኬሲ-ያህ” (“የያህዌህ ዙፋን”) የሚለው አጎዕሮት እንደ ሆነ አድርጎ መውሰዱ ነው። እንዲህ ከሆነ ክፍሉ “በርግጥ፤ እጁ ወደ እግዚአብሔር ዙፋን ነው” የሚል ይሆናል፤ ማለትም፦ ለልመና፣ ለምልጃ ማለት ነው። የክፍሉ አማራጭ ትርጉም “ምክንያቱም እጁ በእግዚአብሔር ዙፋን ላይ በተቃውሞ ተነሥቷል” (የአመትን ማብራሪያ ይመ) የሚለው ነው። ይህ ሁለተኛው አተረጓጎም ከዐውዱ ጋር ይበልጥ የተስማማ ነው።

5. የዮቶር ጥበብ (18፥1-27)

1-5 ዮቶር፣ የሙሴ ዐማት፣ ሙሴንና እስራኤላውያንን በበረሓው “በእግዚአብሔር ተራራ” ተገናኛቸው (3፡1 ይመ)። ዮቶር ወደ ሲና መጥቶ ይጐበኛቸው ዘንድ እንዲያመጡት ሙሴ ሚስቱንና ልጆቹን ወደ ምድያም አስቀድሞ ሳይልካቸው አልቀረም። ሲፓራ፣ ጌርሳምና ኤሊኤዜር ወደ ምድያም የተላኩት በ4፥20-26 ከተጠቀሰው በቤተ ሰቡ መካከል ከተነሣው ጭቅጭቅ በኋላ ሳይሆን አይቀርም። ነገር ግን ለኤሊኤዘር ቀጣዩ ሊቀ ካህናት እንደ መሆኑ፣ እግዚአብሔር እስራኤልን ከግብፅ ያወጣበትን ታምራት ሁሉ በዐይኑ መመልከቱ ከሁሉ የተሻለ በሆነ ነበር።

6-8 ዮቶር መምጣቱን ለሙሴ የገለጠው በመልእክተኛ ሲሆን ሙሴም ሊቀበለው ወጣ (ከዘፍ 18፥2፤ 19፥1፤ 32፥6፤ 33፥1 ጋር ያነጻ) የተለመደውን የምሥራቅ ሰዎች ባህላዊ ሰላምታ ለመለዋወጥ። ሙሴ በመቀጠል “እግዚአብሔር” (ሙሴ የተጠቀመው የእግዚአብሔር ስም እግዚአብሔር ከፍጥረቱ ጋር ያለውን ግንኙነት የሚገልጠውን ኤሎሂም የሚለውን ስም ሳይሆን የቃል ኪዳንና “የግል” ስሙን ነው) ያደረገውን ነገር “ሁሉ” ተረከለት። መዝሙረኛው እንዳዘዘው (መዝ 145፥5-7፡12)፣ እንዲሁ ሙሴ አደረገ፤ እግዚአብሔር እስራኤልን ከግብፅ ያወጣበትንና ቀጥሎም በመንገዳቸው በገጠማቸው መከራቸው ሁሉ ላይ ያደረገላቸውን አስደናቂ ሥራና የተትረፈረፈ በጎነት ዘረዘረለት።

9-12 የሰማው ዜና ከዮቶር ውስጥ “እግዚአብሔር ይመስገን!” የሚል ምስጋና ፈንቅሎ እንዲወጣ አደረገ፤ ይህም አንድም ዮቶር የአባቶቹን አምላክ (ከዘፍ 25፥2 ጋር ያነጻ) ማምለኩን እንደ ቀጠለ ነው፤ አልያም ሙሴ በቤቱ በቁየባቸው አርባ ዓመታት መንፈሳዊ ነገር ቀስሟል ማለት ነው። ዮቶር በመቀጠል “አሁን እግዚአብሔር ከሌሎች አማልክት ሁሉ በላይ መሆኑን ዐውቄያለሁ” አለ። ይህ የምስክርነት ቀመር እግዚአብሔር በግብፅ ካሉት አማልክት ሁሉ በእጅጉ የበላይ የመሆኑ ግልጽ ማስረጃ ነው።

ቀጥሎም ዮቶር የሚቃጠል መሥዋዕት እና የደኅንነት መሥዋዕት (አመት “ሌሎች መሥዋዕቶች”) ለእግዚአብሔር (ኤሎሂም) “ወሰደ” ወይም “አመጣ”። “አመጣ” እንስኳትን ለመሥዋዕት ለማቅረብ ወይም ለማዘጋጀት በተለምዶ የሚውል ቃል ነው፤ በብሉይ ኪዳን “ቍርባን ማቅረብ” በሚለው ትርጉም ይህ ቃል ፈጽሞ ጥቅም ላይ አልዋለም። በመሆኑም እንደ ካህን አይደለም ዮቶር እነዚህን መሥዋዕቶች “ያቀረበው”፤ ነገር ግን ከሙሴና ከአሮን ጋር “በእግዚአብሔር ፊት” አመለከ፤ ከእነርሱም ጋር ኅብረት አደረገ።

በዚህ ቦታ ያህዌ ከሚለው ቃል ኪዳናዊ፣ ግላዊ የእግዚአብሔር ስም ይልቅ ኤሎሂም የሚለው የእግዚአብሔር የወል ስም ነው የተጠቀሰው። ምክንያቱም ምናልባት እግዚአብሔር በአንድ ጊዜ ከአሕዛብና ከአይሁድ ጋር ግንኙነት እያደረገ በመሆኑ ይሆናል። በርግጥ ዮቶር እንግዳ ወገን፣ ባዕድ ነው (“ጌር” ነው፤ ሙሴ ለልጁ የሰጠው ጌርሳም የሚለው ስም እንደሚያመለክተው) ምንም እንኳ ለአማኝነቱ ከቍ 10-11 ድረስ ጠንካራ ምስክርነት ቢሰጥም። “በእግዚአብሔር ፊት” የሚለው ሐረግ በቀላሉ “የእግዚአብሔር ክብር” የሚለውን ሐሳብ የሚያንጸባርቅ ሊሆን ይችላል፤ በዚህ ዐይነት በሕዝቡ መካከል በሚኖረው አምላክ ፊት የቃል ኪዳን ምግብ መመገብን ያመለክታል።

13-16 ዮቶር በእስራኤል አስተዳደራዊ መዋቅር ላይ የማሻሻያ ሐሳብ በመጠቁመ የውጤታማነት ኤክስፐርት (ጠቢብ) ተደርጎ ተገልጾአል (ከቍ 17-23 ጋር ያነጻ) ። ይህንኑ ሐሳብ ሙሴ በእግዚአብሔር ፈቃድ ተግብሮታል። ከዚህ በፊት ሕዝቡ መመሪያ ለመቀበልና ፍትሕን ለማግኘት ወደ ሙሴ መምጣት ነበረባቸው።

17-23 ለዚህ ሕዝቡንና መሪያቸውን ላደከመው ረኻርም ጊዜ ለሚወስድ ሂደት ዮቶር ያመጣው መፍትሒ ሙሴን መንታ ኀላፊነት ወዳለው ሥራ እንዲገባ አድርጎታል፦ ይህም ለሕዝቡ ዋቢ (ጠበቃ) የመሆንና ለእግዚአብሔር ደግሞ የሕጉ ተርጓሚ በመሆን የሕዝቡ አስተማሪ መሆን ነው። ዮቶር እርሱ ያቀረበው ዕቅድ መተግበር ያለበት እግዚአብሔር ደስ ከተሰኘበት ብቻ እንደ ሆነም አስጠንቅቋል።



ይህ ሥዕል በብዙ ምሁራን ዘንድ የሲና ተራራ እንደ ሆነ የሚታሰብና ከላይ (ከአናት) ወደ ታች ወደ ሸለቆው በመመልከት የተወሰደ ሲሆን፣ የእስራኤል ሕዝብ የሰፈረበት ስፍራ ይሆናል። በዚህ ሥዕል ላይ በሸለቆው የሚታየው ሕንጻ (ቤት) የቅድስት ካትሪን ገዳም ነው።

የሙሴ ሥራ የሌሎችን ሰዎች ድጋፍ ማግኘት ያስፈልገዋል። በመሆኑም ሙሴ "ችሎታ ያላቸውን ሰዎች" ይመርጣል። ይህ ምንባብ ሙሴ የራሱን ሠራተኞች በራሱ ሥልጣን የመረጠ ቢመስልም ትክክለኛው ምርጫ ግን ዘዳ. 1፥9፡13 እንደሚያረጋግጠው የሁሉም ሕዝቦች ኀላፊነት ነው። የአመራር መሥመራቸው ወይም ሥራቸው "ዐዋጆችን" (ዝርዝር ዐዋጆችን)፣ "ሕጎች" (አጠቃላይ ዐዋጆችን)፣ "አኗኗር" (ማለት የሕይወት ዘዬዎችንና ተግባሮችን)፣ እና የእያንዳንዱን ሰው ሥራና ኀላፊነት በሚመለከት ለሕዝቡ መመሪያና ትምህርት መስጠት ነው።

እነዚህ ሰዎች የተመለመሉበት መሥፈርት "ብቁ የሆኑ" ወይም "ችሎታው ያላቸው" (ማለትም የዳኝነት የተፈጥሮ ክሂሎት ያላቸው)፣ "እግዚአብሔርን የሚፈሩ (የሚያከብሩ)"፣ እውነተኞች የሆኑ (ማለትም ታማኞች)፣ እና "በማታለል (በሙስና) የሚገኘውን ጥቅም የሚጸየፉ" የሚሉ ናቸው። እነዚህ ሰዎች በዐሥር በሚባዛ እልቅና ይሾማሉ፤ ሙሴ የመጨረሻው ይግባኝ ሰሚ ይሆናል።

24-27 እጅግ በሚያስገርም መልኩ፣ ሙሴ የዐማቱን ምክር ሰማ፤ እስራኤላዊ እንኳ ባልሆነ ሰው የተሰጠውን ትምህርት ተቀበለ።

፪. መለኮታዊ ሥነ ምግባር (19፥1-24፥18)

ሀ. የንስር ክንፍ ንግግር (19፥1-8)

1-2 በሦስተኛው ወር እስራኤል ራፊዲምን ለቀው (ቁ. 17፡1፤8 ይመ) ወደ ሲና ምድረ በዳ መጡ። "በተራራው ፊት ለፊት ያለው ምድረ በዳ" ኤር ራሃ በመባል ይታወቃል (ትርጉሙ "(የእጅ) መዳፍ" ማለት ነው)። ምክንያቱም ከባሕር ወለል በላይ ዐምስት ሺህ ጫማ ከፍታ ላይ የሚገኝ አራት መቶ እስኩዌር ካሬ ሜትር የሚሸፍን ዝርግ አምባ በመሆኑ ነው። በርካታ ተራሮች ከሲና ተራራ ጋር እንደ አንድ ተቁጥረዋል። አብዛኛዎቹ ምሁራን ይህን ተራራ ጌባል ሙሳ (ከኤርራህ ደቡባዊ ጫፍ 7,363 ጫማ ከፍታ ላይ ይገኛል) ነው ማለትን ይመርጣሉ፤ ምክንያቱም ከአምባው ጋር ግንኙነት ስላለው (20፥18 "በርቀትም ቆመ") እንዲሁም እጅግ በገዘፉ ግራጫማ ዐለቶች የተሞላ በመሆኑ ነው።

3-6 በ3፥12 ላይ ለሙሴ የተሰጠው "ምልክት" እዚህ ቦታ ይፈጸማል፡- ሙሴ "ወደ እግዚአብሔር ተራራ" ተመልሶ መጣ (3፥1)። ሙሴ ወደ ተራራው "በወጣ" ጊዜ፣ እግዚአብሔር "የንስር ክንፍ ንግግሩን" አቀረበ። የእግዚአብሔር ሕዝብ መንታ ስያሜ ተሰጥቷቸዋል፡- "የያዕቆብ ቤት" (የጅማሬያቸውን ታናሽነት የሚያስታውስ ነው፤ ከዘፍ 28፥13፤35፥11፤ 49፥7 ጋር ያነጻ) እና "የእስራኤል ሕዝብ" (ይሄ አሁን ያሉበትን ደረጃ ያመለክታል፤ ሕዝብ ወይም መንግሥት ሆነዋል)።

የንስር ክንፍ ተለዋጭ ዘይቤ በፍልስጥኤም ከሚገኙት ጥንብ አንሣዎች በተጨማሪ በሶርያ፣ በፍልስጥኤምና በዐረብ ከሚገኙት ከስምንቱ የንስር ዐይነቶች ውስጥ አንደኛውን የሚመለከት ሳይሆን አይቀርም። ምናልባት በዚህ ቦታ የኋለኞቹን የሚመለከት ሳይሆን አይቀርም። ይሄ ተለዋጭ ዘይቤ በሚገባ ተስፋፍቶ የተገለጸው የእግዚአብሔር ቸርነትና ርኅራኄ፣ ጥበቃ፣ ኃያልነትና ንቁነት ከግርማዊው ንስር ባሕርያት ጋር በተነጻጸረበት በዘዳ 32፥11 ላይ ነው። የንስር ጫጩቶች በእናታቸው አክናፍ ላይ ሰፍረው ከጎጇቸው ወጥተው የመብረርን ጥበብ እንደሚማሩ፣ እንዲሁ እግዚአብሔር እስራኤልን በፍቅር ተሸክሞ በሰላም አገባቸው።

በዚህ ስፍራ የተጠቀሰው ቃል ኪዳን፣ በመጀመሪያ ለአባቶች የተሰጠው ሲሆን፣ የመተላለፉና የመሰጠቱ ሁኔታ ቅድመ ሁኔታ የሌለው ነው፤ ነገር ግን በርግጥ በቃል ኪዳኑ የመጠቀምና በግል የመሳተፉ ጕዳይ ግን ቅድመ ሁኔታ አለው። ይሁን እንጂ በ ቁ. 5 ላይ የሚገኘው ‹‹. . . እንደ ሆነ (if)" የሚለው ቃል እስራኤላውያን ከጸጋው ወጥተው ሕግ ሥር እንዲወድቁ መንገድ ጠርጎላቸዋል ማለት አይደለም፤ ልክ ለአባቶች በተናገረው ተስፋ ውስጥ ቅድመ ሁኔታን አመልካች የሚመስል ቃል መገኘቱ፣ አባቶች (ዘፍ 22፥16-18፤ 26፥5) ወይም ደግሞ ዳዊት (2ሳሙ. 7፥14-15፤ 1ነገ 2፥4፤ 8፥25፤ እና ሌሎችም) ከጸጋው ወድቀዋል ማለት እንዳልሆነ ሁሉ።

ታዛዥና ቃል ኪዳን አክባሪ እስራኤል የምትለማመዳቸውን መለኮታዊ ባርኮቶች ሦስት ስሞች ጠቅለል አድርገው ይገልጻሉ፡- "የተወደደ ርስቴ"፣ "የካህናት መንግሥት"፣ እና "ቅዱስ ሕዝብ" ይሆናሉ። የመጀመሪያው እስራኤል ለተለየ ዐላማ የተዘጋጀች የእግዚአብሔር ክብርት ንብረትና ልዩ ጥሪት (ዘዳ 7፥6፤ 14፥2፤ 26፥18፤ መዝ 135፥4፤ ሚል 3፥17፤ ከቲቶ 2፥14፤ ከ1ጴጥ 2፥9 ጋር ያነጻ) እንደ ሆነች ያመለክታል። በተጨማሪም በመላ አገሪቱ ያሉ ዜጎች እያንዳንዳቸው ካህን ነገሥታት እና ንጉሣውያን ካህናት (ከኢሳ 61፥6፤ ከ1ጴጥ 2፥5፡9፤ ከራእይ 1፥6፤ 5፥10፤20፥6 ጋር ያነጻ) ይሆናሉ። ይህ አባባል "ቅዱስ ሕዝብ" የሚለው ሐረግ ሌላ ስያሜ አይደለም፤ የተለየ ማንነት ነው። መላው የእስራኤል ሕዝብ ለዓለም ሕዝቦች ሁሉ የእግዚአብሔር ጸጋ መካከለኛ (አስተላላፊ) እንዲሆኑ ተጠርተው ነበር (ከ12፥3ሐ ጋር ያነጻ)። የመጨረሻው ስያሜ እስራኤልን ከሌሎች ሀገሮች ልዩና ብቸኛ ሀገር ያደርጋታል፤ የዚህ ምክንያቱ አምላኳ እግዚአብሔር ልዩና ብቸኛ አምላክ በመሆኑና ዕቅዱና ሐሳቡም እንዲሁ ልዩ በመሆኑ ነው (ዘዳ 7፥6፤ 14፥2፡21፤ 26፥19፤ ኢሳ 62፥12፤ ከ1ጴጥ 2፥9 ጋር ያነጻ)።

እግዚአብሔር እስራኤልን በሞግዚትነት የሚያስተዳድር በትና እስራኤልም በእርሱ የበላይ ገዢነት ሥር የምትሆንበት መላው ስምምነት (ውል) በአስገራሚ ሁኔታ ግላዊ (በሁለቱ ልዩ ግንኙነት ላይ የተመሠረተ) ነው። ይህ ኪዳን የሚጀምረውም የሚጨርሰውም "ለእስራኤል ልጆች" በማለት ነው። የመጀመሪያውና የመጨረሻው ሐረጎች የሚተዋወቁት በአጽንዖት በተገለጠ "እናንተ" በሚል ተውላጠ ስም ሲሆን ሌሎች ሁለት "እናንተ"ዎች በቁ.4 ላይም ይገኛሉ።

7-8 ሕዝቡም "እግዚአብሔር ያለውን ሁሉ እናደርጋለን" ብለው መለሱ። አንዳንድ የሥነ መለኮት ምሁራን እግዚአብሔር ያለውን ሁሉ እናደርጋለን ብለው በችኮላ ቃል በመግባታቸው እስራኤልን ይተቻሉ፤ የተስፋውን ቃል ኪዳን መፈጸም ስላቃታቸውና፤ እንደ ተቺዎቹ አባባል፣ ከሕግ ሥር በመውደቃቸው። እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን ምላሽ የሰጠው

አስተያየት ግን ከላይ ከተሰጠው ትችት ጋር የሚቃረንና ይልቁን ደማቅ አምንታዊ ምላሽ ነው፡- “ያሉትም ሁሉ መልካም ነው። ታዲያ እኔን እንዲፈሩና ሁል ጊዜ ትእዛዞቼን እንዲጠብቁ እንደዚህ ያለ ልብ ቢኖራቸው ምን ነበረበት!” (ዘዳ 5፥28-29)።

ለ. የእግዚአብሔር ወደ ሲና መውረድ (19፥9-25)

9 ለእስራኤላውያን ሕጉ የተሰጠው በእግዚአብሔር ሳይሆን የሙሴ የራሱ ፈጠራ ነው በሚል ወደ ፊት ሊነሣ የሚችለውን ሰበብ ከወዲሁ ለማስወገድ እግዚአብሔር ማንም ሥጋ ለባሽ አማኝቶት የማያውቀውን ክብርና መፈራት በሙሴ ላይ አደረገ። ምንም እንኳ በዚህ ቦታ እግዚአብሔር ሙሴን “አንተ” ብሎ በግል ያነጋገረው ቢሆንም እንኳ፣ እግዚአብሔር በከባድ ደመና የመምጣቱ ሁኔታ ግን ለሕዝቡ ሁሉ ነው። በመሠረቱ እግዚአብሔር በሕዝቡ መካከል በደመናና በእሳት ዐምድ ያድር ነበር፤ በዚህ ቦታ ግን ደመናው ከባድና ጥቁር ነበር፤ (የእግዚአብሔር ድምፅ ፍጥረቱን ዘልቆ ሲሰማ) ምናልባትም የመብረቅ ብልጭታና ነጐድጓድም ነበር። እግዚአብሔር ለሙሴ በሚናገርበት ጊዜ (ዘዳ 4፥32-33 ያነጻ)፣ መላው እስራኤልና እውነተኛ የእስራኤል ትውልድ ሁሉ በዚያን ጊዜም ከዚያን በኋላም የሙሴን ቃላት ያምኑ ዘንድ ድምፁ በሰፈር ውስጥ ይሰማ ነበር።

10-15 በሦስተኛው ቀን እግዚአብሔርን ለማግኘት ለሚያደርጉት ውስጣዊ ዝግጅት ምልክት ይሆን ዘንድ ሕዝቡ ልብሳቸውን ማጠብ፣ ከተራራው መራቅና ከግብረ ሥጋ ግንኙነት መታቀብ ነበረባቸው። የዚህ ምንባብ ነገረ መለኮት እግዚአብሔርን ለመገናኘት ብቁ መሆንና እግዚአብሔርን ለማምለክ ዝግጅት ማድረግን የሚመለከት ነው (3፥5 ይመ)። ይህ ማለት ልብሶችን የማጠብና በጋብቻ ውስጥ ከሚፈጸም የግብረ ሥጋ ግንኙነት የመታቀብ ድርጊቶች በራሳቸው ውስጣዊ መንፈሳዊ ዕሴት አላቸው ማለት አይደለም፤ ነገር ግን ውጫዊው ድርጊት ውስጣዊ መቀደስን የመሻታቸው አመላካች ነው።

ተራራውን መከለል በ3፥5 እንደ ተደረገው ዐይነት ጊዜያዊ ወሰን የማበጀት ድርጊት ብቻ ነው፤ ይሁን እንጂ ቅዱሱን እግዚአብሔርን በተገቢው መንገድ ማምለክ እንዲቻል ለማገዝ ሲባል የተደረገ ነው። ወደዚህ ወደ ተቀደሰ ትዕይንት ዘው ብሎ መግባት በሞት መቀጣትን ያስከትላል፤ ምክንያቱም ይህን ግልጽ፣ መለኮታዊ ትእዛዝ የሚተላለፍ ሰው ግበረ ገብ የጐደለው፣ ሃይማኖትን የሚያቃልል በመሆኑ የዚህ ዐይነቱ ሰው በጉባኤው መገኘት ቀሪውን አምላኪ ማኅበረ ሰብ ይበክላል። ይህም በዘኍ 15፥30-31 ላይ “ትእዛዙንም ስለ ጣሰ” ከተባለው ጋር ወይም ደግሞ ዐዲስ ኪዳን “የጸጋንም መንፈስ ያቃሰፋ” (ዕብ 10፥26-31) ከሚለው ጋር ተመሳሳይነት አለው። መለኮት ከፍ ባለ ድምፅ ለረዥም ጊዜ ከተነፋ በኋላ ነው ሕዝቡ ለሁለተኛ ጊዜ ተራራውን መውጣት የቻሉት (ቍ. 13ለ)።

16-19 እግዚአብሔር ወደ ተራራው የወረደው በጣም አስደናቂ በሆነ የተፈጥሮ ኀይላት በፈጠሩት ነውጥ መካከል ነው፡- ነጐድጓድና መብረቅ (ከመዝ 77፥18፤ ከዕብ 12፥18-19፤ ከራእይ 4፥5፤ 8፥5፤ 11፥19 ጋር ያነጻ)፤ እጅግ በጣም በሚያምባርቅ የመለከት ድምፅ (ከራእ 1፥10፤4፥1 ጋር ያነጻ)፤ እና ከባድ ደመና (ዘዳ 19፥9፤ 2ዜና 5፥14)። ይህ በሕዝቡ ላይ ጥልቅ የሆነ ሥነ ምግባራዊ ስሜት ፈጥሯል፤ ምክንያቱም ባሕርዩንና ማንነቱን በሕጉ አማካይነት ሊገልጥ ባለ ታላቅ ክብር ባለው ግርማዊ አምላክ ፊት ናቸውና።

20-25 ሙሴ ለዚህ አስደማሚ ትዕይንት የሰጠው ምላሽ በዚህ ቦታ አልተገለጸም፤ ነገር ግን በዕብ 12፥21 የሙሴ ምላሽ “በፍርሀት እንቀጠቀጣለሁ” የሚል ነው። የእግዚአብሔር ምላሽ በቍ. 21 ላይ ይመጣል። ሕዝቡን ወደ እግዚአብሔር ሀልዎት በመዳፈር እንዳይቀርብ እንዲያስጠነቅቅ ለሙሴ ተናገረው። ጣምራው አጽንዖት (ቍ.12-13፡21-22፡25) መደበኛ የሥነጽሑፍ ዘዬ ሲሆን ዐላማው ትኩረት የሚያሻውን ርእስ ልብ እንድንል ማድረግ ነው። በመሆኑም በመለኮትና በሰዎች መካከል የተለለው ወሰን በሚች ሥጋ ለባሾች በቀላሉ ሊታይ አይገባውም።

ወደ እግዚአብሔር የሚቀርቡ ካህናት “እንኳ” ራሳቸውን መቀደስ ነበረባቸው። በርግጥ ይህ አሮናዊ ክህነት አልነበረም፤ ምክንያቱም እርሱ ገና አልተመሠረተም ነበርና። ከእያንዳንዱ እስራኤላዊ ቤተ ሰብ ለእግዚአብሔር ተለይተው የተቀደሱ “በኵራት” መሆን አለባቸው (13፥2)። በኋላ ላይ ነው የሌዊ ነገድ እያንዳንዱን በኵር ወንድ የተካው (ዘኍ 3፥45)። ሕዝቡ ይህን ትእዛዝ ቢጥሱ እግዚአብሔር “ቍጣውን ያወርድባቸዋል።”

ሐ. ዐሠርቱ ትእዛዛት (20፥1-17)

የእግዚአብሔር ሕግ ሦስት ጣምራ ዐላማ ነው፡- (1) ከእግዚአብሔር ጋር ባላቸው ግንኙነት የግብረ ገብ ርቀት በመፈጠሩ ሰዎች እጅግ አስከፊ በሆነ ሁኔታ ኀጢአተኞች መሆናቸውን ለማሳየት፣ (2) ሰዎች ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ካለባቸው መካከለኛ የሚያስፈልጋቸው መሆኑን ለመግለጽ፣ እና (3) ሰዎች በግብረ ገብ ሕጉ የተገለጠውን የእግዚአብሔርን የማይለወጥ ፍጹም ባሕርይ እንደ መመሪያቸው በመውሰድ እንዴት በተሻለ ሁኔታ የተትረፈረፈ ሕይወት መኖር እንደሚችሉ ለማመላከት ነው።

የእነዚህ ትእዛዛት ሰዋስዋዊ ቅርጽ ጥቂት አስተያየት የሚያሻው ነው። ከቍ. 2-17 ሦስት አምንታዊ አረፍተ ነገሮች ብቻ ናቸው የሚገኙት። ሁሉም የተደመደመ (ፍጹም) ግስ (finite verb) የላቸውም (ቍ. 2፡8፡12)። እነዚህን ሐረጎች በሚከተለው ሁኔታ ማስቀመጥ ይቻላል፡-

1. “እኔ፣ እግዚአብሔር አምላክህ **ስሆን** . . . ” (ስለዚህ ከአንደኛ እስከ ሦስተኛ ያሉትን ትእዛዛት ጠብቅ)
2. “የሰንበትን ቀን **እያስታወስህ** (በማስታወስ) . . . ” (ስለዚህ ከቍ. 9-11 ያሉትን አድርግ)
3. “አባትና እናትህን **እያከበርህ** (በማክበር) . . . ” (ስለዚህ ከስድስተኛው እስከ ዐሥረኛው ያሉትን ትእዛዛት ጠብቅ)

ከዚህ የምናገኘው ንድፍ የሚከተለው ነው፡- (1) ትክክለኛ ግንኙነት ከእግዚአብሔር ጋር (ቍ. 2-7)፣ (2) ትክክለኛ ግንኙነት እግዚአብሔርን በማምለክ (ቍ. 8-11)፣ እና (3) ትክክለኛ ግንኙነት ከኅብረተ ሰብ ጋር (ቍ. 12-17)።

1-2 የእግዚአብሔር ትእዛዛት በቀላሉ “እነዚህን ቃሎች ሁሉ” በሚል ሐረግ ተገልጸዋል። “ዐሠርቱ ትእዛዛት” የሚለው ርእስ የተወሰደው ከዘፀ 34፥28 እና ከዘዳ 4፥13 ነው፤ ዕብ 12፥19 ግን “ቃልን የሚያሰማ ድምፅ” ይለዋል። እነዚህን ትእዛዛት የተናገረው እግዚአብሔር ራሱ ነው (ከዘዳ 5፥12-13፡ 32-33 ጋር ያነጻ)።

ሕግ ሰጪው ሕጉን በጸጋ ድባብ ውስጥ ነው ያስቀመጠው፤ ምክንያቱም “እግዚአብሔር” የሚለውን ስሙን የገለጠው ሕዝቡን ከግብፅ ምድር ባወጣበት የትድግና ጸጋው ነውና። “እኔ” አጽንዖትም የአረፍተ ነገሩ ባለቤትም ነው፤ “እግዚአብሔር” ተሳቢ ነው። በዚህ ቦታ የእግዚአብሔርን ስም ማስተዋወቁ የዘፀአትን ድርጊት ሁለት ጫፎች ያገናኛቸዋል፡- በዘፀ 3፥14 እና 6፥2፣ እግዚአብሔር ሕዝቡን ከግብፅ አወጣለሁ ያለበትን ቃል ኪዳን ከስሙ ጋር አቁራኝቶታል። አሁን የተስፋው ቃል ኪዳን በመፈጸሙ እግዚአብሔር እንደ ገና ስሙን ያውጃል። እግዚአብሔር የሆነው ሁሉ፣ የሚለው ሁሉ እና የሚያደርገው ሁሉ በአንድ ኀይለ ቃል ይጠቃለላል፡- “እኔ

እግዚአብሔር ነኝ።” ቀሪው የአረፍተ ነገሩ ክፍል ከቃለ እግዚአብሔር ታላላቅ ኀይለ ቃሎች አንዱ ሲሆን የእግዚአብሔርን ባሕርይና ቸርነት ለመግለጽ 125 ጊዜ ጥቅም ላይ ውሏል።

3 በመጀመሪያው ትእዛዝ አንድ አስቸጋሪ አገላለጽ ብቻ አለ፡- ይህም “በፊቴ/ከእኔ ሌላ” (before/besides me) የሚለው ሐረግ ነው። በዕብራይስጥ የትም ቦታ ይሄ ሐረግ “ከእኔ በቀር” የሚል ትርጉም የለውም። ምናልባት ከሁሉ የተሻለው ትርጉም “ከእኔ ይልቅ ሌሎች አማልክትን አትምረጥ” የሚለው ነው። ያም ሆነ ይህ ውጤቱ ተመሳሳይ ነው፡- እግዚአብሔር ብቸኛው እውነተኛ አምላክ ነው።

4-6 ሁለተኛው ትእዛዝ ከሚመለከው አምላክ ይልቅ የአምልኮውን መንገድ ይተርካል። ሁለት ክፍሎች አሉት፡- ትእዛዙ (ቁ. 4-5ሀ) እና ቅጣቱ (ቁ. 5ለ-6)። በብሉይ ኪዳን ጣዖታትንና የተቀረጹ ምስሎችን የሚገልጹ በርካታ ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ስያሜዎች (ዐሥራ አራት ናቸው) ይገኛሉ። ቍጥር 23 የተከለከሉት ጣዖታት ክብር የተሠሩ አማልክት ወይም ከወርቅ የተሠሩ አማልክት እንደ ሆኑ ይገልጻል። እንዲሁም “ጣዖት” ከድንጋይና ከዕንጨት የተቀረጹ ምስሎችን ወደ በኋላ ላይ ደግሞ ክብረት የተሠሩትንም ያጠቃልላል። ፔስል (“ጣዖት”) የተቀረጸ የሰው ወይም የእንስሳን ምስል የሚያመለክት በመሆኑ፣ “አምሳያ” ወይም “ቅርጽ” የሚለው ህልውና ባላቸው ወይም አእምሮ ለሚፈጥራቸውና በሥዕል ለሚገለጡት ሊውል ይችላል። ከእነዚህ አንዳቸውንም ለማምለክ በማቀድ መሠራት የለባቸውም። ይህ አባባል ኪነ ጥበባዊ ክሂሎትን ለማዳፈን ያለመ አይደለም፤ ይልቁን እንደ ከነዓናውያን ጣዖታት ከእውነተኛ አምልኮተ እግዚአብሔር የሕዝቡን ልብ በመሥረቅ ተገቢ ያልሆኑ ምትኮችን እንዳይሠሩ ለመከላከል የተደረገ ነው። ምትኮችን ማበጀት ፈጽሞ የተከለከለ አለመሆኑን ለመረዳት የቃል ኪዳኑን ታቦት ከነብዙ ጌጦቹ (ሁሉም በእግዚአብሔር ትእዛዝ የተሠራውን) መመልከቱ ብቻ በቂ ነው።

“አትስገድላቸው፣ አታምልካቸውም” የንግግር ዘይቤ ሲሆን አንድን ነጠላ ሐሳብ በዚህ ዐውድ “አምልኮ ማቅረብ” የሚለውን በሁለት አባባሎች መግለጽ ነው። ይህ አገላለጽ በእስራኤል የተከለከሉ ባዕዳን አማልክትን በሚመለከት ብቻ ጥቅም ላይ የሚውል ነው።

ከዚህ ትእዛዝ ጋር ተያይዘው የተሰጡት ዕቀባዎች የሚጀምሩት “እኔ እግዚአብሔር አምላክ ነኝ (ያህዌ) ቀናተኛ አምላክ ነኝ” በሚለው ግርማዊ ማስታወሻ ነው። “ቀናተኛ” ወይም “ቀናኢ”፤ የሚለው ቃል በስፋት በሚታወቅበት የተሳሳተ ግንዛቤ እግዚአብሔር በባሕርዩ ተጠራጣሪ፣ ማንንም የማያምን፣ ወይም ደግሞ በተሳሳተ መንገድ በሌሎች መከናወን የሚቀና ነው የሚል ግንዛቤ መውሰድ ፈጽሞ አይገባም። ቃሉ ለእግዚአብሔር ሲውል የሚያመለክተው፣ (1) ፍጹም መሰጠትን የሚጠይቀውን ያን ባሕርዩን (ዘፀ 34፥14፤ ዘዳ 4፥24፤ 5፥9፤ 6፥15)፣ (2) በሚቃወሙት ሁሉ ላይ የሚቃጠለውን ያን ቍጣውን (ዘኁ 25፥11፤ ዘዳ 29፥20፤ መዝ 79፥5፤ እና ሌሎችም)፤ እና ሕዝቡን ለመታደግ ያፈሰሰውን ጕልበቱን (2ነገ 19፥31፤ ኢሳ 9፥7፤ 37፥32፤ እና ሌሎችም) ነው። ስለዚህ ቃለ እግዚአብሔር በብዙ ቦታዎች መንፈሳዊ አመንዝራነት ብሎ የሚጠራውን ጣዖት አምልኮ የሚያነሣሣ ወይም ደግሞ ለእግዚአብሔር በሚገባው ክብር፣ ግርማና ዝና ላይ ማንኛውንም ዐይነት ተቀናቃኝ የሚፈቅድ ነገር ሁሉ እግዚአብሔር ለማይለዋውጠው ለገዛ ራሱ ባሕርይና ማንነት ያለውን ቅናት ያስነሣል።

ልጆች ብዙ ጊዜ በግላቸው እግዚአብሔርን በመጥላት የአባቶቻቸውን ኀጢአት ይደግማሉ፤ እናም እንደ አባቶቻቸው ይቀጣሉ። በዘዳ 24፥16 ላይ ሙሴ ቅጣቱ የመጣው በራሳቸው በልጆቹ ኀጢአት የተነሣ መሆኑን ግልጽ ያደርጋል። ያለመታዘዝ ውጤት ለተወሰነ ጊዜ ይቈያል፤ ነገር ግን እግዚአብሔርን የመውደድ ውጤት በጣም ረኀቦም ዕድሜ አለው “እስከ ሺህ (ትውልድ) ነው።”

7 ሦስተኛው ትእዛዝ አንደበታችን እውነተኛ የሆነ ሙገሳን ለእግዚአብሔር ማቅረብ ያለበት መሆኑን የሚመለከት ነው። የእግዚአብሔር “ስም” ሲል መጠሪያውን በቃል መናገርን ብቻ ከማለት በእጅጉ ያለፈ አንድምታ አለው። እናም የእግዚአብሔር ስም ሲል የሚከተሉትን ያጠቃልላል፡- 1) ባሕርዩን፣ ማንነቱን፣ ደግሞም ሰብእናውን (መዝ 20፥1፤ ሉቃ 24፥47፤ ዮሐ 1፥12)፣ 2) ትምህርቱን ወይም ነገረ መለኮቱን (መዝ 22፥22፤ ዮሐ 17፥6፡26)፣ እና 3) ግብረ ገባዊና ሥነ ምግባራዊ ትምህርቱን (ሚክ 4፥5)።

የእግዚአብሔርን ስም በአፍ (በአንደበት) “በከንቱ” “መጥራት” ወይም “ማንሣት” ማለት “አላግባብ መጠቀም” ማለት ነው፤ ማለትም ያለ ዐላማ መጠቀም ማለት ነው። በአንደበት የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ ከምንጠራባቸው መንገዶች፣ 1) አድናቆትን በመግለጽ ወቅት፣ 2) በንግግርና በጸሎት መካከል ያሉትን ክፍተቶች ለመሙላት፣ እና 3) ሐሰት የሆነን ነገር ለማረጋገጥ ስሙን መጥራት ይገኙበታል። ይህ ትእዛዝ ሕጋዊ የሆኑትን መሐላዎች አይመለከትም፤ በብዛት ይገኛሉና (ለምሳሌ፣ ዘዳ 6፥13፤ መዝ 63፥11፤ ኢሳ 45፥23፤ ኤር 4፥2፤ 12፥16፤ ሮሜ 1፥9፤ 9፥1፤ 1ቆሮ 15፥31፤ ፊልጵ 1፥8፤ ራእይ 10፥5-6)።

8-11 አራተኛው ትእዛዝ ሰንበትን ስለ ማክበር ይናገራል። “ሰንበት” የሚለው ቃል የተገኘው “ማረፍ ወይም ሥራን ማቆም” ከሚለው ግስ ነው። ዕብራውያን ሰባተኛውን ቀን ለእግዚአብሔር ለአምላካቸው እንዲለዩ (እንዲቀድሱ) ታዘዋል። ሰንበትን አክብሩ የሚለው ትእዛዝ አንድን ሰው ከጊዜው ላይ የተወሰነውን እግዚአብሔርን ለማምለክና ለማገልገል እንዲያውል የሚጠይቅ በመሆኑ ሥነ ምግባራዊ (ግብረ ገባዊ) ነው፤ ነገር ግን ይህ የሚደረገው በሰንበት ይሁን ብሎ ስለሚያዝ በአል ከማክበር ጋር የተያያዘ (ceremonial) ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ከሞቱ ኋላም በትንሣኤው የፈጸመውን የእግዚአብሔርን ዐዲስ ነጻ የማውጣት ሥራ የመጀመሪያውን ቀን በማክበር ቀደም ብሎ በዘሌ 23 በተጠቀሱ ተምሳሌታዊ በሆኑ በዓላት ተጠቅሞአል፡- “ከሰንበት በኋላ የመጀመሪያው ቀን” (ቁ. 15)፤ “በመጀመሪያው ቀን የተቀደሰ ጉባኤ አድርጉ” (ቁ. 7)፤ “የመጀመሪያው ቀን የተቀደሰ ጉባኤ ነውና . . . በስምንተኛው ቀን” (ቁ. 35-36)። በርግጥ እነዚህ በዓላት ክርስቲያኖች አሁን በየአሐዱ የሚያከብሩትን በትክክል የሚያመላክቱ ድርጊቶች ናቸው!

ይህ ቀን የሚከበርበት ምክንያት በእግዚአብሔር ሁለት ሥራዎች ላይ የተመሠረተ ነው፡- አንዱ ወደ ኋላ የሚመለከት ነው (ቁ. 11 ከፍጥረት ሥራ ጋር ያገናኘዋል)፤ ይህም የመጨረሻው ቀን ወደሚሆነው ዐዲሱ የእግዚአብሔር ዕረፍት ያመለክታል፤ ሌላው በእግዚአብሔር የድነት ታሪክ ውስጥ ወደፊት የሚመለከት ነው (ዘዳ 5፥15 ከግብፅ ከመውጣት ጋር ያገናኘዋል)፤ ይህም በመጨረሻው ቀን ወደሚፈጸመው ዐዲስ ፀአት ወይም መውጣት ያመለክታል። ይህ ትርጓሜ የተወለደው ሰንበት የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ሌላኛው “ምልክት” በመሆኑ ነው (31፥12-17 ይመ) ።

12 ወላጆችህን “አክብር” የሚለው ትእዛዝ (1) ለወላጆች ትልቅ ክብር መስጠትን (ከምሳ 4፥8 ጋር ያነጻ)፤ (2) ክብካቤ ማድረግና ፍቅር ማሳየትን (መዝ 91፥15)፤ እና (3) አክብሮት ማሳየትን ወይም መፍራትን (ሌዋ 19፥3) ይመለከታል። ወላጆችን ማክበር ተገቢ ነው፤ ነገር ግን የትም ቦታ ቃላቸው ከእግዚአብሔር ቃል ጋር በተቃርኖ እንዲቆም ወይም ደግሞ

የእግዚአብሔርን ቃል እንዲተካ አይገባም። በኤፌሶን 6፡2-3 የራስን ወላጅ ከማክበር ትእዛዝ ጋር ተያይዞ የተሰጠው ተስፋ ለየት ያለ ነው፤ ምንም እንኳ የሕይወትን ስጦታ የሚመለከተው ተስፋ ከትእዛዛቱ ሁሉ ጐልቶ የሚታይ ቢሆንም (ዘፀ 4፥1፤ 8፥1፤ 16፥20፤ 30፥15-16)። የእስራኤል በምርኮ መጋዝ ምክንያቱ በከፊል ወላጆቻቸውን አለማክበር ነው (ሕዝ 22፥7፡15)።

13 ስድስተኛው ትእዛዝ መግደልን ይከለክላል። ከዚህ ትእዛዝ ጀርባ ያለው ሥነ ምግባራዊ ነገረ መለኮት ሰዎች ሁሉ በእግዚአብሔር አምሳል ተፈጥረዋል የሚል ነው (ዘፍ 1፥26-27፥9፡16)። በዕብራይስጥ መግደልን የሚገልጹ ሰባት ቃላት ቢኖሩም፣ እዚህ ቦታ የተጠቀሰው ቃል "ራሳ"፤ በብሉይ ኪዳን አርባ ሰባት ጊዜ ብቻ ነው የተጠቀሰው። ዐስቦና ዐቅዶ መግደልን" የሚመለከት ሐሳብ የያዘው ቃል ግን ይሄው ብቻ ነው። እናም ይሄ እገዳ እንስሳትን መግደልን (ዘፍ 9፥3)፣ ቤተ ሰብን (ቤትን) በሌሊት ከሚመጡ ዘራፊዎች መከላከልን (ዘፀ 22፥2)፣ በአደጋ የሚከሠት መግደልን (ዘዳ 19፥5)፣ መንግሥት በነፍስ ገዳዮች የሚፈጸመውን የሞት ቅጣት፣ (ዘፍ 9፥6) ወይም ደግሞ የራስ ሀገር ጦርነት ውስጥ ስትገባ መሳተፍን አይመለከትም። ይሁን እንጂ ራስን በገዛ እጅ ማጥፋትን፣ በእጅ አዙር ማስገደልን (2ሳሙ 12፥9)፣ እና ሥልጣን ኖሯቸው ነፍስ ገዳዮችን ከመቅጣት ቸል የሚሉትን (1ነገ 21፥19) ግን ይመለከታል።

14 ሰባተኛው ትእዛዝ ማመንዘርን ይከለክላል። "አታመንዝር" የሚለው ግስ ለወንድም ለሴትም ይሆናል። የማመንዘር ኀጢአት ቅጣቱ ሞት ሲሆን (ዘዳ 22፥22)፣ ድንግል ሴትን መድፈር ቅጣቱ የተደፈረችውን ማግባት ወይም የገንዘብ መቀጮ ነው (ዘፀ 22፥16-17፤ ዘዳ 22፥23-29)። በብሉይ ኪዳን ምንዝር ከዝሙት (ከሴሰኝነት) ልዩነት እንዳለው ተደርጎ ተገልጸአል።

15 ስምንተኛው ትእዛዝ ሰውንም ሆነ ቍሳቍስን መስረቅን ይከለክላል። ይህ ትእዛዝ የሁሉ ነገር ባለቤት እግዚአብሔር መሆኑን መነሻ ያደርጋል (ከመዝ 24፥1፤ 115፥16 ጋር ያነጻ) እናም የመስጠትም የመውሰድም ሥልጣን የእርሱ ነው የሚል ነው። ስለዚህ ማንም ሰው የገዛ ወገኑ የሆነን ሌላ ሰው በጭካኔ በባርነት መግዛት፣ ወይም ጠልፎ መውሰድ ወይም ደግሞ የራሱ ያልሆነውን ወይም ያልተሰጠውን ንብረት መቀማት የለበትም።

16 ዘጠነኛው ትእዛዝ በመላ ሕይወትና ኑሮ እውነተኛ መሆንን የሚያመለክት ነው፤ ምንም እንኳ ቃሉ በዋነኛነት የእስራኤልን የፍርድ ሂደት የሚያንጸባርቅ ቢሆንም። እውነትን ማቃለል ማንነቱና ባሕርዩ እውነት የሆነውን አምላክ መናቅ ነው።

17 ዐሥረኛው ትእዛዝ መመኘትን ይከለክላል፤ ማለትም "አጥብቆ መመኘት" "በጣም መናፈቅ" "አጥብቆ መጓጓት" (ከዘዳ 5፥21 ጋር ያነጻ) ነው። ይህ ትእዛዝ የአንድን ሰው ውስጣዊ ሐሳብ (ልብ) የሚመለከት ሲሆን ቀደም ብለው የተጠቀሱት ዘጠኙም ትእዛዛት አንዳቸውም ሜዳዊና ውጫዊ ድርጊት ብቻ እንደሚያመለክቱ ተደርገው መወሰድ እንደሌለባቸው ያሳያል። ያን ድርጊት ለመፈጸም የገፋውን ውስጣዊ ግፊት ሁሉ ያጠቃልላል (ከ1ጢሞ 6፥6 ጋር ያነጻ)።

መ. ለእግዚአብሔር መገለጥ የሕዝቡ ምላሽ (20፥18-21)

18 የእግዚአብሔርን መገለጥ ያበሠረው እጅግ አስፈሪና አስደናቂ ትዕይንት ሕዝቡን እጅግ አስፈራቸው። በ19፥16-19 የተገለጸው በዚህ ቦታ ሕዝቡ ለክሥተቱ ከሰጠው ምላሽ አንጻር ያው ድርጊት በድጋሚ ተገልጸአል። "ተራራው ይጤስ" ነበር ምክንያቱም "በእሳት ተያይዞ" ነበርና (ዘዳ 5፥23)።

19 ሕዝቡ በድንገት ወደ እግዚአብሔር ቅዱስ ሀልዎት የመቅረብ ፍላጎት አልነበራቸውም (ከዕብ 12፥19 ጋር ያነጻ)። በእነርሱና በእግዚአብሔር መሃል የሚቆም መካከለኛ ካህን ወይም ደግሞ ወክሏቸው የሚቆም ሰው እንደሚያስፈልጋቸው በደመነፍስ ተረድተው ነበር። ከዚህ ከሕዝቡ የክህነት አገልግሎት ፍላጎት ከብሉይ ኪዳን ታላላቅ መገለጦች አንዱ የሆነውና ረዥም ሂደቶችን ያሳለፈው የመሲሕ መሰጠት የተስፋ ቃል ይፋ ሆነ። እሱም የእግዚአብሔርን ቃል እንዳመጣላቸው እንደ ሙሴ ዐይነት "ነቢይ" ይሆናል (ዘዳ 18፥15-22 ይመ)። በዚህ ስምምነት መሠረት ሕዝቡ "በርቀት ቆሙ" እናም ሙሴ የእግዚአብሔርን ቃል ለእነርሱ አመጣላቸው።

20-21 ሙሴ ሕዝቡን "አትፍሩ" አላቸው (ከ14፥13 ጋር ያነጻ)፤ እግዚአብሔር የመጣው እስራኤልን ሊያጠፋ ሳይሆን (ከዘዳ 5፥24-25 ጋር ያነጻ) ይልቁን ሊፈትናቸው ነውና። ይህ ጥቅስ ሁለት ዐይነት "ፍርሀቶችን" ያነጻጽራል፡- የሚያሠቃይ ፍርሀት (ከበደለኝነት ስሜት ወይም ደግሞ ካልተጨበጠ ዛቻ የሚመጣና ወደ እስራት የሚያስገባ ነው) ወይም ሰላማዊ ፍርሀት (በእግዚአብሔር ፍጹም መደገፍንና ማመንን የሚያመጣ አመለካከት ነው (ከዘፍ 22፥12 ጋር ያነጻ)። ይህ ሁለተኛው ዐይነት ፍርሀት ኀጢአት እንዳንሠራ ያደርገናል (ከምሳ 1፥7፤ ከመክ 12፥13፤ ከሌሎችም ጋር ያነጻ)።

ዐዲስ የተሾመው የእስራኤል መካከለኛ እግዚአብሔር ወደሚገኝበት ጥቅጥቅ ወዳለው ጨለማ "ተጠጋ" ወይም "ቀረበ" እና በቃል ኪዳኑ መጽሐፍ ውስጥ የተሰጡትን መመሪያዎች ተቀበለ።



ሙሴ ዐሠርቱን ትዕዛዛት በተቀበቀበት በሲና መስክ፣ የፀሓይ መውጣት በጀበል ሙሳ በኩል እንደታየው።

ሠ. የኪዳኑ መጽሐፍ (20፥22-23፥33)

የዚህ ክፍል ርእስ የተወሰደው ከ24፥7 ነው። ሕጎቹ በሁለት ዐበይት ክፍሎች ሊከፈሉ ይችላሉ። የመጀመሪያው ቅድመ ሁኔታዊ ቅርጽ ያለው ዋናው ቅድመ ሁኔታና ተጨማሪ ንኡሳን አርእስት "እንደ ሆነ" ወይም "በሚሆንበት ጊዜ" በሚሉ፣ ምክንያትና ውጤትን ወይም በተፈጸመ ድርጊት ላይ የተመሠረተ ሕግን በሚገልጡ ቃላት የሚጀምር ነው፡- "አንድ ሰው . . . እንደ ሆነ" ወይም ደግሞ "አንድ ሰው . . . በሚያደርግባት ጊዜ" የሚሉ ዐይነት ቅርጾች ያሉት ነው። ሁለተኛው ዐይነት ቅድመ ሁኔታዊ ያልሆነ የተወሰነ ትእዛዝ ሲሆን በሁለተኛ መደብ የሚገለጽ (ባብዛኛው ነጠላ የሆነ) ሲሆን፣ ብዙ ጊዜ አሉታዊ ትእዛዞችን ወይም ክልከላዎችን የሚገልጽ ነው። አብዛኛው የዐሠርቱ ትእዛዛት ቅርጽ በዚህኛው ዐይነት (ሁልጊዜ እውነት በሆነ) የቀረበ ነው።

አንዳንድ ምሁራን ከዚህኛው ቅርጽ ሦስተኛ ምድብ ሕጎችን ያወጣሉ። እነዚህ ሕጎች በ21፥12፡ 15-17፤ 22፥19-20 ላይ ይገኛሉ። እነዚህ ትእዛዛት በአብዛኛው በጣም ዐጭር ናቸው (ዐምስት ያህል ዐጫጭር ቃላት ናቸው)፣ የሞትን ቅጣት የሚያስከትሉ ናቸው፤ ሁሉም በዕብራይስጡ ከግስ በሚፈጠር ቃል (participle) ይጀምራሉ። "የዕብራይስጡ የግሳዊ ቃል ሕጎች" በመባል ይታወቃሉ፤ ይሁን እንጂ ቅድመ ሁኔታዊና እውነታን የመግለጥ አገልግሎት ያላቸው ናቸው። እንግዲያው በኪዳኑ ቃል ስለ ሁለት ዐይነት መሠረታዊ ሕጎች መናገር እንችላለን።

1. መቅድም (መግቢያ) (20፥22-26)

22-23 ከቀዳሚው ሐሳብ ጋር ያለው ግንኙነት፡- ምንም እንኳ ምንም ዐይነት የሚታይ ቅርጽ፣ ምስል ወኪል ባታዩም፣ እግዚአብሔር ከሰማይ ሲናገር ሁላችሁም ሰምታችኋል፤ ስለዚህ እኔን በምንም ዐይነት ቍሳዊ ቅርጽ ልትመስሉኝ ፈጽሞ እንዳታስቡ። እንግዲያው በቅድሚያና ከሁሉ በፊት እግዚአብሔርን ስታመልኩት ፈጽሞ ከጣዖታት ጋር መደባለቅ የለባችሁም (20፥4-6 ይመ፤ ከዘዳ 4፥14-16 ጋር ያነጻ)።

24-26 እነዚህ አነስ ያሉ የጭቃ መሠዊያዎች በቅርጻቸውና በአገልግሎታቸው ጊዜያዊ ናቸው (ከዘፍ 12፥7፤ 13፥18፤ 22፥9 ጋር ያነጻ)። ከድንጋይ የሚሠሩ መሠዊያዎች በመሣሪያ ሊጠረቡ አይገባም፤ ምናልባትም ማንም ሰው ወደ ሆነ ቅርጽ ወይም ጣዖት እንዳይቀይራቸው ይሆናል። እንዲሁም ወደ መሠዊያ የሚያወጡ ደረጃዎች መሠራት የላባቸውም፤ አምላኪው ደረጃውን ሲወጣ እርቃኑ እንዳይጋለጥ ለመከላከል ነው። ወደ በኋላ ላይ ደረጃ ያላቸው መሠዊያዎችን መሥራት ሲፈቀድ (ዘሌ 9፥22፤ ሕዝ 43፥13-17)፣ ካህናቱ የበፍታ የውስጥ ሱሪ እንዲለብሱ ታዝዘዋል (ዘፀ 28፥40-42፤ ሕዝ 44፥18)።

2. ባሮችን የሚመለከቱ ሕጎች (21፡1-11)

1 የመሠዊያውን ሕገጋት ከሚደነግገው ክፍል ቀጥሎ ይሄ ርእስ (ቍ. 1 ርእስ ይመስላልና) መከተሉ እንግዳ ነው (20፥22-26)። 22፥18-23፥19 ላይ የሚገኘው ክፍል ባብዛኛው የሚናገረው ሥነ ምግባራዊና ጥበባዊ ምክሮችን፣ ሃይማኖታዊ ክብረ በዓላትን ከሚገልጡ ቀኖች ጋር በመሆኑ ይህ ርእስ ከ21፥2-22፥17 ያለውን ክፍል የሚመለከት እንደ ሆነ መቍጠሩ የተሻለ ነው። እነዚህ "ሕጎች" (ይልቁን "ፍርዶች") የተሰጡት ለእስራኤል የሲቪል አስተዳዳሪዎች (ገዢዎች) እንደ መመሪያ ያገለግሉ ዘንድ ነው። በአብዛኛው ጊዜያዊ በሆኑ ነገሮች ላይ ቢያተኩሩም፣ ነገር ግን በዐሠርቱ ትእዛዛት በግልጽ በተደነገጉ በዚህኛው ወይም በዚያኛው ትእዛዝ ላይ የተመሠረቱ ናቸው። ስለዚህም እነዚህ ሕግ ነክ ወይም ፖለቲካዊ ደንቦች ከዐሠርቱ ትእዛዛት ጋር ተያይዘው መቅረባቸው ተገቢ ነው።

2-4 ዕብራዊ ባሪያን የተመለከቱ ሕጎች የተጠቀሱት በ21፥1-11፤ ዘሌ 25፥39-43፤ ዘዳ 15፥12-18፤ እና ኤር 34፥8-22 ብቻ ነው። ይሁን እንጂ በእነዚህ ትእዛዛት መካከል ልዩነቶች አሉ። በዘዳ 15፥12 ዕብራዊው ባሪያ በሌላ ሰው ሲሸጥ እንመለከታለን፤ በዘሌውያን 25፥39 ግን ራሱን በራሱ ነው የሚሸጠው፤ የአገልግሎቱ ሁኔታ የሚወሰነውም በኢዮቤልዩ ድንጋጌ መሠረት ነው። በዘፀ 21፥2 እና በዘዳ 15፥12 የአገልግሎቱ ዘመን ስድስት ዓመት ነው። በዘፀ 21፥6 እና በዘዳ 15፥17 የባሪያው ፍላጎት ከሆነ አገልግሎቱ የሕይወት ዘመን ነው። "መግዛት" የሚለው ቃል የሕግ ሙያዊ ቃል ሲሆን የራስ ንብረት አድርጎ መውሰድ የሚል ትርጉም አለው። ከስድስት ዓመት አገልግሎት በኋላ ባሪያው "በነጻ" እንዲሰናበት ይደረጋል። ቃሉ "ነጻ ሰው" የሚል ፍቺ ያለው ይመስላል፤ እንደ ገና የዜግነት መብቱን እንዳገኘ ዐይነት ማለት ነው። ባሪያው ለብቻው ወይም ደግሞ ከሚስቱ ጋር ከጌታው ቤት ይሰናበታል፤ ይህም ሲገባ በነበረበት ሁኔታ ይወሰናል። ባሪያው በጌታው አማካይነት ተድሮ ልጆችን አፍርቶ ከሆነ፣ በዚህ ዐይነት ያገባት ሚስቱና የተወለዱለት ልጆቹ የጌታው ይሆናሉ።

5-6 "ጌታዬን . . . ሚስቴንና ልጆቼን እወዳለሁ" የሚለው ቃል ፍቅር (መውደድ) የሚለውን ግንኙነታዊ ስሜት የያዘ ሳይሆን የሕግ ቃል ነው (ከዘዳ 21፥15-17 ጋር ያነጻ፡- "የማይወዳት ቢሆን" ማለት "የሚጠላት ከሆነ" ማለት ነው)። የባሪያውን ጊዜያዊ አገልጋይነት ወደ ቋሚ አገልጋይነት የሚለውጡት "ጻሮች" ሲሆኑ፣ ሥነ ሥርዐቱም በጌታው በር መቃን አጠገብ ይፈጸማል። ጆሮን መብሳት በመካከለኛው ዘመን አሠራውያን ዘንድ አሳፋሪ የቅጣት ዐይነት ነበር።

7-11 ይህ ድንጋጌ በአባቷ ለባርነት ሳይሆን ለሚስትነት የምትሸጥ ልጃገረድን የሚመለከት ነው። ይሁን እንጂ "አገልጋይ" የሚል ስያሜ ተሰጥቷታል። ጋብቻው በውሉ መሠረት ባይፈጸም፤ ውሉን እንደ ማፍረስ ይቁጠራል፤ እናም ግዢው ልጃገረዲቱን ቤዝዎት እንድታገኝ (ነጻ እንድትወጣ) ሊፈቅድላት ይገባዋል፤ ከዚያ ቤተ ሰብ ውጭ ልትሸጥ አይገባም። ሁልጊዜ እንደ ራሱ ልጅ ወይም ደግሞ እንደ ማንኛዋም ነጻ ሴት ያድርግላት። አለዚያ የተጠቀሰው መቀጮ ይወሰንበታል።

3. ነፍስ ማጥፋትን የተመለከቱ ሕጎች

12-14 በዚህ ክፍል የሞትን ቅጣት የሚያስከትሉ ወንጀሎች በዝርዝር ቀርበዋል፡- ነፍስ መግደል፣ አባትን ወይም እናትን መምታት፣ ጠለፋ፣ ወይም አባት እናትን መሳደብ ናቸው። ነፍስን የመግደል ወንጀል በዘፍ 9፥6 የተሰጠውን መለኮታዊ ትእዛዝ ይጥሳል። ሰዎች በእግዚአብሔር ምሳሌ የተፈጠሩ በመሆኑ በሰው ውስጥ ያለውን የእግዚአብሔር መልክ ሆነ ብሎ ማጥፋት ምንም ዐይነት የገንዘብም ሆነ የቍሳቍስ ካሣ ሊዋጀው አይችልም። በድንገተኛ አደጋ የሚከሠት ሞት ሆነ ተብሎ ከሚፈጸም የነፍስ ማጥፋት ወንጀል ጋር ያለው ልዩነት በግልጽ ተቀምጧል። በድንገት ለሚፈጸም የነፍስ ማጥፋት አደጋ የመማጸኛ ከተሞች ይዘጋጃሉ (ዘኍ 35፥6-34፤ ከዘዳ 19፥1-13 ጋር ያነጻ)። ሆነ ብሎ ነፍስ ላጠፋ ወንጀለኛ ግን ምንም ዐይነት የማምለጫ ቦታ ሊሰጠው አይገባም። በዚህ ስፍራ ባልተለመደ ሁኔታ እግዚአብሔር በአንደኛ መደብ የተገለጸበትን ሁኔታ ልብ ይሏል።

15-17 በመጽሐፍ ቅዱሳዊ ሕግ የወላጆች ሥልጣን ከፍ ያለ በመሆኑ ወላጆችን መምታት ወይም መስደብ በሞት የሚያስቀጣ ወንጀል ነው። ቍጥር 15 እና 17 የዐምስተኛው ትእዛዝ ማብራሪያዎች ናቸው። በዚህ ቦታ እናትና አባት በአንድነት መጠቀሳቸው መሠረታዊ እኩልነታቸውን የሚያጐላ መሆኑን ልብ ይሏል። ጠለፋ በሞት የሚያስቀጣ የሆነበት ምክንያት የሰው ስርቆት በመሆኑ ነው።

4. የአካል ጕዳትን የተመለከቱ ሕጎች (21፥18-32)

ቀጥሎ የቀረቡት ከአካል ጕዳት ጋር የተያያዙ ዐምስት ጕዳዮች የሞት ቅጣት ሊያስከትሉ የሚችሉ ጥቃቶች ወይም በአካል ላይ የሚደርሱ ዐምስት አደጋዎች ናቸው።

18-19 የመጀመሪያው ምሳሌ ከሰው ጋር ተጣልቶ ክፉኛ ከተጐዳ በኋላ በሚገባ አገግሞ በበትር ርዳታ ደጅ ለደጅ መንቀሳቀስ የሚችል ሰውን የሚመለከት ነው። ይህ ዐይነቱ ጕዳት ከቍ. 23-25 የተጠቀሰውን "ዐይን በዐይን ፋንታ" የሚለውን ዐይነት ቅጣት አያስከትልም፤ ይሁን እንጂ ጕዳቱን ያደረሰው ሰው ተጐጂው ሰው ለደረሰበት "የጊዜ ኪሣራ" የገንዘብ ኪሣራና ለሕክምና ያወጣውን ወጪ በሙሉ መክፈል ይኖርበታል።

20-21 ሁለተኛው ጕዳይ በጌታው ከተመታ በኋላ “ለአንድ ወይም ለሁለት ቀን” ያህል ሲንገታገት ቈይቶ በመጨረሻው የሚሞት ባሪያን የሚመለከት ነው። ጌታው ሆነ ብሎ ሊገድለው ሳይሆን፣ የሥነ ሥርዐት እርምጃ ሊወስድበት ያደረገው ሙከራ ለሞት እንዳበቃው ተደርጎ በቀላሉ እንዲፈረድለት የሚያደርግ ሂደት ተጠቃሚ ነው። ይሄ ሕግ ከቍ 26-27 ካለው የጌቶቻቸውን ኪስ እስኪጐዳ ድረስ በባሮች ላይ የሚደረግ የጭካኔ ተግባርን ለመግታት ከተሰጠው ሕግ ጋር በአንድነት ሲታይ፣ የባሮችን ሰብኣዊ ክብር የሚያስጠብቅ የተሟላ ዐዲስ የሕግ አንቀጽ ይሆናል ማለት ነው። የዚህ ሕግ ዐላማ ጌታው በባሪያው ላይ ያለውን ሥልጣን መወሰን ነው።

22-25 ሦስተኛው ሁኔታ የሚመለከተው እርስ በርስ የሚጣሉ ሰዎች ካደረሱበት ጕዳት የተነሣ ያለ ቀኗ የምትወልድ ሴትን የሚመለከት ነው። ይህ ሕግ ሁለት አማራጮችን ያቀርባል፦ (1) “ብትወልድ ጕዳቱም ለክፉ የማይሰጥ ቢሆን” እና (2) “የከፋ ጕዳት ቢደርስ” የሚሉ ናቸው።

እናትዬውም ሕፃኗም ቢተርፉም እንኳ ጕዳት አድራሹ ካሣ የመክፈል ግዴታ አለበት (ከ18-19 *ጋር ያነጻ*)። የካሣው (መቀጮው) መጠን በባልዬው ይተመንና በዳኞች ውሳኔ ይጸድቃል። ነፍሰ ጡሯ ሴት ወይም ልጇ የከፋ ጕዳት ቢደርስባቸው፣ እኩል (ተመጣጣኝ) ካሣ እንዲከፈል ሕጉ ያዝዛል፦ “ሕይወት ስለ ሕይወት።” “ዐይን ስለ ዐይን . . . ” የሚለው እዚህ ቦታ የተጠቀሰው ሕግ በቍ 13 የተጠቀሰውን ፣ በአደጋ ለሚደርስ ሞት ተፈጻሚነት አይኖረውም የሚለውን የማያካትት ነው፤ ምክንያቱም ቅጣቱ ከደረሰው ጕዳት *ጋር* ተመጣጣኝ መሆን አለበት እንጂ ሊበልጥ አይገባውም። ይሁን እንጂ ዘጕ 35፥31 ሆነ ተብሎ ካልተፈጸመ የነፍስ ማጥፋት ወንጀል በቀር ሌሎቹን ምትክ ካሣ በመክፈል ቅጣቱ ሊቃለል እንደሚችል ይፈቅዳል። በዚህ ዐይነት ተከሳሽ ለሟቹ ወላጅ አባት ወይም ለሟቿ ባል የእያንዳንዱን ነፍስ ዋጋ (ቍ. 30 ይመለከቷል) አንዳቸው ወይም ሁለቱም ሞተው ከሆነ አምጥቶ ይከፍላል። ይህ ሕግ የሚከፈለውን የካሣ መጠን በገደብ ይወስናል።

26-27 አራተኛው ጕዳይ በጌታው ቋሚ የአካል ጕዳት የደረሰበትን ባሪያ የሚመለከት ነው፤ ወዲያው ነጻነቱን ይጐናጸፋል (ይሁንና ከቍ 20-21 *ጋር ያነጻ*)። ባሪያ እንደ ተራ ቍስ መቈጠር የለበትም። የኢኮኖሚ ዕቀባዎቹ የታቀዱት ምንም እንኳ ጌታው የባሪያው ሰብኣዊ መብትና ክብር ፈጽሞ ደንታ ባይሰጠውም፣ ንዋዩን ስላፈሰሰበት ሲል ብቻ ሥቃይ እንዳያበዛበት ለማድረግ ነው።

28-32 ዐምስተኛው የአካል ጕዳት ምሳሌ በተዋጊ በሬ የሚደርስን የሚመለከት ነው። ሰዎች በራሪዎቻቸው በሰዎች ላይ ለሚያደርሱት ጕዳት ተጠያቂዎች ናቸው። መጽሐፍ ቅዱስ ግድ የሚሰኘው ኢኮኖሚያዊ ለሆኑ ምክንያቶች ሳይሆን ይልቁን ሥነ ምግባራዊና ሃይማኖታዊ ለሆኑ ጕዳዮች ነው (ከዘፍ 9፥5-6 *ጋር ያነጻ*) ። ሕጉ የዕድሜ፣ የኑሮ ደረጃን ወይም ደግሞ የጸታ ጕዳይን ተንተርሶ ልዩነት አያደርግም።

5. በንብረት ላይ የሚደርሱ አደጋዎችን የተመለከቱ ሕጎች (21፥33-22፥15)

33-34 የሌላውን ሰው ንብረት መጥፋት ወይም መጕዳት የሚያስከትል የሚያስጠይቅ ግድ የለሽነት (ጕድጓድን ሳይከድኑ እንደ መተው ያለ) ሙሉ ካሣ መክፈልን ይጠይቃል። የሞተው እንስሳ የግዴለሹ ሰው ንብረት ሆኖ ለሞተው እንስሳ ግን ምትክ መክፈል ይኖርበታል።

35-36 ሁለተኛው የንብረት ጕዳት ካሣ ጕዳይ የሚመለከተው ሁለት እንስሳት ተዋግተው አንደኛው የጎረቤት እንስሳን ሕይወት ሲያጠፋ የሚከሠት ነው። ይህ ሲሆን በሕይወት ያለው እንስሳ ይታረዳል፣ ሥጋው ይሸጣል፣ ገንዘቡንም፣ የሞተውንም እንስሳ ይከፋፈላሉ። ነገር ግን በሕይወት ያለው እንስሳ ተዋጊ መሆኑ የሚታወቅ ከሆነ፣ የበሬው ባለቤት በሬው ላደረሰው ጥፋት ሙሉ ለሙሉ ተጠያቂ ይሆናል።

22፥1-4 ይህ ሦስተኛው የንብረት ጕዳይን የሚመለከተው ምሳሌ፤ ስምንተኛውን ትእዛዝ የሚያብራራ ሲሆን፣ ሌሎች ዐምስት ጕዳዮችንም ይዟል። ሌብነትን የተመለከተው ጕዳት ከሚሰጠው ቅጣት አብዝቶ ይበልጣል። በሬ የሰረቀ ሰው ዐምስት ዕጥፍ እንዲከፍል የተደነገገበት ምክንያት ምናልባት አንድ ሰው የሌላውን ሰው የኑሮ ዋስትና (መተዳደሪያ) ከመስረቁ የተነሣ ሊሆን ይችላል። ይህ መርሕ በየትኛውም የሰውዬው የኑሮ ዋስትና የተመሠረተባቸው ንብረቶች ሁሉ ላይ ተፈጻሚነት አለው።

በሌሊት ቤት ሰብሮ በመግባት የሚፈጸም ሥርቆት ሌባውን ለሞት ሊያጋልጠው ይችላል (የማያስጠይቅ ነፍስ ማጥፋት)፣ በዚህ ጊዜ የቤቱ ባለቤት ተጠያቂ አይሆንም (ከኤር 2፥34 *ጋር ያነጻ*)። ይህ ዐይነቱ ወረራ በቀን የተፈጸመ ከሆነ፣ ጕዳዩ ለየት ይላል፤ ምክንያቱም ምስክሮች ሊኖሩ ስለሚችሉና የወንጀለኛውም ሐሳብ (ለመስረቅ ብቻ ይሁን ወይም ለመግደል) ሊጠና ይችላልና።

የተሰረቁ ንብረቶች የተሸጡ ወይም ደግሞ ጥቅም ላይ የዋሉ ከሆነና ሌባውም ለወንጀሉ የሚከፍለው ምንም ነገር ባይኖረው ለባርነት ይሸጥ፦ ምናልባትም ዕዳውን ከፍሎ እስኪጨርስ ድረስ። ዕቃው ገና በእጁ ከሆነ ግን ንብረቱን በፍቃዱ የመመለስና የንሳሓ ዕድል አለው። ቢያንስ እውነተኛው ባለንብረት ከራሱ እንስሳ *ጋር* እንደ ገና የመገናኘት ዕድል አለው፤ በመቀጫ መልክ ሌባው ተመሳሳይ እንስሳ ይከፍላል። ሌባው በገዛ ፈቃዱ ጥፋቱን ካመነ፣ ዘሌ 6፥4-5 የሰረቀውን ንብረት ዋጋ አንድ ዐምስተኛውን ብቻ እንዲጨምር ያዛል (ዘጕ 5፥6-7 *ጋር ያነጻ*)።

5-6 አራተኛው ዐይነት በንብረት ላይ የሚደርስ ጕዳት እንስሳትን በሌላ ሰው ማሰማሪያ መስክ ላይ በመልቀቅ ማስጋጥን፣ እንዲሁም የተለከሰ እሳት ከቍጥጥር ውጪ ሆኖ የጎረቤትን እህል ክምር ወይም በመስክ ያለ እህል ሲያወድም የሚከሠተውን የሚመለከት ነው። በቍ 5 እና በቍ 6 የሚገኙት ሁለቱም ሐሳቦች “. . . እንደ ሆነ” በሚል ቃል ይጀምራሉ፤ ማለትም እንደ ሁለት የተለያዩ ሕጎች ተወስደዋል ማለት ነው። ስለሆነም ሰዎቹ ለደረሰው ጥቃት ብቻ ሳይሆን ተጠያቂ የሚሆኑት ጥፋቱ እንዲፈጸም ምክንያት ስለ ሆኑም ጭምር ነው፤ ምንም እንኳ ጥፋቱን ሆነ ብለው ያላደረሱት ቢሆንም ካሣው የዕርሻው መሬት እጅግ ምርታማ በሆነ ጊዜ ባፈራው ምርት መጠን ይሰላል፤ ሁሉም ማሳ ወድሞ ከሆነ፤ ወይም ደግሞ ጕዳቱ መላውን ማሳ ያላወደመ ከሆነ፣ ሳይወድም የቀረው ክፍል ለቀሪው ማሳ እንደ መለኪያ ሆኖ ካሣው ይከፈላል።

7-15 የመጨረሻው የንብረትን ጕዳት የሚደነግገው ክፍል ለሌላ ሰው በዐደራ እንዲቀመጡ ስለ ተሰጡ ወይም በውሰት ስለ ተሰጡ አራት ዐይነት ዕቃዎች ይናገራል።

የመጀመሪያው ጕዳይ (ቍ. 7-9) የሚገኘው የሚመለከተው ውድ የሆኑ ቍሶችን ለጥንቃቄ ሲባል እሰው ዘንድ በተቀመጡበት ሲሰረቁ የሚደረገውን ነው። ሌባው ዕጥፍ አድርጎ ካሣውን ይክፈል (ከቍ. 4 *ጋር ያነጻ*)። በቍ. 8-9 ተመሳሳይ ሁኔታ ነው የሚገኘው፤ ለውጡ የሌባው ማንነት አለመታወቁ ነው፤ በመሆኑም ንብረቱን በዐደራ የተረከበው ሰው ዐደራ በሊታ ሆኖ እንደ ሆነ ጥርጣሬ ሲኖር ነው። በዚህ ጊዜ ባለ ዐደራው ወደ “ዳኞቹ” ሊቀርብ ይገባዋል፤ በዚያም ንጽሕናውን ለማረጋገጥ በእግዚአብሔር ፊት በችሎቱ ይምላል።

ምንም እንኳን ይህ ክፍል በግልጥ መሐላን ባይጠቅስም፣ “ . . . እንደ ሆነ” የሚለው ቃል በሌሎች ብዙ ቦታዎች እንደ መሐላ ቀመር (ፎርሙላ) ያገለገለ በመሆኑ በዚህም ቦታ ይህንኑ እንጂ ሌላ ትርጉም እንደሌለው እንቀበላለን (መሐላው በቁ. 11 ላይ በግልጽ ተቀምጧል)። ቁጥር 8 አጠቃላይ መመሪያ የሚሰጥ ነው፤ ቁ. 9 ደግሞ እምነት ለማጉደል ወንጀል የሚገባውን ቅጣት በግልጽ ያስቀምጣል።

ሁለተኛው ጉዳይ (ቁ. 10-11) ለሌላ ሰው በዐደራ የተሰጡ እንስሳት ተሰማርተው ባሉበት ጉዳት ቢደርስባቸው፣ ወድቀው ቢሰበሩ፣ ወይም በዘራፊ ተነድተው ቢወሰዱ፣ ምን መደረግ እንዳለበት ይደነግጋል። በችሎት ተመሳሳይ መሐላ እንዲፈጸም ያዛል፤ ምክንያቱም ምስክሮች ስለሌሉና የባለዐደራውን ተጠያቂ መሆን አለመሆን የሚያውቀው እግዚአብሔር ብቻ በመሆኑ።

በሦስተኛው ጉዳይ (ቁ. 12-13) በዐደራ የተቀመጠው እንስሳ ሲሰረቅ የሚመለከት ነው። ባለ ዐደራው እንስሳውን ሲጠብቅ ንዝህላልነት በማሳየቱ በተሰረቀው እንስሳ ፋንታ ለባለቤቱ ካሣ መክፈል አለበት። ነገር ግን በዐደራ የተቀመጠው እንስሳ በዱር አራዊት ቢዘነጣጠል፣ ባለ ዐደራው ማስረጃ ማቅረብ ብቻ ነው የሚጠበቅበት፤ እንዲከፍል አይጠበቅበትም።

የመጨረሻው ጉዳይ (ቁ. 14-15) አንድ ሰው ከጎረቤቱ እንስሳ ተውሶ ባለቤቱ በሌለበት ቢጐዳ ወይም ቢሞት መደረግ ስላለበት ነገር ይገልጻል። በንዝህላልነት የመጣ ችግር እንደ ሆነ ስለሚታሰብ፣ ሙሉ ክፍያ (ምትክ) እንዲሰጥ ይጠበቅበታል። ነገር ግን ባለቤቱ ባለበት ከሆነ አደጋው የደረሰው፣ እንስሳውን ያከራየበት ዋጋ ለደረሰው ጉዳት ተመጣጣኝ ካሣ እንደ ሆነ ይቁጠራል፤ በእንስሳው ላይ ለደረሰው አደጋ የዐይን ምስክር በመሆኑም የተዋሰው ሰው በግዴለሽነት አድርጎት ይሆናል የሚለውን ጥርጣሬ ያስወግዳል።

6. ማኅበራዊ ሕጎች (ደንቦች)

16-17 ያልታጨችን ልጃገረድ ክብረ ንጽሕና መድፈርና የታጨችን ልጃገረድ ክብረ ንጽሕና መድፈርን በሚመለከት በዘዳ 22፥23 ላይ የተሰጠው ሕግ የተለያየ ነው፤ አስገድዶ መድፈር የሆነ እንደ ሆነ። በዚህ ስፍራ ወንጀለኛው የማጫዋን ዋጋ መክፈልና ሊያገባት መስማማት መቀጫው የሚጥለው ግዴታ ነው። የልጃገረዲቱ አባት ለዚህ ሰው ልጃቸውን ለመዳር ፈቃደኛ ካልሆኑ፣ አሁንም ቢሆን ሰውዬው የማጫዋን ገንዘብ መክፈል ግዴታው ነው። ይህ ክፍያና ለማግባት መስማማት የተሠራውን ኀጢአት ሊያስተሰርይ አይችልም፤ የኀጢአት ስርየት የሚገኘው በንስሓ ብቻ ነውና።

18 “መተተኛ” የሚለው ቃል በዕብራይስጡ በእንስታይ ጾታ የተቀመጠ ነው፤ ትርጉሙም “ጠንቋይ” ወይም “አስማተኛ” እንደ ማለት ነው። የዕብራይስጡ ግስ አጽንዖት ድግመት፣ ጥንቁላ፣ መተትና ሌሎችም የጥንቁላ ጥበቦችን መጠቀምን ያመለክታል። የእንግሊዘኛው “ዊች” የሚለው ቃል “ቱ ዊት” ማለትም “ማወቅ” ከሚለው የመጣ እንደ ሆነ ይታመናል። የሰባ ሊቃናቱ ትርጉም ቃሉን “ፋርማኮስ” (“መራገጦች”) ይለዋል፤ ምክንያቱም መተተኞች መድኃኒቶችንና መድኃኒት ቅመማንም ስለሚጠቀሙ ነው።

19 ይህ ሕግ ከእንስሳት ጋር የግብረሥጋ ግንኙነት መፈጸምን ያወግዛል (ከዘሌ.18፥23፤ 20፥15-16፤ ከዘዳ 27፥21 ጋር ያነጻ)። ሀይቲ የተባሉ ሕዝቦች ሕግ፣ ይህን ክፉ ድርጊት የሚያወግዘው ተላልፎ የሚገኘው ሰው ንጉሡ ይቅር ካላለው በቀር በሞት እንደሚቀጣ ነው። ይህ አስጸያፊ ድርጊት በከነዓናውያን ዘንድ የተስፋፋ እንደ ነበረ ከዚህ መረዳት ይቻላል።

20 ከእግዚአብሔር በቀር ለሌላ አምላክ የሚሠዉ ሁሉ “እንደ እርም ይደምሰሱ” (የተርጓሚው ትርጉም)። ዘዳግም 17፥2-5 ለንጽጽር ይመልከቱ።

21-27 እነዚህ ጥቅሶች በድኾች ላይ፣ በመበለቶች፣ ወላጆቻቸውን ባጡት፣ እንዲሁም በመጻተኞች (በእንግዶች) ላይ የሚደረገውን ጭቈና የሚመለከቱ ናቸው። እነዚህ ተጠቂዎች ጥቂት ወይም ምንም ተከላካይ (ተሟጋች) የሌለላቸው በመሆኑ ልዩ ጥበቃ ሊደረግላቸው ይገባል። እንግዳም፣ መጻተኛም፣ እንዲሁም መበለቶችና ወላጆቻቸውን ያጡ ሕፃናት ጥበቃ ሊደረግላቸው ይገባል (23፥11፤ ዘሌ 19፥9-10፤ ዘዳ 14፥21፤ እና ሌሎችም)።

በብድር የተሰጠ ገንዘብና ወለዱን በሚመለከት በዘሌ 25፥35-37 እና ዘዳ 15፥7፤ 23፥19-20 በስፋትና በምልኡት ተገልጧል (ከኢዮብ 24፥9፤ ከምሳ 28፥8፤ እና ከሌሎችም ጋር ያነጻ)። ጻድቅ ሰው በመዝ. 15፥5 መሠረት “ገንዘቡን ያለ አራጣ የሚያበድር” እና “በአራጣ የማያበድር ወይም ከልክ ያለፈ ወለድ የማይጠይቅ” ሊባል ይችላል። በሕዝ 18፥8 (ከቁ. 13፡17 ጋር ያነጻ) መሠረት። በሌላ በኩል ዘዳ 23፥20 “እንግዳውን ሰው (መጻተኛውን) ወለድ ልትጠይቀው ትችላለህ፤ ነገር ግን ወንድምህ የሆነውን እስራኤላዊ ፈጽሞ” ይላል። ይህ ሕግ “አራጣ”ን በዘመኑ የቃሉ ትርጉም ማለትም ከልክ ያለፈ፣ ወይም ሕገ ወጥ ወለድ በሚለው አይደለም የሚተረጕመው፤ ነገር ግን ማንኛውንም ዓይነት ወለድ ወገን ለሆነ እስራኤላዊ የሚከለክል ነው።

በርግጥ ከወለድ ነጻ የሆነ ብድርም እንኳ የሆነ መያዣ ወይም ዋስትና ይጠይቃል፤ ነገር ግን የአንድን ሰው ልብስ በመያዣነት ይዞ ማሳደር በጥብቅ የተከለከለ ነው። ይህ ካባ (በርኖስ) በሌሊት እንደ ብርድ ልብስ ተለብሶ የሚተኛ በመሆኑ በምሽት አስፈላጊ ነው።

28 የእግዚአብሔርን ክብር የሚያቃልል ማናቸውም ቃል ወይም ድርጊት እግዚአብሔርን እንደ መናቅ ወይም ስሙን በከንቱ እንደ መናቅ ይቈጠራል (20፥7ን ይመ)። በተመሳሳይ በሥልጣን ላይ ያለን ማንኛውንም ሰው ላለመርገም መጠንቀቅ ያስፈልጋል። ምክንያቱም እግዚአብሔርንም ንጉሥንም መርገም ቅጣቱ ሞት ነውና (ከዘሌ 24፥15-16፤ ከ2ሳሙ. 16፥9፤ ከ1ነገ 2፥8-9፤ 21፥10 ጋር ያነጻ)።

29-30 የበኵራት ሕግ “የዕርሻህ የተትረፈረፈ ምርትና የወይን መጥመቂያህ ሙላት ፈሰስ” (ቀጥ. ትርጉም)፣ መጀመሪያ የተወለዱ ልጆቻቸውና መጀመሪያ የተወለዱ እንስሶቻቸው ለእግዚአብሔር እንዲቀርቡ ያዝዛል። ልጆቻቸው በገንዘብ ክፍያ ወይም በእያንዳንዱ ልጅ ምትክ አገልግሎት በሚሰጥ አንድ ሌዋዊ ይዋጃል (13፥13፤ ዘኍ 3፥46-48)። ይህንን ከማድረግ “መቈጠብ” ወይም “መዘግየት” የለባቸውም ይላል ቃሉ ምንም እንኳ ክፍሉ የሰዎችን ተፈጥሯዊ ቸልተኝነት የተረዳ ቢመስልም። በኵራቱ ከእናቶቻቸው ጋር የሚቈዩት እስከ ሰባት ቀን ብቻ ነው፤ ዘሌ 22፥27 ይመ።

31 ማኅበራዊ ግንኙነቶችን አስመልክቶ ከተሰጡት ከእነዚህ ትእዛዛት ጀርባ የሚከተለው የአገልግሎት ጥሪ ይገኛል፡- “እናንተ ለእኔ ቅዱስ ሕዝብ ትሆናላችሁ።” ይህ እንደ እግዚአብሔር በኵር ልጅ (4፥22) ወይም ደግሞ ‹‹የተወደደ ርስት . . . የመንግሥት ካህናትና የተቀደሰ ሕዝብ›› ትሆኑልኛላችሁ (19፥5-6 ያለውን ማብ ይመ.) የሚለው ይህ የተቀደሰ ጥሪ የተቀደሰ ኑሮን የሚጠይቅ ነው። በአራዊት ተዘንጥለው የሞቱ እንስሶች የረከሱ ናቸው፤ ምክንያቱም በእንዲህ ዐይነት መንገድ የተገደሉ እንስሳት ደም በውስጣቸው ስለሚቈይ ያረክሳቸዋል። ይህ ዐይነቱ ሥጋ ለውሾች ሊሰጥ ይገባል። “የቅድስና ሰዎች” (በቁም ትርጉም) በውስጣዊ

መርሖችና በውጫዊ ተግባሮች ሊቀደሱ ይገባል፡- ከእነዚህ አንዱ ቀጥሎ ተገልጸአል።

7. የፍትሐና የጉርብትና ሕጎች (23፥1-9)

1 የሐሰት ወሬን (በችሎትም ሆነ በሌላ ቦታ) በሌላ ሰው ላይ መናገር የዘጠነኛው ትእዛዝ ማጥያ ነው። ዘሌዋውያን 19፥16ን በዘዳ 22፥13-19 እና በ1ነገ 21፥10-13 ካሉት ጉዳዮች ጋር ያነጻጽሩ። "ክፉውን ሰው አታግዝ" ተብሎ በ"ዐመት" የተተረጎመው ሐረግ "እጅህን ከክፉዎች ጋር አታንሣ (አትዘርጋ)" ለሚለው የተሰጠ ነው።

2-3 ፍትሕ አድሏዊ አለመሆንን ይጠይቃል፤ ባልተረጋገጠ ጉዳይ "ከብዙኃኑ" (አመት "ሕዝቡ") ጋር ከመወገን ይልቅ ወይም ደግሞ ለድኻው ከማድላት ይልቅ (ከዘሌ 19፥15 ጋር ያነጻ)።

4-5 አንድ ሰው የወንድሙ እንስሳ በሚጠፋበት ጊዜ እንዴት ፈልጎ ሊያመጣለት እንደሚገባና ወይም ደግሞ በችግር ውስጥ ያለን ሰው እንዴት መርዳት እንደሚያስፈልግ ዘዳግም 22፥1-3 የተሟላ ዝርዝር መረጃ ይሰጣል። ይህ ዐይነቱ የቸርነት ሥራ ቸርነት የሚያደርግለት ሰው ጠላትም ቢሆን ወይም ደግሞ የሚጠላን ሰው ቢሆን ሊደረግለት ይገባል (ከኢዮብ 31፥29፤ ከምሳ 25፥21-22 ጋር ያነጻ)።

6-8 "ድኻውን ሕዝብህን" የሚለውን "ባላጋራህ፣ ባላንጣህ" ("ጠላትህ ቁ. 4፣ እና "የሚጠላህ ሰው" ቁ. 5 ለሚሉት ተመሳሳይ ናቸው) ብለን ብንረዳው ስይሻል አይቀርም። በመሆኑም ጠላትህ (ያንተ ጠላት) የሚለው ባዕድ መድረሻ (suffix) ትርጉም በቀላሉ ግልጽ ይሆናል፤ እናም ትርጉሙ የሚከተለው ነው፡- በጠላትህና በሌላ ሰው መካከል ለዳኝነት ወይም ለምስክርነት በተጠራህ ጊዜ ጠላትህ በመሆኑ ብቻ በሰውዬው ላይ ፍትሕን አታጣምበት። ፍትሕ ሰዎች በሐሰት ከመክሰስ እንዲርቁ ያዝዛል (ቁ. 1)። እግዚአብሔር ይህን የሚሠሩ ሰዎችን ወይም ዳኞችን ከበደል ነጻ አያደርጋቸውም።

ቁ. 8 ላይ በቃል ማለት ይቻላል፤ በዘዳ 16፥19 ላይ ተደግሟል። ጉቦኝነት የተለመደ የዘመኑ ፈተና ሳይሆን አይቀርም፤ በርካታ ምንባቦች ከእነርሱ ያስጠነቅቃሉና።

9 ይህ ጥቅስ ከ22፥21 ጋር በአገላለጹ ተመሳሳይ ነው፤ እዚህ የተጠቀሰበት ምክንያት እስራኤላውያን ፍትሕን እንዲያደርጉ ትልቅ ማነቃቂያ (ማትጊያ) እንዲሆናቸው ነው፡- በግብፅ መጻተኞች በነበራችሁ ጊዜ ምን ይሰማችሁ እንደ ነበር (ደግሞም መጻተኝነት የሚያስከትለውን ነገር ሁሉ) አስታውሱ።

8. የሰንበት (የተቀደሱ ቀናት) ሕጎች (23፥10-19)

10-12 እያንዳንዱ ሰባተኛ ዓመት "ለምድሪቱ የሰንበቶች ሰንበት ይሆናል፤ የእግዚአብሔር ሰንበት ይሁን" (ከዘሌ 25፥4 ጋር ያነጻ)። ምድሪቱ መታረስ የለባትም፤ ዕረፍት ታደርግ ዘንድ ትተው። የዚህ ሕግ መደንገግ ምክንያቱ ድሆችንና የዱር አራዊትን ለመጥቀም ሲባል ነው። በዘሌ 25፥17፡ 18-22፣ ምክንያቶቹ ሕዝባዊ ሳይሆኑ ይልቁን ባመዛኙ ሥነ መለኮታውያን ናቸው፡- "ይህም የእግዚአብሔር ሰንበት ነው" (25፥4)።

ቁ. 12 አራተኛውን ትእዛዝ በድጋሚ ይጠቅሳል፤ ምክንያቱም ማንም ሰው አንድ ጊዜ ሰባተኛው ዓመት በዓል ስለ ተከበረ፣ ሌሎቹ የተለመዱ የመደበኛው ሰንበት አከባበሮች አያስፈልጉም ወደሚል ድምዳሜ እንዳይደርስ ለመጠበቅ ነው። ይህ በ20፥8-9 ያለውን ትእዛዝ መድገሙ ሰንበትን የመጠበቅን ተጨማሪ ምክንያት ይሰጠናል፡- ሰዎችና እንስሳት "ያርፉ ዘንድ።"

13 ሕዝቡ ጣዖት እንዳያመልክ የተሰጠው ይህ ማስጠንቀቂያ ቀደም ብለው የተሰጡትን መለኮታውያን ትእዛዞች ሁሉ የሚያጠቃልል ይመስላል፡- ቃል በቃል ሲጠቀስ፤ "ያልኋችሁን ሁሉ" የሚል ነው። "ከአፋችሁም አይስሙ" የሚለው "እንዲታወሱ (እነዚህ ሁሉ ነገሮች) ምክንያት "አትሁኑ" ከሚለው ጋር ይነጻጸራል፤ (በዐመት ስማቸውን አትጥሩ") ይላል። እግዚአብሔር የጣዖታትን ስም ከምድሪቱ ፈጽሞ የሚያጠፋበት "ቀን" ይመጣል፤ "ከእንግዲህም አይታሰቡም" (ሆሴዕ 2፥17፤ ዘካ 13፥2)። ይህም በመዝ 16፥4 መሠረት የዳዊት ልምምድ ነው (ዘፀ 20፥3፤ ኢያሱ 23፥7ን ልብ ይሏል)።

14-17 ይህ ክፍል ሦስቱን ታላላቅ ዐውደ ዓመታውያን በዓላት ይመለከታል፡- የቂጣ በዓል በጸደይ ወራት በስንዴ መከር መጀመሪያ ላይ ከግብፅ የወጡበትን ጊዜ ለማስታወስ የሚከበር (ቁ. 15)፤ የመከር በዓል (የሰባቱ ሱባኤ በዓል ተብሎ በ34፥22 ተጠቅሷል) በጸደይ ወራት የመከር ማብቂያ ላይ የሕጉን መሰጠት ለማክበር (ቁ. 16ሀ)፤ እና የመክተቻ በዓል የበጋውን ሰብሎች ወይራውንና ወይኑን በክረምቱ መግቢያ ላይ የሚሰበስቡበት ሲሆን የምድረ በዳውን ዙረት ለማስታወስ የሚከበር ነው (ቁ. 16ለ፤ ከ34፥18-26፤ ከዘሌ 23 ጋር ያነጻ)። ሁሉም በዓላት በአንድ ጊዜ ግብርናዊም ታሪካዊም ናቸው፤ እናም ሁሉም ሰው በዓመት አንዴ ያከብራቸው ዘንድ ግድ ነው። የቂጣ በዓል አከባበርን በሚመለከት 12፥34 እና ዘሌ 23፥5-8፤ 10፥14 ይመለከቷል። ይህ በዓል በፋሲካ ጀምሮ ለሰባት ቀናት የሚቈይ ሲሆን በመጀመሪያውና በመጨረሻው ቀን የተቀደሰ ጉባኤ በመጥራት ይከበራል። የበዓላቱ ሁሉ ዋና መመሪያ "ማንም በራቴ ባዶ እጁን አይቅረብ" የሚለው ነው።

የመከሩ በኩራት የሆነው የገብስ ነዶ ከተሰበሰበ ዐምሳ ቀን በኋላ ጰንጠቆስጤ የመባል በኋላ የታወቀው የመከር በዓል ይከበራል (ከዘሌ 23፥15-22፤ ከዘዳ 16፥9-11 ጋር ያነጻ)።

የ(መከር) መክተቻ በዓል ወይም የዳስ በዓል (ከዘሌ 23፥33-36፤ ከዘዳ 16፥13፤ 31፥10፤ ከሮሐ 7፥2 ጋር ያነጻ) የምስጋና ማቅረቢያ ዐይነት በዓል ነው። ቀስ በቀስ በእስራኤል ታሪክ ውስጥ በተደጋጋሚ ቸል የተባለ በዓል ነው (ነህ 8፥17)።

18 የዚህ ጥቅስ የመጀመሪያ ክፍል እርሾ ያለበትን ነገር ከመብላት ጋር ፈጽሞ የተያያዘ አይደለም። ይልቁን ትርጓሜው እያንዳንዱ እስራኤላዊ በቤቱ እርሾ እያለ የፋሲካውን በግ ማረድ እንደሌለበት የሚናገር ነው። የጥቅሱ ሁለተኛ ክፍል ሥጋን አስመልክቶ ምንም የሚለው ነገር የለም፤ ነገር ግን በ34፥25ለ ካለው ጋር በንጽጽር "የፋሲካው በዓል መሥዋዕት" (እዚህ ላይ በቁመ. "የበዓል መሥዋዕቴ") "እስከ ንጋት ድረስ አይቈይ" (ከ12፥10 ጋር ያነጻ) ነው የሚለው። "ሥብ" የሚለውን ቃል በ34፥25ለ ከሚገኘው ተነጻጻሪ ሐሳብ ነጥለን ካጸደቅነው፤ "የበዓሌን ሥብ" የሚል ሐሳብ "የበዓል መሥዋዕቴ" ከሚለው ጋር በተዛራቢ ይቀመጣል፤ እንዲህ ከሆነ እያንዳንዱ ቤተ ሰብ የሆድ ዕቃውን ሥብ ማለዳ ላይ ማስወገድ ይኖርበታል ማለት ነው። ነገር ግን የመጀመሪያው ገለጻ (ማለትም እርሾ አይገኝ የሚለው) ተመራጭ ነው።

19 የበኵራት ሕግና ነገረ መለኮቱ በ4፥22፤ 11፥5፤ እና 12፥29 ላይ ቀደም ብሎ ተብራርቷል። አሁን ግን ወደ እግዚአብሔር ቤት የሚመጣ በመሆኑ ገና ገለጻ ይሰጠዋል።

ጠቦት ፍየልን በእናቱ ወተት እንዳይቀቀል መከልከልን (በተጨማሪ 34፥26፤ ዘዳ 14፥21ለ ይመ) አስመልክቶ ከ1933 ጀምሮ ገለጻዎች እየተሰጡ ነው። እነዚህ ገለጻዎች የተመሠረቱት "የአማልክት መወለድ አስደሳችና ውብ" (ጽሑፍ 52 መሥመር 14) ከሚለው በ13ኛው ክፍለ ዘመን ከተጻፈ የጋሪቲክ መጽሐፍ ውስጥ ከተጐመደ ምንባብ ውስጥ ነው።

አጠቃላይ ስምምነት የተደረሰበት ጉዳይ ቢኖር፣ በዚህ መጽሐፍ የተጠቀሰው የመዋለድ አምልኮታዊ ሥርዐት (fertility rite) ግልገሉን በወተት መቀቀል እንደሚያስፈልግ ይናገራል፤ ነገር ግን በተጐመደው የዩጋሪቲክ ጽሑፍ ውስጥ ወተቱ የእናት ወተት መሆኑን የሚናገር ክፍል የለውም። ዋናው መሠረታዊ ነገር የሞተው (የታረደው) ግልገል ሕይወቱን ባቄየው ወተት እየተቀቀለ ነው የሚል ነው።

9. መካተቻ (መደምደሚያ) (23፥20-33)

ይህ መካተቻ (መዝጊያ) የቃል ኪዳኑን ደንብ ያጠቃልላል። ለእስራኤል የእግዚአብሔር መልአክ፣ የተሟላ ጥበቃ፣ ስኬት እንደሚሰጣት ቃል ተገባላት፤ ለቃል ኪዳኑ ታማኝ ሆነው እስከ ኖሩ ድረስ (ከ33፥1-3፤ 34፥11-16፤ ከዘሌ 26፥3-11፤ ከዘዳ 7፥13-15፤ 28፥1-14 *ጋር ያነጻ*)።

20-22 በዚህ ቦታ የተጠቀሰው መልአክ የእግዚአብሔር መልእክተኛው ሙሴ ሊሆን አይችልም፤ ወይም ደግሞ ሌላ ተራ መልአክም አይደለም፤ ምክንያቱም በዚህ ቦታ የተሰጡት ገለጻዎች በጣም ከፍ ያሉ ስለ ሆኑ እነዚህን አይመጥኑም፤ "ዐመፅህን ይቅር አይልም" (ከእግዚአብሔር በቀር ኀጢአትን ማን ይቅር ሊል ይችላል?) እና "ስሜ በእርሱ ላይ ነውና።" ይህ የቃል ኪዳኑ መልአክ መሆን አለበት (ከኢሳ 63፥9፤ ከሚል 3፥1 *ጋር ያነጻ*) ማለትም የሥላሴ ሁለተኛ አካል ነው። ልክ የእግዚአብሔር ስም በመቅደሱ ዐድሮ እንደ ነበረ ሁሉ (ዘዳ 12፥5፣11፤ 1ነገ 8፥29)፣ ይህ የእግዚአብሔርን ሥልጣንና ስም የያዘው መልአክ እግዚአብሔር ራሱ በልጁ ውስጥ እንደ ተገኘ በቂ ማስረጃ ነው። ለመልአኩ መታዘዝ በምንባቡ ውስጥ የተዘረዘሩትን በረከቶች ለመቀበል ያበቃል። እስራኤል "አታምፅበት" ተብለው ታዝዘዋል፤ ነገር ግን ይህንኑ ነው ያደረጉበት (ዘኍ 14፥11፤ መዝ 78፥17፣ 40፡56)።

23-26 በእዚህ ቦታ ስለ ተዘረዘሩት መንግሥታት በ3፥8 የተሰጠውን ማብራሪያ ይመለከቷል። እነዚህን ሁሉ መንግሥታት የእግዚአብሔር መልአክ "ከፊትህ ይጠርጋቸዋል" ማለት ሀገራዊ (ብሔራዊ) ህልውናቸውን እንጂ ግለሰባዊ ማንነታቸውን ላይሆን ይችላል፤ ምክንያቱም ለምሳሌ፣ በዳዊት ሰራዊት ውስጥ ኬጢያዊያን ነበሩ (2ሳሙ 23፥29)፣ ደግሞም ከኢያቡሳውያን *ጋር* ወዳጅነት ነበረውና (2ሳሙ 24፥18-24)። የእነዚህን አሕዛብ አማልክት ማምለክና መጥፎ ልምዳቸውን መለማመድ ነው በጽኑ የተከለከለው። ነገር ግን እስራኤል አማልክቶቻቸውን እንዲያፈራርሱ የአምልኮ ድንጋዮቻቸውን እንዲያደቅቁ ነው የታዘዙት፤ እነዚህ ድንጋዮች በግልጽ የተተከሉ ድንጋዮች ሲሆኑ አማልክቶቻቸውን በተለይም የወንድ አማልክቶቻቸውን ለማክበር የቆሙ ናቸው።

የእስራኤል አምልኮ በውሃቸውና በምግባቸው ላይ ተጽዕኖ ያሳድራል። እንግዲያውስ ነቢያቱ የእግዚአብሔርን ፍርድ የተወሰነ ባህል ባለው ሕዝብ ላይ ሲያመጡ ከግብርና ውጤት ማሽቆልቆል *ጋር* ቢያያይዙት አይደንቅም (ለምሳሌ፦ ሐጌ 1፥5-11)። ከዚህም በላይ የዕድሜያቸውን እኩሌታ ሳይኖሩ እንደሚሞቱ እንደ ክፉዎች ሳይሆን (መዝ 55፥23) እግዚአብሔርን የሚያመልኩት ታዛዥ ሕዝቦቹ ሙሉ ዕድሜያቸውን ይኖራሉ።

27-30 እግዚአብሔር (በቁ. 20፡23 ከተጠቀሰው መልአክ በተጨማሪ) እስራኤልን ሊቋቋማት በሚያስብ በማናቸውም ሕዝብ ላይ ድንጋጤና ሽብርን እንደሚሰድ ቃል ገብቷል። በጠላቶቻቸው ላይ "ተርብ" ይልክባቸዋል፤ ይህ ቃል በዚህ ቦታ፣ በዘዳ 7፥20 እና በኢያ 24፥12 ብቻ ነው የሚገኘው። ምናልባት "ተርብ" የግብፅ ተምሳሌት ሊሆን ይችላል፤ ልክ ኢሳ 7፥18 "ዝንብ"ንና "ንብ"ን በቅደም ተከተል የግብፅና የአሦር ተምሳሌት አድርጎ እንደ ተጠቀመባቸው ሁሉ።

ምድሪቱን የመውረሱ ፍጥነት በተለያዩ ቦታዎች በተለያየ መንገድ ነው የተገለጸው። ልክ እዚህ ቦታ እንደ ተጠቀሰው መሳ 2፥20-3፥4 ላይም ምድሪቱን የመውረሱ ሂደት ቀስ በቀስ እንደ ሆነ ይሞግታል፤ ይሁን እንጂ ዘዳ 9፥3 "በፍጥነት" ጠላቶቻቸው እንደሚደመሰሱ ይናገራል። መልሱ የቱ ነው ቢባል ምድሪቱን የመውረርና ድል የማድረጉ ሂደት በመርሕ ደረጃ በፍጥነት ነው የተከናወነው። ይሁን እንጂ ከማጽዳት ዘመቻዎች የተነሣ፣ ከነዓናውያን ለቀው በሄዱት ስፍራ ሰዎችን ማስፈርና የዱር አራዊት ጥቃት ሥጋት (ከ2ነገ 17፥25 *ጋር ያነጻ*) የመውረሱን ሥራ የማጠናቀቁን ሂደት ሆነ ብለው እንዲያዘገዩት አድርጓቸዋል።

31-33 እግዚአብሔር ሊያጸናላቸው ቃል የገባላቸው ድንበር ከ"ቀይ ባሕር" (እዚህ ላይ ምሥራቃዊ ድንበር)፣ የአቃባ ባሕረ ሠላጤ ከወደብ ከተማዋ ከኤላት ጭምር፤ እስከ "ፍልስጥኤም ባሕር"፣ ምዕራባዊው የሜዲትራንያን ባሕር፤ በደቡብ ካለው ምድረ በዳ፣ ከኔጌብ፤ በሰሜን እስካለው "ወንዝ" ድረስ ነው። ይህንን "ወንዝ" ኤፍራጥስ ነው ከማለት ይልቅ ዛሬም ድረስ በዐረብኛ ተመሳሳይ ስያሜ ይዞ ከሚገኘው ወንዝ *ጋር* አንድ ማድረጉ ይመረጣል፤ ይኸ ወንዝ በአሁኑ ጊዜ የሊባኖስና የሶርያ ድንበር በመሆን ያገለግላል። ይህ ገለጻ በዘፍ 15፥18 ለአብርሃም ከተሰጠው ወሰን *ጋር* ስምም ከመሆኑም በላይ በዳዊትና በሰሎሞን አገዛዝ ሥር ከነበረው ከተባበረው የእስራኤል መንግሥት የግዛት ወሰን *ጋርም* በጣም የተቀራረበ ነው (2ሳሙ 8፥3-14፤ 10፥6-19፤ 1ነገ 4፥21፡ 24፤ 2ዜና 9፥26)።

ከእነዚህ ሕዝቦች *ጋር* ምንም ዐይነት ቃል ኪዳን መግባት የተከለከለ ነው (ምንም እንኳ የገባዖን ሰዎች አንድ ጊዜ ይህን ለማድረግ ቢሳካላቸውም ኢያ 9፥3-5)። አማልክቶቻቸው ለእስራኤል ወጥመድ የመሆናቸው፣ መጥፎ ተግባራቸውን የመለማመድና አማልክቶቻቸውን ለማምለክ የመፈተኑ አደጋ እጅግ ከፍተኛ ነው። ስለዚህ በእስራኤልና በእነዚህ አሕዛብ መካከል በከነዓን ምድር በሰላም ዐብሮ መኖር የሚባል ነገር በፍጹም ሊታሰብ አይገባም።

ረ. ኪዳኑን ማጽደቅ (24፥1-18)

"የኪዳኑ መጽሐፍ" ውስጥ ያለውን ለማስተዋወቅ ተቋርጦ የነበረው ትረካ (20፥22-23፥33)፣ ከቆመበት ከ20፥21 ጀምሮ አሁን ይቀጥላል። ቁ. 3-8 የተጠቀሱት ድርጊቶች ከተከናወኑ **በኋላ** ሙሴና ረዳቶች ወደ ተራራው ይወጣሉ፤

1 ናዳብና አብድዩ፣ ሁለቱ የአሮን ታላላቅ ልጆች ቀጣዮቹ ሊቃነ ካህናት የመሆን ዕድል ነበራቸው። ነገር ግን ከክፉ ሥራቸው የተነሣ በእግዚአብሔር የፍርድ ቅጣት (ዘኍ 3፥4) ተቀሠፉ። መደበኛዎቹ የዘኍ 11፥16ቶቹ "ሰባ ሽማግሌዎች" ገና አልተሾሙም። በዚህ ቦታ የተመረጡት ዐሥራ ሁለቱን ነገዶቹ እንዲወክሉ፤ ምናልባትም ሰባውን የያዕቆብ ትውልድ ወክለው ይሆናል።

2 በእግዚአብሔርና በእስራኤል መካከል መካከለኛ የሚሆነው ሙሴ ብቻ ነው፤ ልክ ክርስቶስ በዕብ 3፥1-6 ሁለተኛው ሙሴ ተብሎ የዐዲሱ ኪዳን መካከለኛ እንደ ሆነው ማለት ነው (ዕብ 12፥24)።

3 ሕዝቡ እግዚአብሔር ያለውን ሁሉ እንደሚታዘዙና እንደሚጠብቁ ቃል ሲገቡ፣ የተስፋውን በረከቶች በሕጉ አልለወጡትም። "የእግዚአብሔርን ቃላትና ሐረጎች" መጠበቅ የተመሠረተው በቅድሚያ በቀረበው የመሥዋዕቱ ደም ነው። ደሙ "ማድረግ" እና "መታዘዝ" እንዲችሉ ወንዶችንና ሴቶችን አነጻቸው። ይህ ሞገስን ወይም ድነትን ለማግኘት የሚፈጸም "ማድረግ" አይደለም።

4 ይህ ምንባብ የዘፀአትን መጽሐፍ በማቀናበር ውስጥ ሙሴ የነበረውን ቀጥተኛ ተሳትፎ ይመሰክራል። “ሙሴ እግዚአብሔር ያለውን ሁሉ ጻፈ” የሚለው ከአማሌቅ ጋር የተደረገውን ጦርነት መዘገበ ከሚለው (17፡14) ጋርና ዐሠርቱ ትእዛዛት “በእግዚአብሔር ጣት” ከመጻፋቸው ጋር ይስማማል (31፥18) (የ17፥14ን ማብ. ይመ)። “ዐሥራ ሁለቱ የድንጋይ ዐምዶች” ዐሥራ ሁለቱን የእስራኤል ነገዶች ይወክላሉ (ኢያሱ 4፥5፣20፤ 1ነገ 18፥31)።

5 “ወጣት ወንድ እስራኤላውያን በኩራት ሲሆኑ በዘኍ 3፥41 ሌዋውያኑ በእነርሱ ምትክ እስኪመረጡ ድረስ ያገለግሉ ነበር (19፥22፡24 ይመ)።

6 መሠዊያውም ሕዝቡም በእኩሌታው ደም ተረጨ፤ ይህም መሰጠትንና መለየትን ለማመልከት ነው። ዕብራውያን 9፥19 ስለ መሠዊያው አይጠቅስም፤ ነገር ግን “መጽሐፉ” ወይም “የብራና ጥቅሉ” በደም ስለ መረጨታቸው ይናገራል። አንዳንዶቹ እንደሚናገሩት መሠዊያው ጌታን ይወክላል ብሎ መናገሩ ምናልባት ትክክል ላይሆን ይችላል (ከዘፍ 15፥9-10፡17 ጋር ያነጻ)። በዚህ ቦታ የተጠቀሰው ሥርዐት የመንጻት ሥርዐት ነው (በዘሌ 14፥6-7 እና በዕብ 9፥19-20 የሚገኘው ውሃ፣ ቀይ ሐር እና ሂሶጵ አይደለም)። የደሙ እኩል መከፈል የቃል ኪዳኑ ደም ያለውን መንታ ገጽታ የሚያመለክት ነው፡- በመሠዊያው ላይ የተረጨው ደም የእግዚአብሔርን ይቅርታና ቍርባኑን መቀበል በምሳሌነት ያመለክታል፤ በሰዎቹ ላይ የተረጨው ደም ደግሞ ለእግዚአብሔር እንዲታዘዙ በደም መሐላ የመታሠራቸው አመላካች ነው። በሌላ አባባል፣ ቃሉንና ሕጉን መጠበቁ እውን ሊሆን የቻለው በመሠዊያው ላይ ከፈሰሰው የመሥዋዕቱ ደም የተነሣ ነው።

7 የኪዳኑ መጽሐፍ ጠበብ ባለ ትርጉም ከ20፥22-23፥33 የሚገኙትን ቃላት ያጠቃልላል፤ ነገር ግን ምዕ 19ን፣ በምዕ 20 የሚገኙትን ዐሠርቱ ትእዛዛትንና በ20፥22-23፥33 የሚገኙትን ሕጎች ይበልጥ በተሟላ ሁኔታ ይዟል።

8 ኪዳኑ የጸናበትና የታተመበት ደም በእግዚአብሔርና በሕዝቡ መካከል ለሚኖረው ኅብረት መሠረት ነው። ይህ ሐረግ በዐዲስ ኪዳን ከሁሉ የላቀ አስፈላጊ ቃል ነው (ማቴ 26፥28፤ ማር 14፥24፤ ሉቃ 22፥20፤ 1ቆሮ 11፥25፤ ዕብ 9፥20፤ 10፥29፤ በተጨማሪም ዕብ 12፥24፤ 13፥20፤ 1ጴጥ 1፥2)።

9-10 ሙሴና ዐብረውት የነበሩት “የእስራኤልን አምላክ አዩ” የሚለው ወዲያው በ33፥20፤ ዮሐ1፥18፤ እና 1ጢሞ 6፥16 ካለው ቃል ጋር የሚቃረን ይመስላል፤ ነገር ግን ያዩት “የእግዚአብሔርን መልክ (አምሳያ)” ነው (ዘኍ 12፥8፤ ከሕዝ 1፥26፤ ከኢሳ 6፥1 ጋር ያነጻ)። ይህንን ደማቅና አንጸባራቂ ምስል የእግዚአብሔርን ሀልዎት በሚመለከቱት ሰዎች ላይ የፈጠረው ህልው ማንነት ሆነ ተብሎ መልኩና ማንነቱ ተሰውሯል (ግልጽ አልተደረገም)።

ከእግዚአብሔር እግር በታች “ከሰንፔር የተሠራ ወለል”፣ ደማቅ ሰማያዊ፤ ይበልጥ ግልጽ ለማድረግ የሚሶፖታሚያ ላፒስ ላዙሊ፣ አንጸባራቂ፣ ሰማያዊ፣ ወርቃማ ሆኖ እንደ ብርቱካናማ ያለ ጠቃጠቆ ያለው የከበረ ድንጋይ ነው። እውነተኛ ሰምፔር፣ አንጸባራቂ መስታወታማ ድንጋይ በ1400 ቅክ አካባቢ በግብፅ አይታወቅም ነበር። የሰማይ ተምሳሌት ነው (ከሕዝ 1፥22 ጋር ያነጻ)።

11 “እግዚአብሔር መልኩን ባዩት በእስራኤል አለቆች ላይ እጁን አላነሣባቸውም (በቁመ፡- አልዘረጋባቸውም ከ9፥15 ጋር ያነጻ)። “አለቆች” የሚለው ቃል የመጣው ምናልባት “በጥልቀት ሥር መስደድ” ከሚለው ነው፤ እናም “ዝነኞች” “መኳንንት” ወይም “አለቃ የሆኑ ሰዎች” ማለት ነው። እጅግ አስገራሚ ከሆኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባቦች አንዱ በሆነው በዚህ ክፍል እነዚህ ሰዎች እግዚአብሔርን አዩ። ቍጥር 11 ከቁ 10 የተለየ ቃልን ይጠቀማል፤ በዚህ ቦታ ላይ አጽንዖት የተሰጠው ውስጣዊ፣ መንፈሳዊ፣ ትንቢታዊ ለሆነው ራእይ ነው።

“በሉ፣ ጠጡ” የሚለው ከቁ 3-8 የተገለጸውን ኪዳን በማክበር የተደረገ የኪዳን ማዕድ የሚገልጽ ነው። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር በመብሉ ወይም በመጠጡ ስለ መሳተፉ ምንም የተገለጸ ነገር የለም!

12 ሙሴ አሁንም “ወደዚህ ና” ተብሎ ተጠራ (ከቁ 1 ጋር ያነጻ)። ይህ “የድንጋይ ጽላቶች” የሚለው ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠቀሰበት ቦታ ነው።

13-14 እግዚአብሔር ላቀረበለት ጥሪ ምላሽ ሙሴ በኢያሱ ታጅቦ ተራራውን ሸቅብ ወጣ። አሮንና ሖር በ17፥10 የሙሴ ምክትል፣ በ18፥22 ደግሞ ዳኞች ተብለው በመሾማቸው ኀላፊነቱን ተረክበው በዚያው ቁዩ። ሖር በወርቁ ጥጃ አምልኮ ትዕይንት ያለመኖሩን ልብ ይሏል (ምዕ 32)።

15-16 ሙሴ ተራራውን ሲወጣ ማየት የቻለው ነገር ቢኖር የደመና ክምር ብቻ ነው። የእግዚአብሔር ክብር ተራራውን “ሲሸፍነው” መጽሐፍ ቅዱስ ያንኑ “ሸካን” የሚል ቃል ይጠቀማል ቃሉ “ሼኪና” ክብር ከሚለው ጋር ተመሳሳይነት አለው (ከዮሐ 1፥14 ጋር ያነጻ፣ ቃልም በእኛ “ደኸነ” (ወደረ) ማብ. ይመለከቷል)።


17 “የእግዚአብሔር ክብር እንደሚያቃጥል እሳት ነበረ” ለሚለው የ16፥10ን ማብራሪያ ይመለከቷል። የእግዚአብሔር ክብር ሦስት ተምሳሌቶች ማለትም የመገኘቱ ተምሳሌቶች ደመናው፣ እሳቱና የእግዚአብሔር ድምፅ ናቸው። የሀልዎቱ ነጸብራቅ እንደሚንበገበግ የምድጃ እሳት ነበር (ከዕብ 12፥18፡29 ጋር ያነጻ)።

18 አንድ ጊዜ ሙሴ ወደ “ደመናው” ከገባ፣ “አርባ ቀንና አርባ ሌሊት” አይታይም (ከማቴ 4፥2 ጋር ያነጻ)። በእነዚህ ጊዜያት ሙሴ የመገናኛውን ድንኳንና ንዋያተ ቅድሳቱን በሚመለከት ሁሉንም መመሪያ ከ25-31 ባሉት ምዕራፎች ውስጥ ተቀበለ። እስከ 32ኛው ምዕራፍ ድረስ ሙሴና ኢያሱ የእስራኤልን የክሕደት ተግባር ለመጋፈጥ አልመጡም ነበር።

፫. መለኮታዊ አምልኮ (25፥1-40፥38)

የመጨረሻዎቹ የዘፀአት ዐሥራ ስድስት ምዕራፎች አምልኮተ እግዚአብሔርን ማእከል ያደረጉ ናቸው። ይህ ጭብጥ የሚቋረጥበት ብቸኛ ቦታ የወርቅ ጥጃው ክሥተት ነው (ምዕ 32-34)፤ ይህም ክፍል ከማደሪያው ድንኳን ጋር ተያይዞ በመለኮት የተመሠረተውን አምልኮ የሚቃረን ወደ ርኩሰት የሚመራ ሰው ሠራሽ አምልኮ ነው።

የማደሪያውን ድንኳን አስመልክቶ የሚነሣው እጅግ አስፈላጊው ጥያቄ ከፋይዳው ጋር የተያያዘ ነው። የእኔ አመለካከት የማደሪያው ድንኳን በዋናነት የአምልኮ ነገረ መለኮትን የያዘ መሆኑ ነው። የሚነሣበት እውነታም እግዚአብሔር ሁሉን የሚገዛው ታላቁ ንጉሥ ነው፤ ስለዚህ ውዳሴያችንና ሙገሳችን ይገባዋል የሚል ነው። ይበልጥ ግልጥ ለማድረግ፣ የማደሪያው ድንኳን ትርጉም እግዚአብሔር በእስራኤል መካከል “ሊያድር” “ሊደኩን” መጥቷል፤ ልክ በዚሁ ዐይነት አንድ ቀን በተሠግዎ እንደሚመጣና (ዮሐ 1፥14) በዳግም ምጽአቱም እንደሚመጣ (ራእ 21፥3) የሚል ነው። በሚታይ ክብሩ በመቅደሱ ውስጥ በሕዝቡ መካከል ያደረው ጌታ (ዘፀ 25፥8) አንድ ቀን ይመጣና በሙሉ ክብሩ በቅዱሳኑ መካከል ለዘላለም ያድራል።



ይህ ማደሪያ፣ እሥራኤላውያን በሲና ምድረ በዳ የሠሩት ዐይነት ነው። በሥዕሉ ውስጥ ጉላ የሚለው የሚቃጠል መሥዋዕት መሠዊያና ደመና በላዩ ያንዣበበት የመገናኛ ድንኳን ነው። በዙንደርቫን ድርጅት ትብብር © 1984.

ሀ. የማደሪያው (የመገናኛው ድንኳን (25፥1-31፥18)

1. ስጦታ መሰብሰብ (25፥1-9)

1-2 “ስጦታ” (ወይም “መዋጮ”፤) ተብሎ በዚህ ቦታ የተጠቀሰው “የመወዝወዝ መሥዋዕት” አይደለም፤ ይልቁን ለመንፈሳዊ አገልግሎት ተለይቶ ለእግዚአብሔር ስጦታ እንዲሆን የሚቀደስለት ነው። በዘዳ 12፥6፣11፣17 “ልዩ ስጦታ” የሚለውን ትርጉም ይመልከቱ። ቁ.2ለ በአጽንዖት እንደሚገልጸው የበጎ ፈቃድ ስጦታም ነው።

3-7 ለማደሪያው ድንኳን ሥራ የዋሉት በዚህ ቦታ ተዘርዝረዋል። ከእነዚህም ውስጥ (1) ወርቅ፣ (2) ብር እና (3) ነሐስ ናቸው። ቀጥሎ ባለ ሦስት ቀለማት ማጎች ይጠቀሳሉ (4) “ሰማያዊ” ጠንካራ ሽፋን ካለው ዓሣ የሚሠራ ቀለም ሲሆን የተለያዩ ስያሜዎች ይሰጡታል፦ ከእነዚህም ሰማይ ዐይነት (ሰማያዊ)፣ ደማቅ ጥቁር ሰማያዊ፣ ሐምራዊ ወይም ደማቅ ቀይ ይገኙበታል። ፋይዳው ወይም ትርጉሙ ባይገለጽም እንኳ፣ ምናልባት የክርስቶስን ሰማያዊ ባሕርይ ለማመልከት ነው። (5) “ሐምራዊ” ቀለም የሚገኘው ሙሬክስ የሚባል የቀንድ አውጣ ዘር ከሚያመነጨው ምራቅ መሰል ነገር ሲሆን ይህን ምርት በዋናነት የሚያቀርቡት ፊንቄያውያን ናቸው። ሐምራዊ ቀይ ነው፤ ንጉሥነትን ያመለክታል። (6) “ደማቅ ቀይ” ወይም ብሩህ ቀይ የሚገኘው ኮክስ ኢሊሲስ ከሚባል ትል ዕንቁላል ወይም አሳል ነው። ትሉ በሆነ ዛፍ ቅጠል ላይ ይጣበቅና ዕንቁላል ይጥላል። ከዚያም ዕንቁላላቸው ይሰበሰባል፤ ይደርቃል፣ እናም ይፈጫል፤ ከዚያም ዱቄቱ ብሩህ ቀይ (ብጫማ ቀይ) ቀለም ይፈጥራል። ይህ በስጦታ ከሚቀርቡት ነገሮች አንዱ ነው። ምናልባት የሰውን ልጅ (የኢየሱስን) ምድራዊ ኀጎ ያመለክት ይሆናል።

(7) “የበፍታ ድር ልብስ” ከግብፅ በተውሶ የተወሰደ የዕብራይስጥ ቃል ትርጉም ነው። በግብፅ መቃብሮች የተገኙ አንዳንድ በፍታዎች (የሐር ልብሶች) 152 ክሮች በአንድ ኢንች ድር ውስጥ ይገኛሉ። ዘመናዊውና ከፍተኛ በሆነ ቴክኖሎጂ በአሁኑ ጊዜ የሚመረተው በተመሳሳይ መለኪያ 86 ክሮች ብቻ ናቸው። ብዙ ጊዜ የበፍታው ቀለም ነጭ ነው፤ ንጽሕናንና ጽድቅን ይወክላል። (8) “የፍየል ጠጕር” ትላልቅ ጠጕር ካላቸው ፍየሎች የሚገኝ ሲሆን ቀለሙ ጥቁር እንደ ሆነ ይገመታል። ሸካራ ሲሆን አገልግሎቱም ባብዛኛው ለድንኳን ሽመና (መሥሪያነት) ነው። ዘመናዊ አቻው ወፍራም ጨርቅ (ሸራ) ነው። (9) “የአውራ በግ ቁዳ” የበግ ቁዳ የበጉ ሱፍ በሙሉ ከተሸለተ በኋላ ቀይ ቀለም ይቀባል፤ የዘመናችንን የሞሮኮ ቁዳ የሚመስል ነው። (10) “የስፋ ቁዳ” (የባሕር ውስጥ ላሞች ቁዳ) በቀይ ባሕር ውስጥ ከምሥራቅ አፍሪካ የባሕር ውስጥ ላሞች (“ዶልፊን”) የሚገኝ ነው።

(11) “የግራር ዕንጨት” ሚሞሳ ከሚባሉ የዛፍ ዝርያዎች የሚመደብ ሲሆን ዕንጨቱ ከዝግባ ይልቅ የጠቁረና የጠነከረ በመሆኑ ዕንጨት በል ከሆኑ ምስጦች የተጠበቀ ነው። ግራር በሲና ባሕረ ሰላጤ በብዛት ይገኛል። (12) “የወይራ ዘይት”ም አለ፤ የሚሠራውም የወይራን ፍሬ በማድቀቅ ሲሆን አገልግሎቱ የመብራት ኀይል መስጠት ነው። (13) “ቅመም” የሚለው ቃል በዕብራይስጥ ባሳም (“መዐዛማ መሆን”) ከሚለው የተገኘ ነው። ለመቅቢያ ዘይትነት የሚያገለግሉ አራት ምርጥ የዘይት ዐይነቶች በ30፥22-25 ተጠቅሰዋል፦ “ከርቤ” (ከባስላም ዛፍ የሚወጣ ፈሳሽ)፣ “ቀረፋ” (ከቀረፋ ዛፍ ቅርፊት የሚገኝ)፣ “ጠጅ ሳር” (መልካም መዐዛ ያለው ከሸንበቆ ዐይነት ተክል ሥር የሚገኝ) እና “ብርጉድ” (ከቀረፋ ዛፍ የደረቁ አበቦች የሚገኝ) ነው። አራቱ የዕጣን ዐይነቶች በ30፥34-38 ተጠቅሰዋል፦ “የሚንጠባጠብ ሙጫ” (ከቀረፋ ዛፍ ከተንጠባጠበ ፈሳሽ የደረቀው መሃከለኛው የሚወሰድ፤ እንደ ልብ የማይገኝና ዋጋውም እጅግ ከፍ ያለ ነው)፣ “በዛጎል ውስጥ የሚገኝ ሽቱ” (በቀይ ባሕር ከሚገኝ ሙሬክስ ከሚባል የቀንድ አውጣ ዘር የሚገኝ)፣ “የሚሸት ሙጫ” (በሶርያና በፋርስ ከሚበቅል ወተታማ ፈሳሽ ከሥሩ ከሚያወጣ ዛፍ የሚገኝ) እና “ዕጣን” (በደቡባዊ የዐረብ ምድር ከሚበቅል በስቄሊያ ካርቴሪ የሚገኘው ሙጫ በበጋ ከተክሉ ላይ በራሱ ፈቃድ ስለሚንጠባጠብ “ንጹሕ” የሌላ ባዕድ ነገር ቅይጥ የሌለው ነው፦ ንጹሕ “ነጭ” ነው፤ ስለዚህም ነው ስሙ በዕብራይስጥ “ነጭነት” የተባለው።

(14) “መረግድ” ይህን ምን እንደ ሆነ በርግጠኝነት መናገር ያስቸግራል። የሰብዓ ሊቃናቱ ትርጉም “beryl” ብሎ ይተረጉመዋል፤ ባሕር አረንጓዴ ቀለም ነው። ሌላው አስተያየት የዕብነ በረድ ዐይነት ሆኖ ቀለሙ ከሰማያዊ-አረንጓዴ ወደ ብጫ አረንጓዴ እና ወደ አኘል-አረንጓዴ ድረስ ተፈራራቂ የሆነ ነው ይላል። ይህን የዕብነ በረድ ዐይነት ግብፁውያን ያውቁታል። ሌሎቹ የከበሩ ድጋዮች በኤፋድና በደረት ኪስ ላይ የሚደረጉ ናቸውና፣ 28፥6-25 ይመልከቱ።

8 “መቅደስ” ትርጉሙ “ቅዱስ” ቦታ ወይም “የተለየ ቦታ” ማለት ነው። ማደሪያውን በተመለከተ ሁሉም ነገር ቅዱስ ነው። በ1 እና በ2ዜና ይኸው ቃል ለቤተ መቅደሱ ውሏል። ዕብራውያን 9፥1 መቅደሱን “የዚህ ዓለም መቅደስ” ይለዋል (ዐመት “ምድራዊ መቅደስ”)።

9 መቅደሱን በሚመለከት ከሁሉ የላቀ ትኩረት የሚሰጠው ቃል እግዚአብሔር ለሙሴ በሚያሳየው “ንድፍ” መሠረት መሠራት ያለበት መሆኑ ነው። “ንድፍ” (ምሳሌ) የሚለው ቃል አምሳያ ዘይቤ እንዳለ ያመለክታል፤ ምክንያቱም ይሄ የእውነተኛው ነገር “ሞዴል” ወይም “ንድፍ” ብቻ ነውና (ቁ. 40ን ይመለከቷል)። “ማደሪያ ድንኳን” የሚለው ቃል በብሉይ ኪዳን ውስጥ በዚህ ቦታ ነው ለመጀመሪያ ጊዜ የሚጠቀሰው። ቃሉ “ማደር” ከሚለው ቃል የተገኘ ሲሆን እግዚአብሔር በሕዝቡ መካከል የሚያድርበት ማለት ነው (ከ29፥42-46፤ ከዘሌ 26፥9-12፤ ከሕዝ 37፥26-28፤ እና በዐዲስ ኪዳን፣ ከራእይ 21፥2-3 ጋር ያነጻጽሩ)።

2. ታቦትና የስርየት መክደኛ (25፥10-22)

በማደሪያ ድንኳን ውስጥ ከሚገኙት ሙሴ ከያዛቸው ዕቃዎች ዝርዝር ውስጥ በእግዚአብሔር መመሪያ የተሰጠበት የእግዚአብሔር ታቦት ከ“ስርየት መክደኛው” ጋር ነው።

አንዳንድ ትርጉሞች “የምሕረት መቀመጫ” ይሉታል። ይሁን እንጂ ታቦቱ የስርየት ወይም የመማጸኛ ቦታ ነው፤ በመሆኑም ቦታው የእግዚአብሔር ቸርነት ለሕዝቡ የሚገለጥበት ቦታ ነው።

10*ሀ* “ታቦት”፤ “የምስክር ታቦት” (ቁ.15)፤ “የምድር ሁሉ ጌታ የቃል ኪዳን ታቦት” (ኢያሱ 3፥11)፤ “የተቀደሰው ታቦት” (2ዜና 35፥3)፤ እና “የኃይልህ ታቦት” (መዝ 132፥8)። ታቦቱ የእግዚአብሔር ዙፋን ነው። እግዚአብሔር ከውስጥ ከነገሮች ልብ (ማእከል) ነው የሚጀምረው ከውጭ ጀምሮ ወደ ውስጥ ከመግባት ይልቅ (ደግሞም ከዕብ 9፥4 *ጋር ያነጻ*)።

10*ለ*-17 ታቦቱ ርዝመቱ 3¾ ጫማ ስፋቱና ከፍታው 2¼ ጫማ ነው። “በንጹሕ ወርቅ” ይለበጣል። ክፈፍ ወይም “ኮሌታ” የመሰለ ልባስ በዙሪያው አለ፤ አራት የወርቅ ቀለበቶች እዚህ *ጋር* ነው የሚያያዙት። “ከግራር ዕንጨት” የተሠሩት መሎጊያዎች በቀለበቶቹ ውስጥ ሾልከው ታቦቱን ለማንቀሳቀስ ያገለግላሉ። “ምስክሩ” ወይም የዐሠርቱ ትእዛዛት “ሕጎች” በታቦቱ ውስጥ ይቀመጣሉ። በግብፅ፣ በባቢሎንና በኬጢያዊያን ግዛት በጣም ጠቃሚ የሆኑ ሰነዶች በመቅደስ ውስጥ ከአማልክቱ “እግር ሥር” ይቀመጡ ነበር።

“የስርየት መክደኛ” ከሚለው ቃል ጀርባ የሚገኘው “ማስተሰረይ” የሚለው ግስ ትርጉሙ “መቤገር ወይም ምትክ ከፍሎ ነጻ ማውጣት” ማለት ነው። (“ክዳን” ወይም “መክደኛ” ለሚለው የተሰጠ ቃል እዚህ *ጋ* የለም።) የሰብዓው ሊቃናት ትርጉም እንደ ዕብ 9፥5 (የዐመት ማብ ይመ) ሁሉ “የስርየት መክደኛ” ወይም “የምሕረት መቀመጫ” ነው የሚለው። ይህ የሰው ልጆች ኀጢአት የሚሰረይበት ቦታ የክርስቶስ የመቤገር ሥራ ጠቋሚ (አመልካች) (adumbration) (ሮሜ 3፥25፤ ዕብ 9፥23-24፤ 1ዮሐ 2፥2) እናም ስለ እኛ ለሞተው የምናደርገው አምልኮ ማእከል ነው።

18-22 ኪሩብ (“ኪሩቤል”፦ የብዙ ቁጥር) ክንፎች ያሉት፣ ከሰው ራስ፣ ከበሬ፣ ከአንበሳ፣ ወይም ከንስር አካላት “ተውጣጥቶ” እንደ ተሠራ ፍጡር ያለ ነው (ከዘፍ 3፥24፤ ከሕዝ 1፤ ከራእይ 4 *ጋር ያነጻ*)። በግብፅ ስፊኒክስ በብዛት አሉ። በአሦር ተመሳሳይ ዝርያ ያለው ቃል ለቤተ ጣዖት ጠባቂ የተሰጠ ስም ነው። ሁለቱ ኪሩቤል የሚሠሩት ከራሱ (ከስርየት) መክደኛው እንደ ስርየት መክደኛው አካል ሆነው ነው። ዘና ለማለት አልተፈጠሩም፤ ያለማቋረጥ “ፊታቸውን ወደ ስርየት መክደኛው” አቅንተው መመልከት አለባቸውና (ከ1ጴጥ 1፥12 *ጋር ያነጻ*)።

ቁጥር 22 የታቦቱንና የኪሩቤልን እንዲያውም ለእግዚአብሔር የምናቀርበውን አምልኮ ሁሉ ፋይዳ ይሰጠናል፦ “በዚያ . . . ከአንተ *ጋር* እገናኛለሁ።” ሕያው እግዚአብሔር በማደሪያው ያለማቋረጥ ይገኛል፤ በሕዝቡም መካከል ይመላለሳል (ዘሌ 26፥11-12)። ከኪሩቤል በላይ ባለው ከዚህ ዙፋኑ ሆኖ ነው ለሕዝቡ የተናገረውና ከሕዝቡም *ጋር* የተገናኘው (ከ1ሳሙ 4፥4 *ጋር ያነጻ*)።

3. የኅብስቱ ማስቀመጫ ጠረጴዛ (25፥23-30)

የኅብስቱ ማስቀመጫ ጠረጴዛ በቅድስት ውስጥ ከሚገኙ ሦስት ቁሶች አንዱ ነው። በወርቅ ከተለበጠ የግራር ዕንጨት የተሠራ ሲሆን በላዩ ላይ ዐሥራ ሁለት ኅብስቶች ይቀመጡበታል። ጠረጴዛው ከኅብስቱ የአንድን እውነት ሁለት ገጽታዎች ያሳያል፦ እግዚአብሔራዊውንና ሰብኣዊውን ኅን። በመጀመሪያ በእግዚአብሔር ፊት ይቆማል፤ ይህም የእግዚአብሔርን ሁሉን ዐዋቂነትና የእግዚአብሔርን ጥበቃ ለእስራኤል ያስታውሳታል። በመቀጠልም ካህናቱ የሚያገለግሉበት የዕለት እንጀራቸውን የሚያገኙበት ቦታ ነው። እንጀራው ከሰማይ ሊወርድ ወዳለውና ለወንዶችና ለሴቶች የዘላለም እንጀራ ሊሰጥ ወዳለው *ያመለክታል* (ከዮሐ 6 *ጋር ያነጻ*)።

23-28 “ጠረጴዛው” 3 ጫማ ርዝመት በ11/2 ጫማ ስፋት 27 ኢንች ከፍታ አለው። ከሁለተኛው መቅደስ በአንጥያኮስ ኤጲፋንዮስ የተወሰደው ጠረጴዛ ሮማውያን በ70 ዓመተ ምሕረት ከኢየሩሳሌም ከወሰዷቸው ሌሎች ቁሶች *ጋር* በቲቶ ቅስት ላይ በምስል ተቀምጧል። የጠረጴዛው ገለጻ ከታቦት *ጋር* ተመሳሳይ ነው፤ በወርቅ የተለበጠ፣ ዙሪያውን ክፈፍ ያለውና አራት የወርቅ ቀለበቶች፣ የማንጓጉ ኩላቦችን ማስገቢያ አለው።

29 “ዝርግ ሳሕኖችና ወጭቶች፣ . . . ማንቁርቁሪያዎችና ጐድጓዳ ሳሕኖች” ለእግዚአብሔር ምግብ ለማቅረቢያ የሚያገለግሉ አይደሉም እንደ አረማውያን አሕዛብ አማልክት። ለእግዚአብሔር የተለዩ *መሥዋዕቶች* እንኳ ተቀቅለው ወይም ተጠብሰው አይቀርቡም ነበር፤ በእንፍዋሎችና በመዐባ (በሽታ) መልክ ነበር በፊቱ የሚቀርቡት፦ በቁስ መልክ ወይም በምግብ መልክ አይቀርቡም ነበር። በርግጥ አንዳንዶቹ ቁርባኖች ከካህናት *ጋር* የሚከፋፈሏቸው፣ የኅብረት ቁርባን የሚባሉት ደግሞ በሕፈል ከሕዝቡ *ጋር* የሚከፋፈሏቸው ነበሩ።

30 “ኅብስተ ገጹ” በዚህ ቦታ እና እንዲሁም በ1ሳሙ 21፥6 እና 1ነገ 7፥48 ላይ ተጠቅሷል። በዚህ ሐረግ “ገጽ” (በቁሙ “ፊቶች”፤) ራሱን *መለኮታዊውን* ሰው ይወክላል፣ ልክ “የፊቱ መልአክ” (በቁሙ “ፊት(ቶች)”) በኢሳ 63፥9 ወይም ደግሞ በዘፀ 33፥14-15፣ “ዐብሮነቱ (በቁሙ 'ፊቴ') ዐብሮህ ይሄዳል” በብሉይ ኪዳን ክርስቶስን እንደሚያመለክት ማለት ነው። *ዐሥራ* ሁለቱ ኅብስቶች የዐሥራ ሁለቱ የእስራኤል ነገዶች ተምሳሌት ሆነው በማያቋርጠው በእግዚአብሔር ጥልቅ ፍተሻ፣ ክብካቤና ጥበቃ ውስጥ እንዳሉ *ያመለክታል* (ከዮሐ 6፥32-38 *ጋር ያነጻ*)። ልክ ኅብስቱ ለካህናቱ በቅድስት ውስጥ በሰንበት ምግብ እንደ ሆናቸው (ዘሌ 24፥5-9 ይመ)፣ ኢየሱስም በዚህ ትውልድ የልጆቹን ፍላጎት ያሟላል (ዮሐ 6፥32-35)።

4. የወርቅ መቅረዝ (25፥31-40)

31 በቅድስት ውስጥ የሚገኘው ሦስተኛው ቁስ “ከንጹሕ ወርቅ የተሠራ መቅረዝ” (ሜኖራህ) ሲሆን አንድ ወጥ ሆኖ የተሠራ ነው። የሚቀመጠውም ከቅድስት በስተ ደቡብ ወይም በስተ ግራ በኩል ነው።

የመቅረዙ ቅርጽ፦ “እንቡጦችና የፈነዱ አበባዎች” በለውዝ አበባ ንድፍ የተሠሩ ናቸው (ቁ. 33)፤ ለውዝ በሩቅ ምሥራቅ የመጀመሪያው የጸደይ ዛፍ ሲሆን፣ ከታኅሣሥ አጋማሽ ጀምሮ ማቄጥቄጥ ይጀምርና ቅጠል ከማውጣቱ በፊት በአንጸባራቂ ነጭ አበባዎች ይንቄጠቄጣል። የመቅረዙን ልዩ ልዩ ክፍሎች ምንነት ሙሉ ለሙሉ ርግጠኛ ሆኖ መናገር አይቻልም። “ጽዋ መሰል” የተባሉት አንድም አበባ *ዐቃፊዎች* (የአበባው የውጭ ልብስ፤ በዘፍ 44፥2 ላይ ጽዋ ተብሎ ከተተረጐመው ተመሳሳይ ቃል *ጋር ያነጻ*) አልያም የመድኃኒትነትና የአስዋቢነት ባሕርዩ ፍጹም እንደ ሆነ የሚወራለት የለውዝ ፍሬ ነው። “እንቡጡ” በቅርንጫፉ ላይ የሚገኝ ሉል ወይም ሮማን መሳይ ክብ ነገር ነው (ተመሳሳይ ቃል በሰሎሞን ቤተ መቅደስ ባሉት ጕልላቶች ላይ ለጌጥ የተቀመጡትን ለመግለጥ ውሏል) (1ኛ ነገ 7፥18)።

32-36 አጠቃላዩ የጌጣ ጌጦች ቁጥር፦ ማለትም “ስድስቱ ቅርንጫፎች . . . ሦስት ጽዋዎች . . . በመቅረዙ ላይ . . . አራቱ ጽዋዎች . . . አንድ እምቡጥ፣” ወዘተ . . . በአንድ ላይ 69 ይሆናል (6 ቅርንጫፎች ሲበዛ በ3 ጥንዶች ሲባዛ በ3 ቅርጾች ሲደመር 1 ቅርንጫፍ ሲባዛ 4 ጥንዶች ሲባዛ 3 ቅርጾች ሲደመር 3 በእያንዳንዱ ጥንድ ቅርንጫፎች ያሉ እምቡጦች 68 ይሆናሉ)።

37-39 የጥንቱ መቅረዝ (መብራት፣ ኩራዝ) አነስ ያለ፣ ክብ (የሸክላ) ሳሕን፣ መሳይ ሆኖ ዙሪያው ተጠፍጥፎ ወደ ላይ ሾጠጥ ብሎ የሚወጣና በሳሕኑ ውስጥ ባለው ዘይት የተነከረው ክር በሾጣጣው ጫፍ በኩል ወጥቶ ብርሃን እንዲሰጥ ሆኖ የተሠራ ነው። ባለሰባት ቅርንጫፎች መቅረዝ ምሳሌዎች ከሙሴ ዘመን የተገኙ ናቸው (ኋለኛው የነሐስ ዘመን)። ቤት ቫን እና መጊዶ የመብራት ማስቀመጫ እንዲሆኑ የተሠሩ የብረት መቆሚያዎች ተገኝተዋል። እነዚህም ሦስት ጫማ ርዝመት ያላቸው ቀጥ ብለው የወጡ ዘንጎች በሦስት ጫማ ርዝመት ይከፋፈሉና በቀለበት እርስ በርሳቸው ተያይዘው በመሬት ይቀመጣሉ፤ አናታቸው ላይ ለመብራቱ ማስቀመጫ ጐድጓዳ ነገር አላቸው። "አንድ መክሊት ንጹሕ ወርቅ" ወደ ሰባ ዐምስት ፓውንድ ይመዝናል።

40 "ባሳየሁህ ዕቅድ (ንድፍ) መሠረት" የሚለው ሙሴንና ይህን ጽሑፍ የሚያነቡ ቀጣይ ትውልዶች ሁሉ ማስጠንቀቂያ በድጋሚ የያዘ ቍልፍ ቃል ነው፦ ይህም አሁን ሙሴ የሚገነባው በርግጥ ሞዴል (ንድፍ) ብቻ እንጂ (የቍ 9 ማብ ይመለከታል) ከሞዴሉ በስተ ጀርባ ያለው ዋናውና እውነተኛው ነገር አይደለም የሚል ነው። ስለዚህ "ወደ ፊት ለሚመጡ መልካም ነገሮች ጥላ ነው እንጂ እውነተኛው አካል አይደለም" (ዕብ 10፥1)። በመሆኑም በዚህ መገለጥና ከዘፀ 25 እስከ ዘሌ 9 በተቀመጠው የማደሪያው ድንኳንና አገልግሎቱ ሞዴል ውስጥ ዐብሮ የተሠራ (የተሰጠ) እርጅና አለ። እውነተኛውና ዋናው ነገር በእግዚአብሔር ዘንድ ሲቀር እዚህ የተሰጡት ምድራዊ ሞዴሎች ሊመጣ ያለውን አመላካች ብቻ ናቸው።

5. መጋረጃዎች፣ ወጋግራ (አውታር)፣ መሸፈኛ እና መለያ (26፥1-37)

ሀ. የማደሪያው ደንኳኖች (26፥1-14)

ሁለት የተሟሉ መሸፈኛዎችና ሁለት የተሟሉ መጋረጃዎች አሉ። ሁለቱ መሸፈኛዎች ከባሕር እንስሳት ቈዳ የተሠራ ከላይ የሚሆነውና ከፍየል ጠጕር ተሠርቶ ቀይ ቀለም የሚነከረው ከውስጥ የሚደረገው ናቸው። ሁለቱ መጋረጃዎች ደግሞ ከፍየል ቈዳ ወጥ ሆኖ የሚሠራው ከላይ የሚሆነውና በሰማያዊ፣ በሐምራዊና በቀይ ቀለማት ባጌጠ የበፍታ ሐር የተሠራ ከታች የሚሆነው ናቸው። በመቅደሱ ውስጥ ከውስጥ ወደ ውጭ ሲወጣ፣ ከጥሩ በፍታ የተሠሩት መጋረጃዎች የሚታዩት ራሱ ንጽሕናና ጽድቅ የሆነውን ጌታ ለሚያገለግሉት ካህናት ብቻ ነው። ከፍየሎች ፀጕር የሚሠሩት መጋረጃዎች ለየዕለቱ ኀጢአት ከፍየል ጠቦት የሚቀርበውን ቍርባንና (ዘኍ 28፥15) የራሳችንንም ከኀጢአት መንጻት የሚያስታውሱ ናቸው (ዘሌ 16)። ከበግ ቈዳ የሚሠራው መሸፈኛውም ክህነቱን ለመመረቅ (ለማጽደቅ) የተሠዋውን መሥዋዕት ያሳስባል (ዘሌ 8)፤ እናም ሆነ ተብሎ ቀይ ይነከራል፤ ይህም ክህነቱ የተቀደሰው በደም እንደ ሆነ ያመለክታል። በመጨረሻም ከባሕር እንስሳት ቈዳ የተሠራው የመከላከያ ልባስ በእግዚአብሔር የማደሪያ ቦታና በዓለም መካከል ያለውን የመከላከያ ልዩነት ያሳያል።

1-3 "በፍታ"ን በተመለከተ 25፥4ን ይመለከታል። "በቀጭኑ ከተፈተለ የበፍታ ድር" የተሠሩት ዐሥሩ መጋረጃዎች እያንዳንዳቸው ወደ አርባ ሁለት ጫማ ርዝመትና ስድስት ጫማ ስፋት አላቸው። ዐሥሩ መጋረጃዎች በሁለት ተከፍለው ዐምስት ዐምስቱ አንድ ላይ ተገጣጥመው ነው የተሰፉት። መጋረጃዎቹ ከማደሪያው ድንኳን ወጋግራዎች (መዋቅሮች) ይልቅ አስፈላጊ ናቸው፤ ምክንያቱም መጀመሪያ ነውና የተገለጹት፦ ይህም ቀደም ብለን በማደሪያው ድንኳን ውስጥ ያሉት ቍሶች አስፈላጊነት የሚወሰነው በተጠቀሰበት ቅደም ተከተል ነው ባልነው መሠረት ነው።

4-6 እያንዳንዱ ባለ ዐምስት ክፍል መጋረጃ አንድ ላይ ከተሰፋ በኋላ፣ ሁለቱ መጋረጃዎች በአንዱ የመጋረጃ ጠርዝ ዐምሳ ቀለበቶችን፣ በሌላው የመጋረጃ ጠርዝ ዐምሳ ቀለበቶችን በማድረግ ይቀጣጠላሉ። ከዚያም በዐምሳ መንጠቆ መሳይ የወርቅ ማያያዣዎች ይያያዛሉ (ከቍ 11 ጋር ያነጻ) ። በሰማያዊ፣ ሐምራዊና ደማቅ ቀይ ማግ ያሸበረቁት፣ በቀጭኑ ከተፈተለ ማለፊያ ነጭ በፍታ የተሠሩት የእነዚህ መጋረጃዎች ውበት (25፥4 ይመለከታል)፤ በላያቸው ላይ በተጠለፉት የኪሩቤል ምስሎች (25፥18 ይመ) የበለጠ ጕልቶ ወጥቷል።

7-13 ከ"ፍየል ጠጕር" ከተሠሩት የማደሪያውን ድንኳን ላይኛውን ክፍል ከሚሸፍኑት ከዐሥራ ሁለቱ መጋረጃዎች ስድስቱ በአንድ በኩል፣ ዐምስቱ በሌላ በኩል በአንድ ላይ ተሰፍተዋል፤ እንደ ገናም በአንድ በኩል ያሉት ዐምሳ ቀለበቶች በሌላ በኩል ባሉት ዐምሳ ቀለበቶች በዐምሳ ማያያዣዎች ተገጣጥመው ተያይዘዋል። በምሥራቁ ዓለም የፍየል ጠጕር ጥቍር ነው፤ ነጭ አይደለም (ከማሕ 1፥5 ጋር ያነጻ፤ በ25፥4 ላይም ካለው ሐሳብ ጋር ያነጻ)። የ"ድንኳኑ መጋረጃዎች" ከማደሪያው መጋረጃዎች የሚበልጡ በመሆናቸው (ቍ 1-6)፤ በስተ መጨረሻውና በግራና በቀኝ በኩል የተረፈው "ከማደሪያው ድንኳን ጀርባ እንዲንጠለጠል" እና "የማደሪያውን ድንኳን ጎኖች እንዲሸፍን ሆኖ ይንጠለጠላል።"

14. 25፥5ን በሚመለከት ማብራሪያውን ይመለከታል።

ለ. የማደሪያው መዋቅሮች (26፥15-30)

15-25 የ"ግራር ዕንጨትን" አስመልክቶ በ25፥5 ያለውን ማብራሪያ ይመለከታል። "ቀጥ ያሉ ቋሚዎችን" (ከቍ 19፡26 ጋር ያነጻ) እንዲያበጅ የተሰጠው ትእዛዝ "ግድግዳው" የሚሠራባቸውን ሦስት ነገሮች ያስተዋውቃል። በተለምዶ የሚጠራበት "ሣንቃ" የሚለው ቃል ብዙዎች ግድግዳው ድፍንና ጥጥር ነው የሚል ግምት እንዲይዙ አድርጓቸዋል፤ እንዲህ ቢሆን ኖሮ የውስጠኞቹን የበፍታ መጋረጃዎች በመሸፈን እንዳይታዩ ያደርጋቸው ነበር። እነዚህ ወጋግራዎች የሐረግ መደገፊያ ባላ የመሰሉ መዋቅሮችን በመፍጠር የአራቱ መጋረጃዎች መዘርጊያ አውታር ሆነዋል።

እያንዳንዱ ወጋግራ 15 ጫማ ርዝመት በ2¼ ጫማ ስፋት ያለው ነው። የማደሪያው መዋቅር ሀያ ወጋግራዎችን (ሣንቃዎችን) በስተ ሰሜን፣ ሀያ ወጋግራዎችን በስተ ደቡብ ይይዛል፤ በምዕራብ ጠርዝ ያለው ደግሞ ስድስት ወጋግራዎች ይኖሩታል። ዳርና ዳር ያሉት ማእዘኖች እያንዳንዳቸው አንዳንድ ወጋግራ ይኖራቸዋል። "ሁለቱ መቆሚያዎች" (በቁመ "እጆች") ምናልባት በእያንዳንዱ ወጋግራ መቆሚያ ሥር የሚገቡ ሁለት ማያያዣ ቅስቶች ናቸው። ወጋግራዎቹ ከመሠረቱ ጋር የተጣበቁት በእያንዳንዱ ጎን በ"አርባ የብር መቆሚያዎች" ነው።

እስራኤላውያን ለእነዚህ መቆሚያዎች ሥራ የሚውል አንድ መቶ መክሊት ብር አዋጥተዋል (38፥25-28)፤ ይህም የማስተሰረያ ገንዘብ ተብሎ ተጠቅሷል (30፥11-16)። ከዚህ የተነሣ የማደሪያው ድንኳን መሠረት ያረፈው በዎጀ ወይም በመቤገት ላይ ነው ማለት እንችላለን፤ ልክ ቤተ ክርስቲያን "በገዛ ደሙ የዋጃት" የተዋጀች እንደ ሆነች ሁሉ (ሐሥ 20፥28)።

"ማእዘን" የሚለው የዕብራይስጥ ቃል በግልጽ "ጠርዝ" (angles) ማለት ነው። እናም አንዱ ወጋግራ መሃከሉ ላይ በማእዘን ቍርጥ ይቈረጣል፤ ከዚያም ሁለቱ ቍራጮች በሁለቱ የማእዘኑ ጎኖች ያሉትን ጠርዞች (ማእዘኖች) ይሠራሉ ማለት ነው።

26-29 ዐሥራ ዐምስት "አግዳሚዎች" በመዋቅሩ ላይኛ በኩል በመሆን ዳጋፊ ወጋግራዎቹን ያጠናክራሉ፦ በሁለቱ ጎኖች

(ሰሜን እና ደቡብ) በእያንዳንዱ ዐምስት ዐምስት እና በስተ ጀርባ ላለው (ምዕራብ) ዐምስት አግዳሚዎች ይደረጋሉ። ከዐምስቱ አንዱ አግዳሚ ከግድግዳው አጋማሽ ጀምሮ ሙሉ ለሙሉ መራት ይደርሳል፤ ቀሪዎቹ አራቱ ደግሞ የግድግዳው አጋማሽ ድረስ ብቻ ነበር የሚደርሱት ይህም በወጋግራዎቹ በስተ ውጭ ሦስት የአግዳሚ ረድፎችን ፈጥሯል። "የወርቅ ቀለበቶቹ" ለአግዳሚዎቹ እንደ መያዣዎች (በቁሙ "ቤቶች") ያገለግላሉ (ከ25፥26-27 ጋር ያነጻ)።

30 አሁንም በድጋሚ ሁሉም ነገር "በዕቅዱ መሠረት" መሠራት እንዳለበት ያስታውሰናል (የ25፥40 ማብ ይመ፤ ከዕብ 8፥5 ጋር ያነጻ)።

ሐ. የማደሪያው መጋረጃ (26፥31-35)

የውስጡ መሸፈኛ (አመት፣ "መጋረጃ")፣ ቅድስተ ቅዱሳንን ከቅድስት የሚለየው እንደ ውስጣዊው መጋረጃ ባለ ቀድና ንድፍ መሠራት አለበት፤ እንዲሁም በወርቅ በተለበጡ የግራር ምሰሶዎች ይደገፋሉ። "መጋረጃው" "የመክደኛ መጋረጃ" ወይም "መከለያ መጋረጃ" (39፥34፤ 40፥21፤ ዘኍ 4፥5) ወይም ደግሞ "ከምስክሩ ታቦት ፊት ለፊት . . . ያለው መጋረጃ" (27፥21) ተብሎ ተጠርቷል። ክርስቶስ በሞተ ጊዜ፣ ይህ የቤተ መቅደሱ የውስጠኛው መጋረጃ ለሁለት ተተረተረ፣ በዚህም ለአማኙ ወደ እግዚአብሔር ሀልዎት በማናቸውም ጊዜ እንዲገባ ዕድል ሰጠው (ማቴ 27፥51፤ ማር 15፥38፤ ሉቃ 23፥45፤ ዕብ 6፥19፤ 9፥3፤ 10፥19-22)።

መ. የማደሪያው ድንኳን መለያ (screen) (26፥36-37)

36 "ለድንኳኑ ደጃፍ . . . መጋረጃ" የተባለው የማደሪያውን ድንኳን ሁለት ውስጠኛ ክፍሎች (ቁ. 33) የሚለየውን በቁ. 1 የተጠቀሰውን የውስጡን መጋረጃ የሚመስል ነው። በአደባባዩ መግቢያ (ደጃፍ) ላይ ለሚገኘው መጋረጃ (27፥16) የተጠቀሰው የዕብራይስጥ ቃል በዚህ ቦታ ላለው ደጃፍ (screen) እንደ ተሰጠው የዕብራይስጥ ቃል ተመሳሳይ ነው።

37 ይህ መጋረጃ ወደ ውጭና ወደ ግድግዳው ማእዘኖች ስለሚዘልቅ "በወርቅ የተለበጡ ዐምስት ምሰሶዎች" አሉት በአራት ምሰሶዎች ምትክ (ቁ. 32)።

6. የሚቃጠል መሥዋዕት መሠዊያ (27፥1-8)

1-2 ለአምልኮተ እግዚአብሔር ወደ ማደሪያው ድንኳን አደባባይ የሚገባ ሰው በመጀመሪያ የሚያገኘው የመጀመሪያውና ትልቁ ዕቃ "መሠዊያ"ው ነው፣ በዘሌ 4፥7 ፡10 ፡18 የሚቃጠል መሥዋዕት መሠዊያ ነው። የተቀመጠው ልክ በመግቢያው በር አጠገብ መሆኑ በቀላሉ የሚታይ፣ ሊታሰፍና ሊስቱት የማይቻል አድርጎታል። የተሠራው ከግራር ዕንጨት ሲሆን (የ25፥5ን ማብራሪያ ይመለከቷል)፣ መጠኑ 7½ ጫማ ስፋት በ4½ ጫማ ከፍታ ነው። በነሐስ የተለበጠ ነው። አንድ መሠዊያ ብቻ ነው ያለው፤ አንድ የመዳን መንገድ ብቻ እንዳለና ይኸውም በኢየሱስ እንደ ተፈጸመ ሁሉ (ይመ ዮሐ 1፥29፤ ዕብ 9፥13-14፡22-28)። "ቀንዶቹ" ማለትም "በመሠዊያው በአራቱም ማእዘኖች ላይ" የሚደረጉት ቀንዶች የመሠዊያው አራቱ ማእዘኖች ወጣ ብለው የሚታዩ ሹል ነገሮች ሆነው የመሠዊያው አንድ አካል ናቸው። ተምሳሌታቸውም ኀይልን፣ ርዳታንና መጠጊያን የሚያሳይ ነው (ከ1ሳሙ 2፥1፡10፤ ከ2ሳሙ 22፥3፤ ከ1ነገ 1፥50፤ 2፥28፤ ከመዝ 89፥17፤ 112፥9 ጋር ያነጻ)። ቀንዶቹ የመሠዊያው የማስተስረይ ኀይል ተምሳሌት የሆኑበት ምክንያት በማስተስረዩ ሥነ ሥርዐት ወቅት የተወሰነው ደም ከመሠዊያው ሥር ከመፍሰሱ በፊት በቀንዶቹ ላይ ስለሚፈስ ነው (29፥12፤ ዘሌ 4፥7፡18፡25፡30፡34፤ 8፥15፤ 9፥9፤ 16፥18)።

3 "ምንቸቶቹ" ሥጋ የጠገበው ዐመድ "በመጫሪያዎቹ" አማካይነት ከምድጃው በሚወገዱበት ጊዜ ለመያዣነት ያገለግላሉ። "የመርጫ ሳሕኖች" (ጐድንዳ ሳሕኖች) በመሠዊያው አጠገብ የታረደው እንስሳ ደም በኋላ ላይ በመሠዊያው ግርጌ እስኪረጭ ድረስ ለማቄያ የሚያገለግል ነው። ባለ ሦስት አውታር "የሥጋ ሜንጦዎች" (የሥጋ መቆንጠጫዎች) መሥዋዕቱን ለማስተካከል ወይም ደግሞ ለካህናቱ የሚሆነውን ድርሻ ለማንሣት ያገለግላል (1ሳሙ 2፥13)። "የፍም መያዣዎች" (ወይም "ጥናዎች") ምናልባት እሳትን ከዕጣን መሠዊያው ወደ ቅድስት ለመውሰድ ያገለግላሉ (ዘሌ 10፥1፤ 16፥12፤ 1ነገ 7፥50)።

4-8 "የነሐስ ፍርግርግ" ከመሠዊያው አናትና ከመሠዊያው ወለል መካከል ላይ የሚቀመጥ ሳጥን መሳይ ቀኖ ነው። ፍርግርጉ መሠዊያውን በላዕላይና ታሕታይ ክፍሎች ከፋፍሎታል፡- ይህንን ክፍፍል አስፈላጊ ያደረገው የደም መርጨቱ ጉዳይ ነው። በመሠዊያው የላይኛው ግማሽ የሚቀጣጠል ማንኛውም ዓይነት እሳት ከከፍተኛ ሙቀት የተነሣ በሂደት መሠዊያውን ማውደሙ ስለማይቀር፣ ምናልባት መሠዊያውን ከዚህ ዐደጋ ለመከላከል ይሆናል መሠዊያው በሥራ ላይ በሚሆንበት ጊዜ ሁሉ በዐፈር መሞላት ያለበት። ምናልባትም ለዚህ ይሆናል መሠዊያው ውስጡ "ባዶ" ሆኖ እንዲሠራ የታዘዘው። "በአራቱም የመሠዊያው ማእዘኖች" የነሐስ ቀለበቶች ከፍርግርጉ ጋር እንዲያያዙ ይደረጋል፤ መሠዊያውን ማንቀሳቀስ ሲያስፈልግ የግራር ዕንጨት መሎጊያዎች በቀለበቶቹ አስገብቶ ማጓጓዝ ይቻላል። "እርከን" በመሠዊያው የላይኛው ግማሽ ዙሪያውን እንደ ክፈፍ ሆኖ ወጣ ብሎ የሚሠራ ነው።

7. የማደሪያው ድንኳን አደባባይ (27፥9-19)

9-11 "የመገናኛው ድንኳን አደባባይ" 150 ጫማ ቁመት በ75 ጫማ ስፋት ያለው ፍጹም ሬክታንግል (አራት ማእዘን) ነው። አራት አገልግሎቶች አሉት፡- (1) ከደንቡ (ከሕጉ) ውጪ መቅረብን ለመከላከል (2) የዱር እንስሳትን በሙሉ በውጭ ለማቄየት (3) በዓለምና በእግዚአብሔር ቅዱስ ሀልዎት መካከል አዎንታዊ የድንበር ምልክት ለመከለል እና (4) ባለ አንድ መግቢያ ብቻ እንደ መሆኑ ወደ እግዚአብሔር የመቅረቢያ መንገድ እንዲሆን ነው።

አደባባዩ በመጋረጃ ይጋረዳል (ይከለላል)፤ ይኸው መጋረጃ የሚሠራበት ቀድና ቀለሞቹ (ቁ. 16) ከመግቢያው፣ ከመለያ መጋረጃዎችና ከማደሪያው ድንኳን ውስጠኛ መጋረጃዎች ጋር አንድ ዐይነት ናቸው (26፥31-33፡36-37)። የሁሉንም ሰዎች እይታ ለመጋረድ በቂ ከፍታ (7½ ጫማ፣ ቁ. 18) ሊኖረው ይገባል። እያንዳንዱ ረዥም ጎን "ሃያ ምሰሶዎችና ሃያ የነሐስ መቆሚያዎች" ይኖሩታል። በአጠቃላይ ስልሳ ምሰሶዎች (ወይም ደግሞ በየማእዘኑ ያሉት ምሰሶዎች ለውጭ ተመልካች እርሱ ከሚያይበት ጎን ጋር እየደመራቸው ሁለቱ ከተቁጠሩ ዐምሳ ስድስት ይሆናሉ።) በምሰሶዎቹ መካከል የ7½ ጫማ ርቀት አለ፤ በምሰሶዎቹ ላይ ዘንጎችና የብር ኩላቦች ይደረጋሉ፤ ይህም ለመዋቅሩ ጽናት ይሰጠዋል።

12-19 አደባባዩ በሁለት እኩል ክፍሎች የተከፈለ ነው። የማደሪያው ድንኳን በምዕራባዊው አጋማሽ ማእከላዊውን ቦታ ይዟል፤ መሠዊያውና የመታጠቢያው ሳሕን ምናልባት በምሥራቃዊው አጋማሽ ማእከል ላይ ይገኛሉ (የማደሪያውን ድንኳን ልዩ ልዩ ክፍሎች ምስል ይመለከቷል)። ደጃፉ (ዋናው መግቢያ) በጣም ሰፊ ነው፡- "ሃያ ክንድ ርዝመት ያለው መጋረጃ" ወደ ሠላሳ ጫማ ርዝመት ባለው መግቢያ ላይ ይዘረጋል (ከ6፥36-37 ጋር ያነጻ)። በተጨማሪም መግቢያው በዓለምና በእግዚአብሔር ማደሪያ ስፍራ መካከል ያለውን ልዩነት ያመለክታል። በአደባባዩ ዙሪያ የሚገኙት ምሰሶዎች

በሙሉ የብር ዘንጎች ወይም ኩላቦች ላሏቸው፤ እነዚህ ቀጠን ያሉ የማሰሪያ የብረት ዘንጎች በግልጽ እንደ ጌጥ ያገለግላሉ።

8. ክህነት (27÷20-28÷5)

አሮንና አራቱ ልጆቹ ብቻ ናቸው እንደ ካህናት በእግዚአብሔር ፊት ቆመው ማገልገል የሚችሉት። ካህኑ ከእግዚአብሔር ጋር ለሚደረገው ኅብረት ምትክ የለሽ መካከለኛ ነው።

20-21 "ተወቅጦ የተጠለለ ንጹሕ ዘይት" ካልበለለ የወይራ ፍሬ በወፍጮ ከመፍጨት ይልቅ በሙቀጫ ተወቅጦ የሚዘጋጅ ነው። ቀጥሎም የተፈጨው ፍሬ ክምር በቅርጫት ውስጥ ይደረጋል፤ ከዚያም ዘይቱ፣ ምንም ዐይነት ሌላ የወይራ ክፍል ሳይደባለቅበት ከቅርጫቱ እየተንጠባጠበ ጭስ የሌለው ወይም በጣም ትንሽ ጭስ ብቻ ያለው የጠራ ንጹሕ የመብራት ዘይት ያስገኛል። መብራቶቹ "ከምሽት እስከ ንጋት" መብራት አለባቸው (ከ30÷8፤ ከ1ሳሙ 3÷3 ጋር ያነጻ)። አስፈላጊው ነገር ሕዝቡ ዘይቱን ያለማቋረጥ ማቅረብ የነበረበት መሆኑ ነው፤ አለበለዚያ በእግዚአብሔር የማደሪያ ቦታ ጨለማ ይሆናል።

1 ናዳብና አብድዩ ከአራቱ የአሮን ልጆች መካከል ሁለቱ ሲሆኑ የኋላ ኋላ እግዚአብሔር ያላዘዘውን ዐይነት እሳት ለእግዚአብሔር በማቅረባቸው ተቀሥፈዋል (ዘሌ 10÷1-2)፤ በመሆኑም አልዓዛርና ኢታምር ብቻ ቀርተዋል። አሮንና ልጆቹ "ካህናት ሆነው እግዚአብሔርን ያገለግሉ ዘንድ" ተለይተዋል። በእግዚአብሔር ፊት ለመቆም (በዘዳ 10÷8 ላይ ይህ ለሁሉም ካህናት የተሰጠ መብት ነው)፣ "ለኀጢአት የሚሆነውን መባንና መሥዋዕትን ለማቅረብ" እና "አላዋቂ ለሆኑትና ለሚባዘኑት" እንዲራሩ ነው የተጠሩት (ዕብ 5÷1-2)። ሕዝቡን ያስተምራሉ (ነህ 8÷2፡9)፣ ይማልዱላቸዋልም።

2-5 የሊቀ ካህናቱ ልብሶች "ለእነርሱም ማዕረግና ክብር ለመስጠት" ነው፤ ይህም ማለት ለሊቀ ካህናቱ ቢሮና ለአገልግሎቱ ክብር ለመስጠትና እንዲሁም ደግሞ ለአምልኮተ እግዚአብሔር ውበትን ለመስጠት ነው። "ጥበበኛ የሆኑት ሰዎች" ለአሮን የክህነት ልብስ ይሥሩለት። ስምንት ልብሶች ናቸው የተጠቀሱት፡- አራቱ ከውስጥ የሚለበሱት በሁሉም ካህናት የሚለበሱ ናቸው። እነዚህም ሸሚዝ፣ የበፍታ የውስጥ ቁምጣ፣ መታጠቂያና ጥምጥም ናቸው (ቁ. 39-42)። አራቱ ከላይ የሚደረቡ በተለይ አሮን የሚለብሳቸው ደግሞ የደረት ኪስ፣ ኤፋድ፣ ሻማ እና ጥምጥም ናቸው።

9. የካህናቱ ልብሶች (28÷6-43)

6-14 ኤፋድ ምናልባት ሊቃነ ካህናቱ የሚለብሱት እስከ ጭን የሚደርስ መደረቢያ ሲሆን ከሰማያዊ፣ ሐምራዊ ቀይና ነጭ በፍታ ተፈትሎ የሚሠራና ሁሉም በወርቃማ ክር የሚገመድ ነው። እጅጌ፣ የሌለውና እንዲሁም ደግሞ ጠርዞቹ እርስ በርስ ተገጣጥመው ያልተሰፉ ናቸው፤ ሁለት የትከሻ ንጣዮች እያንዳንዳቸው ሁለት የመረግድ ድንጋዮች ተንጠልጥ ለውባቸዋል። በስተ ግራ ያለው መረግድ የስድስቱ የያዕቆብ ታናናሽ ልጆች ስም የተቀረጸበት ሲሆን፣ በስተቀኝ ያለው ደግሞ የስድስቱ ታላላቆች ስም ይቀረጽበታል። የስሞቹ ተምሳሌትነት ሊቀ ካህናቱ በማደሪያው ድንኳን ሲያገለግል መላውን እስራኤልን መወከሉን ለማመልከት ነው። "የወገብ መታጠቂያ" ከኤፋድ ጋር የተሠራበት የክር ዐይነትና የስፌቱ ዐይነት ተመሳሳይ ሲሆን የኤፋዱን የፊትና የኋላ ክፍል ከካህኑ ሰውነት ጋር ያያይዘዋል። የራሱ የሆነ ሃይማኖታዊ ፋይዳ የለውም።

15-30 የፍርድ መስጫው "የደረት ኪስ" አራት ማእዘን የሆነ ቍራጭ ጨርቅ ሲሆን ነገረ ሥራው እንደ ኤፋድ ሆኖ እኩል ለእኩል ወደ ላይ ታጥፎ አንድ ስንዝር ስፋት በአንድ ስንዝር ርዝመት አለው። በውስጠኛው ጠርዞች ሁለት የወርቅ ቀለበቶች የደረት ኪሱን ሰማያዊ ገመድ ካለው የኤፋዱ ጎን ጋር ያያይዙታል። በደረት ኪሱ ላይኛው ጫፍ ላይ የሚገኙ ሁለት የወርቅ ቀለበቶች ከሁለቱ የኤፋዱ የትከሻ ንጣዮች ጋር በሁለት የወርቅ ዘለበቶች ያያይዙታል። ዐሥራ ሁለት ድንጋዮች፣ አንድ ድንጋይ አንድ የእስራኤል ነገድ ወክሎ ሦስት ሦስት ድንጋዮች በያዙ አራት ረድፎች ይቀመጣል፡- የያዕቆብ ልጆች የእያንዳንዳቸው ስም ከታላቁ ጀምሮ እስከ ታናሹ በቅደም ተከተል በድንጋዮቹ ላይ ይቀረጻል። በዚህ ዐይነት አገሪቱ በጌታ ፊት ዕጥፍ ጊዜ ትወከላለች።

"ኡሪምና ቱሚም" (በቁመ. ብርሃናት እና ፍጹምነት) አስቸጋሪ ሁኔታ በሚያጋጥም ጊዜ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመለየት ያገለግላሉ (ዘኍ 27÷21)፤ ይሁን እንጂ እንዴት እንደሚሠሩና ምን እንደሚመስሉ አይታወቅም። ምናልባት ለሊቀ ካህናቱ ብቻ ልዩ መገለጥን የሚወክሉ ይሆናሉ፤ ይህን መረጃ የማግኛ ዘዴ ግን አይደለም። በተጨማሪ ዘሌ 8÷8፤ ዘኍ 27÷21፤ ዘዳ 33÷8፤ እና ሌሎችም ይመልከቱ።

31-35 ከኤፋዱ ሥር ረዥም እጅጌ የሌለው፣ ከጕልበት ትንሽ ዝቅ የሚል ስፌት የሌለው ሰማያዊ ቀሚስ አለ። እጆችን ማስገቢያና እንዲሁም ራስ ማሾለኪያ (ዐንገትጌ) አለው። የእነዚህ ጠርዝ (ክሳድ) በሰማያዊ፣ በሐምራዊ፣ በቀይ ማግ ከሮማኖችና ከወርቅ ሻኩራዎች ጋር በማፈራረቅ ይሠራል። ሊቀ ካህናቱ በማደሪያው ድንኳን በሚያገለግልበት ጊዜ ሻኩራዎቹ (ደወሎቹ) የሚሰጡት ድምፅ ከውጭ ሆነው ለሚሰሙት ሊቀ ካህናቱ በቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ አለመሞቱንና ስለ እነርሱም የመማለድ አገልግሎቱን እንደሚቀጥል ያረጋግጥላቸዋል።



የሊቀ ካህናቱ ልብሶች፣ በደረት ኪሶቹ ከ12 ድንጋዮች ጋር (ለየነገዱ አንድ አንድ)።

36-39 በጥምጣሙ ላይ የሚገኘው በጣም ጕልሕ ሆኖ እይታ የሚስበውና በጣም አስፈላጊው ነገር "ቅድስና ለእግዚአብሔር" የሚል ጽሑፍ የተቀረጸበት የወርቅ ሳሕን ነው። ሳሕኑ ከአንደኛው ጆሮ እስከ ሌላኛው ጆሮ የሚዘልቅ ሲሆን ግምባርን ይሸፍናል። በሳሕኑ ጥግና ጥግ ባሉት ቀዳዳዎች በሚገባ ሰማያዊ ፈትል ይያያዝና ወደ መሃል አናት ላይ ወደሚገኘው በሳሕኑ መሃል ወዳለው ቀዳዳ ይገባል።

“ከቀጭን በፍታ የሚሠራው ሸሚዝ” ያለጥርጥር ከሐር የውስጥ ቁምጣ በላይ የሚደረብ ረዘም ያለ የሐር መደረቢያ (ቍ. 42) ሲሆን ምናልባትም እስከ ቁርጭምጭሚት የሚደርስ ከሰውነት ጋር ጥብቅ እንዲል ተደርጎ የተሰፋ ነው።

40-43 ቀጥሎ የቀረበው ለተራ ካህናት የሚሆነው የልብስ ዐይነት ነው። ዐላማው ካህናቱ በአገልግሎታቸው ወቅት “ሞገስና ክብር” (በቁመ. ግርማና ውበት) እንዲኖራቸው ማድረግ ነው። ቍጥር 41 ወደ ምዕራፍ 29 መሸጋገሪያ ሐሳብ ይሰጣል፤ ይህም ስለ ካህናቱ ሹመት ይናገራል። የተልባ እግር ልብሶችን በሚመለከት 20፥26ን ይመለከቷል።

10. የካህናት ለአገልግሎት መቀደስ /መሾም (29፥1-46)

በ28፥41 ላይ ለሙሴ የተሰጡት ትእዛዞች በዚህ ቦታ በጣም በዝርዝር የቀረቡ ሲሆን በዘሌ 8 ላይ ተተግብረዋል። አሮንና ልጆቹን ለአገልግሎት ለመሾም የተደረገው የመቀደስ ድርጊት ያተኰረው ቅዱሱን አምላካችንን በማምለክ አጠቃላይ ሂደት ውስጥ የተሰጣቸው ኀላፊነት ኮምጫጫነትና የተልእኳቸው ማእከላዊነት ላይ ነው።

1-9 አሮንንና ልጆቹ በቅደም ተከተል ሊቀ ካህናትና አገልጋይ ካህናት በመሆን ተመድበዋል። ይህ የመቅደስ ተግባር በተለይ ለማደሪያው ድንኳን አገልግሎት የተለዩበት ነው። ለዚህ አገልግሎት የሚውሉት መሥዋዕቶች “ነውር የሌለበት” የሚለውን ማሟላት አለባቸው (ከ12፥5 *ጋር ያነጻ*)። በተመሳሳይ ካህናቱን ለአገልግሎት ለመለየት የሚውለው መሥዋዕት “እርሾ የሌለበት” መሆን አለበት (ከ12፥15 *ጋር ያነጻ*)። ከዚያም አሮንና ልጆቹ ይታጠባሉ። የሊቀ ካህናቱ የምደባ ሥነ ሥርዐት ዘጠኝ ተግባሮችን የያዘ ሲሆን (ዘሌ 8፥7-9) ለመደበኛ (ተራ) ካህናት ግን አራት ብቻ ናቸው። መታጠብ (ማጠብ) ተምሳሌትነቱ ከኀጢአት የተነሣ የሚመጣን መቁሸሽ ማስወገድ ነው (ከ40፥12-13፤ ከዘሌ 8፥6-9 *ጋር ያነጻ*፤ ዕብ 10፥22 ይመ)።

አሮንና ልጆቹ በመቀጠል በምዕ. 28 የተገለጹትን ልብሶች ለበሱ፤ ከዚያም ተቀቡ። ሊቀ ካህናቱ አሮን የተቀባበት መንገድ ልጆቹ ከተቀቡበት መንገድ የተለየ ነው (ከቍ. 21 *ጋር ያነጻ*፤ እንዲሁም ከዘሌ 21፥10 *ጋር ያነጻ*)። የቅብዓቱን ዘይት አሠራር በሚመለከት የ30፥22-25ን ማብራሪያ ይመለከቷል።

10-12 ለአሮንና ለልጆቹ ያለፈ ኀጢአት መሥዋዕት እንዲሆን ወይፈን ይቀርባል። ይህም እጃቸውን በወይፈኑ ራስ ላይ በሚጭኑበት ጊዜ ማለትም ኀጢአታቸውን በኀጢአት ተሸካሚው ላይ በሚያስተላልፉበት ጊዜ፣ ተምሳሌታዊ በሆነ መንገድ ይፈጸማል (ከዘሌ 4፥1-5፥13፤ 16፥11፡15፡21 *ጋር ያነጻ*)። በመቀጠልም ወይፈኑ በእግዚአብሔር ፊት ለበደል ስርየት እንዲሆን ይታረዳል። ደሙን በመሠዊያው ቀንዶችና በመሠዊያው ሥር ማፍሰስ የመሥዋዕት ማቅረቢያውን ቦታና መሥዋዕቱንም ጭምር ይቀድሳል።

13-14 *መሥዋዕቱ ከታረደ በኋላ ምርጥ የሆነው የመሥዋዕቱ* ክፍል በመሠዊያው ላይ ይቃጠላል፤ *መሥዋዕቱን* የሸፈነው ሥብም የመሥዋዕቱን እሳት ይበልጥ ያቀጣጥለዋል (ከዘሌ 3፥4-5፡16፤ 7፥23-25 *ጋር ያነጻ*)። ነገር ግን ሥጋውና ቈዳው ከሌሎች የማይፈለጉ ክፍሎች *ጋር* በኀጢአት የተበከሉ እንደ ሆኑ ስለሚቈጠር ከሰፈር ውጭ ይቃጠላሉ። በተመሳሳይ፣ ክርስቶስ *መሥዋዕታችን* መንፈሱን ለሰማዩ አባት አቀረበ፤ ነገር ግን ሥጋው ከ“ሰፈር” ውጭ፣ ወደ መቃብር ውስጥ ገባ (ከዕብ 13፥11-13 *ጋር ያነጻ*)።

15-18 በወይፈኑ ላይ እንዳደረጉት ሁሉ አሮንና ልጆቹ ከሁለቱ አውራ በጎች በአንደኛው ላይ እጃቸውን በመጫን እንዲወክላቸው ያደርጋሉ። ይህ አውራ በግም ሙሉ ለሙሉ ለእግዚአብሔር *መሥዋዕት* ይሆናል። ከመላው ሕይወታቸውና ከሙሉ ልባቸው ለእግዚአብሔር የሆኑትን ሁሉ ወይም ሊሆኑ ያሰቡትን ሁሉ የሚጠይቅ *መሥዋዕት* ነው። ይህም ለእግዚአብሔር በእሳት የሚቀርብ “ጣፋጭ መዐዛ” ነው (ከዘሌ 1፥9 *ጋር ያነጻ*)።

19-21 ሁለተኛውም አውራ በግ ለውክልና የሚሆን ነው፤ ነገር ግን አሮንንና ልጆቹን ለመቀደስ ይውላል። አውራውን በግ ከሠዉት በኋላ፣ “ከደሙ ወስደው” የእግዚአብሔርን ቃል የሚሰማውን የአካል ክፍላቸውን “የቀኝ ጆሮቻቸውን ጫፍ” ይቀባሉ። ቀጥሎም ደሙ ለሕዝቡ የመካከለኛነት (የአማላጅነት) ሥራ በሚሠሩት “የቀኝ እጆቻቸው አውራ ጣቶች” ላይ ይቀባል። ቀጥሎም አሮንና ልጆቹ ደሙን “በቀኝ እግራቸው አውራ ጣቶች” ላይ በመቀባት ካህናቱ በተቀደሰ አካሄዳቸው ለሕዝቡ ምሳሌ ይሆናሉ። በመጨረሻም በመሠዊያው ካለው ደም የተወሰነው ከመቅቢያ ዘይት *ጋር* ተቀይጦ በአሮን፣ በልጆቹና በልብሳቸው ላይ ይረጫል። ይህም የካህናቱን ሙሉ ለሙሉ መቀደስ ይወክላል።

22-26 ሁለተኛው አውራ በግ “የክህነት አውራ በግ” በመባል ይታወቃል፤ በቁመ. ሲተረጎም “የመሙላት አውራ በግ” ማለት ነው። የዚህ አውራ በግ የተመረጡ ብልቶች፣ ያለ እርሾ ከተጋገረው ቂጣ፣ ከዳቦ፣ ከዘይት ከተሠራ እንጎቻና ጎብስት *ጋር* የአሮንንና የልጆቹን እጆች በመሙላት “የመወዝወዝ *መሥዋዕት*” በመሆን ያገለግላሉ። “እጅን መሙላት” የሚለው ዘይቤ መነሻ ምንጭ አይታወቅም፤ ይሁን እንጂ “መሙላት” የሚለው ሐሳብ በሂደት ለአገልግሎት መለየት (መመደብ) የሚል ትርጉም ያዘ። የሚወዘወዘው ከአንድ ጎን ወደ ሌላ ጎን ሳይሆን ወደ መሠዊያው አቅጣጫ እና ከዚያም የኋሊት ነበር፤ ይህም *መሥዋዕቱ* ለእግዚአብሔር እንደሚሰጥና ከዚያም ለራሱ አገልግሎት ዳግመኛ በካህኑ እንደሚወሰድ ያመለክታል (ከዘሌ 7፥30፤ 23፥20 *ጋር ያነጻ*)። “ከአውራ በጉ ፍርምባ” በስተቀር የተወዘወዙት ነገሮች በሙሉ በመሠዊያው ላይ ይቃጠላሉ።

27-28 የእንስሳቱ “የተወዘወዘ ፍርምባና የቀረበውን ወርች” እንደ ጎብረት *መሥዋዕት* ሆኖ ለካህናቱ ይሰጣሉ።

29-30 አሮንና ልጆቹ ለክህነት አገልግሎት የተለዩባቸው ልብሶች ለመጪው ትውልድ ይተላለፋሉ። አሮንን የሚተካው ሊቀ ካህናት እነዚህን ልብሶች ለሰባት ቀናት ይለብሳቸዋል፤ ምናልባትም በምልአት መቀደሱን ለማመልከት።

31-34 “የክህነት አውራ በግ” (ማለትም ፍርምባውና ወርቹ፣ ቍ. 27) “በተቀደሰ ቦታ” ማለትም በማደሪያው አደባባይ ይቀቀላል። ከዚያም አሮንና ልጆቹ ልዩ ልዩ ምግቦችን በጎብረት *መሥዋዕት* ዐይነት በአንድነት ይመገባሉ። ይሄ በጣም ውስጣዊ የሆነ ጎብረት ነው፤ በመሆኑም የተረፈው ምግብ በሙሉ መቃጠል አለበት እንጂ ለሌላ ሊተላለፍ አይገባም።

35-37 አሁንም መታዘዝ አጽንዖት ሲሰጠው ይታያል። መሠዊያው በምልአት ይቀደስ ዘንድ ለሰባቱም የበዓለ ሢመት ቀናት አንዳንድ ወይፈን ያለማቋረጥ ይታረዳል። ለሰባት ቀናት ከተቀደሰ በኋላ፣ መሠዊያው “እጅግ የተቀደሰ” ይሆናል፤ ማለትም መሠዊያውን የነካ ሁሉ ይቀደሳል (ከማቴ 23፥19 *ጋር ያነጻ*)።

38-41 በመቀጠልም ሙሴ የየዕለቱን *መሥዋዕቶች* ባሕርይ በሚመለከት *መመሪያዎችን* ይቀበላል። አንድ ዓመት የሞላቸው ሁለት የበግ ጠቦቶች በየቀኑ ይሠዋሉ፡- አንዱ በማለዳ ሌላው በምሽት (ከዘኍ 28፥3-8 *ጋር ያነጻ*፤ ደግሞም ከ2ነገ 16፥15፤ ከሕዝ 46፥13-15 *ጋር ያነጻ*)። ከማለዳውና ከምሽቱ *መሥዋዕቶች* *ጋር* ዐብረው የሚቀርቡት ከኢፍ

መሥፈሪያ አንድ ዐሥረኛ ዱቄት፣ ከሩብ ኢፍ ዘይት፣ ከሩብ ኢን ወይን የመጠጥ *መሥዋዕት* ጋር ነው። አንድ ጊዜ በድጋሚ እግዚአብሔር ሙሴን *መሥዋዕቱ* ለእግዚአብሔር በእሳት የሚቀርብ ጣፋጭ መዐዛ እንደ ሆነ ያስታውሰዋል።

42-43 እግዚአብሔር ለሙሴ የእስራኤልን መጪ ዘመን አስመልክቶ "በሚመጡት ትውልዶች" በሚለው ሐረግ ትንቢታዊ የጨረፍታ እይታ ይሰጠዋል፤ ከካህናቱና ከእስራኤል ጋር *መሥዋዕቱ* በሚቀርብበት ቍጥር መጠን እንደሚገናኝ ተስፋ ይሰጣል። "ቦታው ይቀደሳል" የሚለው በዕብራይስጥ በቁሙ " . . . ይቀደሳል" ማለት ነው፤ ምናልባት ትርጉሙ "እስራኤል" ይቀደሳል ማለት ነው፤ ምክንያቱም ጎብረቱ የተመሠረተው በስርየት ላይ በመሆኑ ነው።

44-46 እግዚአብሔር ካህናቱንና በርካታ ንዋያተ ቅድሳቱን ከቀደሰ በኋላ "በእስራኤላውያን መካከል (ይኖራል)፤ አምላካቸውም (ይሆናል)።" በርግጥም የእስራኤል ከግብፅ የመውጣታቸው *መለኮታዊ* ዐላማ እግዚአብሔር በሕዝቡ "መካከል ያድር ዘንድ ነው።" የማደሪያው ድንኳን ሥነ መለኮት ትክለኛ ፋይዳ በግልጽ እንደ ተቀመጠው እግዚአብሔር በሕዝቡ *መካከል* "ይደኩን" ወይም "ያድር" ዘንድ ነው፤ ሕዝቡ እግዚአብሔር በርግጥ አምላክ መሆኑን ያውቁ ዘንድ።

11. የዕጣን መሠዊያ (30፥1-10)

ሀ. የግንባታ መመሪያዎች

የዕጣን *መሠዊያውም* የሚገኘው በቅድስት ነው። ወደ አደባባዩ *መግቢያ* ደጅ በውስጥ በኩል የሚገኘው የነሐስ *መሠዊያ* በነሐስ የተለበጠና የማያቋርጥ የደም *መሥዋዕት* የሚቀርብበት ሲሆን፣ የዕጣን *መሠዊያው* ግን በወርቅ የተለበጠና ያለማቋረጥ ዕጣን የሚጨስበት ነው፤ ይህም ቅዱሳን ወደ እግዚአብሔር ያለማቋረጥ የሚያቀርቡትን ምልጃ *ያመለክታል*።

1-6 *መሠዊያው* "ከግራር ዕንጨት" ይሠራል። ይህ በአራቱም ማእዘናት ቀንድ መሰል ነገር ያለው አራት ማእዘን ቍስ ከነሐስ *መሠዊያው* በጣም ያንሳል (ከ27፥1 *ጋር ያነጻ*)። የነሐስ *መሠዊያው* በወርቅ ይለበጣል። *መሠዊያውን* ከቦታ ቦታ ለማንቀሳቀስ እንዲቻል እንደ ተለመደው መሎጊያዎች ይኖሩታል። *መሠዊያው* "የምስክሩን ታቦት ከእይታ" ከሚከልለው *መጋረጃ* ፊት ለፊት ነው የሚቀመጠው።

ለ. የአሠራር መመሪያዎች (30፥7-10)

7-10 በየማለዳውና በየምሽቱ የሚጨሰው ዕጣን የቅዱሳንን ጸሎትና ከእግዚአብሔር ጋር የሚያደርጉትን ጎብረት የሚያመለክት ነው (ከመዝ 141፥2፤ ከሉቃ 1፥10፤ ከራእ 5፥8፤ 8፥3-4 *ጋር ያነጻ*)። በዕጣን *መሠዊያው* ላይ መደረግ የሌለበት ነገር በግልጽ ተጠቀሟል (ቍ. 9)። ይህንን ትእዛዝ *መተላለፍ* *መሠዊያውን* ያረክሰዋል። እንዲሁም በዓመት አንድ ጊዜ *መሠዊያው* ከስርየት *መሥዋዕቱ* በተወሰደ ደም መንጻት ያስፈልገዋል።

12. የሕዝብ ቈጠራ ግብር (30፥11-16)

11-16 ቈጠራውን ማድረግ ያስፈለገበት ትክክለኛ ምክንያት አልተገለጸም። ምናልባት በእግዚአብሔር ቤት ለሚደረገው አገልግሎት ዜጎችን ለማኅበራዊ ኀላፊነት መዝግቦ ለመያዝ ሊሆን ይችላል። ቀደም ሲል በ13፥13 በኩር ወንድ ልጆች ለእግዚአብሔር ስለ ሆኑ በ*መሥዋዕት* ሊቤዠ እንደሚገባ ተገልጾአል። በመሆኑም ሁሉም በኩሮች የእግዚአብሔር ናቸው፤ እናም ለበኩሮች ሁሉ በምትክነት የሌዊን ነገድ ተቀበለ (4፥22፤ ዘኍ 3፥12)። ቍጥር 12 ይህን መርሕ ዘርዘር ያደርገዋል። "ወጀ" ወይም "ማስተስረይ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው "በምትክ ነጻ ማውጣትን ወይም መቤዠት"ን ነው። በዚህ ቦታ ምትኩ ቈጠራ በማካሄድ የሚገኝ ገንዘብ ነው። አብዛኛውን ጊዜ ቈጠራ የሚደረገው ጦር ሰራዊትን ለማጠናከር ነው፤ ለዚህም ነው ዳዊት ያደረገው ቈጠራ በጣም አስከፊ ውጤት ያስከተለው (2ሳሙ. 24)። ይሁን እንጂ በትክክለኛው አካሄድ የተቈጠሩ ሁሉ ከመለኮት ጥበቃ ሥር መሆናቸው ግልጽ ነው።

"ሰቅል" በ21፥32 ተጠቅሷል። ግማሽ ሰቅል ወደ ስድስት ግራም ያህል ይመዝናል። ይህ ግብር ዕድሜያቸው ለዘመቻ በደረሰ ሰዎች የሚከፈል ነው። ሀብታሞችም ከድኾች ጋር እኩል እንዲከፍሉ መደረጉ የሚያመለክተው የአንድን ሰው ነፍስ የሚቤዠው በኪሱ ያለው የገንዘብ መጠን አለመሆኑን ነው። ከዚህ የሕዝብ ቈጠራ ግብር የሚገኘው ገቢ ሌዋውያን እግዚአብሔርን በማደሪያው ድንኳን ሲያገለግሉ እንዲጠ ቀመበትና ለእስራኤላውያን በመታሰቢያነትም እንዲያገለግል ጭምር ነው (ቍ. 16)።

13. የመታጠቢያ ሰን (ሳሕን)፣ መቅቢያ ዘይት እና ዕጣን 30፥17-38

17-21 የመታጠቢያ ሳሕን የሚሠራው ሴቶች በመስታወትነት ከሚጠቀሙበት ነሐስ (38፥8) ሲሆን እንደ በጎ ፈቃድ *መሥዋዕት* የተሰጠ ነው። ትክክለኛ ቅርጹ በትክክል አይታወቅም፤ ነገር ግን ምናልባት "ማስቀመጫው" ለብቻው ያለ ሳይሆን አይቀርም፤ ምክንያቱም ሁል ጊዜ ለብቻ ነው የሚጠቀሰው (ከ31፥9፤ 35፥16 *ጋር ያነጻ*፤ እና ሌሎችም)። ካህናቱ ወደ "መገናኛው ድንኳን" በገቡ ቍጥር ለእግዚአብሔር በእሳት *መሥዋዕት* ለማቅረብ ወደ *መሠዊያው* በቀረቡ ጊዜ፣ እጆቻቸውንና እግሮቻቸውን *መታጠባቸው* በጣም አስፈላጊ ነበር። *መንፈሳዊ* ንጽሕና በሌለበት ሁኔታ እግዚአብሔርን ለማገልገል መነሣት የሞትን አደጋ ያስከትላል (ከዘሌ 10፥1-2 *ጋር ያነጻ*)።

22-38 ቅመሞችንና *መቅቢያ* ዘይትን በሚመለከት በ25፥6 የተሰጠውን ማብራሪያ ይመለከታል። የተለያዩ ቍሳ ቍሶችንና ዕቃዎችን የመቅባቱ ፋይዳ ለእግዚአብሔር አገልግሎት እንዲቀደሱ ለማድረግ ነው። "የተቀደሰ፣ *መቅቢያ* ዘይት" አሠራሩም አጠቃቀሙም ለየት ያለ ነው። ለንግድ ሥራ ማዋል ወይም ይህን የ*መሥራት* ሥልጣን ሳያገኙ አስመስሎ *መሥራት* ከሕዝብ ተለይቶ *መጥፋትን* ያስከትላል። በተመሳሳይ ሁኔታ ዕጣኑም ልዩና እጅግ የተቀደሰ ተደርጎ ሊታይ ይገባል። ለዕጣኑም ተገቢው ጥንቃቄና አጠቃቀም ካልተደረገ እንደ ተቀደሰው ዘይት ሁሉ ከሕዝብ ተለይቶ *መጥፋትን* ያስከትላል።

14. ባለሞያዎችን መሾም (31፥1-11)

1-11 ባስልኤል ማለት "በእግዚአብሔር (የጥበቃ) ጥላ ውስጥ" ማለት ነው። የካሌብ ልጅ ነው ባስልኤል (1ዜና 2፥19)። ኪነ ጥበባዊ *ሥራዎች* ላይ ለመሰማራት መቻሉና እንደ አንድ ባለሞያ ጥበበኛ መሆኑ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ናቸው። የባስልኤል ረዳት የሆነው ኤልያብ ከዳን ነገድ ነው። የስሙ ትርጉም "የአባት ድንኳን" ወይም (መለኮታዊ) አባት ድንኳኔ ነው ማለት ነው። እነዚህ ሁለት ጥበበኛ ባለሞያዎች የማደሪያውን ድንኳንና በዚያ የሚከናወነውን አገልግሎት አስመልክቶ ያለው ኀላፊነት ሁሉ ይመለከታቸዋል፤ ምንም እንኳ እነርሱ በቀጥታ ግንባታው ላይ ሳይሆን የ*ሥራው* ተቈጣጣሪዎች ቢሆኑም።

15 የሰንበት ዕረፍት (31፥12-17)

12-17 ምንም እንኳ የማደሪያው ድንኳንና የንዋያተ ቅድሳቱ ግንባታ የተቀደሰ *ሥራ* ቢሆንም፣ *ሠራተኞቹ* በእግዚአብሔር የተደነገገውን ሰንበትን ለማክበር መጠንቀቅ ነበረባቸው። "ሰንበቴን ማክበር አለባችሁ" ኀይለ ቃል ነው። ሰንበትን አለማክበር፣ በማደሪያው ድንኳን ውስጥ ለመ*ሥራት* እንኳ ቢሆን የሞትን ቅጣት ያስከትላል። "(ሰንበትን) የሚያረክስ"

የሚለው ቃል “የምቀድሳችሁ” ከሚለው ጋር ሲነጻጸር ተቃርኖው በጉልሕ ይታያል። እንደ እግዚአብሔር የቃል ኪዳን ሕዝቦች እስራኤላውያን የዚያን ቃል ኪዳን ምልክት በጥንቃቄ ሊጠብቁ ይገባል። ሰንበት “የዘላቂ ቃል ኪዳን” (በቁሙ “የማያቋርጥ ቃል ኪዳን”) ምልክት ነው፤ ልክ ቀስተ ደመና (ዘፍ 9፥16)፣ ግዘረት (ዘፍ 17፥7፡ 13፡19)፣ የገጽ ኅብስት (ዘሌ 24፥8) እንደ ሆኑት ሁሉ። በመሆኑም ሰንበት የእስራኤልን ልዩ ሕዝብነት የሚያመለክት ስጦታ ነው።

16. የትእዛዞቹ ማጠቃለያ (31፥18)

18 ይህ ጥቅስ ወደ ወርቁ ጥጃ መሸጋገሪያ ነው። አርባው ቀን (ይመ 24፥18) አሁን ተጠናቅቋል። “ሁለቱ የምስክር ጽላቶች” ዐሠርቱን ትእዛዛት ይዘዋል (ከ32፥15-16፤ 34፥28፤ ከዘዳ 4፥13፤5፥22፤ 10፥4 ጋር ያነጻ)። “የእግዚአብሔር ጣት” ለሚለው የ8፥19ን ማብራሪያ ይመለከቷል።

ለ. የወርቅ ጥጃ የስሕተት አምልኮ (32፥1-34፥35)

1. የወርቅ ጥጃ (32፥1-29)

ከ32 እስከ 34 ያሉት ምዕራፎች 24፥18 ላይ የተቋረጠውን ትረካ ቢቀጥሉም፣ በዚህ ቦታ መጀመራቸው ግን ሆነ ብለው በማደሪያው ድንኳን ትእዛዞች ላይ የተሰጡትን የእውነተኛ አምልኮተ እግዚአብሔር መመሪያዎች ሰው ሰራሽ ከሆነው የወርቅ ጥጃ አምልኮት ጋር በተቃርኖ እንዲነጻጸሩ ይመስላል። አንድ ሰው ስለነዚህ ሁለት ተቃራኒ ነገሮች በትክክል ማሰብ መቻሉ እጅግ አስቸጋሪ ነው። ሌላም ተቃርኖ አለ፡- በተራራው ላይ እየሆነ ባለውና በምድረ በዳው ሜዳ ላይ፡- ተቃርኖውም በእግዚአብሔር ሀልዎትና አሳሳች በሆነው የጎጢአት ጎይል መካከል ነው (ከዘዳ 9፥8-21፤ ከነህ 9፥18፤ ከመዝ 106፥19-23 ጋር ያነጻ)። ስለዚህም ከምዕራፍ 32 እስከ 34 ያለው ትረካ የእስራኤልን አምልኮ በሚመለከት በተሰጡት ትእዛዞችና አተገባበራቸው መሃል የገባውን አስደንጋጭና አሳፋሪ ክፍተት የሚመለከት ነው።

1 ትክክለኛ የሆነ የተገለጠ አመራር ከሌለ፣ ሕዝቦች ይስታሉ። አንዳንድ ጊዜ የላቀ ቅድስና ያላቸው እንደ ሙሴ ዐይነት ሰዎች እንኳ ከሕይወት ምስክርነታቸው ጋር የማይጣጣም ድርጊት እንዲፈጽሙ ሊደለሉ ይችላሉ። “ና፤ ከፊታችን የሚሄዱ አማልክትን ሥራልን!” የሚለው የሕዝቡ ጩኸት እግዚአብሔርን በመጠበቅ ወቅት ያላቸው እምነት አነስተኛ መሆኑን ያጋለጠ ነው። “ያ ከግብፅ ያወጣን ሙሴ” የሚለው ሐረግ ሆነ ተብሎ የእግዚአብሔርን ሥራ ለሚች ሥጋ ለባሽ አሳልፈው የሰጡትን የሕዝቡን አስተሳሰብ ይፋ አውጥቶታል።

2-4 አሮን ሕዝቡን “የጆሮ ወርቃችሁን አውልቁ” (በቁሙ “ቅደዱ”) ብሎ አዘዛቸው። ይሄ ጌጣጌጥ ከግብፅ ሲወጡ የበዘበዙት እንደ ሆነ አያጠራጥርም (3፥21-22፤ 11፥2-3፤ 12፥35-36 ይመ) ። ከዚያም አሮን “በጥጃ መልክ ቀርጾ አወጣው፣” ምናልባት የወርቅ ቅጠል በዕንጨት ላይ በመቅረጽ ሠርተው ይሆናል፤ ኋላ ሊቃጠል የቻለውም ስለዚህ ነው (ከ32፥20 ጋር ያነጻ)። ወይም ደግሞ በግርድፉ ጠጣር ወርቅ አድርጎ ቀርጾት ከዚያ በእጁ ወደሚፈለገው ቅርጽ ለውጦት ይሆናል። ጣዖቱ ጥጃ ነው፤ ይህም ትንሽ ወይፈን ሲሆን የወንዳ ወንድነት ጉልበት ምልክት ነው። ሥራውን ካጠናቀቀ በኋላ አሮን እና ምናልባትም ልጆቹም ጭምር ለእስራኤል የሚከተለውን ለማወጅ ደፈሩ፡- “. . . እነዚህ አማልክትህ ናቸው”፤ ይህም በቅርቡ የተሰጣቸውን ሁለተኛውን ትእዛዝ ፊት ለፊት መጣስ ነው (ከ1ነገ 12፥28 ጋር ያነጻ)።

5-6 በግልጽ አሮን መሠዊያውን (ካልተጠረበ ድንጋይና ከጭቃ በ20፥24 እንደ ተጠቀሰው) በጥጃው ፊት ለፊት መሥራቱና “የእግዚአብሔር በዓል” ብሎ ማወጁ የኅሊናውን ክስ ለማምለጥ ያደረገው ሙከራ ነው። በስጦታዎቻቸው እግዚአብሔርን ለማክበር ሙከራ ካደረጉ በኋላ ሕዝቡ የራሳቸውን ፍላጎት ፈጸሙ፤ “ሊዘፍኑም ተነሡ” ማለትም ሊሰክሩ፣ ሊዳሩና ሊያመነዝሩ ጀመሩ ማለት ነው (ከዘፍ 26፥8፤ 39፥14፡17 ጋር ያነጻ)።

7-10 ለእስራኤል ምግባረ ብልሹነት እግዚአብሔር ሙሴን ተጠያቂ አደረገው፤ “ከግብፅ ያወጣሃቸው ሕዝብህ ስተዋልና. . . ” እግዚአብሔር ሆነ ብሎ ባለቤት አመልካቹን ተውላጠ ስም ይቀይረዋል፤ በዚህም እስራኤል ከእንግዲህ የእኔ አይደለችም ብሎ እንደ ተዋት ይጠቁማል (“ሕዝቤ” በ3፥10 እና በሌሎችም ካራት ጋር ያነጻ)። “ረከሱ” በዘፍ 6፥12 የሚገኘውን፣ በኖኅ ዘመን የሆነውን ክሕደት ወይም ርኵሰት ለመግለጽ የዋለውን ግስ ነው የሚጠቀመው። ትርጉሙ “ማፈራረስ ወይም ማጥፋት” የሚል ነው (ከዘዳ 9፥6፤ 10፥16፤ ከመዝ 75፥5፤ ከኤር 17፥23፤ ከሐሥ 7፥51 ጋር ያነጻ)። “ፈቀቅ ለማለት ፈጣኖች” መሆናቸው የሚያመለክተው እስራኤል በቃል ከሰሙትና በዐይናቸው በድርጊት ከተገለጸው እውነት ወደ ኋላ ማለታቸውን ነው። “ዐንገተ ደንዳናዎች” ሕዝቦች ለእግዚአብሔር ሥልጣን ለመስገድ አይፈቅዱም (ኤር 27፥11-12) ምንም እንኳ ለጥጃው “ወድቀው ቢሰግዱለትም።”

እግዚአብሔር በሕዝቡ በጣም ተቈጥቶ ነበር። ጌታ በዚህ ቦታ ምሕረት የለሽ ይመስላል፤ ይሁን እንጂ ይኸው አምላክ ነው በምሕረቱ ሙሴን ለእንዲህ ዐይነቱ ጊዜ ያስነሣው። እናም እግዚአብሔር፤ ሙሴን በመፈተን ዐይነት “እንዳጠፋቸው ተወኝ” አለው። ነገር ግን እግዚአብሔር የተዘጋጀውን ሥራ በእግዚአብሔር መንገድ ለመሥራት በተዘጋጁ ሰዎች ራሱን ሊወስን ይፈቅዳል።

11-14 በመለኮት በሕዝቡና በእግዚአብሔር መካከል እንዲቆም (መካከለኛ እንዲሆን) በተሰጠው ድርሻ መሠረት ሙሴ ለእግዚአብሔር ይግባኝ አለ። በመጀመሪያ እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር የገባውን ልዩ ቃል ኪዳን፤ በዘፀአት የተገለጠውን፣ አስታወሰው። ቀጥሎም እግዚአብሔር ቅዱስና ታማኝ የተባለውን የስሙን ክብር እንዲጠብቅ አቤቱታውን አሰማ። በመጨረሻም ለአስራኤል አባቶች የገባቸውን ታላላቅ የተስፋ ቃሎች ጠቀሰለት። ሙሴ ለእግዚአብሔር ሐሳብ መፈጸም ሲጋደል “እግዚአብሔር ተጸጸተ።” የእግዚአብሔር “መጸጸት” የሚያመለክተን እግዚአብሔር ይህን እንዲያደርግ የሚያስችለው በቂ ነገር ከተሰጠው፣ በሰዎች ላይ ያሰበውን ድርጊትና የቀጣ ስሜቱን እንደሚቀይር ነው፤ እናም በመሠረታዊው ታማኝነቱና በባሕርዩ አይቀየርም (ከመዝ 99፥6፤ 106፥45፤ ከኤር 18፥8፤ ከአሞጽ 7፥3፡6፤ ከዮና 3፥10፤ ከያዕ 5፥16 ጋር ያነጻ)። በቃለ እግዚአብሔር፣ እግዚአብሔር “ይፀፀት” ዘንድ የሚያደርጉ ሦስት ነገሮች ተሰጥተዋል፡- ምልጃ (ከአሞጽ 7፥1-6 ጋር ያነጻ)፤ የሕዝቡ በንስሓ መመለስ (ኤር 18፥3-11፤ ዮና 3፥9-10)፤ እና ርኅራኄ (ዘዳ 32፥36፤ መሳ 2፥18)።

15-16 በዚህ ቦታ ብቻ ነው “ሁለቱ የምስክር ጽላቶች” በሁለቱም ጎኖች እንደ ተጻፈባቸው የተገለጸው። “ጽላቶቹ የእግዚአብሔር ሥራ” መሆናቸው ምንጫቸው መለኮታዊ ለመሆኑ አጽንዖት ይሰጠዋል። በ31፥18 “በእግዚአብሔር ጣት እንደ ተጻፉ” ተገልጾአል፤ ምንም እንኳ 34፥28 “ሙሴ . . . በጽላቶቹ ላይ የቃል ኪዳኑን ቃሎች፣ ዐሠርቱን ትእዛዝት ጻፈ” ቢልም (በ34፥1-3 ላይ የተሰጠውን ማብራሪያ ይመለከቷል)።


17-18 በ24፥13 መሠረት ኢያሱ ከሙሴ ጋር ተራራውን ወጥቷል፣ ምናልባት እስከ ተራራው አጋማሽ ድረስ። ኢያሱ “የሕዝቡ የጩኸት ድምፅ” የጦርነት ቀረርቶ (ሽለላ) መስሎው። ሙሴ ግን ነገሩ ሌላ እንደ ሆነ ተረድቷል። “የ . . . ድምፅ” በቁሙ “የመልስ ድምፅ” ማለት ነው። በዚህ ቦታ “መልስ” የሚለው ቃል በሁለት መንገድ የቃላት ጨዋታ ነው፡- የድል አድራጊው “ቀረርቶ” እና የተሸናፊዎቹ የሽንፈት ጩኸት

አይደለም፤ ነገር ግን ዘፋኞች በቅብብሎሽ (መልስ በመሰጣጣት) የሚዘፍኑት የዘፈን ድምፅ ነው።

19-20 ሙሴ "የሠሩትን ጥጃና ጭፈራቸውን" ባየ ጊዜ እግዚአብሔር ምሕረት እንዲያደርግላቸው በተማጸነላቸው ሕዝቦች ላይ ቍጣው ነደደ። የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን በሕዝቡ መሰበሩን ለማመልከት የተሰባበሩት የድንጋይ ጽላቶች ብቻ አልነበሩም፤ ነገር ግን ሕዝቡ ከሥጋዊነት ጋር የገቡትን ቃል ኪዳን ለመስበርና ለማቆም ሙሴ ጥጃውንና ፌሽታውንም ጭምር በፍጥነት "ሰበረው" ። ሙሴ ጥጃውን ወስዶ "አቃጠለው" "ዱቄት እስኪሆን ፈጨው፣" ከዚያም "በውሃ ላይ በተነው፤ እስራኤላውያንም እንዲጠጡት አደረገ፣" ለአሳፋሪ ድርጊት ተገቢ የሆነ ማሳረጊያ ነው (ከ2ነገ 23፥5 ጋር ያነጻ)።

22-24 አሮን በሕዝቡ ርኩስ ተግባር እንዳልተባበረ አድርጎ ራሱን ነጻ ለማውጣት ፈጣን የፈጠራ ሰበቦች ማዘጋጀት ነበረበት። አራት ሰበቦችን ለማቅረብ ሞከረ፦ (1) ይህ ሕዝብ ሁልጊዜ ለክፋት ያዘነበለ መሆኑን አንተ ታውቃለህ፤ (2) "እነርሱም . . . አሉኝ"፤ እና (3) "ሙሴ ምን እንዳገኘው አናውቅም።" በመጨረሻም ከሁሉ የከፋ "ቀሽም" ምክንያት ያቀርባል፦ "ይህም ጥጃ ወጣ!" አሮን ታምራት ተፈጸመ ለማለት እየሞከረ ይሆን?

25-26 ሕዝቡ ሙሉ ለሙሉ ስድ (መረን) ተለቅቆ (ወጥቶ) ነበር (ከምሳ 29፥18 ጋር ያነጻ)። "ሙሉ ለሙሉ መረን መውጣት" ማለት መላላት ወይም መግለጥ የሚል ስሜት አለው። በቀላሉ ለመረዳት እንደሚቻለው የሕዝቡ የወርቅ ጥጃ አምልኮ ከሃይማኖታዊ ዘማዊነት ጋር የተያያዘ ነበር። ሙሴ በአፋጣኝ ወሳኝ ርምጃ መውሰድ እንሚያስፈልግ ተረዳ። እናም ሕዝቡን አቋም እንዲወስዱ ግድ አላቸው (ከኢያሱ 24፥14-15፤



ይህ በመጀመሪያ በብር ተለብጦ የነበረ የነሐስ ጥጃ በእስቀሉና በሚገኘው የክነዓናውያን ቤተ መቅደስ በ1550 ዓቅክ የተገኘ ነው። እስራኤላውያን በዘፀአት 32 ላይ የጥጃን አምልኮ እንደ ተለማመዱ እንመለከታለን።

ከ1ነገ 18፥21፤ ከማቴ 6፥24 ጋር ያነጻ)። ሌዋውያኑም "ሁሉ" የሚለው ቃል የማጠቃለያ አገላለጽ ነው፤ ምክንያቱም በዘዳ 33፥9 ላይ አንዳንድ ሌዋውያን በተወሰደው ርምጃ እንደ ተገደሉ ይናገራልና (ቍ. 28)።

27-29 እግዚአብሔርን ለመታዘዝ የወሰኑ ሌዋውያን ትጥቃቸውን አሳምረው "ወደ ኋላና ወደ ፊት እየሄዱ እንዲገድሉ" ታዘዙ። ይሄ የነቢይ ትእዛዝ አልነበረም ነገር ግን የቅዱስ አምላክ ነው። ዐንገተ ደንዳናነታቸው ያስከተለውን ፍርድ የተቀበሉት ሰዎች ቍጥር ትንሽ አልነበረም (ከሐዋ 2፥41 ጋር ያነጻ)። እግዚአብሔርን መከተል ማለት እንግዲህ አንዳንዴ የራስን ቤተ ሰብ መካድን ይጠይቃል (ከሉቃ 12፥51-53፤ 14፥26 ጋር ያነጻ)።

የመቀደስ አንዱ አስፈላጊ ጎን ለእግዚአብሔር ትእዛዝ እሺ ማለት ነው፤ ይህም ሁል ጊዜ ከእግዚአብሔር በሆነ በረከት ነው የሚደመደመው። ሌዋውያን እግዚአብሔርን በሙሉ ልባቸው ተከተሉት (ኢያሱ 4፥8) እናም ሌላውን ዝምድናና የዘር ሐረግ በንጽጽር እንደ ምናምን ቈጠሩ (ዘዳ 33፥9)።

2. የሙሴ መካከለኛነት (አማላጅነት) (32፥30-35)

30 ምንም እንኳ ሰዎቹ ክፉ ሥራቸው የተጸጸቱ ቢሆንም፣ የኀጢአት ስርየት ማቅረብ እጅግ አስፈልጎ ነበር። ሙሴም በኀጢአታቸው ምክንያት በእግዚአብሔር ከተወሰነው ፍርድ ሕዝቡን ለመዋጀት ወይም ለመታደግ ምትክ ለማቅረብ ይሞክራል፦ ራሱን።

31-32 ሙሴ እንደ ገና ወደ ተራራው ወጣና ለሁለተኛ ጊዜ ስለ እስራኤል መማለድ ያዘ። ሙሴ ለሕዝቡ ያለው ፍቅር እውነተኛነት በልመናው ላይ በግልጽ ይታያል፦ "እኔን ደምስሰኝ።" (ከሮሜ 9፥1-3 ጋር ያነጻ)። "መጽሐፍ" ወይም "የብራና ጥቅልል" በመዝ 69፥28 "የሕያዋን መጽሐፍ" ተብሎ ተጠርቷል፤ በኢሳ 4፥3 ደግሞ "በሕይወት ከተመዘገቡት ሁሉ ጋር" በሚል ተጠቅሷል (ሕዝ 13፥9፤ ዳን 12፥1፤ ሚል 3፥16፤ ከፊልጵ 4፥3፤ ከራእ 3፥5፤ 20፥12፡15፤ 21፥27 ጋር ያነጻ)።

33-34 ሙሴ ለእስራኤል በደል ራሱን ሊሰጥ ቢጠይቅም እግዚአብሔር ግን እሺ አላለውም። ይልቁን "የበደለኝን ሁሉ ከመጽሐፌ እደመስሰዋለሁ" ብሎ መለሰለት (ከመዝ 9፥5፤ 51፥1 ጋር ያነጻ)። በዚህ ዐይነት የብሉይ ኪዳን መርሕ ዳግመኛ ተረጋግጧል፦ ኀጢአትን የሠራው ሰው ለራሱ ኀጢአት ኀላፊነትን ይወስዳል (ከዘዳ 24፥16፤ ከሕዝ 18፥4፡13፡17 ጋር ያነጻ)። ከዚህ ቀደም መሪው እግዚአብሔር (12፥42፡51፤ 13፥17፤ 15፥13፤ 20፥2)፣ ሙሴ ግን የእግዚአብሔር ባሪያ ብቻ ነበር፤ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ግን ሙሴና መልአክ መሪ ይሆናሉ። "የምቀጣበት ጊዜ ሲደርስ" በቁሙ "በምጐበኝበት ቀን" ማለት ነው። ምናልባት ይሄ አባባል "የእግዚአብሔር ቀን" የሚሉ ማስጠንቀቂያዎች ጅማሬ ሳይሆን አይቀርም።

35 የድርጊቶቹ አፈጻጸም ምናልባት ቅደም ተከተሉን በጥብቅ የጠበቀ አይደለም። እናም መቅሠፍቱ ምናልባት በቍ. 28 የተጠቀሰው ሦስት ሺህ ሰዎች የተገደሉበት ሊሆን ይችላል። መቅሠፍቱ በሕዝቡ ላይ የመጣው ጥጃው እንዲሠራ ስላደረጉ ወይም ጥጃ እንፈልጋለን በማለታቸው ነው። ብዙ ጊዜ በቃለ እግዚአብሔር ውስጥ ድርጊቶች በቀጥታ ከሕዝብ ጋር ይገናኛሉ፤ ምንም እንኳ ሕዝቡ ቀጥተኛ ተሳትፎ ባይኖረውም፣ የአንዱ ወይም የጥቂቶች ድርጊት እንደ ማኅበረ ሰብ አካልነታቸው ብዙዎችን ይነካካልና፤ ልክ አሁንም የአንድ ከሓዲ ወንጀለኛ ድርጊት አንድን ሰራዊት ወይም አገር በመላው ሊነካ እንደሚችል ማለት ነው።

3. የእግዚአብሔር ዐብሬያችሁ አልወጣም ማለትና የሙሴ ጸሎት (33፥1-23)

1-3 እግዚአብሔር ወደ ፊት ጕዟቸውን እንዲቀጥሉ አዘዘ፣ መልአክን በፊታቸው እንደሚልክ ቃል በመግባት (ከ23፥20፡23፤32፥34 ጋር ያነጻ)። በዚህ ቦታ ተስፋ የተገባላቸው መልአክ በኢሳ 63፥9 "የፊቱም መልአክ" ተብሎ ከተጠቀሰው ፈጽሞ የተለየ ነው፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር ይህኛውን መልአክ "ስሜ በእርሱ ላይ ነውና" (23፥21) ብሎ ስለ ተናገረ። መልአኩ አስተርእዮተ ክርስቶስ፤ ማለትም በብሉይ ኪዳን የክርስቶስ መልክ (አምሳያ) መታየት ነው። ምንም እንኳ እግዚአብሔር የራሱን ተወካይ እንደሚልክ ቃል ቢገባም፣ እርሱ

ራሱ ግን "ከእናንተ ጋር አልሄድም" ነው ያለው። ከ23፥20-23 የተገለጠው የመለኮት ዐብሮነት መለየት ምክንያቱ በሕዝቡ ኀጢአት መገኘቱ ነው።

4-6 ሕዝቡ የመለኮት ሀልዎት ከሚለያቸው ይልቅ የመለኮት ቅጣት ቢወርድባቸው ይመርጡ ነበር፤ እናም "ይተክዙ ጀመር" በጌጣጌጦቻቸውም ሊያጌጡ አልወደዱም። ዐንገተ ደንዳንነታቸው በድጋሚ ከተነገራቸው በኋላ "ጌጣጌጦቻችሁን አውልቁ" ተባሉ፤ ማለትም በወቅቱ ያጌጡባቸውን ጌጦች ሲሆን ይህም የንስሓቸውን እውነተኛነት ለመፈተሽ የተደረገ ነው። ማቅ ከመልበስና ዐመድ ከመነስነስ ጋር በሚመሳሰል መልኩ "ጌጦቻቸውን ከላያቸው አወለቁ" ለኀጢአታቸው ማልቀሳቸውን ለማመልከት (ከዘፍ 35፥4፤ ከሕዝ 26፥16 ጋር ያነጻ)።

7-11 "ከሰፈር ውጭ የተተከለው ድንኳን" ከማደሪያው ድንኳን ወይም "ከመገናኛው ድንኳን" የተለየ ነው፤ የመገናኛው ድንኳን ታቦቱንና ሌሎች ንዋያተ ቅድሳትን የያዘና እግዚአብሔርም በቋሚነት የሚያድርበት በመሆኑ። ይሄኛው "የመገናኛ ድንኳን" ከሰፈር ውጭ የሚገኝ ሲሆን ሌላ ቋሚ መጠለያ እስኪዘጋጅ የሚያገለግል ነው (ከ27፥21 እና ከሌሎችም ጋር ያነጻ)። በቍጥር 7 ላይ ያሉት ግሶች ሙሴ ድንኳኑን በየጊዜው ይተክል እንደነበር ያመለክታሉ። ሙሴ ከእግዚአብሔር ጋር መገናኘት በፈለገ ቍጥር የመገናኛውን ድንኳን ይጐበኝ ነበር። ሙሴ ወደ ድንኳኑ በገባ ቍጥር "የደመና ዐምድ ይወርዳል" ይህም እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር እየተነጋገረ መሆኑን አመልካች ነው፦ "ሰው ከባልንጀራው ጋር እንደሚነጋገር" (ከዘኍ 12፥8፤ ከዘዳ 34፥10 ጋር ያነጻ)። ተመሳሳይ የክብር መውረድ በኋላ የማደሪያውን ሥራ መጠናቀቅ አስመልክቶ ይወርዳል (40፥33-34፤ 13፥21 ይመ)። በማደሪያው ድንኳን መግቢያ ላይ የደመናው ዐምድ መታየት በሕዝቡ ዘንድ የአምልኮን መንፈስ ያነሣሣል።

12-14 እስራኤልን የመምራቱን ኀላፊነት መረከብ የነበረበት ቀን ሲቃረብ ሙሴ እግዚአብሔር ዐብሮት እንደሚሆን ቃል የገባለትን ማንነት ለማወቅ አጥብቆ ፈለገ (32፥34፤ 33፥2)። "ዝም ብሎ" መልአክ ብቻ የእግዚአብሔርን ዐብሮነት (ሀልዎት) ሊተካ እንደማይችል ገብቶታል። "በስምህ ስለማውቅህ" ማለት "ለይቼ መርጬሃለሁ" ማለት ነው። ሙሴ እግዚአብሔር ፍቅሩን በይፋ እንዲገልጥለት ጠየቀ፤ ይበልጥ ዐውቆት በተሻለ ሁኔታ ያገለግለው ዘንድ። እግዚአብሔር "ሀልዎቴ (በቁሙ 'ፊቴ'፤) ከአንተ ጋር ይሄዳል" አለው። በዚህ ዐዲስ ቃል እግዚአብሔር "ስሙን" በእርሱ ላይ ያደረገውን፣ የፊቱን መልአክ (23፥20-21) እስራኤልን ወደ ከነዓን እንዲመራ ዳግመኛ ሾመው።

15-18 ሙሴ እግዚአብሔርን የ"ሀልዎቱ" ምሪት ዐብሯቸው የማይሄድ ከሆነ ሕዝቡን እንዳያወጣቸው አጥብቆ ተማጸነው። እስራኤልን ከተቀረው ዓለም የሚለያት የእግዚአብሔር ሀልዎት እንደ ሆነ ሙሴ ያውቃል። እግዚአብሔር ይጠብቀው የነበረው ምላሽ ይህ ነበር፤ ሙሴ ግን አንድ ተጨማሪ ነገር ፈለገ፦ የእግዚአብሔርን "ክብር።"

19-20 "ክብርህን" አሳየኝ ለሚለው የሙሴ ጥያቄ የእግዚአብሔር መልስ "መልካምነቴን ሁሉ በፊትህ እንዲያልፍ አደርጋለሁ" የሚል ነው። "መልካምነቱ" መላውን ባሕርዩንና ማንነቱን ይወክላል። የእግዚአብሔር ባሕርይ ተጨማሪ መገለጫ ስሙን ማወጅ ነው። የእግዚአብሔር ስም ማንነቱን፣ ባሕርዩን፣ ሰብእናውን (መዝ 20፥1፤ ሉቃ 24፥47፤ ዮሐ 1፥12)፤ ሕጉን (doctrine) (መዝ 22፥22፤ ዮሐ 17፥6፡26)፣ እና የአኗኗር መርሖቹን (standards) (ሚክ 4፥5) ያጠቃልላል። በዚህ ቦታ ስሙ "ምሕረቱን" እና "ርኅራኄውን" ይጨምራል። የተከለከለው አንድ ነገር የሙሴ እግዚአብሔርን ማየት ነው። በርግጥ "ማንም እኔን አይቶ መኖር" አይችልም ነው ሙሴ የተባለው (ዮሐ1፥18፤ 6፥46፤ 1ጢሞ 1፥17፤ 1ዮሐ 4፥12 ይመ)።

21-23 የእግዚአብሔርን ክብር ለማየት ሙሴ "በዓለት" ላይ መቆም ነበረበት (ከማቴ 7፥24-27 ጋር ያነጻ)። ክብሩ በሚያልፍበት ጊዜ ሙሴ "በዓለቱ ስንጥቅ ውስጥ" ይሰወራል፤ በእግዚአብሔር እጅም ይጋረዳል። ከዚያም ሙሴ የእግዚአብሔርን ፊት ያይ ዘንድ እግዚአብሔር እጁን ያነሣል። ነገር ግን እግዚአብሔር መንፈስ ስለ ሆነና ቅርጽ አልባ በመሆኑ እንዲሁም ማንም አይቶት በሕይወት መኖር ስለማይችል (ቍ. 20)፤ "ጀርባ" ተብሎ የተተረጎመው ቃል ይበልጥ ትክክለኛ ትርጉም የሚኖረው ከእግዚአብሔር አንጸባራቂ ክብር ማለፍ በኋላ የሚቀረው ነገር ማለት ይሆናል።

4. የቃል ኪዳኑ መታደስ (34፥1-35)

1-3 ሙሴ "የእግዚአብሔር ሥራ" የነበሩትን (32፥16) የመጀመሪያዎቹን ጽላቶች ስለ ሰበራቸው (32፥19)፤ "እንደ መጀመሪያዎቹ ያሉ ሁለት የድንጋይ ጽላቶች መጥረብ" ነበረበት። "እኔም በመጀመሪያዎቹ ጽላቶቹ ላይ የነበሩትን ቃሎች እጽፍባቸዋለሁ" በሚለው በእግዚአብሔር ንግግርና ከቍ 27-28 በሚገኘው ሙሴ የጽሕፈቱን ሥራ እንደ ሠራ በሚናገረው ክፍል መካከል ተቃርኖ የለም። በግልጽ እነዚህ አንድን ነገር በተለያዩ መንገዶች መግለጽን የሚያሳዩ ናቸው። ሕጉ የእግዚአብሔር ሐሳብና ፈቃድ ቀጥተኛ መግለጫ ነው።

4-7 ሙሴ የእግዚአብሔርን ምሪት በመታዘዝ ሁለት የድንጋይ ጽላቶች አዘጋጀ። በነጋታው ማልዶ ወደ ሲና ተራራ አናት ወደ እግዚአብሔር ጽላቶቹን ይዞ ሄደ። እግዚአብሔር በድጋሚ ለሙሴ ተገለጦ ስሙን "እግዚአብሔር (ያህዌ)"ን ዐወጀ (33፥19 ይመ፤ ከ20፥2 ጋር ያነጻ)። ከዚያም እግዚአብሔር "በሙሴ ፊት ዐለፈ።" እግዚአብሔር ራሱን የገለጠበት መንገድ ስሙን ደግሞ በመጥራት ነው፤ ይህም አይለወጤነቱን በአጽንዖት ለመግለጥ ሊሆን ይችላል።

ከ6 እስከ 7 ያሉት ቍጥሮች ዋና ሐሳብ በዘኍ 14፥18፤ 2ዜና 30፥9፤ ነህ 9፥17፤ ዮናስ 4፥2 እና ሌሎችም ተደግሟል። "ርኅሩኅ"፣ ለሚለው በ33፥19 የተሰጠውን ማብራሪያ ይመለከታል። "ቸር አምላክ" የሆነው እርሱ ፈጽሞ ለማይገባቸው የጸጋውን ትሩፋት ያትረፈርፍላቸዋል። ቸርነቱ "ለቍጣ የዘገየ፣ ፍቅሩና ታማኝነቱ የበዛ፣ ፍቅርን ለሺዎች የሚጠብቅ፣ ክፋትን፣ ዐመፅንና ኀጢአትን ይቅር የሚል" በሚሉት ተገልጸአል። ነገር ግን ጸጋው ሚዛናዊ ነው፤ ምክንያቱም "በደለኛውን ግን ሳይቀጣ ዝም ብሎ አይተውም።" ቅጣቱ "እስከ ሦስትና አራት ትውልድ ድረስ" ተጽዕኖ ያመጣል። የተሟላው ሐሳብ (20፥5 ይመ) "ለሚጠሉኝ" የሚል ቅጽል ስም አለው።

8-9 የእግዚአብሔር የማንነቱና የባሕርዩ መገለጥ ሙሴን በትሕትና ሞላው። ይህም ምንም እንኳ ዐንገተ ደንዳናና ጠማማ ቢሆኑም እግዚአብሔር ለአንድ ተጨማሪ ጊዜ ለሕዝቡ ምሕረት እንዲያደርግ እንዲለምን አደረገው።

10-14 "ከአንተ ጋር ኪዳን እገባለሁ" የሚለው የእግዚአብሔር ንግግር እግዚአብሔር ከቍ 10-27 ሁለተኛ ኪዳን እየገባ ነው ማለት አይደለም፤ ይልቁን ከምዕራፍ 33 ክሥተት በኋላ እግዚአብሔር ያንኑ የቀደመውን ትእዛዝ እያደሰ መሆኑን ነው ይበልጥ የሚያመለክተው። "ድንቆች" የሚለው ቃል በግብፅ የተካኩትን መቅሠፍቶች አስመልክቶ በጥቅም ላይ ውሏል (3፥20)። እነዚህ ድንቆች እጅግ ታላላቅ ከመሆናቸው የተነሣ ሕዝቡ በከፍተኛ ሁኔታ ይደነቃሉ። ይሁን እንጂ እስራኤላውያን ከእግዚአብሔር ተኣምራዊ አደራረግ ተጠቃሚ ለመሆን ከፈለጉ ትእዛዙን መጠበቅ ይኖርባቸዋል።

እግዚአብሔር በተጨማሪ እስራኤላውያን ከአሕዛብ ጋር ያልተቀደሰ ጎብረት እንዳያደርጉ ያስጠነቅቃቸዋል (ከ2ቆሮ 6፥14 ጋር ያነጻ)። ከዚያም በላይ በራሳቸው ተነሣሽነት የአረማውያንን "መሠዊያዎች ሰባብሩ፤ የማምለኪያ ዐፀዶቻቸውን አድቅቁ፤ የኤሼራ ዐምዶቻቸውን ቍረጡ" ተብለው ታዘዋል። ኤሼሪም የሚባሉት ምናልባት ከበዓል መሠዊያ አጠገብ የሚተከሉ የአምልኮ ዛፎችና የዕንጨት ዐምዶች ናቸው (መሳ 6፥25፤ 1ነገ 15፥13፤ 2ነገ 21፥7)። የአረማውያን የማምለኪያ ቍሶች ከተወገዱ፣ "ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ" የሚለውን ትእዛዝ የመጣስ ፈተና ቀለል ያለ ይሆናል። በዚህ ቦታ "ቀናተኛ" የሚለው ቃል ለአጽንዖት ሁለት ጊዜ ተጠቅሷል (የ20፥5ን ማብራሪያ ይመ)። ይህ ለየት ያለ የዕብራይስጥ ቃል ለእግዚአብሔር ብቻ የሚነገር ሲሆን በአምልኮተ ጣዖትና በዝሙት መካከል ያለውን ጕድኝት በንጽጽር ያመለክታል (ከዘዳ 22፥22 ጋር ያነጻ)።

15-16 አሁንም በድጋሚ እስራኤል ያልተቀደሰ ጎብረት እንዳያደርጉ ማስጠንቀቂያ ይሰጣቸዋል። በዚህ ጊዜ "ወጥመዶቹ" (ከቍ 12 ጋር ያነጻ) ተገልጸዋል፦ (1) "ይጋብዙሃል፤ አንተም መሥዋዕታቸውን ትበላለህ" እና (2) "ለወንዶች ልጆችህ ሴቶች ልጆቻቸውን" ታጫለህ። ሁለቱም ድርጊቶች ወደ አምልኮተ ጣዖት ይመራሉ።

17 "ቀልጠው የሚሠሩ አማልክት" መከልከላቸው በጣም ተገቢ ነው (ከምዕ 32 ጋር ያነጻ፤ እንዲሁም 20፥4-6 ይመ)።

18-26 ለእነዚህ ጥቅሶች የ23፥14-19ን ማብራሪያ ይመለከታል። የመታዘዝ መንገድ እገዳዎች (ክልከላዎች) ከማስጠንቀቂያዎች ጋር በሚዛናዊነት የሚገኙበት ነው፦ "የቂጣን በዓል አክብር" (የ12፥14-20ን ማብራሪያ ይመለከታል)። "በኵር ሁሉ የእኔ" ስለ ሆነ (የ13፥11-16 ማብራሪያ ይመለከታል)። ስድስት ቀን ሠርቶ በሰባተኛው ስለ ማረፍ የ20፥8፣11ን ማብራሪያ ይመለከታል)። በ23፥16 "የሰባቱ ሱባዔ በዓል" "የመከር በዓል" ተብሎ ተጠርቷል።

እግዚአብሔር የመናኙን መገኘት በሚጠይቁት በሦስቱ ዓመታውያን በዓላት ላይ ልዩ የተስፋ ቃል አክሎባቸዋል። መናኙ በሌለበት ጊዜ አረማዊ ጎረቤቱ ድንበሩን በመግፋት መሬቱን እንዳይሰርቅበት እግዚአብሔር እንደሚጠብቅለት ቃል ገብቶለታል። "በዓመት ሦስት ጊዜ . . . ስትወጣ" የሚለው አረፍተ ነገር ወደ ፊት አሻግሮ በማየት ሕዝቡ ርስቱን ስለሚወርስበት ጊዜ የሚናገር ነው እንጂ ይኸ ጥቅስ ከድርጊቱ ፍጻሜ በኋላ የተጨመረ መሆኑን አያመላክትም (ከዘዳ 16፥16 ጋር ያነጻ)። ቍጥር 25ን በሚመለከት የ23፥18ን ማብራሪያ ይመለከታል። ስለ "በኵራት" የተሰጠውን ሕግና ነገረ መለኮት አስመልክቶ የ23፥19ን ማብራሪያ ይመለከታል (ከ4፥22፤ 11፥5፤ 12፥29 ጋር ያነጻ)።

27-28 እግዚአብሔር ሙሴን "እነዚህን ቃሎች ጻፋቸው" ብሎ ትእዛዝ ስለ መስጠቱ የቍ 1ን ማብራሪያ ይመለከታል። "አርባ ቀንና አርባ ሌሊት" ለሚለው የ24፥18ን ማብራሪያ ይመለከታል። ሙሴ ያለ ምግብና ውሃ ለዚህን ያህል ጊዜ መቈየቱ የእግዚአብሔርን ከተፈጥሮ ሕግ በላይ የሆነ ጥበቃና ጥንቃቄ የጠየቀ ተኣምር ነው (ከዘዳ 9፥9፡18፤ ከማቴ 4፥2 ጋር ያነጻ)።

29-32 ለረኾም ጊዜ በእግዚአብሔር ሀልዎት ውስጥ መቈየቱ በሙሴ ላይ ግልጽ የሆነ ለውጥ አምጥቷል። "ማንጸባረቅ" ወይም "ማብራት" የሚለው ግስ "መለከት" ከሚለው ስም ጋር የተያያዘ ነው። የ4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የላቲኑ ትርጉም እነዚህን ሁለቱን ፍቺዎች አሳክሯቸዋል። ከዚህም የተነሣ በመካከለኛው ዘመን በነበረው የሥዕል ጥበብ ሙሴ ሁለት መለከቶች ታጥቆ እንዲሣል አድርጓል! የሙሴ ፊት በእግዚአብሔር ክብር ተብለጭልጮ ሲያዩ እስራኤላውያን እጅግ ይፈሩ ነበር። ይሁን እንጂ የሙሴ ቃል አሮንን፣ የእስራኤልን አባቶች (መሪዎች) እና መላውን እስራኤልን ወደ እርሱ እንዲቀርቡ አበረታታቸው፤ ከዚያም እርሱ የእግዚአብሔርን ቃል ሰጣቸው።

33-35 የሙሴ ፊት ሲያበራ ለሕዝቡ የሚታየው ሙሴ የእግዚአብሔርን ቃል በእግዚአብሔር ስም ሲያስተላልፍ ብቻ ነው። በሌሎች ጊዜያት ሙሴ ፊቱን በመሸፈኛ ይሸፍን ነበር። ይህ ካህናት ፊታቸው ላይ የሚያጠልቁት "ጭምብል" አይደለም፤ ምክንያቱም ሙሴ እንደ እግዚአብሔር መልእክተኛ ለሕዝቡ ሲናገር ወይም ደግሞ ለብቻው በእግዚአብሔር ፊት ሲሆን መሸፈኛውን ያወልቀው ነበርና (ከ2ቆሮ 3፥7-18 ጋር ያነጻ)።

ሐ. የማደሪያውን ድንኳን መገንባት (35፥1-40፥38)

1. ሕዝቡን ለግንባታው መጥራት (35፥1-19)

1-3 እስራኤላውያንን በአንድነት ሰብስቢያቸው ስለ ነበር፣ ሙሴ የእግዚአብሔርን ትእዛዞች አስተላለፈላቸው። የኪዳኑ ምልክት የሆነው ሰንበት በቅድሚያ ተጠቅሷል፤ ይህም የአስፈላጊነቱ ምልክት ነው። "የሰንበት ዕረፍት ስለሚለው የ20፥8-11 እና የ31፥12-17ን ማብራሪያ ይመለከታል። ምንም እንኳ በሰንበት እሳት ማንደድ የሚከለከል ትእዛዝ በሌላ ቦታ ባይጠቀስም፣ በ16፥23 ላይ በከፊል ተጠቅሟል።

4 በ25፥1-30፥10 የተጠቀሰው እያንዳንዱ ነገር ማለት ይቻላል፤ ከ35፥4-40፥38 በአንድ ዐይነት ወይም በተመሳሳይ ቃላት ተደግሟል፤ በዚህ ቦታ ግሶቹ ባብዛኛው በጎላፊ ጊዜ ከመሆናቸው በቀር። በሩቅ ምሥራቅ ትእዛዛትን ቃል በቃል መድገም የተለመደ ነው፤ የግሶቹን ቅርጽ ከመቀየር በስተቀር።

"ይህ እግዚአብሔር ያዘዘው ነው" የሚለው በቍ 1 የተጠቀሰው ድጋሚ ሲሆን ሰንበትን ስለ ማክበር የመግቢያ ቃላትን ከሰጠ በኋላ ወደ ዋናው ጭብጥ መልሶ ይወስደናል (ከዘሌ 23፥2፡4 ጋር ያነጻ)።

5-9 የ25፥3-7ን ማብራሪያ ይመለከታል። በሁለቱ መካከል ያለው ልዩነት በ25፥3 ከሚገኘው መግቢያ በቀር እዚህ ግባ የሚባል አይደለም፤ ይህ ደግሞ በዚህ ቦታ የሚቀርብበት አንዳችም ምክንያት የለውም።

10-19 በ25፥1-28፥43፤ 30፥1-10፡17-38፤ የተሰጡትን ማብራሪያዎች ይመለከታል፤ እንዲሁም ከ31፥7-11 ጋር ያነጻ።

2. የበጎ ፈቃድ ስጦታዎች (35፥20-29)

20-29 ሙሴ ትእዛዙቱን ከሰጠ በኋላ ሕዝቡ ድርሻቸውን ሊወጡ ለሥራ ተነሣሡ። ልባቸው የተነሣሣ ሁሉ ለመገናኛው ደንኳንና ለአገልግሎቱ የሚሆን መባ (ስጦታ) አመጡ። የሕዝቡ ፈቃደኝነት በተደጋጋሚ ተገልጸአል፦ "ወንዶችም ሴቶችም" የሚለው በተለይ የተገለጸው "ልቡ ያነሣሣው ሁሉ" የሚለው ተባእታይ ጾታ በመሆኑ ሴቶችን አይመለከትም ከሚል የተሳሳተ ድምዳሜ እንዳይደርስ ነው፤ ምንም እንኳ ቍ 25-26 ሴቶችን በሌላ ተያያዥ ጕዳይ የሚያነሣቸው ቢሆንም። የሰዎቹን ልዩ ልዩ ስጦታዎች በሚመለከት የ25፥1-7 ማብራሪያ ይመለከታል።

3. ባስልኤልና የጥበብ ባለሞያዎቹ (35፥30-36፥7)

በእነዚህ ጥቅሶች ላይ ተጨማሪ ማብራሪያ ቢያስፈልግ የ31፥2-6ን ማብራሪያ ይመለከታል።

30-35 እግዚአብሔር ባስልኤልን የመረጠበትና ያስታጠቀበት ምክንያት “ማንኛውንም ዐይነት የጥበብ ሙያ እንዲያከናውን” (በቁሙ “በእያንዳንዱ የሐሳብ ተግባር እንዲሰማራ”) ነው። ይህም ቀደም ብሎ ስለ ሥራው የተሰጠውን ንድፍ ወይም ሐሳብ ያጠቃልላል (ከ31፥4-5 ጋር ያነጻ)። ቍጥር 34 ባስልኤልና ኤልያብ “ሌሎችን የማስተማር ችሎታ” እንደ ተሰጣቸው ጨምሮ ይናገራል፤ ይህም ከእነዚህ ሁለት የጥበብ ባለሞያዎች ጋር ዐብረው የሚሠሩትን ረዳቶች የማሠልጠንና የመምራት ችሎታ ነው። ቍጥር 35 ሙሉ ለሙሉ ማለት ይቻላል ዐዲስ ነው።

36፥1-7 በዚህ ቦታ ምዕራፉ መከፈሉ ተገቢ አልነበረም፤ ባለሞያዎቹ አሁን ወደ ትግበራ መግባታቸውን የሚያሳይ ምንም ዐይነት ዐዲስ ሐሳብ ግሱ አልሰጠንምና። ሕዝቡ ለመስጠት ያላቸው በጎ ፈቃድ ከባለሞያዎቹ ፍላጎት በለጠ፤ በመሆኑም ሕዝቡ ከእንግዲህ ለመቅደሱ ሥራ ምንም መባ እንዳያመጡ ትእዛዝ ተሰጠ። ይሄ ለእግዚአብሔር ቤት ሥራ ሊደረግ የሚገባው የልግስና ስጦታ ዐይነተኛ ማሳያ ነው።

4 የሥራው ሂደትና የሙሴ ባርኮት (36፥8-39፥43)

8-19 የማደሪያው ድንኳን ሥራ በትክክል የሚጀምረው በዚህ ቦታ ነው። የአሠራሩ ቅደም ተከተል ከትእዛዙ ቅደም ተከተል የተለየ ነው። የድንኳኖቹ ሥራ በ26፥1-13 ያለውን ይደግመዋል።

20-34 ወጋግራዎችንና አግዳሚዎችን በሚመለከት የ26፥15-30 ማብራሪያ ይመለከቷል።

35-38 ለውስጠኛ መጋረጃዎች የ26፥31-35 ማብራሪያ ይመለከቷል።

37፥1-9 ስለ ታቦቱ የ25፥10-22ን ማብራሪያ ይመለከቷል። በተለይ ባስልኤል ከሁሉ በልጠው የተቀደሱ የማደሪያውን ቍሶች እንደ ሠራ ተጠቅሷል።

10-16 የኅብስት ማስቀመጫ ጠረጴዛውን በሚመለከት የ25፥23-30ን ማብራሪያ ይመለከቷል።

17-24 መቅረዙን በሚመለከት የ25፥31-40ን ማብራሪያ ይመለከቷል።

25-29 የዕጣን መሠዊያውን በሚመለከት የ30፥1-6ን ማብራሪያ ይመለከቷል። “የተቀደሰውን መቅቢያ ዘይት” አስመልክቶ የ25፥6ን ማብራሪያ ይመለከቷል።

38፥1-7 የሚቃጠል መሥዋዕት መሠዊያን አስመልክቶ የ27፥1-8ን ማብራሪያ ይመለከቷል።

8 የናስ መታጠቢያ ሳሕኑን በሚመለከት የ30፥17-21ን ማብራሪያ ይመለከቷል።


9-20 የማደሪያውን አደባባይ አስመልክቶ የ27፥9-19ን ማብራሪያ ይመለከቷል።

21-39፥1 እነዚህ ጥቅሶች የማደሪያውን ቍሶች ቈጠራ የሚመለከቱ ናቸው። ከ25-26 ያሉት ቍጥሮች የወቅቱን የእስራኤልን የሕዝብ ቍጥር ፍንጭ ይሰጠናል። አንድ መክሊት 3,000 ሰቅል ነው፤ በመሆኑም 3,000 በ100 ሲባዛ 300,000 ሲደመር 1,775፣ 301,775 እያንዳንዱ ሰው (20 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆነው) ተመኑ ግማሽ ሰቅል በመሆኑ፣ ለውጊያ ብቁ የሆኑ ሰዎች ቍጥር ከ600,000 በላይ ነው (301,775 ሲባዛ 2 ውጤቱ 603,550)፤ ይሄ ቍጥር በኋላ ላይ በዘኍ 1፥46 (603,550 ወይም በዘኍ 26፥51 (601,730) ከተደረገው ቈጠራ ጋር በጣም ተመሳሳይ ነው። ይህ የሰራዊቱን ቍጥር የሚጠቅሰው ቍጥር አጠቃላይ የሕዝቡ ቍጥር 2 ሚሊዮን ነው የሚለውን ግምት ተቀባይነት ከፍ ያደርገዋል።

“እግዚአብሔር ሙሴን እንዳዘዘው” የሚለው ኀይለ ቃል ከ39-40 ያሉት ምዕራፎች ትኵረት ነው። ይህ ሐረግ በምዕራፍ 39 ዘጠኝ ጊዜ፣ በምዕራፍ 40 ሰባት ጊዜ ይገኛል።

2-31 የ28፥6-43ን ማብራሪያ ይመልከቱ። “የተቀደሰ አክሊል” እዚህ ቦታ የተጠቀሰ ዐዲስ ስያሜ ነው፤ በ28፥36-37 አይገኝም።

32-41 “በዚህ መሠረት . . . ሥራው በሙሉ ተጠናቀቀ” የሚለው ቃል ዘፍ 2፥1-2 የሚገኘውን፣ የዘፍጥረትን ትረካ ማጠቃለያ ያስታውሰናል። ይህ ክፍል እስራኤላውያን “ልክ እግዚአብሔር እንዳዘዘው” ሥራቸውን እንዳጠናቀቁ በአጽንዖት ይገልጻል። ሠራተኞቹ፣ በመላው የእስራኤል ሕዝብ ስም



ይህ በማደሪያው በውስጠኛው ክፍል የሚታየው ታቦት፣ መቅረዝ፣ የመታጠቢያ ሰን እና ገበታ ነው።

“የማደሪያውን ድንኳን ወደ ሙሴ አመጡት።” አሁንም የዕቃዎቹ ዝርዝር በድጋሚ ቀርቧል (ከ35፥11-19 ጋር ያነጻ፤ የዚህ ክፍል ትረካ ባጭሩ በ31፥7-11 ላይ ይገኛል)። “ከተደረደሩት መብራቶች . . . ጋር” የሚለው በመቅረዙ ላይ በሥርዐት ለተቀመጡት መብራቶች የተሰጠ ዐዲስ አገላለጽ ነው።

42-43 “ሙሴ . . . ልክ እግዚአብሔር እንዳዘዘው መሥራታቸውንም ተመለከተ” የሚለው አሁንም በዘፍ 1፥31 ከሚገኘው ጋር ይነጻጸራል። መደምደሚያው “ስለዚህም ባረካቸው” የሚል ነው (ከዘፍ 1፥22፡28፤ 2፥3 ጋር ያነጻ)።

5. የማደሪያው ድንኳን መተከል (40፥1-33)

1-5 የማደሪያው ድንኳን የተተከለው “በመጀመሪያው ወር በመጀመሪያው ቀን” ነው። ቍ 7 ከምድረ በዳው ጕዞ የ“ሁለተኛው ዓመት” መጀመሪያ ነው የሚል ተጨማሪ መረጃ ይሰጣል። የእስራኤል ሕዝብ ወደ ሲና በረሓ የደረሱት ከግብፅ በወጡ በሦስተኛው ወር በመሆኑ (19፥1) እንዲሁም ሙሴ

በሲና ተራራ ላይ ለአርባ ቀናት በመቈየቱ (24፥18፤ 34፥28) በእነዚህ ላይ ከ19፥1-24፥11 እና ከምዕ 32-33 ያሉት ክሥተቶች ሲደመሩበት የማደሪያውን ድንኳን የመገንባቱ ሥራ ከስድስት ወራት ያነሰ ጊዜ ወስዷል።

አሁንም በድጋሚ፣ ልክ በ25፥10-22 እንደ ሆነው፣ የቃል ኪዳኑ ታቦት፣ በማደሪያው ድንኳን ከሚገኙት ቀሶች ሁሉ በአስፈላጊነቱ የላቀው፣ በቅድሚያ ይጠቀሳል። ይህ በእስራኤል መካከል የሚገኝ የእግዚአብሔር ዙፋን ነበር። “መጋረጃው” እና ይኸው መጋረጃ እንዴት የቃል ኪዳኑን ታቦት እንደ ጋረደው በቁ. 21 በተጨማሪ ተብራርቷል (እንዲሁም ከ26፥31-35፤ 36፥35-38 *ጋር ያነጻ*)።

ስለ “ጠረጴዛው” የ25፥23-30፤ 37፥10-16፤ ስለ “መቅረዙ” የ25፥31-40፤ 37፥17-24፤ ስለ “ወርቁ የዕጣን መሠዊያ” የ30፥1-10፡ 34-38፤ 37፥25-29 *ማብራሪያ ይመለከቷል*።

6-8 ስለ “የሚቃጠል መሥዋዕት መሠዊያ”ው የ27፥1-8፤38፥1-7፤ “የመታጠቢያ ሳህን”ኑን በሚመለከት የ30፥17-21፤ የ38፥8ን *ማብራሪያ ይመለከቷል*። “አደባባዩን” በሚመለከት የ27፥9-19፤ 38፥9-20ን *ማብራሪያ ይመለከቷል*።

9-11 ስለ “መቅቢያ ዘይቱ” የ25፥6፤30፥22-23ን *ማብራሪያ ይመለከቷል*። እነዚህ ትእዛዛት የተተገበሩት በዘሌ 8፥10-12 ነው። “ቀድስ” ማለት በቁመ- “ለየው” ማለት ነው፤ ማለትም ለጌታ አገልግሎት መለየት ነው።

12-16 ካህናቱን የመቅባትና የመቀደስ ሥራ አሮንና ልጆቹንም ያጠቃልላል። የክህነቱ ሥርዐት የተቋቋመው “ለሚመጡት ትውልዶች ሁሉ” ነው (ከ12፥24፤27፥21 *ጋር ያነጻ*)። ምንም እንኳ በዘር የሚተላለፍ አሮናዊ የክህነት አገልግሎት ያበቃ ቢሆንም፣ ክርስቶስ የማያቋርጥ የክህነት አገልግሎቱን ይቀጥላል።

17-33 ቍጥር 17 ከቁ 2 *ጋር* በጣም ተመሳሳይ ነው። ከ18-33 ያሉት ቍጥሮች ሰባት ንኡሳን ክፍሎች አሏቸው፤ እያንዳንዳቸውም “እግዚአብሔር ሙሴን/እርሱን እንዳዘዘው” የሚል ቀመር (ፎርሙላ) አላቸው።

1. “ሙሴ የማደሪያውን ድንኳን ተከለ።”
2. “ምስክሩን ወስዶ በታቦቱ ውስጥ አኖረው” (25፥14፡16፡21 *ይመ*)።
3. “ሙሴ ጠረጴዛውን በቦታው አስቀመጠ” (26፥35፤ 40፥4)
4. “መቅረዙን በቦታው አስቀመጠ” (26፥35፤ 40፥4)
5. “ሙሴ የዕጣኑን የወርቅ መሠዊያ በቦታው አስቀመጠ” (30፥6፤ 40፥5)።
6. “*መጋረጃውን ዘረጋ*” ከዚያም “የነሐስ መሠዊያውን በቦታው አስቀመጠ”
7. “የመታጠቢያ ሰሐኑን በቦታው አስቀመጠ” (30፥18፤ 40፥7)

6. የማደሪያው ድንኳን ምርቃት (40፥34-38)

34-38 የማደሪያው ድንኳን እግዚአብሔር ሙሴን ባዘዘው መሠረት ተገንብቶ ቦታውን ይሟል፤ ይሁን እንጂ አንድ ነገር ጐድሏል። ቅርጽ ባዶ መሆን የለበትም፤ መለኮታዊ በሆነ ሕይወት ሊሞላ ይገባዋል፤ ስለዚህ “የእግዚአብሔር ክብር ማደሪያውን ሞላ።” የእግዚአብሔርን ክብር በሚመለከት የ16፥7፡ 10፤ 24፥16-17፤ 33፥18፡ 22ን *ማብራሪያ ይመለከቷል*። የእግዚአብሔር ክብር ከመምጣቱ የተነሣ፣ የእስራኤል ሕዝብ ጕዟቸውን ለመቀጠል ዝግጁ ነበሩ። ሕዝቡን ይመራ ዘንድ መለኮታዊ መልእክተኛ እንደሚሰጣቸው የተገባላቸው ተስፋ ፍጻሜ አገኘ (23፥20፡ 23፤ 32፥34፤ 33፥2)። አሁን እግዚአብሔር በሕዝቡ መካከል እንደ ንጉሥ ሆኖ ይኖራል፤ ለሚቀጥሉት አርባ ዓመታትም በምድረ በዳው እነርሱን መምራቱን ይቀጥላል። ጕዟቸውን እንዲቀጥሉ የተሰጣቸው ምልክት “ደመናው በተነሣ ጊዜ ሁሉ” ነው (ከ13፥21 *ጋር ያነጻ*፤ 17፥1፤ 25፥22 *ይመ*)።

ብሉይ ኪዳን በዐዲስ ውስጥ

የብሉይ ኪዳን ጥቅስ	የዐዲስ ኪዳን ጥቅስ	ርእሰ ጉዳይ
ዘፀ 1፥8	ሐሥ 7፥18	ዮሴፍን የማያውቅ ንጉሥ
ዘፀ 2፥14	ሐሥ 7፥27-28፣35	ሙሴ በግብጽ ውስጥ
ዘፀ 3፥5	ሐሥ 7፥33	ሙሴ በሚነድደው ቍጥቋጦ
ዘፀ 3፥6	ማቴ 22፥32፤ ማር 12፥26፤ ሉቃ 20፥37፤ ሐዋ 7፥32	ሕያው የሆነው አምላክ
ዘፀ 3፥7-8፡ 10	ሐሥ 7፥34	እግዚአብሔር እስራኤልን ነጻ እንደሚያወጣ ቃል መግባቱ
ዘፀ 9፥16	ሮሜ 9፥17	የሙሴ ዐላማ
ዘፀ 12፥46	ዮሐ 19፥36	ዐጥንት አይሰበርም
ዘፀ 13፥2፡ 12	ሉቃ 2፥23	በኩርን ለእግዚአብሔር መለየት
ዘፀ 16፥4	ዮሐ 6፥31	ከሰማይ የወረደ እንጀራ
ዘፀ 16፥18	2ቆሮ 8፥15	እግዚአብሔር በቂ መግቦት አለው
ዘፀ 19፥12-13	ዕብ 12፥20	ተራራው መነካት የለበትም
ዘፀ 20፥11	ሐዋ 4፥24፤ 14፥15	ጀማሪው እግዚአብሔር
ዘፀ 20፥12	ማቴ 15፥4፤ ማር 7፥10፤ ኤፌ 6፥2-3	ዐምስተኛው ትእዛዝ
ዘፀ 20፥13	ማቴ 5፥21፤ ሮሜ 13፥9፤ ያዕቆብ 2፥11	ስድስተኛው ትእዛዝ
ዘፀ 20፥14	ማቴ 5፥27፤ ሮሜ 13፥9፤ ያዕቆብ 2፥11	ሰባተኛው ትእዛዝ
ዘፀ 20፥15	ሮሜ 13፥9	ስምንተኛው ትእዛዝ
ዘፀ 21፥17	ሮሜ 7፥7፤ 13፥9	ዐሥረኛው ትእዛዝ
ዘፀ 21፥17	ማቴ 15፥4፤ ማር 7፥10	ወላጆችን መስደብ
ዘፀ 22፥28	ሐሥ 23፥5	መሪዎችን መስደብ
ዘፀ 24፥8	ዕብ 9፥20	የኪዳኑ ደም
ዘፀ 20፥24	ማቴ 5፥38	ዐይን ስለ ዐይን
ዘፀ 25፥40	ዕብ 8፥5	የማደሪያው ድንኳን ንድፍ
ዘፀ 32፥1፡ 23	ሐሥ 7፥40	የጣዖት ይሠራልን ጥያቄ
ዘፀ 32፥6	1ቆሮ 10፥7	የአምልኮተ ጣዖት ኀጢአት
ዘፀ 33፥19	ሮሜ 9፥15	የእግዚአብሔር ምሕረት
ዘፀ 34፥33፡ 35	2ቆሮ 3፥13	የሙሴ መሸፈኛ